# መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ።

## በግእዝና ፡ በአማርኛ ።

አ.አ. ፲፱፻፺፮ ዓ.ም.

Scanned by CamScanner

በ፫፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ቀኖና፡ፍጥረት።
መለኮት ፡ ልዑል ፡ አሐደ ፡ ኮነ ፡ ምስለ ፡
፱ ትስብእት ፡ ወኢተወለጠ ፡ ዘኢይትረከብ ፡
ወኢይትዌለጥ፡ይእቲ፡እንተ፡ኮነት፡አሐደ፡
ምስለ፡አምላክ።
፲ ሦጠ፡መዐቶ፡ላእለ፡ዕብራውያን፡ወኬዶሙ፡
በጸዕር፡ወበመዐት።
ምሕረቶ፡ወጽድቆ፡ረሰየ፡ሎሙ፡ለአሕዛብ፡
፲፩ እልክቱ ፡ እለ ፡ ገብሮሙ ፡ ሎቱ ፡ ሕዝበ ፡
ሐዲሰ።
፲፪ ወለእስራኤልሰ ፡ ካዕበ ፡ አኅዞሙ ፡ ዑረተ ፡
ልብ፡እስከ፡ማኅለቅት።
ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕ
ማማቲሁ፡አድኃነነ።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ኅትም፡በከመ፡ኅተምከ፡
በጊዜ፡ነግህ።

## ምዕራፍ፡፶፫።

ትእዛዝ ፡ ወእምዝ ፡ ይትጋብኡ ፡ ካህናት ፡
ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡በዕለተ፡
ዐርብ፡በጊዜ፡ስድስቱ፡ሰዓት፡ለሥርዐተ፡
ጸሎት፡ወይጸልዩ፡በከመ፡ጸለዩ፡በዕለተ፡
ሐሙስ፡ጊዜ፡ስድስቱ፡ሰዓት።
ወይበል ፡ መራሒ ፡ በ፱ቱ ፡ ሃሌታ ፡ ተሰቅለ ፡
ተሰቅለ፡ተሰቅለ፡ወሐመ፡ቤዛ፡ኵሉ፡ኮነ፡
ዬ፡ዬ፡ዬ፡በመስቀሉ፡ቤዘወነ፡እሞት፡
ባልሐነ።
ወይበሉ፡ለከ፡ኃይል።

### ክፍል፡፩።
### ኦሪት፡ዘኍልቍ።
ምዕ፡፳፩፡፩–፱።

፩ ወሰምዐ፡ከነዓን፡ንጉሠ፡አራድ፡ዘይነብር፡
ውስተ፡አዜብ፡ከመ፡መጽኡ፡እስራኤል፡
እንተ፡ፍኖተ፡አታርን፡ወተቃተሎሙ፡ለእስ
፪ ራኤል፡ወማህረከ፡እምኔሆሙ፡ፄዋ።
ወበፅዑ ፡ እስራኤል ፡ ብፅዐተ ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ ወይቤሉ ፡ ለእመ ፡ አግብአ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ለዝንቱ፡ሕዝብ፡ለነ፡ናዐልሎ፡ሎቱ፡
፫ ወለአህጉሪሁ።
ወሰምዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃሎሙ ፡ ለእስ
ራኤል ፡ ወአግብአሙ ፡ ለከነዓን ፡ ውስተ ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፫፡ሰዓት።

ሰው፡ሥጋን፡ከባሕርዩ፡አዋሕዶ፡ለበሰ።
፱ ልዑል መለኮትም፡ከትስብእት፡ጋር፡አንድ፡
ባሕርይ ፡ ሆነ ፡ አልተለወጠም ፡ ይህቺም ፡
ከአምላክ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሆነች ፡ ተዋሕዶ ፡
የማትለወጥ፡የማትመረመር፡ናት።
፲ ቍጣውን ፡ በዕብራውያን ፡ ላይ ፡ ጨመረ ፡
በፍጹም፡መከራም፡ረገጣቸው።
፲፩ ምሕረቱን ፡ ቸርነቱንም ፡ ለአሕዛብ ፡ አደረገ
ላቸው ፡ እነርሱም ፡ አዲስ ፡ ወገኖች ፡ ያደረ
ጋቸው፡ናቸው።
፲፪ እስራኤልን ፡ ግን ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡
የልብ፡ድንቁርና፡ያዛቸው።
መድኃኒታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡
መከራ፡ተቀበለ፡በመከራውም፡አዳነን።
የጸሎቱን ፡ መፈጸሚያ ፡ በነግህ ፡ እንደ ፡
ፈጸምከ፡ፈጽም።

## ምዕራፍ፡፶፫።

ትእዛዝ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በከበረች ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ዐርብ ፡ በስድስት ፡
ሰዓት፡ካህናቱ፡ለጸሎት፡ሥርዓት፡ይሰብሰቡ፡
ሐሙስ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ እንደጸለዩት ፡
ይጸልዩ።
መሪው ፡ በ፱ ፡ ሃሌታ ፡ ይበል ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡
የነበረ፡ዛሬም፡ያለ፡ዓለምን፡አሳልፎ፡የሚኖር፡
ተሰቀለ፡ታመመ፡የዓለም፡ቤዛ፡ሆነ፡ወዮ፡ወዮ፡
ወዮ፡በመስቀሉ፡አዳነን፡ከሞትም፡ነፃ፡አወጣን።
ለከ፡ኃይልም፡ይበሉ።

### ክፍል፡፩።
### ኦሪት፡ዘኍልቍ።
ምዕ፡፳፩፡፩–፱።

፩ በአዜብ ፡ የሚኖር ፡ ከነናዊው ፡ የአራድ ፡
ንጉሥ፡እስራኤል፡በአታርን፡ጎዳና፡እንደ፡
መጡ፡ሰምቶ፡እስራኤልን፡ተዋጋቸው፡ከእሳ
ቸውም፡ምርኮን፡ማረከ።
፪ እግዚአብሔር ፡ ይኸንን ፡ ወገን ፡ በእጃችን ፡
ቢጥልልን፡ሰውንም፡አገሩንም፡ጉልት፡እናደ
ርግለታለን ፡ ብለው ፡ እስራኤል ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ስእለትን፡ተሳሉ።
፫ እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ልመና
ቸውን፡ሰምቶ፡የከነዓንን፡ሰዎች፡በእጃቸው፡

Scanned by CamScanner

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
|---|---|
| እደዊሆሙ፤ወአዕለልዎሙ፡ሎሙ፡ወለአህጉሪሆሙ፡ወሰመዩ፡ስሞ፡ለውእቱ፡መካን፡ማዕለልት። | ጣለላቸው፤ሰዎቹንም፡አገራቸውንም፡ጉልት፡አደረጓቸው፤የዚያንም፡ቦታ፡ስሙን፡ጉልት፡አሉት። |
| ፳ ወግዕዘ፡እፍአ፡እምደብረ፡ሖር፡መንገለ፡ፍኖተ፡ባሕረ፡ኤርትራ፡ወዖድዋ፡ለምድረ፡ኤዶም፡ወተቆጥዑ፡ሕዝብ፡በፍኖት። | ፳ ከሖር፡ተራራ፡አደባባይ፡ወጥተው፡ወደ፡ኤርትራ፡ባሕር፡ጎዳና፡ተጓዙ፤የኤዶምን፡ምድር፡ዞሩዋት፤ሕዝቡ፡በጐዳና፡ተበሳጨ። |
| ፳፩ ወሐመይዎ፡ለእግዚአብሔር፡ወለሙሴ፡ወይቤልዎ፡ለምንት፡አውጻእከነ፡እምድረ፡ግብጽ፡ከመ፡ትቅትለነ፡በውስተ፡ዝንቱ፡ገዳም፡እስመ፡አልቦቱ፡እክል፡ወአልቦቱ፡ማይ፡ወተቆጥዐት፡ነፍስነ፡በዝንቱ፡ኅብስት፡ዘአልቦ፡ባቍዕ። | ፳፩ እህል፡ውኃ፡የለበትምና፤ሰውነታችንም፡ረብህ፡ጥቅም፡የሌለው፡ይህን፡ኅብስቱን፡ሰልችታለችና፡በዚህ፡ምድረ፡በዳ፡ታጠፉን፡ዘንድ፡ለምን፡ከግብጽ፡አወጣኸን፡ብለው፡እግዚአብሔርን፡አሙት፤ሙሴንም፡ተቆጡት። |
| ፳፪ ወፈነወ፡እግዚአብሔር፡አራዊተ፡ምድር፡ላዕለ፡ሕዝብ፡ዘይቀትሉ፡ወይነስኩ፡ወሞቱ፡ሕዝብ፡ብዙኃን፡እምደቂቀ፡እስራኤል። | ፳፪ እግዚአብሔርም፡እየነደፉ፡የሚገድሉ፡የምድር፡እባቦችን፡በሕዝቡ፡አመጣባቸው፤ከእስራኤል፡ልጆች፡ብዙ፡ወገኖች፡ሞቱ። |
| ፳፫ ወመጽኡ፡ሕዝብ፡ኀበ፡ሙሴ፡ወይቤልዎ፡አበስነ፡እስመ፡ሐመይናሁ፡ለእግዚአብሔር፡ወለከኒ፡ጸሊ፡እንከሰ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡ያሰስል፡እምኔነ፡አርዌ፡ምድር። | ፳፫ ሕዝቡም፡ወደ፡ሙሴ፡መጥተው፡እግዚአብሔርን፡አምተናል፤አንተንም፡ተቆጥተናልና፡በደልን፤የምድር፡እባቦችን፡ከእኛ፡ያጠፋልን፡ዘንድ፡እንግዲህስ፡ወዲህ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ለምንልን፡አሉት። |
| ፳፬ ወጸለየ፡ሙሴ፡ኀበ፡እግዚአብሔር፡በእንተ፡ሕዝብ፡ወይቤሎ፡እግዚአብሔር፡ለሙሴ፡ግበር፡ለከ፡አርዌ፡ዘብርት፡ወአንብሮ፡ኀበ፡ይትኤመሩ፡ወእምከመ፡ነሰከ፡አርዌ፡ምድር፡ሰብአ፡ኵሎ፡ዘተነሰከ፡ለይርአዮ፡ወይሕየው። | ፳፬ ሙሴም፡ስለ፡ሕዝቡ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ለመነ፤እግዚአብሔርም፡ሙሴን፡የናስ፡እባብ፡ሠርተህ፡ሕዝቡ፡በሚያዩት፡ቦታ፡አኑረው፤የምድር፡እባብ፡ሰውን፡በነደፈ፡ጊዜ፡የተነደፈው፡ሰው፡ሁሉ፡አይቶት፡ይዳን፡አለው። |
| ፳፭ ወገብረ፡ሙሴ፡አርዌ፡ምድር፡ዘብርት፡ወአቀሞ፡ኀበ፡ይትኤመሩ፤ወኮነ፡እምከመ፡ነሰከ፡አርዌ፡ምድር፡ሰብአ፡ይኔጽሮ፡ለዝክቱ፡አርዌ፡ምድር፡ዘብርት፡ወየሐዩ። | ፳፭ ሙሴም፡ከናስ፡የተሠራ፡የምድር፡እባብን፡ሠርቶ፡በሚያዩበት፡ቦታ፡አቆመው፤የምድር፡አውሬ፡ሰውን፡በነደፈ፡ጊዜ፡ከናስ፡የተሠራ፡ያንን፡የምድር፡እባብ፡አይቶ፡ይድን፡ነበር። |
| ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ይኑርና፡ነቢዩ፡ኢሳይያስ፡የተናገረው፡ትንቢት፡ይህ፡ነው። |
| ምዕ፤፻፬፡፲፯–፲፰። | ምዕ፤፻፬፡፲፯–፲፰። |
| ፲፯ ወመጽአ፡ይጠባሕ፡ከመ፡በግዕ፡ወከመ፡በግዕ፡ዘኢይነብብ፡በቅድመ፡ዘይቀርፆ፡ከማሁ፡ኢከሠተ፡አፉሁ፡በሕማሙ። | ፲፯ እንደ፡በግ፡ይታረድ፡ዘንድ፡መጣ፤በግ፡በሚሸልተው፡ሰው፡ፊት፡እንደማይናገር፡እንደዚያ፡በመከራው፡ጊዜ፡አልተናገረም። |
| ፲፰ እስመ፡ይነሥእዋ፡ለነፍሱ፡ወኢየአምርዎ፡ለልደቱ፡ወይነሥእዋ፡ለሕይወቱ፡በኃጢአተ፡ሕዝብየ፡በጽሐ፡ለሞት። | ፲፰ ሰውነቱን፡ይይዟታልና፤ልደቱንም፡አያውቁትምና፤ሕይወቱንም፡ወደ፡ሞት፡ይወስዷታልና፤በወገኖቹ፡ኃጢአት፡ለሞት፡ደረሰ። |

Scanned by CamScanner

| በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
| --- | --- |
| ወሀብ፡እኩያነ፡ህየንተ፡ሞቱ፡ወአብ ዐለተ፡ህየንተ፡መቃብርቱ፡እስመ፡ኢገብረ፡ ኃጢአተ፡ወኢተረክበ፡ሐሰት፡ውስተ፡ አፉሁ። | ፱፤ ኃጢአትን፡አልሠራምና፡በአንደበቱም፡ ሐሰት፡ነገር፡አልተገኘምና፤ስለሞቱ፡ ክፉዎችን፡ለሞት፡እሰጣለሁ፤ስለ፡ ተቀበረም፡ባለጸጎችን፡አጠፋለሁ። |
| ወፈቀደ፡እግዚአብሔር፡ያንጽሖ፡እምነ፡ መቅሠፍቱ፡ወእመኒ፡ወሀብክሙ፡በእንተ፡ ኃጢአትክሙ፡ትሬኢ፡ነፍስክሙ፡ዘርዐ፡ ዘነዋኀ፡የሐዩ። | ፲፤ እግዚአብሔር፡ከግርፋቱ፡ያነፃው፡ዘንድ፡ ወደደ፤ስለ፡ኃጢአታችሁ፡ገንዘባችሁን፡ለመ ሥዋዕት፡ብትሠዉ፡ሰውነታችሁ፡ብዙ፡ ዘመን፡የሚገዛ፡ዘርን፡ታያለች። |
| ፲፩ ወይፈቅድ፡እግዚአብሔር፡ያእትት፡ ሕማመ፡እምነፍሱ፡ወያርእዮ፡ብርሃነ፡ ወይፈልጥ፡በጥበቡ፡ወያጸድቆ፡ለጻድቅ፡ ለዘይትቀነይ፡ለጽድቅ፡ወለሠናይ፡ ወለብዙኃን፡ኃጢአቶሙ፡ውእቱ፡ይደ መስስ። | ፲፩፤ እግዚአብሔር፡ከሰውነቱ፡ሕማምን፡ያርቅ፡ ዘንድ፡ይወዳል፤ብርሃንንም፡ያሳየዋል፤ በባሕርይ፡ጥበቡም፡ይለየዋል፤ለበጎ፡ነገርና፡ ለጽድቅም፡ለሚገዛ፡ሰው፡የጽድቁን፡ዋጋ፡ ይሰጠዋል፤የብዙ፡ሰዎችንም፡ኃጢአት፡ይደ መስሳል። |
| ፲፪ በእንተ፡ዝንቱ፡ውእቱ፡ይወርሶሙ፡ለእሥ ራኤል፡ወይማህርኮሙ፡ለጽኑዓን፡እስመ፡ ተውህበት፡ለሞት፡ነፍሱ፡ወተኈለቈ፡ ምስለ፡ኃጥአን። ወውእቱ፡ያዐርግ፡ኃጢአቶሙ፡ለብ ዙኃን፡ወበእንተ፡ኃጢአቶሙ፡ተውህበ፡ ውእቱ። | ፲፪፤ ሰውነቱ፡ለሞት፡ተሰጥታለችና፡ከኃጢአተ ኞችም፡ጋራ፡ተቈጥሮአልና፡ስለዚህ፡እስራ ኤልን፡እርሱ፡ይወርሳቸዋል፤ጽኑዓን፡ የሚሆኑ፡አሕዛብንም፡ይማርካቸዋል። እርሱ፡የብዙ፡ሰዎችን፡ኃጢአት፡ይዞ፡ወደ፡ መስቀል፡ይወጣል፤ስለ፡ኃጢአታቸውም፡ እርሱ፡ለሞት፡ተሰጠ። |
| ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ትኑርና፡ነቢዩ፡ኢሳይያስ፡የተናገረው፡ ትንቢት፡ይህ፡ነው። |
| ምዕ፤፲፪፤፪—፮። | ምዕ፤፲፪፤፪—፮። |
| ናሁ፡አምላኪየ፡ወመድኃኒየ፡ወእትዌከል፡ ቦቱ፡ወአሐዩ፡ቦቱ፡ወኢይፈርህ፡እስመ፡እግ ዚአብሔር፡ክብርየ፡ወትርሲትየ፡ወውእቱ፡ ኮነኒ፡መድኃኒየ። | ፪፤ እነሆ፡ፈጣሪዬ፡መድኃኒቴ፡እርሱ፡ነው፤ እኔም፡በእርሱ፡አምኜ፡ከመከራው፡እድንበ ታለሁ፤እግዚአብሔር፡ክብሬ፡ነውና፡ ጌጤም፡ነውና፡እሱም፡መድኃኒት፡ ሁኖኛልና፡አልፈራም። |
| ወትቀድሕ፡ማየ፡በትፍሥሕት፡እምአዘቅተ፡ ሕይወት። | ፫፤ ከሕይወትም፡ጕድጓድ፡ደስ፡እያለህ፡ውኃን፡ ትቀዳለህ። |
| ወትብል፡ይእተ፡አሚረ፡ሰብሕዎ፡ለእግዚአ ብሔር፡ወጸውዑ፡ስሞ፡ወንግርዎሙ፡ ለአሕዛብ፡ስብሐቲሁ፡ወተዘከሩ፡ከመ፡ ተለዓለ፡ስሙ። | ፬፤ የዚያንም፡ጊዜ፡እግዚአብሔርን፡አመስ ግኑት፤ስሙንም፡ጥሩ፤ለአሕዛብም፡ ጌትነቱን፡ንገሩአቸው፤ስሙም፡ከፍ፡ከፍ፡ እንዳለ፡አስቡ፡ትላለህ። |
| ሰብሑ፡ለስመ፡እግዚአብሔር፡እስመ፡ገብረ፡ ልዕልተ፡ኵሎ፡ወንግሩ፡ዘንተ፡ለኵሉ፡ ምድር። | ፭፤ ለእግዚአብሔር፡ስም፡ምስጋና፡አቅርቡ፤ታላ ላቅ፡ተአምራቶችን፡አድርጓልና፡ይኸንንም፡ ያደረገውን፡ተአምራቱን፡ሁሉ፡ለዓለሙ፡ ሁሉ፡ንገሩ። |

Scanned by CamScanner

## በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፮፡ ተፈሥሒ ፡ ወተሐሠዪ ፡ ወለተ ፡ ጽዮን ፡
እስመ፡ ተለዓለ ፡ በማእከሌኪ ፡ ቅዱሰ ፡
እስራኤል።

ምዕ፡፲፫፡፩-፲።

፩፡ ራእይ ፡ ዘርእየ ፡ ኢሳይያስ ፡ ወልደ ፡ አሞጽ ፡
በእንተ፡ባቢሎን።
፪፡ ንሥኡ ትእምርተ ፡ ላዕለ ፡ አድባረ ፡ ገዳም ፡
አንሥኡ፡ቃለክሙ፡ወአጽንዑ፡እደዊክሙ፡
ይምጽኡ፡ወያርኅዉ፡መላእክት።

፫፡ አነ፡እኤዝዞሙ፡ወአነ፡አመጽአሙ፡ለቅዱ
ሳንየ፡አነ፡አመጽአሙ፡ለእለ፡ያርብሕ፡እንዘ፡
ይትፌሥሑ ፡ ወይመጽኡ ፡ ኀቡረ ፡ ወይፌ
ጽሙ፡መዐትየ።

፬፡ ወያንሥርዎሙ ፡ በውውዓ ፡ ብዙኃን ፡
አሕዛብ፡ ወሠራዊት ፡ ወነገሥት ፡ እለ ፡
ተጋብኡ፡ወእግዚአብሔር፡ አዘዘ፡ይምጽኡ፡
አሕዛብ፡መስተቃትላን፡እምርኁቅ፡ብሔር፡
ወእምአጽናፈ፡ምድር።
፭፡ እግዚአብሔር ፡ መስተቃትላኒሁ ፡ አዘዘ ፡
ያጥፍእዋ፡ለዓለም።
፮፡ አውይዉ ፡ እስመ ፡ ቀርበት ፡ ዕለተ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ወይመጽእ፡ተቀጥቅጦ፡እምኀበ፡እግ
ዚአብሔር።
፯፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ እድ ፡ ይደክም ፡
ወኵሉ፡ነፍስ፡ይደነግፅ።

፰፡ ወይትሐወኩ ፡ ሊቃውንት ፡ ወይእኀዞሙ ፡
ማሕምም፡ከመ፡ብእሲት፡እንተ፡ትወልድ፡
ወይትቃተሉ፡በበይናቲሆሙ፤ወይትቀጽዑ፡
ገጾ፡ላህብ፡ገጾሙ።
፱፡ እስመ፡ናሁ፡ትመጽእ፡ዕለተ፡እግዚአብሔር፡
እንተ፡ምልዕት፡መዐት፡ወመቅሠፍት፡ከመ፡
ታጥፍእ ፡ ለምድር ፡ ወታኅልቆሙ ፡
ለብዙኃን፡እለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ።
፲፡ ወኢይበርሁ ፡ እንከ ፡ ከዋክብተ ፡ ሰማይ ፡
ወእለ፡ አርዮብ ፡ ወኵሉ ፡ ዓለመ ፡ ሰማይ ፡
ወፀሐይኒ ፡ ሠሪቆ ፡ ይጸልም ፡ ወወርኅኒ ፡
ኢትሁብ፡ብርሃና።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፮፡ እስራኤልን ፡ የሚያጸና ፡ በመካከልሽ ፡ ከፍ፡
ከፍ ፡ ብሏልና ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ኢየሩሳሌም፡
ደስ፡ይበልሽ።

ምዕ፡፲፫፡፩-፲።

፩፡ የአሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ ስለ ፡ ባቢሎን፡
ያየው፡ራእይ፡ይህ፡ነው።
፪፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡ ዓላማውን፡
አንሡ ፤ ቃላችሁን ፡ አሰሙ ፤ እጃችሁንም፡
አጽኑ ፤ አለቆችም ፡ መጥተው ፡ በሩን ፡
ይክፈቱ።
፫፡ እኔ ፡ አዝዛቸዋለሁ ፤ እኔ ፡ ወዳጆቼን ፡
(እንቂሮስ፡ ዳርዮስን) ፡ አመጣቸዋለሁ፤እኔ፡
አርበኞችንም ፡ አመጣቸዋለሁ ፤ ደስ ፡
እያላቸው ፡ አብረው ፡ ይመጣሉ፤ቍጣዬንም፡
በሠራዊቱ፡ይፈጽማሉ።
፬፡ ብዙዎች ፡ አሕዛብ ፡ እየደነፉ ፡ ያጕሳቍሏ
ቸዋል፤የተሰበሰቡ፡ነገሥታቱና፡ሠራዊቱም፡
ያጕሳቍሏቸዋል ፤ የሠራዊት ፡ ጌታ፡ አሸናፊ፡
እግዚአብሔር፡ አርበኞች፡አሕዛብ፡ከምድር፡
ዳርቻና፡ከሩቅ፡አገር፡ይመጡ፡ዘንድ፡አዘዘ።
፭፡ ዓለምን ፡ ያጠፉአት ፡ ዘንድ ፡እግዚአብሔር፡
አርበኞችን፡አዘዘ።
፮፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ቀርባለችና ፡ከእግዚአ
ብሔርም ፡ ዘንድ ፡ መከራ ፡ ይመጣልና ፡
አልቅሱ።
፯፡ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ እጅ ፡
ይደክማል ፤ የሰውም ፡ ሁሉ ፡ ልቡና ፡ ይደነ
ግጣል።
፰፡ አለቆችም ፡ ይታወካሉ ፤ የምትወልድ ፡ ሴት ፡
ጭንቅ ፡ እንዲይዛት ፡ ጭንቅ ፡ ይይዛቸዋል ፤
እርስበእርሳቸው ፡ ይዋጋሉ ፤ በመከራው ፡
ይጐብጣሉ፤ፊታቸውም፡ይላላባል።
፱፡ እግዚአብሔር ፡ ምድርን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡
ቁጣንና ፡ መቅሠፍትን ፡ የተመላች ፡የእግዚአ
ብሔር ፡ ቀን ፡ እነሆ ፡ ትመጣለችና ፡ በዷ ፡
የሚኖሩ፡ብዙ፡ሰዎችን፡ታጠፋቸዋለች።
፲፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ ከከቦች ፡
አያበሩም ፤ አስታርቦሽሽ ፡ ኮከብም ፡ አያበራም፡
(ልዑላኑ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አያገኙም) ፤ የሰማይ ፡
ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ አያበሩም ፤ ፀሐይም ፡ ታይቶ ፡
ይጠፋል ፤ (ንጉሡ) ፡ ጨረቃም ፡ ብርሃኗን ፡
አትሰጥም፤(ሊቀ፡ካህናቱ)።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ትርጓሜ፡ትንቢተ፡ኢሳይያስ፡ነቢይ።

ናሁ፡አምላኪየ፡ እስከ፡ ኀበ፡ ይብል፡ ወር
፩ ኅኒ፡ ኢትሁብ፡ ብርሃና፤ ይቤ፡ መተ
ርጕም፡ አምላኪየ፡ ወመድኃኒየ፡ ይትረ
ጐም፡ ዘንተ፡ ሶበ፡ ርእዩ፡ ምእመናን፡
በእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ዕለተ፡
ስቅለት፡ ክብርተ፡ ወትእምርታተ፡ ወመን
ክራተ፡ እለ፡ ኮና፡ ጠየቁ፡ ከመ፡ አምላክ፡
ውእቱ፡መድኃኔ፡ኵሉ፡ዓለም።
እስመ፡ ኮነት፡ ልቦሙ፡ ዘኢ.ማእምርተ፡
፪ በእንተ፡ዘኮነ፡ይነግሮሙ፡ቦቱ፡እግዚእነ፡
በእንተ፡ሕማሙ፡ማሕየዊት።
ወበ፡ካልእመ፡ትርጓሜ፡ወውእቱኬ፡ሶበ፡ርእየ፡
፫ ነቢይ፡ በአዕጻዳተ፡ ጥበብ፡ ዕለተ፡ ስቅለተ፡
እግዚእነ፡በከመ፡ርእዮ፡አብርሃም፡አበ፡አበው፡
ወተፈሥሐ፡ ቦቱ፡ ወኮነ፡ ከመ፡ ዘይሬእዮ፡
ውእቱ፤ወውእቱ፡ይብል፡ናሁ እግዚአብሔር፡
መድኃኒየ፡ ወጠየቀ፡ እንከ፡ ከመ፡ ውእቱ፡
መድኅነ፡ዓለም፡ ወረሰየ፡ትውክልቶ፡ላእሌሁ፡
ከመ፡ያድኅኖ፡ምስለ፡አቡሁ፡አዳም።
፬ ይቤ፡ ወእትቄከል፡ ቦቱ፡ ወኢይፈርህ፡
ይትረጐም፡ዘንተ፡እስመ፡እምድኅረ፡አስተ
ርአየ፡ጻድቅ፡ለመሀይምናን፡በስሙ፡ቅዱስ፡
ኅደጉ፡እምኔሆሙ፡ኵሎ፡ዘኮነ፡ወረሰዩ፡ትው
ክልቶሙ፡ላእሌሁ፡ዘእንበለ፡ፍርሀት፡ኢ፡
እምንዴት፡ወኢ፡እምነ፡ሞት።
፭ ይቤ፡እስመ፡እግዚአብሔር፡ ክብርየ፡ወትር
ሲትየ፡ ይትረጐም፡ ዘንተ፡ ነቢይ፡ እለ፡
ተወከሉ፡ላእለ፡እግዚአብሔር፡ ኃሣሥያነ፡
ሥምረቱ፡ ትከውን፡ በረከቱ፡ ኅድርተ፡
ላእሌሆሙ፡ ወኀቤሆሙ፤ ወይሴባሕ፡
አምላክ፡ በላእሌሆሙ።
፮ ይቤ፡ኮነኒ፡ሊተ፡መድኃኒተ፡ይትረጐም፡
ዘንተ፡ እስመ፡ መድኃኒትነ፡ ኮነ፡ ለነ፡
በመስቀለ፡አምላክ፡ቃል።
፯ ይቤ፡ትቀድሕ፡ማየ፡በትፍሥሕት፡እምአ
ዘቅተ፡ ሕይወት፤ ይትረጐም፡ እስመ፡
አሕዛብ፡ አእመርዎ፡ለአምላኮሙ፡ ወአምኑ፡
ቦቱ፤ ወተወከሉ፡ ላዕሌሁ፡ ወኀደረት፡
፰ በረከት፡ላዕሌሆሙ።
ወአምከሮሙ፡ ከመ፡ ይስተዩ፡ ትምህርተ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

የነቢዩ፡ኢሳይያስ፡ትንቢት፡ትርጓሜ።

፩ ናሁ፡አምላኪየ፡ ከሚለው፡ ጀምሮ፡ ወርኅኒ፡
ኢትሁብ፡ ብርሃና፡ እስከሚለው፡ ድረስ፡
ተርጓሚው፡ ፈጣሪዬ፡ መድኃኒቴ፡ አለ፤
በጌታችን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ያመኑ፡
ምእመናን፡የከበረች፡የስቅለት፡ቀን፡ባዩ፡ጊዜ፡
ይህንን፡ይተረጕማል፤እርሱ፡የዓለሙ፡ሁሉ፡
መድኃኒት፡ አምላክ፡ እንደሆነ፡ በተደረጉ፡
አስደናቂ፡ታምራቶች፡ተረድተዋልና።
፪ ጌታችን፡ አዳኝ፡የሆነች፡የሕማሙን፡ነገር፡
በሚናገርበት፡ ነገር፡ ልባቸው፡ የማታውቅ፡
ሁና፡ነበርና።
፫ ሌላም፡ ትርጓሜ፡ አለ፤ ይኸውም፡ የአበው፡
አባት፡አብርሃም፡አይቶ፡ደስ፡እንደተሰኘበት፡
እርሱ፡ እንደሚያየው፡ ሆኖ፡ እነሆ፡ እግዚአ
ብሔር፡ መድኃኒቴ፡ እንዳለ፡ ነቢይ፡ በጥበብ፡
አጸዶች፡ጌታ፡ የተሰቀለባትን፡ቀን፡ባዬ፡ጊዜ፡
እርሱ፡ ያየው፡የዓለም፡ መድኃኒት፡ እንደሆነ፡
ተረድቶ፡ ከአባቱ፡ ከአዳም፡ ጋር፡ እንደሚያ
ድነው፡እምነቱን፡በእርሱ፡ላይ፡አደረገ።
፬ እታመንበታለሁ፤አልፈራም፡አለ፤እውነተኛ፡
አምላክ፡ ለምእመናን፡ በሃይማኖት፡ ከተገለጸ
ላቸው፡ በኋላ፡ ከእርሳቸው፡ የነበረውን፡ ሁሉ፡
ትተው፡ ከችግርም፡ ሆነ፡ ወይም፡ ከሞት፡ ያለ፡
መፍራት፡ እምነታቸውን፡ በእርሱ፡ ስም፡
ያደረጉ፡ስለሆነ፡ይህንን፡ይተረጕማል።
፭ እግዚአብሔር፡ ክብሬ፡ ጌጤም፡ ነውና፡ አለ፤
ነቢይ፡ በእርሱ፡ የሚታመኑትንና፡ ፈቃዱን፡
የሚፈጽሙትን፡ ጸጋው፡ በረከቱ፡ ታድርባቸ
ዋለች፤ በእነርሱም፡ ዘንድ፡ አምላክ፡ ይመሰገ
ናልና፡ይህንን፡ይተረጕማል።
፮ መድኃኒትን፡ ሆነኝ፡ አለ፤ በአምላክ፡ ቃል፡
መስቀል፡ለኛ፡ድኅነታችን፡ሆኖአልና፡ይህን፡
ይተረጕማል።
፯ ደስ፡ ብሎህ፡ ከሕይወት፡ ጕድጓድ፡ ውኃን፡
ትቀዳለህ፡ አለ፤ ይህንንም፡ አሕዛብ፡ ፈጣሪያ
ቸውን፡ እንዳወቁትና፡ እንዳመኑበትም፡
በእርሱም፡ላይ፡እንደተማመኑ፡በረከቱም፡እን
ዳደረችባቸው።
፰ ለነፍሳቸው፡ሕይወት፡መድኃኒት፡የምትሆን፡

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ማሕየዊተ፡መድኃኒተ፡ነፍሳቲሆሙ፡እምአ
ዘቅት፡እምላካዊት፡ዘውእቱ፡ማየ፡ሕይወት፡
በፍሥሐ።

፱፡ ወበእንተ፡ውእቱ፡ይቤ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡
እስመ፡አፍላገ፡ማየ፡ሕይወት፡ይውኅዝ፡
እምከርሡ።

፲፡ ወብሂሎቱ፡በትፍሥሕት፡አኮ፡በከመ፡
ተመጠዉ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡ትእዛዘ
ቲሆሙ፡ወሕገጊሆሙ፡በፍርሀት፡ወበግርማ፡
ዕጹብ፡ወናእከ፡ወሰአልዎ፡ለሙሴ፡እንዘ፡
ይብሉ፡ተናገረነ፡አንተ፡ወኢይትናገረነ፡እግ
ዚአብሔር፡ከመ፡ኢንሙት፡ዳእሙ፡
አእመሮሙ፡ሙሴ፡በአእምሮ፡በዝየ፡በሀየ፡
በፍሥሐ፡እስመ፡ኮኑ፡እምድኅረ፡ግብርናት፡
ውሉደ።

፲፩፡ እስመ፡አግዐዞሙ፡መድኅን፡ለምእመናን፡
በስሙ፡እምግብርናተ፡ሰይጣን፡መሪር፡ወተ
ማየጠሙ፡በደሙ፡ቅዱስ፡ወአልቦሙ፡
ፍርሀት፡ወኢድንጋፄ፡ዳእሙ፡ትፍሥሕት፡
ዘለዓለም፡ወበእንተ፡ውእቱ፡ይቤ፡ሐዋርያ፡
ኩኑ፡ፍሡሓነ፡በእግዚአብሔር፡ዘልፈ።

፲፪፡ ይቤ፡ወትብል፡ይእተ፡አሚረ፡ሰብሕዎ፡ለእግ
ዚአብሔር፡ወጸውዑ፡ስሞ፡ወንግርዎሙ፡
ለአሕዛብ፡ስብሐቲሁ፡ይተረጐም፡ዘንተ፡
እስመ፡ሃይማኖቱ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡እምድኅረ፡ስቅለቱ፡ክቡር፡ወትን
ሣኤሁ፡ቅድስት፡ተሰምዐት፡ውስተ፡ኵሉ፡
አሕዛብ፡ወሰበኩ፡በስሙ፡ውስተ፡ኵሉ፡
መካን።

፲፫፡ ይቤ፡ወተዘከሩ፡ከመ፡ተለዓለ፡ስሙ፡
ይተረጐም፡ከመ፡ውእቱ፡ውስተ፡ፍድፍድና፡
አሕዛብ፡እለ፡አምኑ፡ቦቱ።

፲፬፡ ወእስከ፡ኢተርፈት፡ውስተ፡ምድር፡መካን፡
እለ፡ውስቴታ፡ምእመናን፡በስሙ፡
ይሴብሕዎ፡ወይዜምሩ፡ሎቱ፡በመዐልት፡
ወበሌሊት።

፲፭፡ ይቤ፡ይትፌሣሕ፡ወይትሐሠይ፡እለ፡
ይነብሩ፡ውስተ፡ጽዮን፡እስመ፡ተለዓለ፡በማእ
ከሌኪ፡ቅዱስ፡እስራኤል፤ይተረጐም፡ዘንተ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

ከአምላካዊት፡ጕድጓድ፡የተገኘችውን፤
የሕይወት፡ውኃ፡ትምህርትን፡ደስ፤
ብሏቸው፡እንዲጠጡ፡እንደ፡አስተማራቸው፤
ይተረጐማል።

፱፡ ስለዚህም፡የከበረ፡ወንጌል፡የሕይወት፡ውኃ፡
ከባሕር፡ይፈሳል፡ብሏልና።

፲፡ ደስ፡ብሏቸው፡ያለውም፡የእስራኤል፡ልጆች፤
በመፍራትና፡በሚያስጨንቅ፡ግርማ፤
በልቅሶ፡በሐዘን፡ሕጋቸውንና፡ሥርዓታ
ቸውን፡ሲቀበሉ፡እንደ፡ነበረው፡አይደለም፤
ሙሴንም፡አንተ፡ተናገረን፡እንጂ፡እንዳ
ንሞት፡እግዚአብሔር፡አይናገረን፡እያሉ፤
እንደ፡ለመኑት፡ያለ፡አይደለም፤ነገር፡ግን፡
በዚያ፡ሙሴ፡በዕውቀት፡አሳወቃቸው፤
በዚህም፡ከባርነት፡በኋላ፡ልጆች፡ሁነዋልና።

፲፩፡ ጌታችን፡መድኃኒታችን፡ምዕመናንን፡በከበረ፡
ደሙ፡ዋጅቶ፡መሪር፡ከሆነ፡ከሰይጣን፡
ተገዢነት፡በስሙ፡ነፃ፡አውጥቷቸዋልና፤
እንግዲህ፡ዘለዓለማዊ፡ደስታ፡እንጂ፡ፍርሃት፡
የለባቸውም፤ስለዚህም፡ሐዋርያው፡ሁልጊዜ፡
በእግዚአብሔር፡ደስተኞች፡ሁኑ፡አለ።

፲፪፡ ያን፡ጊዜ፡እግዚአብሔርን፡አመስግኑት፤
ስሙንም፡በምስጋና፡ጥሩ፡ጌትነቱንም፡
ለአሕዛብ፡ንገሩ፡አለ፤ይኸንንም፡በጌታችን፡
በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ማመን፡ልዩ፡ከሆነች፡
ትንሣኤውና፡ከከበረ፡ስቅለቱ፡በኋላ፡
በአሕዛብ፡ሁሉ፡ዘንድ፡እንደ፡ተሰማች፤
በቦታው፡ሁሉ፡በስሙ፡እንደ፡ሰበኩ፤
ይህንን፡ይተረጐማል።

፲፫፡ ስሙ፡ከፍ፡ከፍ፡እንዳለ፡አስቡ፡አለ፤በእመ
ኑበት፡በአሕዛብ፡ብዛት፡ውስጥ፡እንደሆነ።

፲፬፡ በዓለም፡ውስጥም፡በቀንና፡በሌሊት፤
ምእመናን፡በስሙ፡የሚዘምሩበትና፡የሚያ
መሰግኑበት፡ቦታ፡እስከ፡አልቀረ፡ድረስ፤
ሃይማኖት፡እንደ፡ተስፋፋ፡ይተረጐማል።

፲፭፡ እስራኤልን፡የሚያጸና፡በመካከልሽ፡ከፍ፤
ከፍ፡ብሏልና፡በጽዮን፡የሚኖሩ፡ፈጽም፡ደስ፡
ይላቸዋል፡አለ፤ጌታችን፡በመካከላቸው፤

Scanned by CamScanner

## በ፰፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ተለሰሎቶ፡ ለእግዚአን ፡በማእከሌሆሙ፡ዲበ፡
መስቀል ፡ ማሕየዊ ፡ ወተፈሥሐ ፡ ነፍሳተ ፡
ምእመናን፡በእንተ፡መድኃኒት፡ዘለዓለም።

፲፮ ይቤ፡ንሥኡ፡ትእምርተ፡እምአድባረ፡ገዳም፡
ጸይሐት ፡ ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡ ትእምርተ ፡
መስቀል፡ቅዱስ፡እንተ፡ጸርዋ፡ነገሥት፡መሀ
ይምናን ፡ በክርስቶስ ፡እለ ፡ ሖሩ፡ ውስተ ፡
ፍናተ፡ጸይሕት ፡እንተ ፡ ትወስድ ፡ ውስተ ፡
ሕይወት፡ከመ፡ቈስጠንጢኖስ፡ጻድቅ፡ወዘይ
መስሎ።

፲፯ ወለእመ፡ኮነ፡ ሰመያ ፡ እግዚእ ፡ለፍኖት ፡
እንተ፡ትወስድ፡ውስተ፡ሕይወት፡መቅዓን ፤
ወውእቱሰ፡እስመ፡በአምጣነ፡ላዕለ፡ሃይማ
ኖቶሙ ፡ ንፍቅት ፡ ወይገብሩ ፡ ምንናተ ፡
ወይተልዉ ፡ ፍትወታቲሆሙ ፡ ውስተ ፡
በሊዖታት ፤ ወሰትዮታት ፤ ወካልእታኒ ፡
ትክውን፡እንከ፡ፍኖተ፡ሕይወት፡እንተ፡
ይእቲ፡ጾም፡ወጸሎት፡ወምጽዋት፡ወፍቅር፡
ወኀዲገ ፡ ትፍግዕታት ፡ መቅዓን ፡ ጥቀ ፡
በኀቤሆሙ፡ሞት።

፲፰ ወይእቲሰ፡ለኀበ፡መሀይምናን ፡ በአማን ፡
ጥዕምት፡እምጸቃውዕ።

፲፱ ወናሁ፡ይቤ፡ እግዚእን ፡በውስተ ፡ ካልእ ፡
መካን፡እስመ፡ጥዑም፡አርዑትየኒ፡ሠናይ፡
ወጾርየኒ፡ቀሊል።

፳ ይቤ፡ አንሥኡ፡ ቃለክሙ ፡ ወኢትፍርሁ ፡
ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡ በእንተ ፡ አርድእት ፡
ንጹሐን፡እስመ፡አዘዞሙ፡ እግዚእ ፡ከመ ፡
ይሰብኩ ፡ ወንጌለ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍርሀት ፡
ወእለተ፡ፍርሀቶሙ፡በብሂሎቱ፡ሎሙ፡
ናሁ፡አሄሉ፡ምስሌክሙ፡እስከ፡ኅልቀተ፡
ዓለም።

፳፩ የተረጐም ፡ ከመ ፡ ሀለወ ፡ ውእቱ ፡
ምስሌሆሙ፡ በአጽንዖቱ፡ሎሙ፡ወምስለ፡
እለ፡አምኑ፡በላዕለ፡እደዊሆሙ፡ወተወክፉ፡
ትእዛዛቲሁ ፡ እምአፉሆሙ ፡ ቅድስት ፡
ወገብሩ፡ ኪያሃ፡ ወውእቱኬ፡ ምስሌሆሙ ፡
እስከ፡ማኅለቅት።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

አዳኝ ፡ በሆነ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
እንዳለ፡ስለ፡ዘለዓለማዊ፡ድኅነታቸው፡የምእ
መናን፡ነፍሳት፡ደስ፡እንዳላቸውም፡ይህንን፡
ይተረጉማል።

፲፮፤ በተጠረገች ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ተራሮች ፡ ላይ ፡
ዓላማውን ፡ አንሡ ፡ አለ ፤ ይህንንም ፡ በክር
ስቶስ ፡ያመኑ፡ምእመናን፡ነገሥታት፡እንደ፡
ጻድቁ ፡ ቈስጠንጢኖስና ፡ እርሱን ፡
የሚመስሉ፡ወደ፡ሕይወት፡በምታደርስ፡በተ
ጠረገች ፡ መንገድ ፡ ሲሄዱ ፡ የተሸከሙት ፡
የከበረ ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ እንደሆነ ፡
ይህንን፡ይተረጉማል።

፲፯፤ ወደ ፡ ሕይወት ፡ የምትወስደዋን ፡ መንገድ ፡
ጌታ ፡ጭንቅ ፡ የሚላት ፡ ከሆነ ፡ እርሱም ፡
ግማሽ፡ በሆኑች ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የተናቀ ፡
ነገርን፡መብል፡መጠጥን፡በመከተል፡የሚደ
ረገው ፡ ሰፊ ፡ መንገድ ፡ ሲሆን ፤ ሌላይቱ ፡
የሕይወት ፡ መንገድ ፡ የጸሎት ፡ የጾም ፡
የምጽዋት ፡ የፍቅር ፡ ምኞትን ፡ መተው ፡
በእነርሱ፡ዘንድ፡ጭንቅ፡ሞት፡እንደምትሆን
ባቸው፡ይተረጉማል።

፲፰፤ እርሷም ፡ በምእመናን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ማር ፡
ወለላ፡ጣዕም፡ያላት፡ናት።

፲፱፤ እነሆ ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ጌታችን ፡ቀንበሬ ፡
ልዝብ፡ሸክሜ፡ቀላል፡ሕጌም፡ጣፋጭ፡ነው፡
ብሏልና።

፳፤ ድምፃችሁን ፡ አሰሙ ፤ አትፍሩ ፡ አለ ፤
ይኸንንም፡ስለ፡ንጹሐን፡አርድእት፡ይተረ
ጉማል ፤ ወንጌልን፡ያለ፡ፍርሀት፡ይሰብኩ፡
ዘንድ ፡ ጌታ ፡አዝዞአቸው ፡ ነበርና ፤ እስከ ፡
ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡
እኖራለሁ፡ በማለቱ፡ ፍርሃታቸውን፡ አርቆላ
ቸዋልና።

፳፩፤ እነርሱን፡በማጽናቱ፡በእነርሱ፡ትምህርት፡
በአመኑና፡ከከበረች፡አንደበታቸው፡ትዕዛዛ
ቸውን ፡ ተቀብለው ፡ እርሷን ፡ በፈጸሙ ፡
እርሱ፡ከእነርሱ፡ጋር፡እንደሚኖርም፡ይተረ
ጉማል።

## በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፱፡ ይቤ፡አነ፡አመጽአሙ፡ወይመጽኡ፡ኃያላን፡ ወይፌጽሙ፡ መዐትየ፡ በትፍሥሕት፤ ይትረጐም፡ዘንተ፡ከመ፡ለነገሥት፡ወለጠቢባን፡ወለሊቃውንት፡እምኵሉ፡አሕዛብ፡ያስተርኢ፡ሎሙ፡ጽድቅ፡ወይሰሐቡ፡ኀበ፡እግዚእ፡ወይወፅኡ፡እምጽልመት፡እንተ፡ይእቲ፡መዐት፡ወይፌጽሙ፡በሃይማኖት፡በእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወይትፌሥሓ፡አልባቢሆሙ፡በርደተ፡ጸጋ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ላዕሌሆሙ።

፴፡ በከመ፡ኮነ፡ለቆርኔሌዎስ፡መኰንን፡ወጉባኤሆሙ፡ወነሥኢአሙ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡በትምህርተ፡ጴጥሮስ፡ሐዋርያ፡ተፈሥሐ፡ፈድፋደ፡ወበርሀ፡አልባቢሆሙ፡ወአእመሩ፡ከመ፡ውእቶሙ፡ፈጸሙ፡መዋዕሊሆሙ፡እስከ፡ውእቱ፡ጊዜ፡በመዐት፡ወጽልመት፡ዝ፡ውእቱ፡ርሒቅ፡እምሃይማኖት፡ዘበእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።

፴፩፡ ወሶበ፡አምኑ፡ኮኑ፡ፍጹማነ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ወዐብየ፡ፍሥሐሆሙ፡ወሐሤቶሙ።

፴፪፡ ወከማሁ፡ኀጽውኒ፡መጋቢሃ፡ለንግሥተ፡ኢትዮጵያ፡ምስለ፡ፊልጶስ፡ወእፎ፡ኮነ፡የሐውር፡ፍኖቶ፡እንዘ፡ይትፌሣሕ፡ወይትሐሠይ፡በሃይማኖት፡ዘበእግዚእነ፡ወትምህርተ፡ትዕዛዛቲሁ፡እምአፈ፡ሐዋርያቲሁ።

፴፫፡ ይቤ፡ውውዓ፡አሕዛብ፡ወመንግሥታት፡ይትጋብኡ፡በእግዚእ፡ወውእቱኬ፡በከመ፡አቅደመ፡ቃለ፡እስመ፡አሕዛብ፡ወሕዝብ፡ይመጽኡ፡ኀበ፡እግዚእ፡በጽውዓ፡አርድእት፡ንጹሐን፡ኀቤሆሙ።

፴፬፡ ይቤ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ኵሉ፡እድ፡ይደክም፡ወኵሉ፡ነፍስ፡ይደነግፅ፡ወየሐዝን፡አሐዱ፡ምስለ፡ካልኡ፡ወይትባረጽ፡ገጸሙ፡ከመ፡ላህበ፡እሳት፡ይትረጐም፡ዘንተ፤ እስመ፡ሕዝበ፡እስራኤል፡ወአሕዛብ፡ሶበ፡ርእዩ፡ጸጋ፡እንተ፡ኮነት፡ለአርድእት፡ንጹሐን፡በሀብተ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡በጽርሐ፡ጽዮን፡በሀገር፡ቅድስት፡ደንገፁ፡አልባቢሆሙ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፳፱፡ እኔ፡ኃይለኞችን፡አመጣቸዋለሁ፤ደስ፡እያላቸውም፡መጥተው፡ቍጣዬን፡ይፈጽማሉ፡አለ፡ይኸንንም፡ለነገሥታቱና፡ለመምህራን፡ለሊቃውንት፡ከአሕዛብ፡ሁሉ፡መካከል፡እውነት፡እንደ፡ተገለጸላቸው፡ወደ፡ጌታም፡በሃይማኖት፡እንደቀረቡ፡ከጨለማም፡እንደወጡ፡እርሷም፡መዐት፡የተባለች፡ናት፤ በጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ማመን፡ፍጹማን፡ሁነው፡የመንፈስ፡ቅዱስ፡ሀብት፡ጸጋ፡በላያቸው፡ወርዶ፡ደስ፡እንደሚላቸው፡ይተረጐማል።

፴፡ ለሹሙ፡ለቆርኔሌዎስ፡እንደተደረገ፡ከእርሱ፡ዘንድ፡ተሰብስበው፡የነበሩትም፡በጴጥሮስ፡ትምህርት፡ካመኑ፡በኋላ፡መንፈስ፡ቅዱስን፡ተቀብለው፡እጅግ፡ደስ፡እንዳላቸው፡ልቡናቸውም፡በርቶላቸው፡እስከ፡አመኑበት፡ጊዜ፡ያለውን፡ዘመናቸውን፡በመዓትና፡በጨለማ፡እንዳሳለፉት፡አወቁ፤ ይህም፡በጌታችን፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከማመን፡መራቅ፡ነው።

፴፩፡ በአመኑም፡ጊዜ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ፍጹማን፡ሁነው፡ተድላ፡ደስታቸው፡ከፍ፡ከፍ፡አለ።

፴፪፡ እንዲሁም፡ለኢትዮጵያ፡ንግሥት፡መጋቢ፡የነበረው፡ጃንደረባም፡የሐዋርያትን፡ትምህርትና፡ትዕዛዝ፡ተቀብሎ፡በጌታችን፡በማመን፡ደስ፡እያለው፡ከፊልጶስ፡ጋር፡እንዴት፡መንገዱን፡ይጓዝ፡ነበር?

፴፫፡ አሕዛብና፡ነገሥታት፡በድንፋታ፡በጌታ፡ይሰበሰባሉ፡አለ፤ ይህንንም፡እንደ፡ጌታ፡ቃል፡ሕዝብና፡አሕዛብ፡በንጹሐን፡ሐዋርያት፡ጥሪ፡ (ትምህርት)፡ወደ፡ጌታ፡እንደሚሰበሰቡ፡ይተረጐማል።

፴፬፡ ስለዚህም፡የሰው፡እጅ፡ይደክማል፤የሰውም፡ሁሉ፡ልቡና፡ይደነግጣል፤ አንዱም፡ከሌላው፡ጋር፡ያዝናል፤ ፊታቸውም፡እንደ፡እሳት፡ይላላባል፡አለ።

ይህንንም፡እስራኤልና፡አሕዛብ፡በከበረች፡ሀገር፡በጽዮን፡አዳራሽ፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡ስጦታ፡የተነሣ፡ለንጹሐን፡ሐዋርያት፡የሆነችውን፡በአዩ፡ጊዜ፡ልቡናቸው፡እንደ፡ደነገጠ፡ይተረጐማል።

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፰ ወሶበ፡ወጠኑ፡አርድእት፡ያብሥርዎሙ፡በስመ፡ክርስቶስ፡ጠንቀቃ፡አልባቢሆሙ።

፲፱ በከመ፡ስምዐ፡ኮነ፡በእንተ፡ዝንቱ፡መጽሐፈ፡ግብረ፡ሐዋርያት፡ወተባረጸ፡ገጸቲሆሙ፡ከመ፡እሳት፡በእንተ፡ኀፍረቶሙ፡ላዕለ፡ዘገብርዎ፡ወወጠኑ፡ይበሉ፡ለሐዋርያት፡ወውእቶሙ፡በሐዘነ፡ልብ፡አሐዱ፡ምስለ፡ካልኡ፡ምንተ፡ንግበር፡ኦ፡አኃዊነ፡ወይቤልዎሙ፡ነስሑ፡ወእመኑ፡በክርስቶስ።

፳ ይቤ፡ናሁ፡ዕለተ፡እግዚአብሔር፡ትመጽእ፡ዘእንበለ፡ሥርየት፡ይተረጎም ዘንተ፡ምጽአቶ፡ለእግዚእ፡በክብረ፡ስሙ፡በደኀሪት፡ዕለት፤ወኢይከውን፡ለአሐዱሂ፡ሥርየት፡ዘእንበለ፡ዳእሙ፡ከንቱ፤ወይፈድዮ፡ለኵሉ፡አሐዱ፡አሐዱ፡በከመ፡ምግባሩ።

፳፩ ይቤ፡ትመጽእ፡መቅሠፍት፡ወመዐት፡ከመ፡ትኅድጋ፡ለኵላ፡ዓለም፡መዝበረ፡ወታኀልቆሙ፡ለኃጥአን፡እምኔሃ፡ይተረጎም፡ኃጥአነ፡ኅበ፡ከሀድያን፡እለ፡ይከውኑ፡ተላውያኒሁ፡ለሐሳዌ፡መሲሕ፡ዘይከውን፡በደኀሪ፡መዋዕል፡በጊዜ፡ምጽአቱ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ለደይኖታት።

፳፪ ይቤ፡ወኢይበርሁ፡እንከ፡ከዋክብተ፡ሰማይ፡ወእለ፡አርዮብ፡ወኵሉ፡ዓለመ፡ሰማይ፡ወፀሐይኒ፡ሠሪቆ፡ይጸልም፡ወወርኅኒ፡ኢይበርህ፡ይተረጎም፡ዘንተ፡ከመ፡ዕለተ፡ምጽአተ፡እግዚእነ፡ሎቱ፡ስብሐት፡በደመና፡ሰማይ፡ይከውን፡ዝንቱ፡ኵሉ፡በከመ፡ይቤ፡በወንጌል፡ቅዱስ፡እምጸልምቶ፡ፀሐይ፡ወወርኅ፡ወወዲቀ፡ከዋክብት፡ወተሀውኮ፡ኃይለ፡ሰማያት፡ወምዝብርና፡ዓለም።

፳፫ ወይረስየነ፡እንከ፡እግዚአብሔር፡በይእቲ፡ዕለት፡ለእለ፡አልብነ፡ምግባረ፡ሠናይ፡በዘንድነ፡ባቲ፡እምውእቱ፡ግርማ፡ዐቢይ፡ወድንጋጼ፡ዕጹብ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

፲፰፤ ሐዋርያትም፡በክርስቶስ፡ስም፡ያበሥሩአቸው፡ዘንድ፡በጀመሩ፡ጊዜ፡ከልቡናቸው፡ተረዱ።

፲፱፤ ስለዚህ፡የሐዋርያት፡ሥራ፡መጽሐፍ፡ምስክር፡እንደሆነ፡ፊታቸው፡እንደ፡እሳት፡ተላላበ፤በአደረጉትም፡ሥራ፡ስለ፡አፈሩ፡አንዱም፡ከሌላው፡ጋር፡በልቡ፡አዝኖ፡ሐዋርያትን፡ወንድሞቻችን፡ምን፡እናድርግ፡ይሉ፡ዘንድ፡እንደ፡ጀመሩ፡እነርሱም፡ንስሓ፡ግቡ፤በክርስቶስም፡እመኑ፡እንዳሉአቸው፡መስክሮአል።

፳፤ እነሆ፡ያለ፡ይቅርታ፡የእግዚአብሔር፡ቀን፡ትመጣለች፡አለ፤ይኸንንም፡በኋለኛይቱ፡ቀን፡ጌታ፡በጌትነቱ፡እንደሚመጣና፡ለአንዱም፡ለአንዱ፡ይቅርታ፡እንደማይደረግለት፡ከንቱ፡በሆነ፡ሥራው፡ከሚፈረድበት፡በቀር፡ለአንዱም፡ለአንዱ፡እንደ፡ሥራው፡እንደሚከፍለው፡ይተረጉማል።

፳፩፤ ዓለምን፡ሁሉ፡የጠፋች፡የተፈታች፡አድርጋ፡ትተዋት፡ዘንድ፡መቅሠፍት፡የተመላች፡መዓት፡ትመጣለች፤ኃጥአንንም፡ከእርስዋ፡ታጠፋለች፡አለ፤በኋለኛው፡ዘመን፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ለፍርድ፡በሚመጣበት፡ጊዜ፡ኃጢአተኞች፡በተባሉ፡በሐሳዌ፡መሲሕ፡ተከታዮችና፡ከሐዲዎች፡ላይ፡የሚሆነውን፡ይተረጉማል።

፳፪፤ ከዚያም፡በኋላ፡በሰማይ፡ያሉ፡ኮከቦች፡አያበሩም፤አስታርቦሽሽ፡ኮከብም፡አያበራም፤የሰማይም፡ሠራዊት፡ሁሉ፡አያበሩም፤ፀሐይ፡ታይቶ፡ይጠፋል፤ጨረቃም፡አያበራም፡አለ፤ይህንንም፡የክብር፡ባለቤት፡ጌታችን፡በሰማይ፡ደመና፡ሲመጣ፡ይህ፡ሁሉ፡እንደሚሆን፡ይተረጉማል፤ከፀሐይና፡ከጨረቃ፡መጨለም፡ከከዋክብት፡መውደቅ፡ከሰማያት፡ኃይል፡መታወክ፡ከዓለምም፡ኅልፈት፡ሁሉ፡ጋር፡እንደሚሆን፡የከበረ፡ወንጌል፡እንደተናገረ።

፳፫፤ እንግዲህ፡ለእኛ፡በጎ፡ሥራ፡ለሌለን፡በዚያች፡በምታስፈራ፡በምታስደነግጥ፡በምታስጨንቅ፡በታላቋ፡ቀን፡እግዚአብሔር፡በምንድን፡ገንዘብ፡የተዘጋጀን፡ያድርገን።

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፴፬፡ ወንስእሎ፡ ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ለመድኃኒትነ፡ ዘመጽአ፡ ውስተ፡ ዓለም፡ ወተዐገሠ፡ ስቅለተ፡ ወሞተ፡ በእንቲአነ፡ ወከዐወ፡ ደሞ፡ ቅዱሰ፡ በዘቦቱ፡ ተሣየጠነ፡ ከመ፡ ይትወከፍ፡ ጾመክሙ፡ ወጸሎተክሙ፡ ወምጽዋታቲክሙ፡ ወንስሓክሙ፡ ወይትወከፍ፡ ቍርባናቲክሙ፡ ወጽንሓሓቲክሙ፡ ወይ ወይርዳእክሙ፡ ላዕለ፡ ተጋድሎትክሙ፡ ወይ ስማዕክሙ፡ አስተብቍዖተክሙ።

፴፭፡ ወየሀብክሙ፡ ለክሙ፡ በውስተ፡ዛቲ፡ዓለም፡ ምግባራተ፡ ብሩሃተ፡ ወአክሊላተ፡ ወባዝ ግናተ፡ወርቅ፡በደኀሪት፡ዕለት፡አሜን።

፴፮፡ ወይኅዕብ፡ ርስሐታቲክሙ፡ ወይደምስስ፡ አበሳክሙ፤ ወይጸጉክሙ፡ ትዕግሥተ፡ ወየሀ ብክሙ፡ተጋንዮ።

፴፯፡ ወካዕበ፡የሀብክሙ፡ሃይማኖተ፡ጽድቀ፡ለጸኒ ዖትክሙ፡ላዕለ፡አምልኮቱ፡ከመ፡ትትኃየል፡ ባቲ፡ነፍስክሙ፡ወሥጋክሙ።

፴፰፡ ወይባርክ፡ ለክሙ፡ ውስተ፡ ዘወሀበክሙ፡ እምበረከታቲሁ፡ ወያጽንዕ፡ ለክሙ፡ ላዕሌክሙ፡እምጸጋቲሁ።

፴፱፡ ወያቅምክሙ፡ ለዐቂበ፡ ትእዛዛቲሁ፡ ላዕለ፡ ምግባራት፡ ሠናያት፡ ወአፈድፍዶ፡ ውስቴታ፡ወሠኒቅ፡እምኔሃ፡ለዓለም፡እንተ፡ ትመጽእ፡ባቍዐ፡ሥንቀ።

፵፡ ወይክፍልክሙ፡ ገቢረ፡ ፈቃዱ፡ ወያቅር ብክሙ፡ ኀበ፡ ሥምረቱ፡ ወያድኅንክሙ፡ እምግርማ፡ ዘትሚምዑ፡ እምኔሁ፡ ወእምነሉ፡ መከራ፡ ወመንሱት፡ ወበቀል፡ ወቍስላት፡ ወሕማማት፡ ወደዌያት፡ ወንዴት፡ወዕዋሲያት።

፵፩፡ ወያድኅንክሙ፡እመዋግደ፡ምንዳቤያት፡ወአ ብሕርት፡ኀሊና፡መስተመይንት፡ወኃጣይእ።

፵፪፡ ወያእትት፡እምኔክሙ፡ኵሎ፡ኀሊና፡ሥጋዊ፡ ወየሀብክሙ፡ ለክሙ፡ ኵሎ፡ ገድለ፡ መንፈሳዌ፡ ወያግብእ፡ ለዘተሀጕለ፡ እምኔክሙ፡ ወይፈውስ፡ ድውያኒክሙ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፴፬፡ እኛን፡ ለማዳን፡ ወደ፡ ዓለም፡ የመጣውን፡ ስቅለትን፡ሞትን፡የታገሠውን፡እኛን፡የዋጀ በትን፡የከበረ፡ደሙን፡ያፈሰሰውን፡ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ እንለምነው፤ ጾማችሁን፤ ጸሎታችሁን፤ ምጽዋታችሁን፤ ንስሓችሁን፡ ይቀበል፡ ዘንድ፡ ቍርባናች ሁንና፡ ዕጣናችሁንም፤ ተቀብሎ፡ በገድል፡ በትሩፋት፡ሥራችሁ፡ላይ፡ይርዳችሁ፤ምልጃ ችሁንም፡ይስማችሁ።

፴፭፡ በዚችም፡ ዓለም፡ ውስጥ፡ በጎ፡ ሥራ፡ መሥራትን፡ ለእናንተ፡ ይስጣችሁ፤ በኋላ ኛይቱ፡ዕለትም፡የወርቅ፡ማርዳንና፡የብርሃን፡ አክሊላትን፡በእውነት፡ያቀዳጃችሁ።

፴፮፡ ዕድፋችሁን፡ ይጠብላችሁ፤ በደላችሁንም፡ ይደምስስላችሁ፤ ትዕግሥትን፡ መመለስን፡ ይስጣችሁ።

፴፯፡ ደግሞም፡ ሰውነታችሁ፤ ሥጋችሁም፡ ትበረታ፡ ዘንድ፡ በአምልኮቱም፡ ለመጽናት፡ ዕውነተኛውን፡ሃይማኖት፡ይስጣችሁ፤ያጽና ላችሁ።

፴፰፡ ከሰጣችሁም፡ ከበረከቱ፡ ውስጥ፡ እንዳይነ ሣችሁ፡ ይባርክላችሁ፤ ከስጦታውም፡ የሰጣ ችሁን፡ያጽናላችሁ።

፴፱፡ ሕጉን፡ትእዛዙንም፡ለመጠበቅ፡ያቁማችሁ፤ በበጎ፡ ሥራ፡ በውስጥዋ ትሩፋትን፡ በማብዛት፡ ለምትመጣዋም፡ ዓለም፡ የሚጠቅም፡ ሥንቅ፡ ከእርስዋ፡ በመሠነቅ፡ የምትገኙ፡ያድርጋችሁ።

፵፡ ፈቃዱን፡ ለመፈጸም፡ ያድላችሁ፤ ወደ፡ ቸርነቱም፡ ያቅርባችሁ፤ ከሚያሸብራችሁና፡ ከሚያስፈራችሁ፡ ከመከራው፡ ሁሉ፡ ከጥፋትም፡ ከቂም፡ ከበቀል፡ ከቍስል፡ ከሕማም፡ ከደዌ፡ ከችግር፡ ከልምሾነት፡ ያድናችሁ።

፵፩፡ በችግርም፡ማዕበል፡ከመስጠም፡ኃጢአትን፡ ተንኮልን፡ከሚያመጣ፡ሀሳብም፡ያድናችሁ።

፵፪፡ ሥጋዊ፡ አሳብን፡ ሁሉ፡ ከእናንተ፡ ያርቅ፤ መንፈሳዊ፡ የሆነ፡ ገድል፡ ትሩፋትን፡ ያሠራችሁ፤ ከእናንተ፡ ውስጥ፡ የጠፋውን፡ ይመልስ፤ በሽተኞቻችሁን፡ይፈውስ፤መጻተ

## በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወይሚጠሙ፡ ለግዩራኒክሙ፡ ወያግብኡሙ፡
ለነጋድያን፡ኀቤክሙ፡በዳኅና፡ወበሰላም።
፴፫ ወየሀብክሙ፡እግዚእ፡ ኑዛዜ፡ ሠናየ፡ እምሐ
ዘናት፡ እንተ፡ ትትሜጠውዎን፡ በኃይለ፡
መስቀሉ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
ዘሎቱ፡ስብሐት፡ወኃይል፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፶፡፲–፲፩።

፲ መኑ፡ እምኔክሙ፡ ዘይፈርሆ፡ ለእግዚአ
ብሔር፡ ይስማዕ፡ቃለ፡ገብሩ፡እለ፡የሐውሩ፡
ውስተ፡ ጽልመት፡ ወአልቦሙ፡ ብርሃን፡
ተወከሉ፡በስመ፡እግዚአብሔር፡ ወአስምኩ፡
ላዕለ፡ስመ፡እግዚአብሔር።
፲፩ ናሁ፡ኵልክሙ፡ ታነድዱ፡ እሳተ፡ ወአፅበ
ይክሙ፡ ነበልባለ፡ እሳት፡ ሑሩኬ፡ እንከ፡
በብርሃነ፡እሳትክሙ፡ ወበነበልባለ፡ እሳት፡
ዘአንደድክሙ፤ በእንቲአየ፡ ረከበክሙ፡
ዝንቱ፡ወኵልክሙ፡ትሰክቡ፡በሕማምክሙ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፶፩፡፩–፫።

፩ ስምዑኒ፡ኵልክሙ፡እለ፡ትዴግንዋ፡ለጽድቅ፡
ወእለ፡ተኃሥሥዎ፡ለእግዚአብሔር፡ ርእይዋ፡
ለኰኵሕ፡ጽንዕት፡እንተ፡ወቀርክሙ፡ወለአ
ዘቅት፡ዕምቅት፡እንተ፡ከረይክሙ።
፪ ርእይዎ፡ለአብርሃም፡አቡክሙ፡ወለሣራሂ፡
እንተ፡ ሐመት፡ ብክሙ፡ እስመ፡ አሐዱ፡
ውእቱ፡ ወጸዋዕክዎ፡ ወባረክዎ፡ ወአፍቀ
ርክዎ፡ወአብዛኅክዎ።
፫ ወይእዜኒ፡ አስተፌሥሐኪ፡ ለኪ፡ ኢየሩ
ሳሌም፡ወአስተፌሥሕ፡ኵሎ፡አሕቃላተኪ፡
ወእሬስያ፡ለበድውኪ፡ከመ፡ገነት፡ወአሕቃ
ሊሃኒ፡ከመ፡ ገነተ፡ እግዚአብሔር፡ ወይት
ረከብ፡ ውስቴታ፡ ትፍሥሕት፡ ወሐሤት፡
አሚን፡ወቃለ፡ስብሐት።
፬ ስምዑኒ፡ ስምዑኒ፡ ሕዝብየ፡ ወአጽምዑኒ፡
ነገሥት፡ ተግሣፅየ፤ እስመ፡ ሕግ፡ ይወጽእ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ኞቻችሁን፡ ነጋዴዎቻችሁን፡ ወደ፡ እናንተ፡
በሰላም፡በጤና፡ይመልስ።
፴፫ ጌታም፡ ከሐዘን፡ መልካም፡ መጽናናትን፡
በጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ በመስቀሉ፡
ኃይል፡ይስጣችሁ።
ለእርሱ፡ክብር፡ምስጋና፡ኃይል፡ለዘላለሙ፡
ይሁን፡አሜን።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና፡ ነቢዩ፡ ኢሳይያስ፡ የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፶፡፲–፲፩።

፲ ከእናንተ፡ የባርያው፡ የኢሳይያስን፡ ቃል፡
ይሰማ፡ ዘንድ፡ እግዚአብሔርን፡ የሚፈራ፡
ማነው ? በጨለማ፡ የሚሄዱ፡ ናቸው፤
ብርሃንም፡የላቸውም፤እናንተ፡ግን፡በእግዚአ
ብሔር፡ ስም፡አምናችሁ፡ጽኑ።
፲፩ እነሆ፡ ሁላችሁ፡ እሳትን፡ ታነዳላችሁ፤
የእሳትን፡ ነበልባል፡ ታቀጣጥላላችሁ፤ እንግ
ዲህ፡ ሁላችሁም፡ በአነደዳችሁት፡ የእሳት፡
ወላፈንና፡ በአቀጣጠላችሁት፡ እሳት፡ ሂዱዋ !
እኔን፡ ስለካዳችሁ፡ ይህ፡ ሁሉ፡ መከራ፡ አገኛ
ችሁ፤ሁላችሁም፡በመከራ፡ትወድቃላችሁ።

በረከቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑርና፡ነቢዩ፡
ኢሳይያስ፡የተናገረው፡ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፶፩፡፩–፫።

፩ ጽድቅን፡የምትከተሏት፡እግዚአብሔርንም፡
በአምልኮት፡ የምትፈልጉት፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡
ስሙኝ፤ያለዘባችኋትን፡ጽኑ፡አለት፡የቈፈራ
ችኋትንም፡ጥልቅ፡ጉድጓድ፡እዩዋት።
፪ እሱ፡አንድ፡ነበርና፡ጠርቼ፡አከብሬዋለሁና፡
ወድጄዋለሁና፡አብዝቼዋለሁና፡አባታችሁ፡
አብርሃምንም፡እዩት፤አምጣ፡የወለደቻችሁ፡
ሣራንም፡እዩዋት።
፫ ኢየሩሳሌም፡አሁንም፡ደስ፡አሰኝሻለሁ፡አው
ራጆችሽንም፡ ሁሉ፡ ደስ፡ አሰኛለሁ፤ ኢየሩሳ
ሌምንም፡ እግዚአብሔር፡ እንደፈጠራት፡
ገነት፡ አደርጋታለሁ፤ በውስጥዋም፡ ተድላ፡
ደስታ፡ ይገኛል፤ የምስጋና፡ ቃልና፡ ሃይማ
ኖትም፡በእርሷ፡ይገኛል።
፬ ከእኔ፡ ሕግ፡ ይገኛልና፡ ፍርዴም፡ የአሕዛብ፡
ብርሃን፡ ነውና፡ ወገኖቼ፡ ስሙኝ፤ ስሙኝ፤ ነገ

## በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እምነቢየ፡ወፍትሕየኒ፡ብርሃነ፡አሕዛብ።
ትመጽእ፡ጽድቅየ፡ወትበጽሕ፡መድኃኒትየ፡
፭፡ ወይትዌከሉ፡አሕዛብ፡በመዝራዕትየ፤ኪያየ፡
ይሴፈዉ፡አሕዛብ፡ወደሰያትኒ፡ይትዌከሉ፡
በመዝራዕትየ።
፮፡ አንሥኡ፡አዕይንቲክሙ፡ወነጽሩ፡ሰማየ፡
ወምድረኒ፡በታሕቱ፤እስመ፡ሰማይኒ፡ከመ፡
ጢስ፡ጸንተ፡ወምድርኒ፡ከመ፡ልብስ፡ትበሊ፤
ወእለኒ፡ይነብርዋ፡ከመ፡ዘይመውቱ፡ወመድ
ኃኒትየሰ፡ለዓለም፡ይእቲ፡ወጽድቅየኒ፡
ኢተኃልቅ።

፯፡ ስምዑኒ፡እለ፡ተአምሩ፡ፍትሐ፡ሕዝብየ፡እለ፡
ውስተ፡ልብክሙ፡ሕግየ፡ኢትፍርሁ፡
ጽዕለተ፡ሰብእ፡ወትግርምቶሙ፡ወኢትት
መውዑ።
፰፡ እስመ፡ከመ፡ልብስ፡ይበልዩ፡ፍጡነ፡ወኢይ
ጉነድዩ፡ወከመ፡ብልዐ፡ቍንቍኔ፡ይከውኑ፡
ጽድቅየሰ፡ለዓለም፡ትቀውም፤ወመድኃኒ
ትየኒ፡ለትውልደ፡ትውልድ።

ዘዓሞጽ፡ነቢይ፡በረከተ፡እምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፰፡፰-፲፩።
፰፡ ኢትትሀወክኑ፡ምድር፡በዝኒ፡ወይላሕዉ፡
ኵሎሙ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ፡
ወይውኅዝ፡ከመ፡ፈለግ፡ቀትል፡ወይመልዕ፡
ከመ፡ፈለገ፡ግብጽ።

፱፡ ወይከውን፡ይእተ፡አሚረ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፡አምላክ፡የዐርበሙ፡ፀሐይ፡መዐልተ፡
ቀትር፡ወይጸልም፡በዲበ፡ምድር፡በዕለተ፡
ብርሃን።
፲፡ ወእሬስዮን፡ላሐ፡ለበዓላቲክሙ፡ወይከው
ንትክሙ፡ሰቈቃወ፡ኵሉ፡ማሕልይክሙ፤ወአቀ
ወእወዲ፡ለክሙ፡ብርሐተ፡ውስተ፡ሐቌክሙ፡
ኵልክሙ፤ወእሬስየክሙ፡ከመ፡ላሐ፡ፍቁር፤
ወእለሂ፡ምስሌክሙ፡ይከውኑ፡በዕለተ፡
ማሕምም።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ሥታቱም፡ተግሣጼን፡አድምጡኝ።
፭፡ ረድኤቴ፡ትመጣለች፤ድኅነቴም፡ፈጥና፡ትደ
ርሳለች፤አሕዛብ፡በሥልጣኔ፡ያምናሉ፤
አሕዛብም፡እኔን፡ተስፋ፡ያደርጋሉ፤
ደሴቶችም፡በእኔ፡ያምናሉ።
፮፡ ሰማይ፡እንደ፡ጢስ፡ትጠፋለችና፡ምድርም፡
እንደ፡ልብስ፡ታረጃለችና፡በእርሷም፡
የሚኖሩ፡ሰዎች፡እንደ፡ሞቱ፡ሰዎች፡
ናቸውና፡ እንገታችሁን፡አቅንታችሁ፡
ሰማይን፡እዩ፤ከሰማይ፡በታች፡ምድርንም፡
አስተውሉ፤ድኅነቴ፡ግን፡ለዘላለም፡ናት፤
ቸርነቴም፡አትፈጸምም።
፯፡ ሕጌ፡በልባችሁ፡ያለ፡ለወገኖቼ፡መፍረድ፡
የምታውቁ፡ሰዎች፡ስሙኝ፤የሰውን፡ስድብ፡
አትፍሩ፤ግርማቸውንም፡አትፍሩ፤ድልም፡
አትነሡ።
፰፡ እንደ፡አሮጌ፡ልብስ፡ፈጥነው፡ይጠፋሉ፤አይ
ቆዩምና፡ብል፡እንደ፡በላው፡ልብስም፡
ይሆናሉና፡ቸርነቴ፡ግን፡ለዘላለም፡ጸንታ፡
ትኖራለች፤ድኅነቴም፡ለልጅ፡ልጅ፡ነው።

የእምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና፡ነቢዩ፡አሞጽ፡የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፰፡፰-፲፩።
፰፡ አገራችሁ፡በዚህ፡ምክንያት፡አትታወክምን!
በእርስዋም፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡ሁሉ፡ያዝናሉ፤
ያለቅሳሉ፤ያን፡ጊዜም፡ሰልፉ፡እንደ፡ፈሳሽ፡
በዝቶ፡ይፈሳል፤ከዚያም፡ዘንድ፡እንደ፡ግብጽ፡
ወንዝ፡(እንደ፡ዐባይ)፡ይመላል።
፱፡ ፈጣሪ፡እግዚአብሔርም፡ያን፡ጊዜ፡እንዲህ፡
ይሆናል፤በቀትር፡ጊዜ፡ፀሐይ፡ይገባባቸዋል፤
በብርሃኑም፡ቀን፡በዚህ፡ዓለም፡ጨለማ፡ይሆ
ንባቸዋል፡አለ።
፲፡ በዓላችሁን፡ለውጩ፡ልቅሶ፡አደርገዋለሁ፤
ዘፈናችሁም፡ሁሉ፡ተለውጦ፡ልቅሶ፡
ይሆናል፤በወገባችሁም፡ያለቀ፡ጨርቅ፡አስ
ታጥቃችኋለሁ፤በሁላችሁም፡ራስ፡
ቡሀነትን፡አመጣለሁ፤ወዳጅ፡ለወዳጁ፡እንዲ
ያለቅስ፡እናንተንም፡እንድታለቅሱ፡አደርጋ
ችኋለሁ፤ከእናንተም፡ጋራ፡ወዳጅ፡የነበሩት፡
በመከራችሁ፡ቀን፡ጠላት፡ይሆኗችኋል።

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፩ እስመ፡ናሁ፡ይመጽእ፡መዋዕል፡ይቤ፡እግዚ
አብሔር፡ወእፌኑ፡ረኃበ፡ውስተ፡ብሔር፡
ወአኮ፡ረኃበ፡እክል፡ወአኮ፡ጽምአ፡ማይ፡
አላ፡ረኃብሰ፡ዘእምሰሚዐ፡ቃለ፡እግዚአ
ብሔር።

፲፪ ወይትሐመማ፡ማየ፡ባሕር፡ወይረውጹ፡
እምደቡብ፡እስከ፡ጽባሕ፡ይኅሥሡ፡ቃለ፡እግ
ዚአብሔር፡ወኢይረክቡ።

፲፫ ይእተ፡አሚረ፡ይጠፍአ፡ደናግል፡ላሕያት፡
ወይጠፍኡ፡ወራዙት፡ሠናያን፡በጽምእ።
፲፬ እለ፡ይምሕሉ፡በምሥሃለ፡ሰማርያ፡እንዘ፡
ይብሉ፡ሕያው፡አምላክ፡ዳን፡ወሕያው፡
አምላክ፡ቤርሳቤህ፡ወይወድቁ፡ወኢይት
ነሥኡ፡እንከ።

ምዕ፡፱፡፩–፲፭።

፩ ርኢክዎ፡ለእግዚአብሔር፡እንዘ፡ይቀውም፡
ዲበ፡ምሥዋዕ፡ወይቤለኒ፡ዝብጥ፡አዕማደ፡
ጽጌያት፡ወያድለቅልቁ፡ዶዶያት፤እስመ፡
እቀትሎሙ፡በኵናት፡ወይመትርዎሙ፡አር
እስቲሆሙ፡ወአልቦ፡ዘያመሥጥ፡እምኔሆሙ፡
ተርፉ፡ወአልቦ፡ዘይድኅን፡እምኔሆሙ።

፪ እመኒ፡ተወርዉ፡ወወረዱ፡ውስተ፡ቀላይ፡
እምህየኒ፡እደየ፡ታወፅኦሙ፡ወእመኒ፡ዐርጉ፡
ውስተ፡ሰማይ፡እምህየኒ፡አጸድፎሙ።
፫ ወእመኒ፡ተኀብኡ፡ውስተ፡ርእሰ፡
ቀርሜሎስ፡በህየኒ፡አኀሥሦሙ፡ወአወ
ፅኦሙ፡ወእመኒ፡ተሰጥሙ፡ውስተ፡ቀላየ፡
ባሕር፡እምቅድመ፡አዕይንትየ፡በህየኒ፡
እኤዝዞ፡ለከይሲ፤ወይቀለጽዎሙ።

፬ ለእመኒ፡ፄወውዎሙ፡ፀሮሙ፡እምቅድመ፡
ገጽየ፡በህየኒ፡እኤዝዛ፡ለኵናት፡
ትቅትሎሙ፡ወአወትር፡አዕይንትየ፡
ላዕሌሆሙ፡በእኩይ፡ወአኮ፡በሠናይ።
፭ ይቤ፡እግዚአብሔር፡አምላክ፡ዘኵሎ፡
ይመልክ፡ዘይገስሳ፡ለኵላ፡ምድር፡ወያንቀ
ለቅላ፡ወይላሕዉ፡ኵሎሙ፡እለ፡ይነብርዋ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

፲፩፤ እግዚአብሔር፡እነሆ፡እንዲህ፡ያለ፡ወራት፡
ይመጣል፡ብሎአልና፤በሀገር፡ረኃብን፡
አመጣለሁ፤አመጣለሁም፡ያልሁት፡ከእህል፡
መራብ፡ከውኃ፡መጠማት፡አይደለም፤
ረኃብስ፡የእግዚአብሔርን፡ትምህርት፡
ከመስማት፡መከልከል፡የተነሣ፡ነው፡እንጂ።
፲፪፤ የባሕሩ፡ውኃ፡ይደፈርሳል፤(ትምህርቱ፡
ይጠፋል)፡ከምዕራብ፡ጀምረው፡እስከ፡
ምሥራቅ፡ድረስ፡ትምህርትን፡ሊፈልጉ፡
ይሄዳሉ፤ፈልገው፡ግን፡አያገኙም።
፲፫፤ ያን፡ጊዜ፡መልከ፡መልካሞች፡ቈነገሮ
ቶችና፡ጐልማሶች፡ፈጽመው፡ይዝላሉ።
፲፬፤ የቤርሳቤህ፡አምላክ፡ሕያው፡ነው፤የዳንም፡
አምላክ፡ሕያው፡ነው፡እያሉ፡በሰማርያ፡
ጣዖት፡የሚምሉ፡መልከ፡መልካሞች፡ጐል
ማሶችም፡ትምህርት፡አጥተው፡ይጠፋሉ፤
ከጠፉም፡አይገኙም።

ምዕ፡፱፡፩–፲፭።

፩፤ እግዚአብሔርን፡በምሥዋዑ፡ላይ፡ቁሞ፡
አየሁት፤በጦር፡ይወጓቸዋል፤ቸብቸቧቸው
ንም፡ይቆርጧቸዋልና፤አበባ፡ያላቸውን፡ምሰሶ
ዎች፡ምታ፤(በተድላ፡በደስታ፡ያሉ፡ንጉሡ፡
ሊቀ፡ካህናቱ)፡ደጆችም፡ይነዋወጡ፤(ሠራዊቱ፡
ካህናቱ)፡ከሞትም፡ከቀሩ፡ሰዎች፡የሚያመልጥ፡
ከነሱም፡የሚድን፡የለም፡አለኝ።
፪፤ ተወርውረው፡ወደ፡ጥልቅ፡ባሕር፡ቢገቡም፡
ከዚያ፡ሥልጣኔ፡ታወጣቸዋለች፤ወደ፡
ሰማይም፡ቢወጡ፡ከዚያም፡አወርዳቸዋለሁ።
፫፤ ሸሽተው፡በዱር፡ምንም፡ቢሠወሩ፡ከዚያ፡
ፈልጌ፡አወጣቸዋለሁ፤ከዓይኔም፡
ተሰውረው፡ወደ፡ጥልቅ፡ባሕር፡ቢሠጥሙ፡
በዚያ፡ቦታ፡ዘንዶን፡ቀጣቸው፡ብዬ፡አዝዘ
ዋለሁ፤እርሱም፡ይውጣቸዋል።(ናቡከደ
ነጾር)
፬፤ ጠላቶቻቸውም፡ከፊቴ፡ለይተው፡ማርከው፡
ቢወስዷቸው፡በዚያው፡ቦታ፡ትገድላቸው፡
ዘንድ፡ጦርን፡አዝዛታለሁ፤እኔም፡በበጎ፡
ያይደለ፡በክፉ፡ዓይን፡አያቸዋለሁ።
፭፤ ሁሉን፡የሚገዛ፡ምድርንም፡ሁሉ፡በእደ፡
መዐቱ፡የሚዳስሳት፡የሚያነዋውጣትም፡
እግዚአብሔር፡በእሷ፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡ሁሉ፡
መከራ፡መጥቶባቸው፡ያለቅሳሉ፤ሰልፉም፡

Scanned by CamScanner

፳፻፷፩

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወይውኅዝ፡ከመ፡ፈለገ፡ቀትል፡ወይወርድ፡
ከመ፡ፈለገ፡ግብጽ።
፮፡ ዘየሐንጽ፡ውስተ፡ሰማይ፡ጽርሖ፡ወይሣርር፡
ውስተ፡ምድር፡ትእዛዞ፡ዘይጼውዖ፡ለማየ፡
ባሕር፡ወይከዕዎ፡ውስተ፡ገጸ፡ለምድር፡እግ
ዚአብሔር፡ዘኵሎ፡ይመልክ፡ስሙ።

፯፡ አኮኑ፡ከመ፡ደቂቀ፡ኢትዮጵያ፡ አንትሙ፡
በኀቤየ፡አ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፡ ስሙ፡ አኮኑ፡
እስራኤል፡ዘአውፃእክዎ፡እምከላውዴዎን፡
ወእምካራን፡ እምግብጽ፡ ወእምኢሎፍሊ፡
ወእምሶርያሂ።

፰-፱፡ናሁ፡አዕይንቲሁ፡ለእግዚአብሔር፡ ላዕለ፡
መንግሥተ፡ኃጥአን፤ ወእሰዕራ፡ እምገጸ፡
ምድር፡ወባሕቱ፡ለግሙራ፡አኮ፡ዘአጠፍእ፡
ለቤተ፡ እስራኤል፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡
እስመ፡ ናሁ፡ አነ፡ እኤዝዝ፡ እዘርዎሙ፡
ለቤተ፡እስራኤል፤ውስተ፡ኵሉ፡አሕዛብ፡
በከመ፡ ይዘሮ፡ በመስኤ፡ ወድቂቅሂ፡
ኢይወድቅ፡ዲበ፡ምድር።

፲፡ ወይመውቱ፡ በኩናት፡ ኃጥአን፡ ሕዝብየ፡
እለ፡ ይብሉ፡ ኢትበጽሐነ፡ ወኢትረክበነ፡
እኪት።
፲፩፡ ይእተ፡አሚረ፡አሐንጻ፡ለቤተ፡ዳዊት፡እንተ፡
ወድቀት፡ ወአነሥአ፡ ወእነድቅ፡ መዘበራ፡
ከመ፡እመ፡መዋዕለ፡ዓለም።
፲፪፡ ከመ፡ ይኅሥሥዎ፡ እለ፡ ተርፉ፡ ሰብእ፡
ዘኵሎሙ፡ ሕዝብ፡ እለ፡ ዲቤሆሙ፡ ተሰምየ፡
ስምየ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ዘገብረ፡ዘንተ።
፲፫፡ ናሁ፡ መዋዕል፡ ይመጽእ፡ ይቤ፡ እግዚአ
ብሔር፡የኀብር፡ቀሥም፡ምስለ፡ማእረር፡ወይ
ትረከብ፡ዘርዕ፡ምስለ፡ሰዊት፡ወያንጸፈጽፍ፡
መዐር፡ እምአድባር፡ ወያሐመለምል፡
አውግር።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

እንደ፡ፈሳሽ፡በዝቶ፡ይመጣል፤እንደ፡ግብጽ፡
ወንዝም፡በዝቶ፡ይወርዳል፡አለ።

፮፡ ጠፈር፡አዳራሹን፡በውኅነት፡የሚሠራ፡ትዕ
ዛዙንም፡ በዚህ፡ ዓለም፡ የሚያጸና፡ የውቅያ
ኖስን፡ውኃ፡በደመና፡ቋጥሮ፡በነፋስ፡ጭኖ፡
አምጥቶ፡ በዚህ፡ ዓለም፡ የሚያዘንመው፡
ስሙ፡ሁሉን፡የሚገዛ፡እግዚአብሔር፡ነው።

፯፡ የእሥራኤል፡ ልጆች፡ እናንተ፡ በእኔ፡ዘንድ፡
እንደ፡ ኢትዮጵያ፡ ልጆች፡ አይደላችሁምን፤
ስሙ፡ ሁሉን፡ የሚገዛ፡እግዚአብሔር፡ እስራ
ኤል፡ ቀድሞ፡ (እያታችሁ፡ አብርሃምን)፡ ከከላ
ውዴዎን፡ከካራን፡(አባታችሁ፡ያዕቆብን)፡ከሶ
ርያ፤እናንተን፡ከግብጽ፤(ንጉሣችሁ፡ዳዊትን)፡
ከኢሎፍሊ፤ያወጣሁ፡አይደለሁምን፡አለ።

፰-፱፤እነሆ፡ የእግዚአብሔር፡ ዐይኑ፡ መዐቱ፡
በኃጥአን፡ መንግሥት፡ ላይ፡ ነው፤ ከዚህ፡
ዓለምም፡ አጠፋታለሁ፤ ነገር፡ ግን፡እግዚአ
ብሔር፡የእስራኤልን፡ወገኖች፡አስማርካቸው፡
ዘንድ፡እነሆ፡አገዛለሁና፤ምንም፡ባዝባቸው፡
የእስራኤልን፡ወገኖች፡ፈጽሜ፡የማጠፋቸው፡
አይደለሁም፡አለ፤እህልም፡በመንሽ፡እንደሚ
መነሽ፡የእስራኤልን፡ቤት፡በአሕዛብ፡ሁሉ፡
መካከል፡እበትናቸዋለሁ፤ነገር፡ግን፡አንዲት፡
ቅንጣት፡በምድር፡ላይ፡አትወድቅም።

፲፡ መከራ፡ አትደርስብንም፤ አታገኘንም፡
የሚሉ፡ ክፋዎች፡ ወገኖቼ፡ እስራኤል፡ ግን፡
በአሕዛብ፡አገር፡በጦር፡ይሞታሉ።
፲፩፡ ከዚህ፡ ቀድሞ፡ የወደቀች፡ የዳዊትን፡ቤት፡
ያን፡ ጊዜ፡ እሠራታለሁ፤ ስሠራትም፡እንደ፡
ቀድሞ፡ዘመን፡ፍራሿን፡አቀናዋለሁ።
፲፪፡ ይህን፡ ሁሉ፡ ያደረገ፡እግዚአብሔር፡ ስሜ፡
በነሱ፡ የተጠራባቸው፡ ወገኖቼ፡ ሁሉና፡
ከሞትም፡የቀሩ፡ሰዎች፡ሁሉ፡በሕግ፡በአም
ልኮት፡ይፈልጉኝ፡ዘንድ፡ነው፡አለ።
፲፫፡ እነሆ፡እንዲህ፡ያለ፡ወራት፡ይመጣል፤እግዚ
አብሔር፡ የዘይቱ፡ የወይኑ፡ መከር፡
ከሥንዴው፡ ከገብሱ፡ መከር፡ ጋር፡ አንድ፡
ይሆናል፤ዘሩም፡ከእሸቱ፡ጋር፡ይገናኛል፤ከተ
ራራውም፡ማር፡ይፈሳል፤ኮረብታውም፡ይለ
መልማል፡አለ።

Scanned by CamScanner

## በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፬ ወእመይጥ ፡ ፄዋ ፡ ሕዝብየ ፡ እስራኤል ፡
ወየሐንጹ ፡ አህጉረ ፡ ዘማሰና ፡ ወይነብሩ ፡
ይተክሉ ፡ ወይነ ፡ ወይሰትዩ ፡ ወይኖሙ ፡
ወይተክሉ፡አዕጸዳተ፡አቅማሕ፡ወይበልዑ፡
ፍሬሁ።

፲፭ ወእልቦ፡ዘያወፅኦሙ፡እንከ፡እምድሮሙ፡
እንተ፡ወሀብክዎሙ ፡ አነ ፡ ይቤ ፡ እግዚአ
ብሔር፡አምላክ፡ዘኵሎ፡ይመልክ።

ዘሕዝቅኤል ፡ ነቢይ ፡ በረከተ ፡ አምላኩ ፡
ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፴፯፡፲፭–፳፫።

፲፭ ወነበበኒ፡እግዚአብሔር፡ወይቤለኒ።
፲፮ ወልደ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ንሣእ፡ለከ፡በትረ፡
ወጸሐፍ ፡ ላዕሌሁ ፡ ይሁዳሃ ፡ ወደቂቀ ፡
እስራኤል፡ለእለ፡ይትቃወምዎ፡ወየኀብርዎ፡
ወንሣእ፡ለከ፡ካልእተ፡በትረ፡ወትጽሕፍ፡
ለዮሴፍ ፡ በበትረ ፡ ኤፍሬም ፡ ወኵሎሙ ፡
ደቂቀ፡እስራኤል፡እለ፡ተወሰኩ፡እምኀቤሁ።
፲፯ ወትደምሮን፡ለክልኤሆን፡ወተአስሮን፡ወት
ሬስዮን፡አሐተ፡በትረ፡ወየሀልዋ፡ውስተ፡
እዴከ።
፲፰ ወሶበ፡ይብሉከ፡ደቂቀ፡ሕዝብከ፡ኢትነግ
ረነኑ፡ምንት፡ከመዝ፡አተከዘከ፡በሎሙ፡
ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡እግዚእ።
፲፱ ናሁ፡አነ፡አነሥእ፡በትረ፡ዮሴፍ፡ዘውስተ፡
እደ፡ኤፍሬም፡ወሕገበ፡እስራኤል፡ዘኀቤሁ፡
እሁቦሙ፡ውስተ፡ሕዝበ፡ይሁዳ፡ወይከውኑ፡
አሐደ፡በትረ፡ውስተ፡እደ፡ይሁዳ።

፳ ወይከውና፡ውእቶን፡አብትር፡እለ፡ጸሐፍከ፡
በቅድሜሆሙ።
፳፩ ወትብሎሙ፡ከመ፡ዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡
እግዚእ፡ናሁ፡አነ፡እነሥእሙ፡ለኵሎሙ፡
ቤተ፡እስራኤል፡እማእከለ፡አሕዛብ፡እለ፡
ሖሩ፡ህየ፡ወአስተጋብእሙ፡እምኵሎሙ፡
አለ፡ዐውዶሙ፡ወእወስዶሙ፡ውስተ፡
ምድረ፡እስራኤል።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፲፬፤ እኔም፡የወገኖቼ፡የእሥራኤልን፡ምርኮ፡እመ
ልሳለሁ፤እነርሱም፡ብዙ፡ዘመን፡የፈረሱ፡አገ
ሮቻቸውን፡ያቀናሉ፤በእነዚያም፡ይኖራሉ፤
ወይኑን፡ይተክላሉ፤ወይኑም፡ደርሶላቸው፡
ይጠጣሉ፤ ሌላ ፡ አትክልት ፡ ይተክላሉ ፡
ፍሬውም፡ደርሶላቸው፡ይበላሉ።
፲፭፤ ስሙ፡ሁሉን፡የሚገዛ፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔር፡
እኔ፡ከሰጠኋቸው፡አገር፡እንግዲህ፡ወዲህ፡
ማርኮ፡የሚያወጣቸው፡የለም፡አለ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና ፡ ነቢዩ ፡ ሕዝቅኤል ፡ የተናገረው ፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፤፴፯፡፲፭–፳፫።

፲፭፤ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሎ፡ነገረኝ።
፲፮፤ አንተ፡የሰው፡ልጅ፡ለአንተ፡በትርን፡አንሣ፤
በሱም ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ የሚከራከሩት ፡
የአሥሩን፡ነገድ፡ልጆችና፡ሁለቱን፡ነገድ፡ጻፍ፤
አንተ፡ሌላ፡በትርን፡አምጥተህ፡በዮሴፍ፡ፈንታ፡
ነገደ፡ኤፍሬምን፡ጻፍ፤በሱ፡ዘንድ፡የተጨመሩ፡
የእስራኤልንም፡ልጆች፡ሁሉ፡ጻፍ።
፲፯፤ ሁለቱን፡አንድ፡አድርገህ፡አሥረህ፡አንዲት፡
በትርን፡አድርጋቸው፤በእጅህም፡ተይዘው፡
ይኑሩ።
፲፰፤ የወገኖችህም ፡ ልጆች ፡ አትነግረንምን?
እንዲህ፡ምን፡አሳዘነህ፡ባሉህ፡ጊዜ፡ጌታ፡እግ
ዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፡በላቸው።
፲፱፤ በኤፍሬም፡ዕጣ፡ያሉ፡የዮሴፍ፡ወገኖችን፡
እኔ፡እወስዳለሁ፤በሱ፡ዘንድ፡ያሉ፡የእስራኤ
ልንም ፡ ወገኖች ፡ ለይሁዳ ፡ ወገኖች ፡
እሰጣለሁ፤ በይሁዳም፡እጅ፡አንድ፡በትር፡
ይሆናሉ።
፳፤ የጻፍካቸው፡እነዚያም፡በትሮች፡በፊታቸው፡
ይሆናሉ።
፳፩፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤
ተማርከው፡ከሄዱበት፡ከገቡበትም፡ከዚያ፡
ከአሕዛብ፡አገር፡መካከል፡የእስራኤልን፡
ወገኖች፡ሁሉ፡እነሆ፡እኔ፡አመጣቸዋለሁ፤
በዙሪያቸው፡ካሉ፡ከአሕዛብም፡ሁሉ፡አገር፡
ሰብስቤ፡ወደ፡እስራኤል፡አገር፡እወስዳቸ
ዋለሁ፡በላቸው።

Scanned by CamScanner

በ፲፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፱፡ ወእሬስዮሙ ፡ አሐደ ፡ ሕዝበ ፡ በምድርየ ፡ ወበደወለ ፡ እስራኤል ፡ ወአሐደ ፡ ይከውን ፡ መልአኮሙ ፡ ወይነግሥ ፡ ወኢይትናፈቁ ፡ እንከ፡ለክልኤ፡ሕዝብ።

፴፡ ወኢይነግሡ ፡ ለሙ ፡ ክልኤቱ ፡ ነገሥት ፡ ከመ፡ኢይርኵሱ፡በጣዖቶሙ።

## ክፍል፡፪።

### ጸሎት፡ዘስምዖን፡ዐምዳዊ።

፩፡ **እ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡** ዘኮንከ፡ ዕሩቀ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ አዕርቀኒ ፡ እመንፈስ፡ሰይጣን፡ዘጽልመት፡ወመንፈሰ፡ ስሕተት።

፪፡ ወአልብሰኒ ፡ ሜላተ ፡ ሕይወት ፡ በኃይልከ ፡ እትሐደስ፡ወበጥበብከ፡እትመገብ።

፫፡ **እ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡** ዘትትከ ድኖሙ፡ለመላእክት፡ስርጋዌ፡ብርሃን፡ወታ ቀንቶሙ፡ኀይለ፡ቆምከ፡ዕሩቀከ፡ዲበ፡ዕፀ፡ መስቀል።

፬፡ አዕርቅ ፡ ኅሊናየ ፡ እምጸናፌ ፡ ጽልመት ፡ ወጣቃ ፡ ወአሥርቅ ፡ ውስተ ፡ ልብየ ፡ ወኅሊናየ፡ሥነ፡ስብሐቲከ፡ከመ፡ይትወለጡ፡ እምጠባይዓት ፡ ምድራውያት ፡ ኀበ ፡ ጠባይዓት ፡ ሰማያውያት ፡ ወይሰብሕሑከ ፡ ምስለ፡መላእክት።

፭፡ **እ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡** ዘሰፋሕከ፡ እደዊከ፡ቅዱሳተ፡ላዕለ፡ዕፀ፡መስቀል፡ረስዮ፡ ለአእምሮትየ ፡ ይሰፋሕ ፡ ወይኅድር ፡ ውስቴቱ፡አፍቅሮትከ።

፮፡ **እ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡** ዘፈጠ ርኮሙ ፡ ለመላእክት ፡ እምነደ ፡ እሳት ፡ ወረበብኮ ፡ ለሰማይ ፡ ከመ ፡ ኀይመት ፡ ወአብ ዛኅከ፡ራሕባ፡ለምድር።

፯፡ ወአልዓልከ፡ዓለማተ፡መልዕልቴሃ፡ሉዓሌ፡ ዐቢይ፡ወታሕቴሃ፡ዐቢይ፡ዕመቅ፡ወአሰርካ፡ በባሕር ፡ ዘየዓውዳ ፡ ወትእዛዝከ ፡ ይጸውራ ፡ ለምድር፡ወለዙሉ፡ዘውስቴታ።

፰፡ እፎ፡ሰፋሕከ፡እደዊከ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ ወተቀኖከ፡በቅንዋት፡ኀበ፡አይሁድ፡ወረድከ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፳፱፡ በእስራኤል ፡ አውራጃና ፡ በአገሬ ፡ አንድ ፡ ወገንን ፡ አደርጋቸዋለሁ ፤ አሊቃቸውም ፡ አንድ፡ይሆናል፡ንጉሥም፡ይነግሥላቸዋል፡ ከዚህም፡በኋላ፤ከሁለት፡አይከፈሉም።

፴፡ በጉስቍልናቸውና ፡ በጣዖታቸው ፡ በኃጢአ ታቸውም ፡ ሁሉ እንዳይረክሱ ፡ ሁለት ፡ ነገሥታት፡አይነግሡላቸውም።

## ክፍል፡፪።

### የስምዖን፡ዐምዳዊ፡ጸሎት።

፩፡ **ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡** በዕንጨት፡ መስቀል፡ላይ፡ራቁትህን፡የሆንክ፤ጨለማን፡ ከለበሰና፡ስሕተትን፡ከሚያመጣ፡ሰይጣን፡ መንፈስ፡ለየኝ።

፪፡ በኃይልህ ፡ እታደስ ፡ ዘንድ ፡ በጥበብህም ፡ እመገብ፡ዘንድ፡የሕይወት፡ሐር፡ልብስን፡ አልብሰኝ።

፫፡ **ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡** መላእክትን፡ የብርሃን፡መጐናጸፊያ፡የምታጐናጽፋቸው፡ ኃይልንም፡የምታስታጥቃቸው፡በመስቀል፡ ላይ፡ራቁትህን፡ቆምክ።

፬፡ ልቡናዬን ፡ ከፍጹም ፡ ድንቁርና ፡ ጨለማ፡ አርቅ፤(አንፃ)፤በልቤና፡በሕዋሳቴ፡ውስጥም፡ የጌትነትህን ፡ ብርሃን ፡ አብራ ፤ ከምድራዊ፡ ሀሳብና፡ጠባይ፡ተለውጠው፡ከሰማያውያን፡ መላእክት፡ጋራ፡ያመሰግኑህ፡ዘንድ።

፭፡ **ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡** የከበሩ፡ እጆችህን ፡ በዕንጨት ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ የዘረጋህ ፡ ፍቅርህ ፡ በውስጡ ፡ ያድርበት ፡ ዘንድ፡ልቡናዬን፡እንዲከፈት፡አድርገው።

፮፡ **ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡** መላእክትን፡ ከእሳት ፡ የፈጠርካቸው ፡ ሰማይንም ፡ እንደ ፡ ድንኳን ፡ የዘረጋህ ፡ የምድርንም ፡ ስፋቷን ፡ ያበዛህ።

፯፡ በበላይዋም፡ዓለማተ፡ሰማይን፡እጅግ፡ከፍ፡አድ ርገህ፡የፈጠርክ፡ከበታችዋም፡እጅግ፡ጥልቅ፡ያደ ረግህ ፡ ዙሪያዋንም ፡ በባህር ፡ የከበብክ ፡ ትእዛ ዝህም ፡ ምድርን ፡ በባሕር ፡ ላይ፡ጸንታ ፡ እንድ ትኖር፡ያደረጋት፤በውስጥዋ፡ያለውንም፡ሁሉ።

፰፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እጅህን ፡ ዘረጋህ! እንዴትስ ፡ በቀኖት ፡ ተቸነከርክ? ወዴትስ ፡

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እስከ፡አፍቀርከ፡አሕይዎቶ፡ለአዳም፡እስከ፡
በጸሕከ፡ለሞት።
መኑ፡ዘይክል፡እምእለ፡ቦሙ፡አፍ፡ወልሳን፡
ከመ፡የሀብ፡አኰቴተ፡ለስብሐቲከ።
፱ ኦ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ልካእ፡
፲ ውስተ፡ልብየ፡አፍቅሮተከ፡ወአድኅንኒ፡
እማእሰር፡እኩይ፡ወእስረኒ፡በፍቅርከ፡
ዘይሄሉ፡ለዓለም።
፲፩ ኦ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሀበኒ፡
አሕቅፍ፡መስቀለ፡ማሕየዌ፡ወእጼኑ፡
እምኔሁ፡መዐዛ፡መድኀኒት፡ወሕይወት።
፲፪ ወይረድ፡ደምከ፡ንጹሕ፡ላዕለ፡ኅሊናየ፡
ወይቀድሶ፡ከመ፡ይኩን፡ምሥዋዐ፡ቅዱሰ፡
ወያንሳሕስሕ፡ውስቴቱ፡መንፈሰ፡ሕይወት፡
ወይስተይ፡ኅሊናየ፡ኪያከ፡መንፈሰ፡
ሕይወት።
፲፫ ኦ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘሰተይከ፡
ብሒአ፡ወሐሞተ፡በላዕለ፡መስቀል፡
አስትየኒ፡እምፍቅርከ፡ዐቢይ፡ወንጹሕ፡ወአ
ድኅነኒ፡እምረረ፡ሞት።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡
አሐዱ፡አምላክ፡ድርሳን፡ዘብፁዕ፡ወቅዱስ፡
ዲዮናስዮስ፡በረከቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

፩ ወሀሎ፡አሐዱ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘስሙ፡ዲዮና
ስዮስ፡ዘኮነ፡ሰማዕተ፡በሀገረ፡አቴና።

፪ ዝንቱ፡ቅዱስ፡ተለዓለ፡ላዕለ፡ብዙኃን፡
በምክሩ፡ወበጥበቡ፡ወበልቡናሁ፡ወበአእ
ምሮቱ፡እስመ፡ውእቱ፡አሐዱ፡እምነ፡መማክ
ርቲሁ፡ለንጉሥ፡ወእምውስተ፡ማኅበሮሙ፡
ለመሳፍንት፡ማእምራን።
፫ ወእምዝ፡መሀሮ፡ጳውሎስ፡ወአጥመቆ፡
ጥምቀተ፡ክርስትና፡ወሤሞ፡ኤጲስቆጶሰ፡
ላዕለ፡ሀገረ፡አቴና።
፬ ወደረሰ፡ድርሳናተ፡ብዙኃተ፡ወእምኔሆሙ፡
አሐዱ፡ድርሳን፡ዘዕለተ፡ዐርብ፡ዕለተ፡
ስቅለቱ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
መድኃኔ፡ዓለም፡ሎቱ፡ስብሐት።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ወረድክ? ለሞት፡እስክትደርስ፡ድረስ፡
የአዳምን፡ማዳን፡እንደምን፡ወደድክ።
፱፤ አፍና፡አንደበት፡ካላቸው፡ለጌትነትህ፡
ምስጋና፡ማቅረብ፡የሚችል፡ማን፡ነው።
፲፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፤ፍቅርህን፡
በልቤ፡ውስጥ፡ቅረጽ፤ከክፉ፡ማሰሪያ፡
ፍታኝ፤ለዘላለም፡ጸንቶ፡በሚኖር፡ፍቅርህም፡
እሰረኝ።
፲፩፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፤ማሕየዊ፡
መስቀልህን፡አቅፌ፡ከእርሱ፡የሕይወትና፡
የመድኃኒት፡መዐዛ፡አሸት፡ዘንድ፡ስጠኝ።
፲፪፤ በልቡናዬም፡ውስጥ፡ንጹሕ፡ደምህ፡
ይውረድ፤ንጹሕ፡መሠዊያ፡ይሆን፡ዘንድ፡
ልቡናዬን፡ያክብረው፤በውስጡም፡የሕይ
ወትን፡መንፈስ፡ያንቀሳቅስ፤የሕይወት፡
መንፈስ፡አንተን፡ይቀበል።
፲፫፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፤በመስቀል፡
ላይ፡መጻጻንና፡ሐሞትን፡የጠጣህ፤ከታላቁ፡
ንጹሕ፡ፍቅርህ፡አጠጣኝ፤ከመራራው፡ሞተ፡
ነፍስም፡አድነኝ።

አንድ፡አምላክ፡በሆነ፡በአብ፡በወልድ፡
በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡አምነን፡በረከቱ፡
ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑርና፡ንዑሕ፡
ቅዱስ፡የሆነ፡ዲዮናስዮስ፡የደረሰው፡ይህ፡
ነው፤አሜን።

፩፤ በአቴና፡ከተማ፡በሰማዕትነት፡የሞተ፡ስሙ፡
ዲዮናስዮስ፡የሚባል፡አንድ፡ኤጲስቆጶስ፡
ነበረ።
፪፤ ይህም፡ቅዱስ፡በምክሩ፡በጥበቡ፡በፍልስ
ፍናው፡በዕውቀቱ፡በብዙዎች፡ዐዋቂዎች፡
ዘንድ፡ከፍ፡ከፍ፡አለ፤እርሱም፡ከንጉሥ፡አማ
ካሪዎችና፡አዋቂዎች፡ከሆኑ፡መሳፍንት፡
ማኅበር፡ውስጥ፡አንዱ፡ነበርና።
፫፤ ከዚህ፡በኋላ፡ቅዱስ፡ጳውሎስ፡አስተምሮ፤የክ
ርስትና፡ጥምቀትን፡አጠመቀው፤በአቴና፡
ከተማ፡ላይም፡ኤጲስቆጶስነት፡ሾመው።
፬፤ ብዙ፡ድርሳናትንም፡ደርሶአል፤ከድርሳ
ናቱም፡አንዱ፡ክብር፡ምስጋና፡ይግባውና፡
የዓለም፡መድኃኒት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡የተሰቀለባት፡የዕለተ፡ዐርብ፡
ድርሳን፡ነው።

| በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት። |
| --- | --- |
| ፭፡ ወዝንቱ፡ቅዱስ፡እንዘ፡ይነብር፡በአሐዱ፡ ዕለት፡ኀበ፡ይትጋብኡ፡መምህራን፡ውስተ፡ ቤተ፡ጥበብ፡ወእንዘ፡ይነብር፡ምስሌሆሙ፡ ዲበ፡ መንበር፡ ልዑል፡ እስመ፡ ርእሰ፡ ኵሎሙ፡ጠቢባን፡ውእቱ። | ፭፡ ይህ፡ ቅዱስ፡ አንድ፡ ቀን፡ የፍልስፍና፡ ጥበብ፡በሚመረምሩበትና፡ፈላስፎች፡በተሰ በሰቡበት፡ቤት፤የፈላስፎች፡ሁሉ፡አለቃ፡ ነበርና፡ በከፍተኛ፡ ወንበር፡ አብሮአቸው፡ ተቀምጦ፡ሳለ። |
| ፮፡ ወበጊዜ፡ቀትር፡ጸልመ፡ፀሐይ፡ወአድለቅ ለቀት፡ምድር፡ወደንገፁ፡ኵሎሙ፡አሕዛብ፡ ወፈርሁ፡ ወሰአልዎ፡ ለዲዮናስዮስ፡ ወይቤልዎ፡አጠይቀነ፡ዘኮነ፡ውስተ፡ዓለም። | ፮፡ ቀትር፡በሆነ፡ጊዜ፡ፀሐይ፡ጨለመ፤ምድርም፡ ተናወጠች፤ አሕዛብም፡ ሁሉ፡ ደነገጡ፤ ፈሩም፡ ዲዮናስዮስንም፡ በዓለም፡ ውስጥ፡ የሆነውን፡አስረዳን፡ብለው፡ለመኑት። |
| ፯፡ ወነሥአ፡ መጽሐፈ፡ ጥበብ፡ ወርእየ፡ መዓርገ፡በኅሊናሁ፡ወሖረ፡በጥበብ፡ውስተ፡ ፀአተ፡ ፀሐይ፡ ወወርኅ፡ ወከዋክብት፡ ወረከቦሙ፡ኀዱአነ፡ወኢተመይጡ፡እምሕ ዋሮሙ። | ፯፡ የጥበብን፡መጽሐፍ፡ይዞ፡በኅሳቡ፡መዐርገ፡ ፍጥረትን፡ አየ፤ ወደ፡ ፀሐይና፡ ጨረቃ፡ መውጫ፡ በጥበቡ፡ ሄዶ፡ መረመረ፤ ፀጥ፡ ብለው፡ አገኛቸው፤ ከመንገዳቸውም፡ አልተ መለሱም። |
| ፰፡ ወሖረ፡ ውስተ፡ ባሕር፡ ወረከቦ፡ በአርምሞ። ወእምዝ፡ ነሥአ፡ አር ስጣላበ፡ ዘከርታስ፡ ወረከበ፡ በው ስቴቱ፡ ዘይብል፡ ናሁ፡ እምላክ፡ እልመክኑን፡ ዝ፡ ብሂል፡ ፈጣሬ፡ ሰማያት፡ ወምድር፡ ወተንሥአ፡ ላዕሌሁ፡ እሊአሁ፡ ወሰቀልዎ፤ ወሠጠጠ፡ አልባሲሁ፡ ወአኀዘ፡ ዐቢይ፡ሐዘን። | ፰፡ ወደ፡ባሕርም፡ሂዶ፡መረመረ፤ባሕሩንም፡ፀጥ፡ ብሎ፡አገኘው፤ከዚህ፡በኋላ፡የራቀውን፡አቅርቦ፡ የረቀቀውን፡ አጉልቶ፡ የሚያሳየውን፡ የፍል ስፍና፡ መሣሪያ፡ ይዞ፡ አንስቶ፡ መረመረ፤ በውስጡም፡ እነሆ፡ ሥውር፡ እምላክ፡ የሚል፡ አገኘ፤ይህም፡ሰማይና፡ምድርን፡የፈጠረ፡የማይ መረመር፡ አምላክ፡ ወገኖቹ፡ በእርሱ፡ ላይ፡ ተነሥተው፤እንደ፡ሰቀሉት፡አይቶ፡ልብሱንም፡ ቀደደ፤ታላቅ፡ሐዘንም፡አዘነ። |
| ፱፡ ወሰአልዎ፡ መሳፍንት፡ ወመኳንንት፡ ወጠቢባን፡ከመ፡ይከሥት፡ሎሙ፡ዘአስተ ርአዮ፡ሎቱ፡በእንተ፡ዘኮነ፡ጽልመት፡ጊዜ፡ አድለቅለቀት፡ምድር፡ወነገሮሙ፡ኵሎ፡ ዘኮነ። | ፱፡ ምድር፡በተናወጠች፡ጊዜ፡ጨለማ፡ስለሆነ፡ ለእርሱ፡የተገለጠለትን፡ይገልጥላቸው፡ዘንድ፡ መኳንንቱ፡ መሳፍንቱ፡ ፈላስፎቹ፡ ለመኑት፤ እርሱም፡የሆነውን፡ሁሉ፡ነገራቸው። |
| ፲፡ ወሶበ፡ሰምዑ፡ዘንተ፡ፈርሁ፡ዐቢየ፡ፍርሀተ፡ ወእምዝ፡አዘዘ፡ለረድኡ፡ኡሲሞስ፡ከመ፡ ይጽሐፍ፡ኵሎ፡ዘኮነ፡ወስማ፡ለይእቲ፡ዕለት፡ ወስሞ፡ለውእቱ፡ወርኅ፡ወስማ፡ለይእቲ፡ ዓመት። | ፲፡ ይኸንንም፡በሰሙ፡ጊዜ፡ታላቅ፡ፍርሀትን፡ ፈሩ፡ከዚህ፡በኋላ፡ኡሲሞስ፡የተባለ፡ደቀ፡ መዝሙሩን፡የሆነውን፡ሁሉ፡የዕለቲቱን፡ ስም፡የወሩንም፡ስም፡የዚያችንም፡ዓመት፡ ስም፡ይጽፍ፡ዘንድ፡አዘዘው። |
| ፲፩፡ ወዘመኑ፡ዘኮነ፡ከመዝ፡እም፡ዓመተ፡ዓለም፡ በኃምሳ፡ምዕት፡ወኃምስቱ፡ምዕት፡ሠላሳ፡ ወአርባዕቱ፡ ዓመት፡ ወዘመኑሂ፡ ዘመነ፡ ማርቆስ፡ወወርኁሂ፡አዳር፡ዘውእቱ፡ወርኃ፡ መጋቢት፡ወዕለቱሂ፡ዕለተ፡ዓርብ፡ዘውእቱ፡ | ፲፩፡ ዘመኑም፡ ከዓመተ፡ ዓለም፡ መነሻ፡ አምስት፡ ሺህ፡ አምስት፡ መቶ፡ ሠላሳ፡ አራት፡ ዓመት፡ ነበር፤ ዘመኑም፡ ዘመነ፡ማርቆስ፡ወሩም፡አዳር፡ይኸውም፡ መጋቢት፡ ነው፤ ዕለቱ፡ ዓርብ፡ |

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

አመ፡ዕሥራ፡ወሰብዑ፡ወሰዓቱሂ፡ጊዜ፡
ሰድስቱ፡ሰዓት።
፲፱ ወጸሐፈ፡ኵሎ፡በከመ፡አዘዞ፡ዲዮናስዮስ፡
መምህሩ፡ወከዕበ፡ጸሐፈ፡ኀበ፡አንቀጸ፡
ጣዖቶሙ፡እንዘ፡ይብል፡እልመክኑን፡ዝ፡
ብሂል፡ኀቡእ፡ወረደ፡እምሰማይ።
፳ ወእምዝ፡እምድኅረ፡ዐሠርቱ፡ወአ
ርባዕቱ፡ዓመት፡መጽአ፡ጳውሎስ፡
ሐዋርያ፡ኀበ፡ሀገረ፡አቴና፡ወሰበከ፡
በስሙ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክር
ስቶስ፡መድኅኔ፡ዓለም፡ዘከመ፡
ወረደ፡እምሰማይ፡ወተሰብአ፡እም
እግዝእትነ፡ማርያም፡ወበእንተ፡
ሕማሙ፡ወስቅለቱ፡ወሞቱ፡ወት
ንሣኤሁ፡ወዕርገቱ፡ወበእንተ፡ዳግም፡
ምጽአቱ፡ከመ፡ይኰንን፡ሕያዋነ፡
ወሙታነ።
፳፩ ወሶበ፡ሰምዑ፡ሰብአ፡አቴና፡ስብ
ከቶ፡ለጳውሎስ፡ሐዋርያ፡አንከሩ፡
ፈድፋደ፡ወሮጹ፡ኀበ፡ዲዮናስዮስ፡
ወይቤሉ፡ብእሲ፡መጽአ፡ዮም፡ወሰበከ፡
ለነ፡በአምላክ፡ሐዲስ፡ዘኢነአምር፡ንሕነ፡
ወኢአበዊነ፡ወጸውዖ፡ዲዮናስዮስ፡ለጳው
ሎስ፡ወይቤሎ፡ምንት፡ውእቱ፡ዝ፡አምላክ፡
ሐዲስ፡ዘትሰብክ፡ውስተ፡ሀገርነ።
፳፪ ወይቤ፡ጳውሎስ፡እንዘ፡አኀልፍ፡ረከብኩ፡
ጽሑፈ፡ውስተ፡አብያተ፡ጣዖትክሙ፡
ዘይብል፡እልመክኑን፡ዝ፡ውእቱ፡ብሂል፡
ኀቡእ፡አምላክ፡ወረደ፡እምሰማይ።
፳፫ ዝንቱ፡ውእቱ፡ዘእሰብክ፡ለክሙ፡
ቦቱ፤ወሶቤሃ፡አዘዞ፡ዲዮናስዮስ፡ለረ
ድኡ፡ከመ፡ያምጽእ፡ለውእቱ፡መጽ
ሐፍ፡ዘአጽሐፎ፡መጠነ፡ዐሠርቱ፡ወአር
ባዕቱ፡ዓመት።
፳፬ ወአምጽአ፡ሎቱ፡ወአርአዮ፡ወርእዮ፡
አንከረ።
፳፭ ወሐተቶ፡ዲዮናስዮስ፡ኵሎ፡ትእምርተ፡
ዘኮነ፡ጊዜ፡ስቅለቱ፡ለመድኅን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ይኸውም፡ሃያ፡ሰባት፡ቀን፡ሰዓቱም፡
ስድስት፡ሰዓት፡ነው።
፲፱ መምህሩ፡ዲዮናስዮስ፡ያዘዘውን፡ሁሉ፡ጻፈ፤
ዳግመኛም፡በጣዖታቸው፡በር፡ላይ፡እልመ
ክኑን፡ብሎ፡ጻፈ፤ይህም፡ሥውር፡አምላክ፡
ከሰማይ፡ወረደ፡ማለት፡ነው።
፳ እንግዲህ፡ከአሥራ፡ዐራት፡ዓመት፡በኋላ፡
ሐዋርያው፡ጳውሎስ፡ወደ፡አቴና፡ከተማ፡
መጥቶ፡በጌታችን፡በዓለም፡መድኃኒት፡
በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስም፡ሰበከ፤እርሱም፡
ከሰማይ፡እንደ፡ወረደ፡ከእመቤታችን፡
ከድንግል፡ማርያም፡ከሥጋዋ፡ሥጋ፡
ከነፍስዋ፡ነፍስ፡ነሥቶ፡ሰው፡እንደሆነ፡ስለ፡
ሕማሙና፡ስለ፡ስቅለቱ፡ስለ፡ሞቱ፡ስለ፡ትን
ሣኤውና፡ስለ፡ዕርገቱ፡ሕያዋንንና፡ሙታንን፡
ይገዛ፡ዘንድ፡ዳግመኛ፡ስለ፡መምጣቱ፡
አስተማረ።
፳፩ የአቴና፡ሰዎችም፡የሐዋርያ፡ጳውሎስን፡
ትምህርት፡በሰሙ፡ጊዜ፡እጅግ፡አደነቁ፤ወደ፡
ዲዮናስዮስም፡ፈጥነው፡ሄደው፡እኛ፡በማና
ውቀው፡አባቶቻችንም፡በማያውቁት፡
በአዲስ፡አምላክ፡ስም፡የሚሰብክልን፡ሰው፡
ዛሬ፡መጣ፡አሉት፤ዲዮናስዮስም፡ጳውሎስን፡
ጠርቶ፡በሀገራችን፡ውስጥ፡የምትሰብከው፡
ይህ፡አዲስ፡አምላክ፡ምንድነው፡አለው።
፳፪ ጳውሎስም፡በጣዖቶቻችሁ፡ቤቶች፡ላይ፡እል
መክኑን፡የሚል፡ጽሑፍ፡አልፌ፡ስሄድ፡
አገኘሁ፤ይህም፡የተሠወረ፡የማይመረመር፡
አምላክ፡ከሰማይ፡ወረደ፡ማለት፡ነው።
፳፫ ለእናንተ፡የምሰብክላችሁ፡ይህ፡ነው፡አለው፤
በዚያን፡ጊዜም፡ዲዮናስዮስ፡አሥራ፡ዐራት፡
ዓመት፡ያህል፡የሆነውን፡ያጻፈውን፡
መጽሐፍ፡ያመጣው፡ዘንድ፡ደቀ፡
መዝሙሩን፡አዘዘው።
፳፬ አመጣለት፤ለጳውሎስም፡አሳየው፤አይቶም፡
አደነቀ።
፳፭ ዲዮናስዮስም፡በመድኅን፡ጌታ፡ስቅለት፡
ጊዜ፡የሆነውን፡ምልክቱን፡ሁሉ፡
መረመረው።

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፱፤ ወይቤሎ፡ጳውሎስ፡ዘመኑሂ፡ዘመነ፡ማርቆስ፡
ዕለቱኒ፡ዕለተ፡ዓርብ፡ውእቱ፡ወወርኁኒ፡
ወርኀ፡መጋቢት፡እመ፡ዕሥራ፡ወሰብዑ፡
ዕለት፡ሰዓቱኒ፡ጊዜ፡ስድስቱ፡ሰዓት፡ተሰቅለ፡
እግዚእነ።
፳፤ አሚሃ፡ዐሐይ፡ጸልመ፡ወወርኀኒ፡ደመ፡
ኮነ፡ ፡ ኵለንታሁ ፡ ምድር ፡ አድለ
ቅለቀት፡ወወጽኡ፡ሙታን፡እመቃብር፡
ወእምሲኦል።
፳፩፤ ወይቤሎ፡ዲዮናስዮስ፡ካልእሰ፡በአማን፡ኮነ፡
ዘጸሐፍነ፡ቅድመ፡ወዘሙታንሰ፡ነገር፡
ዕጹብ።
፳፪፤ ወይቤሎ፡ጳውሎስ፡በገበ፡ኢትናፍቁ፡
ዘተንሥኡ፡እሙታን፡ሖሩ፡ኀበ፡ሰብአሙ፡
ወእሙንቱ፡ነገሩ፡ከመ፡ማህረከ፡ለሲኦል፡
በመስቀሉ፡መድኃኔ፡ዓለም፡ክርስቶስ፡ወአ
ውጽአሙ።
፳፫፤ ወሶቤሃ፡አምኑ፡ወተጠምቁ፡በስሙ፡ለእግ
ዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡መድኃኔ፡ዓለም፡
ወሰገዱ፡ሎቱ፡ለሐዋርያ፡ጳውሎስ።
፳፬፤ ወሜሞ ፡ ለዲዮናስዮስ ፡ ኤጲስቆጶሰ ፡
ላዕሌሆሙ፤ውእቱኒ፡ገብረ፡ተአምራተ፡
ብዙኃተ፡ወተርጐመ፡ሥርዐተ፡ቤተ፡ክርስ
ቲያን።
፳፭፤ ወእምዝ ፡ መተሩ ፡ ርእሶ ፡ በሰይፍ ፡
ወነሥአ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ በመን
ግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡
ለቅዱስ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ማህሉ ፡ ወም
ሕረቱ ፡ ለመድኃኔ ፡ ዓለም ፡ የሀሉ፡ ምስ
ሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ድርሳን ፡ ዘብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡
አፈ ፡ ወርቅ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሀገር ፡
ዐባይ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ እምቃለ ፡ ጳው
ሎስ፡ሐዋርያ።

፩፤ ዘይቤ ፡ ተዐገሠ ፡ ኀፍረተ ፡ መስ
ቀል ፡ እናሕስዮ፡ በእንተ ፡ ፍሥሓሁ ፡
ዘጽኑሕ ፡ ሎቱ ፤ ወመኑና ፡ ለኀ
ፍረት።
፪፤ ገ ፡ ብሂል ፡ ሶበ ፡ ፍጹመ ፡ ኢፈቀደ ፡
እምኢሐመ፡እስመ፡ኢአበሰ፡ወኢተረክበ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፲፱፤ ጳውሎስም ፡ ዘመኑ ፡ ዘመነ ፡ ማርቆስ ፡
ዕለቱ ፡ ዐርብ ፡ ወሩም ፡ መጋቢት ፡ ሃያ ፡
ሰባት ፡ ቀን ፡ ሰዓቱ ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡
ነው ፤ በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ጌታችን ፡
ተሰቀለ።
፳፤ ያን፡ጊዜም፡ዐሐይ፡ጨለመ፤ጨረቃም፡ሁለ
ንተናው፡ደም፡ሆነ፤ምድርም፡ተናወጠች፤
ሙታንም ፡ ተነሥተው ፡ ከመቃብር ፡
ከሲኦልም፡ወጡ፡አለው።
፳፩፤ ዲዮናስዮስም፡ቀድሞ፡የጻፍነው፡ሌላው፡
በእውነት፡ሁኖአል፤የሙታን፡መነሣት፡
ነገር፡ግን፡ዕፁብ፡ድንቅ፡ነው፡አለው።
፳፪፤ ጳውሎስም ፡ በዚህስ ፡ አትጠራጠሩ ፤ የተነ
ሡትም፡ ሙታኖች፡ወደ፡ሰዎቻቸው፡ሄደው፡
የዓለም ፡ መድኃኒት ፡ ክርስቶስ ፡ በመስቀሉ፡
ሲኦልን፡እንደ፡በዘበዛት፡ነፍሳትንም፡እንዳወ
ጣቸው፡አረጋግጠው፡ተናግረዋል፡አለው።
፳፫፤ ያን፡ጊዜም፡በጌታችን፡በዓለም፡መድኒት፡
በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አምነው ፡
ተጠመቁ፤ለሐዋርያ፡ጳውሎስም፡ሰገዱለት።
፳፬፤ ዲዮናስዮስንም፡ኤጲስቆጶስነት፡በእነርሱ፡
ላይ፡ሾመው፤እርሱም፡ብዙ፡ተአምራትን፡
አደረገ፤የቤተ፡ክርስቲያንንም፡ሥርዓት፡
ተረጐመ።
፳፭፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቸብቸቦውን ፡ በሰይፍ ፡
ቆረጡት፤ የሰማዕትነትን፡አክሊል፡በመን
ግሥተ፡ሰማያት፡ተቀበለ፤የቅዱስ፡ዲዮና
ስዮስ፡ጸሎቱና፡በረከቱ፡የመድኃኔ፡ዓለምም፡
ይቅርታውና ፡ ቸርነቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡
ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

የታላቂቱ ፡ አገር ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ፡
ጳጳሳት፡የተመሰገነ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡አፈ፡
ወርቅ ፡ ከሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ቃል ፡ የተረ
ጐመው፡ድርሳን፡ይህ፡ነው።

፩፤ መከራ፡መስቀልን፡ታግሦ፡የተቀበለ፤ተጠብ
ቆለት ፡ ስላለ ፡ ድኅነት ፡ ምእመናን ፡
መከራውን፡ ንቆ ፡ ኀፍረተ ፡ መስቀልን ፡
አቃለለ፤ናቀ፡ያለውን፡ነው።
፪፤ ይህም ፡ ማለት ፡ ፈቃዱ ፡ ባይሆን ፡ ፈጽሞ ፡
ባልታመመ ፡ ነበር ፤ እርሱ ፡ ራሱ ፡ በከበረ ፡

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ሐሰት፡ውስተ፡አፉሁ፡በከመ፡ይቤ፡ለሊሁ፡ በወንጌል፡ቅዱስ፡ወይመጽእ፡መልአኩ፡ ለዝንቱ፡ዓለም፡ወኢይረክብ፡በላዕሌየ፡ ምንተኒ።

፲፫ ናሁኬ፡ ይትከሀሎ፡ ሶበ፡ ኢፈ ቀደ፡ እምኢሐመ፡ በዲበ፡ መስቀል፡ አስመ፡ ይቤ፡ አነ፡ እሜጥዋ፡ ለነፍ ስየ፡ በፈቃድየ፡ ብውሕ፡ ሊተ፡ አን ብራሂ፡ወብውሕ፡ሊተ፡አንሥአ።

፲፬ እመሰኬ፡ተሰቅለ፡በፈቃዱ፡ዘእንበለ፡ግብር፡ በእንቲአነ፡ሚ፡መጠነ፡ይደልወነ፡ለነኒ፡ ንትዐገሥ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ምንዳቤያት፡በዐቢይ፡ ጥብዐት።

፲፭ ይቤ፡ዘተዐገሠ፡ኀፍረተ፡መስቀል፡በእንተ፡ ፍሥሓሁ፡ ዘጽኑሕ፡ ሎቱ፡ ወመነና፡ ለኀፍረት። ዝ፡ ብሂል፡ ኀረየ፡ ለሞት፡ ወአብደረ፡ጽዕለተ፡ወኀሳረ፡እንዘ፡አልቦ፡ ላዕሌሁ፡ምክንያት፡ፈቂዶ፡ከመ፡ይምሐረነ፡ መንኖ፡ክብር፡ዘሰብእ፡ከመ፡ለሊሁ፡መነና፡ ለኀፍረት።

፲፮ እመቦ፡ዘይቤ፡ለምንት፡ኢይቤ፡መነና፡ ለኀሳር፡አላ፡ይቤ፡መነና፡ለኀፍረት።

፲፯ ንብሎ፡ዘንተ፡ዘይቤ፡በእንተ፡ዘኢተወክፈ፡ ሕማማተ፡ መስቀል፡ በግብር፡ እንዘ፡ የሐምም፡ወየሐዝን።

ምዕ፡፳፫፡፲፱–፳፩።

ረድእሂ፡**ዘመድኀነ፡ዓለም፡**አባ፡አትናቴዎስ፡ ሐዋርያዊ፡ይቤ።

፲፰ አሮ፡ ይብልዎ፡ መናፍቃን፡ በክህ ደቶሙ፡ **ለአምላክ፡ ጽድቅ፡** ዘበአማን፡ ዘኢየሐምም፡ በኵሉ፡ ግብር። ዘው እቱ፡ብርሃን፡ዘበአማን፡ወውእቱ፡ኃይሉ፡ **ለእግዚአብሔር፡ አብ፡** ዘኢይትመዋእ። የሐምም፡ወይመውት፡ወይደክም፡ከመ፡ ሰብእ፡ ዘወሀበ፡ ሕይወተ፡ ለእለ፡ ሞቱ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ወንጌል፡የዚህ፡ዓለም፡ገዥ፡መጥቶ፡በእኔ፡ ላይ፡ምንም፡ምን፡አያገኝብኝም፡እንዳለ፡አል በደለምና፡ በአንደበቱም፡ ሐሰት፡ አልተገ ኘምና።

፲፫ እነሆ፡ባይፈቅድስ፡በመስቀል፡ላይ፡መከራ፡ ባልተቀበለም፡ ነበር፡ ላለመቀበልም፡ በተቻለው፡ ነበር፤ እርሱ፡ እኔ፡ በፈቃዶ፡ ነፍሴን፡ከሥጋዬ፡ልለያት፡ሥልጣን፡አለኝ፤ ደግሞም፡ አዋሕጄ፡ ላስነሣት፡ ሥልጣን፡ አለኝ፡ብሏልና።

፲፬ እንግዲህ፡ግዴታ፡ሳይኖርበት፡ስለ፡እኛ፡ በፈቃዱ፤ከተሰቀለ፡በመከራው፡ሁሉ፡ላይ፡ በፍጹም፡ብርታት፡ምን፡ያህል፡መታገሥ፡ ለእኛ፡ይገባን፡ይሆን?ይገባናል።

፲፭ ተጠብቆለት፡ ስላለ፡ ድኅነተ፡ ምእመናን መከራውን፡ንቆ፡አቃልሎ፡ኀፍረተ፡መስቀ ልንም፡ናቀ፤አቃለላት፤ይህ፡ማለት፡በእርሱ፡ ላይ፡ምክንያት፡ሳይኖር፡ሞትን፡መሰደብን፡ መዋረድንም፡መረጠ፤እርሱ፡ኀፍረትን፡ንቆ፡ እንደ፡ተቀበላት፡ከሰው፡ዘንድ፡የሚሆነውን፡ ክብርን፡መናቅን፡ያስተምረን፡ዘንድ፡ወዶ።

፲፮ ኀፍረትን፡ናቃት፡አለ፡እንጂ፤ለምን፡ጕስቍ ልናን፡ናቃት፡አላለም፡የሚል፡ቢኖር።

፲፯ ይህን፡ያለ፤ሕማማተ፡መስቀልን፡ፈጽሞ፡ እያዘነ፡በግድ፡ስለ፡አልተቀበለ፡ይህን፡አለ፡ እንለዋለን።

ምዕ፡፳፫፡፲፱–፳፩።

**ለዓለም፡መድኃኒት፡**ደቀ፡መዝሙር፡የሆነ፡ ሐዋርያዊ፡አባ፡አትናቴዎስም፡እንዲህ፡አለ።

፲፰ በምንም፡ በምን፡ ሕማም፡ የሌለበት፡ ዕውነተኛ፡**የባሕርይ፡አምላክ፡**እውነተኛ፡ ብርሃን፡ **የእግዚአብሔር፡ አብ፡** ኃይሉ፡ የሚሆን፤ ለሕማም፡ ለሞት፡ የማይደፈር፡ እርሱን፡መናፍቃን፡በክሕደታቸው፡እንደ፡ ሰው፡ በግድ፡ ታመመ፤ ደከመ፤ ሞተ፡ እንደምን፡ ይሉታል? ለሞቱ፡ ሰዎች፡ ሕይወትን፡ የሰጠውን፡ ሙታንን፡ ያሥነ

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወአንሥአ፡ሙታነ። ወአምጽአሙ፡ለእለ፡
ኢሀለዉ፡እምኅበ፡ኢሀልዎ፡ኅበ፡ሀልዎ፤
እፎኑ፡ይብልዎ፡ከመ፡ውእቱ፡ሐመ፡ወሞተ።
ወእፎ፡ይትሀበሉ፡ወይነብቡ፡ዘንተ፡ንባበ፡

፳፤ ወውእቱ፡ላዕለ፡እግዚአብሔር፡ሕያው። ወውእቱ፡ሕይወት፡ወትንሣኤ፡ወውእቱ፡ኀይለ፡እግዚአብሔር፡ወውእቱ፡ዘኮነ፡ሰብአ፡ወተሠገወ፡እምብእሲት፡እንዘ፡ኢይትዌለጥ፡እመለኮቱ። በልዐ፡ወሰትየ፡ከማነ፡ሐመ፡ወተሰቅለ፡ወሞተ፡ተሥዒሎ፡በሥዕለ፡ገብር፡ዘነሥአ፡እምኔነ፡እንዘ፡ውእቱ፡አርአያ፡እግዚአብሔር፡ኮነ፡በአርአያ፡ሰብእ።

፳፩፤ እመሰ፡ተወለጠ፡በመለኮቱ፡ግሙራ፡እፎኑ፡አብሠሮ፡ለፈያታዊ፡በዊአ፡ገነት።

ምዕ፤፴፩፤፩–፬።

ዓዲ፡እምነ፡ተዋሥኦተ፡ሰለባስትርዮስ።

፪፤ ለእመ፡በ፡ፆም፡ወይፈቅዱ፡መቲሮቶ፡በማሕጼ፡በመንፈቀ፡መዐልት፡እንዘ፡ይከድኖ፡ፀሐይ። ወሶበ፡ይዘብጥዎ፡በማሕፄ፡ለፆም፡አኮኑ፡ዝብጠተ፡ማሕጼ፡ይወድቅ፡ዲበ፡ጕንደ፡ፆም፡እንዘ፡ላዕሌሁ፡ፀሐይ፤ይቤ፡ኖኅ፡አይሁዳዊ፡እወ።

፫፤ ይቤ፡ሰለባስትርዮስ፡ይደሉኑ፡ይምትሮ፡ማኅፄ፡ለፀሐይ፡አው፡ይግበር፡ቦቱ፡ትእምርተ፡እንዘ፡ውእቱ፡ይከድኖሙ፡ለፆም፡ወለማሕጼ፡ይቤ፡ኖኅ፡አልቦ።

፬፤ ይቤሎ፡ሰለባስትርዮስ፡ከመዝ፡ውእቱ፡ባህልነ፡በእንተ፡ሕማማቲሁ፡ለክርስቶስ፡እስመ፡ሥጋ፡ይትሜሰል፡ከመ፡ፆም፡ሕማማትኒ፡ከመ፡ማሕጼ፡ፀሐይኒ፡ከመ፡መለኮት፡ወከመዝ፡ሐመ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በሥጋ፡እንዘ፡ኢይረክቦ፡ለመለኮት፡ምንትኒ፡እምሕማማት።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ሣውን፡ያልነበሩትን፡ካለመኖር፡ወደ፡መኖር፡አምጥቶ፡ያስገኛቸውን፡ታመመ፡ሞተ፡እንደምን፡ይሉታል?

፳፤ በሕያው፡እግዚአብሔር፡ላይ፡ደፍረው፡ይኸንን፡ነገር፡እንደምን፡ይናገራሉ?እርሱ፡ሕይወት፡ትንሣኤ፡ነው፤እርሱ፡የእግዚአብሔር፡ኃይሉ፡ነው፤ከባሕርዩ፡ሳይለወጥ፡ከእመቤታችን፡ነፍስን፡ሥጋን፡ነሥቶ፡ሰው፡የሆነ፡እርሱ፡እንደ፡እኛ፡በላ፤ጠጣ፤ከእኛ፡በነሣው፡በሰው፡ባሕርይ፡ሰው፡ሁኖ፡ታመመ፤ተሰቀለ፡ሞተ፡እንጂ፡እርሱ፡የባሕርይ፡አምላክ፡ሲሆን፡ሰው፡ሆነ።

፳፩፤ ከባሕርዩ፡ከተለወጠማ፡ወደ፡ገነት፡መግባትን፡ለፈያታዊ፡እንደምን፡አበሠረው።

ምዕ፤፴፩፤፩–፬።

ዳግመኛ፡ሰለባስትርዮስ፡ከአይሁዳዊ፡ጋር፡ካደረገው፡ክርክር።

፪፤ ሰለባስትርዮስ፡ዛፍ፡ቢኖር፡የፀሐይ፡ብርሃን፡በቀትር፡ጊዜ፡ወድቆበት፡ሳለ፡በምሳር፡እንቆርጣለን፡ቢሉ፡ዛፉን፡በምሳር፡በመቱት፡ጊዜ፡ፀሐይ፡ወድቆበት፡ሳለ፡የብረቱ፡ኃይል፡በግንዱ፡ላይ፡የሚወድቅ፡አይደለምን፡አለ፤አይሁዳዊ፡ኖኅም፡እውነት፡ነው፡አለ።

፫፤ ሰለባስትርዮስም፡ፀሐይ፡በምሳሩና፡በዛፉ፡ላይ፡ወድቆባቸው፡ሳለ፡ምሳር፡ፀሐይን፡ይቆርጠው፡ዘንድ፡ወይም፡ክርክራት፡ፍልቃት፡ያደርግበት፡ዘንድ፡ይቻለዋልን?አለ፤ኖኅም፡አይቻለውም፡አለ።

፬፤ ሰለባስትርዮስም፡ስለ፡ክርስቶስ፡ሕማም፡ሞት፡የምንናገረው፡እንደዚሁ፡ነው፤ሥጋው፡በዛፍ፤ሕማሙ፡በምሳር፤መለኮትም፡በፀሐይ፡ይመሰላልና፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡መለኮቱን፡ከሕማም፡ወገን፡ምንም፡ሳያገኘው፡እንዲሁ፡በሥጋ፡ታመመ፡አለው።

በ፯፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ምዕ፡፸፱፡፩–፫፡፴፯።

፶፮፡ይቤ፡ክቡር፡ወቅዱስ፡ቄርሎስ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ዘእለእስክንድርያ።

አሐዱ፡ውእቱ፡አብ፡አሐዱ፡ውእቱ፡
ወልድ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ዘውእቱ፡ዋህድ፡ቃል፡ዘእምአብ፡ኮነ፡
ሰብአ፡ወኢተአተተ፡እምስብሐተ፡መለ
ኮቱ፡ልዑል፡ዘለዐለ፡ወይሄሉ፡በትስ
ብእቱ፡አምላክ፡ወውእቱ፡እግዚእ፡በአ
ርአያ፡ገብር፡ወቦቱ፡ፍጹም፡መለኮት፡
በአርአያ፡ንደትነ።

ወእንዘ፡ውእቱ፡በድካመ፡ሥጋ፡እግዚአ፡
ኃይላት፡ውእቱ፡ወእንዘ፡በዐቅመ፡ዕጓለ፡
እመሕያው፡ቦቱ፡ልዕልና፡እምኵሉ፡
ፍጥረት። ወቦቱ፡ህልው፡ኵሉ፡ግብረ፡
ትስብእት፡እመንገለ፡ሥጋሁ፡ዘእንበለ፡
ኃጢአት፡ባሕቲታ።

ለሊሁ፡እግዚአብሔር፡ዘበአማን፡ወወ
ልደ፡እግዚአብሔር፡ዋሕድ። ብርሃን፡
ዘእምብርሃን፡ወሕይወት፡ወኃይል፡ነሥአ፡
ዘኢዚአሁ፡ወቦቱ፡አስተርአየ፡በእንተ፡
ሥርዐት፡ወሐሰበ፡ሎቱ፡ኵሉ፡ዘት
ሰብእት፡በእንተ፡ሥጋ፡ዘኮነ፡አሐደ፡
ምስሌሁ፡በሥርዐት፡ኀቡእ፡ዘኢይ
ትነገር፡ወሥጋዊ፡ሥጋሁ፡ውእቱ፡ወአኮ፡
ዘካልእ።

፴፯ እምነገረ፡ቅዱስ፡ቄርሎስ፡ኀበ፡ዮሐንስ፡
መካዕበ፡ይቤ፡ዝንቱ፡መምህር፤ ነአምን፡
ከመ፡ ቃለ፡እግዚአብሔር፡ኢሐማሚ፤
ወኢመዋቲ፡ሐመ፡በሥጋ፡ውእቱ፡ሠራዔ፡
ምስጢር፡በጥበቡ፡ወኢሐመ፡በህላዌ፡
መለኮቱ፡ዘኢይትረከብ፡ከመ፡ንእመን፡
ቦቱ፡ከመ፡መድኃኔ፡ኵሉ፡ውእቱ፤
ተወክፈ፡ሕማመ፡በሥጋሁ፡ከመ፡
ዘሎቱ፡በሥርዐት፡ዘሠርዐ፡ለርእሱ፡
ቃሉ።

እምድርሳነ፡ቅዱስ፡ቄርሎስ።

ምዕ፡፸፫፡፲፩–፲፮፡

፲፩ ይቤ፡ንህነሰ፡ንትሉ፡ሃይማኖተ፡(ሕሊና)፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፯፡ሰዓት።

ምዕ፡፸፱፡፩–፫፡፴፯።

ዳግመኛ፡የከበረ፡የእስክንድርያ፡ሊቀ፡
ጳጳሳት፡ቅዱስ፡ቄርሎስ፡እንዲህ፡አለ።

፶፮፡ አብ፡አንድ፡ነው፤ ወልድ፡ዋህድ፡ጌታችን፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡አንድ፡ነው፤ ይኸውም፡
ከአብ፡አንድ፡አካላዊ፡ቃል፡ነው፤ ሰው፡ሆነ፤
ገንዘቡ፡ከሚሆን፡ከልዑል፡ጌትነቱም፡አል
ተለየም፤ ሰውም፡ቢሆን፡በአምላክነቱ፡
ጸንቶ፡ይኖራል፤ ገዥ፡እርሱ፡በተገዢ፡
ባሕርይ፡ተገለጸ፤ ንዴት፡በሚስማማው፡
በእኛ፡ባሕርይ፡ሳለ፡ፍጹም፡መለኮት፡
ገንዘቡ፡ነው።

፶፯፡ በድካመ፡ሥጋ፡ተገልጦ፡ሳለ፡የኃያላን፡
መላእክት፡ጌታ፡ነው፤ በሰው፡መጠን፡
በአጭር፡ቁመት፡በጠባብ፡ደረት፡ሳለ፡
ከፍጥረት፡ሁሉ፡በላይ፡ነው፤ ከኃጢአት፡
ብቻ፡በቀር፡በሰውነቱ፡የሰውነት፡ሥራ፡
ሁሉ፡ገንዘቡ፡ነው።

አንድ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ከብርሃን፡
የተገኘ፡ብርሃን፡ሕይወት፡ኃይል፡የሚሆን፡
እርሱ፡እግዚአብሔር፡ባሕርዩ፡ያልነበረ፡
ሥጋን፡ተዋሐደ፤ ሰው፡ስለሆነም፡በሥጋ፡
ተገለጸ፤ በማይመረመር፡ረቂቅ፡ተዋሕዶ፡
ከእርሱ፡ጋር፡አንድ፡የሆነ፡ሥጋን፡ስለ፡
ተዋሐደ፡የሰውነትን፡ሥራ፡ሁሉ፡ገንዘብ፡
አደረገ፤ ሥጋም፡ገንዘቡ፡ነው፡የሌላ፡
አይደለም።

፴፯፡ ለዮሐንስ፡ጽፎ፡ከላከው፡ከቅዱስ፡ቄርሎስ፡
መልዕክት፡ዳግመኛ፡እንናገራለን፤ የእግዚአ
ብሔር፡ቃል፡የማይታመም፡እንደሆነ፡እናም
ናለን፤ ቢታመምም፡በሥጋ፡ነው፤ በባሕርይ፡
ጥበቡ፡ተዋሕዶን፡የፈጸመ፡እርሱ፡ነው፤ በማ
ይመረመር፡በባሕርየ፡መለኮቱ፡የማይ
ታመም፡ለሁሉ፡መድኃኒት፡እንደ፡ሆነ፡እና
ምንበት፡ዘንድ፡ቃል፡ለራሱ፡በሠራው፡
ሥርዓት፡የእርሱ፡ገንዘቡ፡እንደ፡መሆኑ፡
በሥጋው፡መከራን፡ተቀበለ።

ቅዱስ፡ቄርሎስ፡ከተናገረው፡ድርሳን።

ምዕ፡፸፫፡፲፩–፲፮፡

፲፩፡ እኛስ፡የቀናች፡የሃይማኖትን፡ነገር፡እንናገ

Scanned by CamScanner

## በ፰፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ርትዕተ ፡ ወንትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ነገረ ፡ ጽድቅ ፡
ወኢንብል ፡ ነኪር፡ ውእቱ ፡ መለኮት ፡ እምነ ፡
ሕማም ፡ ከመ ፡ በዝንቱ ፡ ኢንብል ፡
እምቅድመ፡ ዝ ፡ እስመ ፡ ልደቱ ፡ ሥጋዊ ፡
እኮ ፡ ልደቱ ፡ ወኢንብል ፡ ከመ፡ ውእቱ ፡
ለካልእ።

፲፪ ወኢንክህድ ፡ ዘኮነ ፡ ዲበ ፡ ህላዌ ፡ ልዑል ፡
ዘእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከመ ፡ ሶበ ፡ ይት
ወደይ ፡ ኀጺን፡ ውስተ ፡ ላህበ ፡ እሳት ፡
ወይትዌከፍ ፡ ላህበ ፡ እሳት ፡ በተዋ
ሕዶቱ ፡ ምስሌሁ ። እስመ፡ ሶበ ፡ ይዘበጥ ፡
ኀጺን ፡ ዘምስለ ፡ እሳት ፡ ኅቡረ ፡ ይትዌከፍ ፡
ዝብጠተ ፡ ወኢይትዔመፅ ፡ ህላዌ ፡ እሳት ፡
በምንትኒ ፡ እምነ ፡ ዝብጠት ። ከመዝ ፡ ንለቡ ፡
እስመ፡ በማኑኤል፡ ቃል፡ሐመ፡በሥጋ፡እንዘ፡
ኢየሐምም፡በመለኮት።

፲፫ ይቤ፡ጸውዐኒ፡መፍቅድ፡እትዋሐድ፡ምስለ፡
ሥጋ፡ከመ፡እፍታሕ፡ማእሰረ፡ኃጢአት፡ወተ
ሰቀልኩ ፡ እስመ ፡ ኮንኩ ፡ ሰብአ ፡ በእንቲ
አሆሙ ፡ ከመ ፡ አብጥል ፡ ኃጢአተ ፡ ኵሉ ፡
በሥጋየ፡ወሞትኩ፡በከዊነ፡ዳግማይ፡አዳም።

፲፬ ወኢሞተ ፡ መለኮትየ ፡ አላ ፡ ጌወውኩ ፡
ሲኦለ ፡ ወተንሥእኩ ፡ በሥልጣነ ፡ ባሕ
ቲትየ ፡ ነፋሕኩ፡ በገጸ ፡ አርዳእየ ፡ አጠ
ይቅ ፡ ከመ ፡ ፈጣሪ ፡ አነ ፡ ዘነፋሕኩ ፡
ውስተ ፡ ገጹ ፡ ለብእሲ ፡ ዘነበረ ፡ ውስተ ፡
ገነት፡ዘውእቱ፡አዳም።

፲፭ ወአሐዱ ፡ ዘእምሥላሴ ፡ ውእቱ ፡ ዘተ
ሰቅለ ፡ ወበሥጋ ፡ ተወክፈ ፡ ሞተ ፡ ዝንቱ ፡
ዘኮነ ፡ አሐደ፡ ምስሌሁ ። ወኢሞተ ፡
መለኮት ፡ ዘውእቱ ፡ አሐዱ ፡ ምስለ ፡
አብ ፡ ወምስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡
ኢይበሉ ፡ ካልአንሂ ፡ ተሰቅሉ ፡ ምስ
ሌሁ ፡ እትናገር ፡ በእንተ ፡ አብ ፡ ወመ
ንፈስ፡ቅዱስ።

፲፮ ወለእመ ፡ ንቤ ፡ ከመ ፡ ቃል ፡ ተወክፈ ፡
ሕማመ ፡ በሥጋ ፡ ንህነለ ፡ ነአምን ፡ ከመ ፡
አሐዱ ፡ እምቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ተሰቅለ

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

ራለን፤እውነት፡ነገርንም፡ወደ፡መናገር፡እን
መለሳለን ፡ አለ፤ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ ልደት፡
ሥጋዊ ፡ ገንዘቡ ፡ አልነበረምና ፤ ታመመ፡
የማንል ፡ እንደነበረ ፡ የሌላ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፡ እን
ደማንልም ፡ መለኮት ፡ ከሕማም ፡ ልዩ ፡ ነው ፡
አንልም።

፲፪ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በረቂቅ ፡ ባሕርይ ፡
የሆነውን፡ተዋሕዶ፡እንካድ፤ብረት፡ከእሳት፡
በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፡ ከእሳትም ፡ በመዋሐዱ ፡
የእሳትን ፡ ባሕርይ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲያደርግ፤
ብረት፡በመዶሻ፡በተመታ፡ጊዜ፡ከእሳት፡ጋር፡
በአንድነት ፡ እንዲመታ ፡ ግን ፡ ከመዶሻው ፡
የተነሣ፡የእሳት፡ባሕርይ፡በምንም፡በምን፡እን
ዳይጐዳ ፤ ሰው ፡ የሆነ ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡
በመለኮቱ፡ ሕማም ፡ ሳይኖርበት ፡ በሥጋ ፡
እንደ፡ታመመ፡እንዲህ፡እናስተውል።

፲፫ ፈቃድ ፡ ሥጋን ፡ እንድዋሐድ ፡ አደረገኝ፤የኃ
ጢአትን ፡ ፍዳ ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ መከራም፡
ተቀበልኩ ፤ በሥጋዬ ፡ የሁሉን ፡ ኃጢአት፡
አጠፋ፡ዘንድ፡ስለ፡እነርሱ፡ሰው፡ሁኛለሁና፤
ሁለተኛ፡አዳምን፡ሆኜ፡ሞትኩ።

፲፬ መለኮቴ፡ግን፡አልሞተም፤ሲኦልን፡በዘበዝኩ፡
እንጂ፤በገዛ፡ሥልጣኔም፡ተነሣሁ፡እንጂ፤በገነት፡
በነበረ ፡ ሰው ፡ በአዳም ፡ በንፍሐት ፡ መንፈስ፡
ቅዱስን፡ያሳደርኩ፡ፈጣሪ፡እኔ፡መሆኔን፡እስረዳ፡
ዘንድ ፡ በደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ ፊት ፡ እፍ ፡ ብዬ፡
መንፈስ፡ቅዱስን፡አሳደርኩ፡አለ።

፲፭ የተሰቀለው፡ከሦስቱ፡አካላት፡አንዱ፡አካል፡
ነው ፤ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ይህ፡
ቃል፡ በተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ ሞተ ፤ ከአብ፡
ከመንፈስ፡ቅዱስ፡አንድ፡የሚሆን፡መለኮት፡
ግን ፡ አልሞተም ፤ በአካል ፡ ልዩ ፡ የሚሆኑ፡
አብ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ከእርሱ፡ጋር፡ተሰቀሉ፡
እንዳይሉ ፤ የአብ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ነገር፡
እናገራለሁ።

፲፮ ቃል ፡ በሥጋ ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡
ብናገርም ፡ እኛ ፡ ከሦስቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡
አካል ፡ እንደ ፡ ተሰቀለ ፡ እናምናለን ፤ ከሦስቱ

በ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

መካልእንሰ፡ ህላዌያት ፡ ዘቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ኢሐሙ።

ምዕ፥፶፲፩፥፲፩-፲፫።

ዓዲ ፡ እመልእክተ ፡ ሲኖዲቆን ፡ ዘአባ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ።

፲፩ ይቤ ፡ ነአምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘተሠገወ ፡ አሐዱ ፡ ውእቱ ፡ እንበለ ፡ ውላጤ ፡ ወሥላሴሂ ፡ ዓዲ ፡ ይሄሉ ፡ በሥላሴሁ ፡ ወኢይከውን ፡ ራብዐየ ። ዕሩይ ፡ ውእቱ ፡ ምስለ ፡ አቡሁ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወለነሂ ፡ ይትዔረየነ፡ በትስብእቱ ። ወለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ፍጹም ፡ ዘበአማን ፡ ወይትናገር ፡ ዘይደሉ ፡ ለመለኮት ። ወገብረ ፡ መንክራተ ፡ አምላካውያተ ፡ ዘይትሌዓል ፡ እምኔነ፡ከመ፡አምላክ።

፲፪ ወውእቱ፡ዓዲ፡ገብረ፡ግብራተ፡ትስብእት፡ እንዘ፡ውእቱ ፡ ከመ ፡ ይትዋሐድ ፡ ምስለ ፡ መለኮት፡ወተወክፈ፡ኵሎ፡ሥርዐተ፡ዕጓለ፡ እመሕያው፡ዘእንበለ፡ኃጢአት፡ባሕቲታ ። ዘውእቱ ፡ ረኃብ ፡ ወጽምእ ፡ ወድካም ፡ እምሐዊረ፡ ፍኖት ፤ ተሰቅሎ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ወተቀንዎ ፡ በቅንዋተ ፡ ኀጺን ፡ ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ፍጡር ፡ በሰብእናሁ ፡ ወፈጣሪሂ፡በመለኮቱ። ወአልቦቱ፡ፍልጠት፡ ለግሙራ ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘኢይትከፈል፡ወለሊሁ፡ውእቱ፡ዘሐመ፡ወሞተ፡በእንቲአነ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ወውእቱ ፡ ክመ ፡ ኢሐማሚ፡ወኢመዋቲ፡በመለኮቱ፡ወኢየትዌከፍ፡ሕማማተ፡ወሞተ።

፲፫ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘቀተሎ ፡ ለሞት ፡ በሞቱ ፡ ወዔወዎ፡ለሲኦል።

ምዕ፥፶፲፪፥፲፩።

ወካዕበ፡ይቤ፡ክርስቶዶሎስ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ ዘእለእስክንድርያ።

፲፬ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ ለመድኃኒተ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው፡ ወአኮ ፡ በምትሐት ። ወውእቱሰ ፡ ኢሐማሚ፡ ወኢመዋቲ ፡ በህላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ወበሥርዐቱ ፡ ወበጥበቡ ፡ ልዕልት

ዓርብ፡መዓልት፡በ፩፡ሰዓት።

አካላት ፡ ሁለቱ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መከራ፡አልተቀበሉም።

ምዕ፥፶፲፩፥፲፩-፲፫።

ዳግመኛ ፡ የአንጾኪያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባታችን ፡ አባ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ከላከው ፡ ሲኖዶሳዊ፡መልእክት።

፲፩ ሰው፡የሆነ፡እግዚአብሔር፡ቃልን፡እናውቀዋለን ፤ ያለ ፡ መለወጥ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ሦስትነትም፡ደግሞ፡በሦስትነቱ፡ጸንቶ፡ይኖራል፤ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ከአባቱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሚሆን፡እርሱ፡አራተኛ፡አይሆንም። ሰው፡ በመሆኑም ፡ እኛን ፡ ይመስለናል ፤ እሱ ፡ በእውነት፡ፍጹም፡ሰው፡ሆነ፤ለአምላክነት፡ የሚገባውንም፡ይናገራል፤አምላክም፡እንደ፡ መሆኑ፡ከእኛ፡በላይ፡የሆኑ፡የአምላክነትን፡ ሥራዎች፡ሠራ።

፲፪ እርሱ፡መቾም፡መች፡ከመለኮቱ፡ሳይለይ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፤ ከኃጢአትም ፡ በቀር ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ፡አደረገ፤ይኸውም፡መራብ፡መጠማት፡ መንገድ ፡ በመሄድ ፡ መድከም ፡ በመስቀል ፡ ላይ፡መሰቀል፡በብረት፡ችንካር፡መቸንከር፡ ነው ፤ በሰውነቱ፡መቾም፡መች፡ሰው፡ነው፤ በአምላክነቱም፡ሰውን፡የፈጠረ፡ነው፤ግን፡ ከማይከፈል ፡ ተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ መከፈል ፡ የለበትም፤ ሰው ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ የታመመው ፡ የሞተው ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ በመለኮቱ ፡ ግን ፡ መቾም ፡ መች ፡ አይታመምም፡አይሞትም፡ሕማምንና፡ሞትንም፡ አይቀበልም።

፲፫ በሞቱ ፡ ሞትን ፡ ያጠፋው ፡ እርሱ ፡ ነው ፤ ሲኦልንም፡የበዘበዘው፡እርሱ፡ነው።

ምዕ፥፶፲፪፥፲፩።

ዳግመኛም፡የእስክንድርያ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ክርስቶዶሎስ፡እንዲህ፡አለ።

፲፬ ሰውን ፡ ለማዳን ፡ በሥጋ ፡ ታመመ ፤ በምትሐትም ፡ አይደለም ፤ በባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ እርሱ፡ግን፡የማይታመም፡የማይሞት፡ነው፤ በረቂቅ ፡ ጥበቡ ፡ ሰው ፡ በመሆኑ ፡ በፈቃዱ

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ረሰየ ፡ ሎቱ ፡ ሕማመ ፡ በፈቃዱ ፡ ባሕቲቱ ፤ ወሞተ፡በዲበ፡ዕፀ፡መስቀል

ጸሎቶሙ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ለእሉ ፡ መምሀራን ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ድርሳን፡ዘዮሐንስ፡አፈወርቅ።

ምዕ፡፳፭፡፩-፮።

፩፡ ይቤ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፤ አንሰ ፡ ብህልኩ፡በእንተ፡ተስፋ፡ዘኮነ፡በይሥሐቅ፡ ዘይቤሎ ፡ እምይሥሐቅ ፡ ይሰመይ ፡ ለከ ፡ ዘርዕ።

፪፡ ርኢከኑ፡ጥበቦቶ፡ለአበ፡አበው፡ዘከመ፡ሦዖ፡ ለይሥሐቅ፡በእንቲአሁ፡ዘይቤሎ፡እምኔሁ፡ ይሰመይ፡ለከ፡ዘርዕ።

፫፡ ወኢይምስሎ ፡ ለአሐዱ ፡ ከመ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ በቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ አላ ፡ አምነ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክል ፡ አንሥኦቶ ፡ እምውታን።

፬፡ ወኢኀለየ ፡ ከመ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ አላ ፡ ተአመነ፡በኵሉ፡ግብሩ።

፭፡ ወረሰዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ ወአርአያ ፡ እስመ ፡ ድኅነ ፡ በመሥዋዕተ ፡ መድኃኒት ፡ በግዕ፡ዘተጠብሐ፡ህየንቴሁ።

፮፡ ወከማሁ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠብሐ ፡ ህየንተ ፡ ኵሉ ፡ በመስቀል ፤ ነጸር ፡ አ ፡ ፍቁር ፡ አፍቅሮተ፡እግዚአብሔር፡ሰብአ።

እምድርሳነ፡ቅዱስ፡ቄርሎስ።

፩፡ ጳላድዮስ ፡ ይቤ ፡ ይብሉኬ ፡ ንኤብስ ፡ ዐቢየ ፡ እመ ፡ ንቤ ፡ ሐመ ፡ ቃል ፡ ወኵሎሂ ፡ ክብረ ፡ ምሥጢር ፡ ልቡየ ፡ ንሬሲ።

፪፡ ቄርሎስ ፡ ይቤ ፡ አላ ፡ ተዐጊሦ ፡ ኀፍረተ ፡ በሥጋሁ ፡ አብደረ ፡ ሐሚመ ፡ በከመ፡ጽሑፍ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ብቻ ፡ ሕማምን ፡ ገንዘብ ፡ አደረገ ፤ በፈቃዱ ፡ ብቻ፡በመስቀል፡ላይ፡ሞተ።

የእነዚህ ፡ መምህራን ፡ ጸሎታቸው ፡ በረከ ታቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑር ፡ አሜን።

የዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ፡ድርሳን።

ምዕ፡፳፭፡፩-፮።

፩፡ አባታችን፡ዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ፡እንዲህ፡አለ፡ ከይሥሐቅ ፡ ዘር ፡ ይሆንልሃል ፤ በይሥሐቅም፡ ዘር ፡ አግኝተህ ፡ በርሱ ፡ ስምህ ፡ ይጠራልሃል ፤ ስላለው፡ተስፋ፡እኔ፡እንዲህ፡አልኩ፡አለ።

፪፡ በርሱ ፡ ስምህ ፡ ይጠራል ፤ በዘሩም ፡ መታሰ ቢያህ ፡ ይጸናል ፤ የተባለለት ፡ ይሥሐቅን ፡ ይሠዋው፡ዘንድ፡የአባቶች፡አባት፡የሆነ፡የአ ብርሃምን፡ቆራጥነቱን፡ታያለህን?

፫፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለአንዱም ፡ ለአንዱ ፡ ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ ያደረገ ፡ አይምሰለው ፤ እግዚአ ብሔር፡ከሞት፡ያነሣው፡ዘንድ፡እንዲቻለው፡ አመነ፡እንጂ።

፬፡ ሰው ፡ እንደሚያስብ ፡ አላሰበም ፤ በሥራው፡ ሁሉ፡አመነ፡እንጂ።

፭፡ እግዚአብሔር ፡ ምሳሌውና ፡ አርዓያው ፡ ባደረገው፡ይሥሐቅ፡ስለ፡እርሱ፡በተሠዋው፡ በግ፡መሥዋዕትነት፡እንደዳነ።

፮፡ እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ሁሉ ፡ ድኅነት ፡ የእግዚአ ብሔር፡ልጅ፡በመስቀል፡ላይ፡ተሠውቶአልና፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን፡ምን፡ ያህል፡እንደሚወድ፡ተመልከት።

ከቅዱስ፡ቄርሎስ፡ድርሳን፡የተገኘ።

፩፡ ጳላድዮስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ቃል ፡ ታመመ ፡ ብንል፡ ታላቅ ፡ በደል ፡ እንበድላለን ፤ የተዋሕ ዶንም ፡ ምሥጢር ፡ ክብር ፡ የተሳሳተ ፡ እናደር ጋለን፡ይላሉ።

፪፡ ቄርሎስ፡እንዲህ፡አለ፡እንደ፡ተጻፈ፡ኀፍረት፡ መስቀልን ፡ ታግሦ ፡ በሥጋው ፡ መከራ ፡ መቀበልን፡ወደደ፡እንጂ።

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

...ወ፡ዘይብሉ ፡ ደዌ ፡ አይሁድ ፡ ወአረሚ ፡
...ወአቱ ፡ ዘያስተላብዩ ፡ ሕማመ ፡ መስቀል ፡
...እስመ ፡ ይጽሕፍ ፡ ብፁዕ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዘ ፡
...ይብል ፡ እስመ ፡ አይሁድሂ ፡ ተአምረ ፡
...ይሴአሉ፡ወአረሚኒ፡ጥበበ፡የኀሥሡ።

...ንሕነሰ ፡ ንሰብክ ፡ **ክርስቶስሃ** ፡ ዘተሰቅለ ፡
...ለአይሁድሰ ፡ ዕቅፍት ፡ ወለአሕዛብ ፡
...አበድ።

...ድርሳን፡ዘቅዱስ፡ወብፁዕ፡አባ፡ያዕቆብ፡ኤጲ
...ስቆጶስ ፡ ዘስሩግ ፡ በእንተ ፡ መልአክ ፡
...ወፈያታዊ ። ጸሎቱ ፡ ወበረከቱ ፡ ተሀሉ ፡
...ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

...ርድአኒ፡**ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡**
**...ሕያው ፡** ወአብርሀ ፡ አዕይንተ ፡ ልብየ ፡ ከመ ፡
...እክሥት፡ምሥጢራተ፡መንክራቲከ፡ወአጽ
...ንዐኒ፡ከመ፡እግበር፡ትእዛዛቲከ።

...ብከ፡ጸንዐ፡ስምዖን፡ጴጥሮስ፡ወሖረ፡ዲበ፡
...ማይ፡ወብከ፡እጽናዕ፡ከማሁ፡ከመ፡እክሀል፡
...ተርጕሞ፡መንክራቲከ።

...ስብሐቲከሰ ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፤ ወግሩም ፡
...ዕበይከ፡ፈድፋደ።

...ዋቁ፡ዐቢይ፡ግብርከ፡**እግዚእ፡** ወፈድፋደ፡
...ዕሙቅ፡ኀሊናከ።

...አይቴ ፡ እንከ ፡ እኄሊ ፡ ኀበ ፡ ልደትከኑ ፡
...ወሚመ፡ኀበ፡ሞሎት፡እለ፡ሰብሑከ፡ወመላ
...እክት፡እለ፡ወደሱከ፡በውስተ፡ጎል፡ወሚመ፡
...ኀበ፡ሰብአ፡ሰገል፡እኄሊ።

...ኀበ፡ዮሴፍኑ፡ወሚመ፡ኀበ፡ስምዖን፡ልሂቅ፡
...ዘየኀሥሥ ፡ እምኔከ ፡ ወይስእለከ ፡ ከመ ፡
...ትስዐሮ፡ይኑም፡ወያዕርፍ።

...ኀበ፡ያጠምቀከኑ፡ዮሐንስ፡እዜከር፡ወሚመ፡
...ኀበ፡ሰምዐ፡ኮነ፡**አብ፡** እንዘ፡ይብል፡ዝንቱ፡
...ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ወኪያሁ ፡ ሠምርኩ ፡
...እኄሊ።
...ኀበ፡አንበረኑ፡ወልደ፡መካን፡እዴሁ፡ዲበ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት። ፳፻፴፯

፫፤ ይህ፡የሚሉት፡አይሁድና፡አረሚ፡ያመጡት፡
የክህደት ፡ ደዌ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ መከራ ፡
መስቀሉን፡የሚያሳስቱ፡ናቸው፤የተመሰገነ፡
ጳውሎስ ፡ አይሁድ ፡ ተአምራትን ፡
ይጠይቃሉ፤አረሚም፡ጥበብን፡ይሻሉ፡ብሎ፡
እንደ፡ተናገረ።

፬፤ እኛ፡ግን፡የተሰቀለውን፡**ክርስቶስን፡** እንሰብ
ካለን ፤ ይህም ፡ ለአይሁድ ፡ ዕንቅፋት ፡ ለአሕ
ዛብም፡ስንፍና፡ይሆንባቸዋል።

ልመናውና፡በረከቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና፡የስሩግ፡ኤጲስቆጶስ፡የሚሆን፡የተ
መሰገነ ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ ያዕቆብ ፡ ስለ ፡
መልአኩና፡ስለ፡ፈያታዊ፡ዘየማን፡የደረሰው፡
ድርሳን፡ይህ፡ነው፤አሜን።

፭፤ **የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡**
ርዳኝ ፤ የተአምራትህን ፡ ምሥጢሮች ፡
እገልጽ፡ ዘንድ ፡ ውስጣዊ ፡ አእምሮዬን ፡
ብሩህ፡ አድርግልኝ ፤ ትእዛዝህንም ፡ እሠራ ፡
ዘንድ፡አጽናኝ።

፮፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ በአንተ ፡ ጸንቶ ፡ በባሕር ፡
ላይ ፡ ሄደ ፤ ድንቆች ፡ የሆኑ ፡ ተአምራቶችህን ፡
መተርጐም ፡ እችል ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡
በአንተ፡ልጽና።

፯፤ ጌትነትህም ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤ ልዕልናህም ፡
እጅግ፡ግሩም፡ነው።

፰፤ **አቤቱ ፡** ሥራህ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ፤ ባሕ
ርይህም፡ፈጽሞ፡ጥልቅ፡ነው።

፱፤ እንግዲህ፡የትኛውን፡አስባለሁ?ወደ፡ልደትህ፡
ነውን፡ወይስ፡ወደ፡አመሰገኑህ፡ወደ፡እረኞች፡
ወይም ፡ በበረት ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ አመሰገኑህ ፡
መላእክት ፡ ወይስ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ወደ ፡
አመጡልህ፡የጥበብ፡ሰዎች፡አስባለሁን።

፲፤ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ ነውን ፡ ወይም ፡ አርፎ ፡ ይተኛ ፡
ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ ሰንብት ፡ የሚሻ ፡ በሞት ፡
ያንቀላፋ ፡ ዘንድ ፡ ወደሚለምንህ ፡ ወደ ፡
ሽማግሌው፡ስምዖን፡አስባለሁን።

፲፩፤ ዮሐንስ፡በሚያጠምቅህ፡ጊዜ፡የሆነውን፡አስ
ባለሁን ፡ ወይስ ፡ **አብ ፡** ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የእር
ሱንም ፡ መሥዋዕትነት ፡ የወደድሁት ፡ እያለ ፡
ምስክር፡የሆነውን፡አስባለሁን።

፲፪፤ የመካን፡ልጅ፡ዮሐንስ፡እጁን፡በራስህ፡ላይ፡

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ርእስከ ፡ እዜክር ፡ ወሚመ ፡ ሶበ ፡ ወረደ ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌከ ፡ በርእየተ ፡ ርግብ ፡
እኄሊ።
፱፡ ሶበ ፡ ተጸዋዕከኑ ፡ ውስተ ፡ ከብካብ ፡ ከመ ፡
ሰብእ፡እዜክር፡ወሚመ፡ሶበ፡አጥዐምከ፡ማየ፡
ወረሰይከ፡ወይነ፡እኄሊ።

፲፡ አመ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ርኀብከ ፡ በማእከለ ፡
ሕዝብ ፡ እዜክር ፡ ወሚመ ፡ ዘአጽገብከ ፡ እምኀ
ምስቱ ፡ ኀብስት ፡ ኀምሳ ፡ ምዕተ ፡ ብእሴ ፡
ዘእንበለ፡አንስት፡ወደቅ፡እኄሊ።
፲፩፡ አመ ፡ ጸርሐኑ ፡ ኀቤከ ፡ ዕውር ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
ተማሃለኒ ፡ እዜክር ፡ ወሚመ ፡ ዘጸገውከ ፡
ብርሃነ፡ይርአይ፡እኄሊ።
፲፪፡ አመ፡ኖምከኑ፡በውስተ፡ሐመር፡ከመ፡ሰብእ፡
እዜክር ፡ ወሚመ ፡ ሶበ ፡ ገሠጽከ ፡ ባሕረ ፡
ወነፋሳተ፡ወተአዘዙ፡ለከ፡እኄሊ።

፲፫፡ አመ ፡ ተሰባሕከኑ ፡ በዲበ ፡ ዕዋል ፡ እዜክር ፡
ወሚመ ፡ ሶበ ፡ ሰብሑከ ፡ አዕሩግ ፡ ወሕፃናት ፡
በነሚአ፡አዕጹቀ፡በቀልት፡እኄሊ።
፲፬፡ አመ፡መጽአ፡አይሁድ፡በአብትር፡ወበመጥ
ባሕት ፡ ኀቤከ ፡ እዜክር ፡ ወሚመ ፡ ሶበ ፡
አግባእከ ፡ እገዞ ፡ ለገብረ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡
እኄሊ።
፲፭፡ አመ ፡ ተሰቀልከኑ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡
እዜክር፡ ወሚመ ፡ ሶበ ፡ አንሥአ ፡ ቃልከ ፡
ሙታነ፡እምውስተ፡መቃብር፡እኄሊ።
፲፮፡ አመ ፡ ተረግዘኑ ፡ ገቦከ ፡ በኲናት ፡ እዜክር ፡
ወሚመ ፡ ሶበ ፡ ከሠተ ፡ ቃልከ ፡ አረፋቲሃ ፡
ለሲኦል፡እኄሊ።
፲፯፡ አመ፡ይኬልሉከኑ፡መላእክት፡በክነፊሆሙ፡
እምዕበየ ፡ ግርማከ ፡ እዜክር ፡ ወሚመ ፡
ዘተማለቁ፡ላዕሌከ፡አይሁድ፡እኄሊ።

፲፰፡ አመ ፡ ተፍእኑ ፡ ምራቀ ፡ እኩያን ፡ ሕዝብ ፡
ውስተ ፡ ገጽከ ፡ እዜክር ፡ ወሚመ ፡ ሶበ ፡
ሰፋሕከ፡ እራኀከ ፡ አኀዘ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡
እኄሊ።
፲፱፡ ሶበ ፡ ጸረተከኑ ፡ ዕፀ ፡ ድክምት ፡ እዜክር ፡
ወሚመ ፡ አመ ፡ ተንሥኡ ፡ ለስብሐቲከ ፡
ኵሎሙ፡ሠራዊተ፡መላእክት፡እኄሊ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

መጫኑን ፡ አስባለሁን ፡ ወይስ ፡ በላይህ ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡
መቀመጡን፡አስባለሁ።
፱፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መሆንህ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡
መጠራትህን ፡ አስባለሁን ፡ (አስታውሳ
ለሁን)፡ ወይስ ፡ ውኃውን ፡ አጣፍጠህ ፡ ጠጅ ፡
ማድረግህን፡አስባለሁ።
፲፡ በበረሀ፡ውስጥ፡በሕዝብ፡መካከል፡መራብህን፡
አስባለሁን ፡ ወይስ ፡ ከአምስት ፡ እንጀራ ፡
ከሴቶችና ፡ ከልጆች ፡ በቀር ፡ ለአምስት ፡ ሺህ ፡
ሰው፡ማጥገብህን፡አስባለሁ።
፲፩፡ ዓይነ ፡ ሥውሩ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡
አንተ ፡ መጮኹን ፡ አስባለሁን? ወይስ ፡ ያይ ፡
ዘንድ፡ብርሃን፡መስጠትህን፡አስባለሁ።
፲፪፡ በመርከብ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ማንቀላፋ
ትህን ፡ አስባለሁን? ወይስ ፡ ባሕሩን ፡ ነፋሱን ፡
መገሠፅህን ፡ እነሱም ፡ ለአንተ ፡ መታዘዛ
ቸውን፡አስባለሁ።
፲፫፡ በውርንጫ ፡ ላይ ፡ ሆነህ ፡ መመስገንህን ፡ አስባለ
ሁን? ወይስ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ሕፃናቱ ፡ የዘንባባ
ዝንጣፊ ፡ ይዘው ፡ ማመስገናቸውን ፡ አስባለሁ።
፲፬፡ አይሁድ ፡ ጎመድና ፡ ሾተል ፡ ይዘው ፡ መምጣታ
ቸውን ፡ አስባለሁን? ወይስ ፡ ለሊቀ ፡ ካህናቱ ፡
ባሪያ ፡ የተቆረጠ ፡ ጆሮውን ፡ ማዳንህን ፡
አስባለሁ።
፲፭፡ በእንጨት ፡ መስቀል ፡ መሰቀልህን ፡ አስባ
ለሁን? ወይስ ፡ ከመቃብር ፡ ውስጥ ፡ በቃልህ ፡
ሙታንን፡ማስነሣትህን፡አስባለሁ።
፲፮፡ ጐንህ፡በጦር፡መወጋቱን፡አስባለሁን? ወይስ፡
ቃልህ፡የሲኦልን፡ግድግዳዎቿን፡ማፍረሱን፡
አስባለሁ።
፲፯፡ ከመፈራትህ ፡ ልዕልና ፡ የተነሣ ፡ መላእክት ፡
በክንፋቸው ፡ መጋረዳቸውን ፡ አስባለሁን?
ወይስ ፡ አይሁድ ፡ በአንተ ፡ ላይ ፡ መዘባበታ
ቸውን፡አስባለሁ።
፲፰፡ ክፉዎች ፡ ሕዝቦች ፡ በፊትህ ፡ ላይ ፡ ምራቃ
ቸውን ፡ መትፋታቸውን ፡ አስባለሁን? ወይስ ፡
ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ የያዘውን ፡ መሐል ፡ እጅህን ፡
መቸንከርህን፡አስባለሁ።
፲፱፡ ደካማ ፡ እንጨት ፡ እንደ ፡ ተሸከመችህ ፡ አስባ
ለሁን? ወይስ ፡ ለምስጋናህ ፡ የመላእክት ፡
ሠራዊት፡ሁሉ፡መነሣታቸውን፡አስባለሁ።

Scanned by CamScanner

በ፮:ሰዓተ:መዓልት:ዘዓርብ።

፳ አመ : ትትኬነንኑ : በቅድመ : ኃጥአን :
አዘከር: ወሚመ : አመ : ይሴብሑከ : ወይዌ
ድሱከ:መላእክት:እንኢ።
፳፩ ሰዐ:ይፌደፍድ : ዝንቱ : ምሥጢር : እስመ :
ቅዱስ:ተሰቅለ:ዲበ:ዕፀ:መስቀል:እምኀበ:
ኃጥአን : ወየማነ : እዴሁ : አኃዘ : ኵሉ :
ተአስረ:እምኀበ:ዕልዋን።
፳፪ ወእራኅ:ዘፈጠረ:ኵሎ:በቅንዋት:ተቀነወ፤
ወአፍ : ዘፈጠሮ : ለአቡነ : አዳም : በቃሉ :
ከርቤ:ምስለ:ሐሞት:ቲሱሐ:ሰትየ።

፳፫ ወባሕቱ:ፈጸሙ:ላዕሌሁ:ኵሎ:ዘተነበዩ:
ነቢያት።
፳፬ ቀነውዎ : እደዊሁ : ወእገሪሁ : ወኍለቁ :
ኵሎ:አዕፅምቲሁ:ወተፍኡ:ምራቀ:ውስተ:
ገጹ።
፳፭ ወተማከሩ:ላዕሌሁ:ወተካፈሉ:አልባሲሁ:
ወተዐፀዉ:ዲበ:ዐራዙ።
፳፮ ሰማያት : አንከሩ : ወመላእክት : ደንገፁ :
እስመ : ንጉሥ : ቆመ : ውስተ : ዐውደ :
ኃጥአን: ዘሡራዊተ : መላእክት : ይቀውሙ :
ቅድሜሁ:ተሀውከ:መባርቅት:ከመ:ያማስ
ንዎሙ:ለኵሎሙ : እለ : ይነብሩ : ውስተ :
ዓለም።
፳፯ ደምፀ : ነጐድጓድ : ከመ : ያጥፍአሙ :
ለኵሎሙ:አሕዛብ።
፳፰ ወነደ:እሳት:ከመ:ይብልዮሙ:ለዐላውያን፤
ወአንቀልቀሉ:አድባር:እመሠረታቲሆሙ።

፳፱ ወነፍኀ:ነፋሳት:ውስተ:ኵሉ:ዓለም።
፴ ወለከፎ : ለዓለም : ጽልመት : ወጸልመ :
ብርሃን:ወኮነ:ሌሊተ:መንፈቀ:መዐልት።
፴፩ ኀልቀ:ብርሃን:ወነግሠ:ጽልመት:ተሰወረ:
ፀሐይ:ወኮነ:ሌሊተ።
፴፪ ይሁዳ:አግብአ:ቶማስ:ጐየ:ጴጥሮስ:ክህደ:
ተዘርዉ : አባግዕ : እግዝእትነ : ማርያም :
ላሐወት : ዮሐንስ : ይቀውም : እምርሑቅ፤
አድባር:ይበክዩ:ወጽልመት:ደፈና:ለኵላ:
ዓለም።
፴፫ አርድእት:ጐዩ:እምብዝኀ:ፍርሀት፤ወመላ
እክት:ሰማይ:አንከሩ:እንዘ:ያረምሙ።
፴፬ ደንገፁ : ሰማያውያን : ወምድራውያን፤

ዓርብ:መዓልት:በ፮:ሰዓት።

፳፤ በኃጥአን:ፊት:የተፈረደብህን:አስባለሁን?
ወይስ:መላእክት:ፈጽሞ:ማመስገናቸውን:
አስባለሁ።
፳፩፤ ይህ : ምሥጢር : በሚበዛ : ጊዜ : ከኃጥአን :
በተነሣው:ሁከት:ምክንያት:ጽኑዓ:ባሕርይ:
ወልድ: በዕንጨት:መስቀል:ተሰቀለ:እኩን፤
ሁሉን:የያዘ:ቀኝ:እጁ:በከዳተኞች:ታሰረ።
፳፪፤ ሁሉን:የፈጠረ:መሐል:እጅ:በችንካሮች:
ተቸነከረ ፤ በቃሉ : አባታችን : አዳምን :
የፈጠረ:አፍ:መራራ:ከርቤ:የተቀላቀለበት:
ሐሞትን:ጠጣ።
፳፫፤ ነቢያት : በእርሱ : ላይ : የተናገሩትን : ሁሉ :
ፈጸሙ:እንጂ።
፳፬፤ እጆቹን:እግሮቹን:ቸነከሩት፤አጥንቶቹንም:
ሁሉ : ቈጠሩ : ከፊቱ : ላይም : ምራቃቸውን :
ተፉ።
፳፭፤ በላዩ : ተማከሩ ፤ ልብሶቹንም : ተካፈሉ ፤
በቀሚሱ:ላይም:ዕጣ:ተጣጣሉ።
፳፮፤ በሰማያት : ያሉ : ፍጥረቶች : አደነቁ ፤ መላእ
ክትም : ደነገጡ ፤ የመላእክት : ሠራዊት :
በፊቱ : በፍርሃት : የሚቆሙለት : ሰማያዊ :
ንጉሥ : በኃጥአን : አደባባይ : ቆሚልና ፤
በዓለም : ውስጥ : የሚኖሩትን : ሁሉ : ያጠፉ
አቸው:ዘንድ:መባርቅት:ታወኩ።
፳፯፤ አሕዛብን : ሁሉ : ያጠፉቸው : ዘንድ :
ነጐድጓድ:ድምፅን:አሰማ።
፳፰፤ ከሐዲዎች : አይሁድን : ይበላቸው : ዘንድ :
እሳት : ነደደ ፤ ተራሮችም : ከመሠረታቸው :
ተነዋወጡ።
ነፋሳትም:በዓለም:ሁሉ:ነፈሱ።
፳፱፤ ዓለም : ጨለማ : ያዘው :
፴፤ መላውንም : ዓለም : ጨለማ : ያዘው :
ፀሐይም:ጨለመ፤ቀትርም:ሌሊት:ሆነ።
፴፩፤ ብርሃን : ጠፋ ፤ ጨለማም : ነገሠ ፤ ፀሐይ :
ብርሃኑን:ሰወረ፤ሌሊትም:ሆነ።
፴፪፤ ይሁዳ:አስያዘው፤ቶማስ:ሸሸ፤ጴጥሮስ:ካደ:
በጎቹ : ተበተኑ ፤ እመቤታችን : ማርያም :
አለቀሰች ፤ ዮሐንስም : ከሩቅ : ቆሞ : ነበር ፤
ልዑላኑ : አዘኑ ፤ ዓለምን : በመላዋ : ጨለማ :
ሸፈናት።
፴፫፤ ከፍርሃታቸው : ብዛት : የተነሣ : ሐዋርያት :
ሸሹ፤የሰማይ:መላእክት:በአርምሞ:አደነቁ።
፴፬፤ ሰማያውያንና : ምድራውያን : ፍጥረታት :

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወትቤሎሙ፡ማርያም፡እሙ፡ለብርሃን፡ለመላእክት፡እንዘ፡ትበኪ፡አ፡ገብርኤል፡ነዐ፡ረአዮ፡እንከ፡ለእግዚእከ፡ዘይሣለቁ፡ላዕሌሁ፡ሕዝበ፡አይሁድ፤ ወናሁ፡ቀነዉ፡እደዊሁ፡ወእገሪሁ።
፴፭፤ እመሰ፡አርድእት፡ጐዩ፡ወኀደግዎ፡ለንጉሥ፡ባሕቲቶ፡አንትሙኒ፡መንፈሳውያን፡ለምንት፡ኀደግምዎ።
፴፮፤ እመሂ፡መሬታውያን፡ፈርሁ፡ሞተ፡አንትሙኒ፡ሰማያውያን፡ለምንት፡ርኅቅሙ፡እምኔሁ።
፴፯፤ ብክሙ፡ተመዝበራ፡ሰዶም፡ወገሞራ፤ወእም ክነፊክሙ፡ወዕአት፡እሳት፡ወአውዐየቶሙ፡ለኵሎሙ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስቴቶን።
፴፰፤ እፎ፡ኢተነሥሡ፡በቀለ፡እግዚእክሙ፡እምነበ፡ዕልዋን፡ወመናፍቃን።
፴፱፤ ሙሴኒ፡ነቢይ፡ሐዘነ፡ለሕዝቡ፡ወሰአለ፡በእንቲአሆሙ፡ከመ፡ያድኅኖሙ፡እምግብጻውያን።
፵፤ ወአንትሙኒ፡ለምንት፡ጐንደይክሙ፡ወኢተቤቀሉ፡ፍጡነ።
፵፩፤ ደንገፁ፡ሠራዊተ፡መላእክት፡ወአርመመት፡እሳት።
፵፪፤ ወእግዚእ፡እሳት፡ተሰቅለ፡ዲበ፡ዕፅ፡ሰማያውያን፡ከደኑ፡ገጾሙ፡እምርእዮቱ፤ወመሬታውያን፡ይወርቁ፡ምራቀ፡ውስተ፡ገጹ፡ነቅዐ፡ኰኵሕ፡ወጽልሑተ፡ልቦሙ፡ለዕልዋን፡ኢተመይጠ።
፵፫፤ ተከሥቱ፡መቃብራት፡ወሰምዑ፡ምውታን፡ወእዘኒሆሙ፡ለከሀድያን፡ኢሰምዓ።
፵፬፤ አውሥአ፡መልአክ፡ወይቤላ፡ለእመ፡ብርሃን፡ኢትሕዝኒ፡ወኢትብክዪ፡አ፡ቅድስት፤ሶበሰ፡ኢፈቀደ፡እምኢተሰቅለ፡ወእምኢክህልዎ፡አላ፡በምሕረቱ፡ወበብዝኀ፡ፍቅሩ፡ወረደ፡እምልዑል፡ማኅደሩ።
፵፭፤ ወኮነ፡ሰብአ፡ወበሥምረቱ፡አስተርአየ፡ዲበ፡ምድር፡ከመ፡ያድኅኖ፡ለአዳም፡ወለዘርዑ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

ደነገጡ፤የብርሃን፡እናት፡ማርያምም፡እያለ ቀሰች፡መላእክትን፡ተናገረቻቸው፡ገብርኤል፡ሆይ፡የአይሁድ፡ሕዝብ፡የሚዘብቱበትን፡ጌታህን፡ና፡እየው፤እነሆ፡እጆቹንና፡እግሮቹን፡ቸንከረውታልና።
፴፭፤ ንጉሡን፡ብቻውን፡ትተው፡ፈርተው፡ሐዋርያት፡ቢሸሹ፡እናንተ፡ረቂቃን፡መላእክት፡ለምን፡ተዋችሁት።
፴፮፤ መሬታውያኑ፡ሞትን፡ቢፈሩ፡እናንተ፡ሰማያውያን፡መላእክት፡ከእርሱ፡ለምን፡ራቃችሁ።
፴፯፤ ሰዶምና፡ገሞራ፡የጠፉት፡በእናንተ፡ኃይል፡አይደለምን? ከክንፋችሁም፡እሳት፡ወጥታ፡በውስጣቸው፡የሚኖሩትን፡ሁሉ፡አቃጠለቻቸው።
፴፰፤ ከወንጀለኞቹና፡ከከሀዲዎቹ፡ዘንድ፡የጌታችሁን፡በቀል፡እንዴት፡አትመልሱም።
፴፱፤ ነቢዩ፡ሙሴም፡እንኳን፡ለወገኖቹ፡ራርቶ፡ከግብጻውያን፡እጅ፡ያድናቸው፡ዘንድ፡ለመነ።
፵፤ እናንተስ፡ለምን፡ዘገያችሁ፤ፈጥናችሁ፡አትበቀሉምን።
፵፩፤ የመላእክት፡ሠራዊት፡ደነገጡ፤እሳትም፡ዝም፡አለች፤ማለት፡(የእሳታውያን)፡መላእክት፡ቁጣ፡በጌታ፡ምሕረት፡ተያዘ፡ማለት፡ነው።
፵፪፤ የእሳት፡ፈጣሪ፡በዕንጨት፡ላይ፡ተሰቀለ፤ሰማያውያን፡እርሱን፡እንዳያዩ፡ፊታቸውን፡ሸፈኑ፤ምድራውያን፡ግን፡በፊቱ፡ላይ፡ምራቅን፡ይተፉበት፡ነበር፤ዐለት፡ተሰነጠቀ፤የዐመፀኞች፡ልብ፡ከሽንገላ፡አልተመለሰም።
፵፫፤ መቃብሮች፡ተከፈቱ፤ሙታኖችም፡ሰሙ፤የከሀድያን፡ጆሮዎችም፡አልሰሙም።
፵፬፤ መልአኩም፡ለብርሃን፡እናት፡መለሰላት፤እንዲህም፡አላት፤ቅድስት፡ሆይ፡አትዘኝ፤አታልቅሺም፤ፈቃዱስ፡ባይሆን፡ኑሮ፡ባልተሰቀለ፤ሊሰቅሉትም፡ባልቻሉ፡ነበር፤በይቅርታውና፡በፍቅሩ፡ብዛት፡ከልዕልናው፡ወረደ እንጂ።
፵፭፤ ሰውም፡ሁኖ፡በፈቃዱ፡በምድር፡ላይ፡ተገለጠ፡ታየ፡አዳምንና፡ልጆቹን፡ያድን፡ዘንድ።

በ፰፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ለኪ ፡ እብለኪ ፡ እ ፡ ቅድስት ፡ ወንጽሕት ፡
ወልድኪ፡በሞቱ፡አዕርዐ፡ሞተ፡እምውሉደ፡
አዳም።
በሞቱ፡ለወልድኪ፡ተርኅዋ፡አናቅጸ፡ሲኦል፡
ወተፈትሐ ፡ ማእሰሪሃ ፡ ለኃጢአት ፤ ወአው
ፅአሙ ፡ ለፂውዋን ፡ እ ፡ ወላዲተ ፡ ብርሃን ፤
ሶበሰ፡ ኢሠምረ ፡ እምኢጾረቶ ፡ ዕፅ ፡ ወሶበ ፡
ኢፈቀደ፡እምኢሞተ።

ሙታነ፡አሕየወ፡አዕይተ፡ዕውራን፡ከሠተ።

ወሶበ፡ኢሠምረ፡እምኢተቀነወ፡በቅንዋት።

አለ፡ለምጽ ፡ አንጽሐ ፡ ወምራቀ ፡ ርኩሳን ፡
ዲበ፡ገጹ፡ተወክፈ።
ለፈርዖን፡ወለሠራዊቱ፡አስጠሞሙ፡ውስተ፡
ባሕር፡ወእከዮሙ፡ለዐማጽያን፡ተዐገሠ።
ለማይ፡ረሰዮ፡ወይነ፡ጥዑመ፡ወበዲበ፡ዕፀ፡
መስቀል፡ብሒአ፡ዘምስለ፡ሐሞት፡ሰትየ።

ለማዕበለ፡ባሕር፡አርመሞ፡ወእከዮሙ፡ለዐማ
ፅያን፡ተዐገሠ።
ፀሐየኒ፡አጽለመ፡ወቀታልያን፡ኢተቀየመ።

ኰኵሐ ፡ አንቅዐ ፡ ወአልባቢሆሙ ፡ ለመና
ፍቃን፡ደንገፁ።
ሠራዊተ ፡ ሰማያውያን ፡ አርዐደ ፡ ወመሬታ
ውያን፡ድኩማን፡እሮ፡ይመውእዎ።

ሶበ ፡ ጸርሐ ፡ ንጉሥ ፡ እምዲበ ፡ መስቀል ፡
ወድቁ፡ ኵሎሙ ፡ ፍጥረታት ፡ ሶበ ፡ ሰምዑ ፡
ለመንፈስ፡ቅዱስ፡ ቃሎ።

ወተሠጠ፡መንጦላዕተ፡ምኵራብ፡ወጸልመ፡
ብርሃን፡መዐልት፡ወነግሠ፡ጽልመት።
ደንገፀ፡ሞት፡ፈርሀ፡ፀራዊ፡ወወድቀ፡በገጹ፤
ተከሥቱ ፡ መቃብራት ወተንሥኡ ፡
ምውታን።
ወተነሥቱ ፡ አረፋቲሃ ፡ ለሲኦል ፡ ወወፅኡ ፡
ሙቁሐን፡እምውስተ፡ጽልመት።
ሶቤሃ ፡ አስተርአየ ፡ ብርሃን ፡ ለፈያታይ ፡
ወነሥአ ፡ አክሊለ ፡ መዊእ ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ ፡
ሕዝበ፡አይሁድ፡ይቀውሙ።
ጸርሐ፡ፈያታይ፡ኀበ ክርስቶስ፡እንዘ፡ይብል፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

፵፮፤ ቅድስት ፡ ንጽሕት ፡ ሆይ ፡ እንቺን ፡ እነግር
ሻለሁ ፤ ልጅሽ ፡ በሞቱ ፡ ከአዳም ፡ ልጆች ፡
ሞትን፡አጠፋ።
፵፯፤ በልጅሽ፡ሞትም፡የሲኦል፡ደጆች፡ተከፈቱ፤
የኃጢአት ፡ ማሰሪያም ፡ ተፈታ ፤ የብርሃን ፡
እናት ፡ ሆይ ፡ ተማርከው ፡ የነበሩትንም ፡
አወጣቸው ፤ ፈቃዱስ ፡ ባይሆን ፡ ኑሮ ፡
ዕንጨት፡ ባልተሸከመችውም ፤ ባልሞተም ፡
ነበር።
፵፰፤ ሙታንን ፡ አስነሣ ፤ የዕውሮችን ፡ ዓይን ፡
አበራ።
፵፱፤ ባይፈቅድስ ፡ ኑሮ ፡ በችንካሮች ፡ ባልተቸነ
ከረም፡ነበር።
፶፤ ለምጻሞችን ፡ አነጻ ፤ የርኩሳንን ፡ ምራቅ ፡
በፊቱ፡ተቀበለ።
፶፩፤ ፈርዖንና፡ሠራዊትን፡በባሕር፡አሰጠመ፤የዐ
መፀኞችን፡ክፋት፡ግን፡ታገሠ።
፶፪፤ ውኃውን፡ጣፋጭ፡ጠጅ፡አደረገ፤በዕንጨት፡
መስቀል፡ሁኖ፡መጻጻውን፡ከሐሞት፡ጋራ፡
ጠጣ።
፶፫፤ የባሕሩን፡ማዕበል፡ጸጥ፡አደረገው፤የዐመፀ
ኞችን፡የክፋት፡ማዕበል፡ታገሠ።
ፀሐይን፡አጨለመ፤ገዳዮቹን፡ግን፡አልተቀ
የመም።
፶፬፤ ዐለቱን፡ሰነጠቀ፤የመናፍቃንም፡ልቡናቸው፡
ተሸበረ።
፶፭፤ ሰማያውያን፡የመላእክት፡ሠራዊትን፡አንቀ
ጠቀጠ፤ ድኩማን፡መሬታውያን፡እንዴት፡
ያሸንፉታል።
፶፮፤ ንጉሥ ፡ ክርስቶስ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡
ድምፁን ፡ ባሰማ ፡ ጊዜ ፡ የረቂቅ ፡ መለኮትን ፡
ድምፅ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ፍጥረቶች ፡ ሁሉ ፡
ወደቁ።
፶፯፤ የቤተ ፡ መቅደሱ ፡ መጋረጃ ፡ ተቀደደ ፤ የቀኑ ፡
ብርሃን፡ጨለማ፡ሆነ፤ጨለማውም፡ሠለጠነ።
፶፰፤ ሞት ፡ ደነገጠ ፤ ጠላት ፡ ዲያብሎስም ፡ ፈራ ፤
ተሸበረ ፤ በግንባሩም ፡ ተደፋ ፤ መቃብሮች ፡
ተከፈቱ፤ሙታንም፡ተነሡ።
፶፱፤ የሲኦልም ፡ ግድግዳዎች ፡ ፈራረሱ ፤ እስረ
ኞችም፡ከጨለማው፡ውስጥ፡ወጡ።
፷፤ ያን፡ጊዜ፡ፈያታዊ፡ዘየማን፡ብርሃን፡ታየው፤
የአይሁድ፡ሕዝብ፡ቁመው፡ሳሉ፡የድል፡አድ
ራጊነትን፡ዘውድ፡ተቀዳጀ።
፷፩፤ ፈያታዊ፡ዘየማን፡በመንግሥትህ፡በመጣህ፡

Scanned by CamScanner

በ፯፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

በ፯፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ። ተዘከረኒ፡እግዚኦ፡አመ፡ትመጽእ፡በመንግ
ሥትከ።
አብርሀ፡ማኅቶቱ፡ለፈያታይ፡ወበጽንዐ፡
ሃይማኖቱ፡ሞፆ፡ለብርሃን፡ፀሐይ።
፳፱፡ ወሶበ፡ሞአ፡ፈድፋደ፡መፀቶሙ፡ለከሐ
ድያን፡አይሁድ፡ከመ፡ማዕበለ፡ባሕር፡ጸርሐ፡
ፈያታዊ፡ኀበ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
እንዘ፡ይብል፡ተዘከረኒ፡እግዚኦ፡በውስተ፡
መንግሥትከ፡ወበትንሣኤከ፡እንዘ፡ሀለወ፡
እግዚእ፡ዕሩቆ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ወአልቦ፡
ሠራዊተ፡መላእክት፡ወኢ፡ሠረገላተ፡
ኪሩቤል፡ወአልቦ፡ስብሐት።

፴፡ በርሃ፡አዕይንተ፡ልቡ፡ለፈያታዊ፡ወበጽንዐ፡
ሃይማኖቱ፡ፈያታይ፡ይቤ፡ተዘከረኒ፡እግዚኦ፡
በውስተ፡መንግሥትከ።
፴፩፡ ፈያታዊ፡በትሕትናሁ፡ርእየ፡ኀበ፡ክርስቶስ፡
ወአኮ፡በስብሐት፡ዘያስተርኢ፡እምኔሁ፡
በዕለተ፡ትንሣኤ።
፴፪፡ ኀሠሠ፡እምኔሁ፡ሣህለ፡ወምሕረተ፡ወይቤ፡
ተዘከረኒ፡እግዚኦ፡አመ፡ትመጽእ፡በመንግ
ሥትከ።
፴፫፡ በጽሐት፡ስእለቱ፡ውስተ፡ሰማይ፡ወበጽንዐ፡
ገዐሩ፡ይቤ፡አርኅ፡ሊተ፡እግዚኦ፡አንቀጸ፡
ምሕረትከ፡ኢትግድፈኒ፡ወኢትመንነኒ፡
ወአብእኒ፡ውስተ፡ገነተ፡ትፍሥሕት።
፴፬፡ ሀበኒ፡እግዚኦ፡ስብሐተ፡ሐዲስ፡ርድአኒ፡
እግዚኦ፡በብዝኀ፡ሣህልከ።
፴፭፡ ጸግወኒ፡እግዚኦ፡ሀብተ፡ሰማያዊተ፡
እመዝገበ፡ምሕረትከ፡ዘኢየኀልቅ፤ወኢት
ዝክር፡ሊተ፡አበሳየ፡ወኃጢአትየ፡ዘትካት።
፴፮፡ አሌ፡ሊተ፡ለነዳይ፡ዘቦእኩ፡ዐጸደ፡ወይንከ፡
በዐሥርቱ፡ወአሐዱ፡ሰዓት፡ተሣሃለኒ፡
እግዚኦ፡በከመ፡ዕበየ፡ሣህልከ።

፵፡ ናሁ፡እለሰ፡ተቀንዩ፡እምጽባሕ፡እስከ፡
ሠርክ፡ይከውኑ፡ድልዋነ፡ይንሥኡ፡
ዐስበሙ፡ወአንሰ፡ኢተቀነይኩ፡እምዕለት፡
እንበለ፡አሐቲ፡ሰዓት።
፵፩፡ ደምረኒ፡እግዚኦ፡ምስለ፡እለ፡ተቀንዩ፡
እምጽባሕ፡እስከ፡ሠርክ፡ዘእንበለ፡ኀፍረት፡
ይንሥኡ፡ዐስበሙ።
፵፪፡ ወአንሰ፡እግዚኦ፡ጐንደይኩ፡እስከ፡ይመሲ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፯፡ሰዓት።

ጊዜ፡አስበኝ፡እያለ፡ወደ፡ፈጣሪ፡ክርስቶስ፡
ጮኸ።
የፈታያዊ፡ዘየማን፡ሃይማኖቱ፡ተገለጠ፤በሃይ
ማኖቱም፡ጽናት፡የፀሐይን፡ብርሃን፡አቸነፈ።
፳፱፡ የከሀድያን፡አይሁድ፡ቁጣን፡እንደ፡ባሕር፡
ማዕበል፡በአቸነፈ፡ጊዜ፡በጌትነትህና፡በትን
ሣኤህ፡አስበኝ፡እያለ፡ወደ፡ጌታችን፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጮኸ፤ጌታችን፡
በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡ዕራቁቱን፡
ተሰቅሎ፡እያለ፡ያን፡ጊዜ፡የመላእክት፡
ሠራዊትን፡ወይም፡ኪሩቤል፡የሚሸከ
ሙትን፡መንበር፡አላየም፤የባሕርይ፡
ክብሩንም፡አላየም።
፴፡ የፈያታዊ፡ዘየማን፡ውስጣዊ፡አእምሮው፡
በራ፤በሃይማኖቱም፡ጽናት፡አቤቱ፡በጌት
ነትህ፡አስበኝ፡አለ።
፴፩፡ ፈያታዊ፡ዘየማን፡ጌታችን፡ክርስቶስን፡በት
ሕትናው፡አየው፤በትንሣኤው፡በሚገለ
ጥበት፡በባሕርይ፡ክብሩ፡አይደለም።
፴፪፡ ከእርሱም፡ይቅርታንና፡ምሕረትን፡ፈለገ፤
በጌትነትህ፡በምትመጣ፡ጊዜ፡አቤቱ፡
አስበኝ፡አለ።
፴፫፡ ልመናውም፡ወደ፡ሰማይ፡ደረሰች፤
በጩኸቱም፡ጽናት፡አቤቱ፡የምሕረትህን፡
ደጅ፡ክፈትልኝ፤ፊጽመህ፡አትጣለኝ፤ተድላ፡
ደስታ፡ወደ፡አለባት፡ገነት፡አስገባኝ፡አለ።
፴፬፡ አቤቱ፡አዲስ፡ክብርን፡ስጠኝ፤በይቅርታህ፡
ብዛት፡አድነኝ።
፴፭፡ ከማያልቀው፡ከቸርነትህ፡መዝገብ፡አቤቱ፡
ሰማያዊ፡ሀብትን፡ስጠኝ፤የቀድሞውን፡
በደሌንና፡ኃጢአቴን፡አታስብብኝ።
፴፮፡ ከምግባር፡ከትሩፋት፡ድኃ፡ለሆንኩት፡ለእኔ፡
ወዮልኝ፤በአሥራ፡አንድ፡ሰዓት፡ወደ፡
ወይንህ፡ቦታ፡የገባሁትን፡እንደ፡ይቅርታህ፡
ገናናነት፡ይቅር፡በለኝ።
፵፡ በወይኑ፡ቦታ፡ከጥዋት፡እስከ፡ማታ፡የተገ
ያገለገሉ፡ደመወዛቸውን፡ለመውሰድ፡የተገ
ባቸው፡ዝግጁዎች፡ይሆናሉ፤እኔ፡ግን፡
ከቀኑ፡ያለ፡አንዲት፡ሰዓት፡አላገለገልኩም።
፵፩፡ ከጥዋት፡እስከ፡ማታ፡ከአገለገሉትና፡
ዋጋቸውን፡ያለ፡ማፈር፡ከሚቀበሉት፡ጋራ፡
አቤቱ፡አንድ፡አድርገኝ።
፵፪፡ እኔም፡አቤቱ፡እስከሚመሽ፡ቆይቼአለሁ፡

Scanned by CamScanner

በ፲፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

አላ፡ባሕቱ፡ይብጽሐኒ፡ሣህልከ፡ወምሕረትከ፡ሶበ፡ትሁብ፡ዐስቦሙ፡ለእለ፡ተቀንዩ፡እምቅድሜየ።

፷፫ አቅድም፡ሊተ፡ውሂበ፡እግዚኦ፡ከመ፡ይትፌሥሑ፡ቀደምት፡እለ፡ተቀንዩ፡እምቅድሜየ።

፷፬ እ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ናሁ፡ጸመውኩ፡ምስሌከ፡ጸውዐኒ፡ውስተ፡ከብካብከ፡ሰማያዊ።

፷፭ አስመ፡አንተ፡ትቤ፡እግዚኦ፡አመ፡ወፃእከ፡ትኅሥሥ፡ዘተገድፈ፡ኢመጻእኩ፡እጸውዕ፡ጻድቃነ፡አላ፡ኃጥአነ፡ለንስሓ።

፷፮ ናሁ፡አነ፡ተገደፍኩ፡አንሥአኒ፡እምድቀትየ፡ከመ፡እኩን፡አርአያ፡ለኵሎሙ፡እለ፡ይፈቅዱ፡ንስሓ፡ወይትፌሥሑ፡በኃጥእ፡ሶበ፡ይኔስሕ፡ኀቤከ።

፷፯ እመን፡ብየ፡እግዚእየ፡በቅድመ፡አቡከ፡ዘበሰማያት፡እስመ፡አመንኩ፡ብከ፡በቅድመ፡ሠራዊተ፡ቀያፋ።

፷፰ ኢታርኅቀኒ፡እግዚኦ፡አመ፡ይቀውሙ፡ቅድሜከ፡ኵሉ፡ፍጥረት።

፷፱ አንሰ፡ነዳይ፡ወኃጥእ፡ወአባሲ፡ለሞት፡ተመጦኩ፡ወበከመ፡ጌጋይየ፡ተሰቀልኩ፡ዲበ፡ዕፅ፡ወአንሰ፡በእንተ፡ጕሕሉትየ፡ወቀቲሎትየ፡ኮንኩ፡ድልወ፡ለሞት፡ወእሞት፡ወረድኩ፡ውስተ፡ሕይወት።

፸ አንሰ፡ነበርኩ፡ኵሎ፡መዋዕለ፡ሕይወትየ፡ውስተ፡ጽልመት፡ወኃጢአት፡ወበተፍጻሜተ፡ዕለትየ፡አስተርአየ፡ሊተ፡ብርሃን።

፸፩ አስአለከ፡እግዚኦ፡ወአስተበቍዓከ፡ወአኃሥሥ፡እምነ፡ኂሩትከ፡ከመ፡ትዘከረኒ፡በዐቢይ፡ዕለት፡አመ፡ትመጽእ፡በመንግሥትከ።

፸፪ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ለፈያታዊ፡ወይቤሎ፡በከመ፡ትቤ፡አሜን፡አሜን፡እብለከ፡ከመ፡ዮም፡ትሄሉ፡ምስሌየ፡ውስተ፡ገነት፡ትፍሥሕት፡ወትትፌሣሕ፡ምስሌየ።

፸፫ አመነኒ፡አ፡ብእሲ፡ናሁ፡ሀሎከ፡አንተ፡ውስተ፡ጽልመት፡ወልሳንከ፡ይነብብ፡ቃለ፡ፍሬ፡ሰብሐት፡ዲበ፡ማዕደ፡ሕይወት፡ምስለ፡አብርሃም።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ከእኔ፡በፊት፡ሲያገለግሉ፡ለዋሉ፡ዋጋቸውን፡በምትሰጥ፡ጊዜ፡ይቅርታህና፡ቸርነትህ፡ትደረግልኝ።

፷፫፤ አቤቱ፡ለእኔ፡ዋጋ፡መስጠትን፡አስቀድሞ፤ ከእኔ፡በፊት፡ሲያገለግሉ፡የዋሉ፡ደስ፡ይላቸው፡ዘንድ።

፷፬፤ አቤቱ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ከአንተ፡ጋራ፡መከራ፡ስቀበል፡ደከምሁ፡ወደ፡ሰማያዊ፡ሠርግህ፡ጥራኝ።

፷፭፤ አቤቱ፡የጠፋውን፡ትፈልግ፡ዘንድ፡በወጣህ፡ጊዜ፡ጻድቃንን፡ልጠራ፡አልመጣሁም፤ ኃጥአንን፡ወደ፡ንስሐ፡ልጠራ፡ነው፡እንጂ፡ብለሃልና።

፷፮፤ እነሆ፡እኔ፡ተጥያለሁ፤ ንስሐ፡ለሚፈልጉ፡ሁሉ፡አርአያ፡እሆን፡ዘንድ፡ከወደቅሁበት፡አንሣኝ፤ በኃጢአተኛው፡ንስሐ፡መግባት፡በአንተ፡ዘንድ፡ደስ፡ይበላቸው።

፷፯፤ ጌታዬ፡ሆይ፡በሰማያት፡በአባትህ፡ፊት፡እመነኝ፤ በቀያፋ፡ሠራዊት፡ፊት፡አምኜብሃለሁና።

፷፰፤ ፍጥረቱ፡ሁሉ፡በፊትህ፡በሚቆሙ፡ጊዜ፡አቤቱ፡አታርቀኝ።

፷፱፤ እኔ፡ከበጎ፡ሥራ፡ድኃ፡የሆንኩ፡ለሞት፡የተሰጠሁ፡በደለኛ፡እንደ፡በደሌ፡በዕንጨት፡ላይ፡ተሰቀልኩ፤ እኔም፡በማታለሌና፡ነፍሰ፡ገዳይ፡በመሆኔ፡ለሞት፡የተገባሁ፡ሆንኩ፤ ከሞትም፡ወደ፡ሕይወት፡ሄድሁ።

፸፤ እኔ፡መላ፡ዘመኔን፡በኃጢአትና፡በጨለማ፡ውስጥ፡ኖርኩ፤ በመጨረሻዪቱ፡ቀኔ፡ግን፡ብርሃን፡ተገለጸልኝ።

፸፩፤ አቤቱ፡እለምንሃለሁ፡እማልድሃለሁም፤ በታላቂቱ፡ቀን፡በጌትነትህ፡በመጣህ፡ጊዜ፤ ታስበኝ፡ዘንድ፡ከቸርነትህ፡እሻለሁ።

፸፪፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡ለፈያታዊ፡መለሰለት፤ አንተ፡እንዳልክ፡ይሁንልህ፤ ተድላ፡ደስታ፡በሚደረግበት፡በገነት፡ዛሬ፡ከእኔ፡ጋራ፡እንደምትኖር፡ደስ፡እንደሚልህም፡እውነት፡እውነት፡እልሃለሁ።

፸፫፤ አንተ፡ሰው፡ሆይ፡እመነኝ፡እነሆ፡አንተ፡በጨለማ፡ውስጥ፡አለህ፤ እንደበትህ፡ግን፡ከአብርሃም፡ጋራ፡በሕይወት፡ማዕድ፡ላይ፡ክብር፡ያለውን፡ፍሬ፡ቃል፡ይናገራል።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፬፡ ናሁ ፡ አንተ ፡ ውስተ ፡ ደመና ፡ ጽልመት ፡ ሠረቀ፡ብርሃን፡ማኅቶትከ፡ውስተ፡ከብካበ፡ ሕይወት።
፳፭፡ ምስለ ፡ መላእክት ፡ ትትፌሣሕ ፡ እስመ ፡ እዘኒከ ፡ ሰምዓ ፡ ቃለ ፡ ዕርፈት ፡ ምስለ ፡ ሠራዊተ፡ብርሃን፡አስተፌሥሐከ፡በእንተ፡ ዘአመንከ፡ወአስተኀፈርከ፡ሠራዊተ፡ቀያፋ፡ ወካህናቶሙ ፡ ለአይሁድ ፡ አክሊለ ፡ ክብር ፡ ዘውስተ፡ገነት፡አስተቄጸለከ።
፳፮፡ ለከ፡እብለከ፡አ፡ብእሲ፡ንሣእ፡መራኁተ፡ ብርሃን፡ወሑር፡ውስተ፡ገነተ፡ትፍሥሕት፡ ወጺሕ፡ፍኖቶ፡ለንጉሠ፡ብርሃን።
፳፯፡ ተጸዐን ፡ ዲበ ፡ ነፋሳት ፡ ወኅልፍ ፡ እንተ ፡ ባሕረ፡እሳት፡በማእከለ፡ነበልባል፡ዘእንበለ፡ ፍርሃት።
፳፰፡ ንግሮሙ፡ለኵሎሙ፡ሠራዊተ፡መላእክት፡ ወስብክ፡መዊአ፡ወዝራዕ፡ውስተ፡ገነት፡ ቃለ፡ሰላም።
፳፱፡ ወዜኑ፡ከመ፡አዳም፡ዕልው፡ናሁ፡ገብአ፡ ውስተ፡ዘቀዳሚ፡ንብረቱ።
፴፡ ወእመሂ ፡ ረከበከ ፡ ሠራዊተ ፡ መላእክት ፡ በውስተ፡ፍኖትከ፡ኢትፍራህ፡እምኔሆሙ፡ እስመ፡እሙንቱ፡ይትፌሥሑ፡በመጽሐፈ፡ መልእክትከ፡ወይጸውሩከ፡በክንፈሆሙ።
፴፩፡ ወእምዝ ፡ ጸሐፈ ፡ እግዚእነ ፡ ለፈያታይ ፡ መጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ ወኅተማ ፡ በደሙ ፡ ክቡር፡ለይእቲ፡መጽሐፍ።
፴፪፡ ወተጠምቀ ፡ ፈያታይ ፡ በደሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወርእየ፡ሕይወተ፡ወተዐጽፈ፡ብርሃነ።
፴፫፡ ተኀፅበ ፡ ፈያታይ ፡ በጥምቀት ፡ ዘቱሱሕ ፡ በደም፡ወማይ፡ወለብሰ፡ብርሃነ፡ወግርማ።
፴፬፡ ነሥአ፡መራኁተ፡ገነት፡ወይእተ፡መጽሐፈ፡ ወኀለፈ፡እንተ፡ባሕረ፡እሳት፡ወኢያውዐዮ፡ ነበልባል።
፴፭፡ ወሶበ፡በጽሐ፡ማእከለ፡ፍኖተ፡እሳት፡ረከቦ፡ መልአክ፡ወሐተቶ፡በቍጥዓ፡ወይቤሎ፡ንግረኒ፡ አ፡ብእሲ፡መኑ፡አንተ፡ወእምአይቴ፡መጻእከ፤ ወውስተ፡ፍኖተ፡እሳት፡እፎ፡ኀለፍከ።
፴፮፡ ወነፋሳት፡እፎ፡ጸሩከ፡በክንፈሆሙ፡በውስተ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፳፬፡ እነሆ ፡ አንተ ፡ በጨለማ ፡ ደመና ፡ ውስጥ ፡ ነበርህ ፤ የሃይማኖትህ ፡ ብርሃን ፡ ግን ፡ በሕይወት፡ሥርግ፡ቤት፡ውስጥ፡በራ።
፳፭፡ ከመላእክት ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይልሃል ፤ ጆሮችህ ፡ የስድብ ፡ ቃልን ፡ ሰምተዋልና ፤ ከብርሃን ፡ ሠራዊት ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ አመንክብኝና ፡ የቀያፋን፡ ሠራዊትና ፡ የአይሁድንም ፡ ካህናቶቻቸውን ፡ ስለ ፡ አሳፈርሃቸው ፡ ደስ ፡ አሰኘሃለሁ ፤ በገነት ፡ የሚገኘውን ፡ የክብር ፡ ዘውድ፡አቀዳጅሃለሁ።
፳፮፡ አንተ ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ አንተን ፡ እልሃለሁ፤ የብርሃን ፡ መክፈቻ ፡ ውሰድ ፤ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ወደሚገኝባት ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ሂድ ፤ ለብርሃን ፡ ንጉሥም፡መንገዱን፡ጥረግ።
፳፯፡ በነፋሳትም ፡ ላይ ፡ ተቀመጥ ፡ ያለ ፡ ፍርሃት ፡ የእሳቱን ፡ ባሕር ፡ በነበልባሉ ፡ መካከል ፡ ተሻገር።
፳፰፡ ለመላእክት ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ ንገራቸው ፡ ድሉንም ፡ ስበክ ፤ በገነት ፡ ውስጥም ፡ የሰላምን፡አዋጅ፡ንገር።
፳፱፡ ወንጀለኛው ፡ አዳምም ፡ ወደ ፡ ቀድሞ ፡ መኖሪያው፡እንደ፡ተመለሰ፡ንገራቸው።
፴፡ በመንገድህም ፡ የመላእክትን ፡ ሠራዊት ፡ ብታገኝ ፡ ከእነርሳቸው ፡ አትፍራ ፤ እነርሱ ፡ በያዝከው ፡ መልዕክት ፡ ደስ ፡ ይላቸዋልና ፤ በክንፎቻቸውም፡ይሸከሙሃል።
፴፩፡ ከዚህም፡በኋላ፡ጌታችን፡ለፈያታዊ፡የሕይወት፡ መጽሐፍን፡ጻፈ፤ያቺንም፡መጽሐፍ፡በክቡር፡ ደሙ፡አተማት፤አከበራት።
፴፪፡ ፈያታዊም ፡ በጌታችን ፡ ደም ፡ ከበረ ፤ ሕይወትንም፡አገኘ፤ልጅነትንም፡ተቀበለ።
፴፫፡ ከጌታ ፡ ጐን ፡ በፈሰሰው ፡ ደምና ፡ ውኃ ፡ በመጠመቅ ፡ ፈያታዊ ፡ ነፃ ፤ ብርሃንና ፡ ክብር ፡ ያላትንም፡ልጅነት፡ተጎናጸፈ።
፴፬፡ የገነትን ፡ መክፈቻ ፡ ያችንም ፡ መጽሐፍ ፡ ተቀብሎ ፡ የእሳቱን ፡ ባሕር ፡ ተሻገረ ፤ ነበልባሉም፡አላቃጠለውም።
፴፭፡ ከእሳቱ ፡ መካከል ፡ ካለው ፡ መንገድ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ መልአክ ፡ አገኘው ፤ በቁጣ ፡ መረመረው ፤ አንተ ፡ ማን ፡ ነህ? ንገረኝ ፤ ከወዴትስ ፡ መጣህ? በእሳቱ፡ውስጥስ፡እንደምን፡አለፍክ? አለው።
፴፮፡ ነፋሳቱስ፡በቃጠሎው፡ውስጥ፡እንዴት፡በጎይ

| በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት። |
|---|---|
| ላዕለ፡ወኢያውዐየ፡ድካመከ። | ላቸው ፡ ተሸከሙህ? ደካማ ፡ አንተንስ ፡ እንዴት፡አላቃጠለህም። |
| ፲፯ አፎ፡ኀለፍከ፡ባሕረ፡እሳት፡ወሚመ፡መልከ ጼዴቅ፡ዘአቀበ፡ትእዛዞ፡ወተሰምየ፡ካህኑ፡ ለእግዚአብሔር፡ወኢያውዐዩከ፡መዋግዲሃ፡ መኑ፡ውእቱ፡ዘአጽንዐከ፡ላዕለ፡ባሕረ፡እሳት፡ ዘንወኒ፡ኦ፡ብእሲ። | ፲፯፤ የእሳቱን ፡ ባሕር ፡ እንዴት ፡ አለፍክ? ወይም ፡ ትእዛዙን፡የጠበቀ፤ የእግዚአብሔር ፡አገልጋይ፡ የተባለ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ አንተ ፡ ነህን? የማዕ በሎቿ ፡ ነበልባል ፡ እንዴት ፡ አላቃጠሉህም ፤ በእሳቱ፡ባሕር፡ላይ፡ሥልጣን፡የሰጠህ፡ማነው? አንተ፡ሰው፡ሆይ፡እስቲ፡ንገረኝ። |
| ፲፰ ወአፎ፡ዐዲወ፡ዐባይ፡ባሕር፡መደንግፅት፡ ኢፈራህከ። | ፲፰፤ ታላቋን ፡ አስደንጋጭ ፡ የእሳት ፡ ባሕር ፡ መሻገርን፡እንዴት፡አልፈራህም። |
| ፲፱ አንተኑ፡ውእቱ፡አዳም፡ዘለሐኮ፡እግዚአ ብሔር፡በእዴሁ፡ወሚመ፡አንተ፡ሴት፡ ጻድቅ፡ዘብዙኅ፡መንክራቲሁ። | ፲፱፤ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡በእጁ ፡ የፈጠረው ፡ አዳም ፡ ነህን? ወይም ፡ ትሩፋቱ ፡ ብዙ ፡ የሆነ ፡ ጻድቁ፡ሴት፡ነህ። |
| ፳ አው፡አንተኑ፡ኖኅ፡ዘሞአ፡መዋግዲሁ፡ ለአይኅ፡ወበንጹሕ፡ቍርባኑ፡ዘአሥመሮ፡ለእ ግዚአብሔር። | ፳፤ ወይም ፡ የጥፋት ፡ ውኃ ፡ ማዕበልን ፡ ድል ፡ የነሣና ፡ በንጹሕ ፡ መሥዋዕቱ ፡ እግዚአብ ሔርን፡ደስ፡ያሰኘ፡ኖኅ፡አንተ፡ነህን? |
| ፳፩ አንተኑ፡አብርሃም፡አበ፡አበው፡ወሚመ፡ ይስሐቅ፡ዘአድኅኖ፡እግዚአብሔር፡እምነ፡ መጥባሕት። | ፳፩፤ የአባቶች፡አባት፡አብርሃም፡ወይም፡በሾተል፡ ከመታረድ፡ያዳነው፡ይሥሐቅ፡አንተ፡ነህን? |
| ፳፪ አንተኑ፡ያዕቆብ፡ዘርእዮ፡ለእግዚአብሔር፡ ገጸ፡በገጽ፡በመልዕልተ፡ሰዋስው፡ወሚመ፡ ዮሴፍ፡ዘሞአ፡ለጸብአ፡ሰይጣን፡ከመ፡ኃያል። | ፳፪፤ እግዚአብሔርን ፡በመሰላል ፡ ላይ ፡ ፊት ፡ ለፊት፡ ያየው ፡ ያዕቆብ ፤ ወይም ፡ ኃይለኛ ፡ እንደ፡መሆኑ፡የሰይጣንን፡ጦር፡ድል፡ያደረገ፡ ዮሴፍ፡አንተ፡ነህን። |
| ፳፫ አንተኑ፡ሙሴ፡ዘከፈለ፡ባሕረ፡ወመዋግዲሁ፡ በቅድመ፡ሕዝብ፡ወተናገረ፡ምስለ፡እግዚአ ብሔር፡ወሚመ፡ኢያሱ፡ወልደ፡ነዌ፡ ዘአቀመ፡ፀሐየ፡ቀትረ፡መዐልት። | ፳፫፤ በሕዝብ፡ፊት፡ባሕረ፡ኤርትራን፡የከፈለ፡ማዕ በሉንም ፡ ጸጥ ፡ ያደረገ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራም፡ የተነጋገረ ፡ ሙሴ ፡ ወይም ፡ ፀሐይን ፡ በቀን፡ያቆመ፡የነዌ፡ልጅ፡ኢያሱ፡አንተ፡ነህን? |
| ፳፬ አንተኑ፡ጌዴዎን፡ዘአስተማሰለ፡ርደቶ፡ለእግ ዚአብሔር፡ከመ፡ጠል፡ውስተ፡ፀምር፡ ወሚመ፡ዮፍታሔ፡ዘሦዐ፡ወለቶ፡በእንተ፡ ብፅዓቲሁ፡ለእግዚአብሔር። | ፳፬፤ የእግዚአብሔርን ፡ መውረድ ፡ በመስክ ፡ በባዘቶ፡ላይ፡እንደሚወርድ፡ጠል፡የመሰለ፡ ጌዴዎን፡ወይም፡ስለ፡ስእለቱ፡ሴት፡ልጁን፡ ለእግዚአብሔር ፡የሠዋ ፡ ዮፍታሔ ፡ አንተ ፡ ነህን? |
| ፳፭ አንተኑ፡ኢሳይያስ፡ነቢይ፡ዘሰመዮ፡ በትንቢቱ፡መንክረ፡ወሚመ፡ሕዝቅኤል፡ ዘርእዮ፡ለእግዚአብሔር፡ብዲበ፡ሠረገላሁ። | ፳፭፤ በትንቢቱ፡ ጌታን ፡መንክር፡ብሎ፡የሰየመው፡ (የጠራው)፡ነቢዩ፡ኢሳይያስ፡ወይም፡ እግዚአ ብሔርን ፡ በሠረገላው ፡ ሁኖ ፡ ያየው ፡ ሕዝቅኤል፡አንተ፡ነህን? |
| ፳፮ አንተኑ፡ዳንኤል፡ነቢይ፡ዘኀተመ፡አፈ፡ አናብስት፡ወሚመ፡ሠለስቱ፡ደቂቅ፡ዘኢለ ከፎሙ፡ላህበ፡እሳት። | ፳፮፤ የአንበሶችን ፡ አፍ ፡ የዘጋ ፡ ዳንኤል ፡ ወይም ፡ የእሳት ፡ ወላፈን ፡ ያልነካቸው ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ፡አንተ፡ነህን? |

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፻፯፡ አንተኑ፡ስምዖን፡ጴጥሮስ፡ዘሖረ፡ዲበ፡ ባሕር፡ወሚመ፡ዮሐንስ፡ዘረፈቀ፡ዲበ፡እንግድዓሁ፡ለኢየሱስ፡አው፡ዮሐንስ፡ወልደ፡ ዘካርያስ፡ዘአንበረ፡እዴሁ፡ዲበ፡ርእሱ፡ ለኢየሱስ፡ ወርእየ፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ በአምሳለ፡ርግብ፡እንዘ፡ይወርድ፡ዲቤሁ፡ ወሰምዐ፡ቃለ፡አብ፡እምሰማይ፡ዘይብል፡ ዝንቱ፡ ውእቱ፡ ወልድየ፡ ዘአፈቅር፡ ወኪያሁ፡ሠመርኩ።

፻፰፡ ንግረኒ፡አ፡ብእሲ፡ድኩም፡መኑ፡አንተ፡ ዘጠባዕከ፡ወኀለፍከ፡አብሕርተ፡እሳት፡ ወኢየማስነከ።

፻፱፡ አውሥአ፡ ፈያታዊ፡ ወይቤሎ፡ ኢትትመዐዕ፡አ፡ፍቁር፡መልአክ፡አነ፡እነግረከ፡ ከመ፡መኑ፡አነ፡ወመኑ፡ውእቱ፡ዘፈነወኒ።

፻፲፡ አንሰ፡ፈያታይ፡በኵሉ፡ምግባረ፡እከይ፡ አኅለፍኩ፡ኵሎ፡መዋዕልየ፤ወደመ፡ሰብእ፡ ተቀባዕኩ፡ወእጸንሕ፡ፍኖተ፡ከመ፡እሂድ፡ ወእትዐገል።

፻፲፩፡ ለአብዕልት፡እንደይክዎሙ፡ወለነዳያን፡ አህጕልክዎሙ፡ለአዕሩግ፡ወለሕፃናት፡ወለ ወራዙት፡ኢመሀክዎሙ፡ወብዙኃን፡ቀትለ፡ ቀተልክዎሙ፡ወበደመ፡ሰብእ፡ከመ፡ማይ፡ ተኀፀብኩ።

፻፲፪፡ ወሶበ፡ሰምዐ፡መልአክ፡ነገሮ፡ለፈያታዊ፡ ተደመ፡ወደንገፀ፡ወጸውዖሙ፡ለሠራዊተ፡ መንፈሳውያን፡ወግብተ፡መጽኡ፡ኀቤሁ፡ ወይቤሎሙ፡መልአክ፡ንዑኬ፡አ፡ማኅበረ፡ መላእክት፡አንክሩ፡ምስሌየ፡ዮም፡ወምስለ፡ ዝንቱ፡መሬታዊ።

፻፲፫፡ ወተመይጠ፡ኀበ፡ፈያታዊ፡ወይቤሎ፡አ፡ ፈያታዊ፡ድኩም፡ምንተ፡እንከ፡ትግበር፡ መጻእከ፡ውስተ፡ብሔረ፡ሕያዋን።

፻፲፬፡ አ፡ዘተቀባዕከ፡ደመ፡በአይ፡ፍኖት፡መጻእከ፡ ኀቤነ፡ወኢያውዐየከ፡ላህበ፡እሳት።

፻፲፭፡ አ፡ ሰራቂ፡ አልቦ፡ በውስተ፡ ብሔርነ፡ ዘትሰርቅ፡ ወኢምንተኒ፤ አ፡ ቀታሊ፡ ኢትክል፡ቀቲሎቶሙ፡ለመላእክት።

፻፲፮፡ አ፡ማህጕሌ፡ሰብእ፡ኢትክል፡ታህጕሎሙ፡ ለመንፈሳውያን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፻፯፡ በባሕር፡ላይ፡የሄደ፡ስምዖን፡ጴጥሮስ፡ ወይም፡ በጌታ፡ ኢየሱስ፡ አጠገብ፡ የተቀመጠ፡ ዮሐንስ፡ ወይስ፡ በጌታ፡ ኢየሱስ፡ ራስ፡ላይ፡እጁን፡የጫነ፡በርግብ፡ አምሳልም፡ መንፈስ፡ ቅዱስ፡ በላዩ፡ ሲወርድ፡ ያየና፤ የምወደው፡ልጄ፡ይህ፡ ነው፤ በእርሱም፡ደስ፡የምሰኝበት፡የሚል፡ የአብን፡ ቃል፡ የሰማ፤ የዘካርያስ፡ልጅ፡ ዮሐንስ፡አንተ፡ነህን?

፻፰፡ አንተ፡ደካማ፡ሰው፡ንገረኝ፤አንተ፡ማነህ? የእሳት፡ባሕሮችን፡በርትተህ፡የተሻገርህ፡ አቃጥለው፡ያላጠፉህ፡ብሎ፡ጠየቀው።

፻፱፡ ፈያታዊ፡ ዘየማንም፡ መለሰ፤ ተወዳጅ፡ መልአክ፡ሆይ፡አትቆጣ፤እኔ፡ማን፡እንደ ሆንኩ፡የላከኝም፡ማን፡እንደሆነ፡እነግር ሃለሁ፡አለው።

፻፲፡ መላ፡ ዘመኔን፡ በክፉ፡ ሥራ፡ ያሳለፍኩ፡ ወንበዴ፡ ነኝ፤ የሰውን፡ደም፡ተቀባሁ፡ እቀማ፡ዘንድ፡በመንገድ፡እሸምቅ፡ነበረ።

፻፲፩፡ ባለጸጎችን፡ አደኸየኋቸው፡ ድኆችንም፡ አጠፋኋቸው፤ ሽማግሌዎችን፡ ሕፃናቶ ችንና፡ ወጣቶችን፤(ጎልማሶችን)፡አልራራ ሁላቸውም፤ብዙ፡ግድያም፡ገደልኋቸው፡ በሰው፡ደምም፡እንደ፡ውኃ፡ታጠብሁ።

፻፲፪፡ መልአኩም፡የፈያታዊን፡ነገሩን፡በሰማ፡ ጊዜ፡ተደነቀ፤ደነገጠም፤ረቂቃን፡የመላ እክት፡ሠራዊትንም፡ጠራቸው፤ወደ፡ እርሱም፡ፈጥነው፡መጡ፤የመላእክት፡ ማኅበር፡ሆይ፡እስኪ፡ኑ፡ዛሬ፡ከእኔና፡ከዚህ፡ ከምድራዊው፡ሰው፡ጋራ፡በመሆን፡ አድንቁ፤ማለት፡(አስደናቂ፡ነገርን፡ስሙ)።

፻፲፫፡ ወደ፡ፈያታዊ፡ዘየማን፡ተመልሶ፡አንተ፡ ደካማ፡ወደ፡ሕያዋን፡መላእክት፡ሀገር፡ እንግዲህ፡ምን፡ልታደርግ፡መጣህ፡አለው።

፻፲፬፡ አንተ፡የሰው፡ደም፡የተቀባህ፡በየትኛው፡ መንገድ፡ወደኛ፡መጣህ፤የእሳት፡ወላፈን፡ ያላቃጠለህ።

፻፲፭፡ አንተ፡ሌባ፡በሀገራችን፡ውስጥ፡ምንም፡ምን፡ የምትሰርቀው፡የለም፤ነፍሰ፡ገዳይ፡ሆይ፡መላ እክትን፡ልትገድላቸው፡አትችልም።

፻፲፮፡ አንተ፡ሰዎችን፡ያጠፋህ፡ረቂቃን፡መላእ ክትን፡ታጠፋቸው፡ዘንድ፡አትችልም።

Scanned by CamScanner

## በ፰፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፻፲፯ አ፡ ማዕር፡ እፎ፡ ኀለፍከ፡ ውስተ፡ ባሕረ፡ እሳት፤ወበማእከለ፡መንፈሳውያን፡ምንተ፡ ትገብር፡ሑር፡ተመየጥ፡ወግባእ፡ውስተ፡ ብሔርከ፡ ከመ፡ ኢያውዒከ፡ ላህበ፡ ከነፊሆሙ፡ ለመላእክት፡ ብርሃናውያን፡ ዘእሳት።

፻፲፰ ለበኬ፡አ፡መሬታዊ፡ከመ፡ጥቅማ፡ለገነት፡ እሳት፡ይእቲ፡ ወኢትክል፡ ቀሪበ፡ ኀቤሃ፤ ወለእመኒ፡ ቀረብከ፡ ኀቤሃ፡ ታውዒ፡ ድካመከ።

፻፲፱ እፎ፡ጠባዕከ፡ፈያታይ፡ትዕዱ፡ዲበ፡ዕፃ፡ እሳት።

፻፳ አውሥአ፡ፈያታይ፡ወይቤሎ፡ለመልአክ፡ ስምዐኒ፡ ነገርየ፡ አ፡ መንፈሳዊ፡ እመሰ፡ ነበርኩ፡ በኵሉ፡ ምግባረ፡ እኩይ፡ አላ፡ ባሕቱ፡ ነሥአኒ፡ ምሕረት፡ እሙስና፡ ውስተ፡ ሕይወት፡ ወእምኵሉ፡ አበሳየ፡ አንጽሐኒ።

፻፳፩ አኅለፍኩ፡ ኵሎ፡ መዋዕልየ፡ በጌጋይ፡ ወቀቲል፡ ወበተፍጻሜታ፡ ለዕለትየ፡ ሰሐበተኒ፡ምሕረት፡ውስተ፡ሕይወት።

፻፳፪ ስምዓኒ፡ ቃልየ፡ አ፡ መልአክ፡ ናሁ፡ እግዚእከ፡ ንጉሥ፡ ሰማያዊ፡ ውእቱኬ፡ ዘጸገወኒ፡ሕይወተ፤እስመ፡ሶበ፡አመንኩ፡ ቦቱ፡ አርኀወ፡ ሊተ፡ አናቅጸ፡ ምሕረት፡ ከመ፡እባእ፡ውስተ፡ብሔረ፡ሕያዋን።

፻፳፫ መፍትው፡ ለከ፡ አ፡ መልአክ፡ ከመ፡ ትትፈሣሕ፡በኃጥእ፡ሶበ፡ይኔስሕ፡እስመ፡ እግዚእከ፡ ይትፌሣሕ፡ በዘከማየ፡ ሶበ፡ ይኔስሕ፡ኀቤሁ፡በንስሓ።

፻፳፬ ወዓዲ፡ኵሎሙ፡መላእክት፡ይትፌሥሑ፡ በእንተ፡አሐዱ፡ኃጥእ፡ሶበ፡ይኔስሕ።

፻፳፭ አውሥአ፡መልአክ፡ወይቤሎ፡ለፈያታይ፡ እፎኬ፡ ኢፈነወ፡ አሐደ፡ እመላእክቲሁ፡ ይጺሕ፡ ፍኖቶ፡ ወለምንት፡ እንከ፡ ኀደጎ፡ ለአብርሃም፡ርእሰ፡አበው፡ወፈነወ፡ኪያከ።

፻፳፮ ወእፎ፡ኢፈነወ፡ሙሴሃ፡ወኢያሱሃ፡ወልደ፡ ነዌ፡ወኤልያስሃ፡ወኤልሳዕሃ፡ረድአ፡እሉ፡ ነቢያት፡መንፈሳውያን፡ዘአሕየዉ፡ሙታነ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

፻፲፯፤ የሣር፡ ገለባ፡ ሆይ፡ የእሳቱን፡ ባሕር፡ እንዴት፡ አለፍከ፤ በረቂቃን፡ መላእክት፡ መካከል፡ ምን፡ ትሠራለህ? የብርሃናውያን፡ መላእክት፡ እሳት፡ የሆነው፡ የክንፋቸው፡ ዋዕይ፡ እንዳያቃጥልህ፡ ወደ፡ መጣህበት፡ ሀገርህ፡ተመልሰህ፡ሂድ።

፻፲፰፤ አንተ፡ዐፈር፡ሆይ፡የገነት፡ቅጽርዋ፡እሳት፡ እንደሆነ፡ አስተውል፤ ወደ፡ እርስዋም፡ መቅረብ፡ አትችልም፤ ወደ፡ እርስዋም፡ ብትቀርብ፡ደካማ፡አንተን፡ታቃጥልሃለች።

፻፲፱፤ አንተ፡ ሽፍታ፡ በእሳቱ፡ መከማቻ፡ ላይ፡ ትሻገር፡ዘንድ፡እንዴት፡በረታህ፡አለው።

፻፳፤ ፈያታዊ፡ዘየማንም፡መልሶ፡መልአኩን፡ እንዲህ፡ አለው፤ ረቂቅ፡ መልአክ፡ ሆይ፡ ነገሬን፡ስማኝ፤ምንም፡በክፉ፡ሥራ፡ሁሉ፡ ብኖር፡ ነገር፡ ግን፡ የጌታ፡ ምሕረት፡ ከጥፋት፡ወደ፡ሕይወት፡አነሣኝ፤ከበደሌ፡ ሁሉም፡አነጻኝ።

፻፳፩፤ መላ፡ ዘመኔን፡ በመበደልና፡ ነፍስ፡ በመግደል፡ አሳለፍኩ፤ በመጨረሻዋ፡ ቀኔም፡ የጌታ፡ ምሕረት፡ ወደ፡ ሕይወት፡ ሳበችኝ።

፻፳፪፤ መልአክ፡ ሆይ፡ ቃሌን፡ ስማኝ፤ እነሆ፡ ሰማያዊ፡ ንጉሥ፡ ጌታህ፡ ሕይወትን፡ የሰጠኝ፡ እርሱ፡ ነዋ! አምኜበታለሁና፡ በአ መንኩበት፡ ጊዜ፡ ወደ፡ ሕያዋን፡ ሀገር፡ እገባ፡ ዘንድ፡ የይቅርታውን፡ በር፡ ከፈተልኝ።

፻፳፫፤ መልአክ፡ሆይ፡ኃጥኡ፡ንስሐ፡በገባ፡ጊዜ፡ ደስ፡ ይልህ፡ ዘንድ፡ ይገባሃል፤ ጌታህም፡ እንደ፡እኔ፡ያለው፡ወደ፡እርሱ፡በንስሐ፡ በተመለሰ፡ጊዜ፡ደስ፡ይለዋልና።

፻፳፬፤ ዳግመኛም፡ ንስሐ፡ በሚገባ፡ ጊዜ፡ ስለ፡ አንዱ፡ ኃጥእ፡ መላእክት፡ ሁሉ፡ ደስ፡ ይላቸዋል፡አለው።

፻፳፭፤ መልአኩም፡ ለሽፍታው፡ መለሰ፤ መንገዱን፡ ይጠርግ፡ ዘንድ፡ ከመላእክት፡ አንዱን፡ያልላከ፡እንዴት፡ነው፤የአባቶች፡ አለቃ፡ አብርሃምን፡ ትቶ፡ እንግዲህ፡ አንተን፡ለምን፡ላከ፡አለው።

፻፳፮፤ ሙሴንስ፡እንዴት፡አልላከም፤የነዌ፡ልጅ፡ ኢያሱን፡ ወይም፡ ኤልያስን፡ ወይም፡ ደቀ፡ መዝሙሩ፡ኤልሳዕን፡እኒህ፡ሙታንን፡ያነሡ፡

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወኪያከ፡ፈነወ።

፻፳፯፤ ወለምንት፡ኢፈነወ፡ዳዊትሃ፡ነቢየ፡ዘርእየ፡ ልደቶ ፡ ወሕማማቲሁ ፡ ወሞቶ ፡ ወትንሣኤሁ፡ወዕርገቶ፡ውስተ፡ሰማይ።

፻፳፰፤ ወእፎ ፡ ኢፈነወ ፡ ሕዝቅኤልሃ ፡ ነቢየ ፡ ዘርእየ፡ለእግዚአብሔር፡በዲበ፡ሠረገላሁ።

፻፳፱፤ ለእሉ ፡ እለ ፡ ጾሩ ፡ ክበዳ ፡ ለዕለት ፡ ወዋዕየ ፡ ፀሐይ፡ኅደጎሙ፤እለ፡ጸርሑ፡በትንቢቶሙ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ቀርን ፡ ወዜነዉ ፡ እምቅድመ ፡ ምጽአቱ፡ወኪያከ፡ፈነወ።

፻፴፤ አይቴ ፡ ሀለዉ ፡ አቤል ፡ ጻድቅ ፡ ወሴት ፡ ዘሠናየ፡ይሬኢ፡ወኖኅ፡ኄሩይ፡ወአብርሃም፡ ፍቁሩ ፤ ወይሥሐቅ ፡ ቊልዔሁ ፡ ወእስራኤል፡ ቅዱሱ ፡ ለእሉ ፡ ኄራን ፡ ውሉደ ፡ መንግሥት ፡ ኅደጎሙ ፡ ወኪያከ ፡ ፈነወ ፡ እ ፡ ዘተቀባዕከ ፡ ደመ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ትጺሕ ፡ ፍኖቶ።

፻፴፩፤ አውሥአ ፡ ፈያታይ ፡ ወይቤሎ ፡ ለመልአክ ፡ ስምዐኒ ፡ ቃልየ ፡ እ ፡ መንፈሳዊ ፡ እስመ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ተጋዕዞ ፡ ምስለ ፡ መላእክት ፡ ዘእንበለ ፡ ባሕቱ ፡ እግዚእከ ፡ ዘፈነወኒ ፡ ውስተ፡ገነት።

፻፴፪፤ እስመ ፡ ምሕረት ፡ እንሥአተኒ ፡ እምድ ቀትየ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኅደጎሙ ፡ ለእሉ ፡ ጻድቃን ፡ ዘትቤ ፡ ወኪያየ ፡ ፈነወኒ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ኄራን ፡ ይመጽኡ ፡ ምስለ ፡ እግዚእ፡በዐቢይ፡ስብሐት።

፻፴፫፤ ወኪያየ ፡ ባሕቱ ፡ እምዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ፈነወኒ፡ውስተ፡ገነት፡ድውያንሰ፡ይፈቅዱ፡ ዐቃቤ፡ሥራይ፡ወአኮ፡ጥዑያን፡ዘይፈቅዱ፡ ፈውሰ።

፻፴፬፤ እስመ ፡ ሊተሰ ፡ መሐረኒ ፡ ወተሣሃለኒ ፡ አቅደመ፡ፈንዎትየ፡ውስተ፡ገነት፡እስመ፡ ኢተቀነይኩ፡እምዕለት፡ዘእንበለ፡ዳዕሙ፡ አሐቲ፡ሰዓት።

፻፴፭፤ ወይእዜሰ ፡ እ ፡ መልአክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስማዕ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወንሣእ ፡ መርኆ፡ዘእሳት፡እስመ፡ንጉሥ፡ እግዚእከ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

መንፈሳውያን ፡ ነቢያት ፡ ሳሉ ፡ አንተን፡ እንዴት፡ላከ።

፻፳፯፤ ልደቱን ፤ ሕማሙን ፤ ሞቱን ፤ ትንሣኤውን፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ማረጉን ፡ አይቶ ፡ ትንቢት፡ የተናገረ፡ነቢዩ፡ዳዊትን፡ለምን፡አልላከም፡

፻፳፰፤ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያየው ፡ ሕዝቅኤልን ፡ ለምን፡ አልላከም።

፻፳፱፤ የዕለቲቱን ፡ የድካሟን ፡ ክብደት ፡ የተሸከሙ፤ የፀሐዩንም ፡ ትኩሳት ፡ የቻሉ፡ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ በትንቢታቸው ፡ እንደ፡ ነጋሪት ፡ ድምጽ ፡ አሰምተው ፡ የተናገሩትን፡ ትቶ፡አንተን፡እንዴት፡ላከ።

፻፴፤ ጻድቁ ፡ አቤል ፤ በጎ ፡ ሥራ ፡ ተመልካች፡ የነበረ ፡ ሴት ፤ የተመረጠ ፡ ኖኅና ፡ ወዳጁ፡ አብርሃም ፤ ልጁ ፡ ይሥሐቅና ፡ እስራኤል፡ የተባለው ፡ የከበረ ፡ ያዕቆብስ ፡ ወዴት ፡ አሉ፤ እነዚህ ፡ የተመረጡ ፡ የመንግሥት ፡ ልጆች፡ ናቸው ፤ እርሳቸውን ፡ ትቶ ፡ የሰው ፡ ደም፡ የተቀባህ ፡ አንተን ፡ መንገዱን ፡ ትጠርግ፡ ዘንድ፡እንዴት፡ላከህ፡አለው።

፻፴፩፤ ፈያታዊ ፡ ዘየማንም ፡ ለመልአኩ ፡ መለሰለት፤ መንፈሳዊ ፡ ሆይ ፤ ቃሌን ፡ ስማኝ፤ ከመላእክት ፡ ጋራ ፡ ለመከራከር ፡ ሳይሆን፡ ጌታህ ፡ወደ፡ገነት፡ስለ፡ላከኝ፡ነው፡እንጂ።

፻፴፪፤ ከወደቅሁበት ፡ የጌታ ፡ ምሕረት ፡ አንሥታኛለችና ፤ ስለዚህም ፡ አንተ ፡ ያልካቸውን፡ ጻድቃን ፡ ትቶ ፡ እኔን ፡ ላከኝ፤ እነዚህ ፡ ደጋጎች፡ በታላቅ ፡ ክብር፡ ከጌታ፡ጋራ ፡ ይመጣሉና።

፻፴፫፤ እኔን ፡ ግን ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ ገነት፡ ላከኝ ፤ በሽተኞች ፡ ባለ ፡ መድኃኒትን ፡ ይሹታል ፤ ፈውስ ፡ የሚሹ ፡ ጤነኞች ፡ አይደሉም።

፻፴፬፤ እኔን ፡ ፈጽሞ ፡ ይቅር ፡ አለኝ፤ የእኔንም ፡ ወደ፡ ገነት ፡ መላክ ፡ አስቀደመ ፤ ከዕለቷም ፡ ያለ፡ አንዲት ፡ ሰዓት ፡ አላገለገልኩም ፡ ነበር።

፻፴፭፤ አሁንም ፡ የጌታ ፡መልአክ ፡ ሆይ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ስማ ፤ የእሳቱንም ፡ መክፈቻ፡ አንሣ፤ ንጉሡ ፡ ጌታህ ፡በዕንጨት ፡ መስቀል፡

በ፲፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ፈነወኒ፡እምዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ወወሀበኒ፡
መራኁተ፡ገነት።
፻፴፮ አውሥአ ፡ መልአክ ፡ ወይቤሎ ፡ ለከ ፡
እብለከ፡አ፡ፈያታዊ፡ኢትበውእ፡ውስተ፡
ብሔረ፡ሕያዋን፡እስከ፡ይመጽእ፡ እግዚእከ፡
ወኢትሬእያ፡ለይእቲ፡ጸጋ፡እስከ፡እኔጽር፡
ኀቤሁ።
፻፴፯ ወኢያርኁ፡ማዕጾ፡ዘዐጸወ፡አዳም፡እስከ፡
ይመጽእ፡እግዚኡ፡ለአዳም፡ወያርኁ።

፻፴፰ ሰማዕ፡አ፡ፈያታዊ፡መላእክትኒ፡ኢይክሉ፡
ይርአይዋ፡ለስብሐቲሃ፡ኪያከኑ፡ዘተቀ
ባዕከ፡ደመ፡ይፌንወከ፡ውስተ፡ገነት።

፻፴፱ አውሥአ፡ፈያታዊ፡ለመልአክ፡ወይቤሎ፡
አንሰ፡አመንኩ፡ በእግዚእ ፡እንዘ፡ሰማይ፡
ይትሀወክ፡ወምድርኒ፡አርመመት፡ ወልድ፡
ፍቁር፡እንዘ፡ስቁል፡ዲበ፡ዕፅ፡ወሶበ፡
ሰባሕክዎ፡አነ፡እንከሩ፡ኵሉ፡ፍጥረት፡
ወጸሐፈ፡ሊተ፡ዘንተ፡መጽሐፈ።
፻፵ ወይቤለኒ፡አሜን፡አሜን፡እብለከ፡እመነኒ፡
አ፡ብእሲ፡ከመ፡ትሄሉ፡ምስሌየ፡ውስተ፡
ገነት፡ወተፈሥሑ፡ሊተ፡መላእክተ፡
ሰማይ።
፻፵፩ ወበኀበ፡ሐመ፡ እግዚእከ ፡ኢሀለዉ፡ህየ፡
መሃይምናን፡ወኢመኑሂ፡ዘእንበለ፡
ባሕቲትየ፡አነ፡ሶበ፡አርመመ፡ኵሉ፡
ፍጥረት፡ወሠራዊተ፡ሰማይ፡ይከድኑ፡
ገጾሙ፡በፍርሃት፡ወበረዓድ፡ ወገብርኤል፡
እንዘ፡ያደንን፡ርእሶ፡ ወሚካኤል ፡እንዘ፡
ይኔጽር፡ኀቤሁ።

፻፵፪ ወአክሊለ፡ሦክ፡ዲበ፡ርእሱ፡ወሠራዊተ፡
መንፈሳውያን፡ይቀውሙ፡በድንጋፄ።

፻፵፫ ወአርድእት፡ተኀብኡ፡እምፍርሃት፡
ወማርያም ፡እሙ፡ለሐወት፡ወትቀውም፡
እምርኁቅ።
፻፵፬ ወሁከቶሙ፡ለከሀድያን፡ከመ፡ሞገደ፡
ባሕር፡ወደፈኖ፡ለዕለት፡ጽልመት።

፻፵፭ ወሠራዊተ፡ቀያፋ፡ፍጡነ፡ይጐዩ፡ወምስለ፡
ዝንቱ፡ኵሉ፡ኢያርመምኩ፡አነ፡አላ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ላይ ፡ ሳለ ፡ የገነትን ፡ መክፈቻ ፡ ሰጥቶ ፡
ልኮኛልና።
፻፴፮፤ መልአኩም ፡ መለሰ ፤ ፈያታይ ፡ ሆይ ፡
አንተን፡እናገራለሁ፤ ጌታህ ፡እስከሚመጣ፡
ድረስ፡ከቶ፡ከሕያዋን፡ሀገር፡አትገባም፤
በእርሱ፡ዘንድ፡እስከማይ፡ድረስ፡ያችን፡
ጸጋ፡አታያትም።
፻፴፯፤ የአዳም፡ ጌታው ፡እስከሚመጣና፡እስከሚ
ከፍት፡በአዳም፡ምክንያት፡የተዘጋውን፡
በር፡አልከፍትም።
፻፴፰፤ አንተ፡ፈያታዊ፡ስማ፤መላእክት፡ስንኳ፡
ክብርዋን፡ያዩ፡ዘንድ፡አይችሉም፤የሰውን፡
ደም፡የተቀባኸውን፡አንተን፡ወደ፡ገነት፡
ይልካልን፡አለው።
፻፴፱፤ ሽፍታውም፡ለመልአኩ፡መለሰለት፤ሰማይ፡
ሲታወክ፡ምድርም፡ጸጥ፡ብላ፡ሳለች፡
ወልድ፡ፍቁርም፡በዕንጨት፡ላይ፡ተሰቅሎ፡
ሳለ፡ በጌታ ፡እኔ፡አመንኩበት፡አለው፤በአመ
ሰገንሁትም፡ጊዜ፡ፍጥረቱ፡ሁሉ፡አደነቁ፤
ይህንንም፡መጽሐፍ፡ጻፈልኝ።
፻፵፤ አንተ፡ሰው፡ሆይ፡እመነኝ፡ዛሬ፡ከእኔ፡
ጋራ፡ በገነት፡እንደምትኖር፡እውነት፡
እውነት፡እልሃለሁ፡አለኝ፤የሰማይ፡መላእ
ክትም፡በእኔ፡ደስ፡ተሰኙብኝ።
፻፵፩፤ ጌታህ ፡ መከራ ፡ በተቀበለበት ፡ ቦታ ፡
ምእመናን፡በዚያ፡አልነበሩም፤ፍጥረት፡
ሁሉ፡በድንጋፄ፡ጸጥ፡ባለ፡ጊዜ፡የሰማይ፡
ሠራዊት ፡ በመፍራትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡
ፊታቸውን ፡ በሸፈኑ ፡ ጊዜ ፡ ገብርኤል ፡
አንገቱን፡ሲደፋ፡ ሚካኤልም ፡ወደእርሱ፡
ሲመለከት፡ከእኔ፡ከብቻየ፡በቀር፡ማንም፡
የለም፡ነበር።
፻፵፪፤ የእሾህ ፡ አክሊል ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነው ፤
የመላእክት ፡ ሠራዊት ፡ በመደ
ረቂቃን፡ ንገጽ፡ቁመው፡ነበር።
፻፵፫፤ ከመፍራት፡የተነሣ፡ሐዋርያት፡ተሸሸጉ፤
እናቱ፡ ማርያምም ፡ከሩቅ፡ቁማ፡ታለቅስ፡
ነበር።
፻፵፬፤ የከሀድያን፡አይሁድ፡ሁከትም፡እንደ፡
ባሕር፡ ማዕበል፡ሆነ፤ ቀኑንም፡ጨለማ፡
ሸፈነው።
፻፵፭፤ የቀያፋም፡ሠራዊት፡ፈጥነው፡ሸሹ፤ከዚህም፡
ሁሉ፡ጋራ፡እኔ፡ዝም፡አላልኩም፤በጽኑዕ፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ባሕቲትየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰባሕክዎ
በጽንዐ፡ሃይማኖት።
፻፵፮ ሕዝብሰ፡ይጸርሑ፡ወይነቡ፡ቃለ፡ዕርፌት፡
ወአንሰ፡ሰባሕክዎ፡ለንጉሠ፡ስብሐት፡ሶበ፡
ተሰቅለ፡በግዐ፡ለእግዚአብሔር፡ዲበ፡ዕፀ፡
መስቀል ፡ ወሠራዊተ ፡ ቀያፋ ፡ ይማለቁ ፡
ላዕሌሁ።
፻፵፯ አይቴ፡ሀሎከ፡አንተ፡አሚሃ፡ወኵሎሙ፡
መላእክት ፡ እመ ፡ ያረምም ፡ ሰማይ ፡
ወምድር፡ ወኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ወደፈና ፡
ለዓለም፡ጽልመት።
፻፵፰ አይቴ፡ሀሎከ፡አሚሃ፡ላዕሌየኑ፡ታርኢ፡
ጽንዐ፡ኀይልከ፡ሶበ፡ቀነውዎ፡ለእግዚ
እክሙ፡ለምንት፡አርመምክሙ፡ሶበ፡
ጸፍዕዎ፡እፎ፡ኢተናገርክሙ፡ሶበ፡ወረቁ፡
ውስተ፡ገጹ፡ለምንት፡ርኀቅሙ፡እምኔሁ፡
ሶበ፡ይቤልዎ፡አድኅን፡ርእሰከ፡ለምንት፡
ርዕድክሙ፡ስምዖን፡ርእሶሙ፡ለአርድእት፡
ዘሀለወ፡ምስሌሁ፡ክህደ፡ወመሐለ፡ከመ፡
ኢየአምሮ።

፻፵፱ ወዘሂ፡አምኖ፡ዲበ፡አስከሬነ፡ሙዳየ፡
ወርቅ፡ አግብአ ፡ ወነሥአ ፡ ሤጦ ፡ ወዘረ
ፈቀሰ፡ዲበ፡እንግድዓሁ፡በውስተ፡ድራር፡
ተዐገሠ፡ምስሌሁ፡በሕማሙ።

፻፶ ሶበ ፡ አጽገበ ፡ በኀምስቱ ፡ ኅብስት ፡
ወበክልኤ፡ ዓሣ ፡ ኀምሳ ፡ ምዕተ ፡ ብእሴ ፡
በገዳም፡አነ፡ባሕቲቱ፡ኢሀሎኩ፡ምስሌሁ።
፻፶፩ ሶበ ፡ ረሰዮ ፡ ለማይ ፡ ወይነ ፡ ጥዑመ ፡
ኢሰተይኩ፡እምኔሁ።
፻፶፪ ሶበ፡ገሠጸ፡ባሕረ፡ወነፋሳተ፡ወተአዘዙ፡
ሎቱ፡ኢሀሎኩ፡ምስሌሁ።
፻፶፫ አመ፡አሕየወ፡ምውተ፡እምድኅረ፡ረቡዕ፡
መዋዕል፡ኢርኢኩ።
፻፶፬ ሶበ፡ኀሠሡ፡እኩያን፡እምኔሁ፡ጸባሕተ፡
ቄሳር፡ኢሀሎኩ፡ምስሌሁ።
፻፶፭ ሶበ ፡ ሰደዶሙ ለአጋንንት ፡ እኩያን ፡
እምላዕለ፡ሰብእ፡ኢርኢኩ።
፻፶፮ ወአልቦ ፡ ዘርኢኩ ፡ ወኢምንተኒ ፡
ተአምራተ፡ወመንክራተ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ሃይማኖት፡ብቻዬን፡እግዚአብሔርን፡አመ
ሰገንሁት፡እንጂ።
፻፵፮ ሕዝቡም፡እየጮሁ፡የስድብ፡ቃል፡ይናገሩ፡
ነበር፤እኔ፡ግን፡የክብር፡ባለቤት፡የሆነ፡የእ
ግዚአብሔርን፡በግ፡በዕንጨት፡መስቀል፡
በተሰቀለ ፡ ጊዜ ፡ አመሰገንሁት፤ የቀያፋ፡
ሠራዊትም፡በእርሱ፡ላይ፡ይዘባበቱ፡ነበር።
፻፵፯ ያን ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ወዴት ፡ ነበርክ? መላው፡
መላእክትስ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ፍጥረት፡
ሁሉ ፡ በድንጋጤ ፡ ጸጥ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡
ዓለሙንም፡ጨለማ፡በዋጠው፡ጊዜ።
፻፵፰ ያን ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ወዴት ፡ ነበርክ? የኃይ
ልህን ፡ ብርታት ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ነውን ፡ የምት
ገልጽ፤ጌታችሁን፡በቸነከሩት፡ጊዜ፡ለምን፡
ዝም ፡ አላችሁ ፤ ፊቱን ፡ በጸፉትስ ፡ ጊዜ፡
እንዴት ፡ አልተናገራችሁም ፤ ምራቃ
ቸውን፡ በተፉበት ፡ ጊዜ ፡ ከእርሱ ፡ ለምን፡
ራቃችሁ፤ራስህን፡አድን፡በአሉት፡ጊዜስ፡
ለምን ፡ ተንቀጠቀጣችሁ ፤ ከእርሱ ፡ ጋራ፡
የሚኖር ፡ የሐዋርያት ፡ አለቃ ፡ ስምዖን፡
ጴጥሮስ፡ካደ፤እንደማያውቀውም፡ማለ።
፻፵፱ በግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ላይም ፡ አምኖ ፡ የሾመው፡
ይሁዳ ፡ አሳልፎ ፡ ሸጠው ፤ የሽያጩንም፡
ዋጋ፡ወሰደ፤ከአጠገቡ፡የሚቀመጠው፡ግን፡
በመከራው ፡ ጊዜ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ በመታገሥ፡
አልተለየም።
፻፶ በበረሀ ፡ ውስጥ ፡ በአምስት ፡ እንጀራና፡
በሁለት ፡ ዓሣ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ ሰው፡
በአጠገበ፡ጊዜ፡እኔ፡ከእርሱ፡ጋራ፡አልነበ
ርሁም።
፻፶፩ ውኃውን፡ጣፋጭ፡ጠጅ፡በአደረገው፡ጊዜ፡
ከጠጁ፡አልጠጣሁም።
፻፶፪ ባሕሩንና፡ነፋሳቱን፡በገሠጸና፡እነሱም፡በታ
ዘዙለት፡ጊዜ፤ከእርሱ፡ጋራ፡አልነበርኩም።
፻፶፫ ከአራት፡ቀን፡በኋላ፡የሞተውን፡ከመቃብር፡
ባስነሣ፡ጊ..፡አ ነየሁም።
፻፶፬ ከፉዎች፡ሰዎች፡የቄሳርን፡ግብር፡ከእርሱ፡
በፈለጉ፡ጊዜ፡ከእርሱ፡ጋራ፡አልነበርኩም።
፻፶፭ ከፉዎች ፡ አጋንንትን ፡ ከሰዎች ፡ ላይ፡
አስወጥቶ፡በሰደዳቸው፡ጊዜ፡አላየሁም።
፻፶፮ ከአስደናቂዎች፡ተአምራቶች፡ምንም፡ምን፡
ያየሁት፡አልነበረም።

Scanned by CamScanner

## በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፻፶፯ ወዓዲ፡ኢርኢክዎ፡ዘእንበለ፡ዳዕሙ፡በዲበ፡
ዕፀ፡መስቀል፡ርኢክዎ፡ወአመንኩ፡ቦቱ።
፻፶፰ ወእንሰ፡ኢርኢክዎ፡**ለወልድ**፡አመ፡ዐቀበ፡
ማሕፀና፡**ለድንግል**።

፻፶፱ ወኢርኢኩ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ጥብሉለ ፡ በአጽ
ርቅት፡በውስተ፡ጎል፡ከመ፡ሕፃን።
፻፷ ወኢርኢኩ፡ሶበ፡አምጽኡ፡ሰብአ፡ሰገል፡
ወርቀ፡ወነጸርዎ።
፻፷፩ ወዓዲ፡ኢርኢኩ፡ሶበ፡ተወለጠ፡አርአያሁ፡
**ለኢየሱስ** ፡ ወአርአየ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ለአር
ዳኢሁ፡በርእሰ፡ደብር።
፻፷፪ አመ፡**ቃለ፡አብ**፡እምሰማይ፡ይብል፡ዝንቱ፡
ውእቱ ፡ **ወልድየ** ፡ ዘአፈቅር ፡ ወኪያሁ ፡
ሠመርኩ፡ኢሰማዕኩ።
፻፷፫ ወእንዘ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ስምዖን ፡
ወሰረየ፡ ለብእሲት ፡ ኀጥእት ፡ ኢሀሎኩ ፡
ምስሌሁ።
፻፷፬ ወሶበ ፡ አሕየዋ ፡ ለወለተ ፡ ኢያኢሮስ ፡
እሞት፡ኢሀሎኩ፡ምስሌሁ።
፻፷፭ ወሶበ ፡ አንሥአ ፡ ለመፃጉዕ ፡ ወይቤሎ ፡
ንሣእ፡ዐራተከ፡ወእቱ፡ቤተከ፡ኢርኢኩ።

፻፷፮ ወአመ ፡ ረሰዮሙ ፡ ለፅሙማን ፡ ይስምዑ ፡
ቃለ፡ ወለበሃማን ፡ ይትናገሩ ፡ ኢሀሎኩ ፡
ምስሌሁ።
፻፷፯ አላ፡ባሕቲ፡ሰባሕክዎ፡እንዘ፡ሀሎ፡ስቁለ፡
ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል።
፻፷፰ አመ ፡ ተካፈሉ ፡ አይሁድ ፡ አልባሲሁ ፡
ወተዐፀዉ፡ዲበ፡ዐራዙ፤ሀሎኩ፡ምስሌሁ፤
ሶበ፡ቆሙ፡አርድእት፡እምርኁቅ፡ወይሬ
እይዎ፡ወአርመሙ፡መላእክት፡እምብዝኀ፡
ፍርሃት፡ውእተ፡ጊዜ፡ርኢክዎ።
፻፷፱ ወአመ ፡ ተረግዘ ፡ ገቦሁ ፡ በኲናት ፡ ወተቀ
ብዐት፡ይእቲ፡ዕፅ፡በደሙ፡ክቡር፡ወደፈና፡
ለዙላ ፡ ዓለም ፡ ጽልመት ፡ በፍርሀት ፡
ወበረዐድ ፡ ምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ሕማም ፡
ርኢክዎ፡**ለወልድ**።

፻፸ እነግረከ፡አ፡መልአክ፡አንሰ፡ኢያርመምኩ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፻፶፯ ደግሞም፡አላየሁትም፤በዕንጨት፡መስቀል፡
ላይ፡ተሰቅሎ፡አይቼ፡አመንሁበት፡እንጂ።
፻፶፰ **የድንግልን** ፡ ማኅተመ ፡ ድንግልናዋን ፡
ሳይለውጥ ፡ ጠብቆ ፡ ሲወለድ ፡ አላውቅም ፡
ነበር።
፻፶፱ በበረት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ በጨርቅ ፡
ተጠቅልሎ፡ሳለ፡አላየሁም።
፻፷ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ወርቅ ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡
በአዩት፡ጊዜ፡አላየሁም።
፻፷፩ ደግሞም፡በደብረ፡ታቦር፡ላይ፡መልኩ፡በተ
ለወጠና፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡**የመለኮቱን**፡
ክብር፡በገለጠ፡ጊዜ፡አላየሁም።
፻፷፪ **የአብ ፡ ቃል** ፡ ከሰማይ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡
ይህ፡ ነው ፤ በእርሱም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ ባለ ፡
ጊዜ፡አልሰማሁም።
፻፷፫ በስምዖን፡ዘለምጽ፡ቤትም፡ሳለ፡ሴቲቱን፡
ኃጢአትሽ ፡ ተሰረየልሽ ፡ በአላት ፡ ጊዜ ፡
ከእርሱ፡ጋራ፡አልነበርሁም።
፻፷፬ የኢያኢሮስን፡ልጅ፡ከሞት፡በአዳናት፡ጊዜ፡
ከእርሱ፡ጋራ፡አልነበርሁም።
፻፷፭ መፃጉዕን ፡ በአስነሣውና ፡ አልጋህን ፡
ተሸክመህ፡ወደቤትህ፡ግባ፡በአለው፡ጊዜ፡
አላየሁም።
፻፷፮ ደንቆሮዎችን፡እንዲሰሙ፡ዲዳዎችን፡እንዲ
ናገሩ፡በአደረገ፡ጊዜ፡ከእርሱ፡ጋራ፡አልነበ
ርኩም።
፻፷፯ ነገር ፡ ግን ፡ በዕንጨት ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡
ተሰቅሎ፡ሳለ፡አመንሁት፡እንጂ።
፻፷፰ አይሁድ፡ልብሱን፡በተካፈሉና፡በቀሚሱ፡
ላይ ፡ ዕጣ ፡ በተጣጣሉ ፡ ጊዜ ፡ ሐዋርያት ፡
በሩቅ፡ ቆመው ፡ ሲመለከቱ ፡ መላእክትም ፡
ከፍርሃት፡ብዛት፡የተነሣ፡ዝም፡ባሉ፡ጊዜ፡
ከእርሱ፡ጋራ፡ነበርኩ፤ያን፡ጊዜም፡አየሁት።
፻፷፱ ጎኑን ፡ በጦር ፡ በተወጋ ፡ ጊዜ ፡ ያቺም ፡
ዕንጨት ፡ በከበረ ፡ ደሙ ፡ በተቀባች ፡ ጊዜ ፡
መላዋንም፡ዓለም፡ጨለማ፡በጋረዳት፡ጊዜ፡
ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በመፍራትና ፡ በመንቀ
ጥቀጥ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡
ውስጥ፡ሁኖ፡**ወልድን**፡አየሁት።
፻፸ መልአክ ፡ ሆይ ፡ እነግርሃለሁ ፤ እኔ ፡ ዝም ፡

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ጸራሕኩ ፡ ኀቤሁ ፡ ወሰአ
ልክዎ፡ከመ፡ይዘክረኒ፡አመ፡ይመጽእ፡በመ
ንግሥቱ ፡ ሶቤሃ ፡ ወሀበኒ ፡ ስእለትየ ፡
ወፈነወኒ፡ኀቤከ።
፻፸፩፤ ወይእዜኒ ፡ ንሣእ ፡ መጽሐፈ ፡ መልእክት ፡
ክሥት፡ወአንብብ፡ወርኢ፡ኀበ፡ማኅተሙ፡
ለንጉሥ፡ዐቢይ።
፻፸፪፤ ንሣእ፡አ፡መልአክ፡መርኆ፡እሳት፡ዘማዕጾ፡
እሳት።
፻፸፫፤ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ መልአክ ፡ ለይእቲ ፡
መልእክት፡ ኀትምት ፡ በደሙ ፡ ለእግዚእ ፡
ሰገደ ፡ በቅድሜሁ ፡ ወሰዐሞ ፡ ወጸለሎ ፡
በክነፊሁ፡መንፈሳውያት።
፻፸፬፤ ወይቤሎ ፡ ለፈያታይ ፡ ሰላም ፡ ለከ ፡ አ ፡
መሬታዊ ፡ እስመ ፡ መጻእከ ፡ በትእዛዘ ፡
እግዚእከ ፡ ባእ ፡ ወተፈሣሕ ፡ ውስተ ፡
ማኅደረ፡መንፈሳውያን።
፻፸፭፤ ባእ፡ውስተ፡ገነተ፡ትፍሥሕት፡ዘወጽአ፡
እምኔሃ፡አቡከ፡አዳም።
፻፸፮፤ ባእ ፡ ወተኀለቍ ፡ ምስለ ፡ ሠራዊተ ፡
ሰማያት፡ ውስተ ፡ መንግሥት ፡ ባእ ፡ አ ፡
ፈያታይ፡ወተፈወስ፡እምቍስልከ፡እስመ፡
እግዚእከ፡ረሰየከ፡ድልወ፡ለዛቲ፡ክብር።
፻፸፯፤ ናሁ ፡ ትገዝምደ ፡ ሰማያውያን ፡ ወመሬታ
ውያን፡የሐልዩ፡በእንቲአከ፡እስመ፡ኮንከ፡
በዝ፡ዓለም፡ፈያታየ፡ወበደኃሪት፡ዕለት፡
ወራሴ፡መንግሥተ፡ሰማያት።
፻፸፰፤ በዝ፡ዓለም፡ኮንከ፡ቀታሌ፡ወበደኀሪት፡
ተኈለቈ፡ውስተ፡ጸጋ፡መንፈሳዊት።
፻፸፱፤ አ፡ፈያታይ፡አይቴ፡ሀሎ፡ንጉሥ፡ዘፈነወከ፡
ምንተ፡እንከ፡ይገብር፡ወእሮ፡ጐንደየ፡
ምጽአቱ፡ናሁ፡አድኅኖ፡ለአዳም፡ዘወረደ፡
እምልዑል፡ማኅደሩ፡ከመ፡ይኅሥሦ።
፻፹፤ አውሥአ፡ፈያታይ፡ወይቤሎ፡ለመልአክ፡
ሐረ ፡ ንጉሥ ፡ ኀበ ፡ መቃብር ፡ ከመ ፡
ይንሥት፡ አረፋቲሃ ፡ ለሲኦል ፡ ወያውፅእ ፡
ዘሀለዉ፡ሀየ፡ፂውዋነ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

አላልኩም፤በጌትነቱ፡በሚመጣ፡ጊዜ፡እን
ዲያስበኝ፡ያን፡ጊዜ፡ወደ፡እርሱ፡በመጮሀ፡
ለመንሁት ፤ ልመናዬንም ፡ ወዲያውኑ ፡
ተቀብሎ፡ወደ፡አንተ፡ላከኝ።
፻፸፩፤ አሁንም፡የተላከሁበትን፡ጽሑፍ፡ተቀበል፤
አንብባትም ፤ የታላቁንም ፡ ንጉሥ ፡
ማኅተም፡ተመልከት።
፻፸፪፤ መልአክ፡ሆይ፡የእሳቱ፡መዝጊያ፡የሚከፈት
በትንም፡የእሳቱን፡መክፈቻ፡ያዝ፡አለው።
፻፸፫፤ በጌታችን ፡ ደም ፡ የታተመች ፡ ያችን ፡
መጽሐፍ ፡ በአያት ፡ ጊዜ ፡ በፊቱ ፡ ሰገደ፤
አከበረው ፤ አቀፈውም ፡ በረቂቃን ፡
ክንፎቹም፡ጋረደው።
፻፸፬፤ ፈያታዊ ፡ ዘየማንንም ፡ መሬታዊ ፡ ሆይ ፡
በጌታህ ፡ ትእዛዝ ፡ መጥተሃልና ፡ ሰላምታ ፡
ይገባሃል ፡ አለው ፤ በረቂቃን ፡ መላእክት ፡
ማደሪያ፡ውስጥ፡ግባ፤በዚያም፡ደስ፡ይበልህ።
፻፸፭፤ አባትህ፡አዳም፡ከወጣባት፡ተድላ፡ደስታ፡
ከሚፈጸምባት፡ገነት፡ውስጥ፡ግባ።
፻፸፮፤ በሰማያት ፡ ካሉ ፡ የመላእክት ፡ ሠራዊት ፡
ጋራ፡ ወደ ፡ ሰማያዊ ፡ መንግሥት ፡ ገብተህ ፡
አንድ ፡ ሁን ፤ ፈያታዊ ፡ ሆይ ፡ ገብተህም ፡
ከቁስልህ ፡ ተፈወስ ፤ ለዚች ፡ ክብር ፡ ጌታህ ፡
ዝግጁ፡አድርጎሃልና።
፻፸፯፤ እነሆ ፡ ሰማያውያንና ፡ ምድራውያን ፡ በየነገ
ዳቸው ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ያደንቃሉ ፡ በምድር ፡
ወንበዴ፡ቀማኛ፡ሁነህ፡ኑረህ፡በኋለኛይቱ፡
ቀን ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ወራሽ ፡
ሁነሀልና።
፻፸፰፤ በዚያች፡ምድር፡ነፍስ፡ገዳይ፡ነበርክ፤በኋለ
ኛይቱ ፡ ቀን ፡ ረቂቁን ፡ የልጅነት ፡ ክብር ፡
ለመቀበል፡በቃህ።
፻፸፱፤ ፈያታዊ፡ሆይ፡የላከህ፡ንጉሥ፡ወዴት፡አለ?
ምን፡ይሠራል? መምጣቱስ፡እንዴት፡ዘገየ?
ይፈልገው ፡ ዘንድ ፡ ከከፍተኛ ፡ ማደሪያው ፡
ወርዶ፡የነበረው፡ ጌታ እነሆ፡አዳምን፡አድ
ኖታልና።
፻፹፤ ፈያታይም ፡ ለመልአኩ ፡ መለሰ፤ ሲኦልን ፡
ይበዘብዝ ፡ ዘንድ ፡ በዚያም ፡ ተማርከው ፡
የሚኖሩትን ፡ ነፍሳት ፡ ያወጣ ፡ ዘንድ ፡
ንጉሡ፡ወደ፡ሲኦል፡ወረደ፡አለው።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፹፩ ወበ፡ዐቢይ፡ኪን፡ላዕለ፡ምውታን፡እስመ፡
ውእቱ፡ይፈቅድ፡ያመዝብሮ፡ለሲኦል።

፹፪ ወናሁ፡ቦአ፡ንጉሥ፡ውስተ፡ሀገረ፡
ምውታን፡ከመ፡ያውዕኦሙ፡ለሙቁሓን፡
እስመ፡አስተዳለወ፡ለአዳም፡ልብሰ፡
ሕይወት፡ወሐረ፡ከመ፡ይክድን፡ኀፍረቶ፡
ወያውዕእ፡እመቤተ፡ሞቅሕ፡ዘሐነጸ፡
ሎቱ፡ጸላኢ።

፹፫ ቦአ፡ንጉሥ፡ኀበ፡ምውታን፡ወሰብሕዎ፡
በእንተ፡ድኅነቶሙ፡እስመ፡እሙንቱ፡
ነበሩ፡እንዘ፡ይሴፈውዎ፡በከመ፡ይሴፈዎ፡
ዘርዕ፡ለዝናም።

፹፬ መፍትው፡ለክሙ፡አ፡መላእክት፡ከመ፡
ትረዱ፡ውስተ፡ሲኦል፡ወበህየ፡ታርእዩ፡
ጽንዐ፡ኃይልክሙ።

፹፭ ለከ፡ይደሉ፡አ፡ገብርኤል፡ትረድ፡ውስተ፡
ሲኦል፡ቅድመ፡ወትርአዮ፡ለእግዚእከ፡እንዘ፡
ያሰምክ፡በህየ፡ከመ፡ብእሲ፡በከመ፡አቅደምከ፡
ዜንዎታ፡ለማርያም፡ቅድስት፡ድንግል።

፹፮ ወአንተኒ፡ሚካኤል፡ጽኑዕ፡ወኃያል፡ስርር፡
በጽንዐ፡ኀይልከ፡ወባእ፡ኀበ፡እግዚእከ፡
በከመ፡አርአይከ፡ጽንዐ፡ኀይልከ፡ለሕዝብ፡
ወአኅለፍኮሙ፡በማእከለ፡ባሕር።

፹፯ ረዱ፡ኵልክሙ፡ሠራዊተ፡ብርሃን፡ምስለ፡
ስብሐት፡ወማሕሌት፡ወተቀበልዎ፡ለእግ
ዚእክሙ፡ኢመፍትው፡የሀሉ፡ባሕቲቶ፡
ውስተ፡ሲኦል፡ተቀበልዎ፡እንከ፡
በስብሐት፡ወበማሕሌት፡ወዘምሮ፡
ወውዳሴ።

፹፰ በዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ለእመ፡ኀደግምዎ፡
ባሕቲቶ፡ወበውስተ፡ሲኦልኒ፡ኢይደል
ወክሙ፡ትርሐቁ፡እምኔሁ።

፹፱ አውሥአ፡መልአክ፡ወይቤሎ፡ለፈያታይ፡
አርምም፡አ፡ድኩም፡እስመ፡ለሞት፡
ሥልጣን፡አልቦቱ፡ላዕሌሁ፡ሶበ፡ኢፈቀደ፡
ኢይክልዎ፡አናቅጸ፡ሲኦል፡ይክልኑ፡
አንቄ፡ይንዐዎ፡ለአንበሳ፡ወእፎ፡ይክል፡
ሆባይ፡ድኩም፡ይምሥጦ፡ለነምር፡ጽኑዕ፡
እስመ፡መዊእ፡ለእግዚእ፡ባሕቲቱ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፻፹፩ ሙታንን፡ሕያዋን፡የሚያደርግበት፡
ታላቅ፡ጥበብ፡አለው፤ሞትን፡ያጠፋ፡
ዘንድ፡ወዷልና።

፻፹፪ እነሆ፡ንጉሡም፡የታሰሩ፡ነፍሳትን፡
ያወጣ፡ዘንድ፡ወደ፡ምውታን፡አገር፡ገባ፤
ኀፍረቱን፡ይሸፍንለት፡ዘንድ፡ለአዳም፡
የሕይወት፡ልብስ፡አዘጋጅቶለታልና፤
ጠላት፡ከሠለላትም፡ከሞተ፡ነፍስ፡
ያድነው፡ዘንድ፡ሄደ።

፻፹፫ ንጉሥ፡ሙታን፡ወደ፡አሉበት፡ገባ፤
እነርሱም፡ስለ፡ድኅነታቸው፡አመሰገኑት፤
ዘር፡ዝናምን፡በተስፋ፡እንደሚጠብቅ፤
እነርሱ፡በተስፋ፡ይጠብቁት፡ነበርና።

፻፹፬ መላእክት፡ሆይ፡ወደ፡ሲኦል፡ትወርዱ፡
ዘንድ፡በዚያም፡የኃይላችሁን፡ጽናት፡
ታሳዩ፡ዘንድ፡ለእናንተ፡ተገቢ፡ነው።

፻፹፭ ገብርኤል፡ሆይ፡ቀድሞ፡ለቅድስት፡
ድንግል፡ማርያም፡ልደቱን፡እንደ፡አበሠ
ርሃት፡አስቀድመህ፡በዚያም፡እንደ፡ሰው፡
ሲተኛ፡ታየው፡ዘንድ፡ይገባሃል።

፻፹፮ አንተም፡ጽኑዕ፡ኃያል፡የሆንክ፡ሚካኤል፡
ሆይ፡ጽኑዕ፡የሆነውን፡ኃይልህን፡በግብጻ
ውያን፡ላይ፡ገልጸህ፡የእስራኤልን፡ሕዝብ፡
በባሕር፡መካከል፡እንዳሳለፍካቸው፡ወደ፡
ጌታህ፡ፈጥነህ፡ግባ።

፻፹፯ እናንተ፡የብርሃን፡ሠራዊት፡ሁላችሁም፡
ከምስጋናና፡ከማሕሌት፡ጋራ፡ጌታችሁን፡
ለመቀበል፡ውረዱ፤በሲኦልም፡ውስጥ፡
ብቻውን፡ይሆን፡ዘንድ፡አይገባም፤እንግ
ዲህስ፡በክብር፡በማሕሌት፡በመዘመርና፡
በምስጋና፡ተቀበሉት።

፻፹፰ በመስቀል፡ላይ፡ብትተዉትም፡በሲኦል፡
ውስጥ፡ከእርሱ፡ትርቁ፡ዘንድ፡አይገባ
ችሁም።

፻፹፱ መልአኩም፡ለፈያታዊው፡እንዲህ፡ብሎ፡
መለሰ፤አንተ፡ድኩም፡በእርሱ፡ላይ፡ሞት፡
ሥልጣን፡የለውምና፤ዝም፡በል፤ባይፈቅድስ፡
የሲኦል፡አበጋዞች፡ባልቻሉትም፡ነበር፤
ጭላት፡አንበሳን፡ያድነው፡ዘንድ፡ይችላልን፤
ደካማ፡ዝንጀሮስ፡ብርቱውን፡ነብር፡
ይነጥቀው፡ዘንድ፡እንዴት፡ይችላል?ድል፡
አድራጊነት፡ለጌታ፡ብቻ፡ነውና፡አለው።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ፡ወእሕ

፻፺፡ እኮ፡ገብርኤል፡ዘገብረ፡ተአምራተ፡ወእሕ
የዎሙ፡ለሙታን።
፻፺፩፡ ወእኮ ፡ ሚካኤል ፡ ዘአሕየዋ ፡ ለወለተ ፡
ኢያኢሮስ፡እምት።
፻፺፪፡ ወኢ፡እመላእክት፡ዘአውኀዘ፡ማየ፡ወደመ፡
ለመድኃኒት።
፻፺፫፡ አላ፡ባሕቲቱ፡ወልድ፡ተዐገሠ፡በዝ፡ሕማም፡
በሥጋ፡ዘነሥአ፡እምቅድስት፡ድንግል፡
ከመ፡ያድኅኖ፡ለአዳም፡ወለዘርዑ።
ከመ፡ይትነሥኡ፡
፻፺፬፡ ኄጠ፡ወልድ፡ለሰይጣን፡ከመ፡ይትነሥኡ፡
ላዕሌሁ፡አይሁድ፡እስከ፡ሶበ፡እምጽኡ፡
ላዕሌሁ፡ኮነኔ፡እስመ፡ሶበ፡ተቃረኖ፡
ለሰይጣን፡በመለኮቱ፡እምኢኮነ፡መንክረ፡
ዘእንበለ፡ባሕቲቱ፡ፈቀደ፡ይማእ፡በውእቱ፡
ሥጋ፡ዘተመውአ፡እምኀቤሁ።

፻፺፭፡ ለከ፡እብለከ፡አ፡ፈያታዊ፡ናሁ፡ሰማዕነ፡
ቃለ፡ንጉሥ፡ወሰገድነ፡ለመልእክቱ፡ወተአ
ዘዝነ፡ሎቱ።
፻፺፮፡ ወእምዝ፡ነሥአ፡መልአክ፡ኵናተ፡እሳት፡
ወገድፀ፡አንቀጸ፡ገነት፡ወተርኅወ፡
ኀዋኀው።
፻፺፯፡ ወይቤሎ፡ለፈያታዊ፡ባእ፡ውስተ፡ብሔረ፡
ሕያዋን፡ዘወፅአ፡እምኔሁ፡አቡከ፡አዳም፡
ወተፈሥሕ፡ምስለ፡መላእክት፡እስመ፡ናሁ፡
መጽአ፡ንጉሠ፡ስብሐት፡ለመድኃኒትከ።

፻፺፰፡ ወአሥመረ፡አባሁ፡በክዒወ፡ደሙ፡
ወነሥተ፡አረፍተ፡ማእከል፡ዘማእከሌነ፡
ወማእከሌክሙ።

፻፺፱፡ ኦውሥአ፡ፈያታይ፡ወይቤሎ፡ለመልአክ፡
እምይእዜሰ፡ተመየጥ፡ውስተ፡ብሔርከ፡
ወግባዕ፡ውስተ፡ቅኔ፡ዚአከ፡እስመ፡ናሁ፡
ንህነ፡ገባዕነ፡ውስተ፡ብሔርነ፡ወኮነ፡
ድልዋነ፡ንንበር፡ውስተ፡ዘቀዳሚ፡ርስትነ፡
ወቦቱ፡ንትፌሣሕ፡ወንትሐሠይ።
፪፻፡ ቦኑ፡አርዐቱ፡ለሰማያዊ፡ዘአቍሰለ፡መታከ
ፍቲከ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ትፈቅድ፡ትኩን፡
ዐቃቤሃ፡ለገነት፡እኮ፡ከመዝ፡ዘእንበለ፡
ዳእሙ፡በእንተ፡ኀጢአትነ፡እኮ፡ለነ፡
ዕረፍት።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፻፺፡ ተአምራት፡አድርጎ፡ሙታንን፡በሕይወት፡
ያስነሣቸው፡ገብርኤል፡አይደለም።
፻፺፩፡ የኢያኢሮስንም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ከሞተች፡
በኋላ፡ያስነሣት፡ሚካኤል፡አይደለም።
፻፺፪፡ ከመላእክትም፡አንዱ፡ለዓለም፡መድኃኒት፡
ውኃና፡ደምን፡ያፈሰሰ፡የለም።
፻፺፫፡ አዳምንና፡ልጆቹን፡ያድን፡ዘንድ፡ከቅድስት፡
ድንግል፡በነሣው፡ሥጋ፡የእግዚአብሔር፡
ልጅ፡በዚህ፡ሁሉ፡መከራ፡ታገሠ፡እንጂ።
፻፺፬፡ በእርሱ፡ላይ፡የሞት፡ፍርድ፡እስከሚያመ
ጡበት፡አይሁድን፡እስከ፡እነሣሣበት፡
ድረስ፡ዲያብሎስን፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡
ሸነገለው፤ አስቀድሞ፡በእርሱ፡ድል፡
በተነሣው፡በዚህ፡ሥጋ፡ድል፡ያደርገው፡
ዘንድ፡ወደደ፡እንጂ፤በመለኮቱ፡ኃይል፡ድል፡
አድርጎት፡ቢሆን፡ባልተደነቀም፡ነበር።
፻፺፭፡ ፈያታዊ፡ሆይ፡አንተን፡እናገርሃለሁ፤እነሆ፡
የንጉሥን፡ቃል፡ሰምተን፡ለክብሩ፡
ሰግደናል፤ለመልእክቱም፡ታዝዘናል።
፻፺፮፡ ከዚህ፡በኋላ፡መልአኩ፡የእሳቱን፡መውጊያ፡
አንሥቶ፡የገነትን፡መዝጊያዎች፡ደቃ፤መዝ
ጊያዎቹም፡ተከፈቱ።
፻፺፯፡ ፈያታዊውንም፡አባትህ፡አዳም፡ከወጣበት፡
የሕያዋን፡ሀገር፡ወደ፡ሆነች፡ገነት፡ግባተህ፡
ከመላእክት፡ጋራ፡ደስ፡ይበልህ፤የክብር፡
ባለቤት፡ጌታ፡አንተን፡ለማዳን፡ሰው፡
ሁኖአልና፡አለው።
፻፺፰፡ ደሙን፡በማፍሰሱም ለአባቱ፡ያማረ፡
መሥዋዕት፡ሆነ፤ በእኛና፡በእናንተ፡
መካከል፡የነበረውን፡የጥል፡ግድግዳንም፡
አፈረሰ።
፻፺፱፡ ፈያታዊውም፡መልሶ፡መልአኩን፡እንዲህ፡
አለው፤እንግዲህስ፡ወደቦታህ፡ተመለስህ፡
ወደ፡ሥራህ፡ግባ፤እነሆ፡እኛ፡ወደ፡
ሀገራችን፡ተመልሰን፡ወደ፡ቀድሞውም፡
ርስታችንም፡እንኖር፡ዘንድ፡ዝግጁዎች፡
ሁነናልና፤በዚያም፡ፈጽሞ፡ደስ፡ይለናል።
፪፻፡ በውኑ፡የሰማያዊ፡ንጉሥ፡ቀንበሩ፡ሚጎንቃህን፡
አቁስሎታልን? ስለዚህ፡የገነት፡ጠባቂ፡
ትሆን፡ዘንድ፡ትወዳለህን?እንዲህ፡አይደለም፡
በኃጢአታችን፡ምክንያት፡ገነት፡የኛ፡
ማረፊያ፡አልሆነችም፡ነበር።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እምይእዜሰ ፡ ተመየጥ ፡ ወግባእ ፡ ውስተ ፡ ተግባርከ፡ይኄይሰከ፡እምዘተዐቅብ፡ገነተ።
ለሁ፡እንከ፡ከመ፡ውእቱ፡ቃል፡ዘአዘዘከ፡ከመ፡ትዕቀባ፡ለገነት፡ውእቱኬ፡ዘጸሐፈ፡ሊተ፡ዘንተ፡መጽሐፈ።
ቡሩክ ፡ ውእቱ ፡ **እግዚእከ** ፡ ዘአውረሰነ ፡ መንግሥተ፡ሰማያት።
ዘሎቱ፡ክብር፡ወስብሐት፡ወመንግሥት፡ወኃይል፡ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን፤ወአሜን፡ለይኩን፡ለይኩን።

አንቀጽ፡ዕሥራ፡ወተስዐቱ።

እመጽሐፈ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ዘአበዊነ ፡ ሐዋርያት ፡ በረከቶሙ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ወጊዜ፡ሠለስቱ፡ሰዓት፡አዕረግዎ፡ዲበ፡ዕፅ፡ወበስድስቱ፡ሰዓት፡ሰቀልዎ፡ወአስተይዎ፡ብሒአ፡ከርቤ፡ቱሱሐ፡ምስለ፡ሐሞት፡ወነሥኡ፡አልባሲሁ፡ወተካፈሉ፡በበይናቲሆሙ።
ወሰቀሉ ፡ ምስሌሁ ፡ ክልኤተ ፡ ፈያተ ፡ ገባርያነ፡እኪት፡አሐደ፡በየማኑ፡ወአሐደ፡በፀጋሙ።
ከመ፡ይትፈጸም፡ጽሑፍ፡ዘይብል፡ወወደዩ፡ሐሞተ፡ውስተ፡መብልዕየ፡ወአስተዩኒ፡ብሒአ፡ለጽምእየ።
ወካዕበ፡ይቤ፡ተዓዐዉ፡ዲበ፡ዐራዝየ፤ወቦ፡ገብ፡ይብል፡ተኈለቈ፡ምስለ፡ዐማፅያን፡ወምስለ፡ገበርተ፡ዐመፃ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፻፲፩፤ እንግዲህ፡ግን፡ገነትን፡ከመጠበቅ፡ይሻል ሃልና፡ወደ፡ተግባርህ፡ተመልሰህ፡ግባ።
፻፲፪፤ ገነትን፡እንድትጠብቅ፡አዛህ፡የነበረ፡ቃል፡ይህን፡ደብዳቤ፡የጻፈልኝ፡እርሱ፡እንደሆነ፡አስተውል።
፻፲፫፤ ሰማያዊ፡መንግሥቱን፡ያወረሰን፡**ጌታህ**፡ቡሩክ፡ምስጉን፡ነው።
፻፲፬፤ ምስጋናና፡ክብር፡ገዢነትና፡ኃይል፡ለእርሱ፡ገንዘቡ፡የሆነ፡ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን፤በእውነት፡ይሁን፡ይሁን።

ሃያ፡ዘጠነኛ፡አንቀጽ።

በረከታቸው፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘለዓለሙ፡ትኑርና፡አባቶቻችን፡ሐዋርያት፡ከጻፉት፡ከዲድስቅልያ፡መጽሐፍ፡የተገኘ፡ሃያ፡ዘጠነኛው፡አንቀጽ፡ይህ፡ነው።

፩፤ በሦስት፡ሰዓት፡በዕንጨት፡ላይ፡አወጡት፡በስድስት፡ሰዓትም፡ሰቀለው፡ከርቤ፡የተቀላቀለበትን፡ሐሞት፡አጠጡት፤ልብሱንም፡ወስደው፡እርስ፡በርሳቸው፡ተካፈሉ።
፪፤ ከእርሱ፡ጋርም፡ክፉ፡አድራጊዎች፡የሆኑ፡ሁለት፡ወንበዴዎችን፡አንዱን፡በቀኙ፡አንዱን፡በግራው፡ሰቀሉ።
፫፤ በምግቤ፡ሐሞትን፡ጨመሩበት፤ጥማቴን፡ለማራቅ፡መፃፃውን፡አጠጡኝ።
፬፤ ዳግመኛም፡በመጐናጸፊያዬ፡ላይ፡ዕጣ፡ተጣጣሉበት፡ያለው፡ጽሑፍ፡ይፈጸም፡ዘንድ፤ከዐመፀኞችና፡ዐመፅን፡ከሚሠሩ፡ጋር፡ተቈጠረ፡የሚልም፡አለ።

ወጸመ ቀነዉዎ አይሁድ ለንጉሥ ለእግዚእነ::



አይሁድ ጌታችንን በችንካር እንደቸነከሩት::

ወእምዝ፡ኮነ፡ጽልመት፡ሠለስተ፡ሰዓተ፡እምስድስቱ፡ሰዓት፤እስከ፡ተሱዓት፡ሰዓት።
በረከቶሙ፡ለሐዋርያት፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፭፤ ከዚህ፡በኋላ፡ለሦስት፡ሰዓት፡ያህል፡ከስድስት፡ሰዓት፡እስከ፡ዘጠኝ፡ሰዓት፡ጨለማ፡ሆነ።
የሐዋርያትም፡በረከታቸው፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡አሜን።

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ድርሳን፡ወትምህርት፡ዘአበው፡ሐዋርያት፡
ቅዱሳን፡ዘመሀሩነ።
፩፡ ወእምዝ፡ሖረ፡አሐዱ፡እምኔሆሙ፡ከመ፡
ያምጽእ፡ቅንዋተ፡ወካልኡ፡ያምጽእ፡ዕፀ፡
መስቀል፡ወሣልሱ፡ሰፍነግ፡ወራብዑ፡
መስቀል፡ወኀምሱ፡
አምጽአ፡ጽዋዐ፡ከል፡(ብሂእ)፡ወኃምሱ፡
ይስሕል፡ኲናተ።
፪፡ ወኵሎሙ፡አምጽኡ፡ዘዘዚአሆሙ፡እኪተ፡
ምግባሮሙ።
፫፡ ወቦ፡እምኔሆሙ፡ዘተፍኡ፡ምራቀ፡ውስተ፡
ገጹ፡ወተመየንዎ፡ወተቃጸብዎ፡ወኰርዕዎ፡
ርእሶ፡በኀለት፡ወጸፍዕዎ፡ገጾ፡በእኪት።

፬፡ ወእግዚእ፡ኢየሱስ፡ያረምም፡ወይትዔገሥ፡
ዘንተ፡ኵሎ፡ወኢያውሥአ፡ቃለ፡ከመ፡በግዕ፡
በቅድመ፡ዘይቀርፆ፡ወየሐርዶ፡እስከ፡
ይበጽሕ፡ዕድሜሁ።
፭፡ ወከማሁ፡ኢነበበ፡በሕማሙ፡እስከ፡
ይነሥእዋ፡ለሕይወቱ።

፮፡ ወሶበ፡ፈጸሙ፡አይሁድ፡ምግባሮሙ፡እኪተ፡
እስመ፡ርጉማን፡ሕዝበ፡አዕረቅዎ፡ዘአልበስዎ፡
ልብሰ፡ቀይሐ፡ወአቅነትዎ፡ውስተ፡ሐቌሁ።
፯፡ ወአሰርዎ፡እደዊሁ፡ወእገሪሁ፡ዲበ፡ዕፀ፡
መስቀል፡ወኍለቈ፡ኵሎ፡አዕፅምቲሁ፡
ወቀነውዎ፡በቅንዋት፡ክልኤተ፡ቅንዋተ፡
ውስተ፡እደዊሁ፡ወአሐደ፡ቀኖተ፡ውስተ፡
እገሪሁ።
፰፡ ወቀነውዎ፡ማእከለ፡ዕፀ፡ወአልዐሉ፡
መስቀለ፡ወአቀምዎ፡በእገሪሁ፡እንዘ፡
እሱራን፡ታሕተ፡ወእደዊሁ፡እሱራት፡
ወስፉሐት፡በቅንዋት፡ላዕለ፤ወገጹ፡መንገለ፡
ምዕራብ።
፱፡ ወክልኤተ፡ፈያተ፡ሰቀሉ፡ምስሌሁ፡አሐደ፡
በየማኑ፡ወአሐደ፡በፀጋሙ፡ወእግዚእ፡
ኢየሱስ፡ማእከሎሙ።
፲፡ ወዮሐንስ፡ረድእ፡ቀዊሞ፡ይሬኢ፡ኵሎ፡ከመ፡
ይኩን፡ሰማዕተ፡በእንተ፡ኵሉ፡እምቀዳሚ፡
እስከ፡ደኃሪ።
፲፩፡ ወሶበ፡ርእዮ፡ለእግዚኡ፡ስቁለ፡ደንገፀ፡
ወሐዘነ፡በኵሉ፡መንፈሱ፡ወአውኀዘት፡
ዐይኑ፡አንብዐ፡መሪረ።
፲፪፡ ወሐረ፡እንዘ፡ያፈጥን፡ወበጽሐ፡ኀበ፡ሀለወት፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

የከበሩ፡አባቶች፡ሐዋርያት፡ያስተማሩን፡
ትምህርትና፡ድርሳን፡ይህ፡ነው።
፩፡ ከዚህ፡በኋላ፡ከእነርሱም፡አንዱ፡ችንካርን፡
ሊያመጣ፡ሄደ፤ሁለተኛውም፡መስቀያ፡
ዕንጨት፤ሦስተኛው፡ሰፍነግ፤(ውኃ፡
መጣጭ)፡አራተኛውም፡መፃፃ፡የያዘ፡ጽዋ፡
አምስተኛውም፡ጦርን፡ይስል፡ነበር።
፪፡ ሁሉም፡የየራሳቸውን፡ለክፋት፡የሠሩትን፡
አመጡ።
፫፡ ከእርሳቸውም፡በፊቱ፡ላይ፡ምራቃቸውን፡
የተፉ፡አሉ፤ተተናኰሉትም፡ተቀጣጠ
ቡበት፤ራሱንም፡በዘንግ፡መቱት፤ፊቱንም፡
መላልሰው፡ጸፉት።
፬፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡ይህን፡ሁሉ፡በዝምታ፡
ታግሥ፡ተቀበለ፤በሚሸልተውና፡በሚያ
ርደው፡ፊት፡እንደማይናገር፡በግ፡ጊዜው፡
እስከሚደርስ፡ምንም፡ቃልን፡አልመለሰም።
፭፡ እንዲሁም፡በእነሱ፡ምክንያት፡ሕይወቱን፡
እስከሚያሳልፉት፡ድረስ፡በመከራው፡ጊዜ፡
አልተናገረም።
፮፡ አይሁድም፡ክፉ፡ሥራቸውን፡ከፈጸሙ፡በኋላ፡
የተረገሙ፡ናቸውና፤ያለበሱትን፡ቀይ፡ልብስ፡
ገፈው፡በወገቡ፡ቀይ፡ግምጃ፡አስታጠቁት።
፯፡ እጆቹንና፡እግሮቹን፡በዕንጨት፡መስቀል፡
ላይ፡አሰሩት፤አጥንቶቹንም፡ሁሉ፡ቈጠሩ፤
በችንካሮችም፡ቸነከሩት፤ሁለት፡ችንካ
ሮችን፡በእጆቹ፡አንድ፡ችንካር፡በእግሮቹ።
፰፡ እጆቹ፡ከላይ፡ተዘርግተው፡በችንካሮች፡እን
ደታሠሩ፤እግሮቹም፡ከታች፡በችንካር፡
ታሥረው፡ሳለ፡መስቀሉን፡አንስተው፡ከፍ፡
አድርገው፡ተከሉት፤ፊቱም፡ወደምዕራብ፡
ነበር።
፱፡ ሁለት፡ወንበዴዎችንም፡አምጥተው፡
አንዱን፡በቀኝ፡አንዱን፡በግራው፡ሰቀሉ፤
ጌታ፡ኢየሱስን፡በመካከላቸው።
፲፡ ደቀ፡መዝሙሩ፡ዮሐንስም፡ስለ፡አየው፡
ሁሉ፡ምስክር፡ይሆን፡ዘንድ፡ከመጀመሪያ፡
እስከ፡መጨረሻ፡ቆሞ፡ይመለከት፡ነበር።
፲፩፡ ጌታውንም፡ተሰቅሎ፡በአየው፡ጊዜ፡ደነገጠ፤
በፍጹም፡ልቡናውም፡አዘነ፡ዐይኑ፡መራራ፡
ዕንባን፡አፈሰሰች።
፲፪፡ ፈጥኖ፡ሂዶ፡እመቤታችን፡ድንግል፡ማርያም፡

እግዚአትየ…
እግዚአትየ፡ማርያም፡ እሙ፡ለእግዚአብሔር፡
ቃል፡ተንሥኢ፡ ወንዒ፡ ምስሌየ፡ ከመ፡
አብጽሕኪ፡ ኀበ፡ ሰቀልዎ፡ ለወልድኪ፡
የሐድ፡ ሕዝበ፡ አይሁድ፡ ትርአዩዮ፡
አምቅድመ፡ይቅትልዎ።
፲፫ ወሶበ፡ሰምዐት፡እግዝእትነ፡ማርያም፡ ዘንተ፡
ወድቀት፡በገጸ፡ዲበ፡ምድር፡ወኮነት፡ከመ፡
በድን፡እስከ፡በጽሐት፡ለመዊት።
፲፬ ወአኀዛ፡ ዮሐንስ፡ ወአንሥኣ፡ ወአጽንዓ፡
ወሖረ፡ ምስሌሃ፡ እስከ፡ ቀራንዮ፡ እንዘ፡
የዐወይዉ፡ ክልኤሆሙ፡ ወይበክዩ፡ ብካየ፡
መሪረ።
፲፭ ወካልአን፡ እለ፡ ሀለዉ፡ ምስሌሆሙ፡
ውእቶሙኒ፡ይበክዩ።
፲፮ ወአንስት፡መፍቀርያተ፡እግዚእ፡ ውእቶንሂ፡
ይበክያ፡በእንተ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ ወያስተ
በፅዓ፡እምሥን፡ላሕያ።
፲፯ ወሶበ፡ ርእየቶ፡ እግዝእትነ፡ ማርያም፡
ድንግል፡ ለዋሕድ፡ወልዳ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡
ኢክህለ፡ ያርምም፡ ዐይና፡ እምአንብዕ፡
ተአንበዘ፡ ልባ፡ ውስተ፡ ከርሣ፡ ወውዕየ፡
ነፍሳ፡ ወቀብጸት፡ ሕይወተ፡ ነፍሳ፡ ወሥጋሃ፡
ወኵሎን፡ መለያልዩሃ፡ ይርዕዳ፡ ወጸልመ፡
ኃሊናሃ፡ወአልጸቀት፡ትፃእ፡ነፍሳ።
፲፰ ወለእመ፡ኢያጽንዐ፡ልባ፡ወልዳ፡ፍቁር፡እም
ወፅአት፡ይእተ፡ጊዜ፡ነፍሳ።
፲፱ ወይእቲ፡ ትሬእዮሙ፡ ለአይሁድ፡ እንዘ፡
ይትፌሥሑ፡ዐቢየ፡ፍሥሓ፡በእንተ፡ዘገብሩ፡
እኩየ፡ላዕሌሁ።
፳ ወርእየት፡ አክሊለ፡ ሦክ፡ ዘዲበ፡ ርእሱ፡
ወርእየት፡ቅንዋተ፡እደዊሁ፡ወእገሪሁ።
፳፩ ወበመሳምር፡ኀበ፡ቀነውዎ፡ይውኅዝ፡ደሙ፡
ዲበ፡ምድር።
፳፪ ወርእየቶሙ፡ እንዘ፡ ያስተበርኩ፡ ወይት
ቃጸቡ፡ወይሣለቁ፡ላዕሌሁ፡እንዘ፡ይብሉ፡አ፡
ንጉሠ፡አይሁድ፡ሰላም፡ለከ።
፳፫ ወርእየት፡ጽዋዐ፡ብሒእ፡ዘንቡር፡ቅድሜሁ፡
ወሰፍነግ፡ አርሒሰሙ፡ …

… ድርስ፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡
እናቱ፡እመቤቴ፡ማርያም፡ ሆይ፡የአይሁድ፡
ሕዝብ፡ አንድ፡ ልጅሽን፡ ወደ፡ ሰቀሉበት፡
ቦታ፡ ከመግደላቸው፡ በፊት፡ ታይው፡ ዘንድ፡
እንዳደርስሽ፡ተነሺ፤ከእኔ፡ጋር፡ነዪ፡እንሂድ፡
አላት።
፲፫፤ እመቤታችን፡ማርያምም፡ ይህን፡ በሰማች፡
ጊዜ፡ ከምድር፡ ላይ፡ በግንባርዋ፡ ወድቃ፡
እንደ፡ በድንም፡ ሆነች፤ ለመሞት፡ እስከምት
ደርስ፡ድረስ።
፲፬፤ ዮሐንስም፡ ይዞ፡ አንሥቶ፡ አጽናናት፤ ወደ፡
ቀራንዮም፡እስኪደርሱ፡ሁለቱም፡እየጮኹ፡
መራራ፡ልቅሶም፡እያለቀሱ፡አብረው፡ሄዱ።
፲፭፤ ሌሎችም፡ ከእነርሱ፡ ጋር፡ የነበሩ፡ ያለቅሱ፡
ነበር።
፲፮፤ ጌታን፡ የሚወዱ፡ ሴቶችም፡ እነርሱም፡ ስለ፡
ጌታ፡ ኢየሱስ፡ ያለቅሱ፡ ነበር፤ ከደም፡
ግባቷም፡የተነሣ፡ያደንቁ፡ነበር።
፲፯፤ እመቤታችን፡ ድንግል፡ ማርያም፡ አንድ፡
ልጅዋን፡በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡በአየችው፡
ጊዜ፡ ዕንባ፡ ከማፍሰስ፡ ዐይኗ፡ አልተገታም፤
ልቡናዋም በሰውነቷ፡ ውስጥ፡ በሐዘን፡ ተቅበ
ዘበዘ፤አንጀቷም፡ነደደ፤በነፍሷና፡በሥጋዋም፡
ድኅነት፡ተስፋ፡ቆረጠች፤ሕዋሳቶቿ፡ሁሉ፡ተን
ቀጠቀጡ፤ልቡናዋም፡በሐዘን፡ብዛት፡ጨለመ፤
ነፍሷም፡ልትለይ፡ደረሰች።
፲፰፤ ተወዳጅ፡ልጅዋ፡ልቧን፡ባያጽናና፡ያን፡ጊዜ፡
ነፍሷ፡ከሥጋዋ፡በተለየች፡ነበር።
፲፱፤ በእርሱ፡ላይ፡ክፉ፡ሥራ፡ስለ፡ሠሩ፡ፈጽሞ፡
ደስ፡ብሏቸው፡አይሁድን፡አየቻቸው።
፳፤ በራሱ፡ላይ፡ያለውን፡የእሾኽ፡ዘውድ፡የእጆ
ቹንም፡የእግሮቹንም፡ችንካሮች፡አየች።
፳፩፤ በምስማሮች፡ ከቸነከሩበትም፡ ላይ፡ ደሙ፡
ወደ፡ምድር፡ይፈስ፡ነበር።
፳፪፤ እየተንበረከኩ፡እየተጠቃቀሱ፡እየዘበቱበት፡
የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ ሆይ፡ ሰላም፡ ለአንተ፡
ይሁን፡ሲሉ፡አየቻቸው።
፳፫፤ በፊቱ፡ ያኖሩለትን፡ የመፃፃውን፡ ጽዋ፡
ነክረው፡ በአፉ፡ ውስጥ፡ የሚጨምቁበትን፡

Scanned by CamScanner

## በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ውስተ፡አፉሁ።

፳፬፡ ወርእየት፡ኵናተ፡ስሑለ፡በዘይረግዝዎ፡ገቦሁ፡
ቅድስተ፡ለዋህድ፡ወልደ፡እግዚአብሔር።

፳፭፡ ወሰምዐቶሙ፡እንዘ፡ይረግምዎ፡በምልያሙ፡
እምቀዳሚ፡እስከ፡ደኃሪ፡ዘይገብሩ፡ኵሎ።

፳፮፡ ወሶበ፡ርእየት፡ዘንተ፡እግዝእትነ፡ማርያም፡
ወዘ ደንገፀት፡ወኢተአምር፡ኀበ፡ዘተሐውር፡
ትገብር፡ወትበኪ፡ኀበ፡መስቀሉ፡በሐዘነ፡
ልብ፡እንዘ፡ትብል፡ወይ፡ሊተ፡እ፡ወልድየ፡
አሌ፡ሊተ፡ወአይ፡አዕይንት፡ዘይሬእያከ፡
እንዘ፡ይገብሩ፡እኩየ፡ላዕሌከ።

፳፯፡ ወአንተሰ፡ኢገበርከ፡እኩየ፡ዘእንበለ፡
ሠናያት፡ላዕሌሆሙ፡ከመ፡ዝ፡ረሰዩከ፡
ምስለ፡ፈያት፤ወእሉ፡እለ፡ሰቁላን፡ምስሌከ፡
አሕሰሙ።

፳፰፡ ወንዓ፡ዮም፡ኵልክን፡አንስት፡እለ፡
ወለድክን፡ከመ፡ታእምራ፡ሕማመ፡ዘላዕለ፡
ወልድየ፡ወከመ፡ትብክያ፡ምስሌየ፡ላዕለ፡
ወልድየ፡ዋህድየ፡ዘተወልደ፡እምኔየ፡
ዘእንበለ፡ርኩስ።

፳፱፡ ወርእየ፡በአዕይንትየ፡እቤ፡እግዚእ፡
ተመጠዋ፡ለነፍስየ፡እምቅድመ፡ይርአያ፡አዕ
ይንትየ፡እንዘ፡ይጠብሑከ፡ወይረግዙከ፡
አማንየ፡እ፡ወልድየ።

፴፡ ወሶበ፡ርኢኩ፡እንዘ፡ይኴንኑከ፡ወያሐ
ምሙከ፡ሐጸት፡ነፍስየ፡በእንቲአከ።

፴፩፡ ወሶበ፡ርእየ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ለእሙ፡
ውዕየተ፡ከርሣ፡ወእንዘ፡ታነብዕ፡
ወታውኀዝ፡አንብዐ፡መሪረ፡ኢፈቀደ፡ከመ፡
ትርአዮ፡እንዘ፡ያሰትይዎ፡ሐሞተ፡ወብሒአ፡
መሪረ።

፴፪፡ ወኢፈቀደ፡ትርአዮ፡እንዘ፡ይወግእዎ፡
በኵናት፡ከመ፡ኢትሙት፡በእንቲአሁ።

፴፫፡ ወይቤላ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡እ፡ብእሲቶ፡ዝ፡
ውእቱ፡ወልድኪ፡ወይቤሎ፡ለዮሐንስኒ፡
ዛቲ፡ይእቲ፡እምከ።

፴፬፡ ወበውእቱ፡ጊዜ፡ነሥአ፡ውእቱ፡ረድእ፡
ወአዕተዋ፡ቤቶ፡እንዘ፡ትበኪ፡ወትኬልሕ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ሰፍነግ፡አየች።

፳፬፤ የአንድ፡የእግዚአብሔርን፡ልጅ፡የከበረች፡
ጎኑን፡ሊወጉበት፡የሳሉትን፡ጦርም፡አየች።

፳፭፤ ሁሉም፡በሙሉ፡ሲረግሙት፤ከመጀመሪያ፡
እስከ፡መጨረሻ፡ሰማቻቸው፤የሚያደርጉ
ትንም፡ሁሉ፡አየች።

፳፮፤ እመቤታችን፡ማርያምም፡ይህን፡በአየች፡
ጊዜ፡ደነገጠች፤ወዴት፡እንደምትሄድ፡ምን፡
እንደምትሠራም፡አታውቅም፡ነበር፤በመስ
ቀሉም፡አጠገብ፡ሁና፡ልጄ፡ሆይ፡ወዮልኝ፡
ወዮልኝ፡ይህን፡ክፉ፡ሥራ፡በአንተ፡ላይ፡
ሲሰሩ፡የሚያዩ፡ዐይኖች፡ምን፡ዐይኖች፡
ናቸው፡እያለች፡በልቧ፡አዝና፡ታለቅስ፡ነበር።

፳፯፤ አንተ፡ግን፡ከበጎ፡በቀር፡በእነርሱ፡ላይ፡
ክፋት፡አላደረግህም፤ከወንበዴዎች፡ጋር፡
እንዲህ፡አድርገው፡ሰቀሉህ፤እነርሱም፡
አብረውህ፡የተሰቀሉት፡ክፉ፡ነገርን፡
ተናገሩህ።

፳፰፤ የወለዳችሁ፡ሴቶች፡ሁሉ፡በልጄ፡ላይ፡የደረ
ሰውን፡መከራ፡ታዩ፡ዘንድ፡ያለ፡ርኵሰት፡
ከእኔ፡በተወለደ፡በአንድ፡ልጄ፡ላይ፡ከእኔ፡
ጋር፡ታለቅሱለት፡ዘንድ፡ዛሬ፡ሁላችሁ፡
ወደኔ፡ኑ።

፳፱፤ መከራውንም፡አይቼ፡ሲወጉህና፡ሲሰቁኸ፡
ዐይኖቼ፡ከማየታቸው፡በፊት፡ልጄ፡ሆይ፡
የምለው፡ዕውነቴን፡ነውና፡ነፍሴን፡
ውሰዳት፡እላለሁ።

፴፤ ፈጽመው፡ሲያሰቃዩህ፡በአየሁ፡ጊዜ፡
ሰውነቴ፡ስለ፡አንተ፡አለቀች።

፴፩፤ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ፈጽማ፡መራራ፡ልቅሶ፡
እያለቀሰች፡ዕንባዋን፡ስታፈስ፡የእናቱን፡
አንጀት፡መቃጠል፡በአየ፡ጊዜ፡መራራ፡
ሐሞትንና፡መፃፃውን፡ሲያጠጡት፡ታየው፡
ዘንድ፡አልወደደም።

፴፪፤ ስለ፡እርሱም፡እንዳትሞት፡በጦር፡
ሲወጉትም፡እንድታየው፡አልፈቀደም።

፴፫፤ ጌታ፡ኢየሱስ፡አንቺ፡ሆይ፡ልጅሽ፡ይህ፡
ነው፡ አላት፤ዮሐንስንም፡እናትህ፡ይህቺ፡
ናት፡አለው።

፴፬፤ ወዲያውኑ፡ይህ፡ደቀ፡መዝሙር፡ፈጽሞ፡አ
ለቀሰች፡ሳለ፡ወደ፡ቤቱ፡ወሰዳት።

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፴፭ ወእምድኅረዝ፡ኢያእመረት፡ዘይሬስይዎ።

፴፮ ወተመይጠ፡ዮሐንስ፡እንዘ፡ያፈጥን፡ወቆመ፡
ኅበ፡ገቦሁ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡እንዘ፡ይበኪ፡
ወሰምዐ፡ቃሎ፡ለፈያታዊ፡እንዘ፡ይጸርፍ፡
ላዕለ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡ለእመሰ፡
ኮንከ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡አድኅን፡
ርእሰከ፡ወኪያነሂ።
፴፯ ወካልኡ፡ፈያታይ፡ዘስቁል፡በየማን፡ገሠጸ፡
ወይቤሎ፡ኢትፈርሆኑ፡ለእግዚአብሔር፡
አምላክከ፡ለነሰ፡በአማን፡ይደልወነ፡
ወበከመ፡ምግባሪነ፡ተፈደይነ።
፴፰ ውእቱሰ፡እምላዕሉ፡ውእቱ፤በአማን፡
ወልደ፡እግዚአብሔር፡ዝንቱ፡ዘስቁል፡
ምስሌነ፡እንዘ፡አልቦ፡ኃጢአት፡ወኢ፡
ሐሰት፡ውስተ፡አፉሁ፡ወውእቱ፡በፈቃዱ፡
መጠወ፡ነፍሶ፡ለሞት፡ከመ፡ያድኅን፡
ነፍሳቲነ።
፴፱ ወሰበ፡ፈጸመ፡ዘንተ፡ነገረ፡ለካልኡ፡ይቤሎ፡
ፈያታይ፡ዘየማን፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡
ተዘከረኒ፡እግዚኦ፡አመ፡ትመጽእ፡በመንግ
ሥትከ።
፵ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ወይቤሎ፡አማን፡እብ
ለከ፡ከመ፡ትሄሉ፡ምስሌየ፡ዮም፡ውስተ፡ገነት።

ማህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ተግሣጽ፡ዘዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ።

፩ በከመ፡ነገሥት፡የኀይጡ፡መርዔቶሙ፡
በጽሒፈ፡ክታባት፡ወላእካን፡ወሰብአ፡
ውስጥ፡ወዘአምሳሊሆሙ።
፪ ወለእመ፡ኢተመይጡ፡እምዕልወቶሙ፡
ወኢገብኡ፡እምእከየ፡ምግባሮሙ፡ወኢእ
ሙስና፡ኀሊናሆሙ፡ትሬእዮሙ፡ወይትሜሰሉ፡
በአስኬማ፡ባዕድ፡እምነጋድያን፡አው፡እመስተ
ገብር፡አው፡ከመ፡እለ፡ይፈቅዱ፡ይባኡ፡
ውስተ፡ሀገሮሙ፡ወይትመየጡ፡ማእከለ፡
መራቶሙ፡ከመ፡ይኂጥዎሙ።
፫ አመበ፡ከመ፡ይለብዉ፡ወያቅርቡ፡ሎሙ፡
መፍቅዳተ፡ሠናየ፡ከመ፡ይምጽኡ፡ኀበ፡
ተአገዘ፡ወይሕየዉ፡ወኢይትሀጐሉ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፴፭ ከዚህ፡በኋላ፡ልጅዋን፡የሚያደርጉትን፡አላ
ወቀችም።
፴፮ ዮሐንስም፡ፈጥኖ፡ተመልሶ፡እያለቀሰ፡
በጌታ፡ ኢየሱስ፡አጠገብ፡ቆመ፤ወንበ
ዴውም፡በጌታ፡ኢየሱስ፡ላይ፡የሚናገረውን፡
የስድብ፡ቃል፡አንተ፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡
ከሆንክ፡ራስህን፡አድን፤እኛንም፡አድነን፡
ሲል፡ሰማ።
፴፯ በቀኝ፡የተሰቀለው፡ሌላው፡ወንበዴ፡ግን፡
ፈጣሪህ፡እግዚአብሔርን፡አትፈራውምን?
ለእኛስ፡በእውነት፡ይገባናል፤እንደ፡
ሥራችንም፡ፍርዳችንን፡ተቀብለናል።
፴፰ እርሱ፡ግን፡ይህ፡ከእኛ፡ጋር፡የተሰቀለው፡
በእውነት፡ከላይ፡የመጣ፡የእግዚአብሔር፡
ልጅ፡ኃጢአት፡ሳይኖርበት፡በአንደበቱም፡
ሐሰት፡ሳይገኝበት፡እርሱ፡ወዶ፡ነፍሳችንን፡
ሊያድን፡ነፍሱን፡ለሞት፡አሳልፎ፡ሰጠ።

፴፱ ይህን፡ነገርም፡ለባልንጀራው፡ተናግሮ፡
ሲፈጽም፡የቀኙ፡ወንበዴ፡ጌታ፡ኢየሱስን፡
አቤቱ፡በጌትነትህ፡በመጣህ፡ጊዜ፡አስበኝ፡
አለው።
፵ ጌታም፡ዛሬ፡በገነት፡ከእኔ፡ጋር፡እንድትኖር፡
በእውነት፡እነግርሃለሁ፡ብሎ፡መለሰለት።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

የዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ፡ተግሣጽ።

፩ ዐመፅ፡የፈለጉ፡ሕዝቦቻቸውን፡ደብዳቤ፡
በመጻፍና፡የሚመስሏቸውን፡የውስጥ፡
ሰዎችን፡በመላክ፡እንደሚያባብሉ።
፪ ነገሥታት፡ከክዳታቸው፡ከክፉ፡ሥራቸውና፡
ከተበላሸ፡ሐሳባቸው፡ፈጽመው፡ባይመለሱ፡
ስትመለከታቸው፡እንደ፡ነጋዴዎች፡ትጥቅ፡
ይመስላሉ፤ወይም፡የገበሬዎችን፡ወይም፡
ወደ፡ሀገራቸው፡መግባት፡እንደሚፈልጉ፡
ወገኖቻቸውንም፡ያባብሏቸው፡ዘንድ፡ወደ፡
ርስታቸው፡የሚመለሱትን፡ይመስላሉ።
፫ በጎውን፡ሥራ፡ያስተውሉ፡ዘንድ፡መልካ
ሙንም፡ፍላጎታቸውን፡የሚያቀርብላቸው፡
ቢኖር፡እንዳይጠፉ፡ወደ፡መታዘዝ፡መጥተው፡

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወከማሁ፡እንከ፡ሩካቤ፡ፍጥረትነ።

፬፡ ወመስተሣህል ፡ ለዘመድነ ፡ አስተርአየ ፡ ለዘመደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ቀዳሚ ፡ በአርአያ፡አምሳል፡ኃላፊ፡ለአጠይቆ፡ሕገ፡ ሥርዓት፡ኃላፊ።

፭፡ ወአስተርአዮ ፡ ለአዳም ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘየሐውር፡ውስተ፡ገነት፡ይስማዕ፡ድምፀ፡ ለኵናሁ፡ዲበ፡ምድር።

፮፡ ወአስተርአዮ ፡ ለአቡነ ፡ አብርሃም ፡ ከመ ፡ ብእሲ፡ዘየኀልፍ፡ፍኖተ።

፯፡ ወአስተርአዮ ፡ ለያዕቆብ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘይነብር፡ዲበ፡ሰዋስው፡ዘይበጽሕ፡እምድር፡ እስከ፡ሰማይ።

፰፡ ወአስተርአዮ፡ለሙሴ፡በነበ፡ዕፀ፡ጳጦስ፡ ወበውስተ፡ንስቲት፡ደመና።

፱፡ ወአስተርአዮ፡ለኢያሱ፡በአምሳለ፡መልአክ፡ ወለኢሳይያስ ፡ በአምሳለ ፡ ብእሲ ፡ ወዘአ ምሳሉ፡ዝ፡ብዙኅ።

፲፡ ወሶበ ፡ ተፈጸመ ፡ መዋዕለ ፡ ሕግ ፡ ርቱዕ ፡ ቀዳማይ፡ዘየኀልፍ፡ወቀርበ፡ሕግ፡ፍጹም፡ ዘበአማን፡ዘይነብር፡አስተርአየ፡በአምሳለ፡ ብእሲ ፡ ዘበአማን ፡ በፍጥረቱ ፡ በሥርዐተ ፡ ሕግ፡ዘበአማን፡ዘለዓለም፡ዘኢየኃልፍ።

፲፩፡ ወከመዝ፡ይቤ፡ልዑል፡አስተርአይኩ፡ላዕለ፡ እደ፡አግብርትየ፡ነቢያት፡በኵሉ፡አምሳል።

፲፪፡ ወጳውሎስኒ ፡ ሐዋርያ ፡ ይቤ ፡ በብዙኅ ፡ መክፈልት፡ወበብዙኅ፡አምሳል፡አይድዐ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአበዊነ ፡ በነቢያቲሁ ፡ እምቅድመ፡ዓለም።

፲፫፡ ወበደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ ተናገረ ፡ በወልዱ ፡ ዘረሰዮ፡ወራሴ፡ለኵሉ።

፲፬፡ ወይቤ፡ጠቢብ፡ትሩፍ፡በከመ፡ፈቀደ፡ከመ፡ ይኩን፡ሰብአ፡እስመ፡ይትረከብ፡በሱባዔ፡ በከመ ፡ ጠየቅነ ፡ እምኔሁ ፡ አፈድፍደ ፡ በምግባሩ፡ትሩፍ፡ጸመ፡በሥጋ፡ወሰገደ፡ በሥጋ፡ወበልዐ፡በሥጋ፡ወሰትየ፡በሥጋ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

የሚድኑ፡ቢሆኑ፡እንግዲህ፡እንዲሁ፡ይህን፡የመ ሰለ፡ሁሉ፡ከተፈጥሮአችን፡ጋራ፡የተገናኘ፡ነው።

፬፡ ለባሕርያችን ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ የሆነው ፡ ጌታ ፡ አስቀድሞ፡በአልፎ፡ሂያጅ፡አምሳል፡ፈራሽ፡ በስባሽ ፡ በሆነው ፡ ባሕርይ ፡ ተገለጸ ፡ የኃላ ፊውን፡ሥርዓት፡ሕግ፡ለማስረዳት።

፭፡ በምድር፡ላይ፡የተረከዙን፡ድምጽ፡ይሰማ፡ ዘንድ፡በገነት፡ውስጥ፡እንደሚሄድ፡ሰው፡ ለአዳም፡ተገለጸለት።

፮፡ በመንገድ ፡ እንደሚያልፍ ፡ ሰውም ፡ ለአባ ታችን፡አብርሃም፡ተገለጸለት።

፯፡ ከምድር ፡ እስከ ፡ ሰማይም ፡ በሚደርሰው ፡ መሰላል ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ ሆኖ ፡ ለያዕቆብ፡ታየው።

፰፡ በደደሆ፡ቁጥቋጦና፡በትንሽ፡ደመና፡ውስጥ፡ ለሙሴ፡ተገለጠለት።

፱፡ ለኢያሱም ፡ በመልአክ ፡ አምሳል ፡ ታየው ፡ ለኢሳይያስም ፡ በሰው ፡ አምሳል ፡ ታየው ፡ ይህን፡የመሰለውም፡ብዙ፡ነው።

፲፡ ቀድሞ፡የተሠራውና፡ኀላፊው፡የኦሪት፡ሕግ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ለዘላለም ፡ የሚኖረው ፡ ፍጹም ፡ የሆነው ፡ እውነተኛው ፡ ሕግ ፡ ሲቀርብ፡ የማታልፍ ፡ የወንጌልን ፡ ሕግና ፡ ሥርዓት፡እያስተማረ፡በፍጹም፡ሰው፡ሆኖ፡ በፍጥረቱ፡መካከል፡ተገለጸ።

፲፩፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ በባሮቼ ፡ በነቢያት ፡ ቃል ፡ በሁሉ ፡ አምሳል ፡ ተገለጽሁ።

፲፪፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከቀድሞ፡ጀምሮ፡በነቢያት፡አድሮ፡በብዙ፡ ክፍል ፡ በብዙ ፡ አምሳል ፡ ለአባቶቻችን ፡ ተናገረ።

፲፫፡ በኋላ፡ዘመን፡ግን፡ለሁሉ፡ገዥ፡ባደረገውና፡ ሁሉን፡በፈጠረበት፡በልጁ፡ነገረን፡አለ።

፲፬፡ የትሩፋት ፡ ባለቤት ፡ ጥበበኛ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ከእርሱም ፡ እንደ ፡ ተረዳን ፡ በሱባዔ ፡ ይገኝልና ፡ ትሩፋትን ፡ በሥራው ፡ አብዝቶ ፡ በሥጋ፡ጾመ፡በሥጋም፡ሰገደ፡በሥጋም፡በላ፡ ጠጣ፡አለ።

## በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፭ ወከመዝ ፡ ቢዘወነ ፡ እምሀጕል ፡ ወባልሐነ ፡
እሞት፡በስቅለቱ፡በሥጋ፡ወበሞቱ፡በሥጋ፡
ወበትንሣኤሁ፡በሥጋ።
፲፮ ወፈጸመ ፡ ሥርዐተ ፡ ዘኢይትረከብ ፡ በዕበዩ ፡
ልዑል ፡ በከመ ፡ ንጉሥ ፡ ዐቢየ ፡ ኀሊና ፡
ወልዑለ፡ሥልጣን፡ሶበ፡ተሞቅሐ፡እምነኪር፡
ተመሰለ፡በአምሳለ፡ሰብአ፡ይእቲ፡ሀገር።

፲፯ ወተጠበ፡ለአድኅኖ፡ገብሩ፡ወያረ፡በይእቲ፡
አርአያ ፡ ዘከነ ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ እምነ ፡
ሕማም፡ወኀሳር።
፲፰ ኢይከውኖ፡ዝንቱ፡ኀሳር፡ሕጸተ፡አላ፡ቡነበ፡
ማእምራን፡ይኄልቁዎ፡ክብረ፡ወይከውን፡
ሎቱ፡ተፍጻሜተ፡ኂሩት፡ወልዑለ፡ዝክር፡
ወይሰምይዎ፡በአስተንትኖቱ፡ወይዋሄሁ፡
ወርኅራኄሁ።

፲፱ ወያፈልሱ፡በእንቲአሁ፡ጸሐፍተ፡ወይለክኡ፡
ሎቱ፡ገድለ።
፳ ወከማሁ፡ሶበ፡ተማህለ፡እግዚእነ፡ላዕሌነ፡
ወተራኀርኀ፡ዲበ፡ድካምነ፡ተሰብአ፡ለመድ
ኃኒትነ፡ወጾረ፡ሕማመ፡በሥጋ፡ዘይደሉ፡ለነ፡
ወጼሐ፡ለነ፡ፍኖተ፡መድኃኒትነ፡እምፀርነ።

፳፩ ኢይከውኖ ፡ ዝንቱ ፡ ኀሳር ፡ ሕጸተ ፡ ዳእሙ ፡
ይከውኖ፡ፍጻሜ፡ፍቅር፡ወጥንቃቄ፡ኂሩት፡
ወለጥንቃቄ፡ክብር፡ወድኂን፡እምሲኦል።

፳፪ ወበከመ ፡ ውእቱ ፡ ንጉሥ ፡ ሶበ ፡ ፈቀደ ፡
አድኅኖ፡ገብሩ፡በኃይል፡እምፈነወ፡ጸባኢተ፡
ወሠራዊተ፡ወእምአህጕለ፡ፀሮ።
፳፫ ወከማሁ ፡ ሶበ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡
ስብሐት ፡ አድኅኖ ፡ ዘመድነ ፡ በኃይል ፡
እምፈነወ፡ትእልፊተ፡አእላፋት፡መላእክት፡
ወእምአጥፍኦሙ ፡ ለእልክቱ ፡ አፅራር ፡
ወእመ፡አኮ፡በአውዕዮ፡አው፡በአስጥሞ።
፳፬ አው ፡ በርግዘት ፡ አው ፡ በአናብስት ፡
መፍርህን፡አው፡በሕምዝ፡ዘይቀትል፡እምኢ
ከሀሎ፡ገቢረ፡ከመዝ።
፳፭ አኮ፡ውእቱ፡ዘወሀቦሙ፡ሥልጣነ፡ለአር
ዳኢሁ፡ቅዱሳን፡ከመ፡ያንሥኡ፡ሙታነ፡
ወይፈውሱ ፡ ዱያነ ፡ ወይማኡ ፡ ነገሥተ ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፲፭፤ እንደዚሁም ፡ በሥጋ ፡ በመሰቀሉ ፡ በሥጋ ፡
በመሞቱ ፡ በሥጋም ፡ በመነሣቱ ፡ ከጥፋት ፡
አዳነን፤ከሞትም፡ተቤዠን።
፲፮፤ በፍጹም ፡ ልዕልናውም ፡ የማይመረመር ፡
ሥርዓትን ፡ ፈጸመ ፤ ታላቅ ፡ አስተሳሰብና ፡
ከፍተኛ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ ንጉሥ ፡
በባዕድ፡እጅ፡በታሰረ፡ጊዜ፡በዚያች፡አገር፡
ሰዎች፡ተመሰለ፡
፲፯፤ ባርያውንም ፡ ለማዳን ፡ ተራቀቀ ፤ በባሪያው ፡
ላይ ፡ መሆን ፡ የሚገባውንም ፡ መከራና ፡
ጕስቁልና፡ተሸከመ።
፲፰፤ ይኸም ፡ ጕስቍልና ፡ ክብሩን ፡ አይቀንስ
በትም፤ በአዋቂዎች ፡ ዘንድ ፡ ክብር ፡
አድርገው፡ ይቈጥሩታል ፡ እንጂ ፤ ለእርሱም ፡
ፍጻሜ ፡ የሌላት ፡ ቸርነትና ፡ ታላቅ ፡
መታሰቢያ፡ ትሆንለታለች ፤ በትጋቱ ፡ በየዋህ
ነቱና፡በርኅራኄው፡ይጠሩታል።
፲፱፤ ስለ ፡ እርሱም ፡ ጽሑፎችን ፡ ለውጠው ፡
የእርሱን፡ገድል፡ይጽፋሉ።
፳፤ እንዲሁም፡ጌታችን፡ይቅር፡ባለን፡ጊዜ፡በድ
ካማችንም ፡ ራርቶ ፡ ሊያድነን ፡ ሰው ፡ ሆነ ፤
ለእኛ፡ የሚገባውንም ፡ መከራ ፡ በሥጋ ፡
ተቀበለ ፤ ከጠላታችንም ፡ እጅ ፡ የድኅነትን ፡
መንገድ፡ጠርጎ፡አወጣን።
፳፩፤ ይህም ፡ ኃሳር ፡ የክብር ፡ ጉድለት ፡ አይሆ
ነውም፤የፍቅር፡ፍጻሜ፡መሆኑንና፡ቸርነቱ፡
ክብሩ፡ከሲኦል፡ማዳን፡ፍጹም፡እንደ፡ሆነ፡
በጥንቃቄ፡የሚያስረዳ፡ነው።
፳፪፤ ያ ፡ ንጉሥ ፡ ባሪያውን ፡ በኃይል ፡ ማዳን ፡
ቢፈልግ፡የጦር፡ሠራዊት፡ልኮ፡ጠላቶቹን፡
ባጠፋ፡ነበር።
፳፫፤ እንዲሁም ፡ የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታችን ፡
የሰውን፡ ወገን ፡ በኃይል ፡ ማዳን ፡ ቢወድ ፡
አእላፍ፡መላእክትን፡ልኮ፡እነዚህን፡ጠላቶች፡
ባጠፋቸው ፡ ነበር ፤ ወይም ፡ እሳት ፡ አውርዶ ፡
በማቃጠል፡ወይም፡በባሕር፡በማስጠም።
፳፬፤ ወይም ፡ በጦርነት ፡ ወይም ፡ በሚያስፈሩ ፡
አንበሶች ፡ ወይም ፡ በሚገድል ፡ መርዝ ፡
እንደዚህ፡ማጥፋት፡ባልቻለም፡ነበርን?
፳፭፤ ጽኑአን ፡ ለሆኑ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሙት ፡
ያስነሡ ፡ ዘንድ ፡ ድውይ ፡ ይፈውሡ ፡ ዘንድ ፡
ኃያላን፡ጠቢባን፡ነገሥታትን፡ድል፡ይነሡ፡

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ኀያላነ፡ወጠቢባነ፡ወይሰሐቡ፡ዓለመ፡ኀበ፡
ትምህርቶሙ፡ቅዱስ፡ወማሕየዊ፡ለኵሉ፡
ሰብእ፡ዘበቱ፡ሃይማኖት።

፳፮፡ እምኢክህለኑ፡ይማእ፡ሊቃናተ፡አይሁድ፡
ወሠራዊተ፡ጲላጦስ፡ዳእሙ፡በከመ፡ውእቱ፡
አርአያ፡ዘተመሰለ፡ቦቱ፡ንጉሥ፡ለአድ
ኅኖተ፡ገብሩ፡ይከውን፡በኀበ፡ሰብእ፡ሀገረ፡
መንግሥቱ፡ትዕይርተ፡ወሠራዊቱ፡
ወመርዓቱ፡እለ፡የአምሩ፡ያሌዕሉ፡ፈቃዶ።

፳፯፡ ከማሁ፡አርአያ፡ዘአስተርአየ፡ቦቱ፡እግዚእነ፡
ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወአምሳል፡
ዘፈጸመ፡ባቲ፡ሥርዐተ፡መድኃኒትነ፡ይደሉ፡
ይኩን፡በኀቤነ፡ዐቢየ፡ወልዑለ፡ወክቡረ።

፳፰፡ ኢናዕርዕኬ፡ይእዜኒ፡አ፡አኀውየ፡መሀይ
ምናን፡እምዝክረ፡መስቀሉ፡ለእግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
እስመ፡ውእቱ፡ርእሰ፡ሠናያት፡ወጥንተ፡
ሕይወት፡ወመድኃኒት፡ወአክሊለ፡ምክሕ፡
ለኵሉ፡ዘሥጋ፡ወአርአያ፡ጥብዐት፡ወንዋየ፡
ሐቅል፡ዘመዊእ፡ወትእምርተ፡መድኃኒትነ፡
እምአሕጸሁ፡ለሰይጣን፡እኩይ፡አላ፡
ንዕትብ፡ቦቱ፡ዲበ፡ገጽነ፡ወንግበር፡
በአምሳሉ፡ዲበ፡ንዋይነ፡ወአዝርዕቲነ፡
ወንኅትም፡ቦቱ፡ዲበ፡አልባቢነ።

፳፱፡ ወንትዐቀብ፡ቦቱ፡እምፀርነ፡ወንቅረብ፡ቦቱ፡
ኀበ፡እግዚእነ፡ወአምላክነ፡ወመድኃኒነ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በልብ፡ንጹሕ፡ወበመ
ንፈስ፡ትሑት።

፴፡ ዘሎቱ፡ስብሐት፡ወአኰቴት፡ወዕዘዝ፡
ወዕበይ፡ወክብር፡ወትረ፡እስከ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

እመጽሐፈ፡ስንክሳር።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡
አሐዱ፡አምላክ፡አመ፡ዕሥራ፡ወሰብዑ፡
ለመጋቢት።

፩፡ በዛቲ፡ዕለት፡ተሰቅለ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ሎቱ፡ስብሐት፡በሥጋ፡በእንተ፡
መድኃኒተ፡ዓለም።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ዘንድ፡አዳኝ፡ወደ፡ሆነው፡ሃይማኖታቸው፡
ዓለሙን፡ሁሉ፡ይስቡ፡ዘንድ፡ሥልጣን፡
የሰጣቸው፡እርሱ፡አይደለምን።

፳፮፡ ታዲያ፡ይህን፡የሚያደርግ፡ጌታ፡የአይሁድን፡
አለቆችና፡የጲላጦስን፡ሠራዊት፡ድል፡
መንሳት፡አይችልምን? ነገር፡ግን፡ባሪያውን፡
ለማዳን፡ያደረገውን፡ንጉሥ፡አርአያ፡በመሆን፡
ነው፡እንጂ፤ በመንግሥቱ፡ግዛት፡ላሉት፡
ሰዎች፡ነቀፌታ፡ሲሆን፡ፈቃዱን፡የሚያውቁ፡
ሠራዊቱ፡መንጋዎቹ፡ከፍ፡ከፍ፡ያደርጉታል።

፳፯፡ እንደዚሁም፡ጌታችንና፡መድኃኒታችን፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡የተገለጸበት፡ድኅነታ
ችንን፡ከፈጸመባት፡አምሳል፡ጋር፡በእኛ፡
ዘንድ፡ፈጽሞ፡የከበረ፡ከፍ፡ያለ፡ይሆን፡
ዘንድ፡ይገባል።

፳፰፡ ወንድሞቼ፡ምእመናን፡ሆይ፡የጌታችንን፡
የፈጣሪያችንንና፡የመድኃኒታችንን፡የመከ
ራውን፡መታሰቢያ፡እንግዲህ፡አናቋርጥ፤
እርሱ፡የበጎ፡ነገር፡ሁሉ፡ራስ፡የሕይወት፡
ጥንት፡መሠረት፡ለሥጋውያን፡ለእኛ፡
መመኪያ፡ዘውድ፡ለብርታት፡አብነት፡
የድል፡ማድረጊያ፡የጦር፡መሣሪያ፡ከክፉ፡
ሰይጣን፡ጦር፡መዳኛችን፡ምልክት፡ነውና፤
በዚህም፡የመስቀል፡ምልክት፡በፊታችን፡
በዕቃችን፡በምሳሌው፡እንስራ፤ በአዝር
ዕትና፡ በአካላታቸው፡ሁሉ፡ላይ፡እናማት
ብበት፡እንጂ።

፳፱፡ ከጠላታችን፡እንጠበቅበት፡ዘንድ፡በቅን፡
ልቡና፡በትሑት፡ሰብእና፡ሁነን፡ወደ፡
ጌታችን፡ወደ፡ፈጣሪያችንና፡ወደ፡መድኃኒ
ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እንቅረብ።

፴፡ ለእርሱም፡ክብር፡ጌትነት፡ምስጋና፡
መንግሥት፡ገናናነት፡ዘወትር፡ለዘላለሙ፡
ይገባዋል፡አሜን።

ከመጽሐፈ፡ስንክሳር፡የተገኘ።

አንድ፡አምላክ፡በሆነ፡በአብ፡በወልድ፡
በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡መጋቢት፡ሃያ፡
ሰባት።

፩፡ በዚች፡ቀን፡የክብር፡ባለቤት፡ጌታችን፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ስለ፡ዓለም፡ድኅነት፡
በሥጋ፡ተሰቀለ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

መሰለመት፡ፀሐይ፡ሶበ፡ርእየት፡ፈጣሪሃ፡
ስቁለ፡በፈቃዱ፡ወእንጡልዐ፡ውስተ፡ሥጋ፡
ዘየስተርኢ።

ወኮነ፡መጠነ፡ጽልመታ፡እምጊዜ፡ስድስቱ፡
ሰዓት፡እስከ፡ተሰዓቱ፡ሰዓት።

ወበውእቱ፡ጊዜ፡አጽነነ፡ርእሶ፡**እግዚእነ፡**
በፈቃዱ፡ወመጠወ፡ነፍሶ፡ነባቢተ፡
ወለባዊተ፡ዘነሥአ፡**እምእግዝእትነ፡
ቅድስት፡ድንግል፡ማርያም።**

ወተፈልጠት፡ይእቲ፡ነፍስ፡እምሥጋሃ፡
ወሖረት፡ውስተ፡ሲኦል፡እንበለ፡ፍልጠት፡
**እመለኮት።**

በከመ፡ይቤ፡ሐዋርያ፡ቅዱስ፡ጴጥሮስ፡
እስመ፡ውእቱ፡ምውት፡በሥጋ፡ወውእቱ፡
ሕያው፡በመንፈስ።

ወበውእቱ፡ጊዜ፡ሀሎ፡ሥጋ፡ስቁለ፡ዲበ፡ዕፀ፡
መስቀል፡እንበለ፡ፍልጠት፡**እመለኮት።**

ወከማሁ፡ነፍሱኒ፡ወረደት፡ውስተ፡ሲኦል፡
ከመ፡ትፍትሖሙ፡ለሙቁሓን፤ወይእቲ፡
አሐደ፡ከዊና፡እንበለ፡ፍልጠት፡**እመለኮት።**

ዘኮነ፡ልዑለ፡መልዕልተ፡ሰማያት፡እንዘ፡
ይነብር፡ምስለ፡**አብ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡**
ሎቱ፡ስብሐት፡ወክብር፡ወክሂል፡ለዘቤ
ዘወነ፡በርእሱ፡ወአርኀወ፡ለነ፡ኆኅተ፡
መንግሥቱ፡በረከተ፡መስቀሉ፡የሀሉ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

**ሰላም፡ለሕማማቲከ፡**በተጸፍዖ፡መልታሕት፡
ከመ፡እቡስ፤በተቀሥፎ፡ዘባን፡ዓዲ፡
ወተከሎርዖ፡ርእስ፤እንዘ፡መላኪሆሙ፡አንተ፡
**እግዚአብሔር፡**ንጉሥ።ኢያፍርሁኒ፡ቀታል
ፀሪሃ፡ለነፍስ፤እስመ፡ማኅተምየ፡ደምከ፡
ቅዱስ።

**ሰላም፡ለስቅለትከ፡**በመልዕልተ፡ቅዱስ፡ጸልቦ፤
ለቅንዋቲከ፡ካዕበ፡ወለርግዘትከ፡ገቦ፤**ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡**መቅለሌ፡ነገር፡ለዘዐጸቦ፤ከመ፡
አዕሊ፡በአርአየቱ፡ገነተ፡ኅሩያን፡ኀበ፡ቦ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፪፡ ፀሐይ፡ፈጣሪዋን፡በሚታይ፡ሥጋ፡በፈቃዱ፡
ተሰቅሎና፡ተዘርግቶ፡ባየች፡ጊዜ፡ጨለመች።

፲፫፡ የጨለመችበትም፡ጊዜ፡ከስድስት፡ሰዓት፡
እስከ፡ዘጠኝ፡ሰዓት፡ያህል፡ነበር።

፲፬፡ በዚያም፡ጊዜ፡**ከእመቤታችን፡ከንጽሕት፡
ድንግል፡ማርያም፡**የነሣትን፡የምታውቅና፡
የምትናገር፡ነፍሱን፡ራሱን፡ዘንበል፡አድርጎ፡
በፈቃዱ፡ከሥጋው፡ለያት።

፲፭፡ ያቺም፡ነፍስ፡ከሥጋዋ፡ተለይታ፡ከመለኮት፡
ግን፡ባለመለየት፡ወደ፡ሲኦል፡ሔደች።

፲፮፡ ሐዋርያው፡ቅዱስ፡ጴጥሮስ፡እርሱ፡በሥጋ፡
ምውት፡ሲሆን፤**በመለኮት፡**ሕያው፡ነው፡
እንዳለ።

፲፯፡ በዚያን፡ጊዜም፡**ከመለኮት፡**ባለመለየት፡
ሥጋ፡በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡ተሰቅሎ፡
ነበር።

፲፰፡ እንዲሁም፡ነፍሱ፡እስረኞች፡ነፍሳትን፡
ትፈታቸው፡ዘንድ፡እርሷ፡**ከመለኮት፡**
ሳትለይ፡አንድ፡ሆና፡ወደ፡ሲኦል፡ወረደች።

፲፱፡ ከሰማያት፡በላይ፡ሲኖር፡**ከአብ፡ከመንፈስ፡
ቅዱስ፡**ጋር፡ልዑል፡ባሕርይ፡የሆነ፡ነው፤
በራሱ፡መሥዋዕትነት፡ለተቤዠን፡የመንግ
ሥቱን፡በር፡ለከፈተልን፡ለእርሱ፡ጌትነት፡
ክብር፡ምስጋና፡ይሁን፤የመስቀሉም፡
በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑር፡
አሜን።

አንተ፡ንጉሥ፡**እግዚአብሔር፡**ገዢአቸው፡
ስትሆን፤እንደ፡በደለኛ፡ፊትህን፡በመጸፋት፡
ደግሞ፡ጀርባህን፡በመገረፍና፡ራስህን፡
በመመታት፡ለተቀበልካቸው፡መከራዎችህ፡
**ሰላምታ፡ይገባል፤**ማኅተሜ፡የከበረ፡ደምህ፡
ነውና፤ነፍስን፡የሚያጠፉ፡አያስፈሩኝ።

የከበደ፡ነገርን፡የምታቀል፡**ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ሆይ፡**በቅዱስ፡መስቀል፡ላይ፡ለመ
ሰቀልህ፡ለመቸንከርህና፡ደግሞ፡ጐንህን፡
ለመወጋትህ፡**ሰላም፡ፍቅር፡ይገባል፤**
የተመረጡ፡ጻድቃን፡ወዳሉበት፡ገነት፡
እርሱን፡በማሳየት፡እገባ፡ዘንድ፤

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ለመዝራዕትከ፡ሀበኒ፡ማዕተቦ።

ለመዝራዕትከ፡ሀበኒ፡ማዕተቦ። ሰላም፡ለጸአተ፡ነፍስከ፡እምነ፡ሥጋ፡ፍሉጠ፤ ወለግንዘትከ ፡ በዕፍረት ፡ ዘእደ ፡ ዮሴፍ ፡ ወለግንዘትከ ፡ በዕፍረት ፡ ዘእደ ፡ ዮሴፍ ፡ እግዚእ ፡ ዘቈላተ ፡ እፅዐጠ፤ አመ ፡ ወረድከ ፡ እግዚእ ፡ ዘቈላተ ፡ ደይን ፡ ውስጠ፤ ኀይለ ፡ ስብሐቲከ ፡ ጽንዐ ፡ መንሠገ፡ቀጥቀጠ፤ወገሀነም፡ቄአ፡ነፍሳተ፡ ዘውኀጠ።

## ላሓ፡ማርያም።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ ድርሳን ፡ ዘደረሰ ፡ አባ ፡ ሕርያቆስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘሀገረ ፡ ብህንሳ ፡ በእንተ፡ሐዘና፡ወላሓ፡ለድንግል።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

፩፤ ወለድንግልሰ፡ኮነ፡ዐቢይ፡ብካይ፡የዐውዳ፡ በእንተ፡ዘኢርእየቶ፡ለወልዳ።

፪፤ ወተመይጠት፡ኀበ፡ብካያ፡ወላሓ፡ዳግመ፡ ምዕረ፡በቤተ፡ዮሐንስ፡ወትቤ፡አምሀለከ፡ኦ፡ ዮሐንስ፡ከመ፡ትምርሐኒ፡ኀበ፡ቀራንዮ።

፫፤ አምሀለከ ፡ ኦ ፡ ዮሐንስ ፡ ከመ ፡ ትምጻእ ፡ ምስሌየ ፡ ኀበ ፡ ጎልጎታ፤ ኢርኢኩ ፡ ሰራቂ ፡ እንዘ ፡ ይሰቅልዎ ፡ ወኢፈያታዊ ፡ እንዘ ፡ ይመትሩ፡ርእሶ።

፬፤ አኀድግ ፡ ሀገርየ ፡ ወአኀድግ ፡ ግርማየ ፡ ወአሐውር፡በእገርየ፡ከመ፡እርአይ፡መካነ፡ ዘሰቀልዎ፡ውስቴቱ፡ለወልድየ፡ፍቁር፡ከመ፡ ፈያት።

፭፤ ኦ፡ወልድየ፡አልቦ፡ወኢአሐዱ፡እምአኃዊከ፡ ዘቀውም፡ምስሌከ፡አው፡ዘይትናገር፡በእን ቲአከ፡አሐተ፡ቃለ።

፮፤ ኦ፡ወልድየ፡ፍቁርየ፡ሐዘነ፡እም፡ላዕለ፡ ወልዳ፡ፍቁር፡ካልእ፡ወሐዘነ፡ዐርክ፡ላዕለ፡ ዐርኩ፡ካልእ፡ወበሕማመ፡ልብ፡እምዘ ትበኪ፡ላዕለ፡ወልዳ፡ፍቁራ፡ካልእ፡ወካልእ፡ ብካየ፡ይበኪ፡ዐርክ፡ላዕለ፡ዐርኩ።

፯፤ ሐዘንየ ፡ የዐቢ ፡ እምሐዘነ ፡ ኵሎሙ ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

የሥልጣንህን፡ምልክት፡ስጠኝ።

ከሥጋ፡የተለየች፡ሁና፡ለነፍስህ፡መውጣት፤ የዮሴፍ ፡ እጅ ፡ በሽቱ ፡ ላጣፈጠውም ፡ ለመግነዝህ፡ሰላምታ፡ይገባል፤አቤቱ፡የደይን፡ቆላ፡ ወደ፡ሆነ፡ሲኦል፡በወረድክ፡ጊዜ፡የጌትነትህ፡ ኃይል ፡ የመቆለፊያውን ፡ ጽናት ፡ ቀጠቀጠ፤ ገሃነምም፡የዋጣቸውን፡ነፍሳትን፡ተፋ።

## የማርያም፡ሐዘን።

አንድ ፡ አምላክ ፡ በሆነ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡አምነን፡የብህንሳ፡ኤጲ ስቆጶስ፡አባ፡ሕርያቆስ፡ስለ፡ድንግል፡ሐዘኗና፡ ልቅሶዋ፡የደረሰው፡ድርሳን፡ይህ፡ነው።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

፩፤ ድንግልንም ፡ ልጅዋን ፡ ስለአላየችው ፡ ፍጹም፡ሐዘንና፡ልቅሶ፡አገኛት።

፪፤ በዮሐንስ ፡ ቤትም ፡ ሳለች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ልቅሶዋ ፡ ተመልሳ ፡ ዮሐንስ ፡ ሆይ ፡ ወደ ፡ ቀራንዮ ፡ ትመራኝ ፡ ዘንድ፡ አማጽንሃለሁ ፡ አለች።

፫፤ ዮሐንስ ፡ ሆይ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ጎልጎታ ፡ ትሄድ ፡ ዘንድ ፡ አማጽንሃለሁ ፤ ሌባን ፡ ሲሰቅሉት ፡ ወንበዴን ፡ ቾብቾበውን ፡ ሲቆርጡ፡አላየሁም።

፬፤ እንደ፡ወንበዴ፡ልጄን፡ወዳጄን፡በውስጡ፡ የሰቀሉበትን ፡ ቦታ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ሀገሬን ፡ ክብሬን፡ትቼ፡በእግሬ፡እሄዳለሁ።

፭፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ከወንድሞችህ ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ አብሮህ፡የቆመ፡የለም፤ወይም፡ስለ፡አንተ፡ አንዲት፡ቃል፡የሚናገር፡የለም።

፮፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ በልጅዋ ፡ ላይ ፡ የእናት ፡ ሐዘን ፡ ሌላ፡ ነው ፤ ወዳጅም ፡ ስለ ፡ ወዳጁ ፡ የሚያ ዝነው፡ ሌላ ፡ ነው ፤ እናትም ፡ በተወዳጅ ፡ ልጅዋ፡ ላይ ፡ ከልብ ፡ የምታዝነው ፡ ሐዘን ፡ ልዩ፡ ነው ፤ ወዳጅም ፡ ለወዳጁ ፡ ልዩ ፡ ሐዘን ፡ አዝኖ፡ያለቅሳል።

፯፤ ሐዘኔም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ካሉ ፡ ሰዎች ፡ሁሉ ፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

[ወ]በእ፡ኢየሩሳሌም።
[ጸ]፡ወልድየ፡ብካይየ፡የዐቢ፡እምብካየ፡
[ኵ]ሎሙ፡እለ፡ተጋብኡ፡ኀቤየ፡ኦ፡ወልድየ፡
[ፍ]ቁርየ።
ወሶበ፡ርእየ፡ዮሐንስ፡ከመ፡ኢትክል፡
[አ]ርምሞ፡እምብካይ፡ወላሕ፡ወኢይክል፡
ወእቱ፡ከመ፡ይናዝዛ፡ወይእቲ፡ኮነት፡
[ት]ብል፡ለእመ፡ኢርኢክዎ፡ኢይክል፡
ተናዝዞ።
ወይቤላ፡ዮሐንስ፡ተንሥኢ፡ወአነ፡አሐውር፡
ምስሌኪ፡ኀበ፡ቀራንዮ፡ትርአዪዮ።

ወድንግልሰ፡ወፅአት፡እምቤተ፡ዮሐንስ፡
ወሖረት፡በእገሪሃ፡ውስተ፡መርሕበ፡ሀገረ፡
ኢየሩሳሌም።
ወሰብእ፡እለ፡ኮኑ፡ይሬእይዋ፡ለድንግል፡
እንዘ፡ታፈጥን፡ሐዊረ፡ይብሉ፡በበይና
ቲሆሙ፡መኑ፡ይእቲ፡ዛቲ፡እንተ፡ትጸርሕ፡
ከመዝ።
ወካልአን፡ይብሉ፡እምኀበ፡ምሥያጣት፡
ኢርኢናሃ፡ግሙራ፡ለዛቲ፡እንዘ፡ትሣየጥ፡
መፍቅዳ።
ወካልአን፡ይብሉ፡በበይናቲሆሙ፡ዛቲ፡
እንግዳ፡እስመ፡ተሐውር፡ውስተ፡
መራሕብት፡ዘእንበለ፡አእምሮ።
ወካልአን፡እለ፡ኮኑ፡የአምርዎ፡ለዮሐንስ፡
ከመ፡ውእቱ፡ረድኡ፡ለኢየሱስ፡ይብሉ፡
እንጋ፡ዛቲ፡እሙ፡ትረውጽ፡ከመ፡ትርአዮ፡
በዲበ፡መስቀል።
ወካልአን፡ይብሉ፡ዛቲ፡ብእሲቱ፡ለዮሴፍ፤
ወካልአን፡ይብሉ፡ዜነውዋ፡ዜና፡በእንተ፡
ወልዳ፤ወካልአን፡ይብሉ፡ርእዩ፡እፎ፡ይሜኒ፡
አርአያሃ፡ወላሕያ።
ወካልአን፡ኢርኢነ፡ግሙራ፡ዘከመ፡ዛቲ፡
በውስተ፡ዛቲ፡ሀገር፡ወገጻ፡ይመስል፡ከመ፡
ገጸ፡ወልዳ።
ወኮኑ፡ሰብእ፡ምሥያጥ፡ይትናገሩ፡በእን
ቲአሃ፡ወተሰምዐ፡በውስተ፡ኵሉ፡
መራሕብተ፡ሀገር።
ወሶበ፡ሰሎሜ፡ትተልዋ፡ድኅሬሃ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ሐዘን፡ይጸናል።
ልጄ፡ወዳጄ፡ሆይ፡ልቅሶዬ፡በእኔ፡ዘንድ፡ከተ
ሰበሰቡት፡ሰዎች፡ሁሉ፡ልቅሶ፡ይበልጣል።

፰፤ ዮሐንስም፡ከልቅሶና፡ከሐዘን፡መጽናናትን፡
እንደማትችል፡እርሱም፡ሊያረጋጋት፡እንደ
ማይችል፡ባየ፡ጊዜ፤እርሷም፡ካላየሁት፡
መጽናናት፡አልችልም፡ያለች፡ስለ፡ሆነች።

፱፤ ዮሐንስም፡እኔ፡ካንቺ፡ጋራ፡ወደ፡ቀራንዮ፡
እሄዳለሁ፤ታዪው፡ዘንድ፡ተነሺ፡እንሂድ፡
አላት።

፲፤ ድንግልም፡ከዮሐንስ፡ቤት፡ወጥታ፡በኢየሩ
ሳሌም፡ሜዳዎች፡ውስጥ፡በእግርዋ፡ተጓዘች።

፲፩፤ ድንግልንም፡ፈጥና፡ስትራመድ፡የሚያ
ዩዋት፡ሰዎች፡እንዲህ፡የምታለቅስ፡ይህች፡
ማን፡ናት፡እያሉ፡እርስ፡በርሳቸው፡ይነጋገሩ፡
ነበር።

፲፪፤ ሌሎችም፡ከገበያ፡የምትሻውን፡ስትገዛ፡ከቶ፡
ይህቺን፡አላየናትም፡ይሉ፡ነበር።

፲፫፤ ሌሎችም፡እርስ፡በርሳቸው፡ይቺ፡እንግዳ፡
ናት፤በሀገር፡ውስጥ፡ያለ፡ማስተዋል፡ትሄዳ
ለችና፡ይሉ፡ነበር።

፲፬፤ የጌታ፡ኢየሱስ፡ደቀ፡መዝሙር፡እንደ፡ሆነ፡
ዮሐንስን፡የሚያውቁት፡እንጃ፤ይቺ፡እናቱ፡
ትሆናለች፡በመስቀል፡ላይ፡ተሰቅሎ፡ታየው፡
ዘንድ፡ትሮጣለች፡ይሉ፡ነበር።

፲፭፤ ሌሎችም፡ይቺ፡የዮሴፍ፡ሚስት፡ትሆናለች፤
ስለ፡ልጅዋም፡ወሬ፡ነግረዋት፡ይሆናል፡
ይሉ፡ነበር፤ሌሎችም፡መልኳ፡ደም፡ግባቷ፡
እንዴት፡ያምራል፡እዩ፡ይሉ፡ነበር።

፲፮፤ ሌሎችም፡በዚች፡አገር፡ከቶ፡እንደዚች፡
ያለች፡አላየንም፤መልኳም፡የልጅዋን፡
መልክ፡ይመስላል፡ይሉ፡ነበር።

፲፯፤ በገበያ፡ውስጥ፡ያሉ፡ሰዎች፡ስለ፡እርሷ፡
ይነጋገሩ፡ነበር፤ነገሩም፡በገበያ፡ሁሉ፡
ተሰማ።

፲፰፤ ሰሎሜም፡በኋላዋ፡ትከተላት፡ነበር፤

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወካልእት፡አንስት፡እንዘ፡ይገለብባ፡ርእሶን፡
በልብስ፡እስመ፡ኢትትመየጥ፡ይእቲ፡ኀበ፡
ምንትኒ፡ዘእንበለ፡ሕማመ፡ልብ።

፲፱፡ ወሶበ ፡ በጽሐት ፡ ኀበ ፡ ጎልጎታ ፡ ርእየት ፡
ጽፉቀ፡ ሰብአ ፡ ወእለ ፡ ተጋብኡ ፡ ሕዝበ ፡
ወአሕዛበ፡ወሠራዊተ፡ለዘተሰቅለ፡ዲበ፡ዕፀ፡
መስቀል፡ከመ፡ይርአይዎ።

፳፡ ወኮኑ ፡ ብዙኃን ፡ እምኵሉ ፡ በሐውርት ፡
ወአህጉር፡እለ፡ተጋብኡ፡ኀበ፡ኢየሩሳሌም፡
በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ወርኅ ፡ ቅዱስ ፡ በእንተ ፡
ፍሥሐ፡በግዑ፤ወኵሎሙ፡እመአምሐረይን፡
ወባርቅ ፡ ወሞአብ ፡ ወኮበር ፡ ወደቂቀ ፡
ይስማኤል።

፳፩፡ ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ እንዘ ፡ ይጸዐቁ ፡ በበይና
ቲሆሙ፡በእንተ፡ራእይ፡ዐቢይ፡ወመንክር፤
ነዋ፡ፈጸሙ፡እከዮሙ፡ዮም፡ላዕለ፡ዝንቱ፡
ብእሲ፡በዐመፃ።

፳፪፡ ወካልአን፡ይብሉ፡ነዋ፡ብዙኅተ፡ዓመታተ፡
ዘነበሩ፡እንዘ፡የኀሥሡ፡ሞቶ፡ለዝንቱ፡
ብእሲ።

፳፫፡ ወካልአን፡ይብሉ፡ነዋ፡ቀተሉ፡ዮም፡ኀያለ፡
ወጽኑዐ።

፳፬፡ ወካልአን ፡ ይብሉ ፡ ለእመ ፡ ቦ ፡ ፍትሕ ፡
በውስተ፡ዛቲ፡ሀገር፡እምኢኮኑ፡ይቅትሉ፡
ዘንተ።

፳፭፡ ወካዕበ ፡ ዓዲ ፡ ይብሉ ፡ ካልአን ፡ ዝንቱ ፡
ዘለአከ፡ንጉሥ፡በእንቲአሁ፡ከመ፡ይረስዮ፡
ንጉሠ፡ላዕለ፡ኵሎሙ፡አይሁድ።

፳፮፡ ወበእንተ፡ዝንቱ፡አዘዘ፡ሄሮድስ፡ንጉሥ፡
ከመ፡ይቅትልዎ።

፳፯፡ ወካልአን፡ረገምዎ፡ለሄሮድስ፡በእንቲአሁ፡
እንዘ፡ይብሉ፡ገ፡ውእቱ፡ዘነሥአ፡ብእሲተ፡
እኁሁ፡ እምቅድመ፡ ይሙት፡ ወረሰዮ፡
ምስኪነ፡ወሐርቲመ፤ወነዋ፡ካዕበ፡ቀተሎ፡
ለዝንቱ፡ዘእንበለ፡ምሕረት።

፳፰፡ ወድንግልሰ፡ በእንተ፡ብካያ፡ወትሕትናሃ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ሌሎችም ፡ ሴቶች ፡ ራሳቸውን ፡ ተከናንበው፡
ይከተሉዋት ፡ ነበር ፤ በልብ ፡ ከማዘን ፡ በቀር፡
ምንም፡ወደ፡ቀኝም፡ሆነ፡ወደ፡ግራ፡መለ
ቀለስ፡አትልም፡ነበርና።

፲፱፡ ወደ ፡ ጎልጎታም ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ ሰው፡
ተጨናንቆ ፡ ተሰብስቦ ፡ አየች ፤ በዕንጨት፡
መስቀል፡ላይ፡የተሰቀለውን፡ያዩት፡ዘንድ፡
የተሰበሰቡትን፡ብዙ፡ሕዝብና፡አሕዛብ፡ሠራ
ዊትንና፡የተጨናነቀውን፡ሰው፡አየች።

፳፡ በዚህ ፡ ልዩ ፡ በሆነው ፡ ወር ፡ ስለ ፡ በግዑ፡
ፋሲካው ፡ ከአረማይስጥ ፡ ከባርቅ ፡ ከሞአብ፡
ከኮበር ፡ ከእስማኤል ፡ ልጆች ፡ አገር ፡ ሁሉና፡
ከአውራጃው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የተሰ
በሰቡ ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ።

፳፩፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ አዩት ፡ አስደናቂ ፡ የሆነ፡
ታላቅ ፡ ተአምር ፡ ተጨናንቀው ፡ እርስ፡
በርሳቸው፡እነሆ፡በዚህ፡ሰው፡ላይ፡ክፋ፡ሥ
ራቸውን፡በግፍ፡ፈጸሙ፡ይሉ፡ነበር።

፳፪፡ ሌሎችም ፡ እነሆ ፡ ብዙ ፡ ዘመናት ፡ የዚህ፡
ሰው ፡ ሞት ፡ ሲፈልጉ ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ፡ ይሉ፡
ነበር።

፳፫፡ ሌሎችም፡እነሆ፡ዛሬ፡ኃያልና፡ጽኑዕ፡ብርቱ፡
ሰው፡ገደሉ፡ይሉ፡ነበር።

፳፬፡ ሌሎችም ፡ በዚች ፡ አገር ፡ ዕውነተኛ ፡ ፍርድ፡
ቢኖር፡ይህን፡ባልገደሉ፡ነበር፡ይላሉ።

፳፭፡ ዳግመኛም ፡ እንደገና ፡ ሌሎች ፡ በአይሁድ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ ያነግሠው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እርሱ፡
ንጉሥ ፡ መልእክት ፡ የጻፈለት ፡ ይህ ፡ አይደ
ለምን፡ይሉ፡ነበር።

፳፮፡ ስለዚህም ፡ ንጉሥ ፡ ሄሮድስ ፡ ይገድሉት፡
ዘንድ፡አዘዘ፡አሉ።

፳፯፡ ሌሎችም ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ሳይሞት ፡ የወን
ድሙን፡ ሚስት ፡ ነጥቆ ፡ ጎስቋላ ፡ ያደረገው፡
ይህ ፡ ነው ፤ እያሉ ፡ ሄሮድስን ፡ ረገሙት፡
ዳግመኛም ፡ እነሆ ፡ ያለ ፡ ፍርድ ፡ ይህን፡
ገደለው፡አሉ።

፳፰፡ ድንግልም ፡ ስለ ፡ ጽኑ ፡ መከራዋ ፡ ስለ፡

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ከነ፡ገጸ፡ድኑነ፡ዲበ፡ምድር፡በእንተ፡ብዙኅ፡
ብካይ፡ወዐቢይ፡ጻዕቅ፡ወጉባኤ፡አይሁድ፡
ኢትክል፡ትርአዮ፡ለወልዳ፡ፍቁር።

፳፱ ወትቤሎ፡ለዮሐንስ፡አይቴ፡ሀሎ፡ወልድየ፡
ፍቁር፡ከመ፡እርአዮ፡እስመ፡ጻዕቅ፡ውእቱ፡
ዝንቱ፡ጉባኤ፡ዐቢይ፡ከልአኒ፡ከመ፡
ኢይርአዮ።

፴ ወይቤላ፡ዮሐንስ፡አልዕሊ፡አዕይንተኪ፡
እመንገለ፡ጉባኤ፡ምዕራብ፡እስከ፡መንገለ፡
ምሥራቅ፡ከመ፡ትርአዪዮ፡በዲበ፡መስቀል።

፴፩ ወአልዐለት፡አዕይንቲሃ፡ወርእየቶ፡ወኢኀ
ደገት፡ሐዊረ፡በታሕተ፡ጉባኤ፡ምስለ፡
ዮሐንስ፡እስከ፡በጽሐት፡ወቆመት፡በየማኑ።

፴፪ ወኮነት፡ትሬእዮ፡እንዘ፡ውእቱ፡ውስተ፡
ሕማም።

፴፫ ወሶበ፡ርእየ፡አምላክነ፡ኄር፡ኀበ፡ትሕትና፡
እሙ፡አድነነ፡አዕይንቲሁ፡ኀበ፡ዮሐንስ፡
ወይቤሎ፡አ፡ብእሲ፡ዛቲ፡እምከ፡ወይቤላ፡
ለእሙ፡አ፡ብእሲቶ፡ዝንቱ፡ወልድኪ።

፴፬ ወዮሐንስሰ፡አኅዛ፡ለድንግል፡ከመ፡ይሰዳ፡
ውስተ፡ቤቱ፤ወተናገረት፡ምስሌሁ፡
ወትቤሎ፡ድንግል፡ኅድገኒ፡አ፡ዮሐንስ፡
ከመ፡እብኪ፡ላዕለ፡ወልድየ፡እስመ፡ውእቱ፡
ዘእንበለ፡እኁው፡ወእኅት፡ኢትፍልጠኒ፡
እምኔሁ፡ፍጡነ።

፴፭ አ፡ዮሐንስ፡ውእቱሰ፡አልቦቱ፡አብ፡በዲበ፡
ምድር፤እምተመነይኩ፡አ፡ወልድየ፡ዝንቱ፡
አክሊል፡ዘዲበ፡ርእስከ፡ከመ፡ይኩን፡ዲበ፡
ርእስየ፡ከማከ፡ወእኩን፡እትዐገሥ፡ላዕለ፡
ሕማሙ፡ከማከ።

፴፮ ለእመ፡ኮነ፡ፍትሕ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ፈያት፡
ለቅሳት፡ለምንት፡ኢሰቀሉከ፡አ፡ይሁዳ፡
እስመ፡አንተ፡ሰራቂ።

፴፯ ወለእመ፡ኮነ፡ይደልዎሙ፡ለፈያት፡ከመ፡ያዕ
ርቅዎሙ፡እምቅድመ፡ሞቶሙ፡ለምንት፡አ፡
ይሁዳ፡ዘኢያዕረቁከ፡እስመ፡ሰራቂ፡
ወትሰርቅ፡ዘኮነ፡ውስተ፡አስከሬን።

፴፰ ነጽር፡ኀሳርየ፡ዮም፡አ፡ዮሐንስ፡ውስተ፡
ዝንቱ፡ጉባኤ፤ነጽር፡ኀበ፡ትሕትናየ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ልቅሶዋ፡ስለ፡ብዙ፡ዕንባዋም፡አንገቷን፡ወደ፡
ምድር፡ደፍታ፡ነበር፤ከተሰበሰቡት፡የአይሁድ፡
ብዛት፡የተነሣ፡ታላቅ፡መጨናነቅ፡ነበርና፡የም
ትወደው፡ልጅዋን፡ማየት፡አልቻለችም።

፳፱፤ ዮሐንስንም፡አየው፡ዘንድ፡ልጄ፡ወዳጄ፡
ወደየት፡ነው፤የተጨናነቀው፡ታላቅ፡ጉባዔ፡
እንዳላየው፡ከልክሎኛልና፡አለችው።

፴፤ ዮሐንስም፡በመስቀል፡ላይ፡ታዪው፡ዘንድ፡
ከምዕራብ፡እስከ፡ምሥራቅ፡ባለው፡ጉባኤ፡
ላይ፡ዐይኖችሽን፡ቀና፡አድርጊ፡አላት።

፴፩፤ ዐይኖቿንም፡ቀና፡አድርጋ፡አየችው፤
ደርሳም፡በቀኙ፡እስከቆመች፡ድረስ፡
በጉባኤው፡ውስጥ፡መሄድን፡አላቋረጠችም።

፴፪፤ እሱንም፡በመስቀል፡ላይ፡ሁኖ፡ታየው፡
ነበር።

፴፫፤ ቸሩ፡ፈጣሪያችን፡የእናቱን፡ትሕትና፡አይቶ፡
ዐይኖቹን፡ወደ፡ዮሐንስ፡አተኵሮ፡አንተ፡
ሰው፡ይቺ፡እናትህ፡ናት፡አለው፤እናቱንም፡
አንቺ፡ሆይ፡ይህ፡ልጅሽ፡ነው፡አላት።

፴፬፤ ዮሐንስም፡ወደ፡ቤቱ፡ይወስዳት፡ዘንድ፡
እጅዋን፡ደግፎ፡ያዛት፤ድንግልም፡ዮሐንስ፡
ሆይ፡በልጄ፡ላይ፡አለቅስ፡ዘንድ፡ተወኝ፡
አለችው፤እርሱ፡ያለ፡እኅት፡ያለ፡ወንድም፡
ብቸኛ፡ነውና፤ከእርሱ፡ፈጥነህ፡አትለየኝ፡
ብላ፡ተናገረች።

፴፭፤ ዮሐንስ፡ሆይ፡እርሱስ፡ምድራዊ፡አባት፡
የለውም፤ልጄ፡ሆይ፡ይህ፡በራስህ፡ላይ፡
ያለው፡የእሾህ፡ዘውድ፡መከራውን፡
እንዳንተ፡እታገሠው፡ዘንድ፡በራሴ፡ላይ፡
ሊሆን፡በወደድኩ፡ነበር።

፴፮፤ በወንበዴ፡ሁሉ፡ላይ፡የስቅላት፡ፍርድ፡
የሚገባ፡ከሆነ፡ይሁዳ፡ሆይ፡ለምን፡አልሰቀ
ሉህም፡አንተ፡ሌባ፡ነበርክና።

፴፯፤ ከመሞታቸው፡በፊት፡ሽፍቶችን፡የሚያራቁ
ቷቸው፡ከሆነ፡ይሁዳ፡ሆይ፡ለምን፡አላራቁ
ቱህም፡በሙዳየ፡ምፅዋት፡የገባውን፡የምት
ሰርቅ፡ሌባ፡ነበርክና።

፴፰፤ ዮሐንስ፡ሆይ፡ዛሬ፡በዚህ፡ጉባኤ፡መካከል፡
ጕስቍልናዬን፡ተመልከት፤በመከራው፡

Scanned by CamScanner

በ፲፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወሕማመ ፡ ልብየ ፡ ጎድገኒ ፡ ከመ ፡ እጽገብ ፡
እምገጹ፡አ፡ዮሐንስ፡በዝንቱ፡ደብር፡እስመ፡
ኢይሬእዮ ፡ ግሙራ ፡ ዘእንበለ ፡ ዛቲ ፡ ዕለት ፡
ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ደብር ፡ ማኅደር ፡ ለዕጓለ ፡
ማውታ።

፴፱፤ ጎድገኒ ፡ እብኪ ፡ ላዕሌሁ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡
ምስካቡ ፡ ለኢዮብ ፡ በሕማሙ ፡ እስመ ፡
ሕማምየ ፡ የዐቢ ፡ እምሕማሙ ፡ ምስካበ ፡
ኰሎሙ፡ምስኪናን፡ዛቲ፡መሬት።

፵፤ ጎድገኒ ፡ እጽገብ ፡ እምኔሃ ፡ እስመ ፡ አነ ፡
ድክምት ፡ ወአልብየ ፡ አብ ፡ ወእም ፡
ወኢሰብእ፤ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ላሕ ፡ የዐውዳ ፡
ለድንግል፡እንዘ፡ትቀውም፡በየማኑ፡ወልዳ፡
ወኮነት፡ትኄሊ፡በልባ፡ወበሕማመ፡ኀሊናሃ፡
ወኢትትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ዐቢይ ፡ ጉባኤ ፡
ዘእንበለ፡ብካይ፡ባሕቲቱ።

፵፩፤ ወኮና ፡ እለ ፡ ይቀውማ ፡ አንስት ፡ ዮሐና ፡
ብእሲተ ፡ ኩዛ ፡ ወማርያም ፡ መግደላዊት ፡
ወሰሎሜ ፡ ወውእቶንሰ ፡ የሐቅፋሃ ፡
ለድንግል፡እግዝእትነ፡ወያነሥእሃ።

፵፪፤ ወኮነ ፡ ላሐ ፡ ጥዑመ ፡ እማእከለ ፡ ኵሎን ፡
አንስት፡ንጹሐት፤ወኮና፡ይበክያ፡በእንተ፡
ጣዕመ፡ነገራ።

፵፫፤ ወካልአትሰ፡እምአንስተ፡አይሁድ፡እለ፡ኮና፡
ይሰምዓ፡ብካያ፡እንዘ፡ትበኪ፡ይትዔየራሃ፡
ወይብላሃ፡እስመ፡በቀልነ፡መጽአ፡ላዕሌኪ፡
ዮም፡ምስለ፡ወልድኪ፤እስመ፡በእንቲአኪ፡
ኮነት ፡ ሐፀንነ ፡ ዘእንበለ ፡ ውሉድ ፡ እምክ
ልኤቱ፡ዓመት፡ዘወለድኪዮ።

፵፬፤ ወእለ ፡ ነበሩ ፡ ዐበይት ፡ እምአይሁድ ፡
ምስሌሁ፡ ለሄሮድስ ፡ ያጸንዑ ፡ ልቦ ፡ ከመ ፡
ይቅትሎ።
እስመ፡ውእቶሙ፡አመርዎ፡ለሄሮድስ፡ከመ፡
ጲላጦስ፡ያፈቅሮ፡ለኢየሱስ፤ወብዙኃን፡እም
አይሁድ ፡ ይብሉ ፡ ለእመ ፡ ሖርነ ፡ ንስቅሎ ፡
ይትነሥኡ፡አሕዛብ፡ላዕሌነ፡ወይመሥጥዎ፡
እምእዴነ፡በምክረ፡ጲላጦስ፡ፈኑ፡ይእዜኒ፡
ኀቤነ ፡ ትእዛዘከ ፡ ወሥልጣነከ ፡ ከመ ፡
ንስቅሎ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

መድከሜንና ፡ የልቤንም ፡ ሐዘን ፡ ተወ...
ከተህ ፡ ፊቱን ፡ እጠግበው ፡ ዘንድ ፡ ተወኝ፤
ዮሐንስ፡ሆይ፡የድኃ፡አደግ፡ማደሪያ፡በሆነ፡
በዚህ፡ተራራ፡ያለ፡ዛሬ፡አላየውምና።

፴፱፤ በእርሱ ፡ ላይ ፡ አለቅስ ፡ ዘንድ ፡ ተወኝ፤
በመከራው ፡ ጊዜ ፡ የኢዮብ ፡ መኝታው ፡
ነበርና፤ መከራዬም ፡ ከመከራው ፡ ይበል
ጣልና፤ ይቺም ፡ ቦታ ፡ የድኆች ፡ ሁሉ ፡
መጠጊያ፡ናትና።

፵፤ ከእርስዋም ፡ እጠግብ ፡ ዘንድ ፡ ተወኝ፤ እኔ፡
እናት ፡ አባት ፡ ወይም ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡
የለኝምና፤በልጅዋም፡መስቀል፡ቀኝ፡ቆማ፡
ሳለች ፡ ድንግል ፡ ሐዘኑ ፡ ጸንቶባት ፡ ነበርና፤
ከብቻው ፡ ልቅሶ ፡ በቀርም ፡ ልቧም ፡ በሐዘን፡
እጅግ ፡ ስለተነካ ፡ ያንን ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡
መለስ፡ብላ፡አታይም፡ነበር።

፵፩፤ እንዲህም ፡ ሆነ ፤ ከዚያ ፡ ቁመው ፡ የነበሩ፡
ሴቶች፡የኩዛ፡ሚስት፡ዮሐና፡መግደላዊት፡
ማርያምና፡ሰሎሜ፡እመቤታችን፡ድንግልን
ስትወድቅ፡አቅፈው፡ያነሷት፡ነበር።

፵፪፤ በእነዚህ፡ንጹሐን፡በሆኑ፡ሴቶች፡መካከል፡
ልቅሶዋ ፡ ልብ ፡ የሚነካ ፡ አሳዛኝ ፡ ጣዕም ፡
ያለው ፡ ነበር ፤ ስለ ፡ ልቅሶዋም ፡ ጣዕም ፡
ያለቅሱ፡ነበር።

፵፫፤ ከአይሁድ ፡ ሴቶች ፡ የሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ግን ፡
ስታለቅስ፡ልቅሶዋን፡የሰሙ፡እንዲህ፡እያሉ፡
ተገዳደሩአት፤ከወለድሽው፡በሁለት፡ዓመት፡
በአንቺ ፡ ምክንያት ፡ ከንዳችን ፡ ልጆችን ፡
ከማቀፍ ፡ ተለይቶ ፡ ነበርና ፤ በቀላችን ፡ ዛሬ ፡
በአንቺና፡በልጅሽ፡ላይ፡መጣ።

፵፬፤ ከሄሮድስ ፡ ጋር ፡ የነበሩ ፡ የአይሁድ ፡ ታላ
ቆችም፡ይገድለው፡ዘንድ፡የሄሮድስን፡ልብ
ያስጨክኑ፡ነበር።
እነርሱም፡ጲላጦስ፡ጌታ፡ኢየሱስን፡እንደሚ
ወደው፡ለሄሮድስ፡አመልክተውት፡ነበርና፤
ከአይሁድም ፡ ብዙዎች ፡ ልንሰቅለው ፡
ብንሄድ ፡ አሕዛብ ፡ ይነሡብናል ፤ በጲላ
ጦስም፡ምክር፡ከእጃችን፡ነጥቀው፡ይወስዱ
ታልና፤አሁንም፡እንሰቅለው፡ዘንድ፡ትእዛ
ዝህንና፡ኃይልህን፡ላክ፡አሉ።

Scanned by CamScanner

### በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፴፭ እስመ፡አይሁድ፡ወሀብዎ፡አምኃ፡ብዙኃ፡
ከመ፡ይፈኑ፡ምስሌሆሙ፡ሥልጣኖ፡
ወሐራሁ።

፴፮ ወበእንተ፡ዝንቱ፡ግብር፡ኢ.ወፅአ፡ጲላጦስ፡
ምስሌሁ፡በይእቲ፡ዕለት፡ከመ፡ኢይኩን፡
ጸብእ፡ማእከሌሁ፡ወማእከለ፡አይሁድ፡
እስመ፡ጲላጦስ፡ውብእሲቱ፡ያፈቅርዎ፡
ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ከመ፡ነፍሶሙ።

፴፯ ወዘቀሠፎ፡በጥብጣቤ፡ወዘገብረ፡ከመዝ፡
ከመ፡ያሥምሮሙ፡ለአይሁድ፡አማፅያን፡
ወከመ፡ያሠኒ፡ልቦሙ፡ወይፍትሕዎ፡
ዘእንበለ፡ሞት፡ወእመሰ፡አእመረ፡ጲላጦስ፡
ከመ፡ይሰቅልዎ፡እምኢወሀቦሙ፡ወእምኢያ
ብጽሐ፡ለሞት፡ውእቱ፡ምስለ፡ብእሲቱ፡
ወውሉዱ፡ወእምኢያንበረ፡እዴሁ፡ላዕሌሁ፡
ግሙራ።

፴፰ አላ፡በሐሰት፡አይድዕዎ፡ለጲላጦስ፡እንዘ፡
ይብሉ፡አንተሰ፡እምከመ፡ገሠጽኮ፤ለነ፡
ለዝንቱ፡ብእሲ፡ዘጽኑዕ፡ርእሱ፡ኢይደግም፡
እንከ፡ፈውሶ፡መነሂ፡በሰንበት፤ወንህነሰኬ፡
ንፈትሖ፡ወንሰድዶ።

፴፱ ወበዝንቱ፡ምክንያተ፡ጽልሑቶሙ፡ቀሠፎ፡
ጲላጦስ፡ወመሰሎ፡ከመ፡እሙን፡ቃሎሙ።

፵ ወካዕበ፡እምድኅረ፡ዝንቱ፡ኵሉ፡ንትመየጥ፡
ኀበ፡ዘቀዳሚ፡ነገር።
ኮነት፡ድንግል፡ትቀውም፡በየማነ፡ወልዳ፡
ወዮሐንስ፡ይፈቅድ፡ይሰዳ፡ቤቶ፡ወሖረ፡
ኀቤሃ፡ወሰአላ፡ከመ፡ትሑር፡ምስሌሁ።

፵፩ ወይእቲሰ፡ቆመት፡በብካይ፡ወገዐር፡
ወሰቈቃው፡ወናእክ።

፵፪ ወተመይጠት፡ውስተ፡ሀገር፡እንዘ፡ትብሎ፡

### ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፴፭፤ አይሁድ፡ሥልጣኑንና፡ጭፍሮቹን፡ከእነ
ሳቸው፡ጋር፡ይልክ፡ዘንድ፡ብዙ፡እጅ፡
መንሻ፡ሰጥተውት፡ነበርና።

፴፮፤ ስለዚህም፡ሥራ፡በዚች፡ቀን፡ጲላጦስ፡
ከእርሱ፡ጋር፡አልወጣም፤በእርሱና፡
በአይሁድ፡መካከል፡ጸብ፡እንዳይሆን፡
ጲላጦስና፡ሚስቱ፡ጌታ፡ኢየሱስን፡እንደ፡
ራሳቸው፡ይወዱት፡ነበርና።

፴፯፤ በጅራፍም፡ያስገረፈው፡እንዲህም፡ያደረገ፡
ዐመፀኞች፡አይሁድን፡ደስ፡አሰኝቶ፡ወደው፡
ያለሞት፡እንዲፈቱት፡ነበር፡እንጂ፤እንደሚ
ሰቁሉት፡አውቆ፡ቢሆንስ፡ጲላጦስ፡
ይሰቅሉት፡ዘንድ፡ባልሰጣቸው፡እርሱ፡
ሚስቱና፡ልጆቹ፡ሁነው፡ለሞት፡ባላደረ
ሱትም፡ነበር፤ከቶ፡እጁንም፡በላዩ፡
ባልጫነም፡ነበር።

፴፰፤ ዳግመኛም፡በሰንበት፡ማንም፡ማንን፡እንዳይ
ፈውስ፡ይህን፡ራሱን፡ጽኑዕ፡ያደረገ፡ሰው፡
አንተ፡ብትቀጣልን፡እኛም፡ፈትተን፡እንለ
ቀዋለን፡ብለው፡በሐሰት፡ለጲላጦስ፡
ነገሩት፡እንጂ።

፴፱፤ በዚህም፡ሽንገላቸው፡ምክንያት፡ቃላቸው፡
እውነት፡መስሎት፡ጲላጦስ፡ገረፈው።

፵፤ ዳግመኛም፡ከዚህ፡ሁሉ፡ወደ፡ጥንተ፡
ነገራችን፡እንመለስ።
ድንግልም፡በልጅዋ፡ቀኝ፡ቁማ፡ነበር፤
ዮሐንስም፡ወደቤቱ፡ሊወስዳት፡ወዶ፡ወደ፡
እርስዋ፡ቀረብ፡ብሎ፡ከእርሱ፡ጋር፡ትሄድ፡
ዘንድ፡ለመናት።

፵፩፤ እርሷ፡ግን፡በልቅሶና፡በጩኸት፡በፍጹም፡
ሐዘን፡ሁና፡ቆመች።

፵፪፤ ልጅዋንም፡እንዲህ፡እያለችው፡ወደ፡ሀገር፡

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ለወልዳ ፡ እሰነአለከ ፡ አ ፡ ወልድየ ፡ በሰላም ፡
ወበመስቀል፡ዘሰቀሉከ፡ዲቤሁ።
እሰነአለከ፡በእንተ፡ገጽከ፡ዘምሉዕ፡ብርሃነ፡
ወዘወረቁ፡ላዕሌሁ፡ምራቀ።

፶፫፡ አምኃ፡ወሰላም፡ለዕርቃንከ፡አ፡ንጉሥ፡ዘኮነ፡
ማእከለ፡ክልኤ፡ፈያት።

፶፬፡ አምኃ ፡ ወሰላም ፡ አ ፡ ወልድየ ፡ ለልብስከ ፡
ክቡር፡ዘወእቱ፡ውስተ፡እደ፡ጸላእትከ።

፶፭፡ አምኃ፡ወሰላም፡አ፡ወልድየ፡ለአክሊለ፡ሦክ፡
ዘወእቱ፡ይጼልል፡መልዕልተ፡ርእስከ።

፶፮፡ ዘንተ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ኮነት ፡ ድንግል ፡
ታስቈቊ፡ወትላሑ፡ወአብጽሕዋ፡ኀበ፡ቤተ፡
ዮሐንስ ፡ እንዘ ፡ ትበኪ ፡ ወትግዕር ፡ ወኢታ
ረምም።

፶፯፡ ወኢትሁብ፡ንዋመ፡ለአዕይንቲሃ፡እምብዝኃ፡
ብካያ፡ወሰቈቃዋ።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ምንተኑ፡አዐስየኪ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ ጸሎታ፡
ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

፩፡ ወይቤሎ ፡ እግዚእነ ፡ ለዮሐንስ ፡ ሑር ፡ ኀበ ፡
ጢባርዮስ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ስምዐ ፡
በኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘርኢከ ፡ እምኔየ ፡ ወበከመ ፡
ገብሩ ፡ ላዕሌየ ፡ እንዘ ፡ ሀሎኩ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡
መስቀል።

፪፡ ወእምድኅረ ፡ ይቤ ፡ ዘንተ ፡ መድኅን ፡ ለአር
ዳኢሁ፡ንጹሐን፡ተሠወረ፡እምኔሆሙ።

፫፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ዮሐንስ ፡ ፍቁረ ፡ እግዚእነ ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ኀበ ፡ ጢባርዮስ ፡ ንጉሠ ፡
ሮም ፤ ይቤሎ ፡ ጢባርዮስ ፡ ንጉሥ ፡ ኢክህደ ፡
ብፁዕ፡ዮሐንስ፤አንተኑ፡ዘትሰመይ፡ዮሐንስ፡
ፍቁረ፡እግዚእ።



ተመለሰች ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ በላዩ ፡ በሰቀሉህ ፡
መስቀል ፡ ላይ ፡ እያለሁ ፡ በፍቅር ፡ እሰናበት
ሃለሁ ፤ ብርሃንን ፡ ስለ ፡ ተመላው ፡ ምራቃቸ
ውንም ፡ ስለ ፡ ተፉበት ፡ ፊትህ ፡ እሰናበት
ሐለሁ።

፶፫፤ በሁለት፡ወንበዴዎች፡መካከል፡የተሰቀልከ፡
ንጉሥ፡ሆይ፡ለመራቆትህ፡እጅ፡እነሣለሁ፤
ሰላምታም፡አቀርብልሃለሁ።

፶፬፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ በጠላቶችህ ፡ እጅ ፡ ላለው ፡
ለከበረው፡ልብስህ፡እጅ፡እነሳለሁ፤ሰላምታ፡
አቀርባለሁ።

፶፭፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ከራስህ ፡ በላይ ፡ ለተንሳፈፈው፡
የእሾህ፡ዘውድ፡እጅ፡እየነሣሁ፡ሰላምታ፡አቀ
ርባለሁ።

፶፮፤ ይህንንና፡ይህን፡የመሰለ፡ልቅሶ፡እያለቀሰች፤
እየጮኸች፡ወደ፡ዮሐንስ፡ቤት፡አደረሱዋት፤
እርሷም ፡ ከመጮህና ፡ ከማልቀስ ፡ ዝም፡
አላለችም።

፶፯፤ ከልቅሶዋና ፡ ከሐዘንዋ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ፡
ለዐይኖቿ፡ሽልብታ፡አልሰጠችም።

ልመናዋ ፡ በረከቷ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ምንተኑ፡አዐስየኪ፡በል።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ይደር
ብንና ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ፡
የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡እመቤታችን፡ከብ
ርት፡ማርያም፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፤ ጌታችንም ፡ ዮሐንስን ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡
ሳለሁ፡ አይሁድ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን፡
ከእኔም ፡ ባየኸው ፡ ሁሉ ፡ ሥራ ፡ ምስክር፡
ትሆን፡ዘንድ፡ወደ፡ንጉሥ፡ጢባርዮስ፡ሂድ፡
አለው።

፪፤ መድኅን፡ጌታም፡ ይህን፡ካለ፡በኋላ፡ንጹሐን፡
ከሆኑ፡ደቀ፡መዛሙርቱ፡ተሠወረ።

፫፤ የጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወዳጅ ፡
ዮሐንስም ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ንጉሥ ፡ ጢባርዮስ ፡
በደረሰ፡ጊዜ፡ንጉሥ፡ጢባርዮስ፡የጌታ፡ወዳጅ፡
ዮሐንስ፡የምትባለው፡አንተ፡ነህን፡አለው፤የተ
መስገነ፡ዮሐንስም፡እውነቱን፡አልካደም።

## በ፯፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወባሕቱ፡ይቤ፡እንዘ፡ኢይደልወኒ፡ሰመዩኒ፡ ዘነገሥት፡ስመ፡ ወእመ፡ አኮሰ፡ እብል፡ አ፡ እግዚእየ፡ ንጉሥ፡ መኑ፡ ይክል፡ ፈቲሐ፡ ቀተሉ፡አሣእኒሁ፡እምእገሪሁ።

ወመኑ፡ዘይክል፡እኂዞተ፡ብርሃን፡ወኢ፡ ገሥሦተ፡ዐሐይ፡ወመብረቅ።

ወበመዝ፡ውእቱ፡በጥበቡ፡እንዘ፡ብርሃን፡ ውእቱ፡አምላክነ፡በፈቃዱ፡አትሐተ፡ርእሶ፡ በእንቲአነ፡ ወበፍቅሩ፡ ኀረየነ፡ ወረሰየነ፡ አኀዊሁ፡ወአርዳኢሁ።

አማን፡እብለከ፡አ፡ንጉሥ፡እስመ፡ኢፈቀደ፡ ይስምየነ፡ አግብርቲሁ፡ ወባሕቱ፡ ሰመየነ፡ አኀዊሁ፡ወመዋርስቲሁ።

ወይቤሎ፡ጢባርዮስ፡እንዘ፡ይክል፡ገቢረ፡ ዘንተ፡ኵሎ፡ኃይለ፡እፎ፡እንከ፡ክህልዎ፡ ይርግዝዎ፡አይሁድ፡እንዘ፡**አምላክ፡**ውእቱ።

ወይቤሎ፡ብፁዕ፡ዮሐንስ፡በእንቲአነ፡ወሕይ ወተ፡ከመ፡የሀበነ፡እምነቅዓ፡ማየ፡ሕይወት፡ ዘውኅዘ፡ እምገቦሁ፡ ማይ፡ ወደም፡ እንዘ፡ **አምላክ፡**ውእቱ፡በፈቃዱ፡ተሰቅለ፡አ፡ንጉሥ።

ወካዕበ፡እዜንወከ፡ዘገብረ፡ተአምረ፡አመ፡ ትቤሎ፡እሙ፡አ፡ወልድየ፡ወፍቁርየ፡እስመ፡ አልቦሙ፡ወይን፡ዘያስትዩ፡ለአኀዊከ፡እለ፡ ተጸውዑ፡ ውስተ፡ ከብካብ፡ ወይቤላ፡ አ፡ ብእሲቶ፡ ዝንቱ፡ ትእምርት፡ ዘይከውን፡ በደኀሪት፡ዕለት፡ዘትስእልኒ፡ወይነ፡ቱሱሐ፡ በማይ፡ከመ፡ይስተዩ፡እለ፡ተጸውዑ፡ውስተ፡ ከብካብ።

ወአንሰ፡በደኀሪት፡ዕለት፡እሁቦሙ፡ዘውኅዘ፡ እምገቦየ፡ ዘይከውን፡ ለስርየተ፡ ኃጢአት፡ ዘለዓለም፡ ማየ፡ ወደመ፡ ከመ፡ ይስተዩ፡ እምኔሁ፡ ኵሎሙ፡ ዘላዕለ፡ ምድር፡ ምእመናን።

ወዘገብረ፡ በቀዳሚ፡ ነገርኩከ፡ ወበደኀሪ፡ ወሀበ፡በከመ፡ይቤ።

ወይእዜኒ፡አ፡ንጉሥ፡አኮ፡መፍትው፡ለከ፡ ከመ፡ትኅሥሥ፡ማዕምቀተ፡**መለኮት**።

ወይቤሎ፡ንጉሥ፡አንተኑ፡ውእቱ፡ዘቆምከ፡ ቅድሜሁ፡አመ፡ይሰቅልዎ፡በህየ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፯፡ሰዓት።

፩፡ ነገር፡ ግን፡ እንዲህ፡ አለ፤ አዎ፡ ሳይገባኝ፡ በዚህ፡ ስም፡ ጠሩኝ፤ ጌታዬ፡ ንጉሥ፡ ሆይ፡ ይህማ፡ ባይሆን፡ ከእግሮቹ፡ የጫማውን፡ ማዘቢያ፡መፍታት፡ማን፡ይችላል፡እላለሁ።

፪፡ ብርሃንንስ፡መያዝ፤ ፀሐይንና፡መብረቅንስ፡ መዳሰስ፡የሚችል፡ማነው?

፫፡ እንደዚሁም፡እርሱ፡ብርሃን፡ሲሆን፡በማይመ ረመር፡ ጥበቡ፡ ፈጣሪያችን፡ እርሱ፡ ወዶ፡ ስለእኛ፡ራሱን፡አዋርዶ፡በፍቅሩም፡መረጠን፤ ወንድሞቹና፡ደቀ፡መዛሙርቱም፡አደረገን።

፬፡ ንጉሥ፡ሆይ፡እውነቱን፡እነግርሃለሁ፡እርሱ፡ ባሮቹ፡ ሊለን፡ አልወደደምና፡ ወራሾቹና፡ ወንድሞቹ፡አደረገን፡እንጂ።

፭፡ ጢባርዮስም፡ይህን፡ሁሉ፡ኃይል፡ማድረግ፡ ሲችል፡**አምላክም፡**ሲሆን፡አይሁድ፡ይወጉት፡ ዘንድ፡እንግዲህ፡እንዴት፡ቻሉ?አለው።

፮፡ የተመሰገነ፡ዮሐንስም፡ንጉሥ፡ሆይ፡ከጐኑ፡ ከሚፈሰው፡ የሕይወት፡ ምንጭ፡ ውኃና፡ ደም፡ ከዚያ፡ የሕይወት፡ ውኃን፡ ይሰጠን፡ ዘንድ፡ስለ፡እኛ፡ወዶ፡ተሰቀለ፡አለው።

፯፡ ዳግመኛም፡ያደረገውን፡ተአምራት፡እነግር ሃለሁ፡እናቱ፡ልጄ፡ወዳጄ፡ሆይ፡ወደ፡ሠርግ፡ ለተጠሩት፡ ለወንድሞችህ፡ የሚያጠጡ አቸው፡የወይን፡ጠጅ፡የላቸውም፡ባለችው፡ ጊዜ፤ አንቺ፡ ሆይ፤ የምትለምኚው፡ ይህ፡ ምልክት፤የሚሆነው፡በኋለኛይቱ፡ቀን፡ወደ፡ ሠርግ፡የተጠሩት፡ይጠጡት፡ዘንድ፡ከውኃ፡ ጋር፡የተዋሐደ፡ወይን፡ይሰጣቸዋል፡አላት።

፰፡ እኔም፤ በኋለኛይቱ፤ ቀን፤ ለዘላለሙ፡ ለኃጢአት፡ ማስተስረያ፡ ሊሆን፡ ከእርሱ፡ ይጠጡ፡ ዘንድ፡ በምድር፡ ላይ፡ ለሚኖሩ፡ ምእመናን፡ሁሉ፡ከጐኔ፡የፈሰሰውን፡ውኃና፡ ደም፡እሰጣቸዋለሁ።

፱፡ በመጀመሪያ፡ያደረገውን፡ነገርኩህ፤በኋላም፡ እንደተናገረ፡ሰጠ።

፲፡ አሁንም፡ንጉሥ፡ሆይ፡**የመለኮትን፡**ባሕርይ፡ ትመራመር፡ ዘንድ፡ ለአንተ፡ ተገቢህ፡ አይደለም፡አለው።

፲፩፡ ንጉሥም፡ በሰቀሉት፡ ጊዜ፡ በዚያ፡ በፊቱ፡ ቆመህ፡የነበርከ፡አንተ፡ነህን?አለው።

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፭፡ ወይቤሎ፡ አንሰ፡ ጸሐፍኩ፡ ወስምዐ፡ ኮንኩ፡ በኵሉ፡ ዘገብሩ፡ ላዕለ፡ እግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡እንዘ፡ሀሎ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል።
፲፮፡ ወይቤሎ፡ ንጉሥ፡ ንግረኒ፡ ዘከመ፡ ሰቀልዎ፡ ወይቤሎ፡ ንጉሥ፡ ንግረኒ፡ ዘከመ፡ ሰቀልዎ፡
ወይቤሎ፡ንጉሥ፡ንግረኒ፡ግበር፡ሊተ፡ሥዕሎ፡ ወእመሰ፡ትክል፡ገቢረ፡ግበር፡ሊተ፡ሥዕሎ፡
ወእመሰ፡ትክል፡ገቢረ፡ግበር፡ሊተ፡ሥዕሎ፡ዘከመ፡ርኢከ፡እንዘ፡ሀሎ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ ወይቤሎ፡ እወ፡ አነ፡ እገብር፡ ለከ፡ በኵሉ፡ ዘገብሩ፡ላዕሌሁ፡አ፡ንጉሥ።
፲፯፡ ውእተ፡ ጊዜ፡ አዘዘ፡ ከመ፡ ያምጽኡ፡ ሎቱ፡ ሰፋሐ፡እብነ፡ወክቡረ፡ዘሠናይ፡ራእዩ።
፲፰፡ ወገብረ፡ሎቱ፡ዮሐንስ፡በአምሳለ፡ስቅለተ፡ እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ላዕለ፡ እብን፡ ክቡር።
፲፱፡ ወሶበ፡ፈጸመ፡ብፁዕ፡ዮሐንስ፡ሥዕሎ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ አትሐተ፡ ርእሶ፡ ታሕተ፡ ወሰዐመ፡ ሥዕለ፡ ወልደ፡ እግዚአብሔር፡ሕያው።
፳፡ ወጠግዐ፡ ክናፍረ፡ ሥዕል፡ ምስለ፡ ክናፍረ፡ ብፁዕ፡ ዮሐንስ፡ ጕንዱየ፡ ሰዓተ፡ በይእቲ፡ ዕለት።
፳፩፡ ወንጉሥ፡ ጢባርዮስ፡ ሶበ፡ ርእየ፡ ዘንተ፡ አንከረ፡ ፈድፋደ፤ ወውእተ፡ ጊዜ፡ ጸርሐ፡ ሥዕለ፡ መድኅን፡ ንጉሥኒ፡ እንዘ፡ ይሰምዕ፡ ወኵሉ፡ አሐዱ፡ አሐዱ፡ እምውእደ፡ ይቀውም፡ ይሰምዕ፡ እንዘ፡ ይጸርሕ፡ ሥዕል፡ ወይብል፡“ዮሐንስ፡ፍቁርየ”።
፳፪፡ ወተናገሮ፡ ብዙኀ፡ ነገረ፡ ለዮሐንስ፡ ወእም ድኅረ፡ተናገረ፡ሥዕል፡አርመመ።
፳፫፡ ወሶበ፡ ርእየ፡ ንጉሥ፡ ዘንተ፡ ተአምረ፡ ተንሥአ፡ወሰዐመ፡ርእሶ፡ለዮሐንስ፡ቅዱስ፡ ረድእ፡ወይቤሎ፡አማን፡አንተ፡ረድኡ፡ለክርስቶስ፡ዘበአማን።
፳፬፡ ወእምድኅረ፡ይቤሎ፡ንጉሥ፡ዘንተ፡ሰዐመ፡ ሥዕለ፡ ወልደ፡ እግዚአብሔር፡ ዘሠዐለ፡ ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ወሰገደ፡ሎቱ፡ወአቀሞ፡ኀበ፡ ምድረ፡ሮሚ።
፳፭፡ ወለብፁዕሰ፡ዮሐንስ፡ጸገዎ፡ንጉሥ፡አምኃ፡ ብዙኀ፡ ዘመንክር፡ ወኢፈቀደ፡ ይንሣእ፡ እምኔሁ፡ወኢምንተኒ።
፳፮፡ ወሶቤሃ፡ ወፅአ፡ ገዳመ፡ እምሀገር፡ ጸረቶ፡ ደመና፡ ብርሀት፡ እስከ፡ አብጽሖቶ፡ ኢየሩ ሳሌም፡ኀበ፡አርድእት።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

፲፭፡ በዕንጨት፡ መስቀል፡ ላይ፡ ሳለ፡ በጌታችን፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ አይሁድ፡ያደረጉት፡ሁሉ፡ ምስክር፡የሆንኩ፡የጻፍኩም፡እኔ፡ነኝ፡አለው።
፲፮፡ ንጉሡም፡ እንዴት፡ እንደ፡ ሰቀሉት፡ንገረኝ፡ የምትችልም፡ ከሆነ፡ በዕንጨት፡ መስቀል፡ ላይ፡ ሳለ፡ እንደ፡ አየኸው፡ ሥዕሉን፡ሣልልኝ፡ አለው፤ እርሱም፡ ንጉሥ፡ ሆይ፡ በእርሱ፡ላይ፡ ያደረጉትን፡ሁሉ፡እኔ፡እሥልልሃለሁ፡አለው።
፲፯፡ ያንጊዜም፡ ሰፊ፡ የለዘበ፡ የከበረና፡ መልኩ፡ ያማረ፡ደንጊያ፡ያመጡለት፡ዘንድ፡አዘዘ።
፲፰፡ ዮሐንስም፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በተ ሰቀለበት፡አምሳል፡በከበረው፡ደንጊያ፡ላይ፡ ሣለለት።
፲፱፡ የተመሰገነ፡ዮሐንስም፡የጌታችን፡ኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ሥዕሉን፡ ሠርቶ፡ በፈጸመ፡ጊዜ፡ ራሱን፡ዝቅ፡አድርጎ፡የሕያው፡ባሕርይ፡የእግ ዚአብሔርን፡ልጅ፡ሥዕልን፡ሳመ።
፳፡ የሥዕሉም፡ ከንፈር፡ ከብፁዕ፡ ዮሐንስ፡ ከንፈር፡ጋር፡ተጠግቶ፡ለረጅም፡ጊዜ፡ቈየ።
፳፩፡ ንጉሥ፡ጢባርዮስም፡ይህን፡ባየ፡ጊዜ፡እጅግ፡ አደነቀ፤ በዚያን፡ ጊዜም፡ ንጉሡ፡ እየሰማ፡ የመድኀን፡ ሥዕል፡ ጮኸ፤ አንዱም፡ አንዱ፡ ከዚያ፡ ከቆመበት፡ ዘንድ፡ ሥዕሉ፡“ዮሐንስ፡ ወዳጄ”፡እያለ፡ሲናገር፡ይሰማ፡ነበር።
፳፪፡ ሥዕሉም፡ ለዮሐንስ፡ ብዙ፡ ነገርን፡ ነገረው፤ ከተናገረውም፡በኋላ፡ሥዕሉ፡ዝም፡አለ።
፳፫፡ ንጉሡም፡ ይህን፡ ተአምር፡ ባየ፡ ጊዜ፡ የከበረ፡ ደቀ፡መዝሙር፡ዮሐንስን፡ተነሥቶ፡ሳመው፤ በእውነት፡ አንተ፡ የክርስቶስ፡ ደቀ፡ መዝሙሩ፡ነህ፡አለው።
፳፬፡ ንጉሡም፡ ይህን፡ ካለው፡ በኋላ፡ የወልደ፡እግ ዚአብሔርን፡ ሥዕል፡ ተሳለመ፤ ሰገደለትም፤ በሮም፡ሀገርም፡አቆመው።
፳፭፡ ለከበረ፡ዮሐንስም፡ድንቅ፡የሆነ፡ብዙ፡እጅ፡ መንሻ፡ አቀረበለት፤ ዮሐንስ፡ ግን፡ ምንም፡ ምን፡ከእርሱ፡ሊቀበል፡አልወደደም።
፳፮፡ ወዲያውኑ፡ ከከተማ፡ ወደ፡ዱር፡ ወጣ፤ ሐዋር ያት፡ወዳሉበት፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡እስከምታደ ርሰው፡ድረስ፡ብርሀት፡ደመና፡ተሸከመችው።

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፯ ወይቤሎሙ ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ፡ ወዜነዎሙ ፡ ኵሎ፡ዘከነ፡ወአርድእትሰ፡ሰሚዖሙ፡ዘንተ፡ ወደሰዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ዕበዩ ፡ ተአምራሁ ፡ ዘይትገበር ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ መካን።

፳፰ ወሶበሂ ፡ አርድእት ፡ ሐዋርያት ፡ ንጹሐን ፡ ተበሐሉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ በከመ ፡ ረሰየነ ፡ ድልዋነ ፡ ንርአዮ ፡ ለፍቁርነ ፡ ዮሐንስ ፡ ከመ ፡ ይረስየነ ፡ ካዕበ ፡ ንርአያ ፡ ለእመ ፡ ኵልነ ፡ ንጽሕት ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ።

፳፱ ወእምድኅረ፡ይቤሉ፡እሙንቱ፡ዘንተ፡ናሁ፡ እግዝእትነ ፡ ቅድስት ፡ ድንግል ፡ በክልኤ ፡ ማርያም ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ወረደት ፡ እምሰማይ ፡ በውዳሴ ፡ ዘኢይትከሀል ፡ ይትነገር፡ወቆመት፡ቅድሜሆሙ።

፴ ወሶበ፡ርእይዋ፡ፈርሁ፡ወደንገፁ፡ወወድቁ፡ ታሕተ፡እገሪሃ፡ወኮኑ፡ከመ፡አብድንት፡ ወይእቲሰ፡አኀዘት፡እደዊሆሙ፡ለዮሐንስ፡ ወለያዕቆብ፡ወአንሥአቶሙ፡ቅድመ።

፴፩ ወእምድኅረዝ ፡ አንሥአቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሐዋርያት፡ወአሰሰለት፡እምኔሆሙ፡ፍርሀተ፡ ወዜነወቶሙ ፡ ምሥጢራተ ፡ ዘመንግሥተ ፡ ሰማያት።

፴፪ ርእዩኬ፡ፍቁራንየ፡እግዝእትነ፡ማርያምሰ፡ ረዳኢቶሙ፡ይእቲ፡ለነቢያት፡ወሐዋርያት፡ ወሰማዕታት።

፴፫ ወኵሉ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይጽሐቅ ፡ ይርከብ፡ረድኤታ፡በከመ፡ጽሕቁ፡አርድእት፡ ይርአዩ፡ኪያሃ፡ወይንሥኡ፡በረከታቲሃ።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር ፡ ወመንክር ፡ ዘገብረ ፡ እግዚእነ ፡ ወአምላክነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ሣህሉ ፡ ወምሕረቱ ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።



ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

፳፯፤ ሰላምታ ፡ ሰጥቷቸው ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ነገራቸው፤ሐዋርያትም፡በሰሙ፡ጊዜ፡በቦታ፡ ሁሉ ፡ ስለሚደረግ ፡ ስለ ፡ ተአምራቱ ፡ ገናናነት፡እግዚአብሔርን፡አመሰገኑት።

፳፰፤ በዚያን፡ጊዜም፡ንጹሐን፡ሐዋርያት፡እርስ፡ በርሳቸው ፡ ተወዳጅ ፡ ወንድማችን ፡ ዮሐንስን፡ ለማየት ፡ እንዳደለን ፡ ደግሞ ፡ የሁላችን፡እናት፡የሆነች፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡ በድንጋሌ፡ነፍስ፡የጸናች፡የአምላክን፡እናት፡ ንጽሕት፡እመቤታችን፡ማርያምን፡እናያት፡ ዘንድ፡እንዲሁ፡ያድለን፡ተባባሉ።

፳፱፤ እነርሱም ፡ ይህን ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ አምላክን ፡ የወለደች ፡ በድንጋሌ ፡ ሥጋ ፡ በድንጋሌ ፡ ነፍስ፡ የጸናች ፡ ክብርት ፡ እመቤታችን ፡ ማርያም፡እነሆ፡ሊነገር፡በማይቻል፡ክብር፡ ሁና፡ከሰማይ፡ወርዳ፡በፊታቸው፡ቆመች።

፴፤ በአዩዋትም፡ጊዜ፡ፈርተው፡ደንግጠውም፡ ከእግርዋ፡በታች፡ወደቁ፤እንደ፡በድንም፡ ሆኑ፤እርሷ፡ግን፡በመጀመሪያ፡የዮሐንስንና፡ የያዕቆብን ፡ እጆቻቸውን ፡ ይዛ ፡ አስነሣ ቻቸው።

፴፩፤ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ሐዋርያትን ፡ ሁሉ ፡ አስነሥታ፡ፍርሀትን፡ከእርሳቸው፡አራቀች ላቸው ፤ የመንግሥተ ፡ ሰማያትንም ፡ ምሥጢር፡ነገረቻቸው።

፴፪፤ የተወደዳችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ እመቤ ታችን፡ማርያም፡ለነቢያት፡ለሐዋርያት፡ለሰ ማዕታትም፡ረዳታቸው፡እንደሆነች፡እወቁ።

፴፫፤ እርሷን፡አይተው፡በረከቷን፡ይቀበሉ፡ዘንድ፡ ሐዋርያት፡እንደተጉ፡ረድኤቷን፡ለማግኘት፡ ሰው፡ሁሉ፡ይትጋ።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ ይኑርና ፤ ጌታችን ፡ ፈጣሪያችን ፡ መድኃኒ ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡ ተአምር፡ይህ፡ነው፡አሜን።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፩፡ ወሰቀሉ፡ምስለ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ፡** ክልኤተ፡ ፈያተ፡ ለአሐዱ፡ ስሙ፡ ጥጦስ፡ ለዘንቱ፡ ሰቀልዎ፡በየማኑ። ወስመ፡ካልኡ፡ዳክርስ፡ ወለዝ፡ሰቀልዎ፡በፀጋሙ።

፪፡ ወሶበ፡ነሥኡ፡እምኔሁ፡አልባሲሁ፡**ለእግዚእነ፡** ተዓፀዉ፡ኪራ፡ ላዕሌሆሙ፡ ከመ፡ ይትፈጸም፡ ቃለ፡ዳዊት፡ነቢይ፡ዘይቤ፡ወተካፈሉ፡አልባስየ፡ ለርእሶሙ፡ወተዓፀዉ፡ዲበ፡ዐራዝየ።

፫፡ ወይቤሎ፡**ለእግዚእነ፡** ፈያታይ፡ ዘስቁል፡ በፀጋም፡ እመሰ፡**ወልደ፡እግዚአብሔር፡** አንተ፡አድኅን፡ርእሰከ፡ወኪያነሂ፡አድኅነነ።

፬፡ ወገሠፆ፡ ፈያታይ፡ ዘስቁል፡ በየማን፡ ወይቤሎ፡አርምም፡ንሕነሰ፡በእንተ፡ጌጋይነ፡ ተሰቀልነ፡ ወለዝንቱሰ፡ ብእሲ፡ አልቦቱ፡ ኃጢአት፡ወጌጋይ።

፭፡ ወሶበ፡ይቤ፡ዘንተ፡ተፈትሐ፡አዕይንቲሁ፡ ወርእዮ፡**ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡** እንዘ፡ይነብር፡ ዲበ፡መንበረ፡ስብሐቲሁ፡ውስተ፡ሰማያት፡ ወመላእክት፡ይሴብሑ፡ዐውዶ።

፮፡ ወሶበ፡ርእየ፡ዘንተ፡ከሠተ፡አፉሁ፡ወይቤሎ፡ **ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡** ተዘከረኒ፡**እግዚኦ፡** አመ፡ ትመጽእ፡በመንግሥትከ።

፯፡ ወይቤሎ፡**እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡** ናሁ፡ ደለወከ፡ ትርዓይ፡ ክብርየ፡ ወስብሐትየ፡ አማን፡እብለከ፡ከመ፡ዮም፡ትሄሉ፡ምስሌየ፡ ወምስለ፡ሰብአ፡ርስት፡ሐር፡ውስተ፡ገነተ፡ ተድላ፡ እስመ፡ ናሁ፡ ወሀብኩከ፡ ሥልጣነ፡ ከመ፡ታርኁ፡አናቅጺሃ።

፰፡ ወለእመ፡ርኢኩሙ፡ለመላእክት፡ኢትፍራህ፡ እምባሕረ፡እሳት፡እንተ፡ተሐውር፡ዲቤሃ፡ እስመ፡ኢትክል፡ከሊአተከ።

፱፡ አእምር፡ከመ፡ዮም፡ትሄሉ፡ምስሌየ፡ህየ፡ ወትቀድሞ፡ለአዳም፡በዊአ፡ውስተ፡ገነት።

፲፡ ወእምዝ፡ይቤሎ፡ኢ፡ጥጦስ፡እስመ፡ዮም፡ተፈ ጸመ፡ነገርየ፡ዘእቤለከ፡በውስተ፡ፍኖተ፡ግብጽ። ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፫።

መልእክተ፡ጳውሎስ፡ኀበ፡ሰብአ፡ ገላትያ።

ምዕ፡፮፡፲፬-፲፯።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፩፡ **ከጌታችን፡ኢየሱስም፡** ጋር፡ ሁለት፡ ወንበዴ ዎችን፡ሰቀሉ፡የአንደኛው፡ስሙ፡ጥጦስ፡ነው፡ እርሱንም፡ በጌታ፡ ቀኝ፡ ሰቀሉት፡ የሁለተ ኛውም፡ ስሙ፡ ዳክርስ፡ ነው፡ እርሱንም፡ በግራው፡ሰቀሉት።

፪፡ ልብሶን፡ ለራሳቸው፡ ተካፈሉ፡ በመጐናጸ ፀያም፡ዕጣ፡ተጣጣሉ፡ያለው፡የነቢዩ፡ዳዊት፡ ቃል፡ ይፈጸም፡ ዘንድ፡ ልብሶቹን፡ ከእርሱ፡ በወሰዱ፡ጊዜ፡ጭፍሮች፡ዕጣ፡ተጣጣሉበት።

፫፡ በግራ፡የተሰቀለውም፡ወንበዴ፡**ጌታችንን፡** አንተ፡ **የእግዚአብሔር፡ልጅ፡** ከሆንክ፡ ራስህን፡አድን፤እኛንም፡አድነን፡አለው።

፬፡ በቀኝ፡የተሰቀለውም፡ወንበዴ፡ዝም፡በል፡ ብሎ፡ ገሠፀውና፡ እኛስ፡ በበደላችን፡ ተሰቅ ለናል፤ ይህ፡ ሰው፡ ግን፡ ኃጢአትና፡ በደል፡ የለበትም፡አለው።

፭፡ ይህን፡ባለ፡ጊዜ፡ዐይኑ፡ልቡናው፡ተከፍቶለት፡ **ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡** በሰማያት፡ በጌትነቱ፡ ዙፋን፡ ተቀምጦ፡ መላእክትም፡ በዙሪያው፡ቆመው፡ሲያመሰግኑት፡አየው።

፮፡ ይህንንም፡በአየ፡ጊዜ፡አፉን፡ከፍቶ፡**ጌታ፡ ኢየሱስን፡አቤቱ፡** በጌትነትህ፡በመጣህ፡ ጊዜ፡አስበኝ፡አለው።

፯፡ **ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡** እነሆ፡ ክብሬን፡ ጌትነቴን፡ ለማየት፡ የበቃህ፡ ሁነሃል፤ ርስት፡ ሰማያዊን፡ ከሚወርሱ፡ ሰዎች፡ጋር፡አብረኸኝ፡ዛሬ፡በተድላ፡ገነት፡ እንደምትኖር፡በእውነት፡እነግርሃለሁ፡ወደ፡ ተድላ፡ ገነትም፡ ግባ፤ እነሆ፡ በሮቿን፡ ትከፍት፡ዘንድ፡ሥልጣን፡ሰጥቼሃለሁና።

፰፡ መላእክትንም፡ ብታያቸው፡ አትፍራ፤ በላይዋም፡ ከምትሄድባት፡ የእሳት፡ ባሕር፡ የተነሣ፡አትፍራ፡ልትከለክልህ፡አትችልምና።

፱፡ ዛሬ፡ከእኔ፡ጋር፡በዚህ፡እንደምትኖር፡ወደ፡ ገነት፡ በመግባት፡ አዳምንም፡ እንደምትቀ ድመው፡ዕወቅ፡አለው።

፲፡ ከዚህም፡በኋላ፡ጥጦስ፡ሆይ፡በግብጽ፡ጐዳና፡ የነገርኩህ፡ነገሬ፡ዛሬ፡ተፈጸመ፡አለው። ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ክፍል፡፫።

ወደ፡ገላትያ፡ሰዎች፡የተላከ፡የጳውሎስ፡ መልእክት።

ምዕ፡፮፡፲፬-፲፯።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፬ ወአንሰ ፡ ሐሰ ፡ ሊተ ፡ ኢይዜኀር ፡ ዘእንበለ ፡
በመስቀሉ ፡ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤
ወበኀቤየሰ፡ምዉት፡ዓለም፡ወአነሂ፡ምዉት፡
በኀበ፡ዓለም።
፲፭ እስመ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተገዝሮሂ ፡
ኢይበቍዕ ፡ ወኢተገዝሮሂ ፡ ኢያሰልጥ ፡
ዘእንበለ፡ሐዳስ፡ፍጥረት።
፲፮ ወላዕለ፡ኵሎሙ፡እለ፡ይገብሩ፡በዝንቱ፡ሕግ፡
ሰላም፡ወሣህል፡ወዲበ፡እስራኤል ፡ዘእግዚአ
ብሔር።
፲፯ እምይእዜ፡አልቦ፡ዘያንጥየኒ፡አንሰ፡ሕማሞ፡
ለክርስቶስ፡ እጸውር፡በሥጋየ።

## ትእዛዝ።

ወይቁሙ ፡ ሠለስቱ ፡ ካህናት ፡ ኀበ ፡ ሠለስቱ ፡
ምቅዋም ፡ ነሢኦሙ ፡ ሠለስተ ፡ ጽንሓሓተ ፡
ወይዕጥኑ፡ሥዕለ፡ስቅለት፡በዕጣን፡ወከርቤ።
ወሰብዐቱ ፡ ዲያቆናት ፡ ያብርሁ ፡ ሰብዐተ ፡
መባርህተ ፤ ወበስድስቱ ፡ ሰዓት ፡ ሶበ ፡
ይትነበብ፡ወንጌለ፡ዮሐንስ፡ያጥፍኡ።
ወያንብብ፡ዲያቆን፡በንባብ፡ማሕዘኒ።

፩ አ፡መኑ፡ዝንቱ፡በስድስቱ፡ዕለት፡ወጊዜ፡
ስድስቱ፡ሰዓት፡ተቀኖከ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡
በፈቃድከ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአት ፡ ዘገብረ ፡
አዳም፡በውስተ፡ገነት።
፪ ሥጥኪ ፡ መጽሐፈ ፡ ዘተጽሕፋ ፡ ቦቱ ፡
ኃጣውኢነ።
፫ አ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ አድኀነነ ፤ አንሰ ፡
ጸራሕኩ ፡ ኀበ ፡እግዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡
ወሰምዓኒ።
፬ ስማዕ ፡እግዚእ ፡ ጸሎትየ ፡ ወኢትትሐየይ ፡
ስእለትየ ፤ነጽረኒ፡ወስምዓኒ፡ሠርከ፡ወነግሀ፡
ወመዐልተ፡እነግር።
፭ አየድዕ ፡ ወኢሰምዑኒ ፡ ቃልየ ፡ አድኅና ፡
በሰላም፡ለነፍስየ።
፮ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡
ቅዱስ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፲፬ እኔ ፡ ግን ፡በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
መከራ ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ አልመካም ፤ በእኔ ፡
ዘንድ፡ ዓለም ፡ የሞተ ፡ ነው ፤ እኔም ፡ በዓለም ፡
ዘንድ፡የሞትኩ፡ነኝ።
፲፭ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አዲስ ፡ ሰውነት ፡
(ልጅነት)፡ማግኘት፡ነው፡እንጂ፤መገረዝም፡
አይጠቅምም፡አለመገረዝም፡አይጐዳምና።
፲፮ በዚህ፡ሕግ፡ፀንተው፡ለሚኖሩ፡ሰላም፡ይሁን
ላቸው፤ይቅርታም፡የእግዚአብሔር፡ ወገኖች፡
በሆኑ፡እስራኤል፡(ክርስቲያን)፡ላይ፡ይሁን።
፲፯ እንግዲህ ፡ ወዲህስ ፡ የሚዘበዝበኝ ፡ አይኑር ፤
እኔ ፡የኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ መከራ፡በሥጋዬ፡
እሸከማለሁ።

## ትእዛዝ።

ሦስት ፡ ካህናት ፡ ሦስት ፡ ጽንሓሕ ፡ ይዘው ፡
በሦስት፡ቦታ፡ይቁሙ፤የስቅለቱንም፡ሥዕል፡
በከርቤና፡በዕጣን፡ይጠኑ።
ሰባት፡ዲያቆናትም፡ሰባት፡መብራት፡ያብሩ፤
በስድስት ፡ ሰዓትም ፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡
ሲነበብ፡ያጥፉት።
ዲያቆኑም፡በማሕዘኒ፡ዜማ፡(በውርድ፡ንባብ)።

፩ ወዮ፣ አንተ፡ማነህ፤አዳም፡በገነት፡ሳለ፡ስለ፡
ሠራው ፡ ኃጢአት ፡ በስድስተኛው ፡ ቀን ፡
በስድስት፡ሰዓት፡በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡
በፈቃድህ፡የተቸነከርከ።
፪ ኃጢአታችን ፡ የተጻፈበትን ፡ የዕዳ ፡ ደብዳቤ ፡
አጥፋ።
፫ ፈጣሪያችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ አድነን ፤ እኔ ፡
ወደ ፡ፈጣሪዬ፡ ወደ ፡እግዚአብሔር፡ ለመንሁ፤
እሱም፡ልመናዬን፡ሰማኝ።
፬ አቤቱ፡ ልመናዬን ፡ ስማ ፡ ልመናዬንም ፡ ቸል ፡
አትበል ፡ ልመናዬን ፡ ሰምተህ ፡ በዓይነ ፡
ምሕረት፡ እየኝ ፤ በጧት ፡ በማታ ፡ በቀትር ፡
በመዓልት፡በሌሊት፡ሕግህን፡እስተምራለሁ።
፭ ብመከራቸው ፡ ምክሬን ፡ ትምህርቴን ፡ አልሰ
ሙኝም ፤ ወዳጅ ፡ መስሎ ፡ ከሚመጣ ፡ ጠላት ፡
ሰውነቴን፡አድናት።
፮ ለአብ፡ለወልድ፡ለመንፈስ፡ቅዱስ፡ምስጋና፡
ይሁን።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አምላክነ፡ዘበስድስቱ፡
ሰዓት፡ተቀኖከ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ወበዕፅ፡
አሞትከ፡ለኃጢአት።

፯፤ ወበሞትከ፡ማሕየዊ፡አሕየውከ፡ለዘሞተ፡
ብእሲ፡አዳም፡ዘለሐኰቶ፡እዴከ፡ወዘአቅ
ተለቶ፡ኃጢአት፤ወሐደስኮ፡ለሰብእ፡በአር
አያከ፡ዳግመ፡ወአባእኮ፡ውስተ፡ገነተ፡
ትፍሥሕት።

፰፤ አሙትኬ ፡ ሕማማትየ ፡ በሕማምከ ፡
ማሕየዊት፡ወበቅንዋት፡ዘተቀኖከ፡ቦቶን፤
ሚጥ፡ልብየ፡እምሕማማተ፡ግብረ፡ዓለም፡
ኀበ፡ተዘከሮ፡ትእዛዛቲከ፡ማሕየውያት፡
እስመ፡አንተ፡መስተሣህል።

ይእዜኒ ፡ ወዘልፈኒ ፡ ወለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

፱፤ እስመ፡አልብነ፡ገጽ፡በእንተ፡ብዝኃ፡አበሳነ፡
ወበእንተዝ፡ንቀርብ፡ኀቤኪ፡ትሰአሊ፡በእን
ቲአነ፡ኀበ፡ዘተወልደ፡እምኔኪ፡እ፡ድንግል፡
ንጽሕት፡ወላዲተ፡እግዚእ፡እስመ፡ዐባይ፡
ይእቲ፡ስእለትኪ፡ጽንዕት፡ወውክፍት፡
በኀበ፡እግዚአብሔር።

፲፤ ወእም፡ንጽሕት፡ኢትግድፊ፡ኪያነ፡ኃጥአነ፡
ወአስተሥርዪ፡ጊዜ፡አስተብቍዖትኪ፡ኀበ፡
ዘተወልደ፡እምኔኪ፤እስመ፡መሐሪ፡ውእቱ፡
ወይክል፡አድኅኖተነ፡እስመ፡ሐመ፡በእን
ቲአነ፡ከመ፡ፍጡነ፡ይባልሐነ።

፲፩፤ ለትርከበነ፡ሣህልከ፡እግዚእ፡እስመ፡ጥቀ፡
ተመንደብነ።
ርድአነ፡ወአድኅነነ፡እ፡እግዚአብሔር፡
መድኃኒነ፡በእንተ፡ስምከ፡እ፡እግዚእ፡
አድኅነነ።
ወሥረይ፡ኃጣውኢነ፡በእንተ፡ስምከ፡ቅዱስ።

ስብሐት፡ለአብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡
ቅዱስ፡ለዓለም፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ፈጣሪያችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡በስድ
ስት፡ሰዓት፡በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡የተቸነከ
ርክ፡በዕፀ፡መስቀልህም፡ኀጢአትን፡አጠፋሃት።

፯፤ ሕይወት፡መድኃኒት፡በሆነ፡ሞትህ፡እጅህ፡
የፈጠረችውን፡ኃጢአት፡ያስገደለችውን፡
የሞተ፡ሰው፡አዳምን፡አዳንከው፤በእርእ
ያህም፡ዳግመኛ፡አድሰህ፡ተድላ፡ደስታ፡
ወዳለበት፡ገነት፡አስገባኸው።

፰፤ ሕይወት፡መድኃኒት፡በሆነች፡ሕማምህ፡
በተቸነከርክባቸውም፡ችንካሮች፡ሕማሜን፡
አጥፋ፤ሕማመ፡ነፍስ፡ከሚያመጣ፡
ከዓለማዊ፡ሥራ፡ሕይወት፡ወደሚሆን፡
ትእዛዝህ፡ልቤን፡መልስ፤አንተ፡ይቅር፡ባይ፡
መሐሪ፡ነህና።
ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን።

፱፤ ከበደላችን፡ብዛት፡የተነሣ፡ባለሟልነት፡
የለንምና፤ስለዚህ፡ካንቺ፡ወደ፡ተወለደው፡
ስለእኛ፡ትለምኚልን፡ዘንድ፡ወዳንቺ፡እንቀር
ባለን፤ጌታን፡የወለድሽ፡ንጽሕት፡ድንግል፡
ሆይ፡ልመናሽ፡ታላቅ፡ናትና፡በማማለድም፡
የጸናች፡በእግዚአብሔርም፡ዘንድ፡ተቀባ
ይነት፡ያላት፡ናትና።

፲፤ ንጽሕት፡እናት፡ሆይ፤እኛን፡ኃጢአተኞቹን፡
አትጣዪ፤ካንቺ፡ወደተወለደውም፡በምት
ማልጂ፡ጊዜ፡ኃጢአታችንን፡አስተሥር
ዪልን፤መሐሪ፡ይቅር፡ባይ፡ነውና፤እኛንም፡
ማዳን፡ይችላል፤ፈጥኖም፡ያድነን፡ዘንድ፡
ስለእኛ፡መከራ፡ተቀብሏልና።

፲፩፤ እጅግ፡ተሠቃይተናልና፤አቤቱ፡ይቅርታህ፡
ፈጥና፡ትደረግልን።
መድኃኒታችን፡እግዚአብሔር፡ሆይ፡ስለ
ስምህ፡ብለህ፡ርዳን፤አድነን፡አቤቱ፡
ፈጽመህ፡አድነን።
ስለ፡ከበረውና፡ስለ፡ተመሰገነው፡ስምህ፡
ኃጢአታችንን፡አሥተሥርይልን።
ለአብ፡ለወልድ፡ለመንፈስ፡ቅዱስ፡ምስጋና፡
ይሁን፡[illegible]

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

## ትእዛዝ።

ወይሰግዱ፡ሠለስቱ፡ካህናት፡በጸታ፡እንዘ፡
ይብሉ፡ለለ፡አሐዱ፡አሐዱ፡ለመስቀልከ፡
ንሰግድ፡አ፡ሊቅነ፡ወለትንሣኤከ፡ቅድስት፡
ንሴብሕ፡ኵልነ፡ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ።
(ይ፡ሕ)፡ከማሁ።
(ይ፡ዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ።
፩ መብርከ፡መድኃኒተ፡በማእከለ፡ምድር፡አ፡
ክርስቶስ፡አምላክነ፡ሶበ፡ሰፋሕከ፡እደዊከ፡
ንጹሐተ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡በእንተ፡
ኃጢአተ፡ኵሉ፡ዓለም።
፪ ይጸርሑ፡ኀቤከ፡እንዘ፡ይብሉ፡አ፡እግዚአ፡
ስብሐት፡ለከ፡ስብሐት፡ለአብ፡ወወልድ፡
ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡
ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
(ይካ)፡ሠለስተ፡ጊዜ፡ለመስቀልከ።
(ይ፡ሕ)፡ከማሁ።
(ይዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ።
፫ ለመልክእከ፡ዘኢይማስን፡ንሰግድ፡አ፡ኄር፡
ወነኃሥሥ፡ሥርየተ፡ኃጢአትነ።

፬ አ፡ክርስቶስ፡አምላክነ፡እስመ፡አንተ፡
በፈቃድከ፡ሠመርከ፡ከመ፡ትዕርግ፡ላዕለ፡
መስቀል፡ከመ፡ትባልሖ፡ዘፈጠርከ፡እምተ
ቀንዮ፡ለጸላኢ።
፭ ኀቤከ፡ንጸርሕ፡ወኪያከ፡ንአኵት፡እስመ፡
ኵለሄ፡መላእከ፡ትፍሥሕተ።
፮ አ፡መድኅን፡ሶበ፡መጻእከ፡ከመ፡ተሐውጽ፡
ዓለመ፡እግዚእ።
ስብሐት፡ለከ፡ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።
(ይካ)፡ሠለስተ፡ጊዜ፡ለመስቀልከ።
(ይ፡ሕ)፡ከማሁ።
(ይ፡ዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ።
፯ ንሴብሖከ፡አ፡ምልእተ፡ውዳሴ፡አ፡
ድንግል፡ኵሎ፡ጊዜ፡አ፡ምልእተ፡ጸጋ፡አ፡
ወላዲተ፡እግዚእ፡እስመ፡በወልድኪ፡
ተነሥተ፡አረፋቲሃ፡ለሲኦል፡ወበጠለ፡
ሞት፡በመስቀል፡ወሙታነ፡ከዊነነ፡
ተንሣእነ፡ወለሕይወት፡ድልዋነ፡ኮነ፡
ወተጸጎነ፡ገነተ፡ትፍሥሕት፡ዘቀዳሚ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

## ትእዛዝ።

ሦስት፡ካህናት፡እያንዳንዱ፡እንዲህ፡እያሉ፡
በተራ፡ይስገዱ፤መምህር፡ሆይ፡ለመስቀልህ፡
እንሰግዳለን፡ልዩ፡ለሆነች፡ትንሣኤህም፡
ሁላችን፡እናመሰግናለን፡ዛሬም፡ዘወትርም፡
ሕዝቡም፡እንደርሱ፡ይበሉ።
ዲያቆኑ፡በውርድ፡ንባብ፡ይበል።
፩ ፈጣሪያችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ስለ፡ዓለሙ፡
ሁሉ፡ኃጢአት፡ንጹሐት፡የሆኑ፡እጆችህን፡
በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡በዘረጋህ፡ጊዜ፤
በምድር፡መካከል፡መድኃኒትን፡አደረግህ።
፪ አቤቱ፡ለአንተ፡ምስጋና፡ይገባል፡እያሉ፡
ይጮኻሉ፤ለአብ፡ለወልድ፡ለመንፈስ፡
ቅዱስ፡ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡
ምስጋና፡ክብር፡ይገባል።
ካህኑ፡ሦስት፡ጊዜ፡ለመስቀልከ፡ይበል።
ሕዝቡ፡እንደርሱ፡ይበሉ።
ዲያቆኑ፡በውርድ፡ንባብ፡ይበል።
፫ ለማይለወጠው፡መልክህ፡እንሰግዳለን፤ቸር፡
ሆይ፡የኃጢአታችንን፡ሥርየት፡ካንተ፡
ዘንድ፡እንሻለን።
፬ ፈጣሪያችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ፍጥረትህን፡
ከጠላት፡መገዛት፡ታድን፡ዘንድ፤በመስቀል፡
ላይ፡መሰቀልን፡ወደህ፡በፈቃድህ፡አድርገ
ሃልና።
፭ ወደንተ፡እንጮሃለን፤አንተንም፡እናመሰግ
ናለን።
፮ አቤቱ፡መድኅን፡ሆይ፡ዓለምን፡ልትጐበኝ፡በመ
ጣህ፡ጊዜ፡ተድላ፡ደስታን፡መልተህልናልና።
ለአንተም፡ክብር፡ምስጋና፡ይሁን፡ዛሬም፡
ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን።
ካህኑ፡ሦስት፡ጊዜ፡ለመስቀልከ፡ይበል።
ሕዝቡ፡እንደርሱ፡ይበሉ።
ዲያቆኑ፡በውርድ፡ንባብ፡ይበል።
፯ ሁል፡ጊዜ፡ምስጋናን፡ክብርን፡የተመላሽ፡
ሁሉ፡ጊዜ፡ምስጋናን፡እናመሰግንሻለን፤ጊታን፡
ድንግል፡ሆይ፡እናመሰግንሻለን፤ጌታን፡
የወለድሽ፡ጸጋ፡ክብርን፡የተመላሽ፡ሆይ፡
በልጅሽ፡ሞት፡የሲኦል፡ቅጽሮችዋ፡ፈርሰ
ዋልና፤ሞትም፡በመስቀል፡ጠፍቷልና፤
ሙታኖችም፡ሁነን፡የነበርን፡ተነሥተን፡
ለሕይወት፡የተዘጋጀን፡ሆንን፤የቀደመውን፡
የተድላ፡ገነት፡ተቀበልን።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፤ ወበእንተዝ ፡ ንዌድሶ ፡ ወንአኵቶ ፡ ኃይሎ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ዘኢይማስን ፡ ወንጸርሕ ፡ ኀቤሁ ፡ ኵልነ ፡ እንዘ ፡ ንብል ፡ መሐረነ፡ እግዚኦ ፡ወተሣሃለነ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኃኒነ።
ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

### ትእዛዝ።

ወእምዝ፡ይበሉ፡ካህናት፡ቅዱስ፡ እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፡ኃያል ፡ ቅዱስ ፡ ሕያው ፡ ዘኢይመውት ፡ ዘተወልደ ፡ እማርያም ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ ተሣሃለነ ፡ እግዚኦ ። ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ፡ ኃያል ፡ ቅዱስ ፡ ሕያው ፡ ዘኢይመውት ፡ ዘተጠምቀ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወተሰቅለ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል፡ተሣሃለነ፡ እግዚኦ።

### ክፍል፡፬።

ይዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፡፳፩፡፲፮-፲፯።

ቀነዉኒ፡እደውየ፡ወእገርየ።
ወኈለቁ ፡ ኵሎ ፡ አዕፅምትየ ። እሙንቱሰ ፡ ጠይቆሙ፡ወተበወሩኒ።

### ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፡፳፯፡፳፯-፴፩።

፳፯፤ ወእምዝ ፡ ነሥእዎ ፡ መስተራትዓተ ፡ ሐራ ፡ ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወወሰድዎ፡ውስተ፡ዐውድ፡ ኀበ፡ምኵናን፡ወአስተጋብኡ፡ላዕሌሁ፡ኵሎ፡ ሥርዌ፡ሐራ።
፳፰፤ ወአዕተቱ፡አልባሲሁ፡ወአልበስዎ፡ከለሜዳ፡ዘለይ።
፳፱፤ ወፀፈሩ፡ሐራ፡አክሊለ፡ዘሦክ፡ወአስተቀጸልዎ፡ ዲበ፡ርእሱ፡ወአስተአኀዝዎ፡ኅለተ፡በየማኑ፡ ወአስተብረኩ፡ቅድሜሁ፡ወይሣለቁ፡ላዕሌሁ፡ ወይቤልዎ፡በሓ፡ንጉሠ፡አይሁድ።
፴፤ ወይወርቁ፡ላዕሌሁ፡ወነሥኡ፡ኅለተ፡ወይኰ ርዕዎ፡ርእሶ፡በኅለት።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፤ ስለዚህም ፡ የማይወለጥ ፡ የፈጣሪያችን ፡ የክርስቶስን ፡ሥልጣን፡ፈጽመን፡እናመሰግናለን፤እናከብራለን፤ መድኃኒታችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ፡ ይቅር፡በለን፤ራራልን፡እያልን፡ወደእርሱ፡እንጮኻለን።
ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡በእውነት።

### ትእዛዝ።

ከዚህም፡በኋላ፡ካህናቱ፡እንዲህ፡ይበሉ፤ቅዱስ፡ እግዚአብሔር ፡ቅዱስ ፡ ኃያል ፡ ልዩ ፡ ሕያው ፡ የማይሞት ፡ ከንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ የተወለደ፡ አቤቱ ፡ይቅር፡በለን፤ልዩ፡ገዥ፡ልዩ፡ ኃያል፡ልዩ፡ሕያው፡የማትሞት፡በዮርዳኖስ፡ውኃ፡ የተጠመቅህ ፡ በዕንጨት ፡ መስቀልም ፡ የተሰቀልህ፡ አቤቱ ፡ይቅር፡በለን፡እስከሚለው፡ድረስ።

### ክፍል፡፬።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፡፳፩፡፲፮-፲፯።

እጄን፡እግሬን፡ቸነከሩኝ።
አጥንቶቼንም፡ሁሉ፡ቈጠሩ፤እነሱስ፡አውቀው፡ ተረድተው፡ቸል፡አሉኝ፡ይበል።

### የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፯፡፳፯-፴፩።

፳፯፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የጭፍሮች ፡ ባለወኀች ፡ ጌታ፡ ኢየሱስን ፡ ተቀብለው ፡ ከአደባባይ ፡ ወደሚፈርዱበት፡ቦታ፡ወሰዱት፤የጭፍሮቹንም፡ሠራዊት፡ ሁሉ፡ሰበሰቡ።
፳፰፤ ልብሱን፡ገፈው፡ቀይ፡ግምጃ፡አለበሱት።
፳፱፤ ጭፍሮችም፡የእሾህ፡አክሊል፡ጐንጕነው፡በራሱ፡ ላይ ፡ ደፉበት ፤ በቀኝ ፡ እጁም ፡ ዘንግ ፡ አስያዙት፤ በፊቱም፡ተንበርክከው፡የአይሁድ፡ንጉሥ፡ሆይ፡ ሰላምታ፡ይገባሃል፡እያሉ፡ተዘባበቱበት።
፴፤ በላዩ ፡ ይተፉበት ፡ ያስያዙትንም ፡ ዘንግ ፡ ተቀብለው፡ራሱን፡በዘንግ፡ይመቱት፡ነበር።

ዘከመ አስተቀጸልዎ አይሁድ አክሊለ ሦክ ለእግዚእነ::



አይሁድ ጌታችንን የሾህ አክሊል በራሱ ላይ እንደጫኑበት::

፴፩፤ ወተሣለቆሙ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሰለብዎ ፡ ውእተ ፡ ከለሜዳ ፡ ዘለይ ፡ ወአልበስዎ ፡ አልባሲሁ ፡ ወወሰድዎ፡ይሰቅልዎ።

፴፩፤ ከተዘባበቱበትም ፡ በኋላ ፡ ያን ፡ ቀይ ፡ ግምጃ ፡ ገፈው ፡ ልብሱን ፡ አለበሱትና ፡ ሊሰቅሉት ፡ ወሰዱት።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፴፪ ወእንዘ ፡ ይወፅኡ ፡ ረከቡ ፡ ብእሴ ፡ ቀሬናዌ ፡ ዘስሙ ፡ ስምዖን ፡ ወዐበጥዎ ፡ ይጹር ፡ መስቀሎ።
፴፫ ወበጺሖሙ፡ብሔረ፡ዘስሙ፡ጎልጎታ፡ዘበትርጓሜሁ፡ቀራንዮ፡ወሀብዎ፡ይስተይ፡ወይነ፡ወሐሞተ፡ድሙረ።
፴፬ ወጥዒሞ፡አበየ፡ሰትዮ።
፴፭ ወእምዝ፡ሰቀልዎ፡ወተካፈሉ፡አልባሲሁ፡ወተዐፀዉ፡ላዕሌሁ፡ከመ፡ይትፈጸም፡ቃለ፡መጽሐፍ ፡ ዘይቤ ፡ ተካፈሉ ፡ አልባስየ ፡ ለርእሶሙ፡ወተዓፀዉ፡ዲበ፡ዐራዝየ።
፴፮ ወነበሩ፡የዓቅብዎ፡ህየ።
፴፯ ወአንበሩ ፡ መልእልተ ፡ ርእሱ ፡ ጽሒፎሙ ፡ መጽሐፈ ፡ ጌጋዩ ፡ ዘይብል ፡ ዝ ፡ ንጉሦሙ ፡ ለአይሁድ፡ **ኢየሱስ።**
፴፰ ወእምዝ፡ሰቀሉ፡ምስሌሁ፡ክልኤተ፡ፈያተ፡አሐደ፡በየማኑ፡ወአሐደ፡በፀጋሙ።
፴፱ ወእለሂ፡የሐልፉ፡ይፀርፉ፡ላዕሌሁ፡እንዘ፡የሐውሱ፡ርእሶሙ።
፵ ወይብሉ፡አ፡ዘይነሥቶ፡ለቤተ፡መቅደስ፡ወየሐንጾ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡ አድኅን ፡ ርእሰከ፡ እመሰ ፡ **ወልደ ፡ እግዚአብሔር** ፡ አንተ፡ረድ፡እስከ፡እመስቀልከ።
፵፩ ወከማሁ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናትኒ ፡ ይሣለቁ ፡ ምስለ ፡ ጸሐፍት ፡ ወሊቃናት ፡ እንዘ ፡ ይብሉ።
፵፪ ዘባዕደ ፡ ያድኅን ፡ ወርእሶ ፡ ኢይክል ፡ አድኅኖ ፡ እመሰ ፡ ንጉሠ ፡ እስራኤል ፡ ውእቱ ፡ ለይረድ ፡ ይእዜ ፡ እመስቀል ፡ ንርዓይ ፡ ወንእመን፡ቦቱ።
፵፫ ወለእመ ፡ ተአመነ ፡ **በእግዚአብሔር** ፡ ናሁ ፡ ይእዜ ፡ ለያድኅኖ ፡ እመ ፡ ይፈቅዶ ፡ እስመ ፡ ይብል፡ **ወልደ፡እግዚአብሔር**፡አነ።
፵፬ ወከማሁ፡ፈያትኒ፡እለ፡ተሰቅሉ፡ምስሌሁ፡ይዘንጕጕዎ።
፵፭ ወእምጊዜ፡ስሱ፡ሰዓት፡ጸልመ፡ኵሉ፡ዓለም፡እስከ፡ተሱዓት፡ሰዓት።
**ይካ፡ይዲ፡ይሕ**፡ከመ፡ቀዳሚ።
ጊዜ ፡ ስድስቱ ፡ ሰዓት ፡ አልበስዎ ፡ አልባሲሁ ፡ **ለኢየሱስ** ፡ ወወሰድዎ ፡ ይስቅልዎ።



ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፴፪፤ ሲወጡም፡ስሙ፡ስምዖን፡የሚባል፡የቀሬና፡ሰው ፡ አግኝተው ፡ መስቀሉን ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ፡አስገደዱት።
፴፫፤ ትርጓሜው ፡ የራስ ፡ ቅል ፡ ወደሚሆን ፡ ጎልጎታ፡ወደሚባል፡ቦታ፡በደረሱ፡ጊዜም፡ከሐሞት ፡ የተቀላቀለ ፡ ወይንን ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ፡ሰጡት።
፴፬፤ ቀምሶም፡መጠጣትን፡እምቢ፡አለ።
፴፭፤ ከሰቀሉትም ፡ በኋላ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጥለው ፡ ልብሱን ፡ ተካፈሉ ፤ ልብሴን ፡ ለራሳቸው ፡ ተካፈሉ፤በቀሚሴም፡ላይ፡ዕጣ፡ተጣጣሉ፡ያለው፡የመጽሐፍ፡ቃል፡ይፈጸም፡ዘንድ።
፴፮፤ ከዚያም፡ተቀምጠው፡ይጠብቁት፡ነበር።
፴፯፤ ከራሱም ፡ በላይ ፡ ይህ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ **ኢየሱስ** ፡ ነው ፡ የሚል ፡ የበደሉን ፡ ጽሑፍ ፡ ጽፈው፡አኖሩ።
፴፰፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሁለት ፡ ወንበዴዎች ፡ አንዱን ፡ በቀኙ፡አንዱን፡በግራው፡ከእርሱ፡ጋር፡ሰቀሉ።
፴፱፤ የሚያልፉትም ፡ ራሳቸውን ፡ እየነቀነቁ ፡ ይሰድቡት፡ነበር።
፵፤ ቤተ፡መቅደስን፡የምታፈርሰው፡በሦስተኛው፡ቀን፡የምታንጸው፡አንተ፡ሆይ፤ራስህን፡አድን፤**የእግዚአብሔር፡ልጅስ**፡ከሆንክ፡እስኪ፡ከመስቀልህ፡ውረድ፡ይሉት፡ነበር።
፵፩፤ እንዲሁም ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ከጻፎችና ፡ ከሽማግሌዎች ፡ ጋር ፡ ይዘብቱበት ፡ ነበር ፤ እንዲህ፡እያሉ።
፵፪፤ ሌላውን ፡ ያድናል ፤ ራሱን ፡ ግን ፡ ማዳን ፡ አይችልም ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከሆነ ፡ እንግዲህ ፡ አሁን ፡ ከመስቀሉ ፡ ይውረድና ፡ አይተን፡እንመንበት።
፵፫፤ **በእግዚአብሔር** ፡ ከታመነ ፡ ይወደው ፡ እንደሆነ፡እነሆ፡አሁን፡ያድነው፤እኔ፡**የእግዚአብሔር፡ልጅ**፡ነኝ፡ይላልና።
፵፬፤ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የተሰቀሉ ፡ ወንበዴዎችም ፡ እንዲሁ፡ያሽሟጥጡት፡ነበር።
፵፭፤ ከስድስት፡ሰዓት፡ጀምሮ፡እስከ፡ዘጠኝ፡ሰዓት፡ዓለም፡ሁሉ፡ጨለማ፡ሆነ
**ካህኑ፡ዲያቆኑ፡ሕዝቡም**፡እንዳለፈው፡ይበሉ።
ስድስት ፡ ሰዓት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ **ጌታችን** ፡ **ኢየሱስን**፡ልብሱን፡አልብሰው፡ይሰቅሉት፡ዘንድ፡ወሰዱት።

Scanned by CamScanner

፳፻፫

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ይ፡ ካ፡ ቅዱስ፡ እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፡ ኃያል፡ ቅዱስ፡ ሕያው፡ ዘኢይመውት፡ ፫፡ጊዜ።

ወንጌል፡ዘማርቆስ።

ምዕ፲፭፡፲፮–፴፪።

፲፮፡ ወአብእዎ፡ ሐራ፡ ውሳጤ፡ ዐጸድ፡ ኀበ፡ ምኵናን፡ ወጸውዑ፡ ኵሎ፡ ሠገራተ፡ ሰጺራ።
፲፯፡ ወአልበስዎ፡ሜላተ፡ወፀፈሩ፡አክሊለ፡ዘሦክ፡ ወአስተቀጸልዎ፡ወይሣለቅዎ።
፲፰፡ ወይብልዎ፡በሐ፡ንጉሦሙ፡ለአይሁድ።
፲፱፡ ወይኰርዕዎ፡ርእሶ፡በኀለት፡ወይዌርቅዎ፡ወያስተበርኩ፡ወይሰግዱ፡ሎቱ።
፳፡ ወሶበ፡ተሣለቁ፡ላዕሌሁ፡ሰለብዎ፡ውእተ፡ሜላተ፡ወአልበስዎ፡አልባሲሁ፡ወወሰድዎ፡ ኀበ፡ይሰቅልዎ።
፳፩፡ ወዐበጡ፡አሐደ፡ኀላፌ፡ፍኖት፡እምኃለፍት፡ ስምዖንሃ፡ ቀሬናዌ፡ እትወቶ፡ እምሐቅል፡ አባሆሙ፡ለእለእስክንድሮስ፡ወለሮፎስ፡ከመ፡ ይጹር፡መስቀሎ።
፳፪፡ ወወሰድዎ፡ብሔረ፡ጎልጎታ፡ዘበትርጓሜሁ፡ ይብልዎ፡መካነ፡ቀራንዮ።
፳፫፡ ወወሀብዎ፡ ይስተይ፡ ወይነ፡ ምስለ፡ ከርቤ፡ ቱሱሐ፡ወአበየ፡ሰትየ።
፳፬፡ ወሰቀልዎ፡ ወተዓፀዉ፡ ዲበ፡ አልባሲሁ፡ ወተካፈሉ፡ዘከመ፡ይነሥኡ።
፳፭፡ ወሠለስቱ፡ሰዓት፡ውእቱ፡ጊዜ፡ይሰቅልዎ።
፳፮፡ ወይብል፡ መጽሐፈ፡ ጌጋዩ፡ ንጉሦሙ፡ ለአይሁድ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ነሀን፡ ቅዱስ፡ እግዚአብሔር፡ ቅዱስ፡ ኃያል፡ ቅዱስ፡ ሕያው፡ ዘኢይመውት፡ ሦስት፡ ጊዜ፡ ይበል።

የማርቆስ፡ወንጌል።

ምዕ፲፭፡፲፮–፴፪።

፲፮፡ ወታደሮችም፡ ወደ፡ ግቢ፡ ውስጥ፡ ወደ፡ ፍርድ፡ መቀበያው፡ አገቡት፤ ባለወንቹን፡ ጭፍሮች፡ ሁሉ፡ጠሩ።
፲፯፡ ነጭ፡ ሐርን፡ አለበሱት፤ የእሾህ፡ አክሊልም፡ ጕንጕነው፡ በራሱ፡ ላይ፡ ደፉበትና፡ ተዘባበቱበት።
፲፰፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ ሆይ፡ ሰላምታ፡ ይገባሃል፡ ይሉት፡ነበር።
፲፱፡ ራሱን፡ በዘንግ፡ ይመቱት፡ ይተፉበት፡ ተንበርክ ከውም፡ይሰግዱለት፡ነበር።
፳፡ በተዘባበቱበትም፡ ጊዜ፡ ያንን፡ ነጩን፡ ሐር፡ ገፈፉና፡ልብሱን፡አልብሰው፡ወደሚሰቅሉበት፡ ቦታ፡ወሰዱት።
፳፩፡ መስቀሉንም፡ ይሸከም፡ ዘንድ፡ የቀሬና፡ሰው፡ የሆነ፤ ከመንገደኞችም፡ አንድ፡ ስምዖን፡ የሚባል፡ መንገድ፡ አላፊ፡ ከበረኻ፡ ሲመለስ፡ ያዙት፤ እሱም፡ የእለእስክንድሮስና፡ የሮፎስ፡ አባት፡ነው።
፳፪፡ ትርጓሜው፡ የራስ፡ ቅል፡ ወደሚሉት፡ ወደ፡ ጎልጎታ፡ሥፍራ፡ወሰዱት።
፳፫፡ ከከርቤ፡ ጋር፡ የተቀላቀለ፡ ወይን፡ ሊጠጣ፡ ሰጡት፤መጠጣትን፡እንቢ፡አለ።
፳፬፡ እሱንም፡ ሰቀሉና፡ በልብሶቹ፡ ላይ፡ ዕጣ፡ ተጣጥለው፡እንደ፡ድርሻቸው፡ተካፈሉ።
፳፭፡ ሲሰቅሉትም፡ሦስት፡ሰዓት፡ነበር።
፳፮፡ የበደሉ፡ ደብዳቤም፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ነው፡ ይል፡ነበር።

ዘከመ ዐበጥዎ አይሁድ ለስምዖን ቀሬናዊ ይፁር መስቀሎ።



ቀሬናዊ ስምዖንን መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አይሁድ እንደመለሱት።

፳፯፡ ወሰቀሉ፡ ምስሌሁ፡ ክልኤተ፡ ፈያተ፡ አሐደ፡ በየማኑ፡ወአሐደ፡በፀጋሙ።
፳፰፡ ወተፈጸመ፡መጽሐፍ፡ዘይቤ፡ተኈለቈ፡ምስለ፡ ገበርተ፡ዐመፃ።
፳፱፡ ወኀለፍትኒ፡ ይፀርፉ፡ ላዕሌሁ፡ ወየሐውሱ፡ ርእሶሙ፡ ወይብልዎ፡ አ፡ ዘይነሥቶ፡ ለቤተ፡ መቅደስ፡ ወበሠሉስ፡ ዕለት፡የሐንጾ።
፴፡ አድኅን፡ርእሰከ፡ወረድ፡እመስቀልከ።

፳፯፡ ከእርሱ፡ጋር፡አንዱን፡በቀኙ፡አንዱን፡በግራው፡ ሁለት፡ወንበዴዎችን፡ሰቀሉ።
፳፰፡ መጽሐፍ፡ከዐመጸኞች፡ጋር፡ተቈጠረ፡ያለው፡ ተፈጸመ።
፳፱፡ መንገድ፡ተላላፊዎችም፡ይሰድቡት፡ነበር፤ራሳ ቸውንም፡እየነቀነቁ፡እንዴህ፡ይሉት፡ነበር፤ አወይ፡ቤተ፡መቅደስን፡አፍርሶ፡በሦስተኛው፡ ቀን፡የሚሠራው።
፴፡ ራስህን፡አድን፡ከመስቀልህም፡ውረድ።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፴፩ ወከማሁ፡ሊቃነ፡ካህናትኒ፡ወጸሐፍት፡ይሣለቁ፡
ላዕሌሁ፡ወይብልዎ፡ዘባዕደ፡ያድኅን፡ወርእሶ፡
ኢይክል፡አድኅኖ።
፴፪ ወእመሰ፡ክርስቶስ፡ውእቱ፡ንጉሠ፡እስራኤል፡
ለይረድኬ፡ይእዜ፡እምነ፡መስቀሉ፡ንርአይ፡
ወንእመን፡ቦቱ፡ወእለሂ፡ተሰቅሉ፡ምስሌሁ፡ይዘ
ነጉጉዎ።
፴፫ ወሶበ፡ኮነ፡ጊዜ፡ቀትር፡ጸልመ፡ፀሐይ፡
ወኮነ፡ዓለም፡ጸልመ፡እስከ፡ተሱዓት፡
ሰዓት።
ይካ፡ይዲ፡ይሕ፡ከመ፡ቀዳሚ።
ጊዜ፡ስድስቱ፡ሰዓት፡ቀትር፡ሶቤሃ፡
ሊቃነ፡ካህናት፡ሰቀልዎ፡ለኢየሱስ፡በቀ
ራንዮ፡መካን።
(ይካ)፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡
ኃያል፡ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡፫፡
ጊዜ፡በል።

## ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፡፳፫፡፳፯—፴፩።

፳፯ ወተለውዎ፡ብዙኃን፡ሕዝብ፡ወአንስትኒ፡
ይበክያሁ፡ወያስቈቅዋሁ።
፳፰ ወተመይጠ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ይቤሎን፡
አዋልደ፡ኢየሩሳሌም፡ኢትብክያኒ፡ኪያየሰ፡
አላ፡ብክያ፡ላዕለ፡ርእስክን፡ወላዕለ፡
ውሉድክን።
፳፱ እስመ፡ይመጽእ፡መዋዕል፡አመ፡ይብሉ፡
ብፁዓት፡መካናት፡ወከርሥኒ፡እንተ፡
ኢወለደት፡ወአጥባትኒ፡እለ፡ኢሐፀና።
፴ ወይእተ፡አሚረ፡ይብልዎሙ፡ለአድባር፡
ደቁ፡ላዕሌነ፡ወለአውግርኒ፡ድፍኑነ።
፴፩ በዝ፡ዕፀ፡ርጡብ፡ከመዝ፡ገብሩ፡እፎመ፡
በይቡስ፡ይከውን።
፴፪ ወወሰዱ፡ምስሌሁ፡ካልአነ፡ክልኤተ፡ፈያተ፡
ይሰቅሉ።
፴፫ ወበጺሖሙ፡ብሔረ፡ዘስሙ፡ቀራንዮ፡
በህየ፡ሰቀልዎ፡ወእልክተሂ፡ክልኤተ፡
ፈያተ፡አሐደ፡በየማኑ፡ወአሐደ፡በፀ
ጋሙ፡ሰቀሉ።
፴፬ ወይቤ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡አባ፡ሥረይ፡
ሎሙ፡እስመ፡በዘኢየአምሩ፡ይገብሩ።
ወተዐፀዉ፡ዲበ፡አልባሲሁ፡ወተካፈሉ።
፴፭ ወይቀውሙ፡ሕዝብ፡ወይሬእዩ፡ወይዘነ
ጉጕዎ፡መላእክትኒ፡ወይብልዎ፡ዘባዕደ

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፴፩ እንዲሁም፡የካህናት፡አለቆችና፡ጻፎችም፡ይዘብ
ቱበት፡ነበር፤ሌላውን፡የሚያድን፡ራሱን፡ግን፡
ማዳን፡የማይችል፡ይሉትም፡ነበር።
፴፪ እርሱ፡የእስራኤል፡ንጉሥ፡ክርስቶስ፡ከሆነ፡
እስኪ፡አሁን፡ከመስቀሉ፡ይውረድና፡አይተን፡
እንመንበት፡ይሉ፡ነበር፤አብረውት፡የተሰቀ
ሉትም፡ያሽሟጥጡት፡ነበር።
፴፫ ቀትርም፡በሆነ፡ጊዜ፡ፀሐይ፡ጨለመ፤
ዓለምም፡ሁሉ፡እስከ፡ዘጠኝ፡ሰዓት፡ድረስ፡
ጨለማ፡ሆነ።
ካህኑ፡ዲያቆኑ፡ሕዝቡ፡እንዳለፈው፡ይበሉ።
ስድስት፡ሰዓት፡በሆነ፡ጊዜ፡ያን፡ጊዜ፡ቀትር፡
ነበር፤የካህናት፡አለቆች፡ኢየሱስን፡በቀራንዮ፡
ሰቀሉት።
ካህኑ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ሦስት፡ጊዜ፡
ይበል።

## የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፫፡፳፯—፴፩።

፳፯ ብዙ፡ሰዎችም፡ተከተሉት፡ሴቶችም፡
ያዝኑለት፡ያለቅሱለትም፡ነበር።
፳፰ ጌታ፡ኢየሱስም፡መለስ፡ብሎ፡እንዲህ፡
አላቸው፤የኢየሩሳሌም፡ልጆች፡ለራሳ
ችሁና፡ለልጆቻችሁ፡አልቅሱ፡እንጂ፡ለእኔ፡
አታልቅሱልኝ።
፳፱ መካኖች፤ያልወለደች፡ማሕፀንና፡ያላሳደጉ፡
ጡቶች፤የተመሰገኑ፡ናቸው፡የሚሉበት፡
ወራት፡ይመጣልና።
፴ ያን፡ጊዜ፡ተራሮችን፡በላያችን፡ውደቁ፤ኮረ
ብቶችንም፡ተጫኑን፡ይሏቸዋል።
፴፩ በዚህ፡ርጥብ፡እንጨት፡እንዲህ፡ያደረጉ፡
በደረቁማ፡እንዴት፡ይሆን?
፴፪ ከእርሱም፡ጋር፡ሊሰቅሉ፡ሌሎች፡ሁለት፡
ወንበዴዎችን፡ወሰዱ።
፴፫ ቀራንዮ፡ወደሚባለው፡ቦታ፡በደረሱ፡ጊዜ፡
በዚያ፡ሰቀሉት፤እነዚያንም፡ሁለት፡ወንበ
ዴዎች፡አንዱን፡በቀኙ፡አንዱን፡በግራው፡
ሰቀሉ።
፴፬ ጌታ፡ኢየሱስም፡አባት፡ሆይ፡የማያውቁትን፡
ይሠራሉና፡ይቅር፡በላቸው፡አለ።
በልብሱም፡ላይ፡ዕጣ፡ተጣጣሉና፡ተካፈሉ።
፴፭ ሕዝቡም፡ቆመው፡ይመለከቱ፡ነበር፤የእግዚአ
አለቆችም፡ክርስቶስ፡ከሆነና፡የእግዚአ

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ያድኅን ፡ ርእሶ ፡ ለያድኅን ፡ እመሰ ፡ ክርስቶስ ፡
ውእቱ፡ወኅሩዩ፡ለእግዚአብሔር።
፴፮፡ ወይሣለቁ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሐራ ፡ ወይቀርቡ ፡
ወአምጽኡ፡ሎቱ፡ብሒአ፡ይስተይ።
፴፯፡ ወይቤልዎ፡እመሰ፡ንጉሦሙ፡አንተ፡ለአይሁድ፡
አድኅን፡ርእሰከ።
፴፰፡ ወጸሐፉ ፡ መጽሐፈ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወጽሕፈቱ ፡ በሮ
ማይስጥ ፡ ወበጽርእ ፡ ወበዕብራይስጥ ፡ ዘይብል ፡
ዝንቱ፡ውእቱ፡ንጉሦሙ፡ለአይሁድ።
፴፱፡ ወአሐዱ፡ፈያታዊ፡እምእለ፡ተሰቅሉ፡ምስሌሁ፡
ፀረፈ ፡ ወይቤሎ ፡ ለእመ ፡ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡
አድኅን፡ርእሰከ፡ወኪያነሂ።
፵፡ ወአውሥአ ፡ ካልኡ ፡ ወገሠጾ ፡ ወይቤሎ ፡ ኢትፈ
ርሆኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ አንተሰ ፡
ወአነ፡እንዘ፡ውስተ፡ዝንቱ፡ኲነኔ፡ሀለውነ።
፵፩፡ ወለነሰ፡ዘበርቱዕ፡ረከበነ፡ዘይደልወነ፡ወበከመ፡
ምግባሪነ ፡ ተፈደይነ ። ወዝንቱሰ ፡ አልቦ ፡ እኩየ ፡
ዘገብረ።
፵፪፡ ወይቤሎ፡ ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ተዘከረኒ፡ እግዚኦ፡
አመ፡ትመጽእ፡በመንግሥትከ።

ብሔር፡ምርጥ፡ልጅ፡ከሆነ፡ሌሎችን፡የሚያድን፡
ራሱን፡ያድን፡እያሉ፡ያፌዙበት፡ነበር።
፴፮፡ ጭፍሮችም ፡ ቀርበው ፡ ይዘብቱበት ፡ ነበር ፡
ይጠጣም፡ዘንድ፡መፃፃ፡አመጡለት።
፴፯፡ የአይሁድ ፡ ንጉሣቸው ፡ አንተ ፡ ከሆንክስ ፡
ራስህን፡አድን፡ይሉት፡ነበር።
፴፰፡ በላዩም፡ላይ፡ደብዳቤ፡ጻፉ፤ጽሕፈቱም፡በሮማ
ይስጥ፡በጽርዕና፡በዕብራይስጥ፡ሆኖ፡የአይሁድ፡
ንጉሣቸው፡ይህ፡ነው፡የሚል፡ነበር።
፴፱፡ አብረውት ፡ ተሰቅለው ፡ ከነበሩት ፡ አንዱ ፡
ወንበዴ ፡ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሆንክ ፡ ራስህን ፡
አድን፤እኛንም፡አድነን፡ብሎ፡ተሳደበ።
፵፡ ሁለተኛውም ፡ መለሰና ፡ አንተና ፡ እኔ ፡ በዚህ ፡
ፍርድ፡ውስጥ፡ሳለን፡ ፈጣሪህ፡እግዚአብሔርን፡
አትፈራውምን፡ብሎ፡ገሠፀው።
፵፩፡ ለእኛስ፡በእውነት፡ያገኘን፡በሚገባን፡ነው፤እን
ደሥራችንም፡ፍዳችንን፡ተቀበልን፤እርሱ፡ግን፡
ምንም፡ምን፡የሠራው፡ክፉ፡ሥራ፡የለም።
፵፪፡ ጌታ ፡ ኢየሱስንም ፡ አቤቱ ፡ በመንግሥትህ ፡
በመጣህ፡ጊዜ፡አስበኝ፡አለው።



ዘከመ አጸርዎ አይሁድ መስቀለ ለእግዚእነ::

አይሁድ ጌታችንን መስቀልን እንዳሸከሙት::

፵፫፡ ወአውሥአ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡ወይቤሎ፡አማን፡
እብለከ፡እመን፡ፈድፋደ፡ከመ፡ዮም፡ምስሌየ፡
ትሄሉ፡ውስተ፡ገነት።
፵፬፡ ወቀትር ፡ ጊዜ ፡ ስሱ ፡ ሰዓት ፡ ሞተ ፡
ፀሐይ ፡ ወጸልመ ፡ ዓለም ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ተሱ
ዐት፡ሰዓት

ይካ፡ይዲ፡ይሕ፡ከመ፡ቀዳሚ።
ጊዜ፡ስድስቱ፡ሰዓት፡አበጥዎ፡ለስምዖን፡ከመ፡
ይፁር፡መስቀሎ።
ይ፡ካ፡ቅዱስ፡ እግዚአብሔር ፡ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡፲፡ጊዜ፡በል።

ወንጌል፡ዘዮሐንስ።
ምዕ፡፲፱፡፲፫–፳፯።
፲፫፡ ወሰሚዖ፡ጲላጦስ፡ዘንተ፡ነገረ፡አውጽኦ፡
ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡አፍአ፡ወነበረ፡ዲበ፡
መንበር፡ውስተ፡መካን፡ዘስሙ፡ሊቶስጥሮስ፡
ወበዕብራይስጥ፡ይብልዎ፡ገበታ።

፵፫፡ ጌታ፡ኢየሱስም፡መልሶ፡እውነት፡እልሃለሁ፡
ዛሬ፡በገነት፡አብረኸኝ፡እንደምትሆን፡ፈጽመህ፡
እመን፡አለው።
፵፬፡ ቀትር፡በሆነ፡ጊዜም፡በስድስት፡ሰዓት፡ፀሐይ፡
ጠፋ፤እስከ፡ዘጠኝ፡ሰዓት፡ድረስም፡ዓለም፡ሁሉ፡
ጨለማ፡ሆነ።
ካህኑ፡ዲያቆኑ፡ሕዝቡ፡እንዳለፈው፡ይበሉ።
ስድስት ፡ ሰዓት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ መስቀሉን ፡
ይሸከም፡ዘንድ፡ስምዖንን፡አስገደዱት።
ካህኑ፡ቅዱስ፡ እግዚአብሔር ፡ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ይበል፡፲፡ጊዜ።

የዮሐንስ፡ወንጌል።
ምዕ፡፲፱፡፲፫–፳፯።
፲፫፡ ጲላጦስም፡ይህን፡ነገር፡ሰምቶ፡ጌታ፡ኢየሱስን፡
ወደ፡ውጭ፡አወጣው፤ሊቶስጥሮስ፡በሚባለው፡
በዕብራይስጥም፡ገበታ፡ተብሎ፡በሚጠራው፡
ቦታ፡ላይ፡በወንበር፡ተቀመጠ።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።


፲፬ ወዐርበ፡ፋሲካ፡ውእቱ፡ጊዜ፡ቀትር፡ዘስሱ፡
ሰዓት፡ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ለአይሁድ፡ነዋ፡
ንጉሥክሙ፡ ወከልሑ፡ ወይቤሉ፡ አእትቶ፡
ወስቅሎ።
፲፭ ወይቤሎሙ፡ጲላጦስ፡ለንጉሥክሙኑ፡እስቅሎ፡
ወአውሥኡ፡ሊቃነ፡ካህናት፡ወይቤሉ፡አልብነ፡
ንጉሥ፡ዘእንበለ፡ቄሳር።
፲፮ ወእምዝ፡ወሀቦሙ፡ይስቅልዎ፡ወተመጠውዎ፡
ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወአውጽእዎ፡አፍአ።
፲፯ ወወሰድዎ፡እንዘ፡ይጸውር፡መስቀሎ፡ውስተ፡
መካን፡ዘስሙ፡ቀራንዮ።
፲፰ ወበዕብራይስጥ፡ ይብልዎ፡ ጎልጎታ፡ ኀበ፡
ሰቀልዎ፡ወሰቀሉ፡ምስሌሁ፡ካልአነ፡ክልኤተ፡
ፈያተ፡አሐደ፡እምለፌ፡ወአሐደ፡እምለፌ፡ወማ
እከሎሙ፡ኢየሱስሃ።

፲፱ ወጸሐፈ፡ጲላጦስ፡መጽሐፈ፡ወአንበረ፡ዲበ፡
መስቀሉ፡ወይብል፡መጽሐፉ፡ኢየሱስ፡ናዝራዊ፡
ንጉሦሙ፡ለአይሁድ፡ውእቱ፡ዝንቱ።
፳ ወብዙኃን፡እምነ፡አይሁድ፡እለ፡አንበብዋ፡
ለይእቲ፡መጽሐፍ፡እስመ፡ቅሩብ፡ውእቱ፡
መካን፡ለሀገር፡ ኀበ፡ ሰቀልዎ፡ ለእግዚእ፡
ኢየሱስ፡ወጽሒፈቱ፡ጽሑፍ፡ውእቱ፡በዕብራ
ይስጥ፡ወበሮማይስጥ፡ወበጽርእ።
፳፩ ወይቤልዎ፡ ለጲላጦስ፡ ሊቃነ፡ ካህናት፡
ኢትጽሐፍ፡ከመ፡ውእቱ፡ንጉሠ፡አይሁድ፡አላ፡
ለሊሁ፡ይቤ፡ንጉሦሙ፡ለአይሁድ፡አነ።
፳፪ ወአውሥአ፡ጲላጦስ፡ወይቤሎሙ፡ዘጸሐፍኩ፡
ጸሐፍኩ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት። ፫፻፹፫

፲፬፡ ፋሲካም፡ደረሰ፤ ጊዜውም፡ቀትር፡ስድስት፡
ሰዓት፡ ያህል፡ ነበር፤ ጲላጦስም፡ አይሁድን፡
ንጉሣችሁ፡ ይኸው፡ አላቸው፤ እነርሱም፡
ስቀለው፡ግደለው፡እያሉ፡ጮኹ።
፲፭፡ ጲላጦስም፡ንጉሣችሁን፡ልስቀለውን?አላቸው፤
የካህናት፡አለቆችም፡ከቄሣር፡በቀር፡ንጉሥ፡
የለንም፡ብለው፡መለሱ።
፲፮፡ ከዚህ፡በኋላ፡ሊሰቅሉት፡ሰጣቸው፤ ጌታ፡ኢየሱ
ስንም፡ተቀብለው፡ወደ፡ውጭ፡አወጡት።
፲፯፡ መስቀሉንም፡ እንደተሸከመ፡ ቀራንዮ፡
ወደሚባል፡ቦታ፡ወሰዱት።
፲፰፡ የሰቀሉበትንም፡ቦታ፡በዕብራይስጥ፡ጎልጎታ፡
ይሉታል፤ ከእርሱ፡ ጋር፡ አንዱን፡ በወዲህ፡
አንዱን፡በወዲያ፡አድርገው፡ሌሎች፡ሁለት፡
ወንበዴዎችን፡ ሰቀሉ፤ ኢየሱስንም፡ በመካከ
ላቸው።
፲፱፡ ጲላጦስም፡ ደብዳቤ፡ ጽፎ፡ በመስቀሉ፡ ላይ፡
አኖረ፤ደብዳቤውም፡ይህ፡የአይሁድ፡ንጉሣቸው፡
የናዝሬቱ፡ ኢየሱስ፡ነው፡ይል፡ነበር።
፳፡ ይህቺንም፡ መጽሐፍ፡ ከአይሁድ፡ ያነ
በቧት፡ ብዙዎች፡ ናቸው፤ ጌታ፡ ኢየሱስን፡
የሰቀሉበት፡ ቦታ፡ ለከተማ፡ ቅርብ፡ ነበርና፤
ጽሕፈቱም፡ በዕብራይስጥ፡ በሮማይስጥና፡
በጽርእ፡ነበር።
፳፩፡ የካህናት፡አለቆችም፡ጲላጦስን፡እርሱ፡ራሱ፡
እኔ፡ የአይሁድ፡ ንጉሥ፡ ነኝ፡ እንዳለ፡ እንጂ፡
የአይሁድ፡ንጉሥ፡ነው፡ብለህ፡አትጻፍ፡አሉት።
፳፪፡ ጲላጦስም፡ የጻፍኩትን፡ ጻፍኩ፡ ብሎ፡ መለሰ
ላቸው።

ዘከመ ሰቀልዎ አይሁድ ለእግዚእነ፡፡





አይሁድ ጌታችንን እንደሰቀሉት፡፡

፳፫ ወሐራስ፡ሶበ፡ሰቀልዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡
ነሥኡ፡አልባሲሁ፡ወረሰይዎን፡አርባዕተ፡
ክፍለ፡ለለአሐዱ፡እምሐራ፡ወክዳኖሂ፡እልታሃ፡
ዘአልቦ፡ ርፍእት፡ ዘእምላዕሉ፡ እኑም፡
ዡለንታሁ።
፳፬ ወተበሀሉ፡ በበይናቲሆሙ፡ ኢንግምድ፡
ወኢንሥጥጥ፡አላ፡ንትፋሰስ፡ዘለረከቦ፡ይር
ከቦ፤ከመ፡ይብጻሕ፡ቃለ፡መጽሐፍ፡ዘይቤ፡
ተካፈሉ፡አልባስየ፡ለርእሶሙ፡ወተዓፀዉ፡ዲበ፡
ዐራዝየ፡ወከመዝ፡ገብሩ፡ሐራ።

፳፫፡ ጭፍሮች፡ግን፡ ጌታ፡ኢየሱስን፡በሰቀሉት፡
ጊዜ፡ ልብሱን፡ ወስደው፡ ለእያንዳንዱ፡
አራት፡ክፍል፡አደረጉት፤ ስፌት፡የሌለበት፡
ሥረ፡ወጥ፡የሆነ፡ቀሚሱንም፡አንድ፡ወገን፡
አደረጉ።
፳፬፡ እርስ፡በርሳቸው፡ዕጣ፡እንጣጣልና፡ለደረሰው፡
ይድረሰው፡ እንጂ፡ አንቅደደው፡ ተባባሉ፤
ልብሶቼን፡ለራሳቸው፡ተካፈሉ፡በቀሚሴም፡
ላይ፡ዕጣ፡ተጣጣሉ፡ያለው፡የመጽሐፍ፡ቃል፡
ይደርስ፡ዘንድ፡ጭፍሮች፡እንዲህ፡አደረጉ።

Scanned by CamScanner

## በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፭ ወይቀውማ፡ኀበ፡መስቀሉ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ እሙ ፡ ወእኅታ ፡ ለእሙ ፡ ወማርያም ፡ እንተ ፡ ቀለዮጳ፡ወማርያም፡መግደላዊት።

፳፮ ወሶበ ፡ ርእዮሙ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ለእሙ ፡ ወለረድኡ፡ዘያፈቅር፡እንዘ፡ይቀውሙ፡ይቤላ፡ ለእሙ፡ብእሲቶ፡ነዋ፡ወልድኪ።

፳፯ ወይቤሎ ፡ ለውእቱኒ ፡ ረድእ ፡ ነያ ፡ እምከ ፤ ወእምይእቲ ፡ ሰዓት ፡ ነሥኣ ፡ ውእቱ ፡ ረድእ ፡ ወአእተዋ፡ቤቶ።

ጊዜ ፡ ስድስቱ ፡ ሰዓት ፡ ሰቀልዎ ፡ ለኢየሱስ ፡ ማእከለ፡ክልኤ፡ፈያት።

ይ ፡ ካ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ኃያል ፡ ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡፫፡ጊዜ፡በል።

ድኅረ ፡ ወንጌል ፡ በስድስቱ ፡ ሰዓት ፡ መዓልት ፡ ዘዓርብ።

፩ እ ፡ ዠልክሙ ፡ እለ ፡ ትነብሩ ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ንዑ ፡ ርእዩ ፡ ኀበ ፡ ዛቲ ፡ ራእይ ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ ፡ አይሁድ ፡ አዕረግዎ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወልደ ፡ ዳዊት ፡ ከመ ፡ ይስቅልዎ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ አልበስዎ ፡ ልብሰ ፡ ቀይሐ ፡ ልብሰ ፡ ነገሥት ፡ ዐቢይ፡ ወአክሊለ፡ሦክ፡ዲበ፡ርእሱ።

፪ እ ፡ ለዘአሰርጋዌ ፡ ሰማያት ፡ በስነ ፡ ከዋክብት ፡ ሣራሪሃ፡ለምድር፡በመንፈሰ፡አፉሁ፡ወሠራዒሃ፡ በሥነ፡ጽጌያት፡ረሰዩ፡ኅለተ፡ውስተ፡የማኑ።

፫ ጥበበ ፡ መምህራን ፡ ወጸሐፍት ፡ አልዐለ ፡ መስቀለ ፡ ድኅሬሁ ፡ ከመ ፡ ንጉሥ ፡ መዋኢ ፡ በውስተ፡ጸብእ።

፬ ወሶበ፡ርእያ፡አንስት፡እለ፡መጽአ፡ኀበ፡በዓለ፡ ፋሲካ፡ላሐዋ፡ወበከያ፡በእንተ፡ዘኮነ።

፭ ወተመይጠ ፡ ኀቤሆን ፡ ወይቤ ፡ ከመዝ ፡ እ ፡ ዠልክን ፡ አዋልደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኢትብክያ ፡ ላዕሌየ፡አላ፡ብክያ፡ላዕሌክን፡በእንተ፡ምንዳቤ፡ ዐቢይ፡ዘይረክበክን፡ወሁከተ፡ብዙኅ፡ተአምራ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፳፭ በጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ በመስቀሉ ፡ አጠገብ ፡ እናቱ ፡ የእናቱ ፡ እኅት ፡ የቀለዮጳይቱ ፡ ማርያምና ፡ ማርያም፡መግደላዊት፡ቆመው፡ነበር።

፳፮ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ እናቱንና ፡ የሚወደውን ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ቆመው ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ እናቱን ፡ አንቺ፡ሆይ፡እነሆ፡ልጅሽ፤አላት።

፳፯ ያን ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩንም ፡ እናትህ ፡ እነኋት ፡ አለው፤ ከዚያች ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ ያ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር፡ተቀብሎ፡ወደ፡ቤቱ፡ወሰዳት።

ስድስት፡ሰዓት፡በሆነ፡ጊዜ፡የካህናት፡አለቆች፡ጌታ፡ ኢየሱስን፡በሁለት፡ወንበዴዎች፡መካከል፡ሰቀሉት፤ ካህኑ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡ቅዱስ፡ ሕያው፡ዘኢይመውት፡ሦስት፡ጊዜ፡ይበል።

ዓርብ ፡ መዓልት ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ከወንጌል ፡ በኋላ፡የሚነበብ።

፩ እናንተ፡በኢየሩሳሌም፡የምትኖሩ፡ሁላችሁ፡እነርሳቸው ፡ አይሁድ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስን፡ በዕንጨት ፡ መስቀል ፡ ይሰቅሉት ፡ ዘንድ፡የመንግሥት፡ልብስ፡ታላቅ፡ቀይ፡ግምጃ፡ አልብሰው ፡ በራሱም ፡ ላይ ፡ ከእሾኽ ፡ የተሠራ ፡ ዘውድ ፡ ደፍተው ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ እንዳወጡት ፡ ታዩ፡ዘንድ፡ወደዚህች፡ቦታ፡ኑ።

፪ ሰማይን ፡ በከዋክብት ፡ የሸለመ ፡ ምድርንም ፡ በሥልጣኑ፡የፈጠረ፡በአበቦችም፡ያስጌጠ፡እርሱን፡ ለመዘባበቻ፡በቀኝ፡እጁ፡በትር፡አስያዙት።

፫ የመምህራንና፡የጥበበኞች፡ዕውቀት፡የሚሆን፡ እርሱ፡እንደ፡ድል፡አድራጊ፡ንጉሥ፡በሰልፍ፡ ውስጥ፡መስቀሉን፡በኋላው፡ከፍ፡ከፍ፡አደረገ።

፬ ለፋሲካው ፡ በዓል ፡ የመጡ ፡ ሴቶች ፡ የሆነውን ፡ ባዩ፡ጊዜ፡ፈጽመው፡አለቀሱ።

፭ ወደርሳቸውም፡ተመልሶ፡እናንተ፡የኢየሩሳሌም፡ቆነጃጅት ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ አታልቅሱ፤ስለሚመጣው፡ታላቅ፡መከራና፡ስለሚያገኛችሁ፡ስለ፡ራሳችሁ፡ አልቅሱ፡እንጂ፤ብዙ፡ሁከትንም፡ታውቃላችሁ።

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፯ እምድኅረ፡ንስቲት፡ዘመን፡ናሁ፡ይመጽእ፡
ላዕሌክን፡መዋዕል፡ዘታስተበፅዓ፡ከርሥን፡
ለመካናት፡እለ፡ኢፀንሳ፡ወኢወለዳ፡
ወኢሐፀና፡ወኢያጥበዋ፡አጥባተ።
፰ ወትብላሆሙ፡ለአድባር፡ይደቁ፡ላዕሌክን፡
ወለአውግርኒ፡ይክድኑክን።
፱ ለእመ፡ገብሩ፡ዘንተ፡በዕፀ፡ርጡብ፡
ወምንተኑ፡ይገብሩ፡በይቡስ።
፲ ወሶበ፡ወሰድዎ፡ኀበ፡ቀራንዮ፡ዘውእቱ፡
ጎልጎታ፡አቀሙ፡ዕፀ፡መስቀል፡ወሰቀልዎ፡
ላዕሌሁ፡ሶቤሃ፡በከመ፡ሥርዓት።
፲፩ ወሰቀሉ፡ምስሌሁ፡ገባርያነ፡እከይ፡
ሀየ፡አሐደ፡በየማኑ፡ወአሐደ፡በፀጋሙ፡
ከመ፡ይትፈጸም፡ቃለ፡ነቢይ፡እስመ፡
ውእቶሙ፡ኖለቁዎ፡ምስለ፡ጊጉያን፡
ወሰብእ፡አብዳን።
፲፪ ወነሥኡ፡ሐራ፡አልባሲሁ፡ወጸሐፉ፡ግብሮ፡
ዲበ፡ርእሱ፡ወተዓፀዉ፡ሊቃነ፡ካህናት፡
ላዕሌሆሙ፡ወከፈልዎሙ፡ኀበ፡አርባዕቱ፡
ክፍል
፲፫ ወጸሐፉ፡ከመዝ፡መልዕልተ፡ርእሱ፡
ወተጽሕፈ፡በዕብራይስጥ፡ወተጽሕፈ፡
በጽርእ፡ወተጽሕፈ፡በሮማይስጥ፡ከመ፡
ውእቱ፡ንጉሠ፡አይሁድ።
፲፬ ወናሁ፡ኵሉ፡ሕዝብ፡ኮኑ፡ቀዋምያን፡
ወሊቃናት፡ወመኳንንት።
፲፭ ወኮኑ፡ይሣለቅዎ፡ዘእንበለ፡ፍርሀት፡
ወየሐውሱ፡አርእስቲሆሙ፡ከመ፡ዝ፡እንዘ፡
ይብሉ፡እስመ፡ውእቱ፡አድኃነ፡ባዕዳነ፡
ወከማሁ፡ለያድኅን፡ነፍሶ፡ለእመ፡ኮነ፡
ውእቱ፡ክርስቶስ፡ወልዱ፡ለቡሩክ።
፲፮ ወሐራኒ፡ካልአን፡ኮኑ፡ይሣለቅዎ፡ወይፀርፉ፡
ላዕሌሁ፡ዘልፈ።
፲፯ እመሰ፡ኮንከ፡አንተ፡ውእቱ፡ክርስቶስ፡
ንጉሠ፡አይሁድ፡ረድ፡እመስቀልከ።
፲፰ ወአሐዱ፡እምገባርያነ፡እከይ፡ዘተሰቅለ፡
ምስሌሁ፡ኮነ፡ይፀርፍ፡በቅድመ፡ኵሉ፡
ሰብእ፡ወይብል፡ለእመ፡ኮንከ፡አንተ፡
ክርስቶስ፡አድኅን፡ነፍሰከ፡ወአድኅነነ፡እም
ኀፍረት፡ዘንህነ፡ውስቴቱ።
፲፱ ገሠፆ፡ካልኡ፡ወይቤ፡ኢትፈርሆኑ፡አንተ፡እም
እግዚአብሔር፡በእንተ፡ጌጋይነ፡ወደቅነ፡



ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

፯፤ ከጥቂት፡ዘመናት፡በኋላ፡ያልፀነሱና፡
ያልወለዱ፤አጥብተው፡ያላሰደጉ፡ጡቶችንም፡
የመካኖችን፡ማኅፀን፡የምታመሰግኑበት፡
ወራት፡እነሆ፡ይመጣል።
፰፤ ተራሮችን፡በላያችን፡ይውደቁብን፡ኮረብቶ
ችንም፡ይጫኑን፡ትሏቸዋላችሁ።
፱፤ በዚህ፡በርጥቡ፡እንዲህ፡ካደረጉ፤በደረቁማ፡
ምን፡ያደርጉ፡ይሆን?
፲፤ ወደቀራንዮም፡በወሰዱት፡ጊዜ፡ይኸውም፡
ጎልጎታ፡ነው፤መስቀል፡አቁመው፡እንደ፡
ሕጋቸው፡በላዩ፡ሰቀሉት።
፲፩፤ በነቢይ፡ከበደለኞች፡ጋራ፡ተቈጠረ፡
የተባለው፡ይፈጸም፡ዘንድ፡ከእርሱ፡ጋራም፡
ክፉ፡አድራጊዎችን፡አንዱን፡በቀኙ፡
አንዱን፡በግራው፡ሰቀሉ፤እነሱ፡ከበደለ
ኞችና፡ከሰነፎች፡ጋራ፡ቈጥረውታልና።
፲፪፤ ጭፍሮችም፡ልብሶቹን፡ወሰዱ፤ሥራውንም፡
ጽፈው፡በራሱ፡ላይ፡አኖሩ፤የካህናት፡
አለቆችም፡በልብሶቹ፡ላይ፡ዕጣ፡ተጣጣሉ
ባቸው፤ወደ፡አራት፡ክፍልም፡ከፈሉት።
፲፫፤ እንደዚህም፡የአይሁድ፡ንጉሥ፡እንደሆነ፡
በዕብራይስጥና፡በጽርእ፡በሮማይስጥ፡
ጽፈው፡ከራሱ፡በላይ፡ከትራፊ፡መስቀሉ፡
አኖሩ።
፲፬፤ እነሆ፡ሕዝቡ፡አለቆችና፡መኳንንት፡ሁሉ፡
ቁመው፡ነበር።
፲፭፤ ያለፍርሃትም፡ራሳቸውን፡እየነቀነቁ፡
ሌሎችን፡አዳነ፤የተመሰገነ፡ቡሩክ፡የእ
ግዚአብሔር፡ልጅ፡ክርስቶስ፡እርሱ፡
ከሆነ፡ራሱንም፡ያድን፡እያሉ፡ይሣለ
ቁበት፡ነበር።
፲፮፤ ሌሎችም፡ጭፍሮች፡እንደዚሁ፡ይዘብቱ
በትና፡ይሰድቡት፡ነበር።
፲፯፤ አንተ፡የአይሁድ፡ንጉሥ፡ክርስቶስ፡ከሆንክ፡
ከመስቀልህ፡ውረድ፡እያሉ፡ተሳደቡ።
፲፰፤ ከእርሱ፡ጋራ፡ከተሰቀሉት፡ከክፉ፡
አድራጊዎች፡አንዱ፡አንተ፡ክር
ስቶስ፡ከሆንክ፤ራስህን፡አድን፡እኛ
ንም፡ካለንበት፡ውርደት፡አድነን፡እያለ፡
ተሳደበ።
፲፱፤ ባልንጀራውም፡እግዚአብሔርን፡አትፈራምን፡
እኛንስ፡ስለበደላችን፡ይህ፡ፍርድ፡አገኘ

Scanned by CamScanner

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ውስተ፡ዝንቱ፡ፍትሕ፡ወዛቲ፡ኮነኔ፡እንተ፡
ውስተ፡ዝንቱ፡ፍትሕ፡ወዛቲ፡ኮነኔ፡እንተ፡ዘይ
ንህነ፡ውስቴታ።

፲፱፡ ወዝንቱሰ ፡ ኢገብረ ፡ ምንተኒ ፡ ዘይ
ደልዎ፡ከማነ፡ወውእቱ፡ዘእንበለ፡እከይ፡
ወዐመፃ።

፳፡ ወከሠተ፡አፉሁ፡ወይቤ፡ተዘከረኒ፡**እግዚኦ፡**
በውስተ፡መንግሥትከ።

፳፩፡ ወሰምዖ ፡ **እግዚእ ፡ ሰብሐት ፡** ወተናገረ ፡
ምስሌሁ፡ከመ፡ዕጓለ፡እመሕያው።

፳፪፡ ወይቤሎ፡አንሰ፡እብለከ፡ዮም፡ትከውን፡
ምስሌየ፡ውስተ፡ገነት፡ትፍሥሕት።

፳፫፡ ወአንስት፡እለ፡ይቀውማ፡ኀበ፡መስቀሉ፡**ለእ
ግዚእነ፡ወመድኃኒነ፡** እንተ፡ይእቲ፡እሙ፡
ወእኅታ፡ለእሙ፡ማርያም፡እንተ፡ቀለዮጳ፡
ወማርያም፡መግደላዊት።

፳፬፡ **ወእግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡** ሶበ ፡ ርእየ ፡ ኀበ ፡
እሙ፡ወኀበ፡ካልእ፡ረድኡ፡ዘኮነ፡ያፈቅሮ፡
ቀጸበ፡ኀቤሃ፡ወይቤላ፡አ፡ብእሲቶ፡ናሁ፡
ወልድኪ፡ወይቤሎ፡ለረድኡኒ፡አ፡ብእሲ፡
ናሁ፡እምከ።

፳፭፡ ወእምይእቲ ፡ ሰዓት ፡ ነሥአ ፡ ረድእ ፡
ኀበ ፡ ቤቱ፡ በከመ ፡ **ቃለ ፡ እግዚአ
ብሔር።**

፳፮፡ ወእምጊዜ፡ስድስቱ፡ሰዓት፡እስከ፡ጊዜ፡ተስዐቱ፡
ሰዓት፡ኮነ፡ጽልመት፡ላዕለ፡ኵላ፡ምድር።

፳፯፡ አ፡ዘአሰርጎካ፡ለምድር፡በሥነ፡ጽጌያት፡
ወለፋሌከ፡በብዝኀ፡ከዋክብት፡አልበሱከ፡
ልብሰ፡ቀይሐ፡ወአንበሩ፡ላዕሌከ፡አክሊለ፡
እምሦክ።

፳፰፡ ሰማይ፡ወምድር፡ዘሀለዉ፡ውስተ፡እራኀከ፡
አንበሩ፡ውስተ፡እዴከ፡ኀለተ።

፳፱፡ ደለዎከ፡ኵላ፡ምድረ፡በቀለ፡አፉከ፡ሰቀሉከ፡
ዲበ፡ዕፅ፡በእንተ፡ኀጣውኢነ፡ለጽንዐ፡ሞት፡
አፅራዕካሁ፡**ኦ፡እግዚእነ፡** በመስቀልከ።

፴፡ አ ፡ ለእድ ፡ ጽንዕት ፡ ሶበ ፡ ርእየ ፡ ሰይ
ጣን፡ተደልዎ፡መስቀልከ፡በዲበ፡ምድር፡
ምህወት ፡ ኃይሉ ፡ ወኀለፈት ፡ ጽንዑ ፡
ወፀርዐት ፡ ሥልጣኑ ፡ ወጠፍአ ፡ መና
ግንቲሁ፡
**ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡** መጽአ፡ወሐመ፡በእን
ቲአነ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ።

ትእዛዝ።

ወእምድኅረዝ ፡ ይበሉ ፡ **እግዚእ ፡** መሐረነ ፡
**ክርስቶስ፡** አርብዓ፡ወአሐደ፡ጊዜ፡በዜማ፡ማሕዘኒ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

ቶናል ፤ አሁን ፡ በውስጥዋ ፡ ያለንባት ፡ ፍርድ፡
የምትገባን፡ናት፡ብሎ፡ገሠፀው።

፲፱፡ እርሱ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ የሚያስቀጣው፡
ምንም፡ምን፡አልሠራም ፤ ያለክፋትና፡ያለ፡
ዐመፅ፡ነው።

፳፡ አፉንም ፡ ከፍቶ ፡ **አቤቱ ፡** በጌትነትህ፡
በመጣህ፡ጊዜ፡አስበኝ፡አለ።

፳፩፡ **የክብር ፡ ባለቤት ፡ ጌታም ፡** ሰማው ፤ የሰው፡
ልጅ፡እንደመሆኑ፡ከእርሱ፡ጋራ፡ተነጋገረ።

፳፪፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ባለባት ፡ ገነት ፡ ዛሬ ፡ ከእኔ፡
ጋራ፡እንድትሆን፡እኔ፡እነግርሃለሁ፡አለው።

፳፫፡ ሴቶችም ፡ **በጌታችንና ፡ በመድኃኒታችን ፡**
መስቀል፡አጠገብ፡ቁመው፡ነበር፤እነርሱም፡
እናቱና ፡ እኅቷ ፡ ሰሎሜ ፡ የቀለዮጳ ፡ ሚስት፡
ማርያምና፡ማርያም፡መግደላዊት፡ነበሩ።

፳፬፡ **ጌታችን ፡ ክርስቶስም ፡** ወደ ፡ እናቱና ፡ ወደሚ
ወደው ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ፡
ጠቀሳት ፤ አንቺ፡ሆይ፡እነሆ፡ልጅሽ! አላት፤
ደቀ ፡ መዝሙሩንም ፡ አንተ ፡ ሆይ ፡ እናትህ፡
እነኋት፡አለው።

፳፭፡ ከዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ ያ ፡ ደቀ፡
መዝሙር፡እንደ፡**እግዚአብሔር፡ቃል፡** ወደ፡
ቤቱ፡ወሰዳት።

፳፮፡ ከስድስት ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ፡
ሰዓት፡በምድር፡ሁሉ፡ጨለማ፡ሆነ።

፳፯፡ ምድርን ፡ በአበባ ፡ ሰማይን ፡ በብዙ ፡
ከዋክብት፡ ያስጌጥክ ፡ ሆይ ፡ ቀይ ፡ ግምጃ፡
አለበሱህ ፤ በራስህም ፡ ላይ ፡ የእሾኽ ፡ ዘውድ፡
ደፋብህ።

፳፰፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ በመዳፍህ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ፡
ሲሆን፡በእጅህ፡በትር፡አስያዙህ።

፳፱፡ መላዋን ፡ ምድር ፡ ከአፍህ ፡ በሚወጣ ፡ ቃል፡
የመዘንክ ፡ አንተን ፡ ስለ ፡ ኃጢአታችን ፡
በዕንጨት፡ላይ፡ሰቀሉህ፡**ጌታችን፡ሆይ፡** በመ
ስቀልህ፡የሞትን፡ጽናት፡አጠፋህ።

፴፡ ለጸናችው፡ሥልጣን፡ወዮ፡አንክሮ፡ይገባል፤
የመስቀልህን ፡ መዘጋጀት ፡ በምድር ፡ ላይ፡
ሰይጣን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ሥልጣኑ ፡ ጠፋች፤
ቀለጠች፤ብርታቱም፡ኃይሉም፡ወጥመዱም፡
አለፈች፤ተቋረጠች።
**መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡** ሰው፡ሁኖ፡ስለ፡እኛ፡
መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ትእዛዝ።

ከዚህ፡በኋላ፡**አቤቱ፡ክርስቶስ፡** ማረን፤አርባ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ በሚያሳዝን ፡ ዜማ ፡ ይበሉ፡

Scanned by CamScanner

በ፰፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ዘውእቱ፡ዕዝል።
ወእምዝ ፡ ይንበሩ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡
ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይልበሱ ፡
ሠለስቱ፡ካህናት፡በተገልብቦ፡ልብስ፡ጸሊም፡
ወይትቀነዩ፡በዝንቱ፡ዜማ፡ሠለስተ፡ጊዜ፡
እንዘ፡ይብሉ።
አምንስቲቲ ፡ ሙኪርያ ፡ አንቲ ፡ ፋሲ
ልያሱ፡
አምንስቲቲ፡ሙአግያ፡አንቲ፡ፋሲልያሱ፡
አምንስቲቲ፡ሙዳሱጣ፡አንቲ፡ፋሲልያሱ፡

ሕዝብኒ፡ ይሰጠዉ፡ዘንተ፡፫፡ጊዜ፡ወይበሉ፡
ካህናት፡ በዜማ፡ልዑል፡ተዘከረነ ፡እግዚኦ፡
በውስተ፡መንግሥትከ፡ተዘከረነ፡እግዚኦ፡ አ፡
ሊቅነ፡ተዘከረነ ፡እግዚኦ፡ በውስተ ፡ መንግ
ሥትከ።
ሕዝብኒ ፡ ይሰጠዉ ፡ ዘንተ ፡ ወያንብብ ፡
ዲያቆን፡ በንባብ ፡ ማሕዘኒ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡
ተዘከረነ ፡እግዚኦ፡ በውስተ ፡ መንግሥትከ ፡
ተዘከረነ ፡እግዚኦ ፡ አ ፡ ሊቅነ ፡ ተዘከረነ ፡
እግዚኦ፡ በውስተ፡መንግሥትከ።
ወይትቀነዩ ፡ ካህናት ፡ በቀዳሚ ፡ ዜማ ፡
ተዘከረነ።
ሕዝብኒ፡ ይሰጠዉ፡(ይዲ) ፡ንጉሠ፡ንገሥት፡
ክርስቶስ፡አምላክነ፡እግዚእነ፡ወመድኃኒነ፡
በከመ ፡ ተዘከርኮ ፡ ለፈያታዊ ፡ ምእመን ፡
ዘተሰቅለ፡ምስሌከ፡ወለነኒ፡ካዕበ፡ተዘከረነ፡
በውስተ፡መንግሥትከ።

ወይትቀነዩ ፡ ካህናት ፡ በቀዳሚ ፡ ዜማ ፡
ተዘከረነ።
ሕዝብኒ፡ ይሰጠዉ ፡ዘንተ ፡(ይዲ) ፡ በንባብ ፡
ማሕዘኒ ፡ መኑ ፡ ዘርእየ ፡ ፈያታዊ ፡ አምነ ፡
በንጉሥ ፡ ምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ፈያታዊ ፡ በሃይ
ማኖቱ፡ሠረቀ፡መንግሥተ፡ሰማያት፡ወገነተ፡
ትፍሥሕት።
ብፁዕ፡አንተ፡አ፡ፈያታዊ፡ወሰአሊ፡ሠናየ፡
ነገረ ፡ በዘተናገርከ ፡ ደለወከ ፡ ዘበአማን ፡
መንግሥተ፡ሰማያት፡ወገነተ፡ተድላ፡ብፁዕ፡
አንተ ፡ አ ፡ ፈያታዊ ፡ መኑ ፡ ዘርኢከ ፡ ወም
ንተ፡ነጸርከ፡እስመ፡አመንከ ፡በክርስቶስ፡
ስቁል፡በሥጋ፡ንጉሠ፡ሰማያት፡ወምድር፡
ወአምላክ፡ ኵሉ ፡ ኢርኢከ ፡ ክርስቶስሃ ፡
አምላክነ፡ አመ ፡ ተወለጠ ፡ ራእዩ ፡ በላዕለ ፡
ደብረ፡ታቦር፡በስብሐት፡አቡሁ፡አላ፡ርኢከ

ዓርብ፡መዓልት፡በ፰፡ሰዓት።

ይኸውም፡በዕዝል፡ዜማ፡ነው።
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡
ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ይቀመጡ፤ሦስት፡ካህናትም፡
ጥቁር ፡ ልብስ ፡ በመልበስ ፡ በዕዝል ፡ ዜማ ፡
እንዲህ፡እያሉ፡ይዘምሩ።

አምንስቲቲ ፡ ብሂል ፡ በጽርዕ ፡ ተዘከረነ፤
ሙኪርያ፡ብሂል፡እግዚአ።
ሙዓግያ፡ብሂል፡ቅዱስ።
ሙዳሱጣ፡ብሂል፡ሊቅ፡አንቲ፡ፋሲልያሱ፡
ብሂል፡በውስተ፡መንግሥትከ።
ሕዝቡም ፡ ይህን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይቀ
በሉ፤ካህናቱም፡ በከፍታ ፡ ዜማ ፡አቤቱ፡
በመንግሥትህ ፡ አስበን፤ አቤቱ ፡ መም
ህራችን ፡ አስበን፤ አቤቱ ፡ በጌትነትህ ፡
አስበን።
ሕዝቡም ፡ ይህን ፡ ይቀበሉ ፡ዲያቆኑም ፡
በውርድ፡ንባብ።
አቤቱ፡ በመንግሥትህ፡አስበን፡አቤቱ፡ መም
ህራችን፡አስበን፤አቤቱ፡ በጌትነትህ፡አስበን፡
ይበል።
ካህናቱም ፡ በቀድሞው ፡ ዜማ ፡ ተዘከረነ ፡
ይበሉ
ሕዝቡም፡ ይቀበሉ፤ዲያቆን፡ የነገሥታት፡
ንጉሥ ፡ አምላካችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡
ጌታችንና፡መድኃኒታችን፡ ከአንተ፡ጋራ፡
ተሰቅሎ፡ሳለ፡ያመነብህን፡ፈያታዊውን፡እን
ዳሰብከው።እኛንም፡በመንግሥትህ፡አስበን፡
ይበሉ።
ካህናቱም ፡ በቀድሞው ፡ ዜማ ፡ ተዘከረነ ፡
ይበሉ
ሕዝቡም ፡ ይህንን ፡ ይቀበሉ ፤ዲያቆን ፡
በውርድ፡ንባብ፡ፈያታዊው፡ምንን፡አይቶ፡
በንጉሥ ፡ አመነ ፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ተድላ ፡
በንጉሥ ፡ አመነ ፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ተድላ ፡
ደስታ፡ወደ፡አለበት፡ገነትና፡ወደ፡ሰማያዊ፡
መንግሥት፡በሃይማኖቱ፡ወጣ።
ፈያታይ ፡ ሆይ ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ የምት
ለምን፡ የተመሰገንህ ፡ ነህ ፤ በተናገርከው ፡
ቃል፡ ተድላ፡ገነትና፡መንግሥተ፡ሰማያት፡
የሚገባህ፡ሁነሃልና፤አንተ፡ፈያታይ፡ብፁዕ፡
ነህ፤ያየኸውና፡የተመለከትከው፡ምንድነው?
የሰማይና፡የምድር፡ንጉሥ፡የሁሉም፡ፈጣሪ፡
ክርስቶስ፡ አምነ
ሲሆን፤በሥጋ፡በተሰቀለው፡ክርስቶስ፡ አምነ
ሃልና፤በታቦር፡ተራራ፡ላይ፡በአባቱ፡ክብር፡
የፊቱ ፡ ብርሃን ፡ በአንጸባራቀ ፡ ጊዜ ፡አምላ

Scanned by CamScanner

በ፮፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ኀበ ፡ ሰፍሐዎ ፡ በውስተ ፡ ደብረ ፡ ቀራንዮ ፡ ጸራሕከ፡ወትቤ፡ተዘከረኒ፡እግዚኦ፡በውስተ፡ መንግሥትከ።

ወይትቀንዩ ፡ ካህናት ፡ በቀዳሚ ፡ ዜማ ፡ ተዘከረነ።

ወሕዝብኒ፡ይሰጠዉ፡ዘንተ።

(ይዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ።

ወሶበ ፡ ርእከ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ያድለ ቀልቁ፡ፀሐይ፡ወወርኅ፡በቀትር፡ጸልሙ፡ ወመቃብር፡ተንሥኡ፡ወኮኵሕ፡ነቅዐ፡ወመን ጦላዕተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ተሠጠ ፡ ወኮነ ፡ ክልኤተ፡ክፍለ፤ጸራሕከ፡ወትቤ፡ተዘከረኒ፡ እግዚኦ፡በውስተ፡መንግሥትከ።

ወይትቀንዩ ፡ ካህናት ፡ በቀዳሚ ፡ ዜማ ፡ ተዘከረነ።

ሕዝብኒ፡ይሰጠዉ፡ዘንተ።

(ይዲ)፡ዘንባብ፡ማሕዘኒ።

ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሜን ፡ እብለከ ፡ አ ፡ ፈያታዊ፡አንተ፡ደለወከ፡ከመ፡ዮም፡ትሄሉ፡ ምስሌየ፡ውስተ፡ገነት፡ወትወርስ፡መንግ ሥትየ።

ረድአ፡ክሕደ፡ወፈያታዊ፡ጸርሐ፡እንዘ፡ ይብል፡ተዘከረኒ፡እግዚኦ፡በውስተ፡መንግ ሥትከ።

ወይትቀንዩ ፡ ካህናት ፡ በቀዳሚ ፡ ዜማ ፡ ተዘከረነ።

ወሕዝብኒ፡ይሰጠዉ፡ዘንተ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፮፡ሰዓት።

ካሁን ፡ ክርስቶስን ፡ አላየሁም ፤ በቀራንዮ፡ ተራራ፡ዘርግተው፡በሰቀሉት፡ጊዜ፡አየኸው፡ እንጂ፤አቤቱ፡በመንግሥትህ፡አስበኝ፡ብለህ፡ ተጣራህ፡ይበል።

ካህናቱም ፡ በቀድሞው ፡ ዜማ ፡ ተዘከረነ፡ ይበሉ።

ሕዝቡም፡ይህንኑ፡ይቀበሉ።

ዲያቆኑም፡በውርድ፡ንባብ።

ሰማይና፡ምድር፡ሲናወጹ፡ፀሐይና፡ጨረቃ፡ በቀትር፡ሲጨልሙ፡ሙታን፡ሲነሡ፡ዐለቱ፡ ሲሠነጠቅ ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መጋረጃ ፡ ተከፍሎ፡ሁለት፡ክፍል፡ሲሆን፡በአየህ፡ጊዜ፡ አሰምተህ፡አቤቱ፡በመንግሥትህ፡አስበኝ፡ ብለህ፡ተጣራህ፡ይበል።

ካህናትም ፡ በቀድሞው ፡ ዜማ ፡ ተዘከረነ፡ ይበሉ።

ሕዝቡም፡ይኸንኑ፡ይቀበሉ።

ዲያቆኑም፡በውርድ፡ንባብ።

እግዚአብሔርም፡ፈያታዊ፡ሆይ፡አንተ፡ዛሬ፡ ከእኔ፡ጋራ፡በገነት፡እንደምትኖር፡መንግሥ ቴንም፡እንደምትወርስ፡እውነት፡እልሃለሁ፡ አለ።

ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ካደ ፤ ወንበዴው ፡ በመንግ ሥትህ፡አቤቱ፡አስበኝ፡ብሎ፡ጮኸ፡ይበል።

ካህናቱም ፡ በቀድሞው ፡ ዜማ ፡ ተዘከረነ፡ ይበሉ።

ሕዝቡም፡ይኸንን፡ይቀበሉ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል፤ክርስቶስ፡አምላክነ፡በል፤ሰላም፡ለኪ፡ማርያም፡ምልእተ፡ጸጋ፡ በል፡ሀበነ፡ሰላመከ፡በል፤ግናይ፡ለከሙ፡በል፤(በዕዝል)፡ስብሐት፡ለእግዚአብሔር፡ኪያነ፡ዘፈጠረ፡ከመ፡ ናምልኮ፤ስብሐት፡ለማርያም፡እመ፡አምላክ፡እግዝእትነ፡ወመድኃኒትነ፤ስብሐት፡ለመስቀለ፡ክርስቶስ፡ ዕፀ፡መድኃኒት፡ኃይልነ፡ወፀወንነ፡በል፤ጸሎተ፡ሃይማኖት፡በል፤አ፡ማኅበራኒሁ፡ለኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ወይም፡ነዋ፡በግዑ፡ወይንም፡ወዕቀቦሙ፡በል።የጸሎት፡መፈጸሚያ፡እንደ፡ፊተኛው፡ፈጽም።

ምዕራፍ፡፶፬።

ትእዛዝ።

ወይትጋብኡ፡ካህናት፡ውስተ፡ቤተ፡ክርስ ቲያን፡ቅድስት፡በዕለተ፡ዓርብ፡በጊዜ፡ ተሰዐቱ፡ሰዐት፡ዘመዓልት፡ወይጸልዩ፡በከመ፡ ጸለዩ፡በዕለተ፡ሐሙስ፡ጊዜ፡ተሰዐቱ፡ሰዓት።

ምዕራፍ፡፶፬።

ትእዛዝ።

ዓርብ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ በክበረች ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ካህናቱ ፡ ይሰብሰቡ፡ ሐሙስ፡በዘጠኝ፡ሰዓት፡እንዳደረጉት፡ሁሉ፡ ይጸልዩ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወይበል ፡ መራሂ ፡ በ፱ ፡ ሶበ ፡ ሰቀልዎ ፡ ሶበ ፡ ሰቀልዎ ፡ ሶበ ፡ ሰቀልዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ፀሐይ ፡ ጸልመ፡ወወርኅ፡ደመ፡ኮነ፡ዬ፡ዬ፡ዬ፡አድለቅለቀት፡ምድር፡ወተከሥቱ፡መቃብራት።

ወእምዝ፡ይበሉ፡ለከ፡ኃይል።

## ክፍል፡፩።

### ምንባብ።

ዘኢያሱ ፡ ነቢይ ፡ በረከቱ ፡ ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፭፡፲፩–፲፪።

፲፩ ወኀደሩ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡ውስተ፡ገልገላ፡ ወገብሩ ፡ ፋሲካ ፡ አመ ፡ ዐሡሩ ፡ ወረቡዑ ፡ ለሠርቀ ፡ ወርኅ ፡ እምነ ፡ ሠርክ ፡ በዐረቢሃ ፡ ለኢያሪኮ ፡ በማዕዶተ ፡ ዮርዳኖስ ፡ በውስተ ፡ ገዳም።

፲፪ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኃልቀ ፡ መና ፡ በሳኒታ ፡ እመዘበልዑ ፡ እክለ ፡ ምድር ፡ ወኢረከቡ ፡ እንከ ፡ መና ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ዳግመ ፡ እስመ ፡ አረሩ ፡ ብሔረ ፡ ፊንቆን ፡ በውእቱ ፡ ዓመት።ዘፀ፡፲፮፡፴፭።

## አሪት፡ዘሩት።

ምዕ፡፪፡፲፩–፲፫።

፲፩ ወአውሥአ፡ቦዔዝ፡ወይቤላ፡ዜና፡ዜነዉኒ፡ ኵሎ፡ዘገበርኪ፡ምስለ፡ሐማትኪ፡እምድኅረ፡ሞተ ፡ ምትኪ ፡ ወእፎ ፡ ኀደጊ ፡ አባኪ ፡ ወእመኪ፡ ወብሔረ ፡ ሙላድኪ ፡ ወመጻእኪ ፡ ኀበ፡ሕዝብ፡ዘኢ.ተአምሪ፡ትካት።

፲፪ ወይዕሲኪ፡እግዚአብሔር፡በከመ፡ገበርኪ፡ ወይኩን፡ዕሴትኪ፡ፍጹመ፡በኀበ፡እግዚአብሔር፡ አምላከ ፡ እስራኤል ፡ ዘመጻእኪ ፡ ኀቤሁ፡ከመ፡ትትአመኒ፡በክነፊሁ።

፲፫ ወትቤሎ፡ሩት፡ረከብኩ፡ሞገሰ፡ቅድመ፡አዕይንቲከ፡እስመ፡አስተፍሣሕከኒ፡ወናዘዝካሁ፡ ለልብ፡አመትከ፡ወናሁ፡አነ፡እከውነከ፡ከመ፡ አሐቲ፡እምነ፡አእማቲከ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

መሪ ፡ ይምራ ፡ በዘጠኝ ፡ ሃሌታ ፡ ጌታችንን ፡ በሰቀሉት ፡ ጊዜ ፡ ፀሐይ ፡ ጨለመ ፤ ጨረቃ ፡ ደም ፡ ሆነ ፤ ወዮ ፤ ወዮ ፤ ወዮ ፤ ምድር ፡ ተናወጠች፤መቃብሮችም፡ተከፈቱ።

ከዚህ፡በኋላ፡ለከ፡ኃይል፡ይበሉ።

## ክፍል፡፩።

### ምንባብ።

በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትሁንና ፡ ነቢዩ ፡ ኢያሱ ፡ የተናገረው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አሜን።

ምዕ፡፭፡፲፩–፲፪።

፲፩፤ የእስራኤል ፡ ልጆችም ፡ በመጀመሪያ ፡ ወር ፡ ሚያዝያ ፡ በባተ ፡ ዓሥራ ፡ አራተኛው ፡ በሚሆን፡ ቀን ፡ በኢያሪኮ ፡ ምዕራብ ፡ በዮር ዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በምድረ ፡ በዳው ፡ በሠርክ ፡ ፋሲካን፡በገልገላ፡አደረጉ።

፲፪፤ የዚያን ፡ ሀገር ፡ እኽል ፡ ከበሉ ፡ በኋላ ፡ በማግሥቱ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ መናው ፡ ቀረ ፡ (ቆመ)፡በዚያው፡ዓመት፡የፊንቆንን፡አዝመራ፡ ዘርፈዋልና ፡ (በልተዋልና) ዳግመኛ፡ የእስ ራኤል፡ልጆች፡መና፡አላገኙም።ዘፀ፡፲፮፡፴፭።

## የሩት፡መጽሐፍ።

ምዕ፡፪፡፲፩–፲፫።

፲፩፤ ቦኤዝም፡ባልሽ፡ከሞተ፡በኋላ፡ላማትሽ፡የሰ ራሽውን፡ሥራ፡ሁሉ፡ነግረውኛል፤እናትና፡ አባትሽን ፡ የተወለድሽበትን ፡ አገርሽን ፡ ትተሽ ፡ ቀድሞ ፡ ወደማታውቂው ፡ ወገን ፡ እንደምን፡መጣሽ?ብሎ፡መለሰላት።

፲፪፤ ላማትሽ ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ እንዳደረግሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋጋሽን ፡ ይስጥሽ ፤ በክንፈ ፡ ረድኤቱም፡ ታምኚ፡ዘንድ፡አምነሽ፡ወደሱ፡ በመጣሽበት ፡ በእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ በእግዚአብሔር፡ዘንድ፡ዋጋሽ፡ፍጹም፡ይሁን።

፲፫፤ ሩትም ፡ ደስ ፡ አሰኘተሽኛልና ፡ የኔን ፡ የባሪያህን፡ልቡና፡አረጋግተሃልና፤በፊትህ፡ባለሟልነትን ፡ አገኘሁ ፤ እነሆ ፡ እኔም ፡ ከባሮችህ ፡ እንደ፡አንዲቱ፡ባሪያ፡እሆንሃለሁ፡አለችው።

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፬፤ ወይቤላ፡በዓዝ፡ሶበ፡ኮነ፡ጊዜ፡ምሳሕ፡ንዒ፡ዝየ ፡ ወብልዒ ፡ እክለኪ ፡ ወትጸብጊ ፡ ኅብስተኪ፡በብሒእ።

ዘኤርምያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡እምላኩ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፲፩፤፲፰-፳፫።

፲፰፤ እግዚእ፡ አርእየኒ ፡ ወእእምር ፡ አሜሃ ፡ አርአይከኒ፡ምግባሮሙ።

፲፱፤ ወአንሰ ፡ ከመ ፡ በግዕ ፡ የዋህ ፡ ዘይወስድዎ ፡ ይጦብሕዎ ፡ ወኢያእመርኩ ፤ ወተማከሩ ፡ ምክረ፡እኩየ፡ላዕሌየ፡ወይቤሉ፡ንዑ፡ንደይ፡ዕፀ፡ውስተ፡ኅብስቱ፡ወንቀጥቅጦ፡እምድረ፡ሕያዋን፡ወኢይዝክሩ፡እንከ፡ስሞ።

፳፤ እግዚአብሔር፡መኰንነ፡ጽድቅ፡ዘይፈትን፡ልበ፡ወኵልያተ፡ፍታሕ፡ሊተ፡እምኔሆሙ፡እስመ፡ለከ፡ነገርኩ፡ቅሥትየ።

፳፩፤ በእንተ፡ዝንቱ፡ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡ላዕለ ፡ ሰብአ ፡ ዐናቶት ፡ እለ ፡ የኀሥሥዋ ፡ ለነፍስየ፡እለ፡ይብሉ፡ኢትትነበይ፡በስመ፡ እግዚአብሔር ፡ እመ ፡ አኮ ፡ ትመውት ፡ በእደዊነ።

፳፪፤ ወበበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር፡ኃያል፡ናሁ፡አነ፡እዋሕዮሙ፡ወራዙቶሙኒ፡ይመውቱ፡በኲናት፡ወደቂቆሙኒ፡ወአዋልዲሆሙኒ፡የኀልቁ፡በረኃብ።

፳፫፤ ወአልቦ ፡ ዘይተርፍ ፡ እምኔሆሙ ፡ እስመ ፡ አመጽእ ፡ እኪተ ፡ ላዕለ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ዐናቶት፡በዓመተ፡እሔውጸሙ።

ምዕ፤፲፪፤፩-፲፫።

፩፤ ጻድቅ፡አንተ፡እግዚእ፡ እስመ፡እትዋቀሥ፡በኀቤከ፡ወባሕቱ፡ፍትሐ፡እነግረከ፡ለምንት፡ፍኖተ ፡ ኃጥአን ፡ ድሉት ፡ ወተፈሥሑ ፡ ኵሎሙ፡ዐላውያን፡በማዕሌት።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፬፤ ቦኤዝም፡በምሳ፡ጊዜ፡ወደዚህ፡መጥተሽ፡እንጀራሽን፡ብዪ፤እንጀራሽንም፡በመጣጣው፡አጥልቂ፡አላት።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትኑርና፡ነቢዩ፡ኤርምያስ፡የተናገረው፡ትንቢት፡ይህ፡ነው፤አሜን።

ምዕ፤፲፩፤፲፰-፳፫።

፲፰፤ አቤቱ ፡ ግብራቸውን ፡ ግለጥልኝ፤እኔም፡መርምሬ፡ልወቅ፤ያንጊዜም፡ግብራቸውን፡ገለጥኽልኝ።

፲፱፤ እኔ፡ግን፡ሊያርዱት፡እንደሚወስዱት፡እንደ፡የዋህ፡በግ፡ነኝ፤እንዲገርፉኝ፡አላወቅሁም፤በኔም ፡ ክፉ ፡ ምክርን ፡ መከሩ፤በሚበላው፡እንጀራ፡የመርዝ፡ዕፅ፡ጨምረን፡ከሕያዋን፡አገር ፡ እናጥፋው ፤ እንግዲህ ፡ ስሙንም፡አይጥሩ፡አሉ።

፳፤ ኵላሊት፡ያጤሰውን፡ልቡና፡ያመላለሰውን፡መርምረህ ፡ የምትፈርድ ፡ እውነተኛ ፡ ዳኛ፡እግዚአብሔር፡ሆይ፡ነገሬን፡ለአንተ፡ነግሬአለሁና፡ፈርደህ፡ከነሱ፡አድነኝ።

፳፩፤ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ፡ሰውነቴን፡ለጥፋት፡በሚፈልጓት፡በእግዚአብሔር፡ስም፡አታስተምር፤እምቢ፡ብትል፡ግን ፡ በእጃችን ፡ ትሞታለህ ፡ በሚሉም፡በአናቶት ፡ ሰዎች ፡ በመዓት ፡ አለሁባቸው፡አለ።

፳፪፤ ስለዚህ ፡ ኃያል ፡ የሚሆን ፡ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤እነሆ፡እኔ፡በመዓት፡እጐበኛቸዋለሁ፤ጐልማሶቻቸው፡በጦር፡ይሞታሉ፤ሴቶች፡ልጆቻቸውና፡ወንዶች፡ልጆቻቸው፡በቀጠና፡ያልቃሉ።

፳፫፤ በመዓት፡በጐበኘኋችሁ፡ጊዜ፡መከራውን፡በአናቶት ፡ በሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ አመጣለሁና፡ከነሱም፡የሚቀር፡ሰው፡የለም፡አለ።

ምዕ፤፲፪፤፩-፲፫።

፩፤ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ እከራከራለሁና ፡ አቤቱ፡አንተ ፡ እውነተኛ ፡ ዳኛ ፡ ነህ፤ነገር፡ግን፡ፍርድን፡እጠይቃለሁ፤የኃጥአን፡ሥራቸው፡ለምን፡ተዘጋጀች፤ወንጀለኞችስ፡ሁሉ፡በወን ጀላቸው፡ለምን፡ደስ፡አላቸው።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወተከልከሙ፡ወሰፍሐ፡ሥረዊሆሙ፡ወለዱ፡
ወገብሩ፡ፍሬ፤ቅሩብ፡አንተ፡በአፉሆሙ፡
ወርንቅ፡እምነ፡ኵልያቲሆሙ።

ወለሊከ፡እግዚኦ፡ተአምረኒ፡ወትሌብወኒ፡
ወፈተንከ፡ለልብየ፡በቅድሜከ፡ትጸንሐሙ፡
ከመ፡በግዕ፡ለተጠብሖ፡ወትቄድሶሙ፡
ለዕለተ፡ቀትል።
እስከ፡ማእዜኑ፡ትላሑ፡ምድር፡ወየብሰ፡
ሣዕረ፡ገዳም፡በእከዮሙ፡ለእለ፡ይነብሩ፡
ውስቴታ፡ወኀልቁ፡እንስሳ፡ወአዕዋፍ፡
እስመ፡ይቤሉ፡አልቦ፡ዘይሬኢ፡ደኅሪተነ።

እገሪከ፡ይረውፃ፡ወይደክማከ፡ለምንት፡
ታስተሬሲ፡አፍራሰ፡ወበብሔረ፡ሰንእ፡
አንተ፡ትትአመን፡በእፎ፡ትገብር፡በኅሳረ፡
ዮርዳኖስ።
እስመ፡አኀዊከኒ፡ወቤተ፡አቡከ፡እሙንቱኒ፡
ከሀዱከ፡ወወውዑ፡ወበድኅሬከ፡አንገለጉ፡
ኢትእመኖሙ፡እመ፡ሠናየ፡ነበቡ፡ላዕሌከ።

ኀደጉ፡ቤትየ፡ወኀደጉ፡ርስትየ፡ወሀብክዋ፡
ለፍቅርተ፡ነፍስየ፡ውስተ፡እደ፡ፀራ።

ወኮነተኒ፡ሊተ፡ርስትየ፡ከመ፡አንበሳ፡
በገዳም፡ጥሕረት፡ላዕሌየ፡በእንተ፡ዝንቱ፡
ጸላእክዋ።
ግበ፡ዝእብኑ፡ውእቱ፡ሊተ፡ርስትየ፡ወሚመ፡
በአት፡ይእቲ፡ዘየዐውዱ፡ዐውዳ፡ወይት
ጋብኡ፡ኵሎሙ፡አራዊተ፡ገዳም፡
ወይመጽኡ፡ይብልዕዋ።
ኖሎት፡ብዙኃን፡አማሰኑ፡ዐጸደ፡ወይንየ፡
ወአርኰሱ፡መክፈልትየ፡ወረሰይዋ፡ለመክፈ
ልትየ፡እንተ፡አፈቅር፤በድወ፡ወአፀ።

ወኮነት፡ለሙስና፡ወለሀጕል፡ወበእንቲአየ፡
ኀልቀት፡ኵላ፡ምድር፡ወማሰነት፡እስመ፡
አልቦ፡ሰብእ፡ዘይኄሊ፡ጽድቀ፡በልቡ።
ገበ፡ኵሉ፡ገዳም፡ባኡ፡ወሑሩ፡ገዳመ፡
ኀሡረን፡እስመ፡መጥባሕቱ፡ለእግዚአ
ብሔር፡ትበልዕ፡እምአጽናፈ፡ምድር፡እስከ፡
አጽናፊሃ፡ወአልቦ፡ሰላም፡ለኵሉ፡ዘሥጋ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፪፤ አንተም፡አጸናኻቸው፤አባትነታቸውም፡
በዛ፤ ልጅም፡ወለዱ፤በአፋቸው፡አንተ፡
ቅርብ፡ ነህ፤(እንወድሃለን፡አሉ)፡ከልቡ
ናቸው፡ግን፡ርቀሃል።
፫፤ አቤቱ፡ አንተስ፡እኔን፡ፈጽመህ፡ታውቀ
ኛለህ፤ ልቡናዬን፡በፊትህ፡መረመርከው፤
ሊያርዱት፡በግን፡እንዲጠብቁት፡ትጠብቃቸ
ዋለህ፤ለሰልፋም፡ቀን፡ትለያቸዋለህ።
፬፤ ምድር፡እስከ፡መቼ፡ድረስ፡ታለቅሳለች፤በሷ፡
በሚኖሩባት፡ሰዎች፡ክፋትም፡የምድረ፡
በዳው፡ሣር፡ደረቀ፤ፍጻሜያችንን፡
የሚያውቅ፡የለም፡ብለዋልና፤አዕዋፍና፡
እንስሳ፡አለቁ።
፭፤ እግሮችህ፡ሮጠው፡ይደክማሉ፤በምትታመ
ንባት፡በሰላም፡አገር፡ፈረሶችን፡ለምን፡ታስ
ጌጣለህ፡በዮርዳኖስስ፡ትዕቢት፡ለምን፡
እንዲህ፡ታደርጋለህ።
፮፤ ወንድሞችህ፡ያባትህ፡ወገኖች፡እነሱ፡ክደው
ኻልና፡ብዙ፡ጠላቶችህም፡በኋላህ፡
ተከትለው፡ዶልተውብኻልና፡ለአንተ፡በጎ፡
ነገር፡ቢነግሩህ፡አትመናቸው።
፯፤ ቤቴን፡ተውኩ፡ርስቴንም፡ተውኩ፡ልቡናዬ፡
የሚወዳት፡ቤተ፡እስራኤልንም፡ለጠላቷ፡
እጅ፡አሳልፌ፡ሰጠኋት።
፰፤ ርስቴ፡ኢየሩሳሌም፡በቃችኝ፤በምድረ፡በዳ፡
እንዳለ፡አንበሳም፡ጮኸችብኝ፤ስለዚህ፡
ነገር፡ጠላኋት።
፱፤ ቤቴ፡ርስቴ፡ኢየሩሳሌም፡የጅብ፡ጕድጓድ፡
ናትን? ወይስ፡በዙሪያዋ፡የሚከቧት፡የቀማኛ፡
ዋሻ፡ናትን? የምድረ፡በዳ፡አራዊትም፡ሁሉ፡
ተሰብስበው፡መጥተው፡ያጠፏታል።
፲፤ ብዙ፡እረኞች፡የወይኔን፡ቦታ፡አጠፉ፤ዕድል፡
ፈንታዬንም፡(ማደሪያዬ፡ቤተ፡መቅደ
ስንም)፡አረከሱ፤ያምሮቴን፡ዕድል፡ፈንታ፡
ምድረ፡በዳና፡በረኻ፡አደረጓት።
፲፩፤ እርሷም፡ለፍጹም፡ጥፋት፡ሆነች፤በልቡ፡
እውነትን፡የሚያስብ፡ሰው፡የለምና፡ምድር፡
ሁሉ፡ፈጽማ፡ጠፋች።
፲፪፤ የእግዚአብሔር፡መቅሠፍቱ፡ጽንፍ፡እስከ፡
ጽንፍ፡ታጠፋለችና፡ለሥጋዊ፡ለደማዊም፡
ሁሉ፡ፍቅር፡አንድነት፡የለምና፡እናንተ፡
ጕስቋሎች፡ወደ፡ምድረ፡በዳው፡ሂዱችሁ፡ግቡ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፫፤ ትዘርዑ፡ሥርናየ፡ወተአርሩ፡አሥዋከ፡ወኢይበቍዓክሙ፡መክፈልትክሙ፤ተኀፈርክሙ፡እማእረርክሙ፡ወኀሰርክሙ፡እምቅሠፍተ፡መዐት፡ለእግዚአብሔር።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፳፬፡፩–፲፫።

፩፤ ናሁ፡እግዚአብሔር፡ያማስና፡ለዓለም፡ወያመዘብራ፡ወይቀፍጻ፡ገጻ፡ወይዘርዎሙ፡ለእለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ።

፪፤ ወይከውን፡ሕዝብ፡ከመ፡ካህን፡ወገብር፡ከመ፡እግዚኡ፡ወአመት፡ከመ፡እግዝእታ፡ወዘይሣየጥ፡ከመ፡ዘይሠይጥ፡ወዘይት ሌቃሕ፡ከመ፡ዘይሌቅሕ፡ወዘይፈዲ፡ከመ፡ዘበዐለ፡ዕዳ።

፫፤ ናሁ፡ማስኖ፡ትማስን፡ምድር፡ወተበርብሮ፡ትትበረበር፡ምድር፡እስመ፡አፉሁ፡ለእግዚአብሔር፡ነበበ፡ከመዝ።

፬፤ ለሐወት፡ምድር፡ወማሰነት፡ወተገፍትዐት፡ዓለም፡ወላሐዉ፡ዐበይተ፡ምድር።

፭፤ እስመ፡አበሰት፡ምድር፡ምስለ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ፡እስመ፡ዐለዉ፡ሕገ፡እግዚአብሔር፡ወወለጡ፡ሥርዓተ፡ወከሐዱ፡ኪዳነ፡ዘለዓለም።

፮፤ በእንተ፡ዝንቱ፡እንጋ፡ትውኅጦሙ፡ምድር፡እስመ፡አበሱ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስቴታ፡በእንተ፡ዝንቱ፡ይጼነሱ፡እለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ምድር፡ወይተርፉ፡ኅዳጣን፡ሰብእ።

፯፤ ለይላሕዉ፡ወይን፡ወእዕጻዳተ፡ወይን፡ወይብከዩ፡ኵሎሙ፡እለ፡ይትፌሥሑ፡በነፍሶሙ።

፰፤ ኀልቀት፡ትፍሥሕተ፡ከብሮሙ፡ውኅልቀ፡ትዝኅርቶሙ፡ወብዕለ፡ኃጥአን፡ኀልቀ፡ወቃለ፡መሰንቆ።

፱፤ ወተኀፍሩ፡እለ፡ይሰትይዎ፡ለወይን፡መሪረ፡ኮነ፡ሜስ፡ለእለ፡ይሰትይዎ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፫፤ ሥንዴውን፡ዘርታችሁ፡እሾሁን፡ትለቅማላችሁ፤ዕጣችሁም፡አይጠቅማችሁም፤አይረባችሁም፤ከአዝመራችሁም፡አለማፍራት፡የተነሣ፡አፈራችሁ፤ከእግዚአብሔርም፡መቅሠፍት፡ቁጣ፡የተነሣ፡ጐስቈላችሁ።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ትሁንና፡ነቢዩ፡ኢሳይያስ፡የተናገረው፡ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፳፬፡፩–፲፫።

፩፤ እነሆ፡እግዚአብሔር፡ኢየሩሳሌምን፡ፈጽሞ፡ያጠፋታል፤ኀፍረቷንም፡ይገልጣል፤በእሷ፡የሚኖሩትንም፡ይበትናቸዋል።

፪፤ ከዜዋዌ፡አስቀድሞ፡ጨዋው፡እንደ፡ካህን፤አገልጋይም፡እንደ፡ጌታው፡ይሆናል፤ሴት፡ባርያም፡እንደ፡እመቤቷ፡ትሆናለች፤የሚሸጥም፡እንደሚገዛ፤የሚበደረውም፡እንደሚያበድር፤ዕዳ፡የሚከፍለውም፡እንደሚከፈለው፡ይሆናል።

፫፤ እግዚአብሔር፡በአፉ፡እንዲህ፡ብሎ፡ተናግሮአልና፤እነሆ፡ምድር፡ፈጽማ፡መጥፋትን፡ትጠፋለች፤መበርበርንም፡ትበረበራለች።

፬፤ ምድር፡አለቀሰች፤ጠፋች፤ዓለምም፡ግልብጥብጥ፡አለች፤በዚህ፡ዓለም፡ያሉ፡መኳንንትም፡አለቀሱ።

፭፤ ምድር፡በሷ፡ከሚኖሩ፡ሰዎች፡ጋራ፡ስለ፡በደለች፡የእግዚአብሔርን፡ሕግ፡አፍርሰዋልና፡ለዘላለም፡ሥርዓቱንም፡ለውጠዋልና፡ለዘላለም፡ጸንቶ፡የሚኖር፡መሐላውንም፡ክደዋልና።

፮፤ በሷ፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡በድለዋልና፡ስለዚህ፡እንጃ፡ምድር፡ትውጣቸው፡ይሆን፤ስለዚህም፡በዚህ፡ዓለም፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡ይቸገራሉ፤ጥቂት፡ሰዎችም፡ይቀራሉ።

፯፤ ወይንና፡የወይን፡ቦታዎችም፡ያልቅሱ፤በልባቸው፡ደስ፡የሚላቸው፡ሁሉ፡ያልቅሱ።

፰፤ የክብራቸው፡ተድላ፡ደስታ፡ጠፋች፤በገንዘባቸው፡መኩራታቸውና፡ትዕቢታቸውም፡ጠፋች፤የኀጥአንም፡ገንዘብ፡የመሰንቆም፡ድምፅ፡ጠፋ።

፱፤ ወይንን፡የሚጠጡ፡ሰዎች፡አፈሩ፤ጠጅን፡ለሚጠጡ፡ሰዎች፡ጠጁ፡የመረረ፡ሆነ።

| በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። |
| --- | --- |
| ፲ መዝበራ ፡ ኵሎን ፡ አህጉር ፡ ወተዐጽዋ ፡ ኵሎን፡አብያት፡ከመ፡ኢይባኡ፡ውስቴቶን። | ፲፤ አገሮች፡ሁሉ፡ፈረሱ፤ወደነሳቸው፡እንዳይ ገቡም፡ቤቶች፡ሁሉ፡ተዘጉ። |
| ፲፩ ብከዩ ፡ ብካየ ፡ በእንተ ፡ ወይን ፡ እስመ ፡ ተምዕረ፡ ኵሉ ፡ ትፍሥሕት ፡ እምኵሉ ፡ ምድር። | ፲፩፤ ከአገሩ፡ሁሉ፡ወይን፡ጠፍቷልና፡ስለወይን፡ጥፋት፡ልቅሶን፡አልቅሱ። |
| ፲፪ ወይትኀደጋ፡አህጉር፡መዝበረ፡ወአብያትኒ፡የዐርቃ፡ወይትኀደጋ፡ወይትሀጐላ። | ፲፪፤ አገሮች፡ሁሉ፡ፈርሰው፡ይቀራሉ፤ቤቶችም፡ባዶ፡ይሆናሉ፤ሰዎቹ፡እየተዉዋቸው፡ሄደው፡ይጠፋሉ። |
| ፲፫ ዘንቱ ፡ ኵሉ ፡ ይከውን ፡ ውስተ ፡ ብሔር ፡ ማእከለ፡አሕዛብ። በከመ፡ሕንባባተ፡ዘይት፡ውስተ፡ተቅራም፡ሶበ፡ኃልቀ፡ቀስም፡ከማሁ፡ይቈርምዎሙ፡ለደቂቀ፡እስራኤል፡ወእሙንቱሰ፡ዘልፈ፡የዐወይዉ። | ፲፫፤ ይህ፡ሁሉ፡በአሕዛብ፡መካከል፡ባለ፡አገር፡ይደረጋል። ዓይነተኛው ፡ አዝመራ ፡ በአለቀ ፡ ጊዜ ፡ የዘይት፡ ፍሬን ፡ አጥርተው ፡ እንዲለቅሙ ፡ እንደዚያ ፡ አሕዛብ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ፈጽመው ፡ ይማርኳቸዋል ፤ እነርሳቸውም ፡ በመከራው፡ተይዘው፡ሁል፡ጊዜ፡ይጮኻሉ። |
| ፲፬ ወእለሰ፡ተርፉ፡ውስተ፡ምድር፡ይትፌሥሑ፡ኅቡረ፡በስብሐተ፡እግዚአብሔር፤ይትከወስ፡ማየ፡ባሕር፤እንበይነ፡ዝ፡ስብሐተ፡እግዚአብሔር፡ይከውን፡በደሰያተ፡ባሕር፡ወስመ፡እግዚአብሔር፡ይሴባሕ። | ፲፬፤ ከሞት፡የቀሩ፡ሰዎች፡ግን፡በኢየሩሳሌም፡በእግዚአብሔር፡ተአምራት፡አንድነት፡ደስ፡ይላቸዋል፤ባሕሩም፡ይነዋወጣል፤ስለዚህም፡የእግዚአብሔር፡ክብር፡በባሕር፡ደሴቶች፡ይገለጣል፤ስሙም፡ይመሰገናል። |
| ፲፭ ወይሴባሕ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ እስራኤል፡እምአጽናፈ፡ምድር። | ፲፭፤ የእስራኤል፡ፈጣሪ፡እግዚአብሔርም፡እስከ፡ምድር፡ዳርቻ፡ድረስ፡ይመሰገናል። |
| ፲፮ ሰማዕነ ፡ መንክረ ፡ ተስፋሁ ፡ ለጻድቅ ፡ ወይብሉ፡ አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለዐላውያን ፡ እለ ፡ ዐለዉ፡ሕገ፡እግዚአብሔር። | ፲፮፤ ለጻድቅ ፡ ሰው ፡ የተመሰከረለትን ፡ ተስፋ ፡ ሰማን፤የእግዚአብሔርን፡ሕግ፡ላፈረሱ፡ለወንጀለኞች፡ወዮላቸው፤ይላሉ። |
| ፲፯ ፍርሀት፡ወጸድፍ፡ወመሥገርት፡ላዕሌሆሙ፡ለእለ፡ይነብሩ፡ውስተ፡ምድር። | ፲፯፤ በምድር፡በሚኖሩ፡ሰዎች፡ፍርሃት፡በገደል፡መውደቅ፡ወጥመድ፡አለባቸው። |
| ፲፰ ወዘይጐይይ፡እምፍርሀት፡ይወድቅ፡ውስተ፡ጸድፍ፡ወለዘሂ፡ወፅአ፡እምጸድፍ፡ይእኅዞ፡መሥገርት፡እስመ፡መሳክወ፡ሰማይ፡ይትረኃዋ፡ወያድለቀልቃ፡መሠረታተ፡ምድር። | ፲፰፤ ፈርቶ፡የሸሸ፡በገደል፡ይወድቃል፤ከገደል፡ያመለጠውን፡ወጥመድ፡ይይዘዋል፤የሰማይ፡መስኮቶች፡ይከፈታሉና፤የምድር፡መሠረቶችም፡ይነዋወጣሉና። |
| ፲፱ ትደነግፅ፡ምድር፡ወትትሀወክ፡ወተኀሥር፡ምድር። | ፲፱፤ ምድር ፡ ደንግጣ ፡ ትታወካለች ፤ ትጐሳቈላለች፤ወደ፡ጥፋትም፡ትቀርባለች። |
| ፳ ወትጸንን ፡ ወታድለቀልቅ ፡ ከመ ፡ ልገተ ፡ ዓቃቤ፡ቀምሕ፡ወትትነትን፡ከመ፡ስኩር፡በወይን፡ወትወድቅ፡ወኢትክል፡ተንሥአ፡እስመ፡ከብደ፡ኃጢአታ። | ፳፤ እንደ፡ተክል፡ጠባቂ፡ጎጆ፡ትነዋወጣለች፤በወይን ፡ እንደሰከረ ፡ ሰውም ፡ ትፍገመገማለች፤በመከራም፡ትወድቃለች፤ኃጢአቷ፡በዝቷልና፡መነሣት፡አትችልም። |
| ፳፩ ይእቲ ፡ አሚረ ፡ ያመጽእ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዲበ፡ሰርጐ፡ሰማይ፡እዴሁ፡ወላዕለ፡ነገሥተ፡ምድር። | ፳፩፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነገሥታቱ ፡ ላይና፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እደ ፡ መዐቱን፡ያመጣል። |
| ፳፪ ወይትዐፀዉ፡ወይትጋብኡ፡ወይዬወዉ፡ወይት | ፳፪፤ በመከራ፡ይወድቃሉ፡ተሰብስበውም፡ወደ፡ |

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እሰሩ፡ለካልዕ፡ትውልድ።

፳፫፤ ወእምከመ ፡ ሐወጸሙ ፡ ይትመሰው ፡
ብዝኖሙ፡ወይወድቅ፡አረፍቶሙ፡እስመ፡
ይትነግሥ፡እግዚአብሔር፡ዘለዐቱ፡ኃይል፡
በጽዮን ፡ ወበኢየሩሳሌም ፡ ወይሴባሕ ፡
በቅድመ፡ሊቃናት።

ምዕ፡፳፭፡፩-፲፪።

፩፤ እግዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡ እሴብሐከ ፡
ወእገኒ፡ለስምከ፡እስመ፡ገበርከ፡መንክረ፡
ግብረ፡ወእሙነ፡ኮነ፡ምክረ፡ትካት።

፪፤ እስመ ፡ ረሰይኮን ፡ ለአህጉር ፡ መሬተ ፡
ወአውደቀ፡አህጉረ፡ጽኑአተ፡ወመሠረተ፡
ኃጥአን ፤ ወኢይትሐነጸ ፡ ለዓለም ፡ አሁጉ
ሪሆሙ።

፫፤ በበይነ፡ዝንቱ፡ይባርኩከ፡ሕዝብ፡ነዳያን፡
ወይባርኩከ፡አህጉረ፡ሰብእ፡ግፉዓን።

፬፤ እስመ፡ኮንከ፡ረዳኤ፡ለኵሉ፡አህጉረ፡ሰብእ፡
ትሑታን፡ወከደንኮሙ፡ትፍሥሕተ፡ለእለ፡
ይቴክዙ ፡ በተጽናሰሙ ፡ ወእምሰብእ ፡
እኩያን፡ባላሕኮሙ።

፭፤ ወአስተይኮሙ፡ተፍሥሕተ፡ለነፍሰ፡ሰብእ፡
ግፉዓን፡ወለነፍሰ፡ሰብእ፡እንቡዛን፡ለእለ፡
ጸምኡ፡በጽዮን፡እምሰብእ፡ኃጥአን፡እለ፡
ሎሙ፡መጠውኮሙ።

፮፤ ወይገብር፡እግዚአብሔር፡ጸባኦት፡ለኵሉ፡
ሕዝብ፡በዝንቱ፡ደብር፡ከመ፡ይስተዩ፡ወይነ፡
ወይስተዩ ፡ በትፍሥሕት ፡ ወይትቀብዑ ፡
ዕፍረተ።

፯፤ በዝንቱ፡ደብር፡መጠዎሙ፡ዘንተ፡ኵሎ፡
ለሕዝብ፡እስመ፡ዛቲ፡ምክር፡ለኵሉ፡ሕዝብ፡
ይእቲ።

፰፤ ውኅጠ፡ሞት፡ወኀየለ፤ወካዕበ፡ሰዐረ፡እግዚ
አብሔር፡እግዚእ፡ኵሎ፡አንብዐ፡እምኵሉ፡
ገጽ፡ወሰዐረ፡ጽዕለተ፡ሕዝብ፡እምኵሉ፡
ምድር ፡ እስመ ፡ ነበበ ፡ እግዚአብሔር ፡
በአፉሁ።

፱፤ ወይብሉ፡ውእተ፡አሚረ፡ነዋ፡እግዚአብሔር፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

እምባ ፡ ይጠጋሉ ፡ ለሁለተኛም ፡ ትውልድ ፡
ይቀጠራሉ።

፳፫፤ እግዚአብሔር፡በመዐት፡በጕበኛቸው፡ጊዜ፡
ብዛታቸው ፡ እንደሰም ፡ ይቀልጣል ፤ ኃይል፡
ያለው ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ በኢየሩ
ሳሌም፡በመዐት፡ይነግሣልና፤በሊቃውንትም፡
ፊት፡ይመሰገናልና፤እምባቸው፡ይፈርሳል።

ምዕ፡፳፭፡፩-፲፪።

፩፤ ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንቅ ፡ ተአም
ራትን፡ አድርገሃልና ፤ የቀደመውም ፡ ምክር፡
የታመነ ፡ ሁኖአልና ፡ አመሰግንሃለሁ ፤
ለስምህም፡እገዛለሁ።

፪፤ አገሮችን፡ሁሉ፡ትቢያ፡አድርገሃቸዋል፤ጽኑ፡
ጽኑ ፡ እምባዎችንም ፡ አፍርሰሃል ፤ የኃጥአ
ንንም፡ሥር፡መሠረታቸውን፡አጥፍተሃልና፡
አገሮቻቸው፡ለዘላለሙ፡አይታነጹም።

፫፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ድኆች ፡ ወገኖች ፡ ያመሰግ
ኑሃል፤የተበደሉ፡ሰዎች፡አገሮችም፡ያመሰግ
ኑሃል።

፬፤ ለተዋረዱ ፡ ሰዎች ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ረዳት፡
ሁነሃልና፤በችግራቸው፡ለሚያዝኑ፡ሰዎችም፡
ተድላ፡ደስታን፡አብዝተኀላቸዋልና፡ከክፉ፡
ሰዎችም፡አድነሃቸዋልና።

፭፤ ለተገፉ ፡ ሰዎች ፡ ሰውነት ፡ ተድላ፡ ደስታን፡
አጠጣሃቸው ፤ አእምሮዋቸውንም ፡ ላጡ ፡
ጽዮንን፡ለናፈቁ፡ሰዎች፡ሰውነትም፡ተድላ፡
ደስታን፡ሰጥተሃቸዋልና፡ያመሰግኑሃል።

፮፤ የሠራዊት ፡ ጌታ ፡ አሸናፊ ፡ እግዚአብሔር፡
በዚህ፡ተራራ፡(በኢየሩሳሌም)ሕዝቡ፡ሁሉ፡
በተድላ ፡ በደስታ ፡ ወይንን ፡ ይጠጡ፡ዘንድ፡
እንዲጠጡ ፡ ያደርጋል ፤ ዘይትንም ፡ ይቀቡ፡
ዘንድ፡እንዲቀቡ፡ያደርጋል።

፯፤ ይህች፡ምክር፡ለሕዝቡ፡ሁሉ፡ናትና፡በዚህ፡
በኢየሩሳሌም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ለሕዝቡ ፡
ሰጣቸው።

፰፤ ሞት፡ሁሉን፡አጠፋ፤በረታም፤ዳግመኛም፡
ገዥ ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር፡ ከሰው፡ሁሉ፡
ፊት፡ዕንባን፡ሁሉ፡አጠፋ፤እግዚአብሔር፡
በቃሉ፡ተናግሮአልና፡የሕዝቡንም፡ስድብ፡
ሁሉ፡ከምድር፡አጠፋ።

፱፤ እነሆ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ያመንበት ፡ ፈጣሪያችን፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

አምላክነ፡ዘኪያሁ፡ተወከልነ፡ተፈሣሕነ፡
ወተሐሠይነ፡በመድኃኒነ።
፲ ወይሁበነ፡እግዚአብሔር፡ዕረፍተ፡በዝንቱ፡
ደብር፡ወይከይድዎ፡ለሞአብ፡ከመ፡
ዘየከይዱ፡እክለ፡በመንኰራኵር።

፲፩ ወያነሥኡ፡አእዳዊሆሙ፡ላዕሌሁ፡በከመ፡
ውእቱ፡አሕሠመ፡ወቀተለ፡ወይሥእር፡
ጽዕለተ፡ዘአንሥአ፡እዴሁ፡ላዕሌሁ።

፲፪ ወያንኅሉ፡ላዕሌሁ፡አረፍተ፡ጸወኑ፡
ወይቴሐት፡እስከ፡ምድር።

ምዕ፤፳፮፡፩–፲፡፡

፩ ይእተ፡አሚረ፡የሐልዩ፡ዘንተ፡ማሕሌተ፡
ላዕለ፡ይሁዳ፡ወይብሉ፡ናሁ፡ሀገር፡ጽንዕት፡
ወመድኃኒትነ፡እንተ፡ትገብር፡አረፍተ፡
ወጥቅመ።
፪ አርኅዉ፡አናቅጸ፡ወይባእ፡ሕዝብ፡ዘየዐቅብ፡
ጽድቀ፡ወይትዌከፍ፡ርትዐ፡ወይትማሐፀን፡
ሰላመ፤እስከ፡ለዓለም።

፫ ኪያከ፡ተወከልኩ፡እግዚአ፡አምላክ፡ዐቢይ፡
ዘለዓለም።
፬ ዘአትሐትኮሙ፡ወአውረድኮሙ፡ለእለ፡
ይነብሩ፡ውስተ፡አርያም፡ወትነፅኖን፡
ለአህጉር፡ጽኑዓት፡ወታወርዶን፡እስከ፡
ምድር።
፭ ወይከይዶን፡እግረ፡የዋሃን፡ወትሑታን።

፮ ወይከውን፡ፍኖተ፡ርቱዐ፡ለጻድቃን፡
ወትጺያሕ፡ፍኖተ፡ራትዓን።
፯ እስመ፡ርቱዕ፡ውእቱ፡ፍኖቱ፡ለእግዚአ
ብሔር፡ወተወከልነ፡በስሙ፡ቅዱስ፡
ወረከብነ፡ዘፈተወት፡ነፍስነ።

ዘዘካርያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፲፬፡፭–፲፩።
፭ ወይመጽእ፡እግዚአብሔር፡አምላኪየ፡



ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

እግዚአብሔር፡ይህ፡ነው፤በመድኃኒታችን፡
በእግዚአብሔር፡አምነን፡ፈጽሞ፡ደስ፡አለን።
፲፡ በዚህ፡በኢየሩሳሌም፡እግዚአብሔር፡
ዕረፍትን፡ይሰጠናል፤እህልን፡በመንኰ
ራኵር፡እንዲያበራዩ፡ሞአብን፡ይረግ
ጡታል።
፲፩፡ እሱ፡ክፉ፡እንዳደረገ፡እንዳጠፋም፡በሱ፡
እጃቸውን፡ያነሣሉ፤በነሳቸው፡እደ፡መዐቱን፡
ያነሣ፡እግዚአብሔር፡የሞአብን፡ስድብ፡
ያጠፋል።
፲፪፡ የሚጠጋበት፡አምባውንም፡በላዩ፡ያፈርሱ
በታል፤ምድር፡እስከ፡መሆን፡ድረስም፡
ይዋረዳል።

ምዕ፤፳፮፡፩–፲።

፩፡ ያን፡ጊዜ፡እነሆ፡የጸናች፡የምታድን፡የእግዚ
አብሔርን፡ረድኤት፡አጥር፡ቅጥር፡የምታ
ደርግ፡አገር፡ይህች፡ናት፡እያሉ፡በይሁዳ፡
ይህን፡ምስጋና፡ያመሰግናሉ።
፪፡ ነቢያት፡ካህናት፡የኢየሩሳሌምን፡በሮች፡ክፈቱ፤
ሕግን፡የሚጠብቅ፡የቀና፡ሥራንም፡የሚቀ
በል፡እስከ፡ዘላለሙ፡ድረስ፡ፍቅር፡አንድነትን፡
ገንዘብ፡የሚያደርግ፡ወደ፡ትምህርት፡ይግባ።
፫፡ ለዘላለሙ፡ገናና፡ፈጣሪ፡የምትሆን፡አቤቱ፡
አንተን፡አመንኩ።
፬፡ በልዕልና፡የሚኖሩትን፡ፈጽመህ፡ያዋረድ
ካቸው፡ጽኑ፡ጽኑ፡የሚሆኑ፡አምባዎችንም፡
ያፈረስካቸው፤ምድር፡እስከ፡መሆንም፡
ድረስ፡ያጠፋሃቸው፡አንተ፡ነህ።
፭፡ የተዋረዱ፡ሰዎችና፡የየዋሃን፡እግር፡ይረግጣ
ቸዋል።
፮፡ ለደጋጎች፡የቀና፡ጎዳና፡ይሆናል፤የደጋጎች፡
ጐዳናም፡ትጠረጋለች።
፯፡ የእግዚአብሔር፡ጐዳና፡የቀና፡ነውና፡
በከበረ፡ስሙ፡አምነን፡የልቡናችንንም፡
ፈቃድ፡አገኘን።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና፡ነቢዩ፡ዘካርያስ፡የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፤፲፬፡፭–፲፩።
፭፡ ፈጣሪዬ፡እግዚአብሔር፡በረድኤቱ፡

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወተሎሙ፡ቅዱሳኒሁ፡ምስሌሁ።

ወተከውን፡

፮፤ ወውእተ፡አሚረ፡አልቦ፡ብርሃን፤ወተከውን፡
አሐቲ፡ዕለት፡ቊረ፡ወበረደ።

፯፤ ወይእቲ ፡ ዕለት ፡ እምርት ፡ በኀበ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ወኢኮነት ፡ መዓልተ ፡ ወኢኮነት ፡
ሌሊተ ፤ ወፍና ፡ ሠርክ ፡ ይበርህ ፡ ብርሃነ ፡
ፀሐይ።

፰፤ ወይእተ ፡ አሚረ ፡ ይወፅእ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡
እምኢየሩሳሌም፡መንፈቁ፡መንገለ፡ባሕር፡
ቀዳሚት ፡ ወመንፈቁ ፡ መንገለ ፡ ባሕር ፡
ደኀሪት ፡ ወከማሁ ፡ ይከውን ፡ በክረምት ፡
ወበሐጋይ።

፱፤ ወይነግሥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኵሉ ፡ ምድር ፡
ውእተ ፡ አሚረ ፡ ይከውን ፡ አሐዱ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ወአሐዱ፡ስሙ።

፲፤ ወይበጽሕ፡ኵሎ፡ምድረ፡ወየዐውድ፡ገዳመ፡
እምጌላቡሄ፡እስከ፡ሬማን፡ወደቡባዊ፡ለኢየሩ
ሳሌም፡ወሬማስ፡ትነብር፡ለዓለም፡ውስተ፡
ብሔራ፡እምአንቀጸ፡ብንያም፡እስከ፡አንቀጸ፡
ደወለ ፡ ጸናፌ ፡ አንቀጸ ፡ መአዝን ፡ ወእስከ ፡
ማኀፈደ ፡ አናምሄል ፡ ወእስከ ፡ ምክያደ ፡
ዘቤተ፡ንጉሥ፡ይነብርዋ።

፲፩፤ ወኢትከውን ፡ እንከ ፡ ውግዘተ ፡ ወትነብር ፡
እንከ፡ኢየሩሳሌም፡ተአሚና።

ትርጓሜ፡ትንቢተ፡ዘካርያስ፤ወይመጽእ፡እግ
ዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡ እስከ ፡ ኀበ ፡ ይብል ፡
ወትነብር፡ኢየሩሳሌም፡ተአሚና።

፭፤ ይቤ ፡ መተርጉም ፡ ናሁ ፡ ይመጽእ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አምላኪየ ፡ ወኵሎሙ ፡ ቅዱሳኒሁ ፡
ምስሌሁ ። ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡ ትሥጉተ ፡
አምላክ ፡ ቃል ፡ ወምጽአቶ ፡ ለመድኀኒተ ፡
ትዝምደ፡ሰብእ።

፮፤ ይቤ ፡ መተርጉም ፡ ወቅዱሳኒሁ ፡ ምስሌሁ ፡
ይተረጐም ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ ፡ ላእካኑ ፡
ለንጉሥሙ፡ዘበአማን።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ይመጣል ፤ ወዳጆቹ ፡ ነቢያት ፡ ካህናትም ፡
ሁሉ፡ከእርሱ፡ጋር፡ይመጣሉ።

፮፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ የዚያች ፡ ቀን ፡ ብርሃን ፡ የላትም ፤
አንዲቱም፡ቀን፡በረድና፡ቊር፡ትሆናለች።

፯፤ ያቺም ፡ ቀን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
የታወቀች ፡ ናት ፤ ይህቺውም ፡ መዐልትም ፡
አይደለች፤ሌሊትም፡አይደለች፤ማታ፡ጊዜ፡
የፀሐይ፡ብርሃን፡ይበራል።

፰፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ድኅነት ፡ ያለው ፡
ውኃ፡ይወጣል፤እኩሌታውም፡ወደ፡መጀመ
ሪያዪቱ ፡ ባህር ፡ ምሥራቅ ፤ እኵሌታውም ፡
ወደ ፡ ኋለኛይቱ ፡ ባሕር ፡ ምዕራብ ፡ ይሄዳል ፤
በበጋና፡በክረምት፡እንዲህ፡ይሆናል።

፱፤ እግዚአብሔርም ፡ ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ይነግሣል ፤
ያን ፡ ጊዜም ፡ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይመለካል፤አንዱም፡ስሙ፡ይመሰገናል።

፲፤ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ይደርሳል ፤ ከጌላቡሄ፡ጀምሮ፡
እስከ ፡ ሬማን ፡ ድረስ ፡ እስከ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡
ደቡብ ፡ ምድረ ፡ በዳውን ፡ ይዞራል ፤ ሬማም ፡
በአገርዋ ፡ በተድላ ፡ በደስታ ፡ ትኖራለች ፤
ከብንያም ፡ በር ፡ ጀምሮ ፡ አራት ፡ ማዕዘን ፡
እስካለው ፡ በር ፡ አውራጃ ፡ ድረስ ፤ አናምሄል ፡
የሚባል ፡ ሰው ፡ እስከሚጠብቀው ፡ በር ፡ እስከ ፡
ንጉሡ ፡ ቤት ፡ ዐደባባይ ፡ ድረስ ፡ ይኖሩባታል።

፲፩፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሰው ፡ የተለየች ፡ አትሆንም ፤
ኢየሩሳሌምም ፡ ጠላት ፡ ጠፍቶላት ፡ ተዘልላ ፡
ትኖራለች።

ወይመጽእ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኪየ ፡
ከሚለው ፡ ጀምሮ ፡ ወትነብር ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ተአሚና ፡ እስከሚለው ፡ ድረስ ፡ የዘካርያስ ፡
ትንቢት፡የምሥጢር፡ትርጓሜ፡ይህ፡ነው።

፭፤ ተርጓሚው ፡ እነሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪዬ ፡
ይመጣል ፤ ቅዱሳኖቹ ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡
ይመጣሉ ፡ አለ ፤ ይህንንም ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡
ሰው ፡ ሁኖ ፡ የሰውን ፡ ባሕርይ ፡ ለማዳን ፡
መምጣቱን፡ይተረጉማል።

፮፤ ተርጓሚውም፡ቅዱሳኖቹ፡ከእርሱ፡ጋር፡ናቸው፡
አለ ፤ እነርሱ ፡ ዕውነተኛ ፡ ንጉሣቸውን፡ የሚ
ያገለግሉ፡መላእክት፡እንደሆኑ፡ይተረጉማል።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

መሀ፡ ፈቀደ ፡ በምሕረቱ ፡ ከመ ፡ ይቤዙ ፡
ወለደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ በሥርዐቱ ፡
መንክር ፡ ተሠገወ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለመድኃ
ኒቶሙ ፡ ኢተፈልጥዎ ፡ ላእካን ፡ መንፈሳ
ውያን፡በከመ፡ከነ፡ስምዐ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡
ዘእንቲአሆሙ ፤ ኖሎት ፡ ርእይዎሙ ፡ ለመላ
እክት፡ወውእቶሙ፡እንዘ፡ይሴብሑ፡ሎቱ።
ወጊዜ ፡ ተመክሮቱ ፡ ተልእክዎ ፡ ሎቱ ፡
ወከማሁ፡በሌሊተ፡ሕማሙ፡ማሕየዊት፡ወት
ንሣኤሁ፡ቅድስት፡ወዕርገቱ፡ውስተ፡ሰማይ፡
መላእክት ፡ ውስተ ፡ ተልእኮ ፡ ወበውስተ ፡
ከልእኒ፡ጊዜ።
ይቤ ፡ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ አልቦ ፡ ብርሃን ፤
ተናገረ፡ነቢይ፡በእንተ፡ርደቱ፡ለአምላክ፡
ቃል፡ኀበ፡ዓለም፡እምንጽሕት፡ድንግል።
ዘከረ፡ ዕለተ መድኃኒት ፡ ዘውእቱ ፡ ዕለተ ፡
ሕማሙ፡ማሕየዊት፡ዘባቲ፡አሞቶ፡ለሞት፡
ወለኃጢአትኒ ፡ ወአግዐዞ ፡ ለአዳም ፡ ወለት
ዝምዱ፡እምግብርናቱ፡ለዘይቀንዮሙ።

ይቤ ፡ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ አልቦ ፡ ብርሃን ፡
ይትረጐም፡ውእቱ፡ካዕበ፡በእንተ፡ሕዝብ፡
ዘኀረዮሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአልዐሎሙ ፡
ወአግረረ ፡ ሎሙ ፡ አሕዛበ ፡ ወፈነወ ፡
ኀቤሆሙ፡ ነቢያተ ፡ ለተዐቅቦቶሙ ፡ ወሰባ
ክያነ፡ሎሙ፡በእንተ፡መድኃኒቶሙ፡ወኢ፡ተ
ወክፉ፡ካዕበ፡መድኃኒቶሙ።
መጽአሙ፡በምሕረቱ፡ወገብረ፡ውስቴቶሙ፡
እምነ፡ምሕረት፡ወትሩፋት፡ዘይትሌዐል፡
ልበ።
ወበዝንቱ፡ኀብሩ፡ላዕለ፡ቀቲሎቱ፡ወጸልማ፡
አልባቢሆሙ፡ወረሰዩ፡ርእሶሙ፡ጽልመተ፡
ዘእንበለ ፡ ብርሃን ፤ ወፈድፋደሰ ፡ በዕለተ ፡
ሕማማት ፡ እግዚእ ፡ አላ ፡ እንታክቲ ፡
ጽልመት፡እንተ፡ኮኑ፡ውስቴታ፡በፈቃዶሙ፡
ወኢያእመሩ፡እስመ ፡ ሰያጥንትኒ ፡ ደንገፁ ፡
ወርዕዱ ፤ ወተመይጡ ፡ ንፋጻኒሆሙ ፡
እምውእቱ፡ግርማ፡ራእይ፡ግሩም።
ወውእቶሙሰ ፡ በእንተ ፡ ጽልመተ ፡ አልባ
ቢሆሙ፡ወመዊአተ፡ቅንአቶሙ፡ወቀዊሞተ፡
ፈቃዶሙ፡ኮኑ፡ተቃዋምያነ፡ከመ፡ዘመስተበ
ቅዓነ፡ሎቱ፡ወመስተሣልቃነ፡ቦቱ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፫፤ በችርነቱ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡
በወደደ፡ጊዜ፡ድንቅ፡በሆነ፡ተዋሕዶም፡ለድ
ኅነታቸው ፡ ከእነርሱ ፡ ከሰዎች ፡ ሥጋን ፡
በተዋሐደ፡ጊዜ፡ረቂቃን፡መላእክት፡አልተለ
ዩትምና፡እረኞች፡መላእክትን፡ሲያመሰግኑ፡
አዩዋቸው ፡ ብሎ ፡ የከበረ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡
መሰከረ።
፬፤ እንዲሁም ፡ በሚፈተንበት ፡ ጊዜ ፡ ሕይወት ፡
በሆነችም ፡ በመከራው ፡ ሌሊት ፡ ልዩ ፡
በሆነች፡ በትንሣኤውና፡ ወደሰማይ፡በሚያር
ግበትና፡በሌላም፡ጊዜ፡ሁሉ፡መላእክት፡እን
ዳገለገሉት፡ያስረዳል።
፭፤ በዚያን፡ጊዜ፡ብርሃን፡የለም፡አለ፤አምላክ፡
ቃል ፡ ከንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ሲወለድ፡ ወደ ፡
ዓለም፡ስለ፡መምጣቱ፡ነቢይ፡ተናገረ።
፮፤ አዳምን፡ወገኖቹንና፡ልጆቹን፡ከሚገዛቸው፡
እጅ ፡ ነፃ ፡ እንዳወጣቸው ፤ በእርሷ ፡ ሞትን ፡
ኃጢአትን ፡ ያጠፋባትን ፡ የድኅነት ፡ ቀን ፡
የሆነች ፡ የማሕየዊት ፡ ሕማሙን ፡ ቀን ፡
አስታወሳ!
፯፤ ዳግመኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ መረጣቸው ፡
እስራኤል ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ስለአደረጋቸው ፡
አሕዛብን ፡ ስለአስገዛላቸው ፡ ስለ ፡ ድኅነ
ታቸው፡እንዲጠብቋቸው፡እንዲያስተምሩዋ
ቸውም፡ነቢያትን፡ስለ፡ላከላቸው፡እነርሱ፡
ግን፡የሚድኑበትን፡ትምህርታቸውን፡እንደ፡
አልተቀበሉ፡ይተረጐማል።
፰፤ በቸርነቱም፡ሰው፡ሁኖ፡መጥቶ፡ልብ፡አስቦ፡
የማይደርስበትን፡ትምህርትን፡ተአምራትን፡
ትሩፋትን፡አደረገላቸው።
፱፤ በዚህም፡እርሱን፡በመግደል፡ተባበሩ፤ልቡና
ቸውም፡ጨለመ፤ራሳቸውንም፡ያለ፡ዕውቀት፡
ደናቁርት ፡ አደረጉ ፤ ይልቁንም ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡
ሕማማት፡ቀኑ፡ጨለማ፡ሲሆን፡በፈቃዳቸው፡
በውስጥዋ ፡ በድንቁርና ፡ ጸኑባት ፡ እንጂ ፡
አላወቁም፤ከዚያ፡ከሚያስፈራው፡ግርማው፡
የተነሣ፡ሰይጣናት፡እንኳ፡በመደንገጥና፡በመ
ንቀጥቀጥ፡ድል፡ሆነው፡ተመልሰዋልና።
፲፤ እነርሱ፡ግን፡ስለ፡ልቡናቸው፡መጨለምና፡
የቅናት ፡ መንፈስ ፡ ድል ፡ ስለ ፡ አደረጋቸው ፡
የቅናት ፡ መንፈስ ፡ ድል ፡ ስለ ፡ አደረጋቸው ፡
ፈቃዳቸውንም ፡ ስለአጸኑ ፡ የሚቃወሙት ፡
የሚበቀሉትና፡የሚዘብቡበት፡ሆኑ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፩፡ ወይቤ ፡ ወትከውን ፡ አሐቲ ፡ ዕለት ፡ ቍረ ፡
ወበረድ፡ወዝንቱ፡ይትሜሰል፡በእንተ፡ዘኮኑ፡
ውስቴቱ ፡ መሀይምናን ፡ ወዘኢኮኑ ፡ መሀይ
ምናን፡በዕለተ፡ስቅለት፡ክቡር፤እስመ፡መሀይ
ምናን፡ሰበ፡ርእዩ፡ውእተ፡ዕለተ፡መንክረ፡
ነሥአሙ፡ድንጋጼ፡ወረዓድ፡ወዐቢይ፡ሐዘን፤
ወውእቱ፡በከመ፡ይቤ፡እግዚእ፡ለአርዳኢሁ፡
በእንተ ፡ ዘይከውን ፡ ሎሙ ፡ እምናእከ ፡
ወሐዘን፡ወፍርሀት፡ወጕያ።

፲፪፡ ወዘሰ ፡ ኢኮኑ ፡ መሀይምናን ፡ ረግዐት ፡
ልቡናሆሙ ፡ ወጸንዓ ፡ አልባቢሆሙ ፡ ከመ ፡
ዘይቡስ ፡ በረድ ፡ ኀጡአነ ፡ ሙቀተ ፡ ጸጋ ፡
ዘመንፈስ ፡ ሃይማኖት ፤ ወኮኑ ፡ እንጕግዋነ ፡
በምግባሮሙ፡እንተ፡ኢኮነት፡መሠመሪተ፡
እስከ፡ፈጸሙ፡ሥምረቶሙ።

፲፫፡ ወተፈጸመ፡ላዕሌሆሙ፡ቃለ፡እግዚአብሔር፡
እምቀቲሎቶሙ ፡ ወልደ ፡ ወራሴ ፡ አፍአ ፡
እምዐጸደ፡ወይን፤ወተሐዘቡ፡ከመ፡ይንሥኡ፡
ውእቶሙ፡ርስቶ።

፲፬፡ ወተመልኀ ፡ እንከ ፡ ርስቶሙ ፡ ቀዳማይ ፡
እምኔሆሙ ፡ ወነሥኡ ፡ ርስቶሙ ፡ ዘመን
ግሥተ፡ሰማያት፡ዘለዓለም።

፲፭፡ ይቤ፡ወይእቲ፡ዕለት፡እምርት፡በኀበ፡እግዚአ
ብሔር ፡ ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡ ዕለተ ፡ ኢይቀ
ድምኒ ፡ ዘከማሁ ፡ ወኢይመጽእኒ ፡ ካዕበ ፡
ዘከማሁ፤ወውእቱኒ፡እሙር፡በኀበ፡እግዚአ
ብሔር፡እስከ፡ለዓለም፡ከመ፡ውእቱ፡ዕለተ፡
ስቅለቱ፡ክቡር፡ወቦቱ፡ኮነ፡መድኃኒት፡ለቀ
ደምትኒ፡ወለደኅርትኒ።

፲፮፡ ይቤ፡ኢኮነት፡መዐልተ፡ወሌሊተ፡ወከማሁ፡
ኮነ፡ዕለተ፡ሕማማቲሁ፡ለእግዚእነ፤ኢኮነኒ፡
ፍጹመ፡መዐልተ፡ወኢኮነ፡ፍጹመ፡ሌሊተ።

፲፯፡ ወባሕቱ፡ኮነ፡መዐልተኒ፡ወሌሊተኒ፡በከመ፡
ስምዐ፡ኮነ፡በውእቱ፡ወንጌል፡ቅዱስ፡እስመ፡
መለከታ ፡ ለዙላ ፡ ምድር ፡ ይእቲ ፡ ሌሊት ፡
እምስሱ፡ሰዓት፡እስከ፡ተሱዐት፡ሰዓት።

፲፰፡ ይቤ ፡ ወፍና ፡ ሠርከ ፡ ይበርህ ፡ ብርሃን ፡
ተርጐመ ፡ ከመ ፡ በጊዜ ፡ ተቈልቍሎ ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፩፤ አንዲቱም ፡ ቀን ፡ በረድና ፡ ቍር ፡ ትሆናለች፡
አለ፤ይህም፡በከበረ፡ስቅለቱ፡ቀን፡በውስጡ፡
ስለ ፡ ነበሩ ፡ ያመኑና ፡ ያላመኑ ፡ ሰዎችን፡
ይመስላል ፤ ያመኑት ፡ ያንን ፡ ድንቅ ፡ ግርማ፡
በአዩ፡ጊዜ፡ድንጋፄና፡መንቀጥቀጥ፤ፍጹም፡
ሐዘንም፡ደርሶባቸዋልና፤ይኸውም፡ጌታችን፡
ከፍርሀት ፤ ከፍጹም ፡ ሐዘን ፤ ልቅሶ፤ከሽሽት፡
የተነሣ፡የሚሆነውን፡ለደቀ፡መዛሙርቱ፡እን
ደነገራቸው።

፲፪፤ ያላመኑት ፡ ግን ፡ ልባቸው ፡ የረጋች ፡ ሆነች፤
የሚገኝ፡የመንፈስ፡ቅዱስን፡የሙቀት፡ጸጋን፡
ያጣ ፡ ልባቸውም ፡ እንደ ፡ በረድ ፡ ቀዝቅዞ፤
የረጋ፡ሆነ፤ደስ፡በማታሰኝ፡ሥራቸውም፡የተ
ቅበዘበዙ፡ሆኑ፤ፈቃዳቸውን፡እስከ፡ፈጸሙ፡
ድረስ።

፲፫፤ ርስቱን ፡ እንወርሳለን ፡ ብለው ፡ ተጠራጥረው፡
ወራሹን ፡ ከወይኑ ፡ አትክልት ፡ ውጭ ፡ አውጥ
ተው፡ከመግደላቸው፡የተነሣ፤በእርሳቸው፡ላይ፡
የተነገረው፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ተፈጸመ።

፲፬፤ እንግዲህ ፡ የቀደመው ፡ ርስታቸው ፡ ከእነርሱ፡
ተነቀለ ፤ ዘለዓለማዊ ፡ የሆነ ፡ ሰማያዊ ፡ ርስታቸ
ውንም፡አጡ።

፲፭፤ ያቺም ፡ ቀን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡
የታወቀች፡ናት፡አለ፤ይኸንንም፡ቀን፡የሚቀ
ድመው ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ እንደርሱ ፡ ያለ ፡
ሁለተኛ፡የሚመጣ፡እንደሌለ፤እርሱም፡በእ
ግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለሙ ፡ የታወቀ፡
እንደሆነ ፤ እርሱም ፡ ለፊተኞችና ፡ ለኋለኞች፡
ድኅነት ፡ የሆነበት ፡ የከበረ ፡ የስቅለቱ ፡ ቀን፡
እንደሆነ፡ይተረጕማል።

፲፮፤ መዐልት ፡ አልሆነም ፤ ሌሊትም ፡ አልሆነም፡
አለ ፤ የጌታችን ፡ የመከራው ፡ ቀን ፡ እንዲሁ፡
ሆኖአልና፤ፍጹም፡መዐልት፡ወይም፡ፍጹም፡
ሌሊት፡አልሆነምና።

፲፯፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከስድስት ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፡
ዘጠኝ፡ሰዓት፡ድረስ፡ዓለምን፡ሁሉ፡ጨለማ፡
ሠለጠነችባት ፡ ብሎ ፡ የከበረ ፡ ወንጌል ፡ እንደ
መሰከረ ፡ ግማሽ ፡ ቀን ፡ ግማሽ ፡ ሌሊት ፡ ሆነ፡
እንጂ።

፲፰፤ ማታ ፡ ጊዜ ፡ የፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ይበራል ፡ አለ፤
በመሸ፡ጊዜ፡በእግዚአብሔር፡ትእዛዝ፡ፀሐይ፡

Scanned by CamScanner

መዐልት፡ሠረቀት፡ፀሐይ፡በትእዛዘ፡እግዚአ
ብሔር፡ ሌሊት፡ ኮነ፡ ብርሃነ፡ እስከ፡ ፍና፡
ሙርክ።
፲፱ ይቤ፡ ወውእተ፡ አሚረ፡ ይወፅዕ፡ ማይ፡
ማሕየዊ፡ እምኢየሩሳሌም፡ መንፈቁ፡
መንገለ፡ ባሕር፡ ቀዳሚት፡ ወመንፈቁ፡
መንገለ፡ባሕር፡ደኃሪት፤ይተረጐም፡ዘንተ፡
በዕለት፡ ዝኩር፡ ዘሐመ፡ ቦቱ፡ እግዚእ፡
በፈቃዱ፡ ወወፅአ፡ እምገቦሁ፡ አምላካዊ፡
ማይ፡ማሕየዊ፡ዘቦቱ፡ኮነት፡ሕይወተ፡ኵሉ።
፳ ይቤ፡መንገለ፡ባሕር፡ቀዳሚት፡ይተረጐም፡
ዘንተ፡ በእንተ፡ ትውልድ፡ ዘቀዳሚ፡
እምአዳም፡እስከ፡አሚሃ፡ዕለት፡እለ፡ኮኑ፡
ምውታነ፡ውስተ፡ሲኦል፡በእንተ፡ዕልወት፤
አሕየዎሙ፡ሕይወተ፡እንተ፡ለዓለም፡ወአግ
ብአሙ፡ኀበ፡ዘቀዳሚ፡ርስቶሙ፡ዘተሰዱ፡
እምኔሁ፡በእንተ፡ኃጢአት።

፳፩ ይቤ፡ወመንፈቁ፡መንገለ፡ባሕር፡ደኃሪት፡
ይተረጐም፡ዘንተ፡ትውልደ፡እምውእቱ፡
ዕለት፡ እስከ፡ ማኅለቅት፡ አሕየዎሙ፡
ሕይወተ፡በሃይማኖት፡በስሙ፡ቅዱስ፡ወበጥ
ምቀተ፡ ክርስትና፡ ቅድስት፡ በሥጋሁ፡
ወበደሙ፡ክቡራን።

፳፪ ይቤ፡ ወከማሁ፡ ይከውን፡ በክረምት፡
ወበሐጋይ፤ወውእቱ፡ይትሜሰል፡በእንተ፡
ትርጓሜ፡ ዘቀዳሚ፡ እስመ፡ ይተረጐም፡
ለሐጋይ፡ኀበ፡ዘነበሩ፡ውስተ፡ሐፍሰ፡ሲኦል፡
ወዋዕዩ፤ወለክረምትኒ፡ኀበ፡ዘነበሩ፡ውስተ፡
ሐዘው፡ኀጡአነ፡ሃይማኖት፡ወቍረተ፡አል
ባቢሆሙ፡ እምኀጥአተ፡ እሳተ፡ መንፈስ፡
ቅዱስ፡ እስመ፡ ባቍዐ፡ ስቅለተ፡ እግዚእ፡
ወሕማሙ፡ ማሕየዊት፡ ተዐውዶሙ፡
ለኵሎሙ።
፳፫ ወባሕቱ፡እመቦ፡ዘፈቀደ፡ለነፍሱ፡ጽልመተ፡
ወሐዊረ፡ ውስቴታ፡ ኢያጌብሮ፡ እግዚእ፡
እስመ፡ወሀበ፡ኅርየተ፡ለፈቃዱ።
፳፬ ይቤ፡ ወይነግሥ፡ እግዚአብሔር፡ ለኵላ፡
ምድር፡ ይተረጐም፡ ከመ፡ እምድኅረ፡
ሕማማቲሁ፡ ለእግዚእ፡ ወትንሣኤሁ፡





እንደ፡ወጣች፡ሌሊት፡ሁኖ፡የነበረው፡እስከ፡
ማታ፡ብርሃን፡እንደሆነ፡ይተረጐማል።

፲፱፤ በዚያን፡ጊዜ፡ከኢየሩሳሌም፡ድኅነት፡ያለው፡
ውኃ፡ይወጣል፤እኩሌታው፡ወደ፡መጀመሪ
ያዩቱ፡ባሕር፥እኩሌታውም፡ወደኋለኛይቱ፡
ባሕር፡ይሄዳል፡አለ፤ይህንንም፡ጌታ፡መከራ፡
በተቀበለባት፡ በታሰበችው፡ ቀን፡ ከአም
ላካዊ፡ ጐኑ፡ ሁሉም፡ የዳነበት፡ የሕይወት፡
ውኃ፡እንደወጣ፡ይተረጐማል።
፳፤ እኩሌታውም፡ወደ፡መጀመሪያይቱ፡ባሕር፡
አለ፤ይኸንንም፡ከአዳም፡ጀምሮ፡እስከዚያች፡
ቀን፡ ያሉትን፡ ስለ፡ ቀደሙት፡ ትውልድ፡
ሕግን፡ ስለማፍረስ፡ በሲኦል፡ ውስጥ፡
ምውታን፡ ነፍስ፡ ሁነው፡ ሲኖሩ፡ የዘላለም፡
ሕይወትን፡ ሰጥቶ፡ በኃጢአት፡ ምክንያት፡
ትተዋት፡ ከተሰደቡባት፡ ወደ፡ ቀደመችው፡
ርስታቸው፡እንደ፡መለሳቸው፡ይተረጐማል።
፳፩፤ እኩሌታውም፡ ወደ፡ ኋለኛይቱ፡ ባሕር፡
ይሄዳል፡ አለ፤ ይኸንንም፡ ከዚህ፡ ዕለት፡
ጀምሮ፡እስከ፡ዓለም፡ፍጻሜ፡ስለሚነሣው፡
ትውልድ፡በጸና፡ሃይማኖት፤በከበረ፡ስሙ፡
የክርስትና፡ጥምቀትን፡በመቀበል፡በከበሩ፡
በሥጋውና፡በደሙ፡ ያዳናቸው፡ መሆኑን፡
ይተረጉማል።
፳፪፤ በበጋና፡በክረምት፡እንዲህ፡ይደረጋል፡አለ፤
ይህም፡የቀደመውን፡ትርጓሜ፡ይመስላል፤
በጋ፡ያለውን፡እንዲህ፡ይተረጕመዋል፤ወደ፡
ሲኦል፡ታፍሰው፡ተዘግነው፡በትኵሳቱም፡
ሲሰቃዩ፡ ወደነበሩት፡ ነው፤ ክረምትንም፡
ሃይማኖት፡ የሌላቸው፡ ሁነው፡ ሲኖሩ፤
የመንፈስ፡ቅዱስን፡ጸጋ፡ከማጣት፡የተነሣ፡
የልቡናቸውን፡ቅዝቃዜ፡የጌታ፡ ስቅለቱና፡
መድኃኒት፡የሆነች፡ሕማሙ፡ረብሕ፡ጥቅም፡
ሁና፡ሁሉንም፡ጐብኝታቸዋለችና።
፳፫፤ ነገር፡ ግን፡ ለሰውነቱ፡ ጨለማን፡ የሚሻ፤
ወይም፡ በውስጥዋ፡ መኖርን፡ የሚወድ፤
ቢኖር፡ ጌታ፡ ግድ፡ አይለውም፤ ለፍላጎቱ፡
ምርጫን፡ሰጥቶታልና።
፳፬፤ እግዚአብሔርም፡ ለዓለሙ፡ሁሉ፡ይነግሣል፡
አለ፤ከመከራውና፡ከልዩ፡ትንሣኤው፡በኋላ፡
ስሙ፡በዓለሙ፡ሁሉ፡እንደተገለጸና፤ከፀሐይ፡

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ቅድስት ፡ ተሰጥሐ ፡ ስሙ ፡ ውስተ ፡ ኵላ ፡
ምድር፡ ወአምነ ፡ ቦቱ ፡ ዓለም ፡ እምሥራቀ ፡
ፀሐይ ፡ እስከ ፡ ምዕራቢሃ ፡ ያመልክዎ ፡ ወይቄ
ድስዎ፡ወየዐብዩ፡ስሞ፡ክቡረ።
፳፭፡ ወበእንተዝ ፡ ይቤ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ተውህበ ፡
ሊተ ፡ ሥልጣን ፡ በሰማይ ፡ ወበምድር ፡
ዘውእቱ፡በከመ፡ይየብቡ፡ሰማያውያን፡ወይ
ሴብሕዎ፡ዘእንበለ፡ዕርዐት፡ከማሁ፡ኮነ፡መሀ
ይምናንሂ ፡ በስሙ ፡ በውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡
ይሴብሕዎ፡ወይቄድስዎ።
፳፮፡ ይእተ ፡ አሚረ ፡ ይከውን ፡ አሐዱ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ ወአሐዱ ፡ ስሙ ፡ ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡
እስመ ፡ እምቅድመ ፡ ምጽአቱ ፡ ለእግዚእነ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኀበ ፡ ዓለም ፡ አልቦ ፡
አሐዱሂ ፡ ዘኮነ ፡ የአምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
በአምልኮቱ፡እሙነ፡አእምሮተ፡አምልኮ።
፳፯፡ ወረብሐሙ ፡ በተሠግዎቱ ፡ አምላካዊት ፡
ዘበአማን ፡ እንተ ፡ ታበጽሖሙ ፡ ኀበ ፡
ተፍጻሜተ፡ጸጋ፡እንተ፡ለዓለም፡በብሂሎቱ፡
ለአርዳኢሁ ፡ ከመ ፡ ይስብኩ ፡ ለኵሎሙ ፡
አሕዛብ ፡ ወያጥምቅዎሙ ፡ በስመ ፡ አብ ፡
ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ።
፳፰፡ ወአእመርዎ ፡ እንከ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡
ለአምላክ፡ጽድቅ፡ ሠለስቱ፡በአካል፡ወገጽ።
፳፱፡ ይቤ ፡ ወአሐዱ ፡ ስሙ ፡ ይተረጐም ፡ ዘንተ ፡
በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
እስመ፡እምጊዜ፡አሐደ፡ኮነ፡አምላክ፡ቃል፡
እምጊዜ፡ብሥራት፡በሥጋ፡ዘነሥአ፡እምድ
ንግል ፡ ንጽሕት ፡ በነፍስ ፡ ልቡናዊት ፡
ወነባቢት ፡ ዘእንበለ ፡ ቱስሕት ፡ ወኢትድ
ምርት፡ወኢፍልጠት፡ኮነ፡አሐደ፡መሲሐ፡
ወአሐደ፡እግዚአ፡ ወአሐደ፡አምላከ።
፴፡ ወበእንተዝ፡ይብል፡ሐዋርያ፡ይስግድ፡ኵሉ፡
ብርክ፡ዘበሰማይ፡ወዘላዕለ፡ምድር፡ለስመ፡
ዚአሁ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
፴፩፡ ወውእቱኬ፡አሐዱ፡አምላክ፡
አምላክ፡ ዘእንበሌሁ፡ በከመ፡ ወአልቦ፡ባዕድ፡
ካዕበ፡ እስመ፡ ይቤ፡ ሐዋርያ፡
ምስለ፡ ሥጋዊት፡ አልቦ፡ ተፍጻሜተ፡ መለኮት፡
ወበከመ፡ ቃለ፡ እግዚአ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

መውጫ ፡ እስከ ፡ መግቢያዋ ፡ ድረስ ፡ ዓለሙ ፡
ሁሉ ፡ እንዳመነበት ፡ እንደሚያመልኩትና ፡
እንደሚያመሰግኑት ፡ የከበረ ፡ ስሙንም ፡ ከፍ ፡
ከፍ፡እንደሚያደርጉት፡ይተረጐማል።
፳፭፡ ስለዚህም ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ሥልጣን ፡
ተሰጠኝ ፡ ብሎ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡
ነገራቸው ፡ ይኸውም ፡ ሰማያውያን ፡ ያለ ፡
ማቋረጥ ፡ ፈጽመው ፡ እንደሚያመሰግኑት ፡
ምእመናንም ፡ በስሙ ፡ አምነው ፡ በዓለሙ ፡
ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡ እንደሚያመሰግኑትና ፡ እን
ደሚያከብሩት፡እንዲሁ፡ሁኖአልና።
፳፮፡ ያን፡ጊዜ፡አንድ፡እግዚአብሔር፡ ይመለካል፡
አንድም፡ስሙ፡ይመሰገናል፡አለ፡ይኸንንም፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡
ወደ፡ ዓለም ፡ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፡ እውነተ
ኛውን ፡ አምልኮ ፡ አውቆ ፡ የሚያመልከው ፡
አንድም፡የለም፡ነበርና።
፳፯፡ የዘላለም ፡ ልጅነትን ፡ ፍጹም ፡ ጸጋን ፡
ለመቀበል፡ ወደምታደርሳቸው ፡ በእውነተ
ኛይቱ ፡ አምላካዊት ፡ ሥጋዌው ፡ ጠቅሟቸ
ዋልና ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ እንዲአስተምሩአ
ቸውና ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ስም ፡ እንዲአጠምቋቸው ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡
በመናገሩ፡ረብሕ፡ጥቅም፡ሁኗቸዋልና።
፳፰፡ በአካል ፡ በገጽ ፡ ሦስት ፡ የሆነውን ፡ እውነተ
ኛውን፡አምላክ፡ እስከ፡ዘላለሙ፡አወቁት።
፳፱፡ አንዱ ፡ ስሙ ፡ አለ ፡ ይኸንንም ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከብሥራት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡
የምታውቅ ፡ የምትናገር ፡ ነፍስ ፡ ያለችውን ፡
ሥጋ፡ ከንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ነሥቶ ፡ አካላዊ ፡
ቃል፡ አንድ ፡ ከሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ያለ ፡ መዋ
መር ፡ ያለ ፡ መቀላቀል ፡ ያለ ፡ መለየት ፡ አንድ ፡
መሲሕ፡ አንድ፡ጌታ፡ አንድ፡ሁኖ፡የሚመለክ፡
አንድ፡አምላክ፡ እንደ፡ሆነ፡ይተረጐማል።
፴፡ ስለዚህም ፡ ሐዋርያ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡
ላይ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ ለጌታችን ፡ ለኢየሱስ ፡
ክርስቶስ፡ ስም፡ይስገድ፡አለ።
፴፩፡ እርሱም ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ከእርሱም ፡
በቀር፡ሌላ፡አምላክ፡ የለም ፡ መለኮት ፡ ከሥጋ ፡
ጋር ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሁኖ ፡
በመዋሐዱ ፡ አስቀድሞ ፡ መለኮት ፡ ሕጸጽ ፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ክቡር፡ስሙ፡ዘውስተ፡ወንጌል፡እኔ፡ወአብ፡
አሐዱ፡ንሕነ፡ወእነ፡በአቡየ፡ወአቡየ፡ብየ፡
ወኵሉ፡ዘአቡየ፡ዚአየ፡ውእቱ፡ወዘርእየ፡
ኪያየ፡ርእዮ፡ለአብ።

፴፪ ወካዕበ፡ይቤ፡በእንተ፡መንፈስ፡ቅዱስኒ፡
አስመ፡እምዚአየ፡ይነሥእ፡ወይሁበክሙ።

፴፫ ወይቤ፡ጳውሎስኒ፡ሐዋርያ፡ለእመ፡ኮነ፡
መንፈስ፡እግዚአብሔር፡ኅዱር፡ላዕሌክሙ፡
አማን፡እንከ፡እስመ፡ለእመ፡ኢኮነ፡መንፈስ፡
ክርስቶስ፡ኅዱረ፡ላዕለ፡ብእሲ፡ኢኮነ፡
እምሕዝቡ።

፴፬ ወአጠየቀ፡ከመ፡መንፈስ፡ክርስቶስ፡ውእቱ፡
መንፈስ፡እግዚአብሔር።

፴፭ ወከማሁ፡ይብል፡በውስተ፡ግብረ፡
ሐዋርያት፡ከመ፡ውእቶሙ፡ተማከሩ፡ከመ፡
ይሠወጡ፡ኀበ፡ቢታንያ፡ወኢኀደጎሙ፡
መንፈሱ፡ለኢየሱስ፡ዘውእቱ፡መንፈስ፡
ቅዱስ፡ውእቱኬ፡አሐዱ፡አምላክ፡ዘያመ
ልክዎ።

፴፮ ወበስሙ፡ይትገበራ፡ኀይላት፡ወተአምራት፡
በኵሉ፡በከመ፡ይቤ፡ለአርዳኢሁ፡ዛቲ፡
ተአምር፡ትተልዎሙ፡ለመሀይምናን፡
በስምየ።

፴፯ ወይቤ፡ካዕበ፡እመቦ፡ዘሰአልክሙ፡በስምየ፡
እገብር፡ለክሙ።

፴፰ ወይቤ፡ካዕበ፡ወዘእንበሌየሰ፡አልቦ፡
ዘትክሉ፡ገቢረ፡ወኢምንተኒ።

፴፱ ይቤ፡ወይበጽሕ፡ኵሎ፡ምድረ፡ወየዐውድ፡
ገጻመ፡እስከ፡ሬማ፡ወውእቱኬ፡በከመ፡
ቀዳሚ፡ቃል፡ከመ፡ለኵሉ፡ዓለም፡
ወገዳማት፡ምዝቡራት፡ወአድባራት፡
በድዋት፡ኮነ፡ውስቴቶሙ፡እመሀይምናን፡
በስሙ፡ዘይሴብሖ፡ወይቄድሶ፡ከመ፡ዘመላ
እክት፡መንፈሳውያን፡በሌሊት፡ወበመ
ዐልት፡ዘእንበለ፡ዕርዓት።

፵ ጸጋሁ፡ወረድኤቱ፡ተዐውዶሙ፡ለኵሎሙ፤
ይቤ፡ወይነብርዋ፡ወኢትከውን፡ውግዝተ፡
ይትረጐም፡ከመ፡መሀይምናን፡በስሙ፡ቅዱስ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ኑሮበት፡ያገኘው፡የክብር፡ፍጻሜ፡የለም፡ብሎ፡
ሐዋርያው፡እንደተናገረ፤ስሙ፡የተመሰገነ፡
ጌታም፡በወንጌል፡እኔና፡አብ፡አንድ፡ነን፤እኔም፡
በአባቴ፡ህልው፡ነኝ፤አባቴም፡በእኔ፡ህልው፡
ነው፤ለአባቴም፡የሆነ፡ሁሉ፡የእኔ፡ነው፤እኔንም፡
ያየ፡አባቴን፡አይቷል፤ብሎ፡እንደተናገረ።

፴፪፤ ዳግመኛም፡ስለ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡እንዲህ፡
አለ፤ቃልነትን፡ከእኔ፡ዘንድ፡ወስዶ፡ይነግራ
ችኋል።

፴፫፤ ሐዋርያ፡ጳውሎስም፡የእግዚአብሔር፡
መንፈስ፡በላያችሁ፡ያደረ፡ከሆነ፤እንግዲህ፡
ወገኖቹ፡ናችሁ፤የክርስቶስም፡መንፈስ፡
በሰው፡ላይ፡ያደረ፡ካልሆነ፡ያ፡ሰው፡
ከወገኖቹ፡ውስጥ፡አልሆነም፡አለ።

፴፬፤ የክርስቶስ፡መንፈስ፡የሚለውም፡የእግዚአ
ብሔር፡የባሕርይ፡ሕይወቱ፡መንፈስ፡
ቅዱስ፡እንደሆነ፡አስረዳ።

፴፭፤ እንዲሁም፡በሐዋርያት፡ሥራ፡ውስጥ፡ወደ፡
ቢታንያ፡ሊመለሱ፡እነርሱ፡እንደ፡
ተማከሩና፤ነገር፡ግን፡የኢየሱስ፡መንፈስ፡
አላሰናበታቸውም፤እንደሚል፡ይኸውም፡
ከአብ፡ከወልድ፡ጋር፡አንድ፡አምላክ፡ሁኖ፡
የሚያመልኩት መንፈስ፡ቅዱስ፡ነው።

፴፮፤ በቦታው፡ሁሉ፡በስሙ፡ተአምራትና፡ኃይል፡
ይደረጋል፤በስሜ፡ለሚያምኑት፡ይቺ፡
ምልክት፡ትከተላቸዋለች፡ብሎ፡ለሐዋ
ርያት፡እንደ፡ነገራቸው።

፴፯፤ ደግሞም፡በስሜ፡የለመናችሁት፡ልመና፡
ቢኖር፡አደርግላችኋለሁ፡አለ።

፴፰፤ ዳግመኛም፡ያለ፡እኔ፡ግን፡ምንም፡ምን፡
ማድረግ፡አትችሉም፡አለ።

፴፱፤ በዓለሙ፡ሁሉ፡ይደርሳል፤ከጊላቡሄ፡ጀምሮ፡
እስከ፡ሬማ፡ድረስ፡ምድረ፡በዳውን፡ይዞራል፡
አለ፤ይህም፡እንደ፡ቀደመው፡ቃል፡በዓለሙ፡
ሁሉ፡የተፈቱና፡የጠፉ፡በሆኑ፡ምድረ፡
በዳዎችና፡ተራሮች፡በውስጣቸው፡ምእመ
ናን፡ተመልተው፡ያለ፡ማቋረጥ፡በቀንና፡
በሌሊት፡ረቂቃን፡መላእክት፡ስሙን፡እንደሚ
አመሰግኑ፤እነርሱም፡የሚያመሰግኑትና፡የሚ
ያከብሩት፡እንደሆነ፡ይተረጎማል።

፵፤ ጸጋውና፡ረድኤቱም፡በዙሪያቸው፡ሁና፡
ትጠብቃቸዋለች፤ይኖሩባታል፤ከዚያ፡
በኋላም፡ከሰው፡የተለየች፡አትሆንም፡አለ፤

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ገባርያን፡ስብሐቲሁ፡ኢይከውኑ፡ርሑቃነ፡
እምኔሁ፡ከመ፡ሕዝብ፡ዘቀዳሚ፡እለ፡ኮኑ፡
ከመ፡ዘአግብርት።

፺፭፡ ወባሕቱ፡ቅሩባን፡ኀቤሁ፡ከመ፡ዘውሉድ፡
ፍቁራን፡በከመ፡ቃሉ፡ቅዱስ፡ኀበ፡ሀለዉ፡
ክልኤቱ፡ወሠለስቱ፡ጉቡእነ፡በስምየ፡አነ፡
እሄሉ፡ህየ፡ማእከሎሙ።

፺፮፡ ወውእቱ፡አቅረበሙ፡ኀቤሁ፡በምሕረቱ፡
እስመ፡ተሣየጦሙ፡በደሙ፡ክቡር።

፺፯፡ ወአሰፈዎሙ፡ዘንተ፡በቃሉ፡ወይቤሎሙ፡
አንትሙ፡ፍቁራንየ፡እምከመ፡ገበርክሙ፡
ዘአዘዝኩክሙ፡ኪያሁ፡እምይእዜሰ፡ኢይብ
ለክሙ፡ወኢይሰምየክሙ፡አግብርተ።

፺፰፡ ወትነብር፡ኢየሩሳሌም፡እንከ፡ተአሚና፡
ይተረጐም፡ዘንተ፡ሕማመ፡መሲሓዊተ፡
እስመ፡ይእቲ፡ትነብር፡ተአሚና፡በሃይ
ማኖት፡በስሙ፡ቅዱስ፡ከመ፡ያብጽሓ፡
ውስተ፡መንግሥተ፡ሰማያት።
ሎቱ፡ስብሐት፡ወክብር፡እስከ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

፻፡ ዘአስተሐመመ፡ዘንተ፡ትርጓሜ፡ትንቢተ፡
ነቢያት፡አቡነ፡አባ፡ሰላማ፡ጳጳስነ፡
ወማኀቶተ፡ነፍስነ፡ወሥጋነ፡ወመወፍየ፡
ማህላት፡በከንቱ።

፻፩፡ ወፈጣሪነ፡ኢያኅጥአነ፡ለነ፡ኪያሁ፡ብዙኃተ፡
አዝማነ፡ወአመታተ፡ፍድፍድና፡በጸሎቱ፡
እንዘ፡ይትዓየነነ፡ዘልፈ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ዘኢዮብ፡ጻድቅ፡በረከተ፡አምላኩ፡ትኩን፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፡፲፯፡፲፱–፳።

፲፱፡ ወገደፈኒ፡እግዚአብሔር፡ለፀዋጋን።

፳፡ እንዘ፡ዳኅነ፡እነብር፡ገደፈኒ፡ወመሐወኒ፡
በሥዕርተ፡ድማኀየ፡ወአቀመኒ፡ከመ፡
መጠራ፡ወከመ፡ቃፍ፡ወአስተሐየጸኒ፡ከመ፡
ሰብእ፡ዐይን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

በከበረ፡ስሙ፡ያመኑ፡ምእመናን፡ለጌትነቱ፡
ምስጋና፡የሚያቀርቡ፤እንደ፡ባሮች፡እንደ
ነበሩ፡እንደቀደሙት፡ሕዝቦች፡ያልሆኑ፡
ከእርሱ፡እንደማይርቁ፡ይተረጐማል።

፺፭፡ ነገር፡ግን፡ሁለትም፡ሦስትም፡ሆነው፤
በስሜ፡ወደተሰበሰቡት፤እኔ፡በዚያ፡በመካከ
ላቸው፡እኖራለሁ፡እንዳለው፡እንደ፡ቃሉ፡
እንደሚወደዱ፡ልጆች፡ወደ፡እርሱ፡የቀረቡ፡
ይሆናሉ፡እንጂ።

፺፮፡ በከበረ፡ደሙ፡ዋጅቷቸዋልና፡በቸርነቱ፡
እርሱ፡አቀረባቸው።

፺፯፡ ያንን፡ያዘዝኋችሁን፡ካደረጋችሁት፡እናንተ፡
ወዳጆቼ፡ናችሁ፤ከእንግዲህም፡ባሮቼ፡ብዬ፡
አልጠራችሁም፡ብሎ፡በቃሉ፡ተስፋ፡እንደአ
ስደረገላቸው፡ያስረዳል።

፺፰፡ እንግዲህ፡ኢየሩሳሌም፡ተዘልላ፡ትኖራለች፡
አለ፤ይህቺም፡ክርስቲያናዊት፡መከራ፡እንደ
ሆነች፡ይተረጐማል፤ወደ፡ሰማያዊ፡
መንግሥት፡ያደርሳት፡ዘንድ፤በስሙ፡አምና፡
በሃይማኖት፡ጸንታ፡እርሷ፡ትኖራለችና።
ለእርሱም እስከ፡ዘላለሙ፡ክብር፡ምስጋና፡
ይሁን፡አሜን።

፻፡ ይህን፡የነቢያት፡ትንቢት፡ትርጓሜውን፡
በትጋት፡ያቀነባበረ፡ያለ፡ዋጋ፡የሃይማኖትን፡
ትምህርት፡ያወረሰን፡የነፍሳችንና፡
የሥጋችን፡ፋና፡የሆነ፡ጳጳሳችን፡አባታችን፡
አባ፡ሰላማ፡ነው።

፻፩፡ ፈጣሪያችንም፡እየበዙ፡ለሚሄዱ፡ዘመናትና፡
ዓመታት፤የእርሱን፡የሃይማኖት፡ቅርስ፡አያሳ
ጣን፤በእርሱ፡ጸሎትም፡በዙሪያችን፡ከትሞ፡
ዘወትር፡ይጠብቀን፤ለዘላለሙ፡አሜን።

የአምላኩ፡በረከት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ትኑርና፡ጻድቁ፡ኢዮብ፡የተናገረው፡ቃል፡
ይህ፡ነው፡አሜን።

ምዕ፡፲፯፡፲፱–፳።

፲፱፡ እግዚአብሔርም፡ለከፋዎች፡አሳልፎ፡ሰጠኝ፡

፳፡ በደስታም፡ስኖር፡ጣለኝ፤የራስ፡ጠጉሬ
ንም፡ነቀለብኝ፤እንደ፡ጊጤና፡እንደ፡
ብራኳ፡አቆመኝ፤እንደ፡ጉብኛም፡ተመለ
ከተኝ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፬ አስመ ፡ በኲናንው ፡ ሮዱኒ ፡ ወግኡኒ ፡
ወረገዙኒ፡ ኰልያትየ ፡ ወኢመሐሩኒ ፡ ወተከ
ዕዉ፡ውስተ፡ምድር፡ሐሞትየ።
፲፭ ወበጽሐኒ ፡ ድቀት ፡ በዲበ ፡ ድቀትየ ፡ ወሮጹ ፡
ላዕሌየ፡ኃያላን።
፲፮ ሠቀ ፡ አስተጣበቁ ፡ ላዕለ ፡ ማእስየ ፤ ወተሠ
ልጠት፡ሕማምየ፡በውስተ፡መሬት።
፲፯ ትነድድ፡ክርሥየ፡በብካይ፡ወውስተ፡ቀራን
ብትየ፡ጽላሎተ፡ሞት፡እሬኢ።
፲፰ ወአልበ፡ዐመፃ፡ውስተ፡እደውየ፡ወንጹሕ፡
ጸሎትየ።
፲፱ መሬትኑ፡ ይከድነኒ ፡ ሥጋየ ፡ ወይትከዐው ፡
ደምየ፡ወኢይረክብኑ፡ብሔረ፡ኀበ፡አዐወዩ።

፳ ወይእዜኒ፡ናሁ፡ሰማዕትየ፡ውስተ፡ሰማይ፡
ወየአምር፡ሊተ፡ዘውስተ፡አርያም።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፬፤ በጦር፡ከበቡኝ፤ኵላሊቴንም፡ወጉ፤አልራሩ
ልኝም፤ሐሞቴም፡ወደ፡ምድር፡እንደ፡ውኃ፡
ፈሰሰች።
፲፭፤ በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ መጣብኝ ፤ ኃይለ
ኞችም፡በእኔ፡ላይ፡ይሮጡብኛል።
፲፮፤ በሰውነቴ ፡ ላይ ፡ ማቅ ፡ ታጠቅሁበት ፤
መከራዬም፡በመሬት፡ሠለጠነችብኝ።
፲፯፤ ሰውነቴም፡በልቅሶ፡ትቃጠላለች፤በቅንድ
ቦቼም፡ውስጥ፡የሞትን፡ጥላ፡አያለሁ።
፲፰፤ ነገር፡ግን፡በእጄ፡በደል፡የለም፤ጸሎቴም፡
ንጹሕ፡ነው።
፲፱፤ ከደዌ ፡ ሳልፈወስ ፡ ሥጋዬን ፡ መሬት ፡
ይሸፍነው፡ይሆን?ደሜስ፡በመቃብር፡ይፈስ፡
ይሆን?የምጮኽለትስ፡አገር፡አላገኝ፡ይሆን?
፳፤ ዛሬም ፡ በጎ ፡ ሥራዬን ፡ የሚመሰክርልኝ ፡
በሰማይ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤
በአርያም፡ያለ፡እርሱ፡ያውቅልኛል።

## ክፍል፡፪።

### ጸሎተ፡ስምዖን፡ዐምዳዊ።

፩ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘአጽነንከ፡
ርእሰከ፡ዲበ፡ጕንደ፡መስቀል፡አልዕል፡ርእሰ፡
ነፍስየ፡ዘድኑን፡ወግልቡብ፡በጽልመት፡ከመ፡
አዕርግ፡ኀቤከ፡ስብሐተ፡ወትንቄ፡ነፍስየ፡
በእንዚራ ፡ አምላካዊት ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡
ስብሐት፡ለዘሞተ፡ወአሕየወኒ።
፪ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘሞትከ፡
ላዕለ፡ጕንደ፡መስቀል፤ወበሞትከ፡ተሞአ፡
ሞት፡እስመ፡አንተ፡ተወካፌ፡ሞት፡ወአንተ፡
ሕያው፡በከመ፡አቡከ፡ሕያው።
፫ ወአንተ ፡ ውእቱ ፡ ቀታሊሁ ፡ ለሞት ፡
ወአንተሰ፡ አንተ ፡ ክመ ፤ ወአንተ ፡ ውእቱ ፡
አካለ፡ሕይወት።
፬ ተሰሕብከ፡ለሞት፡ወብከ፡ሞት፡ሞተ፡ሶበ፡
አእመርከ ፡ ለሕይወት ፡ ሞተ ፡ በርእዮትከ ፤
ወሰሚዖ፡ድምፀከ፡ሞት፡ሞተ።

፭ ወሙታንሂ፡ሶበ፡አእመሩከ፡ሐይዉ፡እስመ፡
ሕያው፡ለበስከ፡አልባሰ፡ሞት፡ወወረድከ፡
ኀበ፡ሙታን።
፮ ወሶበ፡ነፍኀት፡ነፍስ፡መዐዛ፡መንፈስከ፡
ላዕሌሆሙ፡ሐይዉ።

## ክፍል፡፪።

### የዓምዳዊ፡ስምዖን፡ጸሎት፡ይህ፡ነው።

፩፤ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሳለህ ፡ ራስህን ፡ ዘንበል ፡
(ዘለስ)፡ያደረግህ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሆይ፡ወደ፡አንተ፡ምስጋና፡አሳርግ፡ዘንድ፡
ለሞተውና፡ላዳነኝ፡ምስጋና፡ይሁን፡እያለች፡
ነፍሴ፡በአምላካዊ፡በገና፡ታመሰግን፡ዘንድ፡
የነፍሴን፡ራስ፡ከፍ፡ከፍ፡አድርግ።
፪፤ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡በመስቀል፡
ላይ፡የሞትክ፡በሞትህም፡ሞት፡ድል፡የሆነ፡
አንተ ፡ እንደ ፡ አባትህ ፡ ሕያው ፡ ስትሆን ፤
በሥጋ፡ሞትን፡የምትቀበል፡ሁነሃልና።
፫፤ ሞትንም ፡ የምታጠፋው ፡ አንተ ፡ ነህና ፤
አንተስ፡መቼም፡መች፡አንተ፡ነህ፤አንተም፡
የሕይወት፡አካል፡ነህ።
፬፤ ለሞት ፡ ተሳብክ ፡ በአንተም ፡ ሞት ፡ ሞት ፡
ጠፋ፤ ሕይወትነትህንም ፡ በአሳወቅኸው ፡
ጊዜ፡ አይቶህ ፡ ሞት ፡ ጠፋ ፤ ድምፅህንም ፡
ሰምቶ፡ሞት፡ጠፋ።
፭፤ ሙታንም ፡ በአወቁህ ፡ ጊዜ ፡ ዳኑ ፤ ሕያው ፡
አንተ ፡ የሞትን ፡ ልብስ ፡ ለብሰህ ፡ ሙታን ፡
ወዳሉበት፡ወርደሃልና።
፮፤ ነፍስህ ፡ የሕይወትን ፡ መዐዛ ፡ እፍ ፡ ባለች
ባቸው፡ጊዜ፡ዳኑ።

### በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፯፡ ወሶበ፡ሰምዑ፡ጽራሐከ፡ተዋሐዱ፡በኀይልከ፡
ወሶበ፡ርእዩ፡ሥነ፡ገጽከ፡በርሁ፡በብርሃንከ፡
አንተ፡ውእቱ፡ቃለ፡ሕይወት፡ወኀይሉ፡
ለአብ።
፰፡ አዳምኒ፡ሶበ፡ሰምዐ፡ቃለከ፡አእመረከ፡
እስመ፡ አንተ፡ ውእቱ፡ ለሐከሎሁ፡
ወሠያሚሁ፡ውስተ፡ገነት።
፱፡ ወውእቱ፡ቀዲሙ፡ሶበ፡ኢሰምዐ፡ቃለ፡
ትእዛዝከ፡በውስተ፡ገነት፡ተጠብለሉ፡
ላዕሌሁ፡አሕባለ፡ሞት፡እስመ፡ውእቱ፡
ተዐደወ፡ትእዛዘከ።
፲፡ ወካዕበ፡ጸዋዕኮ፡አንተ፡በቃልከ፡ማሕየዊ፡
አሕየውኮ፡ወአንግሣእኮ፡እምነ፡ሞት፡ኀበ፡
ሕይወት፡እምንዋም፡ኀበ፡ንቅሐት፡
ወእምረት፡ኀበ፡ጣዕም።
፲፩፡ ወከማሁ፡ነቢያትኒ፡አእመሩከ፡ከመ፡አንተ፡
በውስቴቶሙ፡ወነቀዋ፡እንዚራ፡ቲሆሙ፡
ወይቤሉ፡አይቴ፡ቀኖትከ፡ሞት፡ወአይቴ፡
ጽንዕከ፡ጽልመት።

፲፪፡ ከልሐ፡ዳዊት፡ወይቤ፡እስመ፡ሰበረ፡ኆኃተ፡
ብርት፡ወቀጥቀጠ፡መናሥግተ፡ዘኀጺን።

፲፫፡ እስመ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡መጽአ፡ኀቤነ፡
ወኮነ፡ግዑዛነ፡ወሐየውነ፡ቦቱ።
፲፬፡ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አግዕዘኒ፡
ሊተ፡ወአሕይወኒ፡አንተ፡ለኀጥእ፡ገብርከ፡
እገሌ።
፲፭፡ ወአጽንዕ፡አውታረ፡ዚአሃ፡ለነፍስየ፡ከመ፡
እትቀበልከ፡በዕለተ፡ምጽአትከ፡ዐቢይ።
፲፮፡ ወአድኅነኒ፡እምድቀተ፡ኀሊናት፡ዘመንፈስ፡
ስሕተት።
፲፯፡ አግዕዘኒ፡ወሚመኒ፡ኀበ፡ነቅዐ፡ሕይወት፡
እስመ፡አንተ፡ውእቱ፡ነቅዐ፡ሕይወት።
፲፰፡ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘትቤ፡ብየ፡
ካልአትኒ፡አባግዕ፡ወሀለወኒ፡አምጽአን፡
ወይከውና፡አሐደ፡መርዔተ፡ረስየኒ፡ምስለ፡
አባግዒከ፡ቡሩካን፡ወፍጹማን።
፲፱፡ አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡አንተ፡
ውእቱ፡ዘሜጥኮ፡ለበግዕ፡ዘተገድፈ፡ውስተ፡
ገነት፡ተድላ።

### ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፯፡ ድምፅህንም፡ በሰሙ፡ ጊዜ፡ ኃይልህን፡
ተዋሐዱ፤የፊትህንም፡ፀዳል፡ባዩ፡ጊዜ፡በብ
ርሃንህ፡ብሩሃን፡ሆኑ፤አንተ፡የሕይወት፡
ቃል፡የአብ፡ኃይሉ፡ነህና።
፰፡ አዳምም፡ድምፅህን፡በሰማ፡ጊዜ፡አወቀህ፤
ፈጣሪው፡በገነትም፡ሹመኘው፡የነበርከ፡
አንተ፡ነህና።
፱፡ እርሱ፡አስቀድሞ፡ትእዛዝህን፡ባልሰማ፡ጊዜ፤
የሞት፡ገመዶች፡ተጠመጠሙበት፤እርሱ፡
ትእዛዝህን፡ተላልፎአልና።

፲፡ ዳግመኛም፡አንተ፡ሕይወት፡በሆነ፡ቃልህ፡
ጠርተህ፡አዳንከው፤ከሞት፡ወደ፡ሕይወት፡
ከእንቅልፍ፡ወደ፡መንቃት፡ከመራራ፡ወደ፡
ጣፋጭ፡አሳለፍከው።
፲፩፡ እንዲሁም፡ነቢያት፡በውስጣቸው፡እንደነ
በርክ፡አወቁህ፤የትንቢት፡በገናዎቻቸው፡
እንግዲህ፡ሞት፡ሆይ፡መውጊያህ፡ወዴት፡
አለ? ጨለማ፡መቃብርስ፡ድል፡አድራጊ
ነትህ፡ወዴት፡ነው?እያሉ፡ጮኹ።
፲፪፡ ዳዊትም፡የነሐስ፡መዝጊያዎችን፡ሰበረ፤
የብረት፡መቈለፊያዎችን፡ቀጥቅጦ፡አጠፋ፡
ብሎ፡ጮኸ።
፲፫፡ የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ሰው፡ሆኖ፡ወደእኛ፡
መጥቶ፡በእርሱ፡ነፃ፡ወጥተን፡ድነንበታልና።
፲፬፡ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡እኔን፡
ኃጢአተኛ፡ባሪያህን፡ነፃ፡አውጥተህ፡
አድነኝ።
፲፭፡ በታላቁ፡መምጫህ፡ቀን፡እቀበልህ፡ዘንድ፡
የነፍሴን፡ሃይማኖቷንና፡ምግባርዋን፡አጽና።
፲፮፡ በስሕተት፡መንፈስም፡በኀልዮ፡ከመውደቅ፡
አድነኝ።
፲፯፡ ነፃ፡አድርገኝም፤በሕይወት፡ምንጭ፡ዘንድ፡
አኑረኝ፤አንተ፡የሕይወት፡ምንጭ፡ነህና።
፲፰፡ ሌሎች፡በጎች፡አሉኝ፤አመጣቸው፡ዘንድ፡
አለኝ፤እነርሱም፡አንድ፡መንጋ፡ይሆናሉ፡
ያልክ፡ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡
ቡሩካን፡ፍጹማን፡ከሆኑ፡በጎችህ፡ጋር፡
አንድ፡አድርገኝ።
፲፱፡ ጌታዬ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሆይ፡የጠፋውን፡
በግ፡አዳምን፡ተድላ፡ደስታ፡ወዳለበት፡ገነት፡
የመለስከው፡አንተ፡ነህ።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወረሰይኮሙ፡ ለደቂቀ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡
ይሰብሑ ፡ በቃል ፡ ማሕየዊ ፡ ወበልሳን ፡
እሳታዊ፡ዘያንበለብል፡ወይልህብ።

ወይትዋነዩ ፡ በእንዚራ ፡ አምላካዊት ፡
ቃላሕከ፡ ቃላቲሆሙ ፡ ምስለ ፡ ቃለ ፡
መላእክት፡ ወአስተዋሐድከ ፡ መላእክተ ፡
ምስለ፡ደቂቀ፡ዕጓለ፡እመሕያው፡ወዐረቀ፡
ማእከሌሆሙ ፡ እስመ ፡ ብከ ፡ ኮነ ፡ ዕርቅ ፡
ወሰላም።

ሀበኒ፡ውእተ፡ሰላመከ፡ወዕርቀኒ፡ምስለ፡
አቡከ፡ወመላእክቲከ፡ቅዱሳን።

አ፡እግዚእየ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ዘተረግዘ፡
ገቦከ፡በኲናት፡ወወጽአ፡እምኔሁ፡ደም፡
ወማይ ፡ አስተየኒ ፡ ወፌውሰኒ ፡ በዝንቱ ፡
ፈልፈለ ፡ ነቅዐ ፡ ማይ ፡ ዘቦቱ ፡ ቀደስኮ ፡
ለዓለም።

እምገቦ፡አዳም፡ወፅአት፡ሔዋን፡ወወለደት፡
እንጋደ፡ምድር።

ወከማሁ፡አውፃእከ፡እምገቦከ፡ማሕየዊት፡
ዘተወለድነ፡ውሉደ፡ለመንግሥተ፡ሰማይ።

ለደኒ፡እምዛቲ፡እምከመ፡እረስ፡ሕይወተ፡
እንተ፡አልባቲ፡ማኅለቅት፡ወእሕየው፡ብከ፡
ወእረስ ፡ ሕይወተ ፡ በስምከ ፡ ወስምከ ፡
ይትለካእ፡ውስተ፡ልብየ።

ወያውሕዝ፡ላቲ፡ለነፍስየ፡ሕይወተ፡እስመ፡
ነቅዐ፡ሕይወት፡ውእቱ፡ስምከ፡ለኵላ፡ነፍስ፡
ዘይትኀነተም፡ውስቴታ፡ይምላእ፡ሕይወተ፡
ወብርሃነ።

ወኵላ ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ ትከውን ፡ ዕር
ቅተ ፡ እምኔከ ፡ ትነብር ፡ ውስተ ፡ ጸናፌ ፡
ዕሙቅ ፤ ሀበኒ ፡ ስመከ ፡ ይባዕ ፡ በው
ሳጤ ፡ ሕሊናየ ፡ ወአድኅኖ ፡ ለልብየ ፡
እምድቀተ፡ኅሊናት።

ወአንቅሖ ፡ ለሰብሖ ፡ ስምከ ፡ ቅዱስ ፡
ወአልብሰሙ፡ለኅሊናየ፡ወለልቡናየ፡ስርጋዌ፡
ጽዕድወ፡ከመ፡ይሰብኩ፡ወይበሉ፡ተንሥአ፡
እግዚአብሔር፡ ወአንሥአነ፡ምስሌሁ።

ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፤ የሰው፡ልጆችንም፡ሕያው፡በሆነ፡ቃል፡በሚ
ንበለበልና፡በሚያላልብ፡አንደበት፡እንዲያ
መሰግኑ፡ያደረግሃቸው።

፳፩፤ በአምላካዊት፡ በገናም፡እንዲያመሰግኑ፤ቃላ
ቸውንም፡ከመላእክት፡ቃል፡ጋር፡አንድ፡
አደረግህ፤ መላእክትንና ፡ ሰውን ፡ አንድ ፡
ማኅበር፡አደረግህ፤በመካከልም፡ሁነህ፡አስ
ታረቅህ፤ፍቅር፡አንድነትና፡ዕርቅ፡በአንተ፡
ሁኖአልና።

፳፪፤ ያንን ፡ ሰላምህን ፡ ስጠኝ ፤ ከአባትህና ፡
ከቅዱሳን፡መላእክቶችህም፡ጋር፡አስታርቀኝ።

፳፫፤ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ጎንህ ፡
በጦር፡ ተወግቶ ፡ ከእርሱ ፡ ደምና ፡ ውኃ ፡
የወጣ፡ዓለምን፡በአነጻሕበት፡ከዚህ፡የውኃ፡
ምንጭ፡አጠጥተህ፡አድነኝ።

፳፬፤ ከአዳም ፡ ጐን ፡ ተገኝታ ፡ ሔዋን ፡ የምድር ፡
ነገዶችን፡ወለደች።

፳፭፤ እንዲሁም ፡ ከማሕየዊት ፡ ጐንህ ፡ ለመን
ግሥተ፡ሰማይ፡ልጆች፡ልንሆን፡የምትወል
ደንን፡የሕይወት፡ውኃ፡አወጣህ።

፳፮፤ ፍጻሜ፡የሌላትን፡ሕይወት፡ወርሼ፡በአንተ፡
ሕያው ፡ ሁኜ ፡ እኖር ፡ ዘንድ ፡ በስምህም ፡
ሕይወትን፡እወርስ፡ዘንድ፡ከዚች፡እናት፡
(ጥምቀት) ፡ ውለደኝ ፤ ስምህም ፡ በልቤ ፡
ውስጥ፡ይጻፍ።

፳፯፤ ይህ፡ስምህም፡የሕይወት፡ምንጭን፡ለነፍሴ፡
ያፍስላት፤ስምህ፡የሕይወት፡ምንጭ፡ነውና፤
ስምህ ፡ የሚቀረዕባት ፡ ሰውነት ፡ ሁሉ ፡ ዕው
ቀት፡ሕይወትና፡ብርሃን፡በውስጧም፡ይምላ።

፳፰፤ ከአንተም፡ተራቀኊታ፡የምትኖር፡ሰውነት፡
ጥልቅ ፡ በሆነ ፡ የድንቁርና ፡ ዳርቻ ፡
ትኖላለች፤ስምህ፡በልቡናዬ፡ውስጥ፡ይገባ፡
ዘንድ ፡ ስጠኝ ፤ ልቡናዬንም ፡ በኀሳብ ፡
ከመውደቅ፡አድነው።

፳፱፤ የከበረ ፡ ስምህንም ፡ ለማመስገን ፡ አንቃው ፤
ኅሳቤንና፡ልቤን፡ብሩህ፡ዕውቀትን፡አሳድርባ
ቸው፡እግዚአብሔር፡ ተነሣ፡እኛንም፡ከእርሱ፡
ጋር፡አስነሣን፡እያሉ፡ይሰብኩ፡ዘንድ።

ልመናው፡በረከቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እምድርሳነ፡ቅዱስ፡ቄርሎስ።

፩፡ ጰላድዮስ፡ይቤ፡ዘእምእግዚአብሔር፡አብ፡ በአማን፡ወልድ፡ዘውእቱ፡ዋሀድ።

፪፡ ቄርሎስ፡ይቤ፡አላ፡ባሕቱ፡ጳውሎስ፡ክቡር፡ ዐቃቤ፡ምሥጢር፡ዘኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከመ፡ ኮሉ፡ተገብረ፡ውስተ፡ሀልዎ፡ወከመ፡ አሐዱ፡ውእቱ፡ባሕቲቱ።

፫፡ ወተዘከር፡ቅድመ፡አመ፡ንትረአይ፡በእንተ፡ ስም፡ዘይቤ፡ክርስቶስ፡ፈከርናሁ፡ከመ፡ በእንተ፡ቅብዓት፡ተሰምየ፡ክርስቶስ፡እስመ፡ ክርስቶስ፡ብሂል፡ቅቡዕ፡በመንፈስ፡ቅዱስ፡ ብሂል፡ይእዜ፤እመ፡አኮ፡ይበሉ፡ዘእምእግዚ አብሔር፡አብ፡ቃል፡ከመ፡በሕላዌሁ፡ ተቀብዐ፡ወጽሕቀ፡ቅድሳተ፡ዘእመንፈስ፡ ውስተ፡ፍና፡ዘእምኔሁ፤ወእመ፡አኮ፡ ለያርእዩነ፡እፎ፡ይሰመይ፡ክርስቶስ፡ዘኢተ ቀብዐ።

፬፡ ጰላድዮስ፡ይቤ፡ተውህበ፡ይብሉ፡ዋሀድ፡ እምአብ፡አኮ፡ከመ፡ይሕምም፡በሕላዌ፡ ዚአሁ፡አላ፡ከመ፡የአዝዝ፡በእንቲአነ።

፭፡ ቄርሎስ፡ይቤ፡ግሙራ፡ኢየሐምም፡ በሕላዌሁ፡እስመ፡አመ፡ዘእንበለ፡ሥጋ፡ ውእቱ፡አፍአ፡ውእቱ፡እምሕማም፡አላ፡ እስመ፡በእንተ፡ቃሉ፡በዳዊት፡ዘማሪ፡ ሥጋሰ፡ፈጠርከ፡ሊተ።

፮፡ ኢፈጠረ፡ሎቱ፡ሥጋ፡እምአብ፡አላ፡መጽአ፡ በሥጋ፡ከመ፡ይግበር፡ፈቃዶ፡ዘውእቱ፡ መድኃኒት፡መስቀል፡እንተ፡ቦቱ፡ተገብረት።

፯፡ ጳውሎስኒ፡የኀብር፡ምስለ፡ዝንቱ፡ነገር፡ እንዘ፡ይብል፡ዘንተ፡እመኑ፡ኵልክሙ፡ዘበክ ርስቶስ፡ኢየሱስ፡ዘበአርአያ፡እግዚአብሔር፡ ውእቱ።

፰፡ ወአኮ፡በመሚጥ፡ዘኮነ፡ዕሩየ፡ምስለ፡እግዚአ ብሔር፡አላ፡ርእሶ፡ሰዊጦ፡ወአርአያ፡ገብር፡ ነሢአ፡ኮነ፡በአምሳለ፡ሰብእ፡ወአትሐተ፡ ርእሶ፡ወኮነ፡ሰማዒ፡እስከ፡ለሞት፡ወሞቱሂ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ከቅዱስ፡ቄርሎስ፡ድርሳን፡የተገኘ፡ይህ፡ነው።

፩፡ ጰላድዮስ፡እንዲህ፡አለ፤በእውነት፡ከእግዚአ ብሔር፡አብ፡የተወለደ፡ወልድ፡እርሱ፡ አንድ፡ነው።

፪፡ ቄርሎስም፡የኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ምሥጢር፡ የሚጠብቅ፡ክቡር፡ጳውሎስ፡በእርሱ፡ ቃልነት፡ካለመኖር፡ወደመኖር፡ሁሉም፡ እንደ፡ተፈጠረ፡እርሱ፡አንድ፡ብቻ፡ እንደሆነ፡ነው፡እንጂ፡አለ።

፫፡ ክርስቶስም፡ስለሚለው፡ስም፡አስቀድመህ፡ አስብ፤ሥጋን፡ስለመዋሐዱ፡እንደተረጐ ምነው፤ሥጋን፡ስለመዋሐዱም፡ክርስቶስ፡ እንደተባለ፡አስብ፤ክርስቶስ፡ማለትም፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡አዋሐጅነት፡የከበረ፡ የባሕርይ፡አምላክ፡ማለት፡ነውና፤ይህም፡ ባይሆን፡ከእግዚአብሔር፡አብ፡በባሕርዩ፡ ከበረ፡ይሉ፡ዘንድ፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡ ክብርን፡ሊቀበል፡በባሕርዩ፡ተጋ፡የሚሉ፡ ሥጋን፡ያልተዋሐደ፡ክርስቶስ፡እንዴት፡ ይባላል፡እስቲ፡ያስረዱን፡አለ።

፬፡ ጰላድዮስም፡ዋሕድ፡ወልድ፡ከአብ፡ዘንድ፡ ተሰጠ፡ይላሉ፤ግን፡መከራ፡ሊቀበል፡ አይደለም፤ስለ፡እኛ፡ያገዝዝ፡ዘንድ፡ነው፡ እንጂ።

፭፡ ቄርሎስ፡መልሶ፡በባሕርዩ፡ከቶ፡አይታ መምም፡አለ፤ያለ፡ሥጋ፡በነበረ፡ጊዜ፡ ከሕማም፡የራቀ፡ነበርና፡በዘማሪው፡ዳዊት፡ አድሮ፡ሥጋን፡አዋሐድከኝ፡እንዳለው፡ እንደቃሉ፡ነው፡እንጂ።

፮፡ ሥጋን፡ከአብ፡ዘንድ፡አላመጣም፤ፈቃዱን፡ ያደርግ፡ዘንድ፡መጥቶ፡በሥጋ፡ተገለጠ፡ እንጂ፤ይኸውም፡በእርሱ፡የተደረገ፡ መድኃኒት፡መስቀል፡ነው።

፯፡ ጳውሎስም፡ሁላችሁም፡እግዚአብሔርን፡ በመልክ፡በሚመስለው፡በባሕርይ፡በሚተካ ከለው፡በኢየሱስ፡ክርስቶስ፡እመኑ፡ሲል፡ በዚህ፡ነገር፡አንድ፡ሁኖአል።

፰፡ ከእግዚአብሔር፡ጋር፡የተስተካከለው፡ በመቀማት፡አይደለም፤ራሱን፡ከሥጋ፡ አዋሕዶ፡የአዳምን፡ባሕርይ፡ገንዘብ፡አደረገ፡ ሰው፡ሁኖ፡ራሱን፡ዝቅ፡አድርጎ፡እስከ፡ሞት፡

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ዘበመስቀል።

፱ በእንቲአሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልዐሎ ፡ ወጸገዎ፡ስመ፡ዘመልዕልተ፡ኵሉ፡ስም፡ከመ፡ ለስሙ፡ለኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ይስግድ፡ኵሉ፡ ብርክ፡ዘበሰማይኒ፡ወዘበምድርኒ፡ወዘበማዕ ምቅትኒ፡ወልሳን፡ይግነይ፡ከመ፡እግዚእ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በስብሐተ ፡ እግዚአ ብሔር፡አብ።

፲ መኑ፡እንከ፡ትቤ፡ዘበአርአያ እግዚአብሔር፡ አብ ፡ ወመኑ ፡ ዕሩይ ፡ ምስሌሁ ፡ ዘእንበለ ፡ መሚጥ፤አኮኑ፡ዘእምኔሁ፡ተወልደ፡እግዚአ ብሔር፡ቃል፡ወለኵሉ፡ግሁድ፡ዝንቱ።

፲፩ ወባሕቱ፡ዝንቱ፡አርአያ፡ወዕሪና፡ዘእግዚአ ብሔር፡አርአያ፡ገብር፡ነሥአ።

፲፪ አኮ፡ዘአስተቃረቦ ፡ ለርእሱ ፡ አላ ፡ ቦቱ ፡ ኮነ ፡ ከማነ ፡ ሰብአ ፡ ወአትሐተ ፡ ርእሶ ፡ ወኮነ፡ሰማዔ፡እስከ፡ለሞት፡ወሞቱሰ፡ዘበመ ስቀል።

## ሃይማኖተ፡አበው።

ምዕ፤፳፯፡፲፩–፳፩።

ወካዕበ፡ይቤ፡ብፁዕ፡አትናቴዎስ፡ሐዋርያ፡ ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘእለእስክንድርያ።

፲፩ በእንተ፡ነፍሱ፡ወሥጋሁ፡ወርደቱ፡ለእግ ዚእነ፡ውስተ፡ሲኦል፡ወአዕርጎቱ፡ጻድቃነ።

፲፪ ኀየ፡ፀሐይ፡ወጸልመ፡ወርኅ፡ወከዋክብትኒ፡ ተኀብኡ ፡ ከመ ፡ ኢያብርሁ ፡ ለምዕመናን ፡ በጊዜ፡ስቅለቱ፡ቅዱስ፡እንዘ፡ፍጹም፡በገሃሁ፡ ወርኅ፡ኢያብርሀ።

፲፫ ወሶበ ፡ ጸልመ ፡ ፀሐይ ፡ ኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ጽልሙታነ ፡ ከመ ፡ ኢይነጽሩ ፡ አምላኮሙ ፡ ዘፈጠሮሙ ፡ ስቁለ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ ከመ ፡ ፈያት ፡ ተቈልቊለ፡ዕለት።

፲፬ ወወዕአ፡መልአክ፡ኀሩይ፡እማእከለ፡ኵሎሙ፡ መላእክት፡እንዘ፡ይእኀዝ፡በእዴሁ፡ሰይፈ፡ ከሡተ፡ከመ፡ያጥፍኦሙ፡ለዐላውያን፡ፍጡነ፡



ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ድረስ ፡ ለሞት ፡ ታዛዥ ፡ ሁኖ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሞቱም፡በመስቀል፡ነው።

፱ ስለ ፡ እርሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገው ፤ ከስም ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ስምንም ፡ ሰጠው ፤ ጉልበት ፡ ሁሉ ፡ በሰማይም ፡ በምድርም ፡ በባሕርም ፡ ያለ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ስም፡ይሰግድ፡ዘንድ፤እንደበትም፡ ሁሉ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ፡ጌትነት፡ጌታ፡እንደሆነ፡ያምን፡ዘንድ።

፲ እንግዲህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አርአያ ፡ ያለው ፡ ያለ፡መቀማት፤ከእርሱ፡ጋር፡በዕሪናው፡ያለ፡ ማነው ፡ ትላለህ ፤ ከእርሱ ፡ የተወለደ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ቃል ፡ አይደለምን ፤ ይህ ፡ ለሁሉ ፡ ግልጽ፡ነው።

፲፩ ነገር፡ግን፡የእግዚአብሔርን፡አርአያና፡ዕሪና፡ የተገገርን፡ባሕርይ፡ገንዘብ፡አደረገ፡እንጂ።

፲፪ በኀድረት ፡ አይደለም ፤ እንደ ፡ እኛ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፤ ራሱንም ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ እስከሞት ፡ ለመድረስ ፡ እሺ ፡ በጀ ፡ አለ ፤ ሞቱም፡በመስቀል፡ሆነ።

## የአባቶች፡ሃይማኖት።

ምዕ፤፳፯፡፲፩–፳፩።

የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሐዋርያዊ ፡ ብፁዕ፡አትናቴዎስ፡ዳግመኛ፡እንዲህ፡አለ።

፲፩ ጌታችን ፡ ስለ ፡ ነፍሱና ፡ ስለ ፡ ሥጋው ፡ ወደ ፡ ሲኦልም ፡ ስለመውረዱ ፡ ነፍሳትን ፡ ስለማ ውጣቱ፡ዳግመኛ፡እንዲህ፡አለ።

፲፪ ፀሐይ ፡ ብርሃኑን ፡ ነሣ ፤ ጨረቃም ፡ ጨለመ ፤ ከዋክብትም ፡ በከበረ ፡ ስቅለቱ ፡ ጊዜ ፡ ለምዕ መናን ፡ እንዳያበሩ ፡ ብርሃናቸውን ፡ ነሡ ፤ ጨረቃም፡በምልአት፡ሳለ፡አላበራም።

፲፫ ፀሐይ፡ብርሃኑን፡በነሣ፡ጊዜ፤ፍጡራን፡ሁሉ፡ በጨለማ ፡ ተያዙ ፤ የፈጠራቸው ፡ ፈጣሪ ያቸው፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ እንደ ፡ ወንበዴ ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ተሰቅሎ ፡ እንዳያዩ ፡ ቀኑ ፡ ጨለመ።

፲፬ ባለሟሉ ፡ መልአክም ፡ ከሐድያንን ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ሰይፉን ፡ በእጁ ፡ መዝዞ ፡ ይዞ ፡ ከመላእክት ፡ መካከል ፡ ወጣ ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወሶበ፡ክልኡቱ፡ምሕረቱ፡ለክርስቶስ፡ ዘበጦ፡
ዘከ ፡ መልአክ ፡ በሰይፉ ፡ ለመንጦላዕቱ ፡
ምኵራብ ፡ ወሠጠጠ ፡ ወረሰዮ ፡ ክልኤተ ፡
ክፍለ፡እምላዕሉ፡እስከ፡ታሕቱ።
፲፭ ወኵሎሙ፡መላእክት፡እንዘ፡ይኔጽርዎ፡እም
ሰማያት ፡ ወይትመዐዑ ፡ ኀቡረ ፡ ወናሁ ፡
ክልኢቶሙ፡ምሕረቱ፡ለአብ፡ ወትዕግሥቱ፡
ለወልድ፡ ወኂሩቱ፡ለመንፈስ፡ቅዱስ።
፲፮ ጐየ፡ብርሃነ፡መዐልት፡ወኀደጎ፡ለዓለም፡
ውስተ፡ጽልመት፡እንዘ፡ያመረስስ፡ወዝንቱ፡
ኵሉ ፡ ኮነ ፡ እምቅድመ ፡ ይመጡ ፡ ነፍሶ ፡
እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
፲፯ ወሶበ፡መጠወ፡ነፍሶ፡ሶቤሃ፡ሠረቀ፡ብርሃን፡
በውስተ ፡ ጽልመት ፡ ወሲኦል ፡ ፍጡነ ፡
ወወረደ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ውስተ፡ሲኦል፡በመንፈሱ፡ወአኮ፡በሥጋሁ።
፲፰ ተሀውከት፡ሲኦል፡ወደንገፀ፡መሠረታቲሃ፤
እኀዘ ፡ ኵላ ፡ ምድረ ፡ ከመ ፡ ኢትማስን ፡
እምቅድመ ፡ ጊዜሃ ፡ ከዐወ ፡ ደሞ ፡ ውስተ ፡
ምድር፡ወዐቀባ፡ወለኵሉ፡ዘውስቴታ።

፲፱ ወኀደገ፡ሥጋሁ፡ስቁለ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡
በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፤ ወመንፈሱሰ ፡
ወረደት፡ውስተ፡ሲኦል፡ወፈወሰት፡ነፍሳተ፤
እለ፡ሀለዋ፡ህየ፤ወዒወወት፡ሲኦለ፡ወአኀዘት፡
ኵሎ፡ፍጥረተ።
፳ ወሥጋሁ፡እንሥአ፡ሙታነ፡እለ፡ሀለዉ፡
ውስተ ፡ መቃብር ፤ ወነፍሱሂ ፡ ፈትሐት ፡
ነፍሳተ፡እንተ፡ሙቅሕቶን፡ይነብራ፡ውስተ፡
ሲኦል።
፳፩ ወበይእቲ፡ሰዓት፡እንዘ፡ሀሎ፡ሥጋሁ፡ለእግ
ነ፡ ስቁለ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ተከሥቱ፡
መቃብራት፡ወሶበ፡ነጸርዎ፡ጐዩ፡ዐቀብተ፡
ገሀነም፡ወተሰብሩ፡ሞ'ነተ፡ብርት፤ወተቀ
ጥቀጡ፡መናሥግቲሃ፡ዘኀጺን፤ወፈትሐት፡
ነፍሱ፡ቅድስት፡ነፍሳቲሆሙ፡ለጻድቃን፡
እለ፡ሀለዋ፡ውስተ፡ሲኦል፤ወለእግዚእነ፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ሎቱ፡ስብሐት፡ምስለ፡
ኄር፡አቡሁ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ ዘዕሩይ፡
ምስሌሁ፡ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

የክርስቶስም ፡ ቸርነቱ ፡ በከለከለችው፡ጊዜ፤
ያ፡ መልአክ ፡ የቤተ ፡ መቅደሱን ፡ መጋረጃ፡
በሰይፉ፡መታው፤ቀደደውም፤ከላይ፡እስከ፡
ታችም፡ከሁለት፡አደረገው።
፲፭ መላእክትም፡ሁሉ፡ከሰማይ፡ሁነው፡እርሱን፡
አይተው ፡ በአንድነት ፡ ሲቈጡ ፡ የአብ ፡
ምሕረቱ ፤የወልድ ፡ ትዕግሥቱ ፤የመንፈስ፡
ቅዱስ፡ ቸርነቱ፡ከለከለቻቸው።
፲፮ ፀሐይ፡ብርሃኑን፡ነሣ፤በጨለማ፡ተይዞ፡ሲድ
በሰበስ ፡ ዓለምንም ፡ ተወው ፤ ይህ ፡ ሁሉ፡
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነፍሱን ፡
ከሥጋው፡ከመለየቱ፡አስቀድሞ፡ተደረገ።
፲፯ ነፍሱን ፡ ከሥጋው ፡ በለየ ፡ ጊዜ ፤ ያን ፡ ጊዜ፡
በሲኦል ፡ ፈጥኖ ፡ ብርሃን ፡ ታየ ፤ጌታችን፡
በአካለ፡ሥጋ፡ያይደለ፡በአካለ፡ነፍስ፡ወደ፡
ሲኦል፡ሄደ።
፲፰ ሲኦል፡ተነዋወጠች፡መሠረቶቿም፡እፈርስ፡
እፈርስ ፡ አሉ ፤ ምድርን ፡ ያለ ፡ ጊዜዋ ፡ እንዳ
ታልፍ ፡ አጸናት ፤ ደሙን ፡ በምድር ፡ ላይ፡
አፈሰሰ ፤ ከኀልፈት ፡ ጠበቃት ፤ በርሷ ፡
ያለውንም፡ሁሉ፡ጠበቀ።
፲፱ ስለ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሥጋውን ፡ በመስቀል፡
ላይ ፡ እንደ ፡ ተሰቀለ ፡ ተወው ፤ ነፍሱ ፡ ግን፡
ወደ፡ ሲኦል ፡ ወርዳ ፡ ከዚያ ፡ ተግዘው ፡ የነበሩ፡
ነፍሳትን፡አዳነች፤ሲኦልንም፡በዘበዘች፤ፍጥ
ረትንም፡ሁሉ፡ገንዘብ፡አደረገች።
፳ ሥጋውም ፡ በመቃብር ፡ ያሉ ፡ ሙታንን፡
አስነሣ፤ነፍሱም፡በሲኦል፡ተግዘው፡የነበሩ፡
ነፍሳትን፡ፈታች።

፳፩ በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ የጌታችን ፡ ሥጋው ፡
በመስቀል ፡ ተሰቅሎ ፡ ሳለ ፡ መቃብራት ፡
ተከፈቱ ፤ ገሃነምን ፡ የሚጠብቁ ፡ አጋንንትም፡
ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ሸሹ ፤ የመዳብ ፡ ደጆች ፡ ተሰበሩ፤
(ሊቃነ፡አጋንንት)፡ሠራዊተ፡አጋንንት፡ደል፡
ተነሡ፤የብረት፡ቁልፎች፡ተቀጠቀጡ፤(ፍጻ፡
መርገም ፡ ጠፋ) ፤ ቅድስት ፡ ነፍሱ ፡ በሲኦል፡
ተግዘው፡የነበሩ፡የጻድቃንን፡ነፍሳት፡ፈታች፤
ከቸር፡አባቱ፡ከእርሱ፡ጋር፡አንድ፡ከሚሆን፡
ከመንፈስ፡ቅዱስ፡ ጋር፡ለጌታችን፡ለኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ ክብር፡ምስጋና፡ይግባው፤ዛሬም፡
ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ምዕ፤፳፯፤፳፩–፴።

ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ በውስተ ፡ ድርሳኑ ፡ ዘደረሰ ፡
፳፩ በእንተ ፡ ሕማሙ ፡ ማሕየዊት ፡ ተሰቅለ ፡
ወወሀበነ ፡ መድኃኒተ ፡ ወበሞቱ ፡ አሕየወ ፡
ኵሎ፡ሙታነ።
ነጽር ፡ ይእዜኒ ፡ ወስማዕ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡
፳፪ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ኅቡረ ፤ ሶበሰ ፡ አምላክ ፡
ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ እፎኑ ፡ እምሐመ ፡ አው ፡
እፎኑ፡እምሰቀልዎ፡አው፡እፎ፡እምጥዕመ፡
ሞተ፡እስመ፡ዝንቱ፡ግብር፡ርኁቅ፡ውእቱ፡
እምእግዚአብሔር።
፳፫ ወሶበሂ፡ሰብእ፡ውእቱ፡ባሕቲቱ፡እፎኑ፡ሶበ፡
ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ሞአ ፡ ለሞት ፡ ወአድኀነ ፡
ካልአነ፡ወአሕየዎሙ፤ወዝንቱ፡ይትሌዓል፡
እምኀይለ፡ዕጓለ፡እመሕያው።
፳፬ እስመ፡ውእቱ፡ሐመ፡ወሞተ፡ወአድኀነ፡
ፍጥረቶ ፡ ወሞአ ፡ ለሞት ፡ እስመ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ውእቱ፡ወካዕበ፡ሰብእ፡ውእቱ።
፳፭ ወካዕበ፡ይቤ፡እስመ፡ሥጋ፡ኢኮነ፡ፍጻሜ፡
ለታሕጻጸ ፡ አካለ ፡ መለኮት ፡ አላ ፡ ፍጹም ፡
ውእቱ፡ መለኮት ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ወይሁብ ፡
ፍጻሜ፡ለኵሉ፡ሕጸጽ።

፳፮ ወሶበ፡ለብሰ፡ሥጋ፡ኮነ፡አሐደ፡ምስሌሁ፡
ወዘኢይፈቅድ፡ኅበ፡ወኢምንትኒ፡መጠወ፡
ርእሶ፡ባሕቲቶ፡በሥጋ፡ዘይፈቅድ።

፳፯ ይቤ፡ዮሐንስ፡አፈ፡ወርቅ፡ጠቢብ፡ከማሁኬ፡
ይእዜ ፡ ይትከሀለነ ፡ ንሩጽ ፡ በትዕግሥት ፡
በከመ፡ፈቀድነ፡ወንትልዎ፡ለክርስቶስ።

፳፰ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ወንትልዎ ፡ ለፍጹም ፡
መልአክነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ርእሰ፡አሚን፡
ዝ፡ብሂል ፡ ዘኀረየነ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ በከመ ፡
ይቤሎሙ ፡ አኮ ፡ አንትሙ ፡ ዘኀረይክሙኒ ፡
፳፱ አላ፡አነ፡ኅረይኩክሙ።
ውእቱሰ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወጠነ ፡ ግብረ ፡
ወለሊሁ፡ካዕበ፡ይፌጽም።
፴ ይቤ ፡ ዘተዐገሠ ፡ ኀፍረተ ፡ መስቀል ፡
አናሕሲዮ፡በእንተ፡ፍሥሐሁ፡ዘጽኑሕ፡ሎቱ፡
ወመነና፡ለኃፍረት፡ዝ፡ብሂል፡ሶበ፡ፍጹመ፡
ኢፈቀደ ፡ እምኢሐመ ፡ እስመ ፡ ኢአበሰ ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ምዕ፤፳፯፤፳፩–፴።

፳፩፤ ዳግመኛም፡ሕይወት፤መድኃኒት፡የምትሆን፡
የሕማሙን ፡ ነገር ፡ በተናገረበት፡ መጽሐፉ ፡
እንዲህ ፡ አለ ፤ ተሰቅሎ ፡ ድኅነትን ፡ ሰጠን ፤
በሞቱም፡ሙታንን፡ሁሉ፡አዳነ።
፳፪፤ አሁንም ፡ በተዋሕዶ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አምላክ ፡
እንደሆነ ፡ ሰምተህ ፡ ዕወቅ ፤ አምላክ ፡ብቻ ፡
ከሆነማ፡እንደምን፡በታመመ፡ነበር?ወይስ፡
እንደምን ፡ በሰቀሉት ፡ ነበር ? ወይስ ፡
እንደምን፡በሞተ፡ነበር?ይህ፡ሥራ፡(ሕማም፡
ሞት)፡ከእግዚአብሔር፡የራቀ፡ነውና።
፳፫፤ ሰው፡ብቻ፡ከሆነም፡በታመመ፤በሞተ፡ጊዜ፡
ሞትን ፡ እንደምን ፡ ድል ፡ በነሣው ፡ ነበር ፤
ሌሎችንስ፡በነፍስ፡በሥጋ፡እንደምን፡ባዳነ፡
ነበር፤ይህ፡ከሰው፡ኃይል፡በላይ፡ነውና።
፳፬፤ እርሱ ፡ ታሞ ፡ ሞቶ ፡ ፍጥረቱን ፡ አዳነ ፤
ሞትንም፡ድል፡ነሣ፤ሰው፡የሆነ፡አምላክ፡
ነውና፤ዳግመኛም፡ሰው፡ነውና።
፳፭፤ ዳግመኛም ፡ ለአካለ ፡ መለኮት ፡ ሕጸጽ ፡
ኖሮበት ፡ ሥጋ ፡ ምልአት ፡ የሆነው ፡
አይደለም፤ መለኮት ፡ በአካልም ፡ በክብርም ፡
ፍጹም ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ሕጸጽ ፡ ላለበት ፡ ሁሉ ፡
ፍጹምነትን፡ይሰጣል፡እንጂ፡አለ።
፳፮፤ ሥጋንም ፡ ቢዋሐድ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡
አካል፡አንድ፡ባሕርይ፡ሆነ፤ከምንም፡ምን፡
የማይሻ፡ መለኮት፡በሚሻ፡ሥጋ፡እርሱ፡ብቻ፡
ራሱን፡ለሕማም፡ለሞት፡አሳልፎ፡ሰጠ።

፳፯፤ ብልህ ፡ አዋቂ ፡ የሆነ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ዮሐንስ ፡
እንዲህ፡አለ፤እንደዚሁም፡በመታገሥ፡እንደ
ወደድን፡አሁን፡እንሮጥ፡ዘንድ፡ይቻለናል፤
ክርስቶስንም፡ልንመስለው፡ይቻለናል።
ዳግመኛም፡የእምነታችን፡ራስ፡የሆነ፡አበጋዛ
፳፰፤ ችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንከተለው ፤
ይህም፡ማለት፡የመረጠን፡ማለት፡ነው፤ለደቀ፡
መዛሙርቱ ፡ እናንተ ፡ የመረጣችሁኝ ፡ አይደ
ለም፤እኔ፡መረጥኋችሁ፡እንጂ፡እንዳላቸው።
፳፱፤ የክብር፡ባለቤት፡እርሱስ፡የቸርነቱን፡ሥራ፡
ጀመረ፤ደግሞም፡እርሱ፡ይፈጽማል።
ተጠብቆለት ፡ ስላለ ፡ ድኅነተ ፡ ምእመናን ፡
፴፤ መከራውን፡ንቆ፡አቃሎ፡መከራ፡መስቀልን፡
የታገሠ ፡ ኀፍረተ ፡ መስቀልን ፡ ይሁንብኝ ፡
ብሎ ፡ ተቀበለ ፡ አለ ፤ ይህንንም ፡ ማለት ፡

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወኢተረክበ፡ሐሰት፡ውስተ፡አፉሁ፡በከመ፡ ይቤ፡ለሊሁ፡በወንጌል፡ቅዱስ፡ወይመጽእ፡ መልአኩ፡ ለዝንቱ፡ ዓለም፡ ወኢይረክብ፡ በላዕሌየ፡ወኢምንተኒ።

፳፬፡ ናሁኬ ፡ ይትከሀሎ ፡ ሶበ ፡ ኢፈቀደ ፡ ኢምኢሐመ፡በዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡እስመ፡ ይቤ፡አነ፡እሜጥዋ፡ለነፍስየ፡በፈቃድየ፡ ብውሕ፡ሊተ፡እንብራሂ፡ወብውሕ፡ሊተ፡ እንሥእ።

፳፭፡ እመሰኬ፡ተሰቅለ፡በፈቃዱ፡ዘእንበለ፡ግብር፡ በእንቲአነ፡ወሚመጠነ፡ይደልወነ፡ለነኒ፡ ንትዐገሥ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ምንዳቤያት፡በዐቢይ፡ ጥብዐት።

፳፮፡ ይቤ፡ዘተፀገሠ፡ኀፍረተ፡መስቀል፡አናኅስዮ፡ በእንተ፡ፍሥሐሁ፡ዘጽኑሕ፡ሎቱ፡ወመነና፡ ለኀፍረት ፤ ዝ ፡ ብሂል ፡ ሐረያ ፡ ለሞት ፡ ወአብደረ፡ጽዕለተ፡ውኀሳረ፡እንዘ፡አልቦ፡ ላዕሌሁ፡ምንትኒ፡ምክንያት፡ፈቂዶ፡ከመ፡ ይምሐረነ፡መንኖ፡ክብር፡ዘሰብእ፡በከመ፡ ለሊሁ፡መነና፡ለኀፍረት።

፳፯፡ እመቦ፡ዘይብል፡ለምንት፡ኢይቤ፡መነና፡ ለኀሳር፡አላ፡ይቤ፡መነና፡ለኀፍረት፤ንብሎ፡ ዘንተ ፡ ዘይቤ ፡ በእንተ ፡ ዘኢተወክፈ ፡ ሕማማተ ፡ መስቀል ፡ በግብር ፡ እንዘ ፡ የሐምም፡ወየሐዝን።

፳፰፡ ወለእመ፡ትቤለኒ፡ምንተ፡ኮነ፡እንከ፡እብለከ፡ ናሁ፡ነበረ፡በየማነ፡እግዚአብሔር።

፳፱፡ ርኢከኑ፡አ፡ፍቁርየ፡ዘከመ፡ይቤለከ፡ብፁዕ፡ ጳውሎስ ፡ ወበእንተዝ ፡ አዕበዮ ፡ እግዚአብሔር፡ ወጸገዎ፡ስመ፡ዘየዐቢ፡እምኵሉ፡ ስም፡ ከመ፡ ለስሙ፡ ለኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ይሰግድ፡ኵሉ፡ብርክ።

አንቀጽ፡ዕሥራ፡ወተሰዓቱ።

እመጽሐፈ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ዘአበዊነ ፡ ሐዋርያት ፡ በረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ፈቅዶ፡ባይሆን፡ባልታመመም፡ነበር፤እርሱ፡ ራሱ፡በከበረ፡ወንጌል፡የዚህ፡ዓለም፡ገዥ፡ ይመጣል፤በእኔ፡ላይ፡ምንም፡ምን፡አያገኝም፡ እንዳለ፤አልበደለምና፡በአንደበቱም፡ሐሰት፡ አልተገኘምና።

፳፬፡ እነሆ፡ፈቃዱ፡ባይሆንስ፡ኑሮ፡በዕንጨት፡ መስቀል፡ተሰቅሎ፡መከራን፡ላለመቀበል፡ ይቻለው ፡ ነበር ፤ እርሱ ፡ እኔ ፡ በፈቃዴ፡ ነፍሴን፡ከሥጋዬ፡ልለያት፡ሥልጣን፡አለኝ፤ ደግሞ ፡ ከሥጋዬ ፡ አዋሕጄ ፡ ላስነሣት ፡ ይቻለኛል፡ብሎአልና።

፳፭፡ ግዴታ ፡ ሳይኖርበት ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ወዶ፡ ከተሰቀለ፤በመከራው፡ሁሉ፡ላይ፡በፍጹም፡ ብርታት፡ልንታገሥ፡ለእኛ፡ምን፡ያህል፡ ይገባን፡ይሆን?

፳፮፡ መከራ፡መስቀልን፡ታግሦ፡የተቀበለ፤ተጠብ ቆለት፡ስላለ፡ድኅነተ፡ምዕመናን፡መከራውን፡ ንቆ፤አቃሎ፡ይሁንብኝ፡ብሎ፡አለ፤ይህንንም፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖር ፡ ሞትን፡ መሰደብን፡መዋረድንም፡መረጠ፡ማለት፡ነው፤ እርሱ፡ኃፍረትን፡ንቆ፡አቃሎ፡የተቀበላት፡ ከሰው፡ዘንድ፡የሚሆነውን፡ውዳሴ፡ከንቱ፡ መናቅን፡ያስተምረን፡ዘንድ፡ወዶ፡ነው።

፳፯፡ ኀፍረትን ፡ ናቃት ፡ አለ ፡ እንጂ ፤ ለምን፡ መሰደብን፡ናቃት፡አላለም፤የሚል፡ቢኖር፡ ሕማማተ ፡ መስቀልን ፡ ፈጽሞ ፡ እያዘነ፡ በግድ፡ስላልተቀበለ፡ይህን፡አለ፡እንለዋለን።

፳፰፡ አሁንስ፡እንዴት፡ሆነ፡ብትለኝ፡እኔ፡እነሆ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዕሪና ፡ ተቀመጠ፡ እልሃለሁ።

፳፱፡ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ የተመሰገነ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ሚልህ፡ሰማህን? ስለዚህም፡እግዚአብሔር፡ ፈጽሞ ፡ አከበረው ፤ ከስም ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ፡ ስም፡ ሰጠው ፤ ጉልበት ፡ ሁሉ ፡ ለኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ስም፡ይሰግድ፡ዘንድ።

አሥራ፡ዘጠነኛው፡አንቀጽ፡ይህ፡ነው።

ልመናቸው፡በረከታቸው፡ለዘላለሙ፡ከእኛ፡ ጋር ፡ ይኑርና ፡ አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት፡ ከሰሩት፡የሥርዓት፡መጽሐፍ፡የተገኘ።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፩ ወእምዝ ፡ ሰሰለ ፡ ጽልመት ፡ ወአስተርአየ ፡ ብርሃን ፡ በምሴት ፡ ወበጊዜ ፡ ተሱዓት ፡ ሰዓት ፡ ገዐረ ፡ ኢየሱስ ፡ በዐቢይ ፡ ቃል ፡ ወይቤ ፡ ኤሎሂ ፡ ኤሎሂ ፡ ኤልማስ ፡ ላማ ፡ ሰበቅታኒ ፡ ዘበ ትርጓሜሁ ፡ ይብል ፡ አምላኪየ ፡ አምላኪየ ፡ ለምንት ፡ ኀደገኒ።

፪ ወእምዝ ፡ ካዕበ ፡ ጸርሐ ፡ ወይቤ ፡ አባ ፡ ሥረይ ፡ ሎሙ ፡ እስመ ፡ በዘኢየአምሩ ፡ ይገብሩ።

፫ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ኦ ፡ አባ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ አመሐፅን ፡ ነፍስየ።

ወእምዝ ፡ አጽነነ ፡ ርእሶ ፡ ወወፅአት ፡ መንፈሱ ፡ ሶቤሃ።

በረከቶሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን።

ድርሳን ፡ ወትምህርት ፡ ዘአበው ፡ ሐዋርያት ፡ ዘመሀሩነ።

፩ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ፈጸመ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ኵሎ ፡ ዘይቤሎሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ጸማእኩ።

፪ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ ሰበቁ ፡ ሰፍነገ ፡ ዲበ ፡ ከል ፡ ወሐሞት ፡ ዘምስለ ፡ ከርቤ ፡ ኅዉሥ።

፫ ወአሰሩ ፡ በኀለት ፡ ወአጸሩ ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ ወኢፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይስተይ ፡ በከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ኵሉ ፡ ዘተብህለ ፡ በእንቲአሁ።

፬ አጽነነ ፡ ርእሶ ፡ መንገለ ፡ የማን ፡ ኀበ ፡ ፈያታዊ ፡ ዘየማን ፡ ወወፅአት ፡ መንፈሱ።

፭ ወሶቤሃ ፡ መጽአ ፡ ድልቅልቅ ፡ ወጣቃ ፡ ወጽልመት ፡ ወጸልመ ፡ ፀሐይ ፡ ወወርኅ ፡ ደመ ፡ ኮነ ፡ ወተከሥቱ ፡ መቃብራት ፡ ወተንሥኡ ፡ ምውታን ፡ ወተፈተቱ ፡ አድባር።

፮ ወወድቁ ፡ አክሊላተ ፡ መላእክት ፡ እምአርእስቲሆሙ ፡ ወተሀውኩ ፡ ኵሉ ፡ ኀይለ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ስቁለ ፡ ለእግዚአሙ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ወፈቀዱ ፡ ይቅሥፍዋ ፡ ለምድር ፡ ወሥምረቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኢኀደጎሙ ፡ ይቅሥፍዋ ፡ ለምድር።

፯ ወዝ ፡ ኵሉ ፡ ዘኮነ ፡ እምስድስቱ ፡ ሰዓት ፡ እስከ ፡ ተሰዓቱ ፡ ሰዓት ፡ ዘዓርብ።

ዓርብ ፡ መዓልት ፡ በ፱ ፡ ሰዓት።

፩፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጨለማው ፡ ተወግዶ ፡ በምሽት ፡ ብርሃን ፡ ታየ ፤ በዘጠኝ ፡ ሰዓትም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኤሎሄ ፡ ኤሎሄ ፡ ኤልማስ ፡ ላማ ፡ ሰበቅታኒ ፡ አለ ፤ ትርጓሜውም ፡ አምላኪየ ፡ አምላኪየ ፡ ለምን ፡ ተውከኝ ፡ ማለት ፡ ነው።

፪፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ የማያውቁትን ፡ ይሠራሉና ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፡ ብሎ ፡ አሰምቶ ፡ ተናገረ።

፫፤ ዳግመኛም ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ነፍሴን ፡ በእጅህ ፡ አደራ ፡ አስጠብቃለሁ ፡ አለ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ራሱን ፡ ዘንበል ፡ አድርጎ ፡ ነፍሱን ፡ ከሥጋው ፡ ለየ።

የሐዋርያት ፡ በረከታቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ይኑር ፡ አሜን።

አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ ያስተማሩን ፡ ትምህርትና ፡ ድርሳን ፡ ይህ ፡ ነው።

፩፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለአይሁድ ፡ የተናገረውን ፡ ሁሉ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ተጠማሁ ፡ አለ።

፪፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ሰፍነጉን ፡ ከሐሞትና ፡ ከከርቤ ፡ ከተቀላቀለው ፡ መፃፃ ፡ ውስጥ ፡ ነከሩት።

፫፤ በዘንግ ፡ ላይም ፡ አሥረው ፡ ከአፉ ፡ ላይ ፡ አገናኙት ፡ ጨመቁት ፤ ሊጠጣም ፡ አልወደደም ፤ ስለ ፡ እርሱ ፡ የተባለው ፡ ሁሉ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ሆነ።

፬፤ በቀኙ ፡ ወደ ፡ አለው ፡ ፈያታዊ ፡ ወደ ፡ ተሰቀለበትም ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ራሱን ፡ ዘንበል ፡ አደረገ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነፍሱም ፡ ከሥጋው ፡ ተለየች።

፭፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ድቅድቅ ፡ ጨለማና ፡ ንውጽውጽታ ፡ ሆነ ፤ ፀሐይ ፡ ጨለመ ፤ ጨረቃም ፡ ደም ፡ ሆነ ፤ መቃብሮች ፡ ተከፈቱ ፤ ሙታኖች ፡ ተነሡ ፤ ደንጊያዎችም ፡ ተፈረካከሱ።

፮፤ የመላእክትም ፡ አክሊሎች ፡ ከራሳቸው ፡ ላይ ፡ ወደቁ ፤ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ሠራዊትም ፡ ጌታቸውን ፡ በእንጨት ፡ ላይ ፡ ወዶ ፡ ተሰቅሎ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ምድርን ፡ ያጠፏት ፡ ዘንድ ፡ ወደዱ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቸርነቱ ፡ ምድርን ፡ ያጠፏት ፡ ዘንድ ፡ አላሰናበታቸውም።

፯፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሆነው ፡ ዐርብ ፡ ከስድስት ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ነው።

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፱፡ ወመጽኡ፡ ክልኤቱ፡ ሐራ፡ ከመ፡ ይስብሩ፡ ቊየጺሆሙ፡ ለእልክቱ፡ ፈያት፡ በከመ፡ አዘዞሙ፡ ጲላጦስ፡ መኰንን፡ ከመ፡ ያውርድዎሙ።

፴፡ ወሶቤሃ፡ ፈቀዱ፡ ይስብሩ፡ ቊየጺሁ፡ ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡እሉ፡ሐራ።

፴፩፡ ወውእቱ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡የአምር፡ ኵሎ፡ ዘሀሎ፡ይኩን፡ወዘከመ፡ይፈቅዱ፡ይስብሩ፡ ቊየጺሁ።

፴፪፡ ወሶበ፡ ርእዩ፡ ዘከመ፡ ተፈጸመ፡ ኵሉ፡ ወወጽአት፡ መንፈሱ፡ ኀደግዎ፡ ወኢሰበሩ፡ ቊይጸ፡ሐዘኑ፡ወተምዑ፡ፈድፋደ።

፴፫፡ ወዝንቱ፡ዘኮነ፡ከመ፡ይትፈጸም፡ዘጽሑፍ፡ በእንተ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ዘይቤ፡ ኢትስብሩ፡ዐፅሞ፡እምኔሁ።

፴፬፡ ወካዕበ፡ ይቤ፡ ሀለዎሙ፡ ይርአይዎ፡ ለዘወግእዎ።

፴፭፡ ወሐዘኑ፡ አይሁድ፡ ወነስሑ፡ በእንተ፡ ዘኢሰበሩ፡ቊይጸ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ ሎቱ፡ ስብሐት።

፴፮፡ ወአሐዱ፡እምሐራ፡ነሥአ፡ኲናቶ፡ስሑለ፡ ወቀርበ፡በመዐት፡ወወግአ፡ገቦሁ፡ዘየማን፡ ለመድኀኒነ፡ እምድኅረ፡ ሞተ፡ ወሶቤሃ፡ ውሕዘ፡ ደም፡ ወማይ፡ ወተነጽበ፡ ዕፀ፡ መስቀል፡ ወምድርኒ፡ ተነፅበት፡ በደሙ፡ ክቡር፡ ወዘርእየ፡ስምዐ፡ኮነ፡በእንቲአሁ።

፴፯፡ ወንሕነ፡ አእመርነ፡ ከመ፡ ስምዑ፡ እሙን፡ ውእቱ።

ላሓ፡ማርያም።

በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ አሐዱ፡ አምላክ፡ ድርሳን፡ ዘደረሰ፡ አባ፡ ሕርያቆስ፡ ኤጲስቆጶስ፡ ዘሀገረ፡ ብሕንሳ፡ በእንተ፡ ብካያ፡ ለድንግል፡ በዛቲ፡ ዕለት፡ ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

፩፡ ወሶበ፡በጽሐት፡ኀበ፡ቤቱ፡ለዮሐንስ፡ኢጎ

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፳፱፡ ጲላጦስ፡ እንደ፡ አዘዛቸው፡ የተሰቀሉትን፡ ጭን፡ ጭናቸውን፡ ይሰብሩ፡ ዘንድ፡ ሁለት፡ ወታደሮች፡ መጡ፤ያወርዱአቸውም፡ዘንድ፡ የሁለቱንም፡ ወንበዴዎች፡ ጭናቸውን፡ ሰበሩ።

፴፡ በዚያን፡ ጊዜም፡ የጌታችን፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ጭኖቹን፡ሊሰብሩ፡ወደዱ።

፴፩፡ እርሱ፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ግን፡ ሊሆን፡ ያለውን፡ ሁሉ፡ ጭኖቹን፡ ሊሰብሩ፡ እንደሚፈልጉ፡ያውቅ፡ነበርና።

፴፪፡ በአዩትም፡ ጊዜ፡ ነፍሱ፡ ከሥጋው፡ ተለይታ፡ ሁሉ፡ተፈጽሞ፡ሙቶ፡አገኙት፤ጭኑንም፡አል ሰበሩም፤ክፉዎች፡አይሁድም፡ጭኑን፡እንዳል ሰበሩ፡በአዩ፡ጊዜ፡አዘኑ፤እጅግም፡ተቆጡ።

፴፫፡ ይህም፡የሆነው፡ዐፅሙን፡ከእርሱ፡አትስበሩ፡ ተብሎ፡ ስለ፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ የተጻፈው፡ይደርስ፡ይፈጸም፡ዘንድ፡ነው።

፴፬፡ ሁለተኛውም፡ የወጉትን፡ ያዩት፡ ዘንድ፡ አላቸው፡አለ።

፴፭፡ አይሁድም፡ የክብር፡ ባለቤት፡ የሆነ፡ የጌታችን፡የኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ጭን፡ስለ፡ አልሰበሩ፡አዘኑ፤ተፀፀቱ።

፴፮፡ ከጭፍሮችም፡ አንዱ፡ የተሳለ፡ ጦሩን፡ ይዞ፡ በቁጣ፡ቀረብ፡ብሎ፡ከሞተ፡በኋላ፡የመድኃኒ ታችንን፡ ቀኝ፡ ጎኑን፡ ወጋው፤ ያን፡ ጊዜም፡ ደምና፡ ውኃ፡ ፈሰሰ፤የመስቀሉም፡ዕንጨት፡ ታጠበ፤ምድሪቱም፡በከበረ፡ደሙ፡ታጠበች፤ ያየውም፡(ዮሐንስ)፡ስለ፡እርሱ፡ምስክር፡ሆነ።

፴፯፡ እኛም፡ ምስክርነቱ፡ እውነት፡ እንደሆነ፡ አውቀናል።

የእመቤታችን፡ቅድስት፡ድንግል፡ ማርያም፡ሐዘን።

ልመናዋ፡ ክብሯ፡ ለዘላለሙ፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ይኑርና፤ አንድ፡ አምላክ፡ በሆነ፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ስም፡ አምና፡ የብህንሳ፡ ኤጲስቆጶስ፡ አባ፡ ሕርያቆስ፡ ስላለቀ ድንግል፡ ማርያም፡ እመቤታችን፡ ስላለቀ ሰችው፡ልቅሶ፡በዛሬው፡ቀን፡የደረሰው፡ይህ፡ ነው፤አሜን።

፩፡ ወደ፡ዮሐንስ፡ቤትም፡በደረሰች፡ጊዜ፡አልዘ

ንደየት ፡ እላ ፡ ጐጕአት ፡ ትሑር ፡ ቀራንዮ ፡
ወትነጽር ፡ ተፍጻሜተ ፡ ሕማማት ፡ ዘፍቁር ፡
ወልዳ።
ወሶበ፡አርመመ፡ከመ፡ይመጡ፡ነፍሶ፡በዲበ፡
፱ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ እንገለገት ፡ ኵላ ፡ ሀገር ፡
በእንተ፡ድልቅልቃት፡ዘኮና፡ላዕለ፡ምድር፡
ወመንክራት ፡ ወተአምራት ፡ ዘተገብሩ ፡
ውስተ ፡ ሰማይ ፤ ወሶበ ፡ ርእየት ፡ ድንግል ፡
እንዘ፡ ታድለቀልቅ ፡ ምድር ፡ ወትሰፍሕ ፡
ጽልመት፡ዲበ፡ኵላ፡ምድር፡ከልሐት፡እንዘ፡
ትብል ፡ ነዋ ፡ እሉ ፡ ተአምራት ፡ ትእምርተ ፡
ሞቱ፡ለወልድየ።
፲ ወእንዘ ፡ ትብል ፡ ከመዝ ፡ በጽሐ ፡ ዮሐንስ ፡
ካዕበ፡ወቆመ፡ኃቤሃ፡እንዘ፡ይበኪ።
፲፩ ወትቤሎ ፡ ድንግል ፡ እ ፡ ዮሐንስ ፡ በአማንኑ ፡
ሞተ፡ወልድየ፡በመልዕልተ፡መስቀል።
፲፪ ውእቱኒ ፡ አትሐተ ፡ ርእሶ ፡ ወይቤላ ፡ እወ ፡
ሞተ፡እ፡እምየ።
፲፫ ወእምድኅረዝ ፡ ኮነ ፡ እንከ ፡ ዐቢይ ፡ ብካይ ፡
ወላሕ ፡ ወሰቆቃው ፡ ወከላሕ ፡ ዐገታ ፡
ለድንግል ፡ በይእቲ ፡ ሰዓት ፡ ወትቤ ፡ እንዘ ፡
ትበኪ ፡ በምረተ ፡ ልብ ፡ ወይ ፡ ሊተ ፡ እ ፡
ወልድየ፡ እምዝንቱ ፡ ጻዕረ ፡ ሞት ፡ ዘረከበከ ፡
ኢረከብኩ ፡ ሊተ ፡ ሥዩመ ፡ ዘይኔጽር ፡ ዲበ ፡
ግፍዕየ ፡ ወኢ ፡ መኰንነ ፡ ፍትሕ ፡ ዘይፌትሕ ፡
ዲበ፡ስብረተ፡ልብየ፡በአእምሮ።
፲፬ ወሶበ ፡ ኮንከሰ ፡ ትኴንን ፡ በከመ ፡ ሕግ ፡ እ ፡
መኰንን፡እምኢሰቀልዎ፡ለወልድየ፡ንጉሥ፡
ሕዝበ ፡ አይሁድ ፡ እንዘ ፡ ርኁብ ፡ ወጽሙእ ፡
ውእቱ።
፲፭ ወሶበሰ፡ኮንከ፡ትፌትሕ፡በጽድቅ፡እ፡ሊቀ፡
ካህናት ፡ እምኮነ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይሙት ፡
ገብር፡ህየንተ፡እግዚኡ።
፲፮ ወሶበሰ ፡ ትኴንን ፡ በርትዕ ፡ እ ፡ ሥዩም ፡
እምኢኮነ ፡ ትስቅሎ ፡ ለወልድየ ፡ ህየንተ ፡
በርባን።
፲፯ ሶበሰ፡ኮንከ፡ትፌትሕ፡በጽድቅ፡አንተ፡ሊቀ፡
ካህናት ፡ እምኮነ ፡ ይሁዳ ፡ ለሞት ፡ ድልወ ፡
እምነ፡ወልድየ።
፲፰ ሶበሰ፡ኮነ፡ትጤይቅ፡ፍትሐ፡እ፡ሥዩም፡አኮ፡
መፍትው ፡ ትስቅሎ ፡ ለወልድየ ፡ ሥጋሁ ፡
ዕሩቀ።





የችም ፤ ወደቀራንዮ ፡ ተመልሳ ፡ ልትሄድ ፡
የተወዳጅ ፡ ልጅዋን ፡ የመከራውን ፡ ፍጻሜ ፡
ታይ፡ዘንድ፡ቸኰለች፡እንጂ።
፱ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ነፍሱን ፡ በፈቃዱ ፡ ሰጥቶ ፡
ዝም ፡ በአለ ፡ ጊዜ ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ስለሆነው ፡
ንውጽውጽታና ፡ በሰማይም ፡ ስለተደረጉ ፡
አስደናቂ ፡ ተአምራቶች ፡ ሀገሪቱ ፡ ሁሉ ፡
ተሸበረች፤ ድንግል ፡ እመቤታችንም ፡ ምድር፡
ስትናወጽ ፡ ጨለማም ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ስትሰ
ለጥን ፡ አይታ ፡ እነሆ ፡ እነዚህ ፡ ተአምራቶች ፡
የልጄ ፡ የሞቱ ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው ፡ ብላ ፡
ጮኸች።
፲ እንዲህ ፡ ስትልም ፡ ዳግመኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ደርሶ ፡
እያለቀሰ፡ከእርሷ፡ዘንድ፡ቆመ።
፲፩ ድንግል፡እመቤታችንም፡ዮሐንስ፡ሆይ፡በመስ
ቀል፡ላይ፡ልጄ፡በእውነት፡ሞተን፡አለችው።
፲፪ እርሱም፡ራሱን፡ዝቅ፡አድርጎ፡እናቴ፡ሆይ፡
አዎን፡ሞተ፡አላት።
፲፫ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ታላቅ ፡ ልቅሶ ፡ ሆነ ፤
በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ድንግል ፡ እመቤታችንን ፡
ፍጹም ፡ ጩኸትና ፡ ልቅሶ ፡ ጸናባት ፤ በመረረ ፡
ልቅሶም ፡ እየጮኸች ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ከዚህ ፡
ካገኘህ ፡ የሞት ፡ ፃዕር ፡ የተነሣ ፡ ግፌን ፡ የሚመ
ለከትልኝ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ በሐዘን ፡ የተሰበ
ረውን ፡ ልቤን ፡ አይቶ ፡ በማስተዋል ፡ የሚፈር
ድልኝ፡ዳኛ፡አላገኘሁም፡አለች።
፲፬ መኰንን ፡ ሆይ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ የምትፈርድስ ፡
ቢሆን፡ኖሮ፡ንጉሥ፡ልጄን፡እንደራበው፡እን
ደጠማው ፡ የአይሁድ ፡ ወገኖች ፡ ባልሰቀ
ሉትም፡ነበር።
፲፭ አንተም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በዕውነት ፡ ፈራጅ ፡
ብትሆን ፡ ባርያ ፡ በጌታው ፡ ፈንታ ፡ መሞት ፡
በተገባው፡ነበር።
፲፮ ሹም ፡ ሆይ ፡ በቅን ፡ የምትፈርድ ፡ ብትሆን ፡
ልጄን ፡ በበርባን ፡ ፈንታ ፡ ባልሰቀልከውም ፡
ነበር።
፲፯ አንተም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በዕውነት ፡ የምት
ፈርድ ፡ ብትሆን ፡ ከልጄ ፡ ይልቅ ፡ ይሁዳ ፡
ለሞት፡የተገባው፡በሆነ፡ነበር።
፲፰ ሹም ፡ ሆይ ፡ ፍርድን ፡ የምታውቅ ፡ ቢሆን ፡
ልጄን፡ሥጋውን፡አራቁተህ፡መስቀል፡ባልተ
ገባህም፡ነበር።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፪፡ ወሶበ፡ ኮንከ፡ ትፌትሕ፡ በርትዕ፡ አ፡ ሊቀ፡
ካህናት፡እምኢያድኅንከ፡ለፈያታዊ፡እምት፡
ወእምኢቀተልከ፡ለጻድቅ።
፲፫፡ ሶበሰ፡ ኮንከ፡ ተአምር፡ ፍትሐ፡ ሠናየ፡ አ፡
መኰንን፡ እምኢኮንከ፡ ትቅትሎ፡ ለጽኑዕ፡
እንዘ፡ኩሉ፡ያነሙ፡ይጼልሉ፡መልዕልቴከ።

፲፬፡ ወሶበ፡ ትኪንን፡ በርትዕ፡ አ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡
እምኀፈርከ፡ገጸ፡እግዚእከ።
፲፭፡ አነሂ፡ እሰምዕ፡ በእንተ፡ አጽባእት፡ ወእለ፡
ይጸብኡ፡በሙ፡እስመ፡እሙንቱ፡ሶበ፡ይትአ
ኀሐዝ፡ወልደ፡ንጉሥ፡የዓቅብዎ፡ጥቀ፡ወይ
ትበእሱ፡በእንቲአሁ፡ከመ፡ኢይሙት፡እስከ፡
ያበጽሕዎ፡ ኀበ፡ አቡሁ፡ በክብር፡ ወበስ
ብሐት፡ዐቢይ።
፲፮፡ ለምንትኬ፡አ፡ሊቀ፡ካህናት፡ሶበ፡ተሰአልከ፡
አማነ፡ነገረ፡አጠየቀከ፡ኪያሁ፡ኮነ፡በኀቤከ፡
ጽሉአ፡ወአፍቀርከ፡ሐሰተ፡ወረሰይከ፡ትውከ
ልተከ፡ላዕሌሁ፡እምኀበ፡መኑ፡ትሴአል፡
እንበለ፡አማን።

፲፯፡ ኢተአምርኑ፡ከመ፡ዘይቀውም፡ቅድሜከ፡
ውእቱ፡ አማናዊ፡ ወውእቱ፡ በአማን፡
ሕይወት።
፲፰፡ አ፡ድንግል፡ንጽሕት፡ነዋ፡ርእዩኬ፡ዐቢየ፡
ግፍዐ፡በውስተ፡ሀገረ፡ኢየሩሳሌም፡በዛቲ፡
ትውልድ፡እስመ፡ተጋብኡ፡ላዕለ፡ዘየዐቢ፡
እምኔሆሙ፡ወመጠውዎ፡ለኵነኔ፡ሞት።

፲፱፡ ወእምድኅረ፡ዝንቱ፡ኵሉ፡ኮነ፡ክርስቶስ፡
ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፤አምነ፡መስፍነ፡ምዕት፡
እንዘ፡ይብል፡አማን፡ዝንቱ፡ብእሲ፡ወልደ፡
እግዚአብሔር፡ውእቱ፡ወተአመኑ፡በኀበ፡
ኵሉ፡እሉ፡ተአምራት።
፳፡ ወኵሎሙ፡ መሀይምናን፡ በከዩ፡ ኀቡረ፡
ላዕሌሁ፡እንዘ፡ውእቱ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል።
፳፩፡ ወጲላጦስ፡ ፈነወ፡ ኀበ፡ መስፍነ፡ ምዕት፡
ዘመጽአ፡እምኀበ፡ሄሮድስ፡በእንተ፡ስቅለቱ፡
ወአብአ፡ውስተ፡ቤቱ፡ወይቤሎ፡ነጸርከኑ፡አ፡
እኁየ፡ ዘረሰይዎ፡ ሄሮድስ፡ ወአይሁድ፡
ለዝንቱ፡ብእሲ፡ጻድቅ፡ወሰቀልዎ፡በዐመፃ፡
እስከ፡ኮነ፡ዝንቱ፡ኵሉ፡ዲበ፡ምድር።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፪፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ ሆይ፡ በቅን፡ የምትፈርድ፡
ብትሆን፡ወንበዴውን፡አድነህ፡ጻድቁን፡ባል
ገደልከውም፡ነበር።
፲፫፡ ዳኛ፡ ሆይ፡ መልካም፡ ፍርድን፡ የምታውቅ፡
ብትሆን፡ ኑሮ፡ ጦሮች፡ በላይህ፡ ላይ፡ ሲያን
ጃብቡ፡ ጽኑዕ፡ የሆነውን፡ ባልገደልከውም፡
ነበር።
፲፬፡ አንተም፡ ሊቀ፡ ካህናት፡ በቅን፡ የምትፈርድ፡
ብትሆን፡የጌታህን፡ፊት፡ባፈርክ፡ነበር።
፲፭፡ እኔ፡ ስለጦርነት፡ ሰልፍ፡ ስሰማ፡ የንጉሥ፡
ልጅ፡ በጦርነቱ፡ ውስጥ፡ የተያዘ፡ እንደሆነ፤
እንዳይሞት፡ ስለእርሱ፡ እጅግ፡ በርትተው፡
እየተዋጉ፡ ወደ፡ አባቱ፡ በፍጹም፡ ጌትነትና፡
ክብር፡ እስከ፡ አደረሱት፡ ድረስ፡ ይጠብ
ቁታል።
፲፮፡ ሊቀ፡ካህናት፡ሆይ፡ለምን፡እንዲህ፡ሆነ፤በጠ
የቅኸው፡ ጊዜ፡ ዕውነቱን፡ አስረዳህ፤ግን፡
በአንተ፡ ዘንድ፡ የተጠላ፡ ሆነ፡ ሐሰትን፡
ወደድክ፤ እምነትህንም፡ በሐሰቱ፡ ላይ፡
አጸናህ፤ እንግዲህ፡ ከእውነተኛው፡ ከእርሱ፡
በቀር፡ማንን፡ትጠይቃለህ።
፲፯፡ በፊትህ፡ የቆመው፡ እርሱ፡ እውነተኛ፡
እንደሆነ፡አታውቅምን፡እርሱም፡በዕውነት፡
ሕይወት፡ነው።
፲፰፡ ንጽሕት፡ ድንግል፡ ሆይ፡ በኢየሩሳሌም፡
ከተማ፡ በዚች፡ ትውልድ፡ መካከል፡
የሆነውን፡ታላቅ፡ግፍ፡እዩ፤እነሆ፡ከእነርሱ፡
በሚበልጠው፡ ላይ፡ ተሰብስበው፡ ለሞት፡
ፍርድ፡ሰጥተውታልና።
፲፱፡ ከዚህ፡ ሁሉ፡ በኋላ፡ ክርስቶስ፡ በመስቀል፡
ላይ፡ እንደሆነ፡ ነበር፤ የመቶ፡ አለቃውም፡
በዕውነት፡ይህ፡ሰው፡የእግዚአብሔር፡ልጅ፡
ነው፡ ብሎ፡ አመነ፤ እሊህ፡ ተአምራቶቹ፡
በሁሉ፡ዘንድ፡ታመኑ።
፳፡ በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡ሳለ፡ምእመናን፡
ሁሉ፡በአንድነት፡አለቀሱለት።
፳፩፡ ስለጌታ፡ ስቅለት፡ ከሄሮድስ፡ ዘንድ፡ ወደ፡
መጣው፡ የመቶ፡ አለቃ፡ ጲላጦስ፡ልኮ፡
አስመጥቶ፡ ወደ፡ ቤቱ፡ አስገብቶ፡ ወንድሜ፡
ሆይ፤ ይህን፡ጻድቅ፡ሰው፡አይሁድና፡ሄሮድስ፡
ያደረጉትን፡ አየህን፡ ይህ፡ ሁሉ፡ ተአምራት፡
በምድር፡እስኪሆን፡ድረስ፡በግፍ፡ሰቀሉት።

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፴፪ አማን ፡ እብለከ ፡ አ ፡ እኁየ ፡ እስመ ፡ እላ ፡
እኪያት፡ኵሎን፡እኮ፡ዘኮና፡በፈቃድየ፡አላ፡
በምክረ ፡ ሄሮድስ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ ፈቀድኩ ፡
ከመ፡ እኅድጎ ፡ ኢይሙት ፡ ዳእሙ ፡ ሶበ ፡
ርኢክዎ፡ለሄሮድስ፡ከመ፡ኢይሠምር፡ዘንተ፡
መጠውክዎሙ ፡ ለአይሁድ ፡ ከመ ፡
ይስቅልዎ።

፴፫ ነጸር፡ይእዜ፡አየኑ፡ፍዳ፡ንሁቦ፡ለእግዚአ
ብሔር፡በእንተ፡ወልዱ፡ዘሰቀልናሁ፤ወኮኑ፡
ሐቤ ፡ ምዕት ፡ ወበዓለ ፡ ኩናት ፡ ምስለ ፡
ጲላጦስ፡ ይበክዩ ፡ በምረት ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡
ደሙ ፡ ላዕለ ፡ ሄሮድስ ፡ ወላዕለ ፡ ሊቃነ ፡
ካህናት።

፴፬ ወውእተ ፡ አሚረ ፡ ፈነወ ፡ ጲላጦስ ፡
ወጸውዖሙ፡ለሊቃነ፡ካህናት፡ሐና፡ወቀያፋ፡
ወአምጽእዎሙ፡ኀበ፡ማኅበር፡ወይቤሎሙ፡
ጲላጦስ፡አ፡ተኰላት፡ወቈናጽል፡ሰታይያነ፡
ደም፡በዐመፃ፡ንዑ፡ይእዜኒ፡ነጽሩ፡በእንተ፡
ሞተ፡ናዝራዊ፡በዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ለይኩን፡
ደሙ፡ላዕሌክሙ፡ወላዕለ፡ውሉድክሙ።

፴፭ ወእሙንቱሰ፡ዘበጡ፡እንግድዓቲሆሙ፡ወገጸ
ቲሆሙ፡እንዘ፡ይብሉ፡በአስተፍክኖ፡እስከ፡
ዐሠርቱ፡ምዕት፡ትውልድ፡ለይኩን፡ላዕሌነ፡
ወላዕለ፡ውሉድነ።

፴፮ ወይቤ፡ጲላጦስ፡ይእዜሂ፡እምድኅረ፡ዝንቱ፡
ኵሉ ፡ ተአምር ፡ ዘተከሥተ ፡ በሰማይ ፡
ወበምድር ፡ ኢትፈርሁኑ ፡ ወኢትደነግፁኑ ፡
ምስለ፡ኵሉ፡ሕዝብ።

፴፯ ወይቤልዎ ፡ በእንተ ፡ ምንት ፡ ንፈርሀ ፡ ወንደ
ነግፅ፡እስመ፡ናሁ፡ፈጸምነ፡በከመ፡ሕግነ።

፴፰ ወይቤ፡ጲላጦስ፡አንትሙ፡ፈጸምክሙ፡ሕገ፡
ሐሰት፡ወአኮ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡ሕግ፡እስመ፡
ፈጸምከ፡አንተ፡ዘትሰመይ፡ሊቀ፡ካህናት፡
ወነዋ፡አልባሲከ፡ሥጡጣት።

፴፱ ወሕግኒ፡ይብል፡ሶበ፡ይሠጥጥ፡ልብሶ፡ሊቀ፡
ካህናት፡ይትከላእ፡እምግብረ፡ክህነት።

፵ ወተሰጥዎ፡ሊቀ፡ካህናት፡ወይቤሎ፡አንሰ፡
ዘሠጠጥኩ፡ልብስየ፡እስመ፡ፀረፈ፡ላዕለ፡እግ
ዚአብሔር፡ወላዕለ፡ሕግነ።

፵፩ ወይቤሎ፡ጲላጦስ፡ኢይኤዝዘከ፡እንከ፡ከመ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፴፪ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ በእውነት ፡ እነግርሃለሁ ፤
እነዚህ ፡ ክፋቶች ፡ ሁሉ ፡ የተፈጸሙት ፡
በሄሮድስ ፡ ምክር ፡ እንጂ ፡ በእኔ ፡ ፈቃድ ፡
አይደለም ፤ እኔ ፡ እንዳይሞት ፡ ልተወው ፡
ወደድኩ፤ነገር፡ግን፡ሄሮድስ፡በዚህ፡ደስ፡እን
ደማይለው፡ባየሁ፡ጊዜ፡ይሰቅሉት፡ዘንድ፡
ለአይሁድ፡ሰጠኋቸው፡እንጂ።

፴፫ ተመልከት ፡ አሁን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡
ሰቀልነው ፡ ልጁ ፡ ምን ፡ ብድርን ፡ እንከፍለ
ዋለን ፡ አለው ፤ የመቶ ፡ አለቃውና ፡ ባለጦሩ ፡
ከጲላጦስ፡ጋር፡ደሙ፡በሄሮድስና፡በካህናት፡
አለቆች ፡ ላይ ፡ ነው ፤ እያሉ ፡ መራራ ፡ ልቅሶ ፡
አለቀሱ።

፴፬ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጲላጦስ ፡ ልኮ ፡ የካህናት ፡
አለቆች ፡ ቀያፋና ፡ ሐናን ፡ ወደ ፡ ጉባዔው ፡
አስጠርቶ ፡ እናንተ ፡ በግፍ ፡ ደምን ፡
የምትጠጡ ፡ ተኵላዎችና ፡ ቀበሮዎች ፡
በዕንጨት ፡ መስቀል ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ሞተው ፡
የናዝሬት፡ሰው፡አሁን፡ተመልከቱ፤ደሙም፡
በእናንተና ፡ በልጆቻችሁ ፡ ላይ ፡ ይሁን ፡
አላቸው።

፴፭ እነርሱ፡ግን፡ደስ፡በመሰኘት፡እያፌዙ፡ደረ
ታቸውን፡እየደቁ፡ፊታቸውንም፡እየነጩ፡
እስከ፡ሽህ፡ትውልድ፡በእኛና፡በልጆቻችን፡
ላይ፡ይሁን፡አሉ።

፴፮ ጲላጦስም፡ይህ፡ሁሉ፡ተአምር፡በሰማይና፡
በምድር፡ከተገለጠ፡በኋላ፡ዛሬም፡ከሕዝቡ፡
ሁሉ ፡ ጋር ፡ አትፈሩምን ፡ አትደነግጡምን ፡
አላቸው።

፴፯ እነርሱም ፡ እንደ ፡ ሕጋችን ፡ ፈጽመናል ፡
ስለምን፡እንፈራለን?እንደነግጣለን፡አሉት።

፴፰ ጲላጦስም፡የሐሰት፡ሕግ፡ፈጸማችሁ፡እንጂ፤
ይህ፡ሕግ፡አይደለም፡አለ፤አንተም፡ሊቀ፡
ካህናት ፡ የተባልከው ፡ እነሆ ፡ ልብሶችህ ፡
ተቀደዋል።

፴፱ ሕጉም፡ሊቀ፡ካህናቱ፡ልብሶቹን፡በቀደደ፡ጊዜ፡
ከክህነት፡አገልግሎት፡ይከልከል፡ይላል።

፵ ቀያፋም፡እኔ፡ልብሴን፡የቀደድኩት፡እርሱ፡
በእግዚአብሔርና፡በሕጋችን፡ላይ፡የስድብ፡
ቃል፡ስለ፡ተናገረ፡ነው፡ብሎ፡መለሰለት።

፵፩ ጲላጦስ፡እንግዲህ፡በሊቀ፡ካህናት፡ሥርዓት፡

በ፲፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ። ... 

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፡ሰዓት።

በ፲፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ። ዳግመ፡በአምሳለ፡
ትባእ፡ውስተ፡መቅደስ፡ዳግመ፡በአምሳለ፡
ሊቀ፡ካህናት፡ዳእሙ፡ከመ፡ዐላዊ።
፴፪፡ ወሶበ፡ያየድዐኒ፡ካልእ፡ከመ፡አንተ፡ገባእከ፡
አነ፡እመትር፡ርእሰከ፡እምኔከ።

፴፫፡ ወተሰጥዎ፡ወይቤሎ፡በኑ፡እምነ፡ሥዩማን፡
ዘከልአሙ፡ ለሊ.ቃነ፡ ካህናት፡ በዊአ፡
መቅደስ፡ ወጕንደየ፡ መዋዕለ፡ እምእለ፡
ቀደሙከ፡እመዋዕለ፡ትካት፡እስከ፡ይእዜ።

፴፬፡ ዘንተ፡ ይቤ፡ ውእቱ፡ እንዘ፡ ይትአመን፡
ሥልጣኖ፡ ሄሮድስ፡ ወይቤሎ፡ ጲላጦስ፡
ይእዜኒ፡ዘንተ፡ኵሎ፡ተአምረ፡ኢየአምን፡
ልብከ፡ምስለ፡ኵሉ፡ሕዝብ።
፴፭፡ ወይቤሎ፡ቀያፋ፡ዘይሰመይ፡ሊቀ፡ካህናት፡
ለጲላጦስ፡አንተሰ፡ተክል፡ሐዲስ፡ውስተ፡
ዛቲ፡ሀገር፤ወኢ.ተአምር፡በዘኮነ፡ዝንቱ፡
ተአምር፡ወዘተገብረ።
፴፮፡ እስመ፡ ዝንቱ፡ ጊዜ፡ ውእቱ፡ ማህለ፡
መጋቢት፡ ወዑደተ፡ ፀሐይ፡ ወወርኅ፤
በዝንቱ፡ወርኅ፡ይገብሩ፡መሠርያን፡ወርኅ፡
ከመ፡ደም፡ወይስሕቡ፡ጸዳለ፡ፀሐይ፡በኃይለ፡
ተቅሳም።

፴፯፡ ወየሐትቱ፡ተግባረ፡አግዓዝያን፡ወእስተ
ዳልዎ፡ፍሬያት፡ወሥርናይ፡ወወይን፡
ወዘይት፡ዘንተ፡ወዘይመስሎ፡ኮነ፡ቀያፋ፡
ይነብቦሙ፡በሐሰት።
፴፰፡ ወተንሥአ፡ጲላጦስ፡እመንበሩ፡ወዘበጦ፡
በአንጻ፡ይቡስ፡ወነጸየ፡ጽሕመ፡መንከሱ፡
ወቀሠፎ፡እንዘ፡ይብሎ፡አንተ፡ትፈቅድ፡
ታምጽእ፡መዐተ፡ላዕለ፡ኵላ፡ምድር፡
በእንተ፡ጸሊ.አትከ፡ኪያሁ።
፴፱፡ ወኮኑ፡ሐቤ፡ምዕት፡ወሐራ፡ይዘልፍዎ፡
ለውእቱ፡ሊቀ፡ካህናት፡ወይቤልዎ፡ሎቱ፡
ይደልወከ፡ መዊት፡ ፈድፋደ፡ እምነ፡
ሕይወት።
፵፡ ወእምድኅረ፡ተዛለፍዎ፡በእሐቲ፡ምክር፡ጲላ
ጦስ፡ወሐቤ፡ምዕት፡ወሰድዎ፡ውስተ፡ቤተ፡
መቅደስ፡ውኅብሩ፡ከመ፡ይሰድዎ፡ኀበ፡ንጉሥ።
በረከተ፡ አንብዓ፡ ወምሕረተ፡ ፍቁር፡
ወልዳ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ወደ፡መቅደስ፡አንተ፡እንድትገባ፡አልፈቅድ
ልህም፡እንደ፡ሕግ፡አፍራሽ፡እንጂ።
፴፪፡ አንተ፡ወደ፡መቅደስ፡እንደገባህ፡ሌላው፡
ቢነግረኝ፡ቍብቍቦህን፡ከአንተ፡ላይ፡እቆር
ጣለሁ፡አለው።
፴፫፡ ቀያፋም፡ ከአንተ፡ በፊት፡ ብዙ፡ ጊዜ፡
አልፎአል፤ብዙዎችም፡ሹማምንት፡የሚቀ
ድሙህ፡ አሉ፤ እስከ፡ ዛሬ፡ የካህናት፡
አለቆችን፡ወደ፡መቅደስ፡መግባትን፡የከለከ
ላቸው፡አለን፡ብሎ፡መለሰለት።
፴፬፡ ይህንም፡ያለ፡የሄሮድስን፡ሥልጣን፡በመተ
ማመን፡ነበር፤ጲላጦስም፡ይህን፡ሁሉ፡
ተአምር፡ ስታይ፡ ከሕዝቡ፡ ሁሉ፡ ጋር፡
አሁንም፡ልብህ፡አያምንምን፡አለው።
፴፭፡ ሊቀ፡ካህናት፡የተባለ፡ቀያፋም፡አንተስ፡
በዚች፡አገር፡አዲስ፡ተክል፡ነህ፤ይህ፡
ምልክት፡የሆነበትን፡ነገርና፡የተደረገውን፡
አታውቅም።
፴፮፡ ይህ፡ይቅርታ፡የሚደረግበት፡የመጋቢት፡
ወር፡ ፀሐይና፡ ጨረቃ፡ ዑደታቸውን፡
ፈጽመው፡ተራክቦ፡የሚያደርጉበት፡ሲሆን፤
በዚሁ፡ወር፡መሠርያኖች፡ጨረቃን፡እንደ
ደም፡የሚሆንበትን፡ያደርጋሉ፤የፀሐይንም፡
ብርሃን፡በሥራይ፡ኃይል፡ይስባሉ።
፴፯፡ የአግዓዝያንን፡ተግባር፡ይመረምራሉ፤የምግ
ዶውን፡የወይንንና፡የዘይትን፡ፍሬዎች፡በማ
ዘጋጀት፡ ይህን፡ የመሰለውን፡ ቀያፋ፡
በሐሰት፡ይናገር፡ነበር።
፴፰፡ ጲላጦስም፡ከወንበሩ፡ላይ፡ተነሥቶ፡አንተ፡
እርሱን፡ ከመጥላትህ፡ የተነሣ፡ በዓለሙ፡
ሁሉ፡ላይ፡መዐትን፡ልታመጣ፡ትወዳለህ፡
ብሎ፡ ከቆዳ፡ በተሠራ፡ በደረቀ፡ በትር፡
ደበደበው፤ጽሕሙንም፡ነጨው።
፴፱፡ የመቶ፡ አለቃውና፡ ባለጦሩ፡ ከሕይወት፡
ይልቅ፡ሞት፡ይገባሃል፤እያሉ፡ያንን፡ሊቀ፡
ካህናት፡ይዘልፉት፡ነበር።

፵፡ በአንድነት፡ከዘለፉትም፡በኋላ፡ወደ፡ቤተ፡
መቅደስ፡ ይዘውት፡ ሄዱ፤ ወደ፡ ንጉሥም፡
ይወስዱት፡ዘንድ፡ተስማሙ።
የድንግል፡ማርያም፡ በረከት፡ የተወዳጅ፡
ልጅዋም፡ምሕረት፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይደርብን፤አሜን።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ምንተኑ፡አዐስየኪ፡በል።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡
በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡
ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።
፩ ወሐረት፡መካነ፡ቀራንዮ፡ከመ፡ትርአይ፡
ሕማማተ፡ፍቁር፡ወልዳ።
፪ ርእየት፡አክሊለ፡ሦክ፡ዘአስተቀጸልዎ፡
ወደመ፡ርእሱ፡ዘቈሰለ፡በአክሊለ፡ሦክ፡
እንዘ፡ያንጸፈጽፍ፡ዲበ፡መትከፍቱ።
፫ ወርእየት፡ደመ፡ቅሥፈታቲሁ፡ዘአቍሰልዎ፡
በጥብጣቤ፡እንዘ፡ያንጸፈጽፍ፡ደም፡ዲበ፡
ደም፡እስመ፡ብዙኀ፡ቀሠፍዎ፡ርእየት፡ደመ፡
ቅሥፈታቲሁ፡እንዘ፡ይትከዐው፡ውስተ፡
ጕንደ፡መስቀል።
፬ ወዘንተ፡ርእያ፡ነደ፡ልባ፡በዋዕየ፡ሐዘን፡
እንዘ፡ማኅበረ፡አይሁድ፡ፍሡሐን፡በእንተ፡
ስቅለቱ፡ወርእያ፡ውሕዘ፡እምአዕይንቲሃ፡
ውሒዘ፡አንብዕ፡ወለሰቃልያንሂ፡ኢተራ
ኀርኆ፡ልበሙ።
፭ አሜሃ፡ተሐደሰ፡ልቡናሃ፡ለድንግል፡ከመ፡
በከየ፡ያዕቆብ፡በእንተ፡ዮሴፍ፡ወአስቈቀወ፡
ኤርምያስ፡በእንተ፡ዔዋዌ፡ሕዝቡ።

፮ ለያዕቆብሰ፡ተርፉ፡ሎቱ፡ውሉዱ፡ዐሠርቱ፡
ወአሐዱ፡ወለኤርምያስኒ፡ኮኑ፡ምስሌሁ፡
እንዘ፡ይዔወዉ፡ይትራድኡ፡በበይናቲሆሙ።
፯ እፎኬ፡ኢትበኪ፡ድንግል፡ዘላቲ፡ወልድ፡
እንዘ፡ይጼዐር፡በሕማማተ፡መስቀል፤እፎኬ፡
ኢትበኪ፡ድንግል፡በእንተ፡ወልዳ፡ዋህድ፡
ዘወለደቶ፡በድንግልናሃ።

፰ እፎኬ፡ኢትበኪ፡ድንግል፡እንዘ፡ትኔጽር፡
በላዕሌሁ፡ዝንጓጌሁ፡ለጻድቅ፡ወኀሣሮ፡
ለክቡር፤ነጸረ፡ስቁል፡ኀበ፡እሙ፡
ወኀበ፡ረድኡ፡ዘይንእስ፡ወይቤላ፡ለእሙ፡
ነዋ፡ወልድኪ፡ወይቤሎ፡ለረድኡኒ፡ነያ፡
እምከ።

፱ አማሕፀኖ፡ለረድኡ፡ኀበ፡ወላዲቱ፡ከመ፡
ትዕቀቦ፡በከዊነ፡ወልዳ፡ወአኮ፡በሥርዓተ፡
ላእክ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ምንተኑ፡አዐስየኪ፡በል።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡
ይኑርና፡በድንጋሌ፡ሥጋ፤በድንጋሌ፡ነፍስ፡
የጸናች፤አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመ
ቤታችን፡ያደረገችው፡ተአምር፡ይህ፡ነው።
፩፤ የተወዳጅ፡ልጅዋን፡ሕማም፡ታይ፡ዘንድ፡
ወደ፡ቀራንዮ፡ሄደች።
፪፤ ያቀዳጁትን፡የእሾህ፡አክሊልና፡በእሾህ፡
አክሊል፡የቆሰለ፡የራሱን፡ደም፡በትከሻው፡
ላይ፡ሲንጠፈጠፍ፡አየች።
፫፤ በግርፋትም፡በጅራፍ፡ያቆሰሉትን፡የግርፋ
ቱንም፡ቊስል፡ደም፡በደም፡ሆኖ፡አየችው፤
አብዝተው፡ገርፈውት፡ነበርና፡የግርፋቱም፡
ደም፡በመስቀሉ፡ላይ፡ሲወርድ፡አየች።

፬፤ ስለ፡መሰቀሉም፡አይሁድ፡ደስ፡ሲላቸው፡
አይታ፡ልቡናዋ፡በሐዘን፡ተቃጠለ፤
አይታም፡ከዐይኖቿ፡የዕንባ፡ጐርፍ፡ፈሰሰ፤
የሰቃዮቹም፡ልቡናቸው፡አልራራም።

፭፤ ያንጊዜ፡ያዕቆብ፡ስለ፡ዮሴፍ፡እንዳለቀሰ፤የኤ
ርምያስም፡ልቅሶ፡ስለ፡ወገኖቹ፡ምርኮ፡
እንደሆነ፤የድንግል፡ልቡናዋም፡በሐዘን፡
ተቀሰቀሰ፡(ተዋጠ)።
፮፤ ለያዕቆብም፡አሥራ፡አንድ፡ልጆቹ፡ቀርተው
ለታል፤ለኤርምያስም፡ከሱ፡ጋር፡አብረውት፡
ሲማረኩ፡እርስ፡በርሳቸው፡ይጽናኑ፡ነበር።
፯፤ የእርሷ፡የሆነ፡ልጅዋ፡በመስቀል፡መከራ፡
ሲሠቃይ፡ድንግል፡እንዴት፡አታለቅስ?
ምንስ፡ትሁን?በድንግልና፡ስለ፡ወለደችው፡
ስለ፡አንድ፡ልጅዋ፡ድንግል፡እንዴት፡
አታለቅስ?
፰፤ የባሕርይ፡አምላክ፡
ድንግል፡እውነተኛ፡
ልጅዋን፡የሚያሽሟጥጡትንና፤ክቡር፡ልጅዋን፡
የሚያዋርዱትን፡ስታይ፡እንዴት፡አታለቅስ?
ምንስ፡ትሁን?የተሰቀለውም፡ልጅዋ፡በዕድሜ፡
ወደሚያንሰው፡ደቀ፡መዝሙሩ፡ተመልክቶ፡
እናቱን፡እነሆ፡ልጅሽ፡አላት፤ደቀ፡መዝሙ
ሩንም፡እነኋት፡እናትህ፡አለው።
፱፤ ደቀ፡መዝሙሩንም፡በአገልጋይ፡ሥርዓት፡
ያይደለ፡በልጅነት፡ሥርዓት፡ትጠብቀው፡
ዘንድ፡ወደ፡እናቱ፡አስጠበቀው።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፡ ወአማሕፀነ ፡ እሞሂ ፡ ኀበ ፡ ረድኡ ፡ ከመ ፡
ይነጽራ፡በሥርዐተ፡እም፡ወእኅ፡በሥርዐተ፡
እግዚእት።
፲፩፡ አ ፡ ለዛቲ ፡ ሰዓት ፡ ሕማም ፡ እንተ ፡ ኮነት ፡
ተፈልጠ፡ማዕከለ፡ወልድ፡ወወላዲቱ።

፲፪፡ አ ፡ ለዛቲ ፡ ሰዓት ፡ ላሕ ፡ እንተ ፡ አጽለመቶ ፡
ለፀሐይ፡ወአንሦጠጠቶ፡ለሰማይ።

፲፫፡ አ ፡ ለዛቲ ፡ ሰዓት ፡ ብካይ ፡ እንተ ፡ አርዐደታ ፡
ለምድር፡ወአስተካወሰቶ፡ለቀላይ።

፲፬፡ ብካየ ፡ ለድንግል ፡ አልሐዎሙ ፡ ለአርድእት ፡
እስከ፡ግልሰ፡ዕለት።
ወድምፀ፡ሰቈቃው፡መሰዎ፡ለሥጋሆሙ።

፲፭፡ ኢያዕረፈት ፡ ብካየ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ተንሥአ ፡
ወኢረከበት ፡ ኑዛዜ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ነጸረቶ ፡
ለሰማይ ፤ ወአምኀቶ ፡ ለፀሐይ ፡ በጽባሐ ፡
እሑድ፡ወከዋክብቲሃ፡አንፈርዐጹ፡ምስሌሃ፡
ሶበ፡ነጸርዎ፡ለመምህሮሙ።

፲፮፡ ጣዕዋ፡ንጽሕት፡ሰዐመቶ፡ለመግዝእ፡ላሕም፡
ወአባግዒሃ ፡ ተፈሥሑ ፡ ምስሌሃ ፡ ሶበ ፡
ርእይዎ፡ለሊቀ፡ኖሎት።

፲፯፡ ወለተ፡ዳዊት፡ረከበቶ፡ለፍሬ፡ማሕፀና፡ወላእ
ካኒሃ ፡ ተሐሥዩ ፡ ምስሌሃ ፡ ወሰበኩ ፡
ትንሣኤሁ፡ለእግዚአሙ።

፲፰፡ አ፡እግዚእነ፡ አጥዕየነ ፡ በእንተ ፡ ሕማምከ ፡
ወፈውሰነ፡በእንተ፡ቍስለ፡ሞትከ፡ወናዝዘነ፡
በእንተ፡ብካያ፡ለማርያም፡እምከ።
፲፱፡ ናዝዘነ፡ዘናዘዝኮሙ፡ለአርዳኢከ፡ወከልለነ፡
በሞገስ ፡ መስቀልከ ፡ ወከድነነ ፡ ብርሃነ ፡
ትንሣኤከ፡ለዙልነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።
ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ማህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።
፳፡ ወእምድኅረዝ፡ይቤሎሙ፡ለወዐልት፡እለ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፲፡ እናቱንም፡በእመቤትነት፡ሥርዓት፡ያደደለ፤
በእናትነት፡ሥርዓት፡ይመለከታት፡ዘንድ፡
ለደቀ፡መዝሙሩ፡አደራ፡አስጠበቃት።
፲፩፡ በእናትና፡በልጅ፡መካከል፡መለያየት፡ስተደ
ረገባት ፡ ለዚያች ፡ ሰዓት ፡ ወዮ ! እንክሮ፡
ይገባል።
፲፪፡ ፀሐይን ፡ ላጨለመችው ፤ ሰማይን፡ስቅጥጥ፡
ስቅጥጥ ፡ ላስደረገችው ፡ ለዚያች፡ለልቅሶ፡
ሰዓት፡ወዮ!አንክሮ፡ይገባል።
፲፫፡ ምድርን ፡ ላንቀጠቀጠቻት ፡ ባሕሩን፡ላነቃነ
ቀችው ፡ ለዚያች ፡ ለልቅሶ ፡ ሰዓት ፡ ወዮ!
አንክሮ፡ይገባል።
፲፬፡ የድንግልም ፡ ልቅሶዋ ፡ ሐዋርያትን ፡ እስከ፡
ሦስት፡ቀን፡ድረስ፡አስለቀሳቸው።
የልቅሶውም፡ድምጽ፡ሰውነታቸውን፡እንደ፡
ሰም፡አቀለጠው።
፲፭፡ እስከ ፡ ተንሣ ፡ ጊዜ ፤ ከእንባ ፡ ከልቅሶ፡አላረፈ
ችም ፤ እሑድ ፡ ጥዋት ፡ ሰማይን ፡ ተመልክታ፡
እውነተኛ፡ፀሐይ፡ልጅዋን፡እስከ፡ሳመችው፡
ድረስ፡ ከዋክብቶቿ ፤ ሐዋርያትም፡መምህራቸ
ውን፡አይተው፡ከእርስዋ፡ጋር፡ደስ፡ብሏቸው፡
እስከ፡ዘለሉ፡ድረስ፡መረጋጋትን፡አላገኘችም።
፲፮፡ ንጽሕት፡እምቦሳ፡ድንግልም፡የፋሲካውን፡
ላሕም ፡ ሳመችው ፤ የእረኞችንም ፡ አለቃ፡
በአዩት ፡ ጊዜ ፡ በጎቿ ፡ ሐዋርያት ፡ ከእርስዋ፡
ጋር፡ደስ፡አላቸው።
፲፯፡ የዳዊት ፡ ብላቴና ፡ ድንግልም ፡ የማኅፀንዋን፡
ፍሬ ፡ አገኘችው ፤ አገልጋዮቿ ፡ ሐዋርያትም፡
ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ የጌታቸውን፡
ትንሣኤ፡ሰበኩ።
፲፰፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ስለ ፡ ሕማምህ ፡ አድነን!
በቍስለ ፡ ሞትህም ፡ ፈውሰን ፤ ስለ ፡ እናትህ፡
ልቅሶም፡አጽናናን።
፲፱፡ ደቀ ፡ መዛሙርትህንም ፡ እንዳረጋጋሐቸው፡
አረጋጋን ፤ በመስቀልህም ፡ ግርማ ፡ ጋርደን፤
ሁላችንንም ፡ የትንሣኤህን ፡ ብርሃን ፡
አልብሰን፤ለዘላለሙ፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።
ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ይኑርና ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ፈጣሪ
ያችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡
ተአምር፡ይህ፡ነው።
፳፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚጠብቁትን ፡ ወታደሮች፡

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

የዐቅብዎ፡ጸማእኩ።
ወሀሎ፡ህየ፡በዐለ፡ኀለት፡ብእሲ፡ዘይጠብሕ፡
፪ አባግዐ፡ወኀቤሁ፡ብሒእ፡መጺዕ፡ወይፈቅድ፡
ይሚጦ፡ወውስተ፡እዴሁ፡ይእኅዝ፡ሐሞተ።
፫ ወዝኩ፡ብእሲ፡በዓለ፡ሐሞት፡ይፈቅድ፡
ይግድፎ፡ውስተ፡ፍኖት፡ወተሠጢጦ፡ቦአ፡
ውስተ፡ጻሕለ፡ብሒእ፡ዝኩ፡ሐሞት።
፬ ወይቤሉ፡ወዐልት፡እለ፡የዐቅብዎ፡ናሁ፡
ሰአለ፡ዝንቱ፡ስቁል፡ማየ፡ንዑ፡ነሀብ፡
እምብሒእ፡ዝንቱ፡ብእሲ፡በዓለ፡ኀለት፡
እስመ፡ተወድየ፡ውስቴቱ፡ሐሞት፤
ወይመፅዕ፡በሕቁ፡ወናስትዮ፡እምኔሁ።
፭ ወነሥኡ፡ሰፍነገ፡ወጠምዕዎ፡በዝንቱ፡
ብሒእ፡ወሐሞት፡አቅረብዎ፡ኀበ፡እግዚእ፡
ኢየሱስ፡ወሶበ፡ጥዕመ፡አበየ፡ወኢሰትየ፡
እምኔሁ።
፮ ወዝንቱ፡ኮነ፡ከመ፡ይትፈጸም፡ቃለ፡ዳዊት፡
ነቢይ፡ዘይቤ፡ወወደዩ፡ሐሞተ፡ውስተ፡
መብልዕየ፡ወአስተዩኒ፡ብሒእ፡ለጽምእየ።

፯ ወእምዝ፡ጸርሐ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡በልዑል፡ቃል፡ወይቤ፡ኤሎሄ፡
ኤሎሄ፡ላማ፡ሰበቅታኒ፡ዘበትርጓሜሁ፡
አምላኪየ፡አምላኪየ፡ለምንት፡ኀደገኒ።

፰ ወመሰሎሙ፡ለአይሁድ፡እለ፡ሀለዉ፡ህየ፡
ይጼውዖ፡ለኤልያስ።
፱ ወይቤሉ፡በበይናቲሆሙ፡ኅድግዎ፡ንርአይ፡
እመ፡ይመጽእ፡ኤልያስ፡ያድኅኖ።
፲ ወሶበ፡አዕረግዎ፡ለእግዚእነ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ላዕለ፡ዕፀ፡መስቀል፡ጸልመ፡ፀሐይ፡
እምጊዜ፡ስድስቱ፡ሰዓት፡ዘመዐልት፡
ወወርኀኒ፡ኮነ፡ከመ፡ደም፡ኵለንታሁ፡
ወመዐልት፡ኮነ፡ሌሊተ።
፲፩ ወተሠጠ፡መንጦላዕተ፡ምኵራብ፡እምላዕሉ፡
እስከ፡ታሕቱ።
፲፪ ወኮነ፡ድልቅልቅ፡ዐቢይ፡ወፍርሀት፡
ተሠጥቀ፡ኰኵሕ፡ወተፈትሑ፡መቃብራት።
፲፫ ወወጽኡ፡ብዙኃን፡ምውታን፡እምአበው፡
ጻድቃን።
፲፬ ወሶበ፡ይቤ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሎቱ፡ስብሐት፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡አምላኪየ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ተጠማሁ፡አላቸው።
፪፡ ከዚያም፡በጎችን፡የሚያርድ፡ዘንግ፡መፃፃ፡
ማሰሮ፡ያለው፤በእጁም፡ሐሞት፡የያዘ፡ሰው፡
ነበር፤ሊሸጠውም፡ይወድ፡ነበር።
፫፡ ያም፡ባለ፡ሐሞት፡በመንገድ፡ሊደፋው፡
ወዶ፡ ሳለ፡የሐሞቱ፡ከረጢት፡ተቀዶ፡
ሐሞቱ፡ወደ፡ያዘው፡ማሰሮ፡ገባ።
፬፡ የሚጠብቁት፡ወታደሮችም፡እነሆ፡ይህ፡የተ
ሰቀለው፡ውኃ፡ይለምነናልና፡ኑ፡ይህ፡ባለ፡
ዘንጉ፡ከያዘው፡መፃፃ፡እንስጠው፤ሐሞት፡
ተቀላቅሎበታልና፡እጅግም፡ይከመጥጣልና፡
ከእርሱ፡እናጠጣው፡አሉ።
፭፡ ሰፍነግም፡ወስደው፡ከሐሞቱና፡ከሆምጣጣው፡ነክረው፡ወደ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡
አቀረቡት፤በቀመሰውም፡ጊዜ፡ከእሱ፡
መጠጣትን፡አልጠጣም፡አለ።
፮፡ ነቢዩ፡ዳዊት፡በምግቤ፡ውስጥ፡ሐሞትን፡
ጨመሩ፤ጥማቴንም፡ለማራቅ፡ሆምጣ
ጣውን፡አጠጡኝ፤ያለው፡ይደርስ፡ይፈጸም፡
ዘንድ፡ይህ፡ሆነ።
፯፡ ከዚህ፡በኋላ፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ኤሎሄ፤ኤሎሄ፤ላማ፡ሰበቅታኒ፡ብሎ፡
በታላቅ፡ ቃል፡ጮኸ፤ትርጓሜውም፡
አምላኪየ፡አምላኪየ፡ለምን፡ተውከኝ፡
ማለት፡ነው።
፰፡ ከዚያ፡ያሉ፡አይሁድም፡ኤልያስን፡
የሚጠራ፡መሰላቸው።
፱፡ እርስ፡በእርሳቸውም፡ኤልያስ፡መጥቶ፡
ያድነው፡እንደሆነ፡ተዉት፡እንይ፡አሉ።
፲፡ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስንም፡ከዕንጨት፡
መስቀል፡ላይ፡ባወጡት፡ጊዜ፡ከቀኑ፡ስድስት፡
ሰዓት፡ጀምሮ፡እስከ፡ዘጠኝ፡ሰዓት፡ድረስ፡
ፀሐይ፡ጨለመ፤ጨረቃም፡ሁለመናው፡እንደ፡
ደም፡ሆነ፤ቀኑም፡ጨለማ፡ሆነ።
፲፩፡ የምኵራቡም፡መጋረጃ፡ከላይ፡እስከ፡ታች፡
ተቀደደ።
፲፪፡ ታላቅ፡ንውጽውጽታና፡ፍርሃት፡ሆነ፤አለቱ፡
ተሠነጠቀ፡መቃብሮችም፡ተከፈቱ።
፲፫፡ ከደጋግ፡አባቶች፡ወገን፡ብዙዎች፡ሙታን፡
ተነሡ።
፲፬፡ የክብር፡ባለቤት፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
በመስቀል፡ላይ፡ሁኖ፡አምላኪየ፡አምላኪየ፡

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

አምላኪየ፡ ለምንት፡ኀደገኒ፡ጸርሐ፡በልዑል፡
ቃል፡ወመጠወ፡ነፍሶ፡ኀበ፡አቡሁ።
፲፫፤ ወሖረ፡ኀቤሁ፡አሐዱ፡እምሐራ፡ወወግአ፡
ገቦሁ፡በኲናት፡ወወጽአ፡እመካነ፡ርግዘቱ፡
ደም፡ወማይ፡ድሙረ።
፲፬፤ ወጸልመት፡ምድር፡እምጊዜ፡ስድስቱ፡ሰዓተ፡
መዐልት፡እስከ፡ተሰዓቱ፡ሰዓት።
ማህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፫።

መልእክተ፡ጳውሎስ፡
ኀበ፡ሰብአ፡ፊልጵስዩስ።

ምዕ፡፪፡፭–፲፩።

፭፤ ኵልክሙ፡ፍጹማን፡ዘንተ፡ኀልዩ፡ለነኒ፡
ዘከመ፡ገብረ፡ለነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ።
፮፤ ዘውእቱ፡አርአያሁ፡ለእግዚአብሔር፡ አኮ፡
ሀዩዶ፡ዘኮነ፡እግዚአብሔር።
፯፤ አላ፡አትሐቶ፡ርእሶ፡ነሥአ፡አርአያ፡ገብር፡
ወተመሰለ፡ከመ፡ብእሲ።
፰፤ ወኮነ፡ከመ፡ሰብእ፡ወሰምዐ፡ወተአዘዘ፡
እስከ፡በጽሐ፡ለሞት፡ወሞቱሂ፡ዘበመስቀል።
፱፤ ወበእንተዝ፡አዕበዮ፡እግዚአብሔር፡ ጥቀ፡
ወጸገዎ፡ስመ፡ዘየዐቢ፡እምኵሉ፡ስም።
፲፤ ከመ፡ለስሙ፡ለኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ ይሰግድ፡
ኵሉ፡ብርክ፡ዘበሰማያት፡ወዘበምድር፡ወዘበ
ቀላያት፡ወእለ፡ታሕተ፡ምድር።
፲፩፤ ወኵሉ፡ልሳን፡ይግነይ፡ከመ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ ውእቱ፡እግዚአ፡ በስብሐተ፡እግዚ
አብሔር፡ አብ።

ትእዛዝ።

(ይ፡ካ)፡ በዐቢይ፡ዜማ፡ዕዝል፡አ፡ዘጥዕመ፡
ሞተ፡በሥጋ፤አ፡ዘጥዕመ፡ሞተ፡በሥጋ፤አ፡
ዘጥዕመ፡ሞተ፡በሥጋ፤(ይሕ)፡ ከማሁ።
(ይ፡ዲ)፡ በንባብ፡ማሕዘኒ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ለምን፡ተውከኝ፡ብሎ፡በታላቅ፡ድምጽ፡
ጮኸ፤ነፍሱንም፡በአባቱ፡ፈቃድ፡ከሥጋው፡
በሥልጣኑ፡ለየ።
፲፫፤ ከወታደሮችም፡አንዱ፡ሂዶ፡በጦር፡ጐኑን፡
ወጋው፤ከተወጋበትም፡ጐኑ፡ውኃና፡ደም፡
በአንድነት፡እንደ"ለ"፡ ፊደል፡መንታ፡
ሁኖ፡ወረደ።
፲፬፤ ከቀኑ፡ስድስት፡ሰዓት፡ጀምሮ፡እስከ፡ዘጠኝ፡
ሰዓት፡ድረስ፡ምድር፡ጨለመች።
ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ክፍል፡፫።

ወደ፡ፊልጵስዩስ፡ሰዎች፡
የተላከ፡የጳውሎስ፡መልእክት።

ምዕ፡፪፡፭–፲፩።

፭፤ ፍጹማን፡የምትሆኑ፡ሁላችሁ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ ለእኛ፡ያደረገልንን፡ይህን፡ነገር፡
አስቡ።
፮፤ ይኸውም፡እግዚአብሔርን፡ በመልክ፡የሚመ
ስለው፡በባሕርይ፡የሚተካከለው፡ነው፡እግዚ
አብሔርን፡ የሆነው፡ቀምቶ፡አይደለም።
፯፤ ራሱን፡ዝቅ፡አድርጎ፡የአዳምን፡ባሕርይ፡
ገንዘብ፡አድርጎ፡ሰውን፡መሰለ፡እንጂ።
፰፤ እንደ፡ሰውም፡ሆነ፤ለሞት፡እስኪደርስ፡
ድረስም፡እሺ፡በጄ፡ብሎ፡ለሞት፡ታዘዘ፤
ሞቱም፡በመስቀል፡ሆነ።
፱፤ ስለዚህም፡እግዚአብሔር፡ ፈጽሞ፡አከበረው፡
ከስም፡ሁሉ፡የሚበልጥ፡ስምንም፡ሰጠው።
፲፤ በሰማይና፡በምድር፡በባሕርና፡ከምድር፡
በታች፡ያለ፡ጉልበት፡ሁሉ፡ለኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ ስም፡ይሰግድ፡ዘንድ።
፲፩፤ እንደበትም፡ሁሉ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡በእግ
ዚአብሔር፡አብ፡ ጌትነት፡ጌታ፡ እንደሆነ፡
ያምን፡ዘንድ።

ትእዛዝ።

ካህኑ፡ በታላቅ፡ዜማ፡ወዮ፡በሥጋ፡ሞትን፡
የቀመሰ፡ይበል፡ሦስት፡ጊዜ።
ሕዝቡም፡ እየተቀበሉ፡እንደርሱ፡ሦስት፡
ጊዜ፡ይበሉ፤ዲያቆኑ፡ በውርድ፡ንባብ።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

አ፡ዘጥዕመ፡ሞተ፡በሥጋ፡በተስዐቱ፡ሰዓት፡ ዘእንቲአነ ፡ ቅትል ፡ ጥልቀተ ፡ አበሳነ ፡ ክርስቶስ፡አምላክነ፡አድኅነነ።

(ይ፡ካ)፡አ፡ዘጥዕመ፡ከመ፡ቀዳሚ።
(ይሕ)፡ከማሁ።
(ይዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ፡እመዝሙረ፡ዳዊት።

ታው፡ ለትቅረብ፡ስእለትየ፡ኀቤከ፡እግዚኦ፤
ወበከመ፡ቃልከ፡አለብወኒ።
ትብጻሕ ፡ አስተብቍዖትየ ፡ ቅድሜከ ፡ እግዚኦ።
ወበከመ፡ቃልከ፡አድኅነኒ።
ጐሥዓ፡ከናፍርየ፡ስብሐቲከ።
እስመ፡ምህርከኒ፡ኵነኔከ፤ ነበበ፡ልሳንየ፡ ቃለከ።
እስመ፡ጽድቅ፡ኵሉ፡ትእዛዝከ።
ይኩነኒ፡የማንከ፡ከመ፡ያድኅነኒ።
እስመ፡ትእዛዘከ፡አፍቀርኩ።
አፍቀርኩ፡አድኅኖተከ፡እግዚኦ።
ወሕግከሰ፡ተመሃርየ፡ውእቱ።
ትሕየወኒ፡ነፍስየ፡ወእሰብሕከ።
ወይርድአኒ፡ኵነኔ፡ዚአከ።
ተረሳዕኩ፡ከመ፡በግዕ፡ዘተገድፈ፤ኅሥሥ፡ ለገብርከ፡እስመ፡ትእዛዘከ፡ኢረሳዕኩ።
(ይ፡ካ)፡አ፡ዘጥዕመ፡ከመ፡ቀዳሚ።
(ይሕ)፡ከማሁ።
(ይ፡ዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ።
ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ ለዓለም፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
አ፡ዘመጠከ፡ነፍሰከ፡ኀበ፡አብ፡ሶበ፡ተሰቀልከ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ወጼሕከ ፡ ፍኖተ ፡ ለፈያታዊ፡ ዘየማን ፡ ዘተሰቅለ ፡ ምስሌከ ፡ ለበዊእ፡ውስተ፡ገነት፡ኢትትሀየየኒ፡አ፡ኄር፡ ወኢትግድፈኒ፡ኪያየ፡ግዱፈ፡አላ፡ቀድስ፡ ነፍስየ፡ወሥጋየ፡ወአብርህ፡ልብየ።
ወረስየኒ፡ሱታፌ፡ለጸጋ፡ምሥጢርከ፡ዘኢይ መውት፡ከመ፡ሶበ፡ጥዕምኩ፡እምሠናያቲከ አቅርብ፡ለከ፡ስብሐተ፡ዘእንበለ፡ዕርዐት።
ወእፌቱ ፡ ሥነ ፡ ላሕይከ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኵሉ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። 

፩፡ በዘጠኝ፡ሰዓት፡ስለእኛ፡ሞትን፡በሥጋ፡የቀመስክ፡ወዮ፡ፈጣሪያችን፡ክርስቶስ፡ጥልቅ፡የሆነ፡በደላችንን፡አጥፍተህ፡አድነን፡ ይበል።
(ካ)፡አ፡ዘጥዕመ፡እንዳለፈው፡ይበል፡።
(ሕ)፡እንደርሱ፡ይበሉ።
ዲያቆኑ፡ከዳዊት፡መዝሙር፡በውርድ፡ንባብ፡ ይበል።
፪፡ ታው፡– አቤቱ፡ ልመናዬ፡ከፊትህ፡ትቅረብ፤ እንደ፡ቃልህም፡አስተዋይ፡አድርገኝ።
፫፡ አቤቱ፡ምልጃዬ፡ከፊትህ፡ትድረስ።

፬፡ እንደ፡ቃልህም፡አድነኝ።
ከንፈሮቼ፡ጌትነትህን፡ተናገሩ።
ሥርዓትህን፡አስተምረኸኛልና።
አንበደቴ፡ቃልህን፡ተናገረ።
ትዕዛዝህ፡ሁሉ፡እውነት፡ነውና።
፭፡ ቀኝህ፡ያድነኝ፡ዘንድ፡የሚጠብቀኝ፡ይሁን።
ሕግህን፡ወድጀዋለሁና።
፮፡ አቤቱ፡ትድግናህን፡ወደድሁ።
ሕግህ፡ግን፡መምህሬ፡ነው።
፯፡ አመሰግንህ፡ዘንድ፡ሰውነቴ፡በሕይወት፡ትኑርልኝ፤ፍርድህም፡በመከራዬ፡ጊዜ፡ይርዳኝ።
፰፡ እንደ፡ጠፋ፡በግ፡ተዘነጋሁ፤ሕግህን፡አልዘነጋሁምና፡እኔን፡ባርያህን፡ፈልገኝ።
ካህኑ፡እንደ፡ቀድሞው፡አ፡ዘጥዕመ፡ይበል።
(ሕ)፡እንደርሱ፡ይበሉ።
ዲያቆን፡በውርድ፡ንባብ፡ይበል።
፱፡ ለአብ፡ለወልድ፡ለመንፈስ፡ቅዱስ፡ምስጋና፡ ይገባል፤ለዘላለሙ፡አሜን።
፲፡ ወደ፡አብ፡ነፍስህን፡የሰጠህ፡ሆይ፡ወደ፡ገነት፡ ሊገባ፡በቀኝ፡ከአንተ፡ጋር፡ለተሰቀለው፡ ወንበዴ፡በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡በተሰቀልክ፡ ጊዜ፡መንገድ፡የጠረግህለት፡ቸር፡ሆይ፡እኔን፡ የወደቅሁትን፡አትጣለኝ፤ነፍሴንና፡ሥጋዬን፡ አንጽተህ፡ልቤን፡ብሩህ፡አድርግልኝ፡እንጂ።
፲፩፡ የማይለወጥ፡የምሥጢርህንም፡ስጦታ፡ የምቀበል፡አድርገኝ፤ከበጎ፡ሥጦታህም፡እን ደተቀበልኩ፡(እንደቀመስኩ)፡ያለ፡ማቋረጥ፡ ምስጋና፡አቀርብልህ፡ዘንድ።
፲፪፡ ከሁሉም፡ይልቅ፡የጌትነትህን፡ምስጋና፡ እወዳለሁ።

በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

(ይ፡ካ)፡አ፡ዘጥዕመ።
(ይ.ሕ)፡ከማሁ።
(ይ፡ዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ።

፲፫፡ አ፡ክርስቶስ፡አምላክነ፡አድኅነነ፡ይእዜኒ፡ወዘልፈኒ፡ወለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፲፬፡ አ፡ዘበእንቲአነ፡ተወለድከ፡እምድንግል፡ወጾርከ፡ስቅለተ፡አ፡ኄር፡ወአሞትከ፡ሞተ፡በሞትከ፡ወአግሀድከ፡ትንሣኤ።

(ይካ)፡አ፡ዘጥዕመ።
(ይ.ሕ)፡ከማሁ።
(ይ.ዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ።

፲፭፡ አ፡ክርስቶስ፡አምላክነ፡ኢትትሀየይ፡ዘለሐኮ፡በእዴከ፡ወአርኢ፡አፍቅሮተከ፡ሰብአ።

፲፮፡ አ፡መሐሪ፡ወተወከፍ፡አስተብቍዖታ፡ለወላዲትከ፡ዘበእንቲአነ፡ወአድኅን፡ሕዝበከ፡ትሑታነ፡ወኢትትሀየየነ፡ለዝሉፉ።

፲፯፡ ወኢትመጥወነ፡ለግሙራ፡በእንተ፡ስምከ፡ወኢትሚጥ፡ኪዳነከ፡ወኢታርኅቅ፡ምሕረተከ፡እምኔነ፤በእንተ፡አብርሃም፡ፍቁርከ፡ወበእንተ፡ይስሐቅ፡ቍልዔከ፡ወበእንተ፡እሥራኤል፡ቅዱስከ።

(ይካ)፡አ፡ዘጥዕመ።
(ይ.ሕ)፡ከማሁ።
(ይ.ዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ።

፲፰፡ ሶበ፡ነጸረ፡ፈያታዊ፡ርእሰ፡ሕይወት፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ስቁለ፡ይቤ፡ሶበሰኬ፡ኢኮነ፡ዘስቁል፡ምስሌነ፡አምላክ፡ዘተሠገወ፡እምኢኀብአ፡ፀሐይ፡ጸዳሎ፡ወምድርኒ፡እምኢያድለቅለቀት፡በረዓድ፡ዳእሙ፡ከሃሌ፡ኵሉ።

፲፱፡ ተዘከረኒ እግዚእ፡አመ፡ትመጽእ፡በመንግሥትከ።

(ይካ)፡አ፡ዘጥዕመ፡ሞተ፡በሥጋ።
(ይ.ሕ)፡ከማሁ።
(ይ.ዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ፡
ስብሐት፡ለአብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ።

፳፡ አ፡ዘተወከፍከ፡አሚኖቶ፡ለፈያታዊ፡በዲበ፡መስቀል፡ተወከፈኒ፡ኀቤከ።

፳፩፡ ንህነ፡እለ፡ድልዋነ፡ለፍትሐ፡ሞት፡በእንተ፡አበሳነ፡ንትአመን፡ከማሁ፡ኃጣውኢነ፡ወናነብብ፡መለኮተከ፡ወንጸርሕ፡ምስሌሁ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ካህኑ፡አ፡ዘጥዕመ፡ይበል፤
ሕዝቡም፡እንደርሱ፡ይበሉ።
ዲያቆን፡በውርድ፡ንባብ።

፲፫፡ ፈጣሪያችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡አድነን፡ዛሬም፡ዘወትርም፡ለዘላለሙ፡አሜን።

፲፬፡ ስለ፡እኛ፡ድኅነት፡ከድንግል፡የተወለድከ፡ሆይ፤መከራ፡መስቀልንም፡ተሸከምከ፤ቸር፡ሆይ፡በሞትህ፡ሞትን፡አጥፍተህ፡ትንሣኤን፡ገለጽከ።

ካህኑ፡አ፡ዘጥዕመ፡ይበል፡
ሕዝቡም፡እንደርሱ፡ይበሉ።
ዲያቆን፡በውርድ፡ንባብ።

፲፭፡ ፈጣሪያችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡በእጅህ፡የፈጠርከውን፡ቸል፡አትበል፤ሰው፡መውደድኅንም፡ግለጽ።

፲፮፡ ይቅር፡ባይ፡ሆይ፡ስለእኛ፡የምታደርገውን፡የእናትህን፡ምልጃ፡ተቀበል፤የተዋረዱ፡ወገኖችህን፡አድን፤ለዘወትርም፡ቸል፡አትበለን።

፲፯፡ ስለ፡ስምህ፡ብለህ፡ፈጽመህ፡ለጠላት፡አሳልፈህ፡አትስጠን፤ቃል፡ኪዳንህንም፡አትለውጥብን፤ይቅርታህንም፡ከእኛ፡አታርቅ፡ስለ፡ወዳጅህ፡ስለ፡አብርሃም፡ስለ፡ልጅህ፡ስለ፡ይስሐቅ፡ብለህ፡ስለ፡ቅዱስህ፡(በስምህ፡ስለ፡ጠራኸው፡) ስለ፡ያዕቆብም፡ብለህ፡አድነን።

ካህኑ፡አ፡ዘጥዕመ፡ይበል፤
ሕዝቡ፡እንደርሱ፡ይበሉ።
ዲያቆኑ፡በውርድ፡ንባብ።

፲፰፡ ፈያታዊው፡የሕይወትን፡ራስ፡በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡ተሰቅሎ፡በአየ፡ጊዜ፡እንዲህ፡አለ፤ከእኛ፡ጋር፡የተሰቀለው፡ሰው፡የሆነ፡አምላክ፡ባይሆን፡ኖሮ፡ፀሐይ፡ብርሃኑን፡ባልሠወረም፡ነበር፤ምድርም፡በመንቀጥቀጥ፡ባልተነዋወጠች፡ነበር፤እርሱ፡ሁሉን፡የሚችል አምላክ፡ቢሆን፡ነው፡እንጂ።

፲፱፡ አቤቱ፡በጌትነትህ፡በምትመጣ፡ጊዜ፡አስበኝ።

ካህኑ፡አ፡ዘጥዕመ፡ይበል፡
(ሕዝቡ)፡እንደርሱ፡ይበሉ።
ዲያቆን፡በውርድ፡ንባብ።
ለአብ፡ለወልድ፡ለመንፈስ፡ቅዱስ፡ምስጋና፡ይገባል፡ይበል።

፳፡ በመስቀል፡ላይ፡ሳለህ፡የፈያታዊን፡እምነት፡የተቀበልክ፡ሆይ፡ወዳንተ፡አቅርበኝ።

፳፩፡ እኛ፡ስለ፡በደላችን፡ለሞት፡ፍርድ፡የተገባን፡ስንሆን፡ኃጢአታችንን፡እንታመናለን፤ጌትነትህንም፡እንናገራለን፤በጌትነትህ፡በመጣህ፡

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ዘላነ፡እንዘ፡ንብል፡ተዘከረነ፡እግዚእ፡አመ፡
ትመጽእ፡በመንግሥትከ።
(ይካ)፡አ፡ዘጥዕመ፡ሞተ፡በሥጋ።
(ይሕ)፡ከማሁ።
(ይዲ)፡በንባብ፡ማሕዘኒ።
፳፱ ወይእዜኒ፡ሶበ፡ነጸረት፡ወላዲቱ፡ኀበ፡በግዕ፡
ናባዊ፡ወመድኀነ፡ዓለም፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡
ስቁል ትቤ፡እንዘ፡ትበኪ፡እስመ፡ዓለም፡
ይትፌሣሕ፡በተወክፎቱ፡መድኃኒተ፡ወአማ
ዑትየሰ፡ይውዒ፡ሶበ፡ነጸርኩ፡ውስተ፡
ስቅለትከ፡ዘአንተ፡ዕጉሥ፡ላዕሌሃ፡በእንተ፡
ሕይወተ፡ኵሉ፡አ፡ወልድየ፡ወአምላኪየ፡
ወመድኀንየ።
(ይካ)፡አ፡ዘጥዕመ፡ሞተ፡በሥጋ።
(ይሕ)፡ከማሁ።

ትእዛዝ።
ወእምዝ፡ያዕርጉ፡ዕጣነ።
(ይዲ)፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፳፰፡፳፩–፳፪።
ወወደዩ፡ሐሞተ፡ውስተ፡መብልዕየ።
ወአስተዩኒ፡ብሒአ፡ለጽምእየ።
ለትኩኖሙ፡ማእዶሙ፡መሥገርተ፡በቅድ
ሜሆሙ።

ወንጌል፡ዘማቴዎስ።
ምዕ፤፳፯፡፵፮–፶።
፵፮ ወጊዜ፡ተሱዓት፡ሰዓት፡ጸርሐ፡እግዚእ፡
ኢየሱስ፡በቃል፡ዐቢይ፡እንዘ፡ይብል፡
ኤሎሄ፡ኤሎሄ፡ላማ፡ሰበቅታኒ፡ዝ፡ውእቱ፡
ብሂል፡አምላኪየ፡አምላኪየ፡ለምንት፡
ኀደገኒ።
፵፯ ወሰሚያሙ፡እለ፡ይቀውሙ፡ህየ፡ይቤሉ፡
ዝሰ፡ኤልያስሃ፡ይጼውዕ።
፵፰ ወውእተ፡ጊዜ፡ሮጸ፡አሐዱ፡እምኔሆሙ፡
ወነሥአ፡ሰፍነገ፡ወመልአ፡ብሒአ፡ወአሰረ፡
ውስተ፡ኀለት፡ወአስአዘዞ፡ውስተ፡አፉሁ።
፵፱ ወበ፡እለ፡ይቤሉ፡ኅድጉ፡ንርአይ፡ለእመ፡
፶ ይመጽእ፡ኤልያስ፡ያድኅኖ።
ወጸርሐ፡ካዕበ፡እግዚእ ኢየሱስ፡በዐቢይ፡
ቃል፡ወወፅአት፡መንፈሱ፡ሶቤሃ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት። 

ጊዜ፡አቤቱ፡አስበን፡እያልን፡ከእርሱ፡
ከፊያታይ፡ጋር፡እንጮኻለን።
(ካህኑ)፡አ፡ዘጥዕመ፡ይበል፡
(ሕዝቡም)፡እንደርሱ፡ይበሉ።
(ዲያቆኑ)፡በውርድ፡ንባብ።
፳፱፤ አሁንም፡ወደ፡ዓለም፡መድኃኒት፡መሥዋዕት፡
ወደሆነው፡ወደ፡ጠባቂያችን፡በዕፀ፡መስቀል፡
ላይ፡ተሰቅሎ፡እናቱ፡ባየች፡ጊዜ፡እያለቀሰች፡
እንዲህ፡አለች፤ዓለም፡ድኅነትን፡በመቀበሉ፡
ደስ፡ይለዋል፤ልጄ፡ሆይ፡ፈጣሪዬና፡
መድኃኒቴ፡ስለ፡ሁሉ፡ሕይወት፡ብለህ፡ወደ፡
ታገሥከት፡ወደ፡ስቅለትህ፡በተመለከትኩ፡
ጊዜ፡አንጀቴ፡ተቃጠለ፡አለች፡ይበል።
(ካህኑ)፡ወዮ፡ሞትን፡በሥጋ፡የቀመሰ፡ይበል።
(ሕዝቡ)፡እንደርሱ፡ይበሉ።

ትእዛዝ።
ከዚህ፡በኋላ፡ዕጣን፡ያሳርጉ።
ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፤፳፰፡፳፩–፳፪።
በምግቤ፡ውስጥ፡ሐሞትን፡ጨመሩ።
ጥማቴንም፡ለማርካት፡መፃፃውን፡አጠጡኝ።
ማዕዳቸው፡በፊታቸው፡ወጥመድ፡ትሁን
ባቸው፡ይበል።

የማቴዎስ፡ወንጌል።
ምዕ፤፳፯፡፵፮–፶።
፵፮፤ በዘጠኝ፡ሰዓትም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡
ኤሎሄ፤ኤሎሄ፤ላማ፡ሰበቅታኒ፡ብሎ፡በታ
ላቅ፡ድምፅ፡ጮኸ፤ይኸውም፡አም
ላኪየ፤አምላኪየ፡ለምን፡ተውከኝ፡ማለት፡
ነው።
፵፯፤ ከዚያ፡ቆመው፡የነበሩትም፡በሰሙ፡ጊዜ፡
ይኸስ፡ኤልያስን፡ይጠራል፡አሉ።
፵፰፤ ያን፡ጊዜም፡ከእነርሱ፡አንዱ፡ሮጠና፡ጁህ፡
ወስዶ፡መጣጣውን፡መልቶ፡በዘንግ፡አስሮ፡
በአፉ፡ላይ፡ጨመቀው።
፵፱፤ ኤልያስ፡መጥቶ፡ያድነው፡እንደሆነ፡ተዉት፤
እንይ፡ያሉም፡አሉ።
፶፤ ዳግመኛም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡በታላቅ፡ድምፅ፡
ጮኸ፤ነፍሱን፡ከሥጋው፡ለየ።

Scanned by CamScanner

## በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ይካ፡ይዲ፡ይሕ፡ከመ፡ቀዳሚ።
ጊዜ፡ተስዐቱ፡ሰዓት፡ጸርሐ፡ኢየሱስ፡በቃሉ፡
ወይቤ፡ኤሎሂ፡ኤሎሂ።
ይ፡ካ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡፫፡ጊዜ።

### ወንጌል፡ዘማርቆስ።

ምዕ፤፲፭፡፴፬–፴፯።

፴፬፤ ወጊዜ፡ተሱዐት፡ሰዓት፡ገዐረ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡በዐቢይ፡ቃል፡ወይቤ፡ኤሎሂ፡ኤሎሂ፡ላማ፡ሰበቅታኒ፡ዘበትርጓሜሁ፡ይብል፡አምላኪየ፡
አምላኪየ፡ለምንት፡ኀደገኒ።

፴፭፤ ወቦ፡እለ፡ይቤሉ፡እምእለ፡ይቀውሙ፡ህየ፡ኤልያስሃ፡ይጼውዕ።

፴፮፤ ወሮጸ፡አሐዱ፡ወመልአ፡ሰፍነገ፡ብሒአ፡ወአሰረ፡በኀለት፡ወአስተዮ።
ወይቤ፡ኅድጉ፡ንርአይ፡ለእመ፡ይመጽእ፡ኤልያስ፡ያውርዶ።

፴፯፤ ወገዐረ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡በዐቢይ፡ቃል፡ወመጠወ፡ነፍሶ።

ይካ፡ይዲ፡ይሕ፡ከመ፡ቀዳሚ።
ጊዜ፡ተሰዓቱ፡ሰዓት፡ከልሐ፡ኢየሱስ፡በቃሉ፡ወአማኀፀነ፡ነፍሶ፡ሶቤሃ።
(ይ፡ካ)፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡፫፡ጊዜ።

### ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፤፳፫፡፵፭–፵፮።

፵፭፤ ወጸልመ፡ፀሐይ፡ወተሠጠ፡መንጦላዕተ፡ምኵራብ፡እምላዕሉ፡እስከ፡ታሕቱ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

ካህኑ፤ዲ፡ሕ፤እንዳለፈው፡ይበሉ።
በዘጠኝ፡ሰዓት፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ቃሉን፡አሰምቶ፡ኤሎሂ፡ኤሎሂ፡አለ።
ካህኑ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ሦስት፡ጊዜ፡ይበል፡

### የማርቆስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፲፭፡፴፬–፴፭።

፴፬፤ ዘጠኝ፡ሰዓት፡በሆነ፡ጊዜም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡በታላቅ፡ድምጽ፡ኤሎሂ፤ኤሎሂ፡ላማ፡ሰበቅታኒ፡ብሎ፡ጮኸ፤ትርጓሜውም፡አምላኪየ፡አምላኪየ፡ለምን፡ተውኸኝ፡ማለት፡ነው።

፴፭፤ ከዚያ፡ቆመው፡ከነበሩትም፡ኤልያስን፡ይጠራል፡ያሉ፡አሉ።

፴፮፤ አንዱም፡ሮጦና፡በዐይነ፡በኀው፡መፃፃውን፡መልቶ፡በዘንግ፡አስሮ፡አጠጣው።
ዝም፡በሉ፡ኤልያስ፡መጥቶ፡ያወርደው፡እንደሆነ፡እንይ፡አለ።

፴፯፤ ጌታ፡ኢየሱስም፡በታላቅ፡ቃል፡ጮኸ፤ነፍሱንም፡ከሥጋው፡ለየ።

ካህኑ፤ዲያቆኑ፤ሕዝቡ፤እንዳለፈው፡ይበሉ።
በዘጠኝ፡ሰዓት፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ቃሉን፡አሰምቶ፡ተናገረ፤ያን፡ጊዜም፡ነፍሱን፡አደራ፡ሰጠ።
ካህኑ፡ቅዱስ፡እግዚአብሔር፡ቅዱስ፡ኃያል፡ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ሦስት፡ጊዜ፡ይበል።

### የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፳፫፡፵፭–፵፮።

፵፭፤ ፀሐይ፡ጨለመ፤የምኵራቡም፡መጋረጃ፡ከላይ፡እስከ፡ታች፡ተቀደደ።

ዘከመ ሰትየ እግዚእነ ብሒአ ወመጠወ ነፍሶ ለሞት ።



ጌታችን መጻጻውን ቀምሶ ነፍሱን ለሞት እንደሰጠ።

፵፮፤ ወሶቤሃ፡ጸርሐ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡በዐቢይ፡ቃል፡ወይቤ፡አባ፡ውስተ፡እዴከ፡አመሐፅን፡ነፍስየ፤
ወዘንተ፡ብሂሎ፡መጠወ፡ነፍሶ።
ይካ፤ይዲ፤ይሕ፤ከመ፡ቀዳሚ።
ጊዜ፡ተስዐቱ፡ሰዓት፡ገዓረ፡ኢየሱስ፡በቃሉ፡ወወጽአት፡መንፈሱ፡ሶቤሃ።

፵፮፤ ያን፡ጊዜም፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ድምፁን፡ከፍ፡አድርጎ፡አባት፡ሆይ፤ነፍሴን፡በእጅህ፡አደራ፡እሰጣለሁ፡ብሎ፡ጮኸ።
ካህኑ፤ዲያቆኑ፤ሕዝቡ፡እንዳለፈው፡ይበሉ።
በዘጠኝ፡ሰዓት፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ቃሉን፡አሰምቶ፡ጮኸ፤ያን፡ጊዜም፡ነፍሱ፡ከሥጋው፡ተለየች።

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

**(ይ፡ካ)** ቅዱስ፡**እግዚአብሔር፡** ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡፫፡ጊዜ።

ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፲፱፡፳፰–፴።

፳፰ ወእምዝ፡ሶበ፡አእመረ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ፡**
ከመ፡ተፈጸመ፡ኵሉ፡ከመ፡ይብጻሕ፡ቃለ፡
መጽሐፍ፡ይቤ፡ጸማእኩ።
፳፱ ወቦ፡ ህየ ፡ ግምዔ ፡ ዘምሉዕ ፡ ብሒአ ፡
ወመልኡ፡ ሰፍነገ ፡ እምብሒእ ፡ ወአሰሩ ፡
በቈጽለ፡ሁስጱ፡ዲበ፡ኀለት፡ወአስተርከቡ፡
ውስተ፡አፉሁ፡ወዐጸሩ።
፴ ወሠረቦ፡**እግዚእ፡ኢየሱስ፡** ብሒአ፡ይቤ፡
ተፈጸመ፡ኵሉ፡ወአጽነነ፡ርእሶ፡ወመጠወ፡
ነፍሶ።

**ይካ፤ይዲ፤ይሕ፤** ከመ፡ቀዳሚ።

ጊዜ፡ተስዐቱ፡ሰዓት፡አጽነነ፡ርእሶ፡ኢየሱስ፡
ወይቤ፡ተፈጸመ፡ኵሉ።

**(ይ፡ካ)** ፡ቅዱስ፡**እግዚአብሔር፡** ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡፫፡ጊዜ፡በል።

ድኅረ፡ወንጌል፡**በተስዐቱ፡ሰዓት፡ዘዓርብ።**

፩ እምትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ዓመቲከ ፡
ኢተኀልቅ ፡ ወእምቅድመ ፡ ፀሐይ ፡ ሀሎ ፡
ስምከ፤ተርእይከ፡ዮም፡ስቁለ፡ዲበ፡ዕፀ፡
መስቀል።
፪ አ፡ኖላዊሆሙ፡ለኵሉ፡ፍጥረት፡እፎ፡ደፈሩ፡
ላዕሌከ፡ዐላውያን፡እሊአከ።

፫ አ፡ለብሓዊ፡ዘሰሐበ፡ኀቤሁ፡ልሕኵተ፡አ፡
ዐቃቤ፡ሥራይ፡ዘበአማን፡ቍሱላኒሆሙ፡
ፈወስከ።
፬ አዕረጉከ፡ዲበ፡ዕፅ፡ከመ፡ገባሬ፡እከይ፡
ሕዝብ፡ዘምሉአን፡ኀጢአተ፡እልክቱ፡እለ፡
አልዐሉ፡ቃሎሙ፡እኪተ፡እንዘ፡ይብሉ፡
አልብነ፡ንጉሥ፡ዘእንበለ፡ቄሳር።
፭ ወሶበ፡ቀርበ፡ጊዜ፡ተስዐቱ፡ሰዓት፡
መድኃኒነ፡ስቁል፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ከሠተ፡
አፉሁ፡በነገረ፡ሱርስት፡እንዘ፡ይብል፡ከመ፡
ዝ፡**ኤሎሄ፡ኤሎሄ፡ላማ፡ሰበቅታኒ፡** ዘውእቱ፡
**አምላኪየ፡አምላኪየ፡** ለምንት፡ኀደገኒ፡
አሰከ፡ፈርሁ፡ኵሎሙ፡እለ፡የዐውድዎ፤
ከመዝ፡ጽሑፍ፡ውስተ፡መዝሙር።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

**ካህኑ፡** ቅዱስ፡**እግዚአብሔር፡** ቅዱስ፡ኃያል፡
ቅዱስ፡ሕያው፡ዘኢይመውት፡ይበል፡፫፡ጊዜ።

የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፲፱፡፳፰–፴።

፳፰፤ ከዚህም፡በኋላ፡**ጌታ፡ኢየሱስ፡** ሁሉ፡እንደ፡
ተፈጸመ፡አይቶ፡የመጽሐፍ፡ቃል፡ይፈጸም፡
ዘንድ፡ተጠማሁ፡አለ።
፳፱፤ ከዚያም፡መፃፃን፡የተመላ፡ማሰሮ፡ነበር፤
ከመፃፃው፡ሰፍነጉን፡ነክረው፡በአሽክት፡
ቅጠል፡ከዘንግ፡ላይ፡አስረው፡አስጠግተው፡
ከአፉ፡ውስጥ፡ጨመቁት።
፴፤ **ጌታ፡ኢየሱስም፡** መፃፃውን፡ጕር
ጕጭ፡አድርጎ፡ሁሉ፡ተፈጸመ፡አለና፡ራሱን፡
ዘለስ፡(ዘንበል)፡አድርጎ፡ነፍሱን፡ከሥጋው፡ለየ።

**ካህኑ፤ዲያቆኑ፡ሕዝቡ፤** እንዳለፈው፡ይበሉ።

በዘጠኝ፡ሰዓት፡ጌታ፡ኢየሱስ፡ራሱን፡ዘንበል፡
(ዘለስ)፡አድርጎ፡ሁሉ፡ተፈጸመ፡አለ።

**ካህኑ፡** ቅዱስ፡**እግዚአብሔር፡** ቅዱስ፡ኃያል፡ቅዱስ፡
ሕያው፡ዘኢይመውት፡ሦስት፡ጊዜ፡ይበል።

ከወንጌል፡በኋላ፡**ዐርብ፡በዘጠኝ፡ሰዓት፡**
የሚነበብ፡ይህ፡ነው።

፩፤ የፍጥረቱ፡ሁሉ፡ጠባቂያቸው፤ለልጅ፡ልጅ፡
ዘመንህ፡የማያልቅ፡ከፀሐይ፡አስቀድሞ፡
ስምህ፡የነበረ፡ዛሬ፡በዕንጨት፡መስቀል፡
ላይ፡ተሰቅለህ፡ታየህ።
፪፤ የፍጥረቱ፡ሁሉ፡ጠባቂ፡ሆይ፡ወገኖችህ፡
የነበሩ፡እሊህ፡ወንጀለኞች፡ይህን፡
ለመሥራት፡በአንተ፡ላይ፡እንዴት፡ደፈሩ?
ፍጥረቱን፡ወደ፡እርሱ፡ያቀረብክ፡ሠሪ፡ሆይ!
፫፤ ባለ፡መድኃኒት፡ሆይ! በዕውነት፡የቈሰ
ሉትን፡ፈወስክ።
እሊህ፡ኃጢአትን፡የተመሉ፡ወገኖች፡
፬፤ የከፋች፡ቃላቸውን፡ከፍ፡አድርገው፡ከቄሳር፡
በቀር፡ንጉሥ፡የለንም፡ያሉ፡እንደ፡ክፉ፡ሠሪ፡
በመስቀል፡ላይ፡አውጥተው፡ሰቀሉህ።
ዘጠኝ፡ሰዓትም፡ሲቃረብ፡**ጌታችን፡መድኃኒ**
፭፤ **ታችን፡** በመስቀል፡ላይ፡ሳለ፡በሱርስት፡
ቋንቋ፡አንደበቱን፡ገልጾ፡**ኤሎሄ፡ኤሎሄ፡**
**ላማ፡ሰበቅታኒ፡** አለ፤ይኸውም፡**አምላኪየ፡**
**አምላኪየ፡** ለምን፡ተውከኝ፡ማለት፡ነው፤
በዙሪያው፡የነበሩ፡እስኪፈሩ፡ድረስ፡
እንደዚህ፡በመዝሙረ፡ዳዊት፡ተጽፎአልና።

Scanned by CamScanner

በ፱፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፩፡ ወሶበ ፡ ቀርበት ፡ ኀቤሁ ፡ ዘኮነ ፡ የአምራ ፡
ውእቱ፡ባሕቲቱ፡አውሥአ፡ወይቤ፡ጸማእኩ፡
ይእዜ፡እስመ፡ውእቱ፡ማእምር፡ዘተጽሕፈ፡
በእንቲአሁ።
፪፡ ወነሥአ ፡ አሐዱ ፡ ብሒአ ፡ በሰፍነግ ፡
ወአዕረጋ፡ዲበ፡ኀለት፡ወአስተዮ።

፫፡ ወጥዕመ፡ብሒአ፡ወይቤ፡ናሁ፡ተፈጸመ፡
ቃለ፡ዳዊት፡ዘይቤ፡በመዝሙር።
፬፡ ወእምድኅረ፡ብሒእ፡አድነነ፡ርእሶ፡ወጸርሐ፡
በቃሉ፡ወመጠወ፡ነፍሶ።

፲፡ መኑ፡ይዜንዎሙ፡ለፂውዋን፡መኑ፡ይቀድም፡
ኀበ፡ገነት፡ከመ፡ያስተዳሉ፡ፍኖተ፡ቅድመ፡
ንጉሥ።
፲፩፡ ፍሥሐ ፡ ይከውን ፡ ለክሙ ፡ አ ፡ ጻድቃን ፡
ወነቢያት፡ወሊቃነ፡ጳጳሳት፡ወቅዱሳን።
፲፪፡ ወብእሲ ፡ ቀዳሚ ፡ መኰንን ፡ ዘበልየ ፡
በሕማማት፡ተሐደሰ፡ዮም፡በእንተ፡ብእሲ፡
ሐዲስ፡ዘቀተሎ፡ለሞት፡ወኀይሎሂ፡ዕጽብተ፡
ረሰየ፡ዕርቅተ፡ወአዕርዐ፡ፍጹመ።

፲፫፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ገሀነም ፡
በነፍስ ፡ ዘነሥአ ፡ እምዘመድነ ፡ ወረሰያ ፡
አሐደ፡ምስለ፡መለኮቱ።
፲፬፡ ወለነፍሳት ፡ እለ ፡ ነበራ ፡ ውስተ ፡ ሞቅሕ ፡
አዕረጎን፡ምስሌሁ፡በከመ፡ዕበየ፡ምሕረቱ።
፲፭፡ ወአሰሮ፡ለጸላኢ፡ዘውእቱ፡ሰይጣን፡በመዋ
ቅሕት፡ወሰናስል።
፲፮፡ ወሶበ ፡ ርእይዎ ፡ ዐቀብት ፡ እኩያን ፡ ወሐራ
ቲሆሙ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡
ጐዩ፡ወሐሩ።
፲፯፡ ወኢክህሉ ፡ ይቁሙ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡
አእመሩ ፡ ኀይሎ ፡ ወብዝኀ ፡ ጽንዐ ፤ ወለአ
ናቅጸ፡ብርት፡ሰበሮሙ፡በሥልጣኑ።
፲፰፡ ወለመናሥግተ ፡ ኀጺን ፡ ሰበሮሙ ፡ ወቀጥ
ቀጦሙ።
፲፱፡ ፂውዋን፡ሶበ፡ርእይዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡
መድኀኔ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ጸርሑ ፡ በቃል ፡
ወይብሉ፡ሠናይ፡ምጽአትከ፡አ፡ባላሒሆሙ፡
ለአግብርቲከ።
፳፡ አኀዘ፡ቅድመ፡እዴሁ፡ለአዳም፡ወሰሐቦ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

፩፡ እርሱ ፡ ብቻውን ፡ የሚያውቃት ፡ ሰዓት ፡
በደረሰች፡ጊዜ፡መልሶ፡ተጠማሁ፡አለ፤ስለ፡
እርሱ፡የተጻፈውን፡እርሱ፡ያውቃልና።

፪፡ ከእነርሱም፡አንዱ፡ዓይነ፡በጎውን፡ወስዶ፡
ከመፃፃው፡ነከረው፤በዘንግ፡ላይ፡አስሮ፡ወደ፡
አፉ፡አስጠግቶ፡አጠጣው።
፫፡ መፃፃውንም ፡ ቀምሶ ፡ ዳዊት ፡ በመዝሙሩ፡
የተናገረው፡ተፈጸመ፡አለ።
፬፡ ከመፃፃውም፡በኋላ፡ራሱን፡ዘለስ፡(ዘንበል)፡
አድርጎ፡ ድምፁን ፡ አሰምቶ ፡ ነፍሱን ፡
ከሥጋው፡ለየ።
፲፡ ለምርኮኞች፡የምስራች፡ማን፡ይነግራቸዋል?
በንጉሥ፡ፊት፡መንገድን፡ለማዘጋጀት፡ማን፡
ወደ፡ገነት፡ይቀድም፡ይሆን?
፲፩፡ ጻድቃን ፡ ነቢያት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱሳን፡
ሆይ፡ደስታ፡ለእናንተ፡ይገባችኋል።
፲፪፡ ገዥ ፡ የነበረ ፡ የቀደመው ፡ ሰው ፡ አዳም፡
አርጅቶ ፡ የነበረ ፡ በጌታ ፡ ሕማማት ፡ ዛሬ፡
ታደሰ ፤ ሞትን ፡ ስለ ፡ አጠፋው ፡ ስለ ፡ አዲሱ፡
ሰው ፡ ታደሰ ፤ አስጨናቂ ፡ የነበረች ፡ የሞትን፡
ኃይል፡ባዶ፡አደረገ፤ፈጽሞም፡አጠፋት።
፲፫፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከባሕርያችን ፡
በነሣትና፡ ከመለኮቱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ በአደ
ረጋት፡በአካለ፡ነፍስ፡ወደ፡ሲኦል፡ሄደ።
፲፬፡ በግዞት ፡ የነበሩትንም ፡ ነፍሳት ፡ እንደ
ቸርነቱ፡ገናናነት፡ከእርሱ፡ጋር፡አወጣቸው።
፲፭፡ ጠላትንም ፡ በሰንሰለትና ፡ በእግር ፡ ብረት፡
አሰረው፤እርሱም፡ሰይጣን፡ነው።
፲፮፡ ጠባቆች ፡ የነበሩና ፡ በጨለማ ፡ የሚኖሩ፡
ክፉዎች ፡ አጋንንትም ፡ ሠራዊቶቻቸውም፡
ባዩት፡ጊዜ፡ፈጽመው፡ሸሽተው፡ሄዱ።
፲፯፡ ሊቆሙ፡አልቻሉም፤እነርሱ፡የጸናች፡ኃይሉን፡
ሥልጣኑንም፡ዐውቀዋልና፤የነሐስ፡መዝጊያ
ችንም፡በሥልጣኑ፡ሰብሮአቸዋልና።
፲፰፡ የብረት፡መቆለፊያዎችንም፡ቀጥቅጦ፡አደቀ
ቋቸዋልና።
፲፱፡ የነፍሳቸው ፡ መድኃኒት ፡ የሆነ ፡ ጌታችን፡
ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ምርኮኞች፡ባዩት፡ጊዜ፡
ባሮችህን ፡ የምታድን ፡ ሆይ ፡ መምጣትህ፡
መልካም፡ነው፡ብለው፡ጮኹ።
፳፡ አስቀድሞ ፡ የአዳምን ፡ እጅ ፡ ይዞ ፡ ሰቦ፡

## በ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወአዕረጎ፡ወለደቂቁ፡ምስሌሁ፡አዕረጎሙ፡ወወሰዶሙ፡ኀበ፡ገነት፡ማኅደረ፡ትፍሥሕት፡ወዕረፍት።

እመጽሐፈ፡ኪዳን፡ዘመሐረ፡**እግዚእነ፡ወአምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡**ለሐዋርያቲሁ፡ቅዱሳን።

፩ መጺአ፡እምድኅረ፡ሐመ፡ወወሪዶ፡ውስተ፡ሲኦል፡ዘውእቱ፡ነፍሰ፡ምውታን፡ዔወወ፡ለሕይወት።

፪ ዘ፡ውእቱ፡**እግዚእ፡**ዘርእዮ፡ሞት፡እንዘ፡ይወርድ፡ኀቤሁ፡ተደመ፡ጌገዮ፡ወአምሰሎ፡ዘቦቱ፡ከመ፡ያለምድ፡ውኂጠ።

፫ ርእየ፡በላዕሌሁ፡ሥነ፡**መለኮቱ፡**ጸርሐ፡በልዑል፡ቃል፡እንዘ፡ይብል፡መኑ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡ዘእምሥልጣንየ፡ሰብአ፡ለቢሶ፡ዘሀሎ፡ኀቤየ፡ሊተ፡ሞእኒ።

፬ መኑ፡ውእቱ፡ዘእምሥልጣንየ፡ዘሐደሶ፡ለሥጋ፡እምነ፡ህጕል፡ወተወክፎ፡እሙስና።

፭ መኑ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡እንበለ፡ሙስና፡ዘተወልደ፡ወተወክፎ፡ለሙስና፡ውእቱሰ፡ኢይማስን።

፮ መኑ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡ዘለብሰ፡ሰብአ፡ምድራዊ፡ውእቱሰ፡ሰማያዊ፡ውእቱ።

፯ መኑ፡ዝንቱ፡ዘነኪር፡እምሕግየ፡መኑ፡ውእቱ፡ዘእምዚአየ፡ይዔውዎሙ፡ለአሕዛብ፡እለ፡ነበሩ፡ኀቤየ።

፰ መኑ፡ውእቱ፡ዘኮነ፡ሲሳየ፡ለኀይለ፡ነደ፡እሳት፡ወሞት፡ወውእቱሰ፡ሞአሙ።

፱ መኑ፡ዝንቱ፡ዘኢይክሉ፡መዛግብተ፡ጽልመት፡ከመ፡ይሞቅሕዎ።
መኑ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡ዘሀሎ፡በዝንቱ፡አርአያ፡ወስብሐት፡ሐዲስ።

፲ ውኂደ፡ዚአሁ፡ትክልአኒ፡እግበር፡ዘአፈቅድ፡ቦቱ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፱፡ሰዓት።

አወጣው፤ከዚያም፡ልጆቹን፡ከእርሱ፡ጋር፡አውጥቶ፡የተድላ፡ደስታና፡የዕረፍት፡ቦታ፡ወደ፡ሆነች፡ገነት፡ወሰዳቸው።

**ጌታችን፡ፈጣሪያችንና፡መድኃኒታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡**ለንጹሐን፡ሐዋርያቶቹ፡ከአስተማረው፡ከኪዳን፡መጽሐፍ፡የተገኘ፡ይህ፡ነው።

፩፡ ወደዚህ፡ዓለም፡መጥቶ፡በሰውነቱ፡መከራ፡ከተቀበለ፡በኋላ፡ወደ፡ሲኦል፡ወርዶ፡የሙታንን፡ነፍስ፡ለሕይወት፡ማረከ።

፪፡ ይህም፡**ጌታ፡**ነው፤በሥጋ፡መከራ፡ከተቀበለ፡በኋላ፡በአካለ፡ነፍስ፡ወደ፡ሲኦል፡ሲወርድ፡ዲያብሎስ፡አየው፤ወደ፡እርሱም፡ተመልክቶ፡ተደነቀ፤ስሁት፡ነህ፡አለው፤ቍራኝነትንም፡ያስለመደበት፡ዕሩቅ፡ብእሲ፡ንም፡አስመሰለው።

፫፡ በላዩ፡ያለ፡ባሕርየ፡**መለኮቱን፡**አይቶ፡በእኔ፡ሥልጣን፡ተይዞ፡የነበረ፡ሥጋን፡ተዋሕዶ፡ድል፡ያደረገኝ፡ይህ፡ማነው?ብሎ፡በታላቅ፡ድምፅ፡ጮኸ።

፬፡ በእኔ፡ሥልጣን፡ተይዞ፡የነበረን፡ሥጋ፡ያደሰው፡ከጥፋትም፡ተቀብሎ፡ያዳነው፡ይህ፡ማነው?አለ።

፭፡ ያለ፡መለወጥ፡የተወለደ፡ይህ፡ማነው?የሚለ ወጥንም፡ባሕርየ፡ሥጋ፡ገንዘብ፡ያደረገ፡እርሱ፡ግን፡አይለወጥም።

፮፡ ምድራዊ፡ሥጋን፡የተዋሐደ፡ይህ፡ማነው?እርሱስ፡ሰማያዊ፡ነው።

፯፡ ከእኔ፡ሕግ፡ልዩ፡የሚሆን፡ይህ፡ማነው?ከእኔ፡ዘንድ፡የነበሩትን፡አሕዛብን፡እየማረከ፡የሚወስዳቸው፡ይህ፡ማነው?

፰፡ ለነደ፡እሳት፡ኃይልና፡ለሞት፡ሲሳይ፡የሆነ፡እርሱም፡ድል፡ያደረጋቸው፡ይህ፡ማነው?

፱፡ የጨለማ፡ክምችቶች፡(አጋንንት)፡ሊያስሩት፡የማይችሉ፡ይህ፡ማነው?በዚህ፡አርአያና፡ጌትነት፡ያለ፡ይህ፡ማነው?

፲፡ የምወደውንም፡እንዳላደርግበት፡የእርሱ፡ኃይል፡የምትከለክለኝ፡ይህ፡ማነው?

## በ፲፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፩ መኑ፡ውእቱ፡እንበለ፡ኃጢአት፡ዘሞተ፡መኑ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ዘበብዝኀ ፡ ብርሃኑ ፡ ለጽልመት፡ አየር ፡ ወኢኀደገኒ ፡ ላዕለ ፡ እሊአየ፡እስፍን፡እላ፡ኵሎ፡ለኀበ፡ሰማያት፡ ይስሕብ፡እለ፡ተውህባኒ፡ነፍሳተ።
፲፪ ምንትኑ ፡ ዝንቱ ፡ ስብሐት ፡ ዘኮነ ፡ እሐደ ፡ ምስለ፡ ዘይማስን ፡ ወይከልአኒ ፡ አማስኖቶ ፤ መኑ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘለኪፎቶ ፡ ኢይክል ፤ መኑ ፡ ውእቱ፡ዘየዐውዶ፡ብርሃን፡ዘኢይነትግ።
፲፫ መኑ፡ውእቱ፡ዘሰዐረኒ፡እምሢመትየ፡ከመ፡ ኢያህጉል፡እሊአሁ፡ለዝንቱሰ፡ዘአማስን፡ በላዕሌሁ፡አልብየ።
፲፬ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተ ሰቅለ፡ዘቦቱ፡ፀጋማይ፡የማናየ፡ኮነ፡ወአዕ ርጎሙ ፡ ለትሑታን ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ እስከ፡ ሰማይ፡ ላዕለ ፡ ወለደኀርት ፡ ረሰዮሙ ፡ ቅድመ።
፲፭ ሲኦለ ፡ ከይዶ ፡ ወወሪዶ ፡ በሞቱ ፡ ለሞት ፡ ደምሰሶ።

ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡በእን ቲአነ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
ማኅተመ፡ጸሎትሰ፡ከመ፡ቀዳሚ።

## ምዕራፍ፡፶፩።

### ትእዛዝ።

በዐሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ ሰዓተ ፡ መዓልት ፡ ዘዓርብ፡ ወእምዝ ፡ ይትጋብኡ ፡ ካህናት ፡ ውስተ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ቅድስት፡በዕለተ፡ ዓርብ ፡ ጊዜ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአሐዱ ፡ ሰዓተ ፡ መዐልት ። ወይጸልዩ ፡ መዝሙረ ፡ ዳዊተ ፡ ፻ወ፶፤

ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ እስከ ፡ ኀበ ፡ ይብል ፤ ወአሰ ሰልኩ ፡ ጽዕለተ ፡ እምደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ዐሠርተ ፡ ወኀምስተ ፡ መሐልየ ፡ ነቢያት ። ወኀምስተ ፡ መሐልየ ፡ ሰሎሞን ። ወውዳሴ ፡ ማርያም ፡ ዘዐርብ ፡ ወቀዳሚት ፡ ወእሑድ ፡ ወአንቀጸ፡ብርሃን።

ወእምዝ ፡ ይበል ፡ መራሒ ፡ በ፲ ፡ ንዜኑ ፡ ንዜኑ፡ዘአምላክነ፡ ኂሩተ ፡ ትሕትና ፡ ወየዋሀተ ፡ ዘእንበለ ፡ ዐቅም ፡ ዬ ፡ ዬ ፡ ዬ ፡ እንዘ ፡ ይጼዕልዎ ፡ ኢጸዐሎሙ ፡ ወእንዘ

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፩ ኃጢአት፡ሳይሠራ፡የሞተ፡ይህ፡ማነው?በብር ሃኑስ ፡ ብዛት ፡ ጨለማን ፡ ዕውር ፡ ያደረገው፤ በወገኖቼ፡እሠለጥንባቸው፡ዘንድ፡ያልተወኝ፤ ይህ፡ማነው? ተሰጥተውኝ፡የነበሩትን፡ሁሉ፡ ነፍሳት፡ወደ፡ሰማያት፡ይሰባል፡እንጂ።
፲፪ ከሚለወጥ ፡ ሥጋ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ይህ፡ ጌትነት ፡ ይህ፡ብርሃን፡ምንድን፡ነው?እኔም፡ ላጠፋው፡የማልችል፡መንካቱን፡መዳሰሱን፡ የማይቻለኝ ፡ ይህ ፡ ማነው ? የማይጐድል፡ ብርሃን፡የሚከበው፡ይህ፡ማነው?
፲፫ ከወገኖቼ ፡ እንዳላጠፋ ፡ ከሥልጣኔ፡የሻረኝ፡ ይህ፡ማነው?እንግዲህ፡ሠልጥኜ፡የምጐዳው፡ ነገር፡የለኝም።
፲፬ እርሱስ ፡ ያሰቀልሁት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ በግራ ፡ የነበረ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ያለፈበት፡ በሲኦልም፡ተዋርደው፡የነበሩትን፡ወደ፡ላይ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያወጣቸው ፡ ኋለኞችን ፡ ቀዳሚዎች፡ያደረጋቸው፡ነው።
፲፭ ሲኦልንም ፡ ረግጦ ፡ ወርዶ ፡ በሞቱ ፡ ሞትን፡ አጠፋው።

መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው፡ ሁኖ፡መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ጸልዩ፡በእንተ፡ጽንዐ፡ዛቲ፡በል።
የጸሎቱ፡ፍጻሜ፡እንደፊተኛው፡ነው።

## ምዕራፍ፡፶፩።

### ትእዛዝ።

ዐርብ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ የሚፈጸም፡ ሥርዓት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐርብ፡ ከቀኑ ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ካህናቱ፡ በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ፡ ይሰብሰቡ ፤ መቶ ፡ አምሣውን ፡ መዝሙረ፡ ዳዊት፡ይድገሙ፤

ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ከሚለው ፡ ጀምሮ ፡ ወአሰ ሰልኩ፡ጽዕለተ፡እምደቂቀ፡እስራኤል፡እስከ ሚለውና ፡ አሥራ ፡ አምስቱን ፡ መሐልየ፡ ነቢያት፡ አምስት ፡ መሐልየ ፡ ሰሎሞንን፡ ውዳሴ ፡ ማርያም፡ ከዐርብ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፡ አንቀጸ፡ብርሃን፡ይጸልዩ።

ከዚህ፡በኋላ፡መሪ፡ በዘጠኝ፡ሃሌታ፡ከመጠን፡ በላይ፡የሆነውን፡የአምላካችንን፡ቸርነት፡ትሕ ትናንና፡ደግነትን፡እንናገራለን፤ወዮ፡ወዮ፡ ወዮ፡ሲሰድቡት፡ላልሰደባቸው፡መከራ፡ሲያ

...ሠ፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

...ምምዎ፡ኢተቀየሞሙ።
...ለከ፡ኃይል፡ወኪርያላይሶን።

## ክፍል፡፩።
## ኦሪት፡ዘፀአት።
### ምዕ፡፲፪፡፩–፲፬።

ወይቤሎሙ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ለሙሴ ፡
ወለአሮን፡በምድረ፡ግብጽ።
ሃ፡ወርኅ፡ቀዳማዊ፡አውራኅ፡ይኩንክሙ፡
ወቅድምዎ፡እምአውራኅ፡ዓመት።
ወንግር፡ለኵሉ፡ማኅበረ፡ደቂቀ፡እስራኤል፡
ወበሎሙ፡በዐሡሩ፡ለዝ፡ወርኅ፡ይንሣእ፡
...ቱ፡ብእሲ፡ብእሲ፡በበ፡ቤቱ፡ወበበዘመዱ፡
ወለለ፡ማኅደሩ፡በግዐ።
ወለእመ፡ውኁዳን፡እሙንቱ፡እለ፡ውስተ፡
ቤት፡ወኢይፄድኡ፡አሐደ፡በግዐ፡ይንሣእ፡
ምስሌሁ፡ካልአ፡ዘኀሩ፡በኍልቊ፡ዘነፍስ፡
ለለአሐዱ፡አሐዱ፡ዘየአክሎ፡ከመ፡ይወድኡ፡
በግዐ።
ወበግዕ ፡ ፍጹም ፡ ተባዕት ፡ ዘዓ
መት፡ይኩንክሙ፡እመራዕይ፡ትነሥኡ፡
ማሕስዐ።
ወዕቁብ ፡ ይኩንክሙ ፡ እስከ ፡ ዐሡሩ ፡
ወረቡዑ ፡ ለዝ ፡ ወርኅ ። ወይሕርድዎ ፡
ኵሉ፡ማኅበሮሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡
ፍና፡ሠርክ።
ወይንሥኡ፡እምደሙ ፡ ወይደዩ ፡ ውስተ ፡
ራግዛት ፡ ክልኤቱ ፡ ወውስተ ፡ መርፈቁ ፡
ለውእቱ፡ቤት፡ኀበ፡ይበልዕዎ።
ወይብልዑ፡ሥጋሁ፡በዛ፡ሌሊት፡ጥብሶ፡
በእሳት፡ወናእተ፡ምስለ፡ሐምለ፡ብሒእ፡
ትበልዑ።
ወኢትብልዑ፡እምኔሁ፡ጥሬዮ፡ወኢብስሎ፡
በማይ፡እንበለ፡ጥብሶ፡በእሳት፡ርእሶ፡ምስለ፡
እገሪሁ፡ትዌድእዎ።
ወኢታትርፉ፡እምኔሁ፡ለነግህ ። ወዐፅሞ፡
ኢትስብሩ፡እምኔሁ፡ወለእመ፡ቦ፡ዘተርፈ፡
እምኔሁ፡ለነግህ፡አውዕይዎ፡በእሳት።
ወከመዝ፡ባሕቱ፡ብልዕዎ ፤ እንዘ ፡ ቅንቱ፡
...ቋቂክሙ፡ወአሣእኒክሙ፡ውስተ፡እገሪክሙ

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ኑበት፡ላልተቀየማቸው፡**ጌታ**፡አንክሮ፡ይገባል።
ለከ፡ኃይልና፡ኪርያላይሶን፡ማለት፡የለም።

## ክፍል፡፩።
## ኦሪት፡ዘፀአት።
### ምዕ፡፲፪፡፩–፲፬።

፩፤ **እግዚአብሔርም**፡አሮንና፡ሙሴን፡በግብጽ፡
ምድር፡እንዲህ፡ብሎ፡ተናገራቸው።
፪፤ ይህ፡ወር፡የወር፡መጀመሪያ፡ይሁናችሁ፤
ከዘመኑም፡ወሮች፡አስቀድሙት፡አላቸው።
፫፤ ለእስራኤልም፡ልጆች፡ወገን፡ሁሉ፡ንገር፤
በዚህ ፡ ወር ፡ ባሥረኛው ፡ ቀን ፡ አንዱ ፡
አንዱም፡ሰው፡በየቤቱ፡በየዘመዱ፡በየወገኑ፡
ለራሱ፡አንድ፡አንድ፡በግ፡ያምጣ፡አለው።
፬፤ በቤቱ፡ያሉ፡ሰዎች፡አንሰው፡አንድን፡በግ፡
የማይጨርሱ፡ቢሆኑ፡አንዱ፡አንዱም፡የሚበ
ቃውን ፡ በሰው ፡ ቍጥር ፡ አንድ ፡ በግ ፡
ይጨርሱ፡ዘንድ፡ከእርሱ፡ጋር፡ከጎረቤቱ፡
ያምጣ።
፭፤ በጉም፡ዓመት፡የሆነው፡ጠቦት፡ይሁን፤
ጠቦቱንም፡ከመንጋው፡ለይታችሁ፡ታመጣ
ላችሁ።
፮፤ ይኸውም ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አሥራ ፡
አራተኛው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የተጠበቀ ፡
ይሁናችሁ፤ በጉንም፡የእስራኤል፡ልጆች፡
ወገኖች፡ሁሉ፡ማታ፡ጊዜ፡ይረዱት።
፯፤ ከደሙም፡ቀድተው፡ሁለቱን፡መቃን፡የሚበ
ሉበትን ፡ የዚያን ፡ ቤት ፡ መድረኩን ፡
ይቅቡት።
፰፤ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ሥጋውን ፡ በእ
ሳት ፡ ጠብሰው ፡ ከመፃፃም ፡ ቂጣ ፡ ጋር ፡
ይብሉት።
፱፤ በእሳት፡የተጠበሰውን፡እንጂ፡ከእርሱ፡ብርን
ዶውን ፡ በውኃውም ፡ የተቀቀለውን ፡
አትብሉ፤ራሱንም፡ከእግሩ፡ጋር፡ጋጡት።
፲፤ ከእርሱም፡ለነገ፡ብላችሁ፡አታሳድሩ፤ዐጥን
ቱንም ፡ አትስበሩ ፤ የሚተርፍም ፡ ቢኖር ፡
በእሳት፡አቃጥሉት።
፲፩፤ እንዲህ፡ሁናችሁ፡ወገባችሁን፡ታጥቃችሁ፡
ጫማችሁን፡ተጫምታችሁ፡በእጃችሁም፡

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወቀስታማቲክሙ፡ውስተ፡እደዊክሙ፡ወት
በልዕዎ፡እንዘ፡ትጔጕኡ፤እስመ፡ፋሲካሁ፡
ለእግዚአብሔር፡ውእቱ።
፲፪፡ ወእመጽእ፡ውስተ፡ምድረ፡ግብጽ፡በዛ፡
ሌሊት፡ወእቀትል፡ኵሎ፡በኵረ፡በምድረ፡
ግብጽ፡እምሰብእ፡እስከ፡እንስሳ፡ወእገብር፡
በቀለ፡እምኵሉ፡አማልክተ፡ግብጽ፡አነ፡እግ
ዚአብሔር።
፲፫፡ ወይከውን፡ዝ፡ደም፡ተአምረ፡ለክሙ፡
ውስተ፡ አብያት፡ ኀበ፡ ሀሎክሙ፡ ህየ፡
ወእሬእዮ፡ለውእቱ፡ደም፡ወእከድነክሙ፡
ወኢትከውን፡ዲቤክሙ፡መቅሠፍት፡ለተቀ
ጥቅጦ፡ሶበ፡አምጻእክዎ፡ዲበ፡ምድረ፡
ግብጽ።
፲፬፡ ወትኩንክሙ፡ዛ፡ዕለት፡ተዝካረ፡ወት
ገብሩ፡በዓለ፡እግዚአብሔር፡ባቲ፡በመ
ዋዕሊክሙ፡ሕገ፡ዘለዓለም፡በዓልክሙ፡
ይእቲ።

ዘኢሳይያስ፡ነቢይ፡በረከተ፡አምላኩ፡
ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡
አሜን።

ምዕ፡፶፩፡፱–፲፫።

፱፡ ተንሥኢ፡ ተንሥኢ፡ ኢየሩሳሌም፡
ልበሲ፡ኀይለ፡መዝራዕትኪ፡ተንሥኢ፡
ከመ፡መዋዕለ፡ትካት፡ዘእምፍጥረተ፡
ዓለም።
፲፡ አኮኑ፡አንቲ፡እንተ፡አንፀፍኪያ፡ለባ
ሕር፡ወአይበስኪ፡ማየ፡ቀላይ፡ብዙኀ፤
ወረሰይኪያ፡ ለቀላየ፡ ባሕር፡ ፍኖተ፡
መጽያሕት።
፲፩፡ ለእለ፡ድኅኑ፡ወተባልሑ፡ሚጠሙ፡እግዚአ
ብሔር፡ወአተዉ፡ጽዮንሃ፡በትፍሥሕት፡
ወበሐሜት፡ዘለዓለም። እስመ፡ውስተ፡
ርእሶሙ፡ ሰብሐት፡ ወይረክበሙ፡
ትፍሥሕት፡ወሐሜት፡ኀልቀ፡እንከ፡ሕማም፡
ወትካዝ፡ወናእክ።
፲፪፡ አነ፡ውእቱ፡ዘአስተፌሥሐኪ፡አእምሪ፡
እንከ፡አንቲኒ፡መኑ፡ፈራህኪ፡ሰብእ፡
መዋቱ፡ወዕጓለ፡እመሕያውኑ፡ዘይየብስ፡
ከመ፡ሣዕር።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

በሎታችሁን፡ ይዛችሁ፡ እየተቻኰ
ላችሁ፡ብሉት፡የእግዚአብሔር፡ፋሲካ፡
ነውና።
፲፪፡ እኔ፡እግዚአብሔር፡በዚች፡ሌሊት፡ወደ፡
ግብጽ፡ምድር፡መጥቼ፡ከሰው፡ጀምሮ፡እስከ፡
ከብት፡ድረስ፡በግብጽ፡አገር፡ያለውን፡
በኵር፡ ሁሉ፡ እገድላለሁ፤ ተበቅዬም፡
የግብጽን፡ጣዖታት፡ሁሉ፡አጠፋለሁ።
፲፫፡ ይህም፡ደም፡ባላችሁበት፡በዚያ፡ቤት፡
ለእናንተ፡ምልክት፡ይሆናችኋል፤ያንንም፡
ደም፡አይቼ፡ከመከራው፡እሠውራችኋለሁ፤
በግብጽ ምድርም፡ ባመጣሁት፡ ጊዜ፡
በእናንተ፡የሚያጠፋ፡መቅሠፍት፡አይመጣባ
ችሁም።
፲፬፡ ይቺም፡ ቀን፡ መታሰቢያ፡ ትሁናችሁ፤
በእርሷም፡የእግዚአብሔርን፡በዐል፡አድርጉ፤
በዐላችሁ፡ናትና፡በዘመናችሁም፡የዘላለም፡
ሕግ፡ትሁናችሁ።

የአምላኩ፡በረከት፡ለዘለዓለሙ፡ከእኛ፡ጋር፡
ትኑርና፡ ነቢዩ፡ ኢሳይያስ፡ የተናገረው፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፶፩፡፱–፲፫።

፱፡ ኢየሩሳሌም፡ ተነሺ፤ ተነሺ፡ ሥልጣንሽን፡
የምትገልጪበት፡ኃይልሽን፡ልበሽ፤ ገንዘብ፡
በነበረው፡በቀድሞው፡ወራትና፡በጥንቱ፡ዘመን፡
በነበረው፡ትውልድ፡እንደ፡ሆነው፡ተነሺ።
፲፡ ባሕርን፡ያደረቅሻት፡አንቺ፡አይደለሽምን፤
ሰፊ፡የሆነ፡የጥልቁንስ፡ውኃ፡ያደረቅሽው፡
የውኃውንስ፡መፍሰሻ፡ጥርጊያ፡ጎዳና፡ያደረ
ግሽው፡አንቺ፡አይደለሽምን?
፲፩፡ ከመከራ፡የዳኑትን፡ከሞትም፡የቀሩትን፡እግ
ዚአብሔር፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡መለሳቸው፤
ዘውድ፡ ደፍቶላቸው፡ ዘላለም፡ ጸንቶ፡
በሚኖር፡ ተድላ፡ደስታ፡ወደ፡ጽዮን፡ገቡ፤
ተድላ፡ደስታ፡ያገኛሉ፤ እንግዲህ፡ሐዘን፡
መከራ፡ተፈጸመ።
፲፪፡ ደስ፡የማሰኝሽ፡እኔ፡ነኝ፤ እንግዲህ፡ዕወቂ፤
አንቺ፡ ማንን፡ ፈራሽ? እንደሣር፡ ፈጥኖ፡
የሚጠፋ፡ፈራሽ፡በስባሽ፡የሚሆን፡ሰውን፡
ፈራሽን?

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፫ ወአንቲሰ ፡ ረሳዕኪዮ ፡ ለእግዚአ
ብሔር ፡ ዘፈጠረኪ ፡ ወዘገብረ ፡ ሰማየ ፡ ወሣ
ረረ ፡ ምድረ ፡ ወፈራህኪ ፡ በኵሉ ፡ ልብኪ ፡
ወበኵሉ ፡ መዋዕልኪ ፡ እምገጸ ፡ መዐቱ ፡
ለዘሣቀየኪ ፡ እስመ ፡ መከረ ፡ ከመ ፡ ይት
መዐክ።
፲፬ ወይእዜኒ ፡ አይቴ ፡ መዐቱ ፡ ለዘሣቀየኪ ፡
እስመ፡እምከመ ፡ ድኅንኪ ፡ ኢይሄሉ ፡ እንከ ፡
ወኢይጐነዲ።
፲፭ እስመ ፡ አነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አም
ላክኪ ፡ ዘአከውሳ ፡ ለባሕር ፡ ወአ
ደምፆ ፡ ለማዕበላ ፤ ወስምየኒ ፡ እግዚአ
ብሔር፡ጸባኦት።
፲፮ አወዲ ፡ ቃልየ ፡ ውስተ ፡ አፉከ ፡ ወእከድነከ ፡
ታሕተ ፡ ጽላሎተ ፡ እዴየ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡
ሰፋሕክዎ ፡ ለሰማይ ፡ ወሣረርክዋ ፡ ለምድር ፡
ወእብላ፡ለጽዮን፡ሕዝብየ፡አንቲ።
፲፯ ተንሥኢ ፡ ተንሥኢ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወቁሚ ፡
እንተ ፡ ሰተይኪ ፡ እምእደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ጽዋዐ፡መዐቱ፡ዘያወድቀኪ፡ወሶጥኪዮ።
፲፰ ወኀጣእኪ፡ዘይናዝዘኪ፡እምኵሉ፡ደቂቅኪ፡
ዘወለድኪ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይሜጥወኪ ፡ እዴሁ ፡
እምኵሉ፡ውሉድኪ፡ዘአልሀቂ።
፲፱ ወይእዜኒ፡እሉ፡አርባዕቱ፡ይጸንሑኪ፡ኀሳር፡
ወድቀት ፡ ወመጥባሕት ፡ ወረኃብ ፡ መኑ ፡
እንከ፡ዘይናዝዘኪ።
፳ ደቂቅኪኑ ፡ እለ ፡ ጸማሕየዩ ፡ ወተነፅኑ ፡
ውስተ፡ ኵሎን ፡ ፍናዋት ፡ ከመ ፡ ሐምለ ፡
ቀባዕ፡ዕቡር፡ዘምሉእ፡ላዕሌሁ፡መዐተ እግ
ዚአብሔር።
፳፩ በበይነ፡ዝንቱ፡ስምዒ፡ኀስርት፡ወሰክርት፡
አኮ፡እምወይን።
፳፪ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አም
ላክ ፡ ዘፈትሐ ፡ ለሕዝቡ ፡ ናሁ ፡ ነሣ
እኩ ፡ እምእዴኪ ፡ ጽዋዐ ፡ ድቀትኪ ፡
ወጽዋዐ ፡ መዐትየ ፡ ወኢትደግሚ ፡ እንከ ፡
ሰትዮቶ።
፳፫ ወአገብእ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ እለ ፡ ገፍዑኪ ፡
ወውስተ፡እደ፡እለ፡አኅሰሩኪ፡ወውስተ፡እደ፡
እለ፡ይብልዋ፡ለነፍስኪ፡ድንኂ፡ወንትዓዶኪ፡
ወአስከቡኪ ፡ ውስተ ፡ መሬት ፡ በከብድኪ

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፫፤ አንቺ ፡ ግን ፡ የፈጠረሽን ፡ ሰማይን ፡ የዘረጋ ፡
ምድርን ፡ ያረጋ ፡ እግዚአብሔርን ፡ረሳሺው ፤
ይቆጣሽ ፡ ዘንድ ፡ መክሮአልና ፡ መከራ ፡
ካጸናብሽ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቁጣ ፡ መገለጥ ፡
የተነሣ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናሽ ፡ ባለ ፡ ዘመንሽ ፡
ሁሉ፡ፈራሽ።
፲፬፤ አሁንም ፡ ከዳንሽ ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ መከራ ፡ ካንቺ ፡
ጋር፡ አይኖርምና ፡ አይዘገይምና ፡ መከራ ፡ ያጸና
ብሽ፡የእግዚአብሔር፡ቍጣው፡ወዴት፡አለ?
፲፭፤ ባሕርን ፡ የማነዋውጣት ፡ ማዕበሏንም ፡
እንዲሰማ ፡ የማደርገው ፡ ፈጣሪሽ ፡ እግዚአ
ብሕር፡እኔ፡ነኝ፤ስሜም፡አሸናፊ፡የሠራዊት፡
ጌታ፡እግዚአብሔር፡ነው።
፲፮፤ ባፍህ ፡ ቃሌን ፡ እንድትናገር ፡ አደርግሃለሁ ፤
ሰማይን ፡ በዘረጋሁበት ፡ ምድርን ፡ ባረጋ
ሁበት፡ ሥልጣኔ ፡ ጥላ ፡ እሠውርሃለሁ ፤
ጽዮንንም፡ወገኔ፡አንቺ፡ነሽ፡እላታለሁ።
፲፯፤ በመከራ፡የሚጥልሽ፡የቍጣውን፡ጽዋ፡ከእግ
ዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ተቀብለሽ ፡ ጨልጠሽ ፡
የጠጣሽ፡ኢየሩሳሌም፡ተነሺ፡ተነሺ፡ቁሚ።
፲፰፤ ከወለድሻቸው ፡ ልጆችሽ ፡ ሁሉ ፡ የሚያረ
ጋጋሽ ፡ አጣሽ ፤ ካሳደግሻቸውም ፡ ልጆችሽ ፡
ሁሉ፡እጇን፡ሰጥቶ፡የሚያነሣሽ፡የለም።
፲፱፤ አሁንም፡እነዚህ፡አራቱ፡መከራ፡ጕስቍልና፡
ቀጠናና ፡ ሰይፍ ፡ ደጅ ፡ ይጠኑሻል ፤ እንግዲህ ፡
የሚያረጋጋሽ፡ማነው?
፳፤ የእግዚአብሔር ፡ ቁጣ ፡ እንደ ፡ ተመ
ላበት ፡ እንደ ፡ ዘይት ፡ ቅጠል ፤ የጠወለጉ ፡
በጐዳናውም ፡ ሁሉ ፡ የወደቁ ፡ ልጆችሽ ፡
ናቸውን?
፳፩፤ ስለዚህ፡በወይን፡ያይደለ፡በኃጢአት፡አረቄ፡
ሰክረሽ፡የተዋረድሽ፡ኢየሩሳሌም፡ስሚ።
፳፪፤ ለወገኖቹ ፡ የፈረደ ፡ ገዥ ፡ የሚሆን ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ እነሆ ፡ በመከራ ፡
የሚጥልሽ ፡ ጽዋን ፡ የቍጣዬንም ፡ ጽዋ ፡
ከእጅሽ ፡ ወሰድሁ ፤ እንግዲህ ፡ ዳግመኛ ፡ አት
ጠጪውም፡አለ።
፳፫፤ ወደ ፡ በደሉሽ ፡ ሰዎችና ፡ ወደ ፡ አጐሳቈሉሽ ፡
ሰዎች ፡ እጅ ፡ ሰውነትሽንም ፡ አጐንብሽ ፡
ድልድይ ፡ አድርገን ፡ እንሻገርብሽ ፡
ወደሚሏት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ እመልሰዋለሁ ፤

Scanned by CamScanner

ወኬዱኪ፡ኵሎሙ፡ኅላፍያነ፡ፍኖት።

ምዕ፡፶፪፡፩–፲፩።

፩፡ ተንሥኢ ፡ ተንሥኢ ፡ ጽዮን ፡ ወል
በሲ ፡ ኀይለኪ ፡ ወአንቲኒ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
ልበሲ፡ ትርሲተኪ ፡ ሀገር ፡ ቅድስት ፡
ወኢየኀልፍ ፡ እንከ ፡ እንተ ፡ ኀቤኪ ፡
ቈላፍ፡ወርኩስ።

፪፡ ተናገፊ፡ጸበለኪ፡ወተንሥኢ፡ኢየሩሳሌም፡
ወንበሪ፡ወግድፊ፡ጋጋ፡እምክሣድኪ፡ወለተ፡
ጽዮን፡ፂውውት።

፫፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከንቱአ ፡
ተሣየጥኩክሙ ፡ ወአኮአ ፡ በወርቅ ፡ ዘእቤዝ
ወክሙ

፬፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግብጽአ ፡
ወረዱ፡ሕዝብየአ፡ቀዲሙአ፡ውኅደሩ፡ህየአ፡
ወእምዝ ፡ ወሰድክዎሙአ ፡ ብሔረ ፡ ፋርስ ፡
በግብር።

፭፡ ወይእዜኒ፡ምንት፡አቀመክሙ፡ዝየ፡ከመዝ፡
ይቤ፡እግዚአብሔር፡እስመ፡አነሥእዎሙአ፡
ለሕዝብየ ፡ በከንቱ ፡ አንከርክሙ ፡ ወከላ
ሕክሙ።

፮፡ ከመዝ፡ይቤ፡እግዚአብሔር፡በእንቲአክሙ፡
ይፀርፉ፡አሕዛብ፡ላዕለ፡ስምየ።

፯፡ በእንተ፡ዝንቱ፡የአምሩ፡ሕዝብየ፡ስምየ፡
ውእተ፡አሚረ፡ከመ፡አነ፡ውእቱ፡ዘነበብኩ፡
ወሀሎኩ።

፰፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ በውስተ ፡ አድባር ፡
ዘይዜኑ ፡ ዜና፡ ሰላም ፡ ወከመ ፡ ዘይዜኑ ፡
ዜና ፡ ሠናየ ። እስመ ፡ ነገረ ፡ እገብራ ፡
ለመድኃኒትየ ፡ ወእብላ ፡ ለጽዮን ፡ ይነ
ግሥ ፡ ለኪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓ
ለም።

፱፡ እስመ፡ተለዓለ፡ቃሎሙ፡ለእለ፡የዐቅቡኪ፡
ወኅቡረ፡ይትፌሥሑ፡በቃሎሙ፡እስመ፡
ዐይነ፡በዐይን፡ይትሬአዩ፡አመ፡ተሣሃላ፡እግ
ዚአብሔር፡ለጽዮን።

፲፡ ወይፈለፍል፡ሐሤት፡ኅቡረ፡በድዋ፡ለኢየሩ
ሳሌም፡እስመ፡ተሣሃላ፡ወአድኀና፡እግዚአ
ብሔር።

በምድር፡ላይ፡በልብሽ፡ደፍተው፡አስተኙሽ፡
መንገደኞችም፡ሁሉ፡ረገጡሽ።

ምዕ፡፶፪፡፩–፲፩።

፩፡ ጽዮን፡ተነሺ፡ተነሺ፡ኃይልሺንም፡ገንዘብ፡
አድርጊ፤ አንቺ፡ክብርት፡ሀገር፡የምትሆኚ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ጌጥሽን ፡ ገንዘብ ፡ አድርጊ፤
እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ያልተገረዘ ፡ አረማዊ ፡
ወዳንቺ፡አይገባም።

፪፡ ትቢያሽን፡አራግፊ፤ኢየሩሳሌም፡ተነስተሺ፤
ተቀመጪ ፤ ተማርከሽ ፡ የነበርሽ ፡ የጽዮን ፡
ልጅ ፡ ዛጐላውን ፡ (አገዛዝ) ፡ ከአንገትሽ ፡
አውርደሽ፡ጣዪ።

፫፡ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡አለ፤ቀድሞ፡ያለ፡
ዋጋ ፡ ዋጀኋችሁ ፤ የምገዛችሁም ፡ በወርቅ ፡
አይደለም፡አለ።

፬፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ቀድሞ ፡
ወገኖቼ፡ወደ፡ግብጽ፡ወረዱ፤በዚያም፡ኖሩ፤
ከዚያም፡በኋላ፡በግድ፡ወደ፡ፋርስ፡አገር፡ወሰ
ድኳቸው።

፭፡ አሁንስ ፡ ከዚህ ፡ ምን ፡ አቆማችሁ ! እግዚአ
ብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ ወገኖቼን ፡ በከንቱ ፡
ማርከው ፡ ወስደዋቸዋልና ፡ ጩኻችሁ ፡ አደነ
ቃችሁ፡አለ።

፮፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ በእናንተ ፡
ምክንያት፡አሕዛብ፡ስሜን፡ይሰድባሉ።

፯፡ ስለዚህ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ወገኖቼ ፡ የተናገርኩ ፡
በዚያም፡ያለሁ፡እኔ፡እንደ፡ሆንኩ፡ስሜን፡
ያውቃሉ።

፰፡ በተራራ ፡ ሁኖ ፡ የተድላ ፡ የደስታ ፡ ወሬ ፡
የሚያወራ ፤ በጎ ፡ ነገርንም ፡ የሚናገር ፡ ሰው ፡
ያማረ ፡ የተወደደ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እኔም ፡ የተና
ርሁት፡ነገር፡ያማረ፡የተወደደ፡ነው፤ሚጠትን፡
ቁም፡ነገር፡አደርጋታለሁና፡ጽዮንን፡እግዚአ
ብሔር፡ይነግሥልሻል፡እላታለሁ።

፱፡ እግዚአብሔር፡ጽዮንን፡ይቅር፡ባላት፡ጊዜ፡
ዐይን ፡ ለዐይን ፡ የሚተያዩ ፡ ስለሆነ ፡ የሚጠ
ብቁሽ ፡ የነቢያት ፡ ቃል ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና፡
በቃላቸው፡አንድነት፡ደስ፡ይላቸዋል።

፲፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ብሎ ፡ አድኗታልና፡
በኢየሩሳሌም ፡ አውራጃ ፡ አንድነት ፡ ተድላ ፡
ደስታ፡ይደረጋል።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፮ ወይከሥት ፡ እግዚአብሔር ፡ መዝራዕቶ ፡
ቅዱሰ ፡ በቅድመ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡
ወይሬእዩ፡ኵሎሙ፡አሕዛብ፡መድኃኒተ፡እግ
ዚአብሔር።
፲፯ ርሒቀ፡ረሐቁ፡ወፃኡ፡እምህየ፡ወኢትግስሱ፡
ርኩሰ፡ወፃኡ፡እምነ፡ማእከላ፡ወተፈለጡ፡
ንዋየ እግዚአብሔር።
፲፰ እስመ ፡ አኮ ፡ በሁከት ፡ ዘትወፅኡ ፡
ወአኮ ፡ በጕያ፡ ዘተሐውሩ ፡ ዳእሙ ፡ የሐ
ውር፡እግዚአብሔር፡ፍጽመ፡ቅድሜክሙ፡
ወያስተጋብአክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አም
ላከ፡እስራኤል።
፲፱ ናሁ ፡ ይሌቡ ፡ ቍልዔየ ፡ ወይትሌዓል ፡
ወይከብር፡ወይትፌማሕ፡ፈድፋደ።
፳ ወያነክሩ ፡ በእንቲአሁ ፡ ብዙኃን ፡ ከመ ፡
ዘነኪር ፡ ራእዩ ፡ እምሰብእ ፡ ወክቡር ፡
እምዕጓለ፡እመሕያው።
፳፩ ወኪያሁ ፡ ያነክሩ ፡ አሕዛብ ፡ ብዙኃን ፡
ወኢይፈትሁ ፡ አፉሆሙ ፡ ነገሥት ፡ እስመ ፡
እለ፡ኢዜነውዎሙ ፡ በእንቲአሁ ፡ ያእምርዎ ፡
ሀለዎሙ ፡ ወእለኒ ፡ ኢሰምዕዎ ፡ ሀለዎሙ ፡
ይለብውዎ።

ዘሶፎንያስ ፡ ነቢይ ፡ በረከተ ፡ አምላኩ ፡
ትኩን ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።

ምዕ፡፪፡፭–፲፭።

፭ አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለፈላስያን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡
ጥቃ ፡ ባሕር ፡ ፈላስያነ ፡ ቀርጤስ ፡ ቃለ ፡
እግዚአብሔር ፡ ላዕሌክሙ ፡ ምድረ ፡ ኢሎ
ፍሊ ፡ ወያጠፍአክሙ ፡ እምበሐው
ርቲክሙ።
፮ ወትከውን ፡ ቀርጤስ ፡ ፂዖተ ፡ መራዕይ ፡
ወምርዓየ፡አባግዕ።
፯ ወይከውን ፡ በሐውርተ ፡ ብሔር ፡ ለተረፈ ፡
ይሁዳ ፡ ወይትረዐይዎሙ ፡ በውስተ ፡ አብያ
ቲሆሙ ፡ አስቀሎናሰ ፡ ድንግዓሂሆሙ ፡
ይነብሩ፡እምቅድመ፡ገጾሙ፡ለደቂቀ፡ይሁዳ፡
እስመ ፡ ተሣሃሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡
አምላኮሙ፡ወሜጠ፡ፄዋሆሙ።



ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፮፤ እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡
ጽኑ ፡ ሥልጣኑን ፡ ይገልጣል ፤ አሕዛብም ፡
ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያደርገውን ፡
ድኅነት፡ያያሉ።
፲፯፤ ፈጽማችሁ ፡ ራቁ ፤ ከባቢሎንም ፡ ውጡ ፤
ጣኦት፡ አታምልኩ ፤ ከመካከሏም ፡ ውጡ ፤ የእ
ግዚአብሔር፡ወገኖችም፡ተለዩ።
፲፰፤ እግዚአብሔር፡በፊታችሁ፡ፊታውራሪ፡ሁኖ፡
ይሄዳል ፤ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይሰበስባችኋል፡እንጂ፡በመታወክ፡የምትወጡ፡
አይደለምና ፡ በመሸሽም ፡ የምትሄዱ ፡ አይደ
ለምና፡የእግዚአብሔር፡ወገኖች፡ተለዩ።
፲፱፤ እነሆ ፡ ወዳጄ ፡ ልብ ፡ ያደርጋል ፤ ከፍ ፡ ከፍም ፡
ይላል፤ይከብራል፤ፈጽሞም፡ደስ፡ይለዋል።
፳፤ መልኩ ፡ ከሰው ፡ ልዩ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡
ከሰውም፡ ይልቅ ፡ የተወደደ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡
ብዙ፡ሰዎች፡የሱን፡ነገር፡ያደንቃሉ።
፳፩፤ ብዙዎች ፡ አሕዛብም ፡ እሱን ፡ ያደንቃሉ ፤
ነገሥታቱ ፡ ግን ፡ አያመሰግኑትም ፡ ነቢያት ፡
ያልነገርዋቸው ፡ የሱን ፡ ነገር ፡ ኋላ ፡ ያውቁ ፡
ዘንድ ፡ አላቸውና ፤ ከነቢያት ፡ ያልሰሙትም፡
ሰዎች፡ልብ፡ያደርጉት፡ዘንድ፡አላቸውና።

የአምላኩ ፡ በረከት ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ለዘላለሙ ፡
ትኑርና ፡ ነቢዩ ፡ ሶፎንያስ ፡ የተናገረው ፡
ትንቢት፡ይህ፡ነው።

ምዕ፡፪፡፭–፲፭።

፭፤ ከቀርጤስ፡ተሰድደው፡ሂደው፡በባሕር፡ዳር፡
ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ወዮላቸው ፤ እናንተም ፡
የኢሎፍሊ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የእግዚአብሔር ፡
ትእዛዝ ፡ በእናንተ ፡ አለባችሁ ፤ ከአገራችሁ ፡
ያጠፋችኋል።
፮፤ በዚያ፡ወራት፡ቀርጤስም፡መንጋ፡የሚውልባት፡
መስክ፡በጎችም፡የሚሠማሩበት፡ትሆናለች።
፯፤ ከአገር፡የቀረው፡አገር፡ከይሁዳ፡ወገኖች፡ለቀረ፡
ሰው፡ይሆናል፤ቤታቸውንም፡ይሠማሩባቸዋል፡
ፈጣሪያቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ብሏቸ
ዋልና፡ምርኮአቸውንም፡መልሷልና፡ከይሁዳ፡
ልጆች፡ገጽ፡መዐት፡የተነሣ፡የአስቀሎና፡ሰዎች፡
የደነገጡ፡ሁነው፡ይኖራሉ።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፰፡ ወሰምዐ፡እግዚአብሔር፡ጽዕለተ፡ሞአብ፡
ወኵርዐቶሙ፡ለደቂቀ፡አሞን፡ዘከመ፡አኀሰ
ርዎሙ፡ ለሕዝብየ ፡ ወተዘኀሩ ፡ ላዕለ ፡
ብሔርየ።
፱፡ በእንተ፡ዝንቱ፡ሕያው፡አነ፡ይቤ፡እግዚአ
ብሔር፡ኃያል፡አምላከ፡እስራኤል፡እስመ፡
ሞአብኒ፡ከመ፡ሰዶም፡ትከውን፡ወደቂቀ፡
አሞን፡ከመ፡ገሞራ፡ወደማስቆኒ፡ተኀልቅ፡
ከመ፡ክምረ፡እክል፡ወትማስን፡ለዓለም፡
ወእለ፡ተርፉ፡ሕዝብየ፡ይበረብርዎሙ፡ወይ
ወርስዎሙ።
፲፡ ወዛቲ ፡ ትከውኖሙ ፡ ህየንተ ፡ ጽዕለ
ቶሙ ፡ እስመ ፡ ኢነስሑ ፡ ወኢተመይጡ ፡
ወተዐበዩ፡ላዕለ፡እግዚአብሔር፡ዘኵሎ፡
ይመልክ።
፲፩፡ ወያመጽእ ፡ እግዚአብሔር ፡ መዐተ ፡
ላዕሌሆሙ ፡ ወይሤርዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡
አማልክተ፡አሕዛብ፡ምድር፡ወይሰግዱ፡ሎቱ፡
ኵሎሙ ፡ በበሐውርቲሆሙ ፡ ወኵሎሙ ፡
ደሰያተ፡አሕዛብ።
፲፪፡ ወአንትሙኒ፡ኢትዮጵያ፡ቅቱላን፡አንትሙ፡
በኵናት።
፲፫፡ ወአነሥእ ፡ እዴየ ፡ ላዕለ ፡ ደቡብ ፡
ወአጠፍእሙ ፡ ለፋርስ ፡ ወእሬስያ ፡
ምዝብርተ ፡ ለነነዌ ፡ ከመ ፡ በድው ፡ ዘአ
ልቦ፡ማይ።
፲፬፡ ወይትረዐዩ ፡ መራዕይ ፡ በማእከላ ፡ ወኵ
ሎሙ ፡ አራዊተ ፡ ገዳም ፡ ወኵሉ ፡ አራ
ዊተ ፡ ምድር ። ወይነብሩ ፡ ዐቃርብት ፡
ውስተ፡ጺያታ፡ወይነቅዉ፡አራዊተ፡ገዳም፡
በውስተ ፡ አፍላጊሃ ፡ ወቋዓት ፡ በውስተ ፡
አናቅጺሃ።
፲፭፡ እስመ፡ከመ፡አርዝ፡ኑኃ፡ለዛቲ፡ሀገር፡
ዐማፂት፡እንተ፡ትነብር፡ተአሚና፡እንዘ፡
ትብል፡በልባ፡አነ፡ይእቲ፡ወአልቦ፡እንተ፡
ከማየ፡እፎ፡እንከ፡ማሰነት፡ወኮነት፡ምርዓየ፡
ለአርዌ፡ገዳም፡ወኵሉ፡ዘየኀልፍ፡እንተ፡
ላዕሌሃ፡ይትፋጸይ፡ወይጠፍሕ፡እዴሁ፡እንዘ፡
ይብል።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፰፡ ወገኖቼን ፡ እንደ ፡ አጐሳቈሉአቸው ፡
በአገሬም፡በኢየሩሳሌም፡እንደ፡ታበዩ፡እግ
ዚአብሔር፡የሞአብን፡ስድብ፡የአሞንንም፡
ልጆች፡ኩራታቸውን፡ሰምቷል።
፱፡ ስለዚህ፡ሞአብ፡እንደ፡ሰዶም፡እንድትሆን፡
የአሞንም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ገሞራ ፡ ልጆች ፡
እንዲሆኑ፡ደማስቆም፡እንደ፡እህል፡ክምር፡
ጥቂት፡ጥቂት፡እያለች፡ለዘላለም፡እንድትጠፋ፡
የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ ኃያል ፡ እግዚአብሔር ፡
ሕያው፡ነኝ፡አለ፤ከሞት፡የቀሩ፡ወገኖቼ፡ጠላቶ
ቻቸውን፡ይበረብሩዋቸዋል፤ይወርሷቸዋል።
፲፡ ሁሉን፡በሚገዛ፡በእግዚአብሔር፡ላይ፡ታብየ
ዋልና፤ በንስሐም ፡ አልተመለሱምና፡ስለ፡
ተሳደቡት፡ስድባቸው፡ፈንታ፡ይህች፡ትሆና
ቸዋለች።
፲፩፡ እግዚአብሔርም ፡ ቁጣውን ፡ በነሱ ፡ ላይ ፡
አምጥቶ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉ ፡ የአሕዛብን ፡
ጣዖታት ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋቸዋል ፤ በአሕዛብ ፡
ደሴቶች፡የሚኖሩ፡ሰዎች፡ሁሉ፡በየአውራጃዎ
ቻቸው፡ሆነው፡ሁላቸውም፡ይሰግዱለታል።
፲፪፡ እናንተም፡የኢትዮጵያ፡ሰዎች፡በጦር፡ተወግ
ታችሁ፡አልቃችኋል።
፲፫፡ ገጸ፡መዐቴን፡በባቢሎን፡አነሣባታለሁ፤የፋር
ስንም ፡ ሰዎች ፡ አጠፋቸዋለሁ ፤ ነነዌንም፡
የፈረሰች፡ውኃ፡እንደሌለባትም፡ምድረ፡በዳ፡
አደርጋታለሁ።
፲፬፡ እሷ፡ጠፍታ፡መንጋዎች፡በመካከሏ፡ይሠማሩ
ባታል፤በምድረ፡በዳ፡ያሉ፡በከተማም፡ያሉ፡
አውሬዎች፡ሁሉ፡ይሠማሩባታል፡ጊንጦችም፡
በመስኳ፡ይኖራሉ፤በምድረ፡በዳ፡ያሉ፡አውሬ
ዎችም ፡ በፈሳሾቿ ፡ መካከል ፡ ይራጯሉ ፡
ቍራዎችም፡በበሮቿ፡ሠፍረው፡ይጮሀሉ።
፲፭፡ በልቧ፡እመቤት፡እኔ፡ብቻ፡ነኝ፤እንደኔ፡ያለ፡
ገዥም፡የለም፤እያለች፡ጠላት፡ጠፍቶላት፡
ተዘልላ፡የምትኖር፡ዐመፀኛ፡የሆነች፡አገር፡
ገናንነቷ፡እንደ፡ዋንዛ፡እንደ፡ዝግባ፡ነበርና፡
እንዴት፡ጠፋች? ለምድረ፡በዳ፡አራዊትም፡
እንዴት ፡ መሠማሪያ ፡ ሆነች ? እንዴትስ ፡
እንዴት ፡ መሠማሪያ ፡ ሆነች? እንዴትስ፡
ጠፋች? እያለ፡በእሷ፡የሚሄድ፡መንገደኛ፡
ሁሉ፡ያፏጫል፤እጁንም፡ያጨበጭባል።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ምዕ፡፫፡፩-፰።

አ፡ላሕይት፡ወሥናይት፡ርግብ፡ሀገር፡እንተ፡
ኢትሰምዕ።
ወኢትትዌከፍ ፡ ተግሣጸ ፡ ወኢትትዌ
ሎ፡በእግዚአብሐር፡ ወኢቀርበት ፡ ኀበ ፡
አምላካ።
መኳንንቲሃ፡በውስቴታ፡ይጥሕሩ፡ከመ፡
አንበሳ፡ወዐበይቲሃ፡ከመ፡ተኵላተ፡ዐረብ፡
ዘኢያበይቱ፡ለሙ፡ለነግህ።
ነቢያቲሃኒ ፡ ዕደው ፡ መስተአብዳን ፡
ወካህናቲሃኒ፡ያረኵሱ፡መቅደሰ፡ወየዐልዉ፡
ሕገ።
ወጻድቅሰ፡በማእከላ፡ኢይገብር፡ዐመፃ፡
ከመ፡በጽባሕ፡ይሁብ፡ኵነኔሁ፡ወኢይ
መውእ፡እንከ፡ዐማፂ። ወኢተኀብአ፡ወኢየ
አምር፡ዐመፃ፡ውስተ፡ሐተታ፡ወኢ፡ውስተ፡
ተሰናን፡ግፍዐ።
ወነፃኅክዎሙ፡ለዕቡያን፡በሞት፡ወአማ
ሰንኩ፡በሐውርቲሆሙ፡ወአበዲ፡ፍኖቶሙ፡
ለግሙራ፡ከመ፡ኢይክሀሉ፡ኀሊፈ፡
ውስቴታ፤ወኀልቃ፡አህጉሪሆሙ፡ወአልቦ፡
ዘተርፈ፡ዘይነብሮን።
ወእቤ፡ፍርሁኒ፡ወተወከፉ፡ተግሣጽየ፡
ከመ፡ኢትሚረዉ፡እምቅድመ፡አዕ
ይንትየ፡ወኵሉ፡ዘተበቀልክዎ፡
ይዴሎ፡ይጊስ፡እስመ፡ማሰነ፡ኵሉ፡
ምርጸሙ።
በእንተ፡ዝንቱ፡ተዐገሡኒ፡እስከ፡አመ፡
እትነሣእ፡ይቤ፡እግዚአብሐር።

ክፍል፡፪።

ተግሣጽ፡ዘአቡነ፡አትናቴዎስ፤በረከቱ፡
ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
ጽሑፍ፡በውስተ፡መጻሕፍተ፡ነቢያት፡
መሰበ፡ትከውን፡ነፍስነ፡እስርተ፡በሕገ፡እግ
ዚአብሐር፡ ኢይክል፡ይሠለጥ፡ላዕሌሃ፡
አሐዱሂ፡እመኳንንተ፡ጽልመት፡ወሶበ፡
ትርሕቅ፡ነፍስነ፡እምእግዚአብሐር፡
ወእቶሙ፡ይሚለጡ፡ላዕሌሃ።
ወእንተሰ፡አ፡ብእሲ፡ዘትፈቅድ፡ትድኅን፡
መሐር፡ርእሰከ፡ትጽብት፡ውስተ፡ባሕረ፡ጸጋ፡
ዘበ፡እግዚአብሔር፡ ስፋሕ፡እዴከ፡ላዕለ፡
አምሳለ፡መስቀል፡ከመ፡ትኅልፍ፡ባሕረ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

ምዕ፡፫፡፩—፰።

፩፤ ቢመክርዋት፡ቢአስተምርዋት፡ለማትሰማ፡ለአማረች፡ለተወደደች፡ለነነዌ፡ወዮላት።
፪፤ ምክር፡እዝናትን፡የማትቀበል፡በእግዚአብሔርም ፡ ለማታምን ፡ ወደ ፡ ፈጣሪዋም ፡ በአምልኮ፡ለማትቀርብ፡ለነነዌ፡ወዮላት።
፫፤ በሷም ፡ ያሉ ፡ አለቆቿ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ይጮሃሉ፤ ሹማምንቶቿም፡ልክ፡እንደማያ ሳድሩ፡እንደ፡ጨለማ፡ተኵላዎች፡ናቸው።
፬፤ መምህሮቿ፡ነቢያት፡ሰነፎች፡ናቸው፤ካህናቶቿም፡ቤተ፡መቅደስን፡ያረክሳሉ፡ሕጉንም፡ያፈርሳሉ።
፭፤ ዕውነተኛ ፡ ግን ፡ (ሕዝቅያስ ፡ ዘሩባቤል) ፡ በመካከሏ ፡ አመፅን ፡ አይሠራም ፤ በእሷ ፡ ፈጥኖ ፡ ፍርድን ፡ ይሰጣል ፤ አመፀኛውም ፡ ድል፡አይነሣውም፤በጥልም፡ጊዜ፡ግፍን፡አያውቅም።
፮፤ ትዕቢተኞችን፡በሞት፡አጠፋኋቸው፤አገራቸውንም፡አጠፋሁ፤ወደሷም፡መሄድ፡እንዳይችሉ፡ጐዳናቸውን፡ፈጽሚ፡ምድረ፡በዳ፡አደርገዋለሁ፤አገሮቻቸውም፡ጠፉ፤የሚኖርባቸውም፡ሰው፡የለም።
፯፤ እኔን፡ፍሩኝ፤አምልኩኝ፤ከገጸ፡መዐቴም፡የተነሣ ፡ እንዳትጠፉ ፡ ሕጌን ፡ ተቀበሉ ፡ አልኩ፤ልጆቻቸው፡ሁሉ፡በሕፃንነት፡ጠፍተዋልና፤የተበቀልሁት፡ሁሉ፡በሕግ፡በአምልኮት፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ይገሥግሥ።
፰፤ እግዚአብሔርም፡እስክነሣ፡ድረስ፡ስለዚህ፡ነገር፡ታገሡኝ፡አለ።

ክፍል፡፪።

በረከቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ትኑርና፡የአባታችን፡የአትናቴዎስ፡ምክር፡ይህ፡ነው።
፩፤ በነቢያት ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ እንዲህ ፡ ተጽፎአል ፤ ሰውነታችን ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን፡በመጠበቅ፡በጸናች፡ጊዜ፡የጨለማ፡አበጋዞች ፡ አጋንንት ፡ ሊሠለጥኑባት ፡ አይችሉም፤ነገር፡ግን፡ሕገ፡እግዚአብሔርን፡በዘነጋች፡ጊዜ፡ይሠለጥኑባታል።
፪፤ በእግዚአብሔር፡ድኅነትን፡የምትሻ፡አንተ፡ሰው! በእግዚአብሔር፡ጥበብ፡ጸጋ፡ባሕር፡ውስጥ፡ትዋኝ፡ዘንድ፤ራስህን፡አስተምር፤ታላቁንም፡ባሕር፡ዋኝተህ፡ታልፍ፡ዘንድ፡እጅህን፡በመስቀል፡

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡ዘንተ፡ዘመን፡ወትሐር፡

ዐቢየ፡ዝ፡ውእቱ፡ዝንቱ፡ዘመን፡ወትሐር፡
ኀበ፡እግዚአብሔር።
፫፤ ወለእመሰ፡ መንሱታት፡ ዘይከልእዎሙ፡
እምነ፡ጽብተታት፡ይእቲ፡ለእለ፡የሐውሩ፡
ዘእንበለ፡ትእዛዘ፡እግዚአብሔር፡ወቤተ፡ክር
ስቲያን።
፬፤ ኀቡአ፡እትኔበይ፡ሕጸተ፡ሃይማኖት፡ዝሙት፡
ወሐሜት፡ፍቅረ፡ብሩር፡ይእቲ፡ሥርወ፡
ለኵሉ፡እከይ።
፭፤ ወእመሰ፡ ትእምርተ፡ መስቀል፡ ይእቲ፡
ትትረከብ፡በውስተ፡ኵሉ፡ፍጥረት።
፮፤ ፀሐይሰ፡ሶበ፡ኢይሰፍሕ፡ጸዳሎ፡ኢይክል፡
ያብርህ፡ወወርኀኒ፡ከማሁ፡እመ፡ኢፈነወ፡
ጸዳሎ፡ኢይከውን፡ሎቱ፡ብርሃን።
፯፤ ወያፌ፡ ሰማይኒ፡ እመ፡ ኢሰፍሐት፡
ክነፊሃ፡ ኢትክል፡ ትስርር፡ ወሐመርኒ፡
እመ፡ ኢሰፍሐት፡ ሥራዓ፡ ኢትክል፡
ትሑር።
፰፤ ሙሴኒ፡ሊቀ፡ነቢያት፡ሶበ፡ሰፍሐ፡እደዊሁ፡
ነትዐ፡ዐማሌቅ።

፱፤ ወበእንተ፡ዝንቱ፡ድኅነ፡ዳንኤል፡እምአፈ፡
አናብስት፡ ወዮናስ፡ እምከርሠ፡ ዐንበሪ፡
ወጤቀላዊ፡ ሰማዕት፡ ሶበ፡ ገደፍዋ፡ ለአና
ብስት፡ድኅነት፡በትእምርተ፡መስቀል።
፲፤ ወሶስናሂ፡ከማሁ፡ድኅነት፡እምእደ፡ረበናት፡
ወዮዲት፡እምእደ፡ሆሎፎርኒስ።
፲፩፤ ወሠለስቱ፡ ደቂቅ፡ እምእቶነ፡ እሳት፡
ዘይነድድ።
፲፪፤ ወእሙንቱ፡ ኵሎሙ፡ ቅዱሳን፡ ድኅኑ፡
በትእምርተ፡ መስቀል፡ በውስተ፡ መካነ፡
ዋሕድ፡ ዛ፡ ይእቲ፡ ቅድስት፡ ቤተ፡
ክርስቲያን።
፲፫፤ አ፡ አኀውየ፡ ንሴሰይ፡ እምነገረ፡ መጻሕፍት፡
ወእምነ፡ሥጋ፡ክርስቶስ፡ወእምደሙ፡ክቡር፡
ዝ፡ውእቱ፡ሲሳይ፡ሰማያዊ።

ወንትፈሣሕ፡ኵሎ፡ጊዜ፡በነገረ፡መጻሕፍት፡
ቅዱሳት፡ዘለእግዚእነ።
ሎቱ፡ ክብር፡ ወስብሐት፡ ለዓለመ፡ ዓለም፡
አሜን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

አምሳል፡ ዘርጋ፤ ይህም፡ ይህ፡ ዘመን፡ ነው፤
ወደ፡እግዚአብሔር፡ ትደርስ፡ዘንድ፡ትጋ።
፫፤ መሰናክሎች፡ የሚከለክሉዋቸው፡ ቢሆን፡
ከእግዚአብሔር፡ ትእዛዝና፡ ከቤተ፡ ክርስቲ
ያንም፡ ሥርዐት፡ ውጭ፡ የሚሠሩትን፡
ነው።
፬፤ ሥውር፡ የሆነውንም፡ አስተምራለሁ፤ ሃይማ
ኖትን፡ የሚያጐድል፡ ዝሙት፡ ሐሜት፡
ገንዘብን፡መውደድ፡የክፋት፡ሁሉ፡ሥር፡ናት።
፭፤ ይህችም፡ የመስቀል፡ ምልክት፡ ከሆነች፡
በፍጥረት፡ሁሉ፡ትገኛለች
፮፤ ፀሐይም፡ ጨረሩን፡ ካልዘረጋ፡ ሊያበራ፡
አይችልም፤ ጨረቃም፡ እንዲሁ፡ ክበቡን፡
ጸዳሉን፡ካልላከ፡ብርሃን፡አይሆንለትም።
፯፤ የሰማይ፡ ያፍም፡ ክንፎቿን፡ በመስቀል፡
አምሳል፡ ካልዘረጋች፡ ልትበር፡ አትችልም፤
መርከብም፡ ሸራዋን፡ ካልዘረጋች፡ መሄድ፡
አትችልም።
፰፤ የነቢያት፡ አለቃ፡ ሙሴም፡ በመስቀል፡
ምልክት፡ እጆቹን፡ በዘረጋ፡ ጊዜ፡ አማሌቅ፡
ድል፡ሆነ።
፱፤ በዚሁ፡ አርአያ፡ ከአንበሶች፡ አፍ፡ ዳንኤል፡
ዳነ፤ ዮናስ፡ በከርሠ፡ አንበሪ፡ ሳለ፡ ተጠበቀ፤
ሰማዕት፡ የሆነች፡ ጤቀላም፡ ለአንበሶች፡
በጣሏት፡ጊዜ፡በመስቀል፡ምልክት፡ዳነች።
፲፤ ሶስናም፡ እንዲሁ፡ ከረበናት፡ እጅ፡ ዳነች፤
ዮዲትም፡ከሆሎፎርኒስ፡እጅ።
፲፩፤ ሠለስቱ፡ ደቂቅም፡ ከሚነድ፡ እሳት፡
ዳኑ።
፲፪፤ እነዚህ፡ ሁሉ፡ ቅዱሳን፡ የመስቀልን፡
ምልክት፡ ይዘው፡ ዋሕድ፡ ጌታ፡ በሚመሰ
ንበት፡ቦታ፡ዳኑ፤ይቺም፡የከበረች፡ቤተ፡ክር
ስቲያን፡ናት።
፲፫፤ ወንድሞቼ፡ ሆይ፡ ከመጻሕፍት፡ ቃል፡
እንዲሁም፡ ከክርስቶስ፡ ከከበረ፡ ሥጋው፡
ከከበረ፡ደሙ፡እንመገብ፤ይኸውም፡ሰማያዊ፡
ምግብ፡ነው።
የጌታችን፡ በሆኑ፡ በከበሩ፡ መጻሕፍትም፡
ቃላቸውን፡በመስማት፡ሁልጊዜ፡ደስ፡ይበለን።
ለርሱም፡ ለጌታ፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግባው፡
ለዘላለሙ፡አሜን።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

## ክፍል፡፫።

ይ፡ዲ፡ቅድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፻፵፪፤፯።

እንግልአከ ፡ እደውየ ፡ ኀቤከ ። ነፍስየኒ ፡ ከመ ፡ ምድረ ፡ በድው ፡ ጸምዐተከ ። ፍጡነ ፡ ስምዐኒ ፡ እግዚኦ፡ ኀለፈት ፡ ነፍስየ።

### ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፤፳፯፤፶፩–፶፮።

፶፩ ወእምዝ ፡ ተሠጠ ፡ መንጦላዕተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ፡ እምላዕሉ ፡ እስከ ፡ ታሕቱ ፡ ወኮነ ፡ ለክልኤ ፡ ክፍል ፡ ወአድለቅለቀት ፡ ምድር ፡ ወነቅዐ፡ኰኵሕ።
፶፪ ወተከሥቱ ፡ መቃብራት ፡ ወተንሥኡ ፡ ብዙኃን፡እምአብድንቲሆሙ፡ለጻድቃን።
፶፫ ወወጽኡ ፡ እመቃብሪሆሙ ፡ ወቦኡ ፡ ሀገረ ፡ ቅድስተ ፡ እምድኅረ ፡ ተንሥኡ ፡ ወአስተርአይዎሙ፡ለብዙኃን።
፶፬ ወመኰንነ ፡ ምዕትሰ ፡ ወእለ ፡ ምስሌሁ ፡ የዐቅብዎ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ርእዮሙ ፡ ውእተ ፡ ድልቅልቀ ። ዘኮነ ፡ ፈርሁ ፡ ጥቀ ፡ ወይቤሉ ፡ አማን ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ፡ዝንቱ።
፶፭ ወሀለዋ፡ሀየ፡ብዙኃት፡አንስት፡እለ፡ይሬእያ፡እምርሑቅ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ ፡ ወውእቶን ፡ እለ ፡ ተለዋሁ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ እምገሊላ ፡ ከመ፡ይትለአካሁ።
፶፮ ወእማንቱ ፡ ማርያም ፡ መግደላዊት ፡ ወማርያም፡ እንተ ፡ ያዕቆብ ፡ ወእሙ ፡ ለዮሳ ፡ ወእሞሙ፡ለደቂቀ፡ዘብዴዎስ።

### ወንጌል፡ዘማርቆስ።

ምዕ፤፲፭፤፴፰–፵፩።

፴፰ ወተሠጠ፡መንጦላዕተ፡ምኵራብ፡ለክልኤ፡እምላዕሉ፡እስከ፡ታሕቱ።
፴፱ ወርእዮ፡ ሐራዊ፡ሊቀ፡ምዕት፡ዘይቀውም፡መንጸረ፡ከመ፡ከመዝ፡ገዓሮ፡ሞተ፡ይቤ፡አማን፡ዝንቱ፡ብእሲ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡ውእቱ።
፵ ወሀለዋ ፡ አንስትኒ ፡ ይቀውማ ፡ ወይኔጽራ ፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

## ክፍል፡፫።

ዲያቆኑ፡ከወንጌል፡አስቀድሞ።

መዝ፤፻፵፪፤፯።

እጆቼን ፡ ወዳንተ ፡ አነሣሁ ። ሰውነቴም ፡ ምድረ፡በዳ፡ዝናምን፡እንዲናፍቅ፡አንተን፡ናፈቀች ፤ አቤቱ ፡ ሰውነቴ ፡ አለይ ፡ አለይ ፡ ብላለችና፡ፈጥነህ፡ስማኝ፡ይበል።

### የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፳፯፤፶፩–፶፮።

፶፩፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መጋረጃ ፡ ከላይ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ተቀደደ ፤ ለሁለትም ፡ ተከፈለ ፤ ምድር ፡ ተናወጠች ፤ አለቱ ፡ ተሠነጠቀ።
፶፪፤ መቃብሮችም ፡ ተከፈቱ ፤ ከቅዱሳን ፡ በድኖችም፡ብዙዎች፡ተነሡ።
፶፫፤ ከተነሡም ፡ በኋላ ፡ ከመቃብራቸው ፡ ወጥተው፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ ሀገር ፡ ገቡ ፤ ለብዙ ዎችም፡ታዩአቸው።
፶፬፤ የመቶ ፡ አለቃውና ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስን ፡ይጠብቁት ፡ የነበሩት ፡ ግን ፤ ያን ፡ ንውጽውጽታ ፡ የሆነውንም ፡ ሁሉ ፡ አይተው፡ እጅግ ፡ ፈሩና ፡ በእውነት ፡ ይህ ፡ የእግዚአ ብሔር፡ልጅ፡ነው፡አሉ።
፶፭፤ ከዚያም ፡ የሆነውን ፡ የሚያዩ ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ ፤ እነርሱም ፡ ሊያገለግሉት ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስን ፡ ከገሊላ ፡ ጀምሮ ፡ የተከተሉት ፡ ነበሩ።
፶፮፤ እነርሱም ፡ ማርያም ፡ መግደላዊት ፤ የያዕቆብ ፡ እናት ፡ የዮሳ፡እናት ፡ ማርያም ፡ የዘብዴዎስም ፡ ልጆች፡እናት፡ነበሩ።

### የማርቆስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፲፭፤፴፰–፵፩።

፴፰፤ የምኵራብ ፡ መጋረጃም ፡ ከላይ ፡ እስከታች ፡ ከሁለት፡ተቀደደ።
፴፱፤ ፊት ፡ ለፊት ፡ የቆመው ፡ የመቶ ፡ አለቃም ፡ እንዲህ ፡ ጮኾ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ይህ፡ ሰው ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ነው፤ አለ።
፵፤ ከሩቅ ፡ ቆመው ፡ የሚያዩት ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ ፤

Scanned by CamScanner

| በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት። |
| --- | --- |

እምርሑቅ ፡ ማርያም ፡ መግደላዊት ፡
ወማርያም ፡ እንተ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘይንእስ ፡
ወእሙ፡ ለዮሳ ፡ ወሰሎሜ ፡ እለ ፡ ተለዋሁ ፡
እምገሊላ፡ወተልእክሁ።
፵፩፤ ወባዕዳትኒ፡በዙኃት፡እለ፡ዐርጋ፡ምስሌሁ፡
ኢየሩሳሌም።

## ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፤፳፫፡፵፯–፵፱።

፵፯፤ ወርእዮ፡መስፍን፡ምዕት፡ዘኮነ፡አእኰቶ፡ለእ
ግዚአብሔር፡ ወይቤ፡አማን፡ጻድቅ፡ውእቱ፡
ዝ፡ብእሲ።
፵፰፤ ወኵሎሙ፡ሕዝብ፡ሶበ፡ርእዩ፡ዘኮነ፡ጐድዑ፡
እንግድዓቲሆሙ፡ወተሠውጡ።
፵፱፤ ወአተዉ ፡ አብያቲሆሙ ፡ ወይቀውሙ ፡
ኵሎሙ፡እለ፡የአምርዎ፡እምርሑቅ፡ወአን
ስትኒ፡እለ፡ተለዋሁ፡እምገሊላ፡ርእያ፡ዘንተ።

## ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፤፲፱፡፴፩–፴፮።

፴፩፤ ወአይሁድሰ፡እስመ፡ዐርብ፡ውእቱ፡ይቤሉ፡
እላንቱ ፡ ሥጋት ፡ ኢይቢታ ፡ ዲበ ፡ መስቀ
ሊሆን ፡ በእንተ ፡ ሰንበት ፡ እስመ ፡ ዐባይ ፡
ዕለታ፡ ለይእቲ ፡ ሰንበት ፤ ወሰአልዎ ፡
ለጲላጦስ፡ከመ፡ያውርድዎሙ፡ሰቢሮሙ፡
ቈየጺሆሙ።
፴፪፤ ወመጽኡ፡ሐራ፡ወሰበሩ፡ቈይጾ፡ለቀዳማዊ፡
ወለካልኡኒ፡እለ፡ተሰቅሉ፡ምስሌሁ።
፴፫፤ ወሶበ፡ሖሩ፡ሐራ፡ኀበ፡እግዚእ፡ኢየሱስ፡
ወርእይዎ፡ከመ፡ሠለጠ፡መዊተ፡ኢሰበሩ፡
ቈይጾ።
፴፬፤ አላ፡አሐዱ፡እምሐራ፡ረገዞ፡ገቦሁ፡ዘየማን፡
በኲናት፡ ወሶቤሃ፡ ወፅአ፡ እምኔሁ፡ ደም፡
ወማይ።
፴፭፤ ወዘርእየ፡ ስምዐ፡ ኮነ፡ ወጽድቅ፡ ውእቱ፡
ስምዑ፡ ወእእመረ፡ ውእቱ፡ ከመ፡ ጽድቀ፡
ይነግር፡ከመ፡አንትሙኒ፡ትእመኑ።
፴፮፤ ወዝንቱ፡ኵሉ፡ዘኮነ፡ከመ፡ይብጻሕ፡ቃለ፡
መጽሐፍ ፡ ዘይቤ ፡ ዐፅሞ ፡ ኢትስብሩ ፡
እምኔሁ።

እነዚህም፡ከገሊላ፡ጀምሮ፡የተከተሉትና፡ያገ
ለገሉት ፡ ማርያም ፡ መግደላዊት ፡ የታናሹ፡
የያዕቆብ ፡ እናት ፡ የዮሳ ፡ እናት ፡ ማርያምና፡
ሰሎሜም፡ነበሩ።
፵፩፤ ከእርሱም ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም፡የወጡ፡
ብዙዎች፡ሌሎች፡ሴቶችም፡ነበሩ።

## የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፳፫፡፵፯–፵፱።

፵፯፤ የመቶ ፡ አለቃውም ፡ የሆነውን ፡ አይቶ፡
በእውነት ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ፡
ነው፡ብሎ፡እግዚአብሔርን፡አመሰገነው።
፵፰፤ ሕዝቡም፡ሁሉ፡የሆነውን፡ባዩ፡ጊዜ፡ደረታ
ቸውን፡እየደቁ፡ወደ፡ቤታቸው፡ተመለሱ።
፵፱ የሚያውቁት ፡ ሁሉ ፡ ከሩቅ ፡ ቆመው ፡ ነበር፤
ከገሊላ፡ጀምሮ፡የተከተሉት፡ሴቶችም፡ይህን፡
ያዩ፡ነበሩ።

## የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፲፱፡፴፩–፴፮።

፴፩፤ አይሁድ ፡ ግን ፡ መሽቷልና ፡ እነዚህ ፡ እስከ
ሬኖች ፡ ስለ ፡ ሰንበት ፡ በየተሰቀሉበት ፡
አይደሩ፤የዚች፡ሰንበት፡ቀን፡ታላቅ፡ናትና፤
ጭን ፡ ጭናቸውን ፡ ሰብረው ፡ ያወርዷቸው፡
ዘንድ፡ጲላጦስን፡ለመኑት።
፴፪፤ ጭፍሮችም ፡ መጥተው ፡ አብረውት ፡ የተሰቀ
ሉትን፡የመጀመሪያውን፡ወንበዴ፡ጭን፡የሁ
ለተኛውንም፡ሰበሩ።
፴፫፤ ጭፍሮችም ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ በሄዱ፡
ጊዜ፤ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ አይተው ፡
ጭኑንም፡አልሰበሩትም።
፴፬፤ ከጭፍሮች ፡ አንዱ ፡ የቀኝ ፡ ጐኑን ፡ በጦር፡
ወጋው፡እንጂ፤ያን፡ጊዜም፡ከእርሱ፡ደምና፡
ውኃ፡ወጣ።
፴፭፤ ያየው ፡ መሰከረ ፤ ምስክርነቱም ፡ ዕውነት፡
ነው፤እናንተ፡ልታምኑ፡እርሱ፡እውነት፡እን
ደሚናገር፡ያውቃል።
፴፮፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የሆነው ፡ ከእርሱ ፡ ዐፅሙን፡
አትስበሩ፡ያለው፡የመጽሐፍ፡ቃል፡ይደርስ፡
ይፈጸም፡ዘንድ፡ነው።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

መሰብ፡ይብል፡ካልእኒ፡መጽሐፍ፡ሀለዎሙ፡
ይርአይዎ፡ለዘወግዕዎ።

ድኅረ፡ወንጌል፡በዐሠርቱ፡ወአሐዱ፡ሰዓት፡
ዘዐርብ።

ወእስራኤልሰ፡ምንት፡ተዔወወ፡ዘአበሳሁ፡
ዘደነት፡ሰማየ፤ወርእዮ፡መኰንነ፡
ምዕት፡ብእሲ፡ነኪረ፡ዘመድ፡አምኖ፡
ለዘተሰቅለ።

ወኢኮነ፡ውእቱ፡ባሕቲቱ፡አላ፡እለሂ፡
ምስሌሁ፡ጸርሑ፡ኵሎሙ፡እንዘ፡ይብሉ፡
አሰመ፡ዝንቱ፡ውእቱ፡ወልደ፡እግዚአ
ብሔር።

ወከመዝ፡ፈያታይኒ፡ዘተስቅለ፡ምስሌሁ፡
አእመረ፡ኀይሎ፡ወኀሠሠ፡ምሕረቶ።

ርእየ፡ኀበ፡መንጦላዕተ፡ምኵራብ፡ዘተሠጠ፡
እምላዕሉ፡እስከ፡ታሕቱ፡ወኮነ፡ክልኤተ፡
ክፍለ፡ወርእየ፡ከመ፡ፀሐይ፡ከደነት፡
ጸዳላቲሃ፡ወኮነት፡ጽልመተ፡በማዕከለ፡
መዐልት።

ወወርኀኒ፡ካዕበ፡ከደነ፡ገጾ፡ወኮነ፡ደመ፡
በእንተ፡ፈጣሪሁ።

ኀይላተ፡ሰማይ፡ደንገፁ፡ወከዋክብትኒ፡
ብዙኃን፡ወድቁ፡እምሰማይ፡በዝንቱ፡አሐዱ፡
መዐልት።

ምድርኒ፡አድለቅለቀት፡ወጸላዕት፡
ተሠጥቀት፡ወመቃብራት፡ተከሥቱ፡
ወወጽኡ፡ምውታን፡ወሖሩ፡ኀበ፡ሀገር፡
ቅዱስ፡ወአእመርዎሙ፡ብዙኃን፡ሰብእ።

ወሶበ፡ርእዩ፡እልክቱ፡አእመሩ፡ኀይሎ፡ለዘ
ተሰቅለ፡ዲበ፡ዕፅ፡ወሰአልዎ።

ወለእስራኤልሰ፡ካዕበ፡ፆረት፡ዐይኖሙ፡ወኢ
ርእየት፡ወኢያእመረት።

ወበዕለተ፡ዐርብ፡ኢይደሉ፡ከመ፡ትትኀደግ፡
ሥጋ፡እንዘ፡ስቅልት፡ዲበ፡ዕፅ፤ሰአልዎ፡ለመኰ
ንን፡ከመ፡ይስብሩ፡ቍየጺሆሙ፡ለፈያት፡
ወሶቤሃ፡ይሙቱ፡ወሰበሩ፡ቍየጺሆሙ።

ወለመድኀንሰ፡ረከብዎ፡ዘነዋ፡ሞተ፡
ወሮጸ፡አሐዱ፡እምሐራ፡ወወግአ፡ገቦሁ፡
ዘየማን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፴፯፡ ሌላም፡መጽሐፍ፡የወጉትን፡ያዩት፡ዘንድ፡
አላቸው፡ይላል።

ዐርብ፡በአሥራ፡አንድ፡ሰዓት፡ከወንጌል፡
በኋላ፡የሚነበብ፡ይህ፡ነው።

፩፡ በደሉ፡ወደ፡ሰማይ፡የደረሰች፡እስራኤልስ፡
የተናቀ፡ሆኖ፡በክሕደት፡ተማረከ፤በነገዱ፡
ልዩ፡የሆነ፡የመቶ፡አለቃው፡ግን፡የተሰቀ
ለውን፡አይቶ፡የባሕርይ፡አምላክ፡እንደሆነ፡
አመነው።

፪፡ እርሱ፡ብቻውን፡ያመነ፡አይደለም፡
አብረውት፡ያሉት፡ይህ፡በእውነት፡የእግዚአ
ብሔር፡ልጅ፡ነው፡እያሉ፡ሁላቸው፡ጮኹ፡
እንጂ።

፫፡ እንዲሁም፡አብሮት፡የተሰቀለ፡ወንበዴ፡አም
ላክነቱን፡አውቆ፡ይቅርታውን፡ፈለገ።

፬፡ ፈያታዊም፡ከላይ፡እስከ፡ታች፡ተቀዶ፡
ሁለት፡ክፍል፡ወደሆነው፡የምኵራብ፡
መጋረጃ፡ተመለከተ፤ፀሐይም፡ብርሃንዋን፡
ሠውራ፡በቀን፡ጨለማ፡እንደሆነች፡አየ።

፭፡ ስለ፡ፈጣሪው፡መራቆት፡ጨረቃም፡
ብርሃኑን፡ሠውሮ፡ደም፡እንደ፡ሆነ፡አየ።

፮፡ የሰማይ፡ሠራዊት፡ደነገጡ፤በዚህ፡አንድ፡
ቀንም፡ብዙ፡ከዋክብቶች፡ከሰማይ፡ወደቁ።

፯፡ ምድርም፡ተናወጠች፤አለቶችም፡
ተሠነጠቁ፤መቃብሮችም፡ተከፍተው፡
ሙታኖች፡ተነሡ፤ወደ፡ቅድስት፡አገርም፡
በግልጽ፡ገቡ፤ብዙዎችም፡ሰዎች፡
አወቋቸው።

፰፡ እነርሱም፡በዕንጨት፡ላይ፡የተሰቀለውን፡
አምላክነቱን፡አይተው፡ባወቁ፡ጊዜ፡
ለመኑት።

፱፡ የእስራኤል፡ዐይናቸው፡ግን፡ታወረች፤
አላየችም፤አላወቀችም።

፲፡ በዕለተ፡ዐርብ፡ሥጋን፡እንደ፡ተሰቀለ፡
መተው፡አይገባም፡ብለው፡እንዲሞቱ፡የወንበ
ዴዎቹን፡ጭን፡ጭናቸውን፡ይሰብሩ፡ዘንድ፡
ሹሙን፡ለመኑትና፡ጭን፡ጭናቸውን፡ሰበሩ።

፲፩፡ እነሆ፡መድኀን፡ጌታን፡ግን፡ፈጽሞ፡ሙቶ፡
አገኙት፤ከጭፍሮችም፡አንዱ፡ሩጦ፡ሂዶ፡
የቀኝ፡ጐኑን፡ወጋው።

## በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፲፪፡ ወወጽአ ፡ እምኔሁ ፡ ደም ፡ ወማይ ፡ በአሐቲ ፡
ምዕር ፡ በቅድመ ፡ ጉቡዓን ፡ ወስምዐ ፡ ኮነ ፡
ዘበአማን፡ዘርእየ፡ዘንተ።
፲፫፡ ወአማን ፡ ውእቱ ፡ ስምዑ ፡ ወውእቱ ፡ ካዕበ ፡
የአምር፡ከመ፡ውእቱ፡ይቤ፡አማነ፡በእንተ፡
ዘንቱ፡ጸሐፈ፡በከመ፡ርእየ።
፲፬፡ ወነገረ ፡ አሪት ፡ ተፈጸመ ፡ ላዕሌሁ ፡ እስመ ፡
ዐፅም፡ዘሎቱ፡ኢይሰበር።
፲፭፡ ወካዕበ ፡ ይሬእይዎ ፡ እለ ፡ ወግእዎ ፡ ቅድመ ፡
አዕይንቲሆሙ፡ወይፈትሕ፡ላዕሌሆሙ።
፲፮፡ ወመኰንን ፡ ምዕትስ ፡ ሖረ ፡ እንዘ ፡ ይደነግፅ ፡
ኀበ ፡ ቤቱ ፡ ወይሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
እስመ፡ኮነ፡ይዴመም፡በልቡ።
፲፯፡ ወእስራኤልሰ ፡ ኢያእመሮ ፡ ወመድኃኒነ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሕማሙ ፡ መድኃኒት ፡
አድኃነ፡ዓለመ፡አድኀኖተ፡ዘለዓለም።

ክርስቶስ ፡ መድኃኒነ ፡ መጽአ ፡ ወሐመ ፡ በእን
ቲአነ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ፤ወቤዘወነ።
ማኅተመ፡ጸሎትስ፡ከመ፡ቀዳሚ፡ኅትም።

## ምዕራፍ፡፶፮።

በ፲፡ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዐርብ።

ክፍል፡፩።

ሰቈቃወ፡ኤርምያስ፡ነቢይ፡ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡
ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ምዕ፤፫፤፩–፷፮።

፩፡ አሌፍ ፡ አነ ፡ ብእሲ ፡ ዘይሬኢ ፡ ተጽናሰ ፡
በበትረ፡መዐቱ።

፪፡ ነሥአኒ ፡ ወወሰደኒ ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡
ዘአልቦ፡ብርሃን።
፫፡ ወሚጠ፡እዴሁ፡ኀቤየ፡ኵሎ፡ዕለተ።
፬፡ ወበልየ፡ሥጋየ፡ወማእሰየ፡ወተቀጥቀጣ፡አዕ
ዕምትየ።
፭፡ ቤት፡ሐነጸ፡ጥቅመ፡ላዕለ፡ርእስየ፡ወሠርሐ፡
ፍኖተ፡ሕማም፡ላዕሌየ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፲፪፤ ከእርሱም፡በተሰበሰቡት፡ሰዎች፡ፊት፡በአንድ፡
ጊዜ ፡ አንድነት ፡ ውኃና ፡ ደም ፡ መንታ፡ሆኖ፡
ወጣ፤ያየውም፡በእውነት፡ምስክር፡ሆነ።
፲፫፤ ምስክርነቱ ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እርሱም፡
እውነት ፡ እንደተናገረ ፡ ያውቃልና ፡ ስለዚህ፡
እንዳየ፡ጻፈ።
፲፬፤ ዐጥንቱ ፡ እንዳይሰበር ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ በኦሪት፡
የተጻፈው፡ተፈጸመ።
፲፭፤ ዳግመኛም ፡ የወጉትን ፡ በዐይናቸው ፡ ፊት፡
ያዩታል፤በእነርሱም፡ላይ፡ይፈርዳል፡ያለው።
፲፮፤ የመቶ ፡ አለቃውም ፡ ደንግጦ ፡ እግዚአብ
ሔርን፡እያመሰገነ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሄደ፤በልቡ፡
የሚደነቅ፡ሁኖአልና።
፲፯፤ እስራኤል ፡ ግን ፡ አላወቀውም ፤ መድኃኒ
ታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ሕይወት፡
መድኃኒት ፡ በሆነች ፡ ሕማሙ ፡ የዘላለም፡
ድኅነትን፡ለዓለም፡ሰጠ።
መድኃኒታችን፡ክርስቶስ፡ሰው፡ሁኖ፡መከራ፡
ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን፤ተቤዠንም።
የጸሎት፡መፈጸሚያ፡እንዳለፈው፡ፈጽም።

## ምዕራፍ፡፶፮።

ዐርብ፡በአሥራ፡ሁለት፡ሰዓት፡የሚነበብ፡
ይህ፡ነው።
ክፍል፡፩።

በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑርና፡
የነቢዩ፡ኤርምያስ፡ሐዘን፡(ለቅሶ)፡ይህ፡ነው።

ምዕ፤፫፤፩–፷፮።

፩፤ አሌፍ፡ማለት፡አንድ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡
ነው፤በቍጣው፡በትር፡ችግርን፡የሚጠብቅ፡
ሰው፡እኔ፡ነኝ።
፪፤ ይዞ ፡ ብርሃን ፡ ወደ ፡ ሌለበት ፡ ወደ ፡ ጨለማ፡
ወሰደኝ።
፫፤ ዘወትር፡እጁ፡መዐቱን፡ወደ፡እኔ፡መለሰ።
፬፤ ቍርበቴና ፡ ሥጋዬ ፡ አረጀ ፤ አጥንቶቼም፡
ተቀጠቀጠ።
፭፤ ቤት፡ማለት፡ባለ፡ጸጋ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡
ነው፤መከራ፡ግንቡን፡በራሴ፡ላይ፡ሠራ፡የመከ
ራውንም፡ጐዳና፡በእኔ፡ላይ፡አቀና።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

መውስተ፡ጽልመት፡አንበረኒ፡ከመ፡ምውተ፡
ዓለም።

ወነደቀ፡ላዕሌየ፡ወኢይወፅእ፡ወአክበደ፡
ሞቅሕየ።

ጋሜል፡ እጸርሕ፡ወዐወዩ፡እስመ፡ተፈጸመ፡
ጸሎትየ።

ወሐነጸ፡ፍኖትየ፡በኰኵሕ፡ወዐጸወ፡
ፍኖትየ።

ዳሌጥ፡ ድብ፡እንተ፡ትንዑ፡ውእቱ፡ሊተ፡
ወከመ፡አንበሳ፡ጽሚት።

ዴገነኒ፡ወአኅለቀኒ፡ወረሰየኒ፡ኀዳመ።

ሄ፡ ወሰቀ፡ቀስቶ፡ወአቀመኒ፡ከመ፡መጠራ፡
ለሐጽ።

ወነደፈኒ፡ውስተ፡ኵልያትየ፡በአሕጻሁ።

ወኮንኩ፡ሠሐቀ፡ለኵሉ፡ሕዝብየ፡ወየሐ
ለዩኒ፡ኵሎ፡አሚረ።

ዋው፡ አጽገበኒ፡ሕምዘ፡ወአርወየኒ፡
ሐሞተ።

ወሰበረኒ፡ስነንየ፡በኖጻ፡ወአቅሐመኒ፡
ሐመደ።

ወቀብጸት፡ነፍስየ፡ሰላመ፡ወረሳዕክዋ፡ለሠና
ይትየ።

ወሀጐልኩ፡ተስፋየ፡ወትውክልትየ፡በኀበ፡
እግዚአብሔር።

ዛይ፡ ተዘከር፡ተጽናስየ፡ወተሰዶትየ።

ወአንበዘት፡ነፍስየ፡በላዕሌየ።

ወአነብር፡ውስተ፡ልብየ፡ትካዘ፡በእንተ፡
ዝንቱ፡እትዔገሥ።

ሔት፡ ምሕረተ፡እግዚአብሔር፡እስመ፡
ኢኀልቀ፡ወኢተፈጸመ፡ሣህሉ።

---



ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

፮፥ እንደ፡ዘገየ፡ሬሳም፡በጨለማ፡ውስጥ፡
አኖረኝ።

፯፥ ግንብ፡መከራውን፡በእኔ፡ላይ፡ሠራ፤እኔ፡ግን፡
የምወጣበት፡የለኝም፤መከራውን፡
አጸናብኝ።

፰፥ ጋሜል፡ማለት፡ ግሩም፡እግዚአብሔር፡
ማለት፡ነው፤ጸሎቴ፡መከራውን፡ይዞ፡በእኔ፡
ተፈጽሟልና፡ወዳንተ፡ፈጽሜ፡እጮኻለሁ።

፱፥ ጎዳናዬን፡በአለቱ፡ላይ፡ሠራ፤ጎዳናዬንም፡
ዘጋው።

፲፥ ዳሌጥ፡ማለት፡ ድልው፡እግዚአብሔር፡ማለት፡
ነው፤ለእኔ፡እንደምታድን፡ግስላ፡ነው፤እንደ፡
አንበሳም፡ቀስ፡ብሎ፡የሚያድን፡ነው።

፲፩፥ ተከተለኝ፤ጨርሶም፡አጠፋኝ፤ምድረ፡
በዳም፡አደረገኝ።

፲፪፥ ሄ፡ማለት፡ ህልው፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
ቀስቱ፡መዐቱን፡ቀፈረ፤ዓላማን፡ለፍላጻ፡እንዲ
ያቆሙለት፡ለመከራው፡አቆመኝ።

፲፫፥ በፍላጻ፡መዐቱም፡ኵላሊቴን፡ወጋኝ።

፲፬፥ ለወገኖቼም፡ሁሉ፡መዘባበቻ፡ሆንኩ፤
ሁልጊዜም፡ይዘፍኑብኛል።

፲፭፥ ዋው፡ማለት፡ ዋሕድ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡
ነው፤መርዙን፡አጠገበኝ፤ሐሞትንም፡
አረካኝ።

፲፮፥ ጥርሴንም፡በአሸዋ፡ሰበረኝ፤አመዱንም፡
አቃመኝ።

፲፯፥ ልቡናዬ፡የሰላምን፡ተስፋ፡ቆረጠች፤
መልካም፡ነገርንም፡ዘነጋኋት።

፲፰፥ በእግዚአብሔርም፡ ዘንድ፡አለኝ፡ታዬን፡እምነ
ቴንም፡አጣሁ።

፲፱፥ ዛይ፡ማለት፡ ዝኩር፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤
መሰደዴን፡መከራዬን፡የሐሞቱን፡ምሬት፡አስብ።

፳፥ በኔ፡ላይ፡ያለች፡ልቡናዬ፡አእምሮዋን፡
አጣች።

፳፩፥ በልቡናዬ፡ሐዘንን፡አኖራለሁ፤ስለዚህም፡
እታገሣለሁ።

፳፪፥ ሔት፡ማለት፡ ሕያው፡እግዚአብሔር፡ማለት፡
ነው፤የእግዚአብሔር፡ቸርነቱ፡አላለቀምና፡
ይቅርታውም፡አልተፈጸመምና።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፳፫: ሐዳሳት፡ለለጸባሒ፡ብዝኀ፡ጽድቅከ።

፳፬: ክፍልየ : እግዚአብሔር : ትቤ : ነፍስየ : በእንተ፡ዝንቱ፡ጸናሕኩ።

፳፭: ጤት : ኄር : እግዚአብሔር : ለእለ : ይትዔገሥዎ።

፳፮: ለነፍስ : እንተ : ተኀሥሦ : በሠናይ : ወትት ዔገሥ : ወታረምም : ለመድኀኒተ : እግዚአብሔር።

፳፯: ሠናይ : ለብእሲ : ሶበ : ይነሥእ : አርዑተ : እምንእሱ።

፳፰: ዮድ : ወይነብር : ባሕቲቶ : ወይጸሙ : ሶበ : አንሥኡ፡ላዕሌሁ፤ይወዲ : ውስተ : መሬት : አፉሁ።

፳፱: የጊ : በተስፋ : ይመይጥ : መልታሕቶ : ለዘይጸፍዖ፡ወይጸግብ፡ጽዕለተ።

፴: ካፍ : እስመ : ኢይገድፎ : እግዚአብሔር : ለዓለም።

፴፩: እስመ፡ዘአሕመመ፡ይሣህል፡በከመ፡ብዝኀ፡ምሕረቱ።

፴፪: እስመ : ኢተቈጥዐ : ልቡ : ወኢሐመመ : ደቂቀ፡ ዕጓለ : እመሕያው ፤ ከመ : ይኅስር : በታሕተ፡እገሪሆሙ፡ወበኵሎሙ፡ኅሱራነ፡ምድር።

፴፫: ላሜድ ፤ ከመ : ይሚጥ : ፍትሐ : ብእሲ : በቅድመ፡ገጸ፡ልዑል።

፴፬: ይደይ፡ብእሴ፡ውስተ፡ኵነኔ፡ሶበ፡ይኴንን፡እግዚአብሔር፡ዘኢአዘዘ።

፴፭: ሚም ፤ መኑ : ዘይቤ : ዘይከውን : እግዚአብሔር፡ዘኢአዘዘ።

፴፮: ወእምአፈ : ልዑል : ዘኢወፅአ : እኩይኒ : ወሠናይኒ።

፴፯: ለምንት፡ያንጐረጕር፡ሰብእ፡እንዘ፡ሕያው፡ብእሲ፡በእንተ፡ኀጢአቱ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

፳፫፤ የቸርነትህ : ብዛት : ጧት : ጧት : አዲዲስ፡ሥራን፡ይሠራል።

፳፬፤ ልቡናዬ : እግዚአብሔር : ዕድል : ፈንታዬ፡ነው፡አለች፤ስለዚህ፡ቸርነቱን፡ጠበቅሁ።

፳፭፤ ጤት : ማለት : ጠቢብ : እግዚአብሔር፡ማለት፡ ነው ፤ ለሚታገሡት እግዚአብሔር፡ቸር፡ነው።

፳፮፤ በበጎ : ነገር : ለምትፈልገው : የእግዚአብሔርን፡ድኅነት፡ለማግኘት፡መከራውን፡ለምትታገሥ : ቢናገሩአትም : ዝም : ለምትል፡ሰውነት፡ቸር፡ነው።

፳፯፤ ከሕፃንነቱ : ጀምሮ : ቀንበሩን : (ቀኖና)፡ቢሸከም፡ለሰው፡በጎ፡ነገር፡ነው።

፳፰፤ ዮድ : ማለት : የማነ : እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤ብቻውን፡ተቀምጦ፡ይደክማል፤በሱ፡እጃቸውን፡በአነሡበትም፡ጊዜ፡አፉን፡ወደ፡መሬት፡ይደፋል።

፳፱፤ እነሆ፡በአለኝታውም፡በጥፊ፡ለሚመታው፡ሰው : ፊቱን : መልሶ : ይሰጣል ፤ ስድብንም፡ይጠግባል።

፴፤ ካፍ : ማለት : ከሃሊ : እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤እግዚአብሔር፡በመከራ፡ፈጽሞ፡አይተ ለውምና።

፴፩፤ ያሳዘነውን : ሰው : እንደቸርነቱ : መጠን፡ብዛት፡ይቅር፡ይለዋል።

፴፪፤ ልቡናው፡አልተበሳጨምና፡በዚህ፡ዓለም፡በጐሰቈሉ : ሰዎች : ሁሉ : ከእግራቸው፡በታች፡ ሁኖ : ይጐሰቍል፡ዘንድ፡በሰዎች፡ልጆች፡አላዘነምና።

፴፫፤ ላሜድ : ማለት : ልዑል : እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤በእግዚአብሔር፡ፊት፡የሰውን፡ፍርድ፡ይለውጥ፡ዘንድ።

፴፬፤ ሰውን : በመከራ : ይጥላል ፤ እግዚአብሔር፡ያላዘዘውን፡ፍርድ፡በፈረደ፡ጊዜ።

፴፭፤ ሚም : ማለት : ምዑዝ : እግዚአብሔር፡ማለት፡ ነው ፤ እግዚአብሔር : ያላዘዘው፡መከራ፡ይመጣል፡የሚል።

፴፮፤ ከእግዚአብሔር : አፍ፡ያልወጣ፡ክፉውም፡በጎውም፡ይደረጋል፡የሚል፡ማነው?

፴፯፤ ሰው፡ሕያው፡ሲሆን፡ስለ፡ኃጢአቱ፡መከራ፡በመጣበት፡ጊዜ፡ለምን፡ያንጐራጕራል!

በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ኖን፡ ንሕትት፡ ፍኖተነ፡ ወንኅሥሥ፡ ወንትመየጥ፡ኀበ፡እግዚአብሔር።

ናንሥእ፡ ልበነ፡ ወእደዊነ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ሰማየ።

ንሕነ፡አበስነ፡ወጌገይነ፡አንተኒ፡መሀከነ።

ሳምኬት፡ከደንከነ፡በመዓትከ፡ወሰደድከነ፡ወቀተልከነ፡ወኢመሀከነ።

ጸለልከነ፡በደመና፡እምወዊእ፡ለምዕራገ፡ጸሎትነ፤ከመ፡ንሕምም፡ወከመ፡ኢንርአይ፡አንበርከነ፡ማእከለ፡አሕዛብ።

ዔ፡ከሠቱ፡አፉሆሙ፡ላዕሌነ፡ኵሎሙ፡ፀርነ።

ፍርሀት፡ወረዓድ፡አኀዘነ።

ፈለገ፡ማይ፡ውኅዘ፡እምዐይንየ፡በእንተ፡ቅጥቃጤ፡ወለተ፡ሕዝብየ።

ፌ፡ዐይንየ፡ተደፍነት፡ወኢያረምም፡እንከ፡እምአልዕሎ፡እስከ፡ይሬኢ፡እግዚአብሔር፡እምሰማይ።

ዐይንየ፡አሕመሞ፡ለነፍስየ፡በእንተ፡ኵሉ፡ነፍሰ፡አዋልደ፡ሀገርየ።

ጻዴ፡ንዒወ፡ነዐዉኒ፡ፀር፡ከመ፡ዖፍ።

ወቀተሉ፡ሕይወትየ፡በከንቱ፡ውስተ፡ዐዘቅት፡ወከደኑኒ፡እብነ።

ተከዐወ፡ማይ፡ላዕለ፡ርእስየ፡እቤ፡ተኀደጉ፡እምኔሁ።

ቆፍ፡ጸዋዕኩ፡ስመከ፡እግዚእ፡እምግብ፡ታሕቱት።

ወሰማዕከኒ፡ቃልየ፡ወኢትሚጥ፡እዝነከ፡እምኑ፡ስእለትየ።

ቀረብ፡በዕለተ፡እጼውዓከ፡ወበለኒ፡ኢትፍራህ።



ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

፴፰፤ ኖን፡ማለት፡ንጉሥ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤ሥራችንን፡ፈጽመን፡እንመርምር፤ወደ፡እግዚአብሔርም፡በንስሐ፡እንመለስ።

፴፱፤ ልቡናችንን፡እደ፡ቃላችንንም፡ወደ፡ሰማይ፡ወደ፡እግዚአብሔር፡እናንሣ።

፵፤ እኛ፡ ፈጽመን፡ በደልን፡ አንተ፡ ግን፡ ራራልን።

፵፩፤ ሳምኬት፡ማለት፡ሰፋኒ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤ተቈጥተህ፡በመከራው፡ሸፈንከን፤አስወጥተህም፡ሰደድከን፤ገደልከን፤አልራራህልንም።

፵፪፤ ጸሎታችን፡ወደ፡ሚያርግበት፡ከመውጣት፡በደመና፡ ሸፈንከን፤ በመከራ፡ እንድንታመም፤ እንጸናም፡ ዘንድ፡ በአሕዛብም፡መካከል፡አኖርከን።

፵፫፤ ዔ፡ማለት፡ዓቢይ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤ ጠላቶቻችን፡ሁሉ፡በኛ፡አፋቸውን፡ከፈቱ።

፵፬፤ ፍርሀትና፡እንቅጥቅጥ፡ያዘን።

፵፭፤ ስለ፡ወገኔ፡ልጅ፡መከራ፡ከዐይኔ፡የዕንባ፡ጐርፍ፡ፈሰሰ።

፵፮፤ ፌ፡ማለት፡ፍቁር፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤ ዐይኔ፡በዕንባ፡ተሸፈነች፤በሰማይ፡ያለ፡እግዚአብሔር፡ግፌን፡እስኪያይልኝ፡ድረስ፡እንግዲህ፡ወዲህ፡ቃሌን፡ከፍ፡ከፍ፡ማድረግ፡ዝም፡አልልም።

፵፯፤ ዐይኔ፡ስለ፡አገሬ፡ልጆች፡ሰውነት፡ሁሉ፡ሰውነቴን፡አሳዘነው።

፵፰፤ ጻዴ፡ማለት፡ጻድቅ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤ጠላቶች፡እንደ፡ወፍ፡ማደንን፡አደኑኝ።

፵፱፤ ሰውነቴንም፡ በከንቱ፡ አጥፍተው፡ በጉድጓድ፡ውስጥ፡ደንጊያውን፡ገጠሙብኝ።

፶፤ በራሴም፡ላይ፡መከራው፡በዝቶ፡መጣብኝ፤ እኔም፡ከሱ፡ተለየሁ፡አልሁ።

፶፩፤ ቆፍ፡ማለት፡ቅሩብ፡እግዚአብሔር፡ማለት፡ነው፤ በጥልቅ፡ ጕድጓድ፡ ቈሜ፡ ስምህን፡ አቤቱ፡ጠራሁ።

፶፪፤ ቃሌን፡ ሰማኸኝ፤ ከልመናዬም፡ ጆሮህን፡ አትመልስ።

፶፫፤ በለመንኩህ፡ቀን፡ወደኔ፡ቅረብ፡አትፍራ፡በለኝ።

Scanned by CamScanner

፱፻፺፬

| በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት። |
|---|---|
| ፶፰፡ ሬስ ፡ ኰንንከ ፡ እግዚኦ ፡ ኵነኔ ፡ ነፍስየ ፡ ወቤዘውከ፡ሕይወትየ። | ፶፰፡ ሬስ ፡ ማለት ፡ ርእስ ፡እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው ፤ አቤቱ ፡ የሰውነቴን ፡ ፍርድ ፡ ፈርደህ፡ አዳንኸኝ። |
| ፶፱፡ ርኢከ ፡እግዚኦ ፡ ኵሎ ፡ ዘይመክሩ ፡ ላዕሌየ ፡ ወፍታሕ፡ፍትሕየ። | ፶፱፡ አቤቱ ፡ በኔ ፡ የመከሩትን ፡ ሁሉ ፡ አይተህ፡ ፍርዴን፡ፍረድልኝ። |
| ፷፡ ርኢ ፡ ኵሎ ፡ ተበቅሎቶሙ ፡ ወኵሎ ፡ ኀሊናሆሙ፡ብየ። | ፷፡ እኔን፡የተበቀሉትን፡በቀል፡ሁሉ፡በኔ፡ያሰቡ ትንም፡ኀሳባቸውን፡ሁሉ፡ተመልከት። |
| ፷፩፡ ሳን ፡ ሰማዕከ ፡ ኵሎ ፡ ጽዕለቶሙ ፡እግዚኦ ፡ ወኵሎ፡ኀሊናሆሙ፡ላዕሌየ። | ፷፩፡ ሳን ፡ ማለት ፡ ስቡሕ ፡እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው፤አቤቱ፡ ስድባቸውን፡ሁሉ፡ሰማህ፤ኀሳባቸውም፡ሁሉ፡በኔ፡ነው። |
| ፷፪፡ ወዘአሉሉ፡ከናፍሪሆሙ፡ብየ፡ኵሎ፡ዕለተ። | ፷፪፡ ሁልጊዜ ፡ ከንፈራቸውን ፡ የሚያላውሱት፡ በኔ፡ነው። |
| ፷፫፡ ንብረቶሙ ፡ ወተንሥኦቶሙ ፡ ርኢ ፡ አነ ፡ ማሕሌቶሙ። | ፷፫፡ ተቀምጠውም ፡ ተነሥተውም ፡ የሚዘፍኑት፡ በእኔ፡ነው። |
| ፷፬፡ ታው ፡ ፍድዮሙ ፡ ወስድዶሙ ፡ በመ ዐትከ። | ፷፬፡ ታው፡ ማለት፡ትጉህ ፡እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው ፤ ፍዳውን ፡ አምጣባቸው ፡ ተቆጥተህም፡ አስወጥተህ፡ስደዳቸው። |
| ፷፭፡ ሀቦሙ፡በከመ፡እከየ፡ልቦሙ። | ፷፭፡ አቤቱ ፡ እንደ ፡ ልቡናቸው ፡ ክፋት ፡ መጠን፡ ፍዳውን፡ስጣቸው። |
| ፷፮፡ ወአጥፍአሙ፡እምታሕተ፡ሰማይ፡እግዚኦ። | ፷፮፡ አቤቱ ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ በምድር፡ ያሉትን፡ ክፉዎች፡ሰዎች፡አጥፋቸው። |
| ሙኃልየ ፡ ሙኃልይ ፡ ዘሰሎሞን ፡ በረከቱ ፡ ትኩን፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን። | በረከቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለሙ ፡ ትኑርና፡ ሰሎሞን፡የተናገረው፡የምስጋና፡ምስጋና። |
| ፩፡ ከርቤ ፡ ወዐልው ፤ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ መቅድመ ፡ ዕፍረታት። ነቅዐ ፡ ገነት ፡ ዐዘቅተ ፡ ማየ ፡ ሕይወት ፡ ዘይውኅዝ፡እምሊባኖስ። | ፩፡ ከርቤ ፡ ዐልው ፡ የሚባሉ ፡ ሽቱዎች ፡ ከነዚህ፡ ሁሉ፡ሽቱዎች፡ጋራ፡አሉሽ። የተክል ፡ ቦታ ፡ ምንጭ ፡ የሕይወት ፡ ውኃ፡ ጕድጓድ፡ከሊባኖስ፡የሚፈስ፡ወንዝ፡ነሽ። |
| ፪፡ ተንሥኢ ፡ ሰሜን ፡ ወነዐ ፡ ደቡብ ፡ ንፋኅ ፡ ገነትየ። ለየሐዝ ፡ አፈዋተ ፡ ዚአየ ፤ ለይረድ ፡ወልድ ፡ እኁየ፡ ውስተ፡ገነቱ። | ፪፡ ሰሜናዊ ፡ ነፋስ ፡ ተነሥ ፤ ደቡባዊ ፡ ነፋስም፡ና፡ ለተክሌ፡ቦታ፡ንፈስ። ሽቱዬ ፡ ይፍሰስ ፤ልጅ ፡ ወንድሜ ፡ መርዓዊ፡ ወደ፡ተክሉ፡ቦታ፡ይውረድ። |
| ፫፡ ወይብላዕ፡እምፍሬ፡አቅማሒሁ። ቦእኩ፡ውስተ፡ገነትየ፡እኅትየ፡መርዓት። | ፫፡ ከሽቱውም፡ቅመም፡ፍሬ፡ይብላ። እኅቴ ፡ መርዓት ፡ (ሙሽራዬ) ፡ ወደ ፡ ተክሌ፡ አልገባም፡መስሎሻልን፡ገብቻለሁ። |
| ፬፡ አረርኩ፡ከርቤ፡ምስለ፡አፈዋትየ። በላዕኩ፡ኅብስትየ፡ምስለ፡መዓርየ። ሰተይኩ፡ወይንየ፡ምስለ፡ሐሊብየ። | ፬፡ ከሽቱዬ፡ጋር፡ከርቤን፡ለቀምሁ። ከማሬም፡ጋራ፡እንጀራዬን፡በላሁ። ከወተቴም፡ጋራ፡ወይኔን፡ጠጣሁ። |
| ፭፡ በልዑ፡ካልአንየ፡ወጸግቡ። ሰትዩ፡ውሉደ፡እኁውየ፡ወስክሩ። | ፭፡ ወዳጆቼ ፡ ይህን ፡ በልተው ፡ ጠገቡ ፤ የወን ድሞቼ፡ልጆች፡ወይን፡ጠጥተው፡ሰከሩ። |
| ፮፡ አነ፡ንውም፡ወልብየ፡ንቅህት። | ፮፡ እኔ፡ተኝቼ፡ነበር፤ልቡናዬ፡ግን፡ነቅቶ፡ነበር። |

## ክፍል፡፪።
### ሃይማኖተ፡አበው።
ምዕ፤፯፤፲–፲፩።

ይቤ፡ቅዱስ፡ሄሬኔዎስ፡ረድአሙ፡ለሐዋርያት።

፲ ተሰቅለ፡በሕማመ፡ሥጋ፡ወሐይወ፡በኃይለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘውእቱ፡መለኮቱ፡ ወወረደ፡ ውስተ፡መትሕተ፡ዕመቀ፡ምድር፡ወጼወወ፡ ነፍሳተ፡ሰብእ።

፲፩ ወከዐበ፡ዐርገ፡ሉዓሌ፡ሰማያት። ተርእየ፡ ጽውረ፡ለተወድዮ፡ውስተ፡መቃብር፡እንዘ፡ ውእቱ፡ይመልእ፡ኵሎ፤ሞተ፡በሥጋ፡ ወውእቱ፡ሕያው፡ለዓለመ፡ዓለም።

ምዕ፤፲፯፤፳–፳፫።

ዓዲ፡ይቤሉ፡ሠለስቱ፡ምዕት፡ዐሠርቱ፡ ወሰመንቱ፡ርቱዓነ፡ሃይማኖት።

፳ ብርሃን፡ዘእምብርሃን፡አምላክ፡ዘእም አምላክ፡ ዘበአማን፡ ዘተወልደ፡ ወአኮ፡ዘተገብረ፡ ኀቡር፡ ህላዌሁ፡ምስለ፡ አቡሁ።

፳፩ ዘቦቱ፡ኵሉ፡ኮነ፡ወዘእንበሌሁሰ፡አልቦ፡ ዘኮነ፡ ወኢምንትኒ፡ዘበሰማይኒ፡ወዘበም ድርኒ።

፳፪ ዘበእንቲአነ፡ለሰብእ፡ወበእንተ፡መድኃ ኒትነ፡ ወረደ፡እምሰማያት፡ተሰብአ፡ ወተሠገወ፡እመንፈስ፡ቅዱስ፡ወእማርያም፡ እምቅድስት፡ድንግል።

፳፫ ኮነ፡ብእሴ፡ወተሰቅለ፡በእንቲአነ፡ በመዋዕለ፡ ጲላጦስ፡ጰንጤናዊ፡ሐመ፡ ወሞተ፡ወተቀብረ።

ምዕ፤፲፡፲–፲፩።

ዓዲ፡ይቤ፡ቅዱስ፡አትናቴዎስ፡ሐዋ ርያዊ።

፲ በልዐ፡ወሰትየ፡ወደከመ፡በሐዊረ፡ፍኖት፤ ወተቀነወ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ቃለ፡እግዚአ ብሔር፡ ተዋሒዶ፡ምስሌሁ፡እንዘ፡ ኢይቀርቦ፡ኵሉ፡ሕማም።

፲፩ ወዓዲ፡ዝንቱ፡ሥጋ፡ተወድየ፡ውስተ፡ መቃብር፡እንዘ፡ኢይትፈለጥ፡እመለኮቱ፡

## ክፍል፡፪።
### የአባቶች፡ሃይማኖት።
ምዕ፤፯፤፲–፲፩።

የሐዋርያት፡ደቀ፡መዛሙራቸው፡ሄሬኔዎስ፡ እንዲህ፡አለ።

፲፤ ለሥጋ፡በሚስማማ፡ሕማም፡ተሰቀለ፤በእግ ዚአብሔርነቱ፡ ኃይል፡ተነሣ፤ይኸውም፡ መለኮቱ፡ ነው፤ወደ፡ሲኦልም፡ወርዶ፡ ነፍሳትን፡ማረከ።

፲፩፤ ዳግመኛ፡ወደ፡ሰማየ፡ሰማያት፡ዐረገ፤እርሱ፡ በሁሉ፡ምሉዕ፡ሲሆን፡ወደ፡መቃብር፡ ለመውረድ፡ተሸከመውት፡ታየ፤በሥጋ፡ ሞተ፤ይኸውም፡ለዘላለም፡ሕያው፡ነው።

ምዕ፤፲፯፤፳–፳፫።

ዳግመኛም፡ሃይማኖታቸው፡የቀና፡ሦስት፡መቶ፡ አሥራ፡ስምንት፡ሊቃውንት፡እንዲህ፡አሉ።

፳፤ ከብርሃን፡የተገኘ፡ብርሃን፤ከባሕርይ፡አም ላክ፡ የተገኘ፡የባሕርይ፡አምላክ፡ የተወ ለደ፡እንጂ፡የተፈጠረ፡ያይደለ፤ባሕርዩ፡ ከአባቱ፡ጋር፡በመለኮቱ፡አንድ፡የሚሆን።

፳፩፤ ሁሉ፡የተፈጠረበት፤ያለ፡እርሱ፡ግን፡ምንም፡ ምን፡የተፈጠረ፡የሌለ፤በሰማይ፡በምድር፡ ያለው፡ቢሆን።

፳፪፤ እኛን፡ስለማዳን፡ከሰማየ፡ሰማያት፡ ወርዶ፡በግብረ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ከቅ ድስት፡ድንግል፡ማርያም፡ ፍጹም፡ሰው፡ ሆነ።

፳፫፤ የሠላሳ፡ዘመን፡ጐልማሳ፡ሆኖ፡በጳንጦስ፡ ሰው፡በጲላጦስ፡የሹመት፡ዘመን፡ስለእኛ፡ ተሰቀለ፤ስለእኛም፡ታመመ፤ሞተ፤ተቀበረ።

ምዕ፤፲፡፲–፲፩።

ዳግመኛም፡ሐዋርያዊው፡ቅዱስ፡አትና ቴዎስ፡እንዲህ፡አለ።

፲፡ በላ፤ጠጣ፤መንገድ፤በመሄድ፡ደከመ፤ ሕማም፡ሁሉ፡ሳይኖርበት፡አካላዊ፡ቃል፡ ሥጋን፡ተዋሕዶ፡በዕፀ፡መስቀል፡ላይ፡ ተቸነከረ።

፲፩፤ ዳግመኛም፡ይህ፡ሥጋ፡ከመለኮቱ፡ ሳይ ለይ፡በመቃብር፡አደረ፤ነፍሱም፡ከመ

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወነፍሱሂ፡እንዘ፡ኢትትፈለጥ፡እመለኮት፡ ወረደት፡ውስተ፡ሲኦል፡ከመ፡ታብሥር፡ መድኃኒተ፡ለነፍሳት፡እለ፡ሙቁሕቶን፡ ይነብራ፡ውስተ፡ገሀነም፡ወታግዕዞን፡በከመ፡ ይቤ፡ጴጥሮስ፡ሐዋርያ።

፴፪፡ ወበዝንቱ፡ አእመርነ፡ ጥቀ፡ ሕጸተ፡ አእምሮቶሙ፡ለእለ፡ይብሉ፡እስመ፡ቃል፡ ተወለጠ፡ወተመይጠ፡ኀበ፡ከዊነ፡ዕፅም፡ ወሥጋ፡ሰበሰ፡ከነ፡ዝንቱ፡እሙነ፡እምኢተ ቀብረ፡ሥጋ፡ውስተ፡መቃብር፡አላ፡ እምወረደ፡ውስተ፡ሲኦል፡ከመ፡ያብሥር፡ ግዕዛነ፡ለነፍሳት፡እለ፡ሀለዋ፡ህየ።

፴፫፡ ወባሕቱ፡ ቃል፡ ዘይትዋሐድ፡ ምስለ፡ ነፍስ፡ወሥጋ፡ውእቱ፡ወረደ፡በነፍስተ፡ ሥጋ፡ውስተ፡ሲኦል፡ወሰበከ፡ግዕዛነ፡ ለነፍሳት።

፴፬፡ ወሥጋሰ፡ተርፈ፡ኀበ፡ዮሴፍ፡ወኒቆዲሞስ፡ በኀልጎታ፡እንዘ፡ይገንዝዎ፡ወይጠበልልዎ፡ በሰበን፤በከመ፡ዜነወ፡ወንጌል፡ቅዱስ።

ምዕ፡፴፬፡፲፪–፲፬።

ዓዲ፡ይቤ፡ቅዱስ፡ባስልዮስ፡ኤጲስቆጶስ፡ ዘቂሳርያ።

፲፪፡ ርኅበ፡ ወጸምአ፡ ዘበጽድቅ፡ ወአኮ፡ በምትሐት።

፲፫፡ ወዓዲ፡በልዐ፡ወሰትየ፡ምስለ፡ኃጥአን፡ወመጸ ብሐን፡ወዘአቅረቡ፡ሎቱ፡በልዐ።

፲፬፡ ወመጠወ፡ ርእሶ፡ ለስቅለት፡ ወተቀነዋ፡ እደዊሁ፡ ወእገሪሁ፡ ወተረግዘ፡ ገቦሁ፡ በኲናት። ወወፅአ፡እምኔሁ፡ደም፡ወማይ፡ አምሳሊሁ፡ለምሥጢር፡ቅዱስ።

ምዕ፡፴፮፡፳፫–፴።

ወዓዲ፡ይቤ፡ቅዱስ፡ጎርጎርዮስ፡ኤጲስቆጶስ፡ ዘኑሲስ።

፳፫፡ ወዝውእቱ፡ዘለብሰ፡አርአያ፡ገብር፡ወነድየ፡ ከመ፡ንብዐል፡ንሕነ፡በንዴተ፡ሥጋሁ፡ ዝንቱ፡ዘተዐገሠ፡ሕማመነ፡ወፆረ፡ደዌነ፡ ወነሥአ፡ጌጋየነ፡ወሦዐ፡ርእሶ፡በእንቲአነ፡ መሥዋዕተ፡ ንጹሐ፡ ውእቱ፡ ካህን፡

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

ለኮት፡ ሳትለይ፡ በገሃነም፡ ተግዘው፡ ለነ በሩ፡ ነፍሳት፡ ድኅነትን፡ ታበስር፡ ዘንድ፡ ነፃም፡ ታደርጋቸው፡ ዘንድ ወደ፡ሲኦል፡ወረደች፤ሐዋርያው፡ጴጥሮስ፡ እንደ፡ተናገረው።

፴፪፤ ቃል፡ ዐፅም፡ ሥጋ፡ ወደመሆን፡ ፈጽሞ፡ እንደ፡ ተለወጠ፡ የሚናገሩ፡ የመናፍቃንን፡ የአእምሮዋቸውን፡ ጕድለት፡ ፈጽመን፡ በዚህ፡ዐወቅን፤ይህስ፡እውነት፡ከሆነ፡ሥጋ፡ በመቃብር፡ባልተቀበረም፡ነበር፤በሲኦል፡ ላሉ፡ ነፍሳት፡ ነፃነትን፡ ያበሥር፡ ዘንድ፡ ወደሲኦል፡በወረደ፡ነበር፡እንጂ።

፴፫፤ ነገር፡ግን፡ከነፍስና፡ከሥጋ፡ጋር፡የተዋሐደ፡ ቃል፡ ነው፤ እርሱ፡ የሥጋ፡ ሕይወት፡ በምትሆን፡ በአካለ፡ ነፍስ፡ ወደ፡ ሲኦል፡ ወርዶ፡ለነፍሳት፡ነፃነትን፡ሰበከ።

፴፬፤ ሥጋ፡ግን፡በበፍታ፡እየገነዙት፡በጎልጎታ፡ በዮሴፍና፡በኒቆዲሞስ፡ዘንድ፡ነበር፤ቅዱስ፡ ወንጌል፡እንደተናገረ።

ምዕ፡፴፬፡፲፪–፲፬።

ዳግመኛ፡ የቂሳርያ፡ ኤጲስቆጶስ፡ ቅዱስ፡ ባስልዮስ፡እንዲህ፡አለ።

፲፪፤ ምትሐት፡ ያይደለ፡ በእውነት፡ ተራበ፤ ተጠማ፡እንጂ።

፲፫፤ ዳግመኛም፡ከኃጥአን፡ከመጸብሐን፡ጋር፡በላ፡ ጠጣ፤ያቀረቡለትንም፡በላ።

፲፬፤ ራሱን፡ አሳልፎ፡ ለመስቀል፡ ሰጠ፤ እጆቹን፡ እግሩን፡ ተቸነከረ፤ ጎኑን፡ በጦር፡ ተወጋ፤ ከእርሱም፡ቅዱስ፡ምሥጢር፡የተገለጠበት፡ ደምና፡ውኃ፡ፈሰሰ፡(ወጣ)።

ምዕ፡፴፮፡፳፫–፴።

ዳግመኛም፡የኑሲስ፡ኤጲስቆጶስ፡ቅዱስ፡ጎር ጎርዮስ፡እንዲህ፡አለ።

፳፫፤ የተገኘ፡ ባሕርይን፡ የተዋሐደ፡ በእርሱ፡ ትሕትና፡እኛ፡እንከብር፡ዘንድ፡የተዋረደ፡ እርሱ፡ ነው፤ ሕማማችንን፡ የታገሠ፡ ደዌያችንን፡ የተሸከመ፡ በደላችንን፡ የተቀበለ፡ ስለእኛ፡ ራሱን፡ የማያልፍ፡ የማይለወጥ፡

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፱፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ዘለዓለም።

፳፮ ወውእቱ ፡ በግዐ ፡ መሥዋዕት ። ውእቱ ፡ ካህን ፡ ሠዋዒ ፡ ወውእቱ ፡ ተወካፌ ፡ መሥዋዕት ፡ ምስለ ፡ አቡሁ ፡ ወመንፈስ፡ቅዱስ።

፳፯ ዝ፡ውእቱ፡ዘተወክፈ፡ሕማመ፡በሥጋሁ፡በፈቃዱ ፡ ወተዐገሠ ፡ ኵሎ ፡ ሕማማተ ። መጽአ፡ይጠባሕ፡ከመ፡በግዕ፡ወከመ፡በግዕ፡ዘኢይነብብ፡በቅድመ፡ዘይቀርፆ፡ኢከሠተ፡አፉሁ፡ወኢተረክበ፡ሐሰት፡ውስተ፡አፉሁ።

፳፰ ወወሰድዎ ፡ ኀሙዮ ፡ ውስተ ፡ ዐውደ ፡ ምኵናን፡ ወፈትሑ ፡ ላዕሌሁ ፡ መኳንንት ፡ ዐማፅያን ፡ ወፈደይዎ ፡ እኪተ ፡ ህየንተ ፡ ሠናይት።

፳፱ ወተዐገሠ ፡ በኵሉ ፡ እስከ ፡ በጽሐ ፡ ለሞት ፡ ሞቱሂ ፡ ዘበመስቀል ፡ ወኢከሠተ ፡ አፉሁ ፡ አሐደ፡ቃለ።

፴ ወአድኀነ ፡ በርደቱ ፡ እመስቀሉ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል፡ወፈትሐ፡እለ፡ሀለዉ፡ጻድቃን፡ህየ፡እለ ፡ ሙቁሐን ፡ በኃጢአተ ፡ አዳም ፡ አቡሆሙ።

ምዕ፡፴፰፡፫–፬።

ዓዲ፡ይቤ፡ቅዱስ፡ፊልክስ፡ሰማዕት፡ወሊቀ፡ጳጳሳት።

፫ ወውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘቦቱ ፡ ልደት፡በሥጋ፡ወሕማማት፡በዲበ፡መስቀል፡ወመዊት፡ወትንሣኤ።

፬ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ዲበ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ውእቱ ፡ ኵሎ ፡ እለ ፡ ሰከቡ ፡ እምዓለም፡ያነሥእ።

ምዕ፡፵፪፡፳–፳፭።

ዓዲ፡ይቤ፡ቅዱስ፡አቡሊዲስ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘሮሜ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፱፡ሰዓት።

መሥዋዕት፡አድርጎ፡ያቀረበ፡የማይሻር፡የማይለወጥ፡የዘላለም፡ካህን፡እርሱ፡ነው።

፳፮፤ የሚሠዋ፡በግ፡እርሱ፡ነው፤የሚሠዋ፡ካህን፡እርሱ ፡ ነው ፤ ከባሕርይ ፡ አባቱ ፡ ከአብ ፡ ከባሕርይ ፡ ሕይወቱ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋርም፡መሥዋዕት፡የሚቀበል፡እርሱ፡ነው።

፳፯፤ በፈቃዱ ፡ መከራን ፡ በሥጋው ፡ የተቀበለ ፡ መከራንም፡ሁሉ፡የታገሠ፡እርሱ፡ነው፤እንደ፡በግ፡ሊሠዋ፡መጣ፤በግ፡በሚሸልተው፡ሰው፡ፊት ፡ እንዳይናገር ፡ አልተናገረም ፤ በአንደበቱም፡ሐሰት፡አልተገኘበትም።

፳፰፤ የግንግሪት ፡ አሥረው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ አደባባይ፡ወሰዱት፤ዐመፀኞች፡ሹማምንት፡ይሙት፡በቃ፡ፈረዱበት፤በጎ፡ስለ፡አደረገላቸው፡ፈንታ፡ክፉ፡መለሱለት።

፳፱፤ ነፍሱን፡ከሥጋው፡እስከ፡መለየት፡ደርሶ፡በሁሉ፡መከራን፡ታገሠ፤ሞቱም፡በመስቀል፡ሆነ፤በአንደበቱም፡አንድ፡ነገርን፡ስንኳ፡አልተናገረም።

፴፤ ከመስቀሉ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ በመውረዱ ፡ አዳነን፤ በአባታቸው ፡ በአዳም ፡ በደል ፡ በሲኦል ፡ ተግዘው ፡ የነበሩ ፡ ጻድቃንን፡ፈታ።

ምዕ፤፴፰፡፫–፬።

ዳግመኛ ፡ ሰማዕት ፡ የሆነ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ፡ፊልክስ፡እንዲህ፡አለ።

፫፤ በሥጋ ፡ መወለድ ፡ በመስቀል ፡ መከራ ፡ መቀበል፡መሞት፡መነሣት፡ገንዘቡ፡የሆነ፡እርሱ፡እግዚአብሔር፡ቃል፡ነው።

፬፤ ስለዚህም፡በመስቀል፡ላይ፡ሳለ፡ከጥንት፡ጀምሮ፡በመቃብር፡ያሉ፡ሙታንን፡ሁሉ፡አስነሣ።

ምዕ፡፵፪፡፳–፳፭፡

ዳግመኛ ፡ የሮሜ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቅዱስ ፡ አቡሊዲስ፡እንዲህ፡አለ።

በ፲ወ፪፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፭ ወኢይትአመን ፡ መኑሂ ፡ በክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዕሩቅ ፡ ከመ ፡ ኢይደኀፅ ፡ እመለኮት ፡ ከመ ፡ ኢይ እምነ ፡ መድኀኒት ፡ እስመ ፡ ብእሲ ፡ ኢይክል ፡ ያድኅን ፡ ዓለመ ፡ ወሞቱ ፡ ለብእሲ ፡ ኢያነጽሖ ፡ ለዘይጠመቅ ፡ በስሙ ፡ ወኮልነ፡ንጠመቅ፡በሞተ፡ክርስቶስ።

፮ ወነአምን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሞቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ መላኪ ፡ ሕይወትነ ። አፍለሰ ፡ ሞተነ፡ኀበ፡ትንሣኤ፡ወክርስቶስ፡ አብጠለ፡ ሞተ ፡ ወአብርሃ ፡ ለሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ በከመ፡ጽሑፍ።

፯ ወኢይክል ፡ መኑሂ ፡ እምሰብእ ፡ ያብጥል ፡ ሞተ፡ ወያብርሃ ፡ ለሕይወት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ መኑ ፡ ሰብእ ፡ ዘየሐዩ ፡ ወኢይሬእያ ፡ ለሞት፤ወመኑ፡ዘያድኅና፡ለነፍሱ፡እምእደ፡ ሲኦል።

፰ ወዘኢክህለ፡ያድኅን፡ነፍሶ፡እፎመ፡ይክል፡ ያድኅን ፡ ካልአነ ፡ ወዘኢክህለ ፡ ያድኅን ፡ አሐደ፡ እፎኑመ ፡ ይክል ፡ ያድኅን ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ፡እስመ፡ኃጢአት፡የኀድር፡በውስተ፡ ሰብእ፡ወሞትኒ፡ይተልዎ።

፱ ይቤ ፡ እስመ ፡ ሞት ፡ ቀነዮሙ ፡ ለሰብእ ፡ እምአዳም፡እስከ፡ሙሴ፡ወለካልአንሂ፡እለ፡ ኢአበሱ ፡ አምሳለ ፡ ዕልወቱ ፡ ለአዳም ፡ እምቀዲሙ ፡ ዘአበሰ ፡ ቦቱ ፡ አዳም ፤ ወሶበ ፡ አበሰ ፡ አዳም ፡ ሶቤሃ ፡ ወለደ ፡ ዘከመ ፡ አምሳሊሁ።

፲ ወእምውእቱ፡መዋዕል፡በጽሐ፡ላዕለ፡ኵሉ፡ አሐዱ ፡ ትእዛዝ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይብል፡መሬት፡አንተ፡ወውስተ፡መሬት፡ ትገብእ።

፲፩ ወሙሴሂ ፡ ኢክህለ ፡ ያሰስል ፡ ሞተ ፤ እላ ፡ ሎቱኒ፡ አኀዞ፡ ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ኮኑ፡እምድ ኅሬሁ፡ቀነዮሙ፡ሞት።

ወክርስቶስሰ ፡ በሀብቱ ፡ ለሊሁ ፡ ወሀበ ፡ ሕይወተ፡ለኵሉ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

፭ ማንም ፡ ማን ፡ ከመለኮት ፡ የተለየ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በክርስቶስ ፡ አይመን፤ ከሕይወት ፡ እንዳይለይ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ዓለምን፡ያድን፡ዘንድ፡አይችልምና፤የዕሩቅ፡ ብእሲ ፡ ሞትም ፡ በሱ ፡ አምኖ ፡ የሚጠመ ቀውን ፡ አያከብረውምና ፤ ሁላችን ፡ በክር ስቶስ፡ ሞት፡እንከብራለን፡እንጂ።

፮ የሕይወታችን ፡ መገኛ ፡ የሚሆን ፡ የክርስቶስ፡ ሞት ፡ የእኛን ፡ ሞት ፡ ወደ ፡ ትንሣኤ ፡ እንደ ለወጠ ፡ እናምናለን ፤ ክርስቶስም ፡ ሞትን፡ አጥፍቶ ፡ ለዘላለም ፡ የማታልፍ ፡ ሕይወትን፡ ገለጠ፤በመጽሐፍ፡እንደ፡ተጻፈ።

፯ ከሰውም፡ወገን፡ማንም፡ማን፡ሞትን፡ያጠፋ፡ ዘንድ ፡ ትንሣኤንም ፡ ይገልጣት ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ዳዊት ፡ በሕያውነት ፡ የሚኖር፡ ሞትንም ፡ የማያያት ፡ ሰው ፡ ማነው? ነፍሱን፡ ከሲኦል ፡ ሥጋውን ፡ ከመቃብር ፡ የሚያድን፡ ማነው?ብሎ፡እንደተናገረ።

፰ ራሱን ፡ ማዳን ፡ ያልቻለው ፡ ሌላውን ፡ ማዳን፡ እንደምን ፡ ይችላል? አንድ ፡ ራሱን ፡ ማዳን፡ ያልቻለስ ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ ሊያድን ፡ እንደምን፡ይችላል?ኃጢአት፡በሰው፡አድሮ፡ ይኖር፡ነበርና፡ሞትም፡ይከተለው፡ነበርና።

፱ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ሰዎችን ፡ በአዳም ፡ በደል ፡ አምሳል ፡ ያልበደሉ ፡ ሌሎችንም ፡ ሞት ፡ እንደገዛቸው ፡ ተናገረ፤ መጀመሪያ ፡ የበደለ ፡ አዳም ፡ ነው፤ አዳምም፡ በበደለ ፡ ጊዜ ፡ የሚመስሉትን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ወለደ።

፲ በዚያን፡ወራት፡አዳምን፡መሬት፡ነህ፤ወደመ ሬትነትህ፡ተመለስ፡የሚል፡ከእግዚአብሔር፡ የታዘዘ፡አንድ፡አዋጅ፡በሁሉ፡ላይ፡ተነገረ።

፲፩ ሙሴም ፡ ሞትን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አልቻለም፤ እርሱንም ፡ ይዞ ፡ ገዛው ፡ እንጂ ፤ ከእርሱም፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ ነቢያትንም ፡ ሁሉ ፡ ሞት፡ ገዛቸው፡እንጂ።

ክርስቶስ ፡ ግን ፡ በቸርነቱ ፡ እርሱ ፡ ለሁሉ ፡ ሕይወትን፡ሰጠ።

በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ምዕ፡፴፩፡፯።

ዓዲ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ አዮክንድዮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ዘሮሜ።

አልቦቱ ፡ ለመለኮት ፡ ፍልጠት ፡ እምነ ፡
፯ ትስብእት፡እንዘ፡ስቁል፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ ኢተፈልጠ ፡ መለኮቱ ፡ እምትስብእቱ ፡ ኢ ፡ አሐተ፡ሰዓተ፡ወኢ፡ከመ፡ቅጽበተ፡ዐይን፤ ወእንዘሂ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ ኢተፈልጠ ፡ መለኮቱ፡እምትስብእቱ።

ምዕ፡፴፰፡፲፱-፳።

ዓዲ፡ይቤ፡ቅዱስ፡ኤራቅሊስ፡ኤጲስቆጶስ፡ ዘኪስኪስ።

፲፱ አንተ፡ዘኢትመውት፡ዘከመ፡ዕሪናከ፡ምስለ፡ አብ ፡ ወአንተ ፡ መዋቲ ፡ ዘከመ ፡ ዕሪናከ ፡ ምስሌነ።

፳ ወአንተ፡ውስተ፡መቃብር፡ወአንተ፡ንቡር፡ ዲበ፡ኪሩቤል።

አንተ ፡ ውስተ ፡ ምውታን ፡ ወበእንቲአከ ፡ ተውህበ፡ሕይወት።

አንተ፡ውስተ፡ምውታን፡ወአንተ፡ዘትሁብ፡ ግዕዛነ፡ለምውታን።

አንተ ፡ ዘኮንከ ፡ ምውተ ፡ ሠሉሰ ፡ መዋዕለ ፡ ወአንተ ፡ ህልው ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወምስለ ፡ መንፈስ፡ቅዱስ፡በኵሉ፡አዝማን።

አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘበአማን ፡ ዘሐመ ፡ በሥጋ ፡ እንዘ ፡ ኢየሐምም ፡ በመለኮቱ።

ምዕ፡፶፱፡፲፮።

ዓዲ፡ይቤ፡ቅዱስ፡ዮሐንስ፡ኤጲስቆጶስ፡ዘኢየ ሩሳሌም።

፲፮ ንህነሰ፡ነአምን፡ከመ፡ውእቱ፡ሐመ፡ወሞተ፡ በሥጋ፡በእንተ፡ኃጣውኢነ፡ወገነዘ፡ሥጋሁ፡ ሶበ፡ተፈልጠት፡እምነፍሱ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

ምዕ፡፴፩፡፯።

ዳግመኛ፡የሮሜ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አዮክንድዮስ፡ እንዲህ፡አለ።

፯፤ በመስቀል ፡ በሥጋ ፡ ተሰቅሎ ፡ ሳለ ፡ ለመለኮት ፡ ከሥጋ ፡ መለየት ፡ የለበትም ፤ አንዲት ፡ ሰዓትም ፡ ቢሆን ፡ የዐይን ፡ ጥቅሻ ፡ ያህል ፡ ስንኳ ፡ ቢሆንም ፡ መለኮት ፡ ከትስ ብእት ፡ አልተለየም ፤ በመቃብር ፡ ውስጥ ፡ ሳለም፡ መለኮት፡ከትስብእት፡አልተለየም።

ምዕ፡፴፰፡፲፱-፳።

ዳግመኛ ፡ የኪስኪስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቅዱስ ፡ ኤራቅሊስ፡እንዲህ፡አለ።

፲፱፤ ከአብ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ እንደመሆንህ ፡ ሞት ፡ የሌለብህ፡አንተ፡ነህ፤ከእኛም፡ጋር፡አንድ፡ እንደ፡መሆንህ፡በፈቃድህ፡የሞትክ፡አንተ፡ ነህ።

፳፤ በመቃብር፡ያደርህ፡አንተ፡ነህ፤ በኪሩቤል፡ ላይ፡ያለህ፡አንተ፡ነህ።

ከሙታን፡ጋር፡በመቃብር፡የነበርክ፡አንተ፡ ነህ ፤ በአንተ ፡ ሕማምና ፡ ሞትም ፡ድኅነት ፡ ተሰጠ።

ከሙታን ፡ ጋር ፡ የተቈጠርክ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ለሙታንም ፡ ትንሣኤን ፡ የምትሰጥ ፡ አንተ ፡ ነህ፤

ሦስት፡መዐልት፡ሦስት፡ሌሊት፡በመቃብር፡ ያደርክ ፡ አንተ ፡ ነህ ፤ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ፡ቅዱስ፡ጋር፡የምትኖር፡አንተ፡ነህ።

በመለኮት ፡ ሕማም ፡ ሳይኖርብህ ፡ በሥጋ ፡ የታመምክ ፡ አካላዊ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አንተ፡ነህ።

ምዕ፡፶፱፡፲፮።

ዳግመኛ፡የኢየሩሳሌም፡ኤጲስቆጶስ፡ቅዱስ፡ ዮሐንስ፡እንዲህ፡አለ።

፲፮፤ ኃጢአታችንን፡ለማስተስረይ፡በሥጋ፡እንደ፡ ታመመ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ከነፍሱም ፡ በተለየ ፡ ጊዜ፡ሥጋውን፡እንደ፡ገነዙ፡እናምናለን።

Scanned by CamScanner

## በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ምዕ፤፶፰፤፳፮–፳፰።

ዓዲ፡ይቤ፡ቅዱስ፡ኤጲፋንዮስ፡ኤጲስቆጶስ፡
ዘደሴተ፡ቆጵሮስ።
፳፮፡ መጽአ፡**እግዚአብሔር፡ቃል፡** ወኮነ፡ሰብአ፡
ከማነ፡ወለብሰ፡ሥጋ፡ዚአነ፡ዘቦቱ፡ነፍስ፡
ነባቢት፡ወናሁ፡አነ፡አቀውም፡ለከ፡ኵሎ፡
ስምዐ፡በእንተ፡ዝንቱ፡እምብሉይ፡ወሐዲስ።
፳፯፡ ዳዊትኒ፡ነቢይ፡ይቤ፡እስመ፡ኢተኀድጋ፡
ውስተ፡ሲኦል፡ለነፍስየ፡ወኢትሁቦ፡
ለጻድቅከ፡ይርአይ፡ሙስና።

ወበዝንቱ፡ይከሥት፡ኅብረተ፡ነፍስ፡ወሥጋ፡
ዘብእሲ፡ዘለብሶ፡**እግዚእ፡** ከመ፡የሀሉ፡
ውስቴቱ፡ልቡና፡ወአእምሮ፡ርቱዕ።
፳፰፡ ወከማሁ፡ኮነ፡እሙነ፡እስመ፡ነፍስ፡ምስለ፡
**መለኮት፡** ወረደት፡ውስተ፡ሲኦል፡ወእምነ፡
ሥጋሂ፡ኢተፈልጠ፡**መለኮት፡** እንዘ፡ሀሎ፡
ውስተ፡መቃብር፡ሠሉሰ፡መዋዕለ፡ከመ፡
ይከሥት፡ጽድቀ፡ትስብእቱ፡ቅዱስ፤
እስመ፡**መለኮት፡** ወነፍስ፡ፈጸሙ፡
ምሥጢረ፡በውስተ፡ሲኦል፡ወኢተእኅዘ፡
ውስቴቱ።

ምዕ፤፻፲፮፤፩።

፩፡ ዓዲ፡ይቤ፡ቅዱስ፡አባ፡ዘካርያስ፡ይሒያ፡
ወልደ፡ዓደይ፡ወልድ፡ውዱስ፡ወልደ፡
ዘካርያስ፤በመልእክቱ፡ኀበ፡አብ፡ኄር፡ወልድ፡
ፍቁር፡አውሥአተ፡በእንተ፡ንስጥሮሳውያን።
ወሃይማኖትነሰ፡ለነ፡ለያዕቆባውያን፡
በእንተ፡ትስብእተ፡**እግዚአብሔር፡ቃል፡**
ለሊሁ፡**እግዚአብሔር፡ቃል፡ወልደ፡እግ
ዚአብሔር፡** ውእቱ፡ቀዳማዊ፡ወረደ፡
እምሰማይ፡ወተሠገወ፡ወተሰብአ፡**እመ
ንፈስ፡ቅዱስ፡ወእማርያም፡ድንግል፡
ንጽሕት፡** ተወልደ፡ወተሰቅለ፡ለቢሃ፡
ኵሉ፡ዕጓለ፡እመሕያው፤ሐመ፡ወሞተ፡
ወተቀብረ።
በረከቶሙ፡ለእሉ፡መምህራን፡የሀሉ፡
ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
እምቃለ፡አረጋዊ፡መንፈሳዊ፡ድርሳን፡
ዕሥራ፡ወኅምስቱ።
፪፡ አ፡ዘበከይከ፡ላዕለ፡አልዓዛር፡ወአውሐዝከ፡

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

ምዕ፤፶፰፤፳፮–፳፰።

ዳግመኛ፡የቆጵሮስ፡ደሴት፡ኤጲስቆጶስ፡
ቅዱስ፡ኤጲፋንዮስ፡እንዲህ፡አለ።
፳፮፡ **እግዚአብሔር፡ቃል፡** መጥቶ፡እንደእኛ፡ሰው፡
ሆነ፤የምትናገር፡ነፍስ፡ገንዘቡ፡የምትሆን፡የእ
ኛን፡ሥጋ፡ተዋሐደ፤ስለዚህም፡እነሆ፡ከብሉይ፡
ከሐዲስ፡ምስክር፡አምጥቼ፡አስረዳሀለሁ።
፳፯፡ ነቢይ፡ዳዊትም፡ነፍሴን፡በሲኦል፡አትተ
ዋትም፡የባሕርይ፡ልጅህንም፡ሙስና፡
መቃብርን፡ያይ፡ዘንድ፡አሳልፈህ፡አትሰ
ጠውም፡አለ።
ይህም፡**ጌታ፡** በተዋሐደው፡አካል፡ያለውን፡
የነፍስና፡የሥጋን፡ተዋሕዶ፡ያስረዳል፤የቀና፡
ልቡና፡ዕውቀት፡በእርሱ፡ጸንቶ፡ይኖር፡ዘንድ።
፳፰፡ ዳዊት፡እንደተናገረው፡ዕውነት፡ሆነ፤ነፍስ፡
**መለኮትን፡** ተዋሕዳ፡ወደ፡ሲኦል፡ወርዳ
ለችና፤ሥጋም፡ሦስት፡መዐልት፡ሦስት፡
ሌሊት፡በመቃብር፡ሳለ፡**መለኮት፡** ከሥጋ፡
አልተለየም፤**አምላክ፡** ሰው፡የመሆኑን፡ዕውነ
ትነት፡ያስረዳ፡ዘንድ፤**መለኮት፡** ነፍስን፡
ተዋሕዶ፡በአካለ፡ነፍስ፡በሲኦል፡
ምሥጢርን፡ፈጽሟልና፡በሲኦልም፡በቁራ
ኘነት፡አልተያዘምና።

ምዕ፤፻፲፮፤፩።

፩፡ ዳግመኛ፡የዓደይ፡ልጅ፡የውዱስ፡ልጅ፡የዘካ
ርያስ፡ልጅ፡ይሒያ፡ቅዱስ፡አባ፡ዘካርያስ፡
ወደ፡ቸር፡አባቱ፡ስለ፡ንስጥሮሳውያን፡
በላከው፡መልስ፡እንዲህ፡አለ።
ለእኛ፡ለያዕቆባውያንስ፡ሃይማኖታችን፡
እንዲህ፡ነው፤ስለ፡**እግዚአብሔር፡ቃል፡**
ሰው፡መሆን፡ራሱ፡**እግዚአብሔር፡ቃል፡**
አስቀድሞ፡የነበረ፡እርሱ፡**የእግዚአብሔር፡**
ልጅ፡ከሰማይ፡ወርዶ፡በግብረ፡**መንፈስ፡
ቅዱስ፡ከንጽሕት፡ድንግል፡ማርያም፡**
ከሥጋዋ፡ሥጋ፤ከነፍሷ፡ነፍስ፡ነሥቶ፡ሰው፡
ሆኖ፡ተወለደ፤ለሰው፡ሁሉ፡ቤዛ፡ሆኖ፡
ተሰቀለ፤ታመመ፤ሞተ፡ተቀበረ።
የእነዚህ፡መምህራን፡በረከታቸው፡ከኛ፡ጋር፡
ለዘላለሙ፡ትኑር፡አሜን።
ከአረጋዊ፡መንፈሳዊ፡የተገኘ፡ሃያ፡አምስ
ተኛው፡ድርሳን፡ይህ፡ነው።
፪፡ ለአልዓዛር፡አዝነህ፡ያለቀስከና፡ዕንባን፡

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፪፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

አንብዐ፡ሐዘን፡ተወከፍ፡ምረረ፡ሐዘንየ፡ወአ
ንብዐየ።
፪ ፈውስ፡ሕማማትየ፡በሕማማቲከ፡አጥዒ፡
ቍስላትየ፡በቍስላቲከ፡ቶስሕ፡ደምየ፡
በደምከ፡ወደምር፡ውስተ፡ሥጋየ፡መዐዛ፡
ሕይወት፡ዘቅዱስ፡ሥጋከ።
፫ ከርቤ፡ዘሰተይከ፡እምነ፡ጸላእያን፡
ያጥዕማ፡ለነፍስየ፡እንተ፡ሰትየት፡ሐሞተ፡
እኩየ።
፬ ሥጋከ፡ዘተሰፍሐ፡ዲበ፡ዕፅ፡ስፉሐ፡ይረስዮ፡
ለኅሊናየ፡ኀቤከ፡እስመ፡ናሁ፡ተመውአ፡
እምኀበ፡ሰይጣን።
፭ ርእስከ፡ዘጸነ፡ዲበ፡ዕፀ፡መስቀል፡ያልዕሎ፡
ለርእስየ፡ዘተዘብጠ፡እምኀበ፡እኩያን፡
ወርኩሳን።
፮ እደዊከ፡ቅዱሳት፡እለ፡ተቀነዋ፡በቅ
ንዋት፡እምኀበ፡ከሓድያን፡ይምጥቃኒ፡
ኀቤከ፡እምግብ፡እኩይ፡በከመ፡አሰፈውከ፡
በአፉከ።
፯ ገጽከ፡ዘተወክፈ፡ምራቀ፡ርኩሰ፡ወኀሳረ፡
እምዐላውያን፡ያብርሆ፡ለገጽየ፡ዘከፍአ፡
በኃጢአት።
፰ ነፍስከ፡እንተ፡በጸልቦ፡ፈለሰት፡ኀበ፡አቡከ፡
ታብጽሐኒ፡ኀቤከ፡በጸጋከ።

፱ አንከር፡ብዝኀ፡ምሕረትከ፡እንተ፡ኢትት
ረከብ፡**አ፡ወልደ፡እግዚአብሔር፡** ዘከል
አቶሙ፡ለመላእክት፡ከመ፡ኢያውዕዩ፡
ዓለመ፡ወእለ፡የኀድሩ፡ውስቴታ።
፲ አራኅርኅ፡ልብየ፡ወይሠጠቅ፡እምፍርሀትከ፡
በከመ፡ተሠጥቁ፡አዕባን።
፲፩ ወእንሥእ፡ለልቡናየ፡መዋቲ፡በከመ፡
ተንሥኡ፡ምውታን።
፲፪ ረስየኒ፡**እግዚኦ፡** ከመ፡እትመየጥ፡ኀበ፡
መቃብሪከ፡ቅድስት፡በልቡናየ።
ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡የሃሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

አንቀጽ፡ዕሥራ፡ወተሰዐቱ፡እመጽሐፈ፡ዲድ
ስቅልያ፡ዘአበዊነ፡ሐዋርያት፤በረከቶሙ፡
የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።
፩ ወዕደው፡ጻድቃን፡አውረድዎ፡ውስተ፡
መቃብር፡ሐዲስ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

ያፈሰስከ፡**አምላክ፡ሆይ፡** የመረረ፡ሐዘኔንና፡
ዕንባዬን፡ተቀበል።
፪ ሕማሜንም፡በሕማምህ፡ፈውስ፤ቍስ
ሌንም፡በቍስልህ፡አድን፤ደምህንም፡በደሜ፡
ጨምር፤**የቅዱስ፡ሥጋህንም፡** የሕይወት፡
መዐዛ፡ከሥጋዬ፡ጋር፡አንድ፡አድርግ።
፫ ከጠላቶች፡እጅ፡የጠጣኸው፡ከርቤ፡ክፉ፡
ሐሞት፡ኃጢአትን፡ለጠጣች፡ለነፍሴ፡
ጣዕም፡ይሁናት።
፬ በዕፀ፡መስቀል፡ላይ፡የተዘረጋው፡ሥጋህ፡
ልቡናየን፡ወደ፡አንተ፡የተዘረጋ፡ያድርገው፤
እነሆ፡በሰይጣን፡ድል፡ሆኖአልና።
፭ በመስቀል፡ላይ፡ዘንበል፡ያለው፡ራስህ፡በር
ኩሳንና፡በክፉዎች፡አጋንንት፡ዘንድ፡የተደ
በደበ፡ራሴን፡ከፍ፡ከፍ፡ያድርገው።
፮ በከሐድያን፡አይሁድ፡በችንካሮች፡የተቸ
ነከሩ፡የከበሩ፡እጆችህ፡በአንደበትህ፡ተስፋ፡
እንዳስደረግህ፡ከክፉ፡ጕድጓድ፡ወዳንተ፡
ይምጠቁኝ።
፯ ከወንጀለኞች፡ርኵስ፡ምራቅንና፡ውርደትን፡
የተቀበለ፡ፊትህ፡በኃጢአት፡የጨለመ
ውንና፡የከፋውን፡ፊቴን፡ያብራው።
፰ በመስቀል፡ላይ፡በሥልጣንህ፡የተለየችው፡
ነፍስህ፡በቸርነትህ፡ወደ፡አባትህ፡ወደ፡
አንተ፡ታድርሰኝ።
፱ **የእግዚአብሔር፡ልጅ፡ሆይ፡** የማትመረመር፡
የቸርነትህን፡ብዛት፡አደንቃለሁ፤ዓለምንና፡
በውስጥዋ፡የሚኖሩትን፡እንዳያጠፉ፡መላእ
ክትን፡የከለከለቻቸው።
፲ ልቡናዬን፡አራራ፡አለቱም፡እንደተሠነጠቀ፡
አንተን፡ከመፍራት፡የተነሣ፡ይሠንጠቅ።
፲፩ ሙታንም፡እንደተነሡ፡ምውት፡ልቡናዬን፡
አንሣው።
፲፪ **አቤቱ፡** ወደ፡ከበረች፡መቃብርህ፡እንድ
መለስ፡አድርገኝ።
ልመናው፡በረከቱ፡ለዘላለሙ፡ከእኛ፡ጋር፡
ይኑር፤አሜን።

የአባቶቻችን፡ሐዋርያት፡በረከታቸው፡ከእኛ፡
ጋር፡ለዘላለሙ፡ይኑርና፡ከዲድስቅልያ፡መጽሐፍ፡
የተገኘ፡ሃያ፡ዘጠነኛ፡አንቀጽ፡ይህ፡ነው።
፩ ደጋግ፡ሰዎች፡ወደ፡አዲስ፡መቃብር፡አወ
ረዱት።

በ፲ወ፪፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፪፡ ወፈጺሞ ፡ ኵሎ ፡ ነገረ ፡ እምቅድመ ፡
ይሕምም ፡ ከመ ፡ ይኅብር ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡
እመሕያው ፡ ውስተ ፡ ከርሠ ፡ ምድር ፡ ሠሉሰ ፡
መዋዕለ፡ወሠሉሰ፡ለያልየ።
፫፡ ወካዕበ ፡ አዘዘነ ፡ ንጹም ፡ ጾመ ፡ ቅድስት ፡
ፋሲካ፡ ሰዱሰ ፡ ዕለተ ፡ በእንተ ፡ ዕልወቶሙ ፡
ለዕልዋን ፡ ወእከዮሙ ፡ ለአይሁድ ፡ እለ ፡
ውጹእን፡ወግዱፋን፡እምሕግ።
፬፡ ወካዕበ ፡ አዘዘነ ፡ ንጹም ፡ ረቡዐ ፡ ወዐርበ ፡
ረቡዐሰ፡በእንተ፡ዘፈጸሙ፡አይሁድ፡ምክረ፡
እኩየ፡ላዕሌሁ፡ወዐርበሰ፡በእንተ፡ሕማሙ፡
ማሕየዊት።

ድርሳን ፡ ወትምህርት ፡ ዘአበው ፡ ሐዋ
ርያት ፡ ቅዱሳን ፡ ዘመሀሩነ ፡ በረከቶሙ ፡
የሀሉ ፡ ምስሌነ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡
አሜን።
፭፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ መጽአ ፡ ዮሴፍ ፡
እምአርማትያስ፡ዘውእቱ፡ረድኡ፡ለእግዚእ፡
ኢየሱስ ፡ ወኒቆዲሞስ ፡ ዘበጽሐ ፡ ቀዲሙ ፡
ሌሊተ ፡ ኀበ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ አምጽአ ፡
ከርቤ፡ኀውሠ፡ምስለ፡አፈዋት፡ምዕተ፡ልጥረ።
፮፡ ወነሥእዎ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየ
ሱስ ፡ ወገነዝዎ ፡ በሰንዱናት ፡ ሐዲሳት ፡
በከመ ፡ ሕገ ፡ አይሁድ ፡ ወአሪት ፡ ዘይ
ገንዙ፡ወየዐጥኑ።
፯፡ ወሀሎ ፡ ገነት ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ ኀበ ፡
ሰቀልዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡ወውስተ፡ውእቱ፡
መካን ፡ ሀሎ ፡ መቃብር ፡ ሐዲስ ፡ ዘአልቦ ፡
ዘተቀብረ ፡ ውስቴቱ ፡ ወውእቱ ፡ መቃብር ፡
ቅሩብ ፡ በኀቤሆሙ ፤ እስመ ፡ ዐርቦሙ ፡
ለአይሁድ ፡ ውእቱ፡ ዕለት ፡ ወሀየ ፡ ቀበርዎ ፡
ለእግዚእ፡ኢየሱስ።
፰፡ ወመጽኡ ፡ አይሁድ ፡ ምስለ ፡ ሐራ ፡ ወአንከ
ርኰሩ ፡ እብነ ፡ ዐቢየ ፡ ኀበ ፡ አፈ ፡ መቃብር ፡
ወኀተምዎ።
፱፡ ወእምዝ ፡ ገብአ ፡ ዮሐንስ ፡ ኀበ ፡ ቤቱ ፡ ወተ
ናገረ ፡ ምስለ ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ማርያም ፡
ድንግል ፡ዙሎ፡ዘከመ፡ርእየ፡ወዘከመ፡ገብሩ፡
አይሁድ ፡ ላዕለ ፡ ወልዳ ፡ ዋህድ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ።
፲፡ ወኢያዕረፈት ፡ እምሐዘን ፡ ወኢጥዕመት ፡
እክለ፡ወኢሰትየት፡ማየ፡እምብዝኀ፡ሐዘን ፡
እንዘ ፡ ትበኪ ፡ መዐልተ ፡ ወሌሊተ ፡ ወኢያ
ዕርፃ፡አንብዐ፡አዕይንቲሃ፡እስከ፡ይትፌጸም፡
ሠሉስ፡መዋዕል።
በረከቶሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ የሀሉ ፡ ምስሌነ ፡
ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

፪፡ ሁሉንም ፡ ፈጽሞ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ክር
ስቶስ ፡ በምድር ፡ ሆድ ፡ ሦስት ፡ መዐልት ፡
ሦስት ፡ ሌሊት ፡ እንዲኖር ፡ ከመታመሙ ፡ በፊት ፡
ነገረን ።
፫፡ ዳግመኛም ፡ ከሕግ ፡ የወጡና ፡ የተጣሉ ፡ ወገኛ
ለኞች ፡ አይሁድ ፡ በከፋታቸው ፡ ስለ ፡ ፈጸሙት ፡
ድፍረት ፡ የከበረች ፡ የፋሲካን ፡ ጾም ፡ ስድስት ፡
ቀን፡እንድንጾም፡አዘዘን።
፬፡ ዳግመኛም ፡ ረቡዕና ፡ ዐርብን ፡ እንድንጾም ፡ አዘዘን፤
ረቡዕን ፡ የምንጾም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ምክራ
ቸውን ፡ ስለፈጸሙበት ፤ ዐርብንም፡ የምንጾም ፡
መድኃኒት፡ሕይወት፡ስለሆነች፡መከራው፡ነው።

በረከታቸውና ፡ ረድኤታቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡
ለዘላለሙ ፡ ይኑርና ፡ አባቶች ፡ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡
ያስተማሩትና ፡ የደረሱት ፡ ለእኛም፡ ያስተማሩን ፡
ትምህርት፡ይህ፡ነው፤አሜን።
፭፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከአርማትያስ ፡ ዮሴፍ ፡ መጣ፤
እርሱም ፡ የጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ደቀመ
ዝሙሩ ፡ ነው፤ አስቀድሞ ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሂዶ ፡ የነበረው ፡ ኒቆዲሞስም ፡
መቶ፡ልጥር፡ከርቤ፡ቅልቅል፡ሽቱ፡አመጣ።
፮፡ ሁለቱም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡
ወስደው ፡ በኦሪት ፡ እንደሚገንዙና ፡ እንደሚ
አጥኑ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ሕግ ፡ በአዲስ ፡ ድርብ ፡
በፍታ፡ገነዙት።
፯፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተሰ
ቀለበት ፡ በዚያም ፡ በአትክልቱ ፡ ቦታ ፡ ሰው ፡
ያልተቀበረበት ፡ አዲስ ፡ መቃብር ፡ ነበረ፤
መቃብሩም ፡ ለእነሱ ፡ ቅርባቸው ፡ ነበር፤
ያም ፡ ዕለት ፡ የአይሁድ፡ የሥራ ፡ መካተቻ ፡
ነበርና ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ በዚያ ፡
ቀበሩት።
፰፡ አይሁድም ፡ ከጭፍሮች ፡ ጋር ፡ መጡ፤ ወደ ፡
መቃብሩም፡አፍ፡ታላቅ፡ደንጊያ፡አንከባልለው፡
መቃብሩን፡ገጠሙት።
፱፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ፡
ከአምላክ ፡ እናት ፡ ከድንግል ፡ ማርያምም ፡ ጋር ፡
በአንድ ፡ ልጅዋ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ላይ ፡
አይሁድ ፡ እንዴት ፡ እንዳደረጉ ፡ ያየውን ፡ ሁሉ ፡
ከእርሷ፡ጋር፡ተነጋገረ።
፲፡ ቀንም ፡ ሌሊትም ፡ ስታለቅስ ፡ ስትጮኽ ፡ ከሐ
ዘን ፡ ተጽናንታ ፡ እህል ፡ ውኃን ፡ አልቀመ
ሰችም ፤ ከሐዘንም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሦስቱ ፡
ቀን ፡ እስኪፈጸም ፡ ከዐይኖቿ ፡ ዕንባ ፡ አልተቋ
ረጠም።
የሐዋርያት፡በረከታቸው፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

በ፲ወ፪፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ላሐ፡ማርያም።

በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ አሐዱ፡አምላክ፡ ድርሳን፡ ዘደረሰ፡ አባ፡ ሕርያቆስ፡ ኤጲስቆጶስ፡ ዘሀገረ፡ ብህንሳ፡ በእንተ፡ ሐዘና፡ ለድንግል፡ በዛቲ፡ ዕለት። ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ወሶበ፡ ተፈጸመ፡ ዝንቱ፡ ነገረ፡ ጲላጦስ፡ ምስለ፡ ሐቤ፡ ምዕት፡ ይቤሎ፡ እፎ፡ ይደሉ፡ ከመ፡ይኩን፡ዝንቱ፡ሥጋ፡ስቁለ፡ዲበ፡ዕፀ፡ መስቀል።

ወይቤሎ፡ ሐቤ፡ ምዕት፡ ለጲላጦስ፡ አ፡ ሥዩም፡ ለከ፡ ሥልጣን፡ ከመ፡ ትግበር፡ ዘትፈቅድ።

ወይቤሎ፡ጲላጦስ፡እፈቅድ፡ከመ፡ናውርዶ፡ እምዲበ፡ ዕፀ፡ መስቀል፡ ወናኅድሮ፡ ኀበ፡ ብእሲ፡መሐይምን፡እስከ፡ሣልስት፡ዕለት፡ እስመ፡ውእቱ፡አንሥአ፡ብዙኃነ፡ምውታነ፡ እምሰብእ፡የጊመ፡ውእቱ፡ይትነሣእ።

ወእንዘ፡ይብል፡ጲላጦስ፡ከመ፡ዝ፡ድንቀተ፡ ጠርዑ፡ኵሎሙ፡ዐበይተ፡አይሁድ፡እንዘ፡ ይብሉ፡አኮ፡ዝንቱ፡ሕግ፡ከመ፡ይኅድር፡ ምውት፡ ኀበ፡ ብእሲ፡ አላ፡ ማኅደረ፡ ምውታንሰ፡መቃብር፡ውእቱ።

ወእንዘ፡ይብልዎ፡ዘንተ፡ዐበይተ፡ሀገር፡ ለጲላጦስ፡መጽአ፡ዮሴፍ፡ዘአርማትያስ፡ ኀበ፡ጲላጦስ፡ወሰአለ፡ሥጋሁ፡ለእግዚእ፡ ኢየሱስ፡ከመ፡ያውርዶ፡እምዕፀ፡መስቀል፡ ወአሚሃ፡ ተፈሥሐ፡ ጲላጦስ፡ ወአዘዘ፡ የሀብዎ።

ወኮኑ፡ አይሁድ፡ ይተልውዎ፡ ድኅሬሁ፡ምስለ፡ ዐቀብት፡ ወአውረዶ፡ እመል ዕልተ፡ መስቀል፡ ወገነዝዎ፡ ውእቱኒ፡ ወኒቆዲሞስ።

ወኮኑ፡ አይሁድ፡ ይትጋእዝዎሙ፡ ወይ ትላኰይዎሙ፡ እስመ፡ እሙንቱ፡ ኢፈ ቀዱ፡ከመ፡ ያውርድዎ፡ እምዲበ፡ ዕፀ፡ መስቀል፡ አላ፡ ይኅድግዎ፡ ዲበ፡ ዕፅ፡ ምስለ፡ ፈያት፤ እስመ፡ ውእቱ፡ ቀደመ፡ ነገረ፡በእንተ፡ትንሣኤሁ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

የማርያም፡ሐዘን።

አንድ፡ አምላክ፡ በሆነ፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ ልመናው፡በረከቱ፡ ከእኛ፡ጋራ፡ለዘላለሙ፡ይኑርና፡የብህንሳው፡ ኤጲስቆጶስ፡አባ፡ሕርያቆስ፡በዚች፡ቀን፡ስለ፡ ድንግል፡ ማርያም፡ ሐዘን፡ የተናገረው፡ ድርሳን፡ይህ፡ነው።

፴፩፤ ይህም፡የጲላጦስ፡ነገር፡ከሙቶ፡አለቃው፡ ጋራ፡የተነጋገረው፡በተፈጸመ፡ጊዜ፡ይህ፡ ሥጋ፡በዕንጨት፡መስቀል፡ላይ፡ተሰቅሎ፡ ማደሩ፡እንዴት፡ይሆናል፡አለው።

፴፪፤ ሙቶ፡አለቃውም፡ጲላጦስን፡ሹም፡ሆይ፡የፈ ቀድከውን፡ ታደርግ፡ ዘንድ፡ ለአንተ፡ ሥልጣን፡አለህ፡አለው።

፴፫፤ ጲላጦስም፡ ከመስቀል፡ ላይ፡ አውርደን፡ ከታማኝ፡ሰው፡ዘንድ፡እስከ፡ሦስት፡ቀን፡ ድረስ፡እንድናሳድረው፡እወዳለሁ፤ እርሱ፡ ከሰዎች፡ ብዙዎች፡ ሙታኖችን፡ አስነሥ ቷልና፡እርሱም፡እኮ፡ይነሣል፡አለው።

፴፬፤ ጲላጦስም፡እንደዚህ፡ሲናገር፡የአይሁድ፡ ታላላቆች፡በድን፡በሰው፡ዘንድ፡እንዲያድር፡ ሕግ፡ አይደለም፤ የሙታን፡ ማደሪያ፡ መቃብር፡ ነው፡ እንጂ፡ እያሉ፡ በድ ንገት፡ጮሁ።

፴፭፤ የሀገሩም፡ታላላቆች፡ለጲላጦስ፡ይህን፡እየተ ናገሩ፡ ሳለ፡ የአርማትያስ፡ ሰው፡ ዮሴፍ፡ መጥቶ፡ የጌታ፡ ኢየሱስ፡ ሥጋውን፡ ከመስቀል፡ ላይ፡ ያወርደው፡ ዘንድ፡ ጲላጦስን፡ ለመነው፤ ያንጊዜም፡ጲላጦስ፡ ደስ፡ብሎት፡ይሰጡት፡ዘንድ፡አዘዘ።

፴፮፤ አይሁድም፡ከጠባቂዎች፡ጋር፡በኋላ፡በኋላው፡ ይከተሉት፡ ነበር፤ ከመስቀልም፡ ላይ፡ አወረደው፤ እርሱም፡ኒቆዲሞስም፡ሁነው፡ ገነዙት።

፴፯፤ አይሁድም፡ይጣሏቸውና፡ይጨቃጨቋቸው፡ ጀመር፤ እነርሱ፡ ከወንበዴዎቹ፡ ጋር፡ በመስቀል፡ ላይ፡ ሊተዉት፡ እንጂ፡ ከመስቀል፡ ላይ፡ ሊያወርዱት፡ አልወደ ዱምና፤ እሱ፡አስቀድሞ፡ስለ፡ትንሣኤው፡ ተናግሮ፡ነበርና።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፪፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፰፡ ወካዕበ፡እሙንቱ፡ገነዝዎ፡ሠናየ፡ግንዘተ፡ በአፈው፡ ወከርቤ፡ ወበልብሰ፡ ገርዜን፡ ሐዲስ፡ዘኢለብሶ፡ሰብእ፡ጥቀ።

፱፡ ወመቃብርኒ፡ ሐዲስ፡ ካዕበ፡ ዘኢተቀብረ፡ ውስቴቱ፡ ሥጋ፡ ሰብእ፡ ምንትኒ፡ እስመ፡ ተገብረ፡በቅሩቡ፡ለዮሴፍ፡ዘውእቱ፡በዓለ፡ ገነት፤ወእሙንቱ፡አንበርዎ፡ውስቴቱ፡ወአ ጽንዕዎ፡በዘ፡ጽንዕ።

፲፡ ወይቤሉ፡እስመ፡ ንሬኢ፡እስከ፡ሣልስት፡ ዕለት።

ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

ተአምሪሃ፡ለእግዝእትነ፡ቅድስት፡ድንግል፡ በክልኤ፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፡ጸሎታ፡ ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ዓለም፡ አሜን።

፩፡ ወካዕበ፡አዘዘ፡ውእቱ፡እግዚእ፡ደብተራ፡ ዓባየ፡ ወመጽአት፡ እምሰማይ፡ ወነፍሰ፡ ድንግል፡ውስቴታ፤ወሶቤሃ፡ወፅአት፡እምኔሁ ታክቲ፡ ደብተራ፡ ወአምኀት፡ ሥጋሃ፡ ባሕቲታ።

፪፡ ወትቤሎ፡ለወልዳ፡አ፡ወልድየ፡ፍቁር፡ መካን፡ዘእከውን፡አነ፡ውስቴታ፡ይኩን፡ ሥጋየ፡እንተ፡ኀደርከ፡አንተ፡ውስቴቱ፡ ተሰዓተ፡አውራኀ፡እስከ፡ዕለተ፡ትንሣኤ።

፫፡ ወበጊዜሃ፡ አዘዘ፡ እግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ተዓይነ፡መላእክት፡ ወሠራዊተ፡ ኪሩቤል፡ወሱራፌል፡ወሐራ፡ብርሃናውያን፡ ሰባሕያን፡ተዓይናውያን፡ከመ፡ይስግዱ፡ላቲ፡ ለሥጋ፡ድንግል።

፬፡ ወሶቤሃ፡ ተመይጠ፡ እግዚእ፡ መድኅን፡ ወይቤለኒ፡ አ፡ ዮሐንስ፡ ፍቁርየ፡ አንተ፡ ትሰምዕ፡በእንተ፡ሥጋየ፡ሶበ፡ አውረዱኒ፡ እምዲበ፡ዕፀ፡ መስቀል፡ እሉ፡ እሙንቱ፡ ዮሴፍ፡ወኒቆዲሞስ።

፭፡ ወይእዜኒ፡ ነዐ፡ ኀበ፡ ሥጋ፡ ወላዲትየ፡ ወእኅዛ፡ በእዴከ፡ ወደያ፡ ውስተ፡ ዛቲ፡ ሠረገላ፡እስመ፡አንተ፡ዘጾርከ፡ሥጋሃ፡ዲበ፡ ዐራት፡አመ፡ዕለተ፡ሞታ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

፰፡ ዳግመኛ፡ ፈጽሞ፡ ሰው፡ በአልለበሰው፡ በበፍታ፡በግምጃ፡በሽቱ፡በከርቤ፡መልካም፡ ግንዘትን፡ገነዙት።

፱፡ መቃብሩም፡ ደግሞ፡ ሰው፡ ያልተቀበረበት፡ ለራሱ፡ለዮሴፍ፡በቅርቡ፡የታነጸ፡ነው፤ባለ ቦታ፡ እርሱ፡ ነውና፤ እነርሱም፡ በዚያ፡ አኖሩት፤ በደንጊያም፡ ገጥመው፡ አጠና ከሩት።

፲፡ እስከ፡ ሦስት፡ ቀን፡ ድረስ፡ የሚሆነውን፡ እናያለን፡አሉ።

ልመናው፡በረከቱ፡ከኛ፡ጋራ፡ለዘለዓለሙ፡ ይኑር፡አሜን።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡ ይኑርና፡በድንጋሌ፡ሥጋ፡በድንጋሌ፡ነፍስ፡ የጸናች፡አምላክን፡የወለደች፡ክብርት፡እመ ቤታችን፡ድንግል፡ማርያም፡ያደረገችው፡ ተአምር፡ይህ፡ነው።

፩፡ ዳግመኛ፡ጌታ፡ አዘዘና፡ታላቅ፡ድንኳን፡ ከሰማይ፡ መጣች፤ የድንግል፡ ነፍስም፡ በውስጧ፡ ነበረች፤ ያንጊዜም፡ ከዚያች፡ ድንኳን፡ወጥታ፡ሥጋዋን፡ብቻ፡ተሳለመች።

፪፡ ልጄ፡ ወዳጄ፡ ሆይ፡ እኔ፡ በውስጧ፡ የማር ፍባት፡ቦታ፡አንተ፡ዘጠኝ፡ወር፡ያደርክበት፡ ሥጋየ፡እንደ፡ከበረ፡እስከ፡ትንሣኤ፡ቀን፡ ድረስ፡የከበረች፡ትሁን፡አለችው።

፫፡ በዚያን፡ጊዜም፡ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ የመላእክትን፡ነገድ፡ሠራዊት፡የኪሩቤልና፡ ሱራፌልን፡ ሠራዊት፡የሚያመሰግኑት፡ብርሃ ናውያን፡ጭፍሮቻቸውንና፡ሠራዊቶቻቸውን፡ ለድንግል፡ሥጋ፡ይሰግዱላት፡ዘንድ፡አዘዘ።

፬፡ ያንጊዜም መድኅን፡ጌታ፡ መለስ፡ ብሎ፡ ወዳጄ፡ዮሐንስ፡ሆይ፡ዮሴፍና፡ኒቆዲሞስ፡ ከመስቀል፡ በነ.ወረዱኝ፡ ጊዜ፡ አንተ፡ ስለ፡ ሥጋየ፡የሆነውን፡ታይ፡ትሰማ፡ነበር።

፭፡ አሁንም፡ወደ፡እናቴ፡ሥጋ፡ና፤በእጅህም፡ ይዘህ፡ወደሠረገላው፡አስገባት፤በሞተችም፡ ጊዜ፡ሥጋዋን፡በአልጋ፡የተሸከምክ፡አንተ፡ ነበርክና።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፪፡ሰዓተ፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፮ ወአንተ፡ጸርከ፡እስከ፡ቤተ፡ዮሳፍጥ፡እስመ፡
አንተ፡ዘተአመንከ፡ላዕለ፡ዛቲ፡በእንተ፡
ንጽሕናከ።

፯ ወሶበ፡ኮነ፡ዝንቱ፡ናሁ፡መላእክት፡
ወሊቃናት፡ኪሩቤል፡ወሱራፌል፡ነሥኡ፡
መዓጥነ፡ዕጣን፡ወአዕጹቀ፡እምዕፀ፡
ሕይወት፡ዘመሩ፡ወሰብሑ፡ቅድመ፡ሥጋሃ፡
ለድንግል፡በውስተ፡መካን፡ዘኮኑ፡ቅውማነ፡
ውስቴቱ።

፰ ወተርፈት፡ሰማይ፡ካልዕታ፡ምስለ፡ካልዕታ፡
ቅድሚሃ፡እስከ፡ተቀበለት፡ነፍሳ፡ወሥጋሃ፡
ብርሃናዌ፡ወመንፈሳዌ።

፱ ወእግዚእነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ቅድሚሆሙ፡
ወውእቱ፡እንዘ፡ይሴብሕ፡ወይዜምር፡
ቅድሚሃ፡ዝማሬያተ፡ወስብሐታተ፤ወከመ፡
ዝኮነ፡ዕርገታ፡ውስተ፡ሰማይ።

፲ ዕፁብ፡ጥቀ፡ወመድምም፡ዕበየ፡ክብራ፡ወተ
አምራቲሃ፡ወስብሐቲሃ፡ዘከመ፡አግብአ፡
ነፍሳ፡ውስተ፡ደብተራ፡ብርሃን፡ወዘከመ፡
ወደሳ፡ለእሙ፡መድኅን።

ጸሎታ፡ወበረከታ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ተአምር፡ወመንክር፡ዘገብረ፡እግዚእነ፡ወአ
ምላክነ፡ወመድኃኒነ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡
ሣህሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
ዓለም፡አሜን።

፲፩ ወሐሩ፡እለ፡የዐቅቡ፡መስቀለ፡ወሰበሩ፡
ቈየጺሆሙ፡ለክልኤቱ፡ፈያት፡ከመ፡
ይሙቱ።

፲፪ ወእምዝ፡ሐሩ፡ኀበ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ፡
ክርስቶስ፡ከመ፡ይስብሩ፡ቈይጾ፡ወረከብዎ፡
ከመ፡ሠለጠ፡መዊተ፡ወኢሰበሩ፡ቈይጾ።

፲፫ ወዝኒ፡ዘኮነ፡ከመ፡ይብጻሕ፡ቃለ፡መጽሐፍ፡
ዘይቤ፡ኢትስብሩ፡ዐፅሞ፡እምኔሁ።

፲፬ ወሀሎ፡ህየ፡ሊቀ፡ሐራ፡ኢየሩሳሌም፡
ይቀውም።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

፮፤ አንተም፡እስከ፡ዮሣፍጥ፡ቤት፡ድረስ፡ተሸከ
ምካት፤ስለ፡ንጽሕናህም፡ለዚች፡ሥራ፡
የታመንክ፡ሁነሃልና።

፯፤ ይህም፡በሆነ፡ጊዜ፡እነሆ፡መላእክት፡
አለቆቹም፡ሱራፌልና፡ኪሩቤል፡ዕጣን፡የሚ
ያጥኑበትን፡ጽንሓሕ፡ያዙ፤ከዕፀ፡
ሕይወትም፡አዕፁቆችን፡ይዘው፡ቁመው፡
በአሉበት፡ቦታ፡በድንግል፡ሥጋ፡ፊት፡
ፈጽመው፡ዘመሩ፤አመሰገኑ።

፰፤ ብርሃናዊና፡መንፈሳዊ፡የሆነ፡ሥጋዋንና፡
ነፍሷን፡በፊቷ፡ሁና፡እስከ፡ተቀበለች፡
ድረስ፡ሌላዋ፡ሰማይ፡ከሌላዋ፡ሰማይ፡ጋር፡
ጠበቀች።

፱፤ ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስም፡በፊታቸው፡
ሁኖ፡ፍፁም፡በሆኑ፡ምስጋናዎችና፡ክብር፡
እንደዚህ፡ባለ፡ሁኔታ፡ወደ፡ሰማይ፡ዐረገች።

፲፤ በልዕልና፡በክብር፡በምስጋና፡ነፍስዋን፡ወደ
ብርሃን፡ድንኳን፡መድኅን፡ጌታ፡ሲያስገባት፡
ዕፁብ፡ድንቅ፡ነበር።

ልመናዋ፡በረከቷ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ጥዑመ፡ስም፡በል።

ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘለዓለሙ፡
ይኑርና፡ጌታችን፡ፈጣሪያችን፡መድኃኒ
ታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ያደረገው፡ድንቅ፡
ተአምር፡ይህ፡ነው፤አሜን።

፲፩፤ መስቀሉንም፡የሚጠብቁት፡ሄደው፡ይሞቱ፡
ዘንድ፡የሁለቱን፡ወንበዴዎች፡ጭናቸውን፡
ሰበሩ።

፲፪፤ ከዚህ፡በኋላ፡ጭኑን፡ይሰብሩ፡ዘንድ፡ወደ፡
ጌታችን፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ሄዱ፤ፈጽሞ፡
ሙቶ፡አገኙት፤ጭኑንም፡አልሰበሩም።

፲፫፤ ይህም፡የሆነው፡ዐፅሙን፡ከእርሱ፡አትስበሩ፡
ያለው፡የመጽሐፍ፡ቃል፡ይደርስ፡ይፈጸም፡
ዘንድ፡ነው።

፲፬፤ በዚያም፡በኢየሩሳሌም፡የጭፍሮች፡አለቃ፡
ቁሞ፡ነበር።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፭ ወሶበ፡ርእየ፡ከመ፡ፀሐይ፡ጸልመ፡ወባዕዳንሂ፡ ተአምራት ፡ ይቤሎሙ ፡ ለሐራሂ ፡ ወለወ ዐሉቱ፡እሙነ፡እብል፡ከመ፡ዝንቱ፡ብእሲ፡ ወልደ፡እግዚአብሔር።

፮ ወሖረ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ እንዘ ፡ ይዴመም ፡ ወኰድዐ፡እንግድዓሁ፡በእደዊሁ።

፯ ወተጋብኡ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወመላህቅ ቲሆሙ ፡ ወካህናቲሆሙ ፡ ወሖሩ ፡ ኀበ ፡ ጲላጦስ ፡ ወይቤልዎ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ መስሐቲ፤ (ሎቱ ፡ ስብሐት) ፡ ይቤ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይትነሣእ ፡ እምነ ፡ ምውታን ፡ እምድኅረ ፡ ሠሉስ ፡ መዋዕል ፤ ወይእዜኒ ፡ አዝዝ ፡ ያውርድዎ ፡ ወለእለሂ ፡ ተሰቅሉ ፡ ምስሌሁ፡እመሳቅሊሆሙ፡ወያውዕይዎሙ፡ በእሳት፡ዮም፡በዛቲ፡ምሴት፡እምቅድመ፡ በአቱ፡ለሰንበት።

፰ ወይቤሎሙ ፡ ጲላጦስ ፡ አንሰ ፡ ኢያውዒ ፡ ሥጋ፡ንጉሥ፡ወኢይተሉ፡እበደክሙ።

፱ ወፈድፋደሰ፡በእንተ፡ዘአርአየ፡ተአምራተ፡ ወመንክራተ፡በሕይወቱ፡ወጊዜ፡ስቅለቱ፡ ይቤልዎ ፡ አ ፡ እግዚእነ ፡ እስመ ፡ ልማደ ፡ ሀገርነ፡ዛቲ፤እመ፡ተሰቅለ፡ውስቴታ፡ብእሲ፡ ያውዕይዎ፡በእሳት፡እምድኅረ፡አውረድዎ፡ እምላዕለ፡መስቀል፡ወኢታኀድግነ፡ዘንተ፡ ሥርዓተ።

፲ ወአዘዘ ፡ ጲላጦስ ፡ ከመ ፡ ይስድድዎሙ ፡ እምኀቤሁ።

፲፩ ወዓዲ ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ያውርዱ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ለእለ፡ተሰቅሉ፡እመሳቅሊሆሙ።

፲፪ ወመጽአ ፡ ብእሲ ፡ እምሰብአ ፡ ሀገረ ፡ አርማ ትያስ፡ዘይብልዎ፡ዮሴፍ፡ወዘመዱ፡ውእቱ፡ ለኒቆዲሞስ፡እኀወ፡ቀለዮጳ፡ዘመደ፡እስጢ ፋኖስ፡ቀዳሚ፡ሰማዕት።

፲፫ ሰአሎ፡ለጲላጦስ፡የሀቦ፡ሥጋሁ፡ለእግዚእነ፡ ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ወወሀቦ፡እስመ፡ጻድቅ፡ ውእቱ፡ወወቀረ፡ዮሴፍ፡ኰኵሐ፡ሐዲስ፡ መቃብሪሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ዘኢተወድየ ፡ ውስቴቱ ፡ መኑሂ ፡ እምሰብእ ፤ ወመካኑሂ ፡ ቅሩብ፡እመካነ፡መስቀል፡ዘተሰቅለ፡ቦቱ፡ እግዚእነ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

፭ ፀሐይ ፡ እንደ ፡ ጨለመና ፡ ሌሎች ፡ ተአምራ ቶችን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ለጭፍሮቹ ፡ ለሎሌዎቹ፡ ይህ፡ ሰው ፡ በውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ፡ እንደሆነ፡እውነቱን፡እናገራለሁ፡አላቸው።

፮ እያደነቀ ፡ ደረቱንም ፡ በእጆቹ፡እየደቃ፡ወደ፡ ቤቱ፡ሄደ።

፯ የካህናት፡አለቆችና፡የሕዝቡም፡አለቆች፡ካህ ናቶቻቸውም ፡ ተሰበሰቡ ፤ ወደ ፡ ጲላጦስም፡ ሂደው ፡ ይህ ፡ መስሐቲ ፡ (ምስጋና ፡ ለሱ፡ ይሁን) ፤ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እነሣለሁ፡ ብሏልና ፡ አሁንም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የተሰቀ ሉትን ፡ ጭምር ፡ ከተሰቀሉበት ፡ አውርደው፡ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ምሽት ፡ ሰንበት ፡ ከመግባቱ፡ በፊት ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሏቸው ፡ ዘንድ፡እዘዝ፡ አሉት።

፰ ጲላጦስም ፡ እኔ ፡ የንጉሥ ፡ ሥጋን ፡ አላቃ ጥልም፤ ስንፍናችሁንም ፡ አልከተልም፡ አላቸው።

፱ ይልቁንም፡በሕይወቱ፡ሳለ፡በስቅለቱ፡ጊዜ፡ ስለ፡ አሳየው፡ ተአምራት፡ ተጠራጥረዋልና፤ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ የሀገራችን ፡ ባህል ፡ ነውና፡ ሰው ፡ የተሰቀለ ፡ እንደሆነ ፡ ከተሰቀለበት፡ ካወረዱት ፡ በኋላ ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉታልና፡ ይህን፡ባህላችንን፡አታስቀርብን፡አሉት።

፲ ጲላጦስም ፡ ከደጁ ፡ ያበርሩአቸው ፡ ዘንድ፡ አዘዘ።

፲፩ ዳግመኛም ፡ የተሰቀሉትን ፡ ከተሰቀሉበት፡ ሥጋቸውን፡ያወርዱ፡ዘንድ፡አዘዘ።

፲፪ ከአርማትያስም ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ፡ ዮሴፍ፡ የሚሉት፡ ሰው፡ መጣ፤እርሱም፡ለመ ጀመሪያ ሰማዕት ፡ ለእስጢፋኖስ ፡ ዘመዱ፡ ለሆነ ፡ ለቀለዮጳ ፡ ወንድም ፡ ለኒቆዲሞስ፡ ዘመዱ፡ነው።

፲፫ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ሥጋውን፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ጲላጦስን ፡ ለመነው፡ እርሱም ፡ ፈቀደለት ፡ ዮሴፍም ፡ ደግ ፡ ሰው፡ ነውና ፤ ከሰው ፡ ወገን ፡ ማንም ፡ ያልተቀበረ በትን ፡ አዲስ ፡ መቃብር ፡ አዘጋጀቶ ፡ ነበር፡ ቦታውም ፡ ጌታችን ፡ ለተሰቀለበት ፡ ቦታ፡ ቅርብ፡ነበር።

Scanned by CamScanner

| በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ። | ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት። |
|---|---|

...ሙረ፡ዮሴፍ፡ሥጋሁ፡**ለእግዚእነ**፡ኒቆዲሞስ፡
...ቀለዮጳ ፡ አምጽኡ ፡ አፈወ ፡ ወገነዝዎ ፡
...ዘለሙ፡ ልማዶሙ፡ ለምውታኒሆሙ ፤
...ወሰተ፡ውእቱ፡መቃብር፡ወደዩ፡ሥጋሁ።
...ሀሉ፡ወምሕረቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡
...ዓለም፡አሜን።

ክፍል፡፫።

**ይ፡ዲ፡**ቀድመ፡ወንጌል።

መዝ፤፹፯፤፭–፮።

በእንተ ፡ ስመ ፡ ዚአሁ ፤ እመኒ ፡ ሖርኩ ፡
ማዕከለ፡ጽላሎተ፡ሞት፤ኢይፈርሆ፡ለእኩይ፡
እስመ፡አንተ፡ምስሌየ።

ወንጌል፡ዘማቴዎስ።

ምዕ፤፳፯፤፶፯–፷፩።

...ወመስዮ ፡ መጽአ ፡ ብእሲ ፡ ባዕል ፡ እምአርማ
ትያስ፡ዘስሙ፡ዮሴፍ፡ወውእቱሂ፡ይፀመዱ፡
**ለእግዚእ፡ኢየሱስ።**
...ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ጲላጦስ ፡ ወሰአለ ፡ ሥጋሁ ፡
**ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ** ፡ ወአዘዘ ፡ ጲላጦስ ፡
የሀብዎ።
...ወነሢአ፡ዮሴፍ፡ሥጋሁ፡**ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡**
ገነዞ፡በሰንዱናት፡ንጹሕ።
...ወቀበሮ፡ውስተ፡መቃብር፡ሐዲስ፡ዘሎቱ፡
አውቀረ፡ውስተ፡ኰኵሕ፡ወአንኰርኰረ፡
እብነ ፡ ዐቢየ ፡ ወአንበረ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡
መቃብር፡ወኀለፈ።
...ወሀለዉ ፡ ህየ ፡ ማርያም ፡ መግደላዊት ፡
ወካልእታሂ ፡ ማርያም ፡ ይነብራ ፡ ቅድመ ፡
መቃብር።

ወንጌል፡ዘማርቆስ።

ምዕ፤፲፭፤፵፪–፵፮።

...ወመስዮ ፡ ዐርብ ፡ አሚሃ ፡ በዓተ ፡ ሰንበት ፡
ውእቱ።
...መጽአ ፡ ዮሴፍ ፡ እምአርማትያስ ፡ ብእሲ ፡
...ኄር ፡ ወጠቢብ ፤ ወውእቱ ፡ ይሴፎ ፡ መን
...ግሥተ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ወተኃበለ ፡ ወቦአ ፡
...ኀበ፡ጲላጦስ፡ወሰአለ፡ሥጋሁ፡**ለእግዚእ፡**
**ኢየሱስ።**

---

፲፬፡ **የጌታችንን** ፡ ሥጋ ፡ ዮሴፍ ፡ ተሸከመ ፤ ኒቆዲ
ሞስና፡ቀለዮጳም፡ሽቱ፡አመጡ፤ሙታኖቻቸ
ውንም ፡ እንደሚገንዙ ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡
ገንዘው፡ሥጋውን፡ቀበሩ።
ይቅርታው፡ቸርነቱ፡ከእኛ፡ጋር፡ለዘላለሙ፡
ይኑር፡አሜን።

ክፍል፡፫።

**ዲያቆኑ፡**ከወንጌል፡በፊት።

መዝ፤፹፯፤፭–፮።

ስለ ፡ ስሙ ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ መካከል ፡ እንኳ ፡
ብሄድ፡አንተ፡ከእኔ፡ጋር፡ነህና፡ክፉን፡አል
ፈራም።

የማቴዎስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፳፯፤፶፯–፷፩።

፶፯፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ስሙ ፡ ዮሴፍ ፡ የሚባል ፡
ባለጸጋ፡ሰው፡ከአርማትያስ፡መጣ፤እርሱም፡
**ጌታችን፡ኢየሱስን፡**ይከተለው፡ነበር።
፶፰፤ ወደ፡ጲላጦስም፡ሂዶ፡**የጌታችን፡የኢየሱስን፡**
ሥጋ፡ለመነ፤ጲላጦስም፡እንዲሰጡት፡አዘዘ።

፶፱፤ ዮሴፍም ፡ **የጌታችን ፡ የኢየሱስን** ፡ ሥጋ ፡
ተቀብሎ፡በንጹሕ፡በፍታ፡ገነዘው።
፷፤ ለራሱ ፡ ብሎ ፡ ከአለት ፡ በአስፈለፈለው ፡
በአዲስ ፡ መቃብር ፡ ቀበረው ፤ ታላቅ ፡
ደንጊያም፡አንከባልሎ፡የመቃብሩን፡አፍ፡
ገጥሞ፡ሄደ።
፷፩፤ ከዚያም፡ማርያም፡መግደላዊትና፡ሌላይቱ፡
ማርያም ፡ ከመቃብሩ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡
ተቀምጠው፡ነበር።

የማርቆስ፡ወንጌል።

ምዕ፤፲፭፤፵፪–፵፮።

፵፪፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ዐርብ ፡ መሽቶ ፡ ሰንበት ፡
መግባቱ፡ነበር።
፵፫፤ ዮሴፍም፡ከአርማትያስ፡መጣ፤ብልህና፡ደግ፡
ሰው ፡ ነበር ፤ እርሱም ፡ **የእግዚአብሔርን** ፡
መንግሥት ፡ ተስፋ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ ደፍሮ ፡
ወደ፡ጲላጦስ፡ገባና፡**የጌታችን፡የኢየሱስን፡**
ሥጋ፡ለመነ።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፩፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

፵፬፡ ወአንከረ ፡ ጲላጦስ ፡ ወይቤ ፡ እፎ ፡ ሞተ ፡ ወጸውዖ፡ለሐራዊ፡ወይቤሎ፡ወድአኑ፡ሞተ፡ ወይቤ፡እወ፡ሞተ።

፵፭፡ ወአእሚሮ፡በኀበ፡ሐራዊ፡ከመ፡ሞተ፡አዘዘ፡ ይጸግውዎ፡ለዮሴፍ፡ሥጋሁ።

፵፮፡ ወተሣየጠ ፡ ዮሴፍ ፡ ሰንዱናተ ፡ ወአውረዶ ፡ ወገነዞ ፡ በሰንዱናት ፡ ወቀበሮ ፡ ውስተ ፡ መቃብር፡ዘአውቀረ፡ውስተ፡ኰኵሕ፤ወአን ኰረኰረ፡እብነ፡ውስተ፡አፈ፡መቃብር።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፩፡ሰዓት።

፵፬፡ ጲላጦስም ፡ እንዴት ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ አደነቀ ፡ ወታደሩን ፡ ጠርቶ ፡ በውኑ ፡ ፈጽሞ ፡ ሞተን? አለው፤እርሱም፡አዎን፡ሞተ፡አለው።

፵፭፡ እንደሞተም፡ከወታደሩ፡ተረድቶ፡ሥጋውን፡ ለዮሴፍ፡እንዲሰጡት፡አዘዘ።

፵፮፡ ዮሴፍም ፡ በፍታ ፡ ገዝቶ ፡ አውርዶ ፡ በበፍታ ፡ ገንዞ ፡ ከአለት ፡ በአስፈለፈለው ፡ አዲስ ፡ መቃብር ፡ ቀበረው ፤ ደንጊያም ፡ አገላብጦ ፡ የመቃብሩን፡አፍ፡ገጠመ።

ዘከመ ሰአለ ዮሴፍ ያውርድ ሥጋሁ ለእግዚእን።



ዮሴፍ የጌታችን ሥጋውን ላውርድ ብሎ እንደለመነ።

፵፯፡ ወማርያም፡መግደላዊት፡ወማርያም፡እንተ፡ ዮሳ፡ርእያ፡ኀበ፡ቀበርዎ።

ወንጌል፡ዘሉቃስ።

ምዕ፡፳፫፡፶-፶፮።

፶፡ ወመጽአ ፡ ብእሲ ፡ ዘስሙ ፡ ዮሴፍ ፡ ብእሲ ፡ ባዕል ፡ ዘቦቱ ፡ ምክር ፡ ሠናይ ፡ ኄር ፡ ወጻድቅ ፡ ወጠቢብ።

፶፩፡ ወውእቱሰ፡ኢሀሎ፡ውስተ፡ምክሮሙ፡ወምግ ባሮሙ ፡ ለአይሁድ ፤ ወሀገሩ ፡ አርማትያስ ፡ ዘይሁዳ ፡ ወኮነ ፡ ይሴፈዋ ፡ ውእቱኒ ፡ ለመን ግሥተ፡እግዚአብሔር።

፶፪፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ጲላጦስ ፡ ወሰአለ ፡ ሥጋሁ ፡ ለእግዚእ፡ኢየሱስ።

፶፫፡ ወአውረዶ፡ ሥጋሁ፡ ወገነዞ፡ በሰንዱናት፡ ወቀበሮ፡ ፡ ውስተ፡መቃብር፡ዘአውቀረ፡ለርእሱ፡ኀበ፡አልቦ፡ ዘተቀብረ፡ውስቴቱ፡ወአንኰርኰረ፡ዕብነ፡ዐቢየ፡ ወአንበረ፡ውስተ፡አፈ፡መቃብር፡ወኀለፈ።

፶፬፡ ወዐርብ ፡ ውእቱ ፡ ዕለት ፡ አሜሁ ፡ ለጸቢሐ ፡ ሰንበት።

፶፭፡ ወተለዋሁ፡ከልኤቲ፡አንስት፡እለ፡መጽኣ፡እምገ ሊላ፡ወርእያ፡መቃብሮ፡ወዘከመ፡ተወድየ፡ሥጋሁ።

፶፮፡ ወአተዋ ፡ ወተመይጣን ፡ አስተዳለዋ ፡ አፈዋተ፡ ወኀደጋ ፡ በሰንበት ፡ ወኢሖራ ፡ እስመ ፡ ከማሁ ፡ ሕጎሙ።

፵፯፡ ማርያም ፡ መግደላዊትና ፡ የዮሳ ፡ እናት ፡ ማርያም፡የተቀበረበትን፡ተመለከቱ።

የሉቃስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፳፫፡፶-፶፮።

፶፡ ዮሴፍ፡የሚባል፡ሰውም፡መጣ፤ሰውዬውም፡ ባለጸጋ ፡ ምክር ፡ አዋቂ ፡ ቸር ፡ ዕውነተኛ ፡ ብልህ፡ሰው፡ነበረ።

፶፩፡ እርሱም፡በአይሁድ፡በምክራቸው፡በሥራቸው፡ አልገባም፤ሀገሩም፡የይሁዳ፡ከተማ፡ከሚሆን፡ አርማትያስ፡ነበር፤እርሱም፡የእግዚአብሔርን፡ መንግሥት፡ተስፋ፡ያደርጋት፡ነበር።

፶፪፡ ወደ፡ጲላጦስም፡ሂዶ፡የጌታችን፡የኢየሱስን፡ ሥጋ፡ለመነ።

፶፫፡ ሥጋውንም ፡ አውርዶ ፡ በበፍታ ፡ ገንዞ ፡ ማንም፡ ባልተቀበረበት ፡ ለራሱ ፡ በአስፈለ ፈለው ፡ መቃብር ፡ ቀበረው ፤ ታላቅ ፡ ደንጊያ፡ አንከባሎ፡መቃብሩን፡ገጥሞት፡ሄደ።

፶፬፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ ቀኑ ፡ ዐርብ ፡ ማታ ፡ ለቅዳሜ፡ አጥቢያ፡ነበር።

፶፭፡ ከገሊላ ፡ የመጡ ፡ ሁለት ፡ ሴቶችም ፡ ተከተሉ ትና፡ሥጋው፡የተቀበረበትን፡መቃብሩን፡አዩ።

፶፮፡ ተመልሰውም፡ወደ፡ቤታቸው፡ሂደው፡ሽቱ፡ አዘጋጁ ፤ ግን ፡ በሰንበት ፡ አልሄዱም ፡ ሕጋቸው፡እንዲህ፡ነውና።

Scanned by CamScanner

ዘ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

ወንጌል፡ዘዮሐንስ።

ምዕ፡፲፱፡፴፰–፵፪።

ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ሰአሎ ፡ ለጲላጦስ ፡
ዮሴፍ ፡ ዘአርማትያስ ፡ ወዝንቱ ፡ ረድአ ፡
ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወህለወ ፡ ይሴሮ ፡
ወኀቡእ፡ በእንተ ፡ ፍርሃቶሙ ፡ ለአይሁድ ፡
ከመ፡ይንሣእ፡ሥጋሁ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡
ወአብሖ ፡ ጲላጦስ ፡ ወሖረ ፡ ውእቱኒ ፡
ወነሥአ፡ሥጋሁ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ።
ወመጽአ ፡ ኒቆዲሞስኒ ፡ ዘሖረ ፡ ኀቤሁ ፡
ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ቀዲሙ ፡ ሌሊተ ፡
ወአምጽአ፡ምዕተ፡ልጥረ፡ከርቤ፡ወዐልወ፡
ኅውሡ፡በዘቦቱ፡ይቀብርዎ።
ወነሥኡ ፡ ሥጋሁ ፡ ለእግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡
ወገነዝዎ፡በመዋጥሕ፡ክታን፡ዘሰንዱናት፡
ምስለ፡አፈው፡በከመ፡ሕግ፡አይሁድ፡ሶበ፡
ይገንዙ፡ወይቀብሩ።
ወቦ፡ህየ፡ገነት፡ውስተ፡ውእቱ፡መካን፡ኀበ፡
ሰቀልዎ፡ወውስተ፡ውእቱ፡ገነት፡ዝጐር፡
ሐዲስ፡ዘአልቦ፡ዘተቀብረ፡ውስቴቱ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

የዮሐንስ፡ወንጌል።

ምዕ፡፲፱፡፴፰–፵፪።

፴፰፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አይሁድን ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡
በሥውር ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ደቀ ፡
መዝሙር ፡ የነበረ ፡ የአርማትያሱ ፡ ሰው ፡
ዮሴፍ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡
ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ጲላጦስን ፡ ለመነ ፡
ጲላጦስም ፡ ፈቀደለት ፡ እርሱም ፡ ሂዶ ፡
የጌታችን፡የኢየሱስን፡ሥጋ፡ወሰደ።
፴፱፡ አስቀድሞ ፡ በሌሊት ፡ ወደ ጌታችን ፡
ኢየሱስ፡ ሄዶ ፡ የነበረው ፡ ኒቆዲሞስም ፡
መጥቶ ፡ ገነዘው ፡ የሚቀብሩበትን ፡ መቶ ፡
ንጥር፡ከርቤ፡ቅልቅል፡ሽቱም፡አመጣ።
፵፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስንም ፡ ሥጋ ፡ በሚገነዙ
በትና ፡ በሚቀብሩበት ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡ እንደ
ሚያደርጉት ፡ ሕግ ፡ ከሽቱ ፡ ጋር ፡ በድርብ ፡
በፍታ፡ገነዙት።
፵፩፡ በሰቀሉበት፡በዚያ፡ቦታም፡የአትክልት፡ሥፍራ፡
ነበር ፡ በዚያ ፡ በአትክልቱም ፡ ቦታ ፡ በውስጡ ፡
ሰው፡ያልተቀበረበት፡አዲስ፡መቃብር፡ነበር።

... ገነዝዎ ለእግዚእነ
... ወኒቆዲሞስ።



ዮሴፍና ኒቆዲሞስ
. ጌታችንን እንደገነዙት።

ወህየ፡ቀበርዎ፡ለእግዚእ፡ኢየሱስ፡እስመ፡
ተፍጻሜተ፡ ዐርበሙ ፡ ውእቱ ፡ ለአይሁድ ፡
ወቅሩብ፡ውእቱ፡መቃብር፡ኀበ፡ሰቀልዎ።

ድኅረ፡ወንጌል።

ወሠርቱ ፡ ወክልኤቱ ፡ ሰዓት ፡ መዓልት ፡
ዘዓርብ።
ወኮነ፡ሠርከ፡ውእቱ፡ዕለተ፡ዐርብ፡ዘለበዓል፡
ዘዚይ ፡ እንተ ፡ መጽአት ፡ እምቅድመ ፡
ሰንበት፡ዘለምሥጢረ፡ፈጣሪ።
ወመጽአ ፡ ብእሲ ፡ ባዕል ፡ ዘስሙ ፡ ዮሴፍ ፡
ወውእቱ፡ሌዋዊ፡ዘየአምር፡አሬተ፡ወብእሲ፡
ዘመከረ፡ዕዕብተ።
ወኒቆዲሞስ ፡ መፍቀሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዝንቱ ፡

፵፪፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስን ፡ ከዚያ ፡ ቀበሩት ፡
ለአይሁድ፡የመሰናዶአቸው፡ፍጻሜ፡ነበርና፡
መቃብሩም፡ለሰቀሉበት፡ቦታ፡ቅርብ፡ነበር።

ከወንጌል፡በኋላ።

ዐርብ ፡ ከቀኑ ፡ በአሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡
ከወንጌል፡በኋላ፡የሚነበብ፡ይህ፡ነው።
፩፡ የታላቁ፡ፋሲካ፡በዓል፡በዚሁ፡በዐርብ፡ቀን፡
ምሽት ፡ ከፈጣሪ ፡ የበዓል ፡ ምሥጢር ፡
አስቀድማ፡የመጣች።
፪፡ ስሙ፡ዮሴፍ፡የሚባል፡ባለ፡ጸጋ፡ሰው፡መጣ፡
እርሱ ፡ ሌዋዊ ፡ የሆነ ፡ አሬትን ፡ የተማረ ፡
አስደናቂ፡ምክርን፡የመከረ፡ሰው፡ነው።
ኒቆዲሞስም ፡ ፈጣሪውን ፡ የሚወድ ፡ ነው ፡

## በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ። ወእበዊሁ፡ ኮኑ፡ ያስተ
ዮሴፍ፡ካዕበ፡ውእቱ፡ ወእበዊሁ፡ኮኑ፡ያስተ
ሐምሙ፡ለሥጋተ፡ቅዱሳን።

፫፡ ወሖረ፡ኀበ፡ጲላጦስ፡ወሰአለ፡ሥጋሁ፡ለቃል፡ዋሕድ፡ወኮነ፡ይስእሎ፡ለእመ፡እንጋ፡ሞተ፡ ውእቱ። ወአንከረ፡መኰንን፡ ወአዘዘ፡ ከመ፡ ይትወሀብ፡ሎቱ፡ሥጋ፡እግዚእነ፡ኢየሱስ።

፬፡ ወነሥአ፡ ሥጋሁ፡ ወአስተሐመመ፡ ቦቱ፡ ሌዋዊ፡ ጻድቅ፡ አውጽአ፡ አልባሰ፡ ክታን፡ ጸዓድወ፡ በከመ፡ ይደሉ፡ ለወልደ፡ እግዚአብሔር።

፭፡ ወአምጽአ፡ ኒቆዲሞስ፡ ዕፍረታተ፡ ሠናያተ፡ ምዕተ፡ ልጥረ፡ ዘብዙኅ፡ ሤጡ፡ ወቀበርዎ፡ ከመዝ፡ በከመ፡ ልማዶሙ፡ ለዕብራውያን፡ ወወደዩ፡ ዕፍረተ፡ ላዕለ፡ ቡሩክ።

፮፡ ወመቃብር፡ ሐዲስ፡ ኮነ፡ ውስተ፡ ገነት፡ ዘኢተወድየ፡ ውስቴቱ፡ አሐዱሂ፡ ንጹሕ፡ ወጽሩይ።

፯፡ ተወድየ፡ሥጋሁ፡ለዋሕድ፡ውስተ፡ ዝኩ፡ መቃብር፡ወእብን፡ዲቤሁ።

፰፡ ወተፈልጡ፡ እምኔሁ፡ በከመ፡ ትእዛዝ፡ ወገብሩ፡በእንተ፡ሰንበት።

፱፡ ወአንስት፡ እለ፡ ይቀውማ፡ ማርያም፡ መግደላዊት፡ ወማርያም፡ ካልእት፡ ኮና፡ ይሬእያ፡ዘኮነ፡ ወአእመራ፡ ሠናየ፡ አይቴ፡ ተወድየ።

ክርስቶስ፡መድኃኒነ፡መጽአ፡ወሐመ፡ወበሕማማቲሁ፡አድኃነነ፡ወቤዘወነ።

ጸሎት፡ አኰቴት፡ እምድርሳነ፡ ቅዱስ፡ ኤፍሬም፡ሶርያዊ፡አፈ፡በረከት፡ወበቍዔት፡ ጸሎቱ፡ወበረከቱ፡የሀሉ፡ምስሌነ፡ለዓለመ፡ ዓለም፡አሜን።

፩፡ አ፡ ዘአልብከ፡ ኀጢአት፡ ባሕቲትከ፡ አ፡ ዘአግባእከ፡ርእሰከ፡በእንቲአየ፡ሊተ፡ለኃጥእ፡ አ፡ ዘኢኮንከ፡ ድልወ፡ ለሞት፡ ወዘ ሞትከ፡ከመ፡ታግዕዝ፡ነፍስየ፡ እማእሰረ፡ ኀጢአት።

፪፡ ምንተኑ፡ አዐስየከ፡ አ፡ እግዚእየ፡ ህየንተ፡ ሠናይት፡ዛቲ፡ዘገበርከ፡ሊተ፡ወአልብየኬ፡ ምንተኒ።

፫፡ ወባሕቱ፡ እብል፡ ስብሐት፡ ለከ፡ አ፡ ኄጳጒ፡አበሳት፡ወሰራዬ፡ኃጢአት፡ስብሐት፡ ለከ።

## ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት።

ዳግመኛም፡ የዚህ፡ የዮሴፍ፡ ወላጆች፡ የቅዱሳንን፡ሥጋ፡ለማከናወን፡የሚተጉ፡ነበር።

፫፡ ወደ፡ ጲላጦስም፡ ሄዶ፡ የዋሕድ፡ አካላዊ፡ ቃልን፡ ሥጋ፡ ለመነው፤ ሹሙም፡ እንዴ፡ ሞተን? ብሎ፡አደነቀ፤የጌታችን፡የኢየሱስን፡ ሥጋ፡ለዮሴፍ፡እንዲሰጠው፡አዘዘ።

፬፡ እርሱም፡ሥጋውን፡ወስዶ፡ለእግዚአብሔር፡ ልጅ፡ እንደሚገባ፤ በማስተንተን፡ ሌዋዊው፡ ጻድቁ፡ ዮሴፍ፡ የድርብ፡ በፍታ፡ ልብሶችን፡ አወጣ።

፭፡ ኒቆዲሞስም፡ ዋጋው፡ ብዙ፡ የሆነ፡ መቶ፡ ንጥር፡(ቅልቅል)፡መልካም፡ሽቱን፡አመጣ፤ እንደ፡ ዕብራውያን፡ ልማድ፡ ቀበሩት፤ ሽቱውንም፡ቡሩክ፡ምስጉን፡በሆነ፡ጌታችን፡ ላይ፡አፈሰሱት።

፮፡ መቃብሩም፡ በአታክልቱ፡ ውስጥ፡ የሆነ፡ ማንም፡ማን፡ያልተቀበረበት፡አዲስ፡የነጸ፡ የጸራ፡ነበር።

፯፡ የዋሕድ፡ ጌታ፡ ሥጋም፡ በዚያ፡ ተጨመረ፤ በላዩም፡ደንጊያ፡ገጠሙት።

፰፡ ተለይተውትም፡ሄዱ፤ስለ፡ሰንበትም፡ክብር፡ እንደ፡ትእዛዙ፡አደረጉ።

፱፡ በዚያም፡ የቆሙ፡ ሴቶች፡ ማርያም፡ መግደላዊት፡ ሌላይቱ፡ ማርያም፡ የሆነውን፡ አይተው፡ የት፡ እንደ፡ ተቀበረ፡ መልካም፡ አድርገው፡አወቁ።

መድኃኒታችን፡ ክርስቶስ፡ ሰው፡ ሁኖ፡ መከራ፡ተቀበለ፤በመከራውም፡አዳነን።

ልመናው፡ በረከቱ፡ ከእኛ፡ ጋር፡ ለዘላለሙ፡ ይኑርና፡ ረብህ፡ ጥቅምና፡ በረከትን፡ የሚያስገኝ፡ አንደበት፡ ካለው፡ ከቅዱስ፡ ኤፍሬም፡ ድርሳን፡የተገኘ፡ይህ፡ነው፤አሜን።

፩፡ አንተ፡ ብቻህን፡ ኃጢአት፡ የሌለብህ፡ ስለ፡ እኔ፡ ስለ፡ ኃጢአተኛው፡ ራስህን፡ ለሞት፡ ያሳለፍክ፡ ሆይ፡ ለሞት፡ የማትገባ፡ ስትሆን፡ ከኃጢአት፡ ማሰሪያ፡ ነፍሴን፡ ነጻ፡ ታወጣ፡ ዘንድ፡የሞትክ፡ሆይ።

፪፡ ጌታዬ፡ ሆይ፡ ስለዚች፡ ስለ፡ አደረግህልኝ፡ በጎነት፡ ምን፡ ወረታ፡ እመልስልሃለሁ! ምንም፡ምን፡የለኝማ!

፫፡ ነገር፡ ግን፡ ኃጢአትን፡ ለምታስተሰርዩና፡ በደልንም፡ ይቅር፡ ለምትል፡ ለአንተ፡ክብር፡ ምስጋና፡ይገባል።

Scanned by CamScanner

በ፲ወ፪፡ሰዓት፡መዓልት፡ዘዓርብ።

እ፡ዘወረድከ ፡ እምሰማይ ከመ ፡ ታድኅን ፡
ነፍሰነ፡ስብሐት፡ለከ።
እ፡ዘተሠገውከ፡እማኅፀነ ድንግል፡ማርያም፡
ስብሐት፡ለከ።
እ፡ዘተወልደ ፡ ለቤዛ ፡ ብዙኃን ፡ ስብሐት ፡
ለከ።
እ፡ዘተአስረ፡ስብሐት፡ለከ።
እ፡ዘተቀሥፈ፡ስብሐት፡ለከ።
እ፡ዘወረቁ፡ላዕሌሁ፡ስብሐት፡ለከ።

እ፡ዘተሰቀልከ፡ስብሐት፡ለከ፡
እ፡ዘሐመ፡ወሞተ፡ወተቀብረ፡ስብሐት፡ለከ፤
አሜን።

## ምዕራፍ፡፹፯።

በ፩፡ሰዓት፡ሌሊት፡ዘቀዳም።

ትእዛዝ።

በቀዳሚት፡ሰዓት፡ሌሊት፡ዘሰንበተ፡አይሁድ።
እምድኅረ ፡ ተፈጸመ ፡ ዝንቱ ፡ ያወርዱ ፡ አል
ባሰ ፡ ጸሕል ፡ ክዱናተ ፡ ወያልዕሉ ፡ ሥዕለ ፡
ስቅለት ፡ ወመስቀለ ፡ ወወንጌለ ፡ ወመባ
ርሀተ፡ሠምዕ።
ወይበሉ ፡ በምሥራቅ ፡ ወበምዕራብ ፡ በሰ
ሜን፡ወበደቡብ እግዚኦ፡መሐረነ፡ክርስቶስ፡
ምዕተ፡ምዕተ ፡ጊዜ ፡ ወይትመየጡ ፡ መንገለ ፡
ምሥራቅ፡ወይባኡ፡ቤተ፡መቅደስ፡ወይዑዱ፡
ታቦተ ፡ ሠለስተ ፡ ጊዜ ፡ ወይግንዙ ፡ ሥዕለ ፡
ስቅለት።
ወእምድኅሬሁ፡ይበሉ፡እ፡ዘወረድከ።
(ይ.ካ)፡እ፡ዘወረድከ፡እምሰማያት፡በእንቲአነ።
(ይ.ሕ)፡ስምዐነ፡አምላክነ፡ወመድኃኒነ፡እ፡
ክርስቶስ።
(ይ.ካ)፡እ፡ዘተወለድከ ፡ እምድንግል ፡ በእን
ቲአነ፡(ይ.ሕ)፡ስምዐ፡አም፡ወመ፡እ፡ክ።
(ይ.ካ)፡እ ፡ ዘሰኩብከ ፡ ውስተ ፡ ጎል ፡ በእ
ንቲአነ፡
(ይ.ሕ)፡ስም፡አም፡ወመ፡እ፡ክ።
(ይ.ካ)፡እ፡ዘተጠብለልከ ፡ በአጽርቅት ፡ በእን
ቲአነ፡(ይ.ሕ)፡ስም፡አም፡ወመ፡እ፡ክ።

ዓርብ፡መዓልት፡በ፲፪፡ሰዓት። 

፬፤ ነፍሳችንን ፡ ልታድን ፡ ከሰማይ ፡ የወረድክ ፡
ሆይ፡ለአንተ፡ክብር፡ይገባል።
ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ሰው ፡ የሆንክ ፡ ሆይ ፡
ክብር፡ለአንተ፡ይገባል።
፭፤ ለብዙዎች ፡ ቤዛ ፡ የተወለድክ ፡ ሆይ ፡ ክብር ፡
ለአንተ፡ይገባል።
የታሰርክ፡ሆይ፡ክብር፡ለአንተ፡ይገባል።
የተገረፍክ፡ሆይ፡ክብር፡ለአንተ፡ይገባል።
፮፤ ምራቃቸውን ፡ የተፋብህ ፡ ሆይ ፡ ክብር ፡
ለአንተ፡ይገባል።
የተሰቀልክ ፡ ሆይ ፡ ክብር ፡ ለአንተ ፡ ይገባል።
መከራ፡ተቀብለህ፡ሙተህ፡የተቀበርክ፡ሆይ፡
ክብር፡ምስጋና፡ለአንተ፡ይገባል፤አሜን።

## ምዕራፍ፡፹፯።

ቀዳሜ፡ሌሊት፡በ፩፡ሰዓት።

ትእዛዝ።

ቀዳሜ፡ሌሊት፡የአይሁድ፡ሰንበት።
ይህ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ጸሕሉ ፡ የለበሰውን ፡
ልብስ ፡ ያውርዱ ፤ የስቅለቱን ፡ ሥዕል ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ያድርጉ ፤ ወንጌሉንና ፡ የሠሙንም ፡
መብራት፡ከፍ፡አድርገው፤
በምሥራቅ ፡ በምዕራብ ፡ በሰሜን ፡ በደቡብ ፡
መቶ፡መቶ፡ጊዜ፡አራት፡መቶ፡ጊዜ፤እግዚኦ፡
መሐረነ ፡ ክርስቶስ ፡ ይበሉ ፤ ወደ ፡
ምሥራቅም፡ ተመልሰው ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡
ገብተው፡ታቦቱን፡ሦስት፡ጊዜ፡ይዞሩ፤የስቅ
ለቱንም፡አምሳያ፡ይገንዙ።
ከዚህ፡በኋላ፡እ፡ዘወረድከ፡ይበሉ።
ከሰማያት፡የወረድክ፡ሆይ፡
፩፤ ካህኑ፡ስለ፡እኛ፡ 
ይበል ፤ ሕዝቡም ፡ ፈጣሪያችን ፡ መድኃኒ
ታችን፡ክርስቶስ፡ሆይ፡ስማን፡ይበሉ።
ካህኑ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ከድንግል ፡ የተወለድክ ፡
፪፤ ሆይ፤ይበል፤ሕዝቡም፡እንዳለፈው፡ይቀበሉ።
(ካህኑ)፡ስለ፡እኛ፡በበረት፡ውስጥ፡የተኛህ፡
፫፤ ሆይ፡ይበል፤
ሕዝቡም፡እንዳለፈው፡ይበሉ።
ካህኑ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ በጨርቅ ፡ የተጠቀለልክ ፡
፬፤ ሆይ፡ይበል፤ሕዝቡም፡እንደ፡በፊቱ፡ይበሉ።

Scanned by CamScanner